ጣሊያኑ ጅየገጣ

(ትንግርት ያ'ረገለት ለው ትውስታ)



በቀለ ወልደ ኪዳን

ጣልቃ እየገባ

(ትንግርት ያረገለት ለው ትውስታ)

በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)

2006 ዓ.ም.

ዕቅጣና ሁለት ሙ. ወ. ኦ. ቢ/ክ
ሽንጎ ማሠረፊያ ያተባረከተ

ጣልቃ እየገባ

(ትንግርት ያረገለት ሰው ትውስታ)

በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)

2006 ዓ.ም.

ጣልቃ እየገባ
(ትንግርት ያረገለት ሰው ትውስታ)

2005 ዓ.ም መጀመሪያ ታተመ::
2006 ዓ.ም ተሻሽሎ ታተመ::

© 2006 ዓ.ም. በበቀለ ወልደ ኪዳን
የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

በተለይ ካልተገለጸ በስተቀር በዚህች መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በ1993 ዓ.ም. ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው:: በኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ፈቃድ ተቀድቶ የታተመ::

የደራሲው አድራሻ

የመ.ሣ.ቁ. 3587
አዲስ አበባ

e-mail: gash_beke@rocketmail.com

በሰሜን አሜሪካ አሳታሚና አከፋፋይ አቶ ወርቁ ሰገሠ
e-mail: wlegesse@gmail.com

የሽፋን ሥዕል : ልዑል ገብርኤል

ለጌታ ኢየሱስ፤

ለገነት ሀብተ ማርያም

እና ለልጆቻችን፦

ራሔል ወንድም አገኘሁ፥

ጌዲዎን አሉላ እና

የሴፍ ይድነቃቸው።።

ምስጋና

መጽሐፍ፥ ይልቁንም ደግሞ መንፈሳዊ ይዘት ያለው መጽሐፍ፥ መጻፍ አገልግሎት ነው። አገልግሎትም፥ ከእግዚአብሔር በታች፥ የአንድ ብልት ብቻ ሳይሆን የአካል - ማለትም የብዙ ብልቶች - እስተዋጽዖ ውጤት እንደ ሆነ ይታወቃል። ይህች መጽሐፍ የእንድ ሰው "ትውስታ" ብትሆንም አንኳን፥ ተደርሳ እና ተደጉሳ አንባቢ እጅ ለመግባት የብዙ ብልቶች አስተዋጽዖ አስፈልጓታል። ከእነዚህ ብዙ ብልቶች መካከል የጥቂቶቻችሁን ስም መጥራት እና "እግዚአብሔር ይስጥልኝ" ማለት ይገባኛል።

በመጀመሪያ "እግዚአብሔር ይስጥልኝ" ማለት የምፈልገው ለቤተ ክርስቲያኔ መሪዎች ነው። ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያኗ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ብሆንም፥ ¾ ኛውን ያህል የሥራ ጊዜዬን መጽሐፍ ለመጻፍ እንዳውለው ፈቅዳችሁል ኛል። እናንተ እንደዚህ ባታደርጉልኝ ኖሮ፥ በሁለት ዓመት ከሩብ ውስጥ ሁለት መጻሕፍት ለእንባቢያን ማድረስ አንዴት ይቻለኝ ኖሯል?

የሰው ስም፥ ቁጥር፥ ቀን፣ ቦታ እና ሁኔታ የመሳሰሉትን ዝርዝር መረጃዎች በመሰጠት ቤተ ክርስቲያን-ነክ የሆነውን ትውስታዬን የተሟላ ያደረጋችሁልኝ ወንድም ወንድም አገኘሁ መርሻ፥ ወንድም መላኩ ወልደ ሰንበት እና መጋቢ አበራ በላይ ናችሁ። በናይሮቢ (ኬንያ) ያለችዋን ቤተ ክርስቲያን በተመለከተ ጠቃሚ መረጃ የሰጠኸኝ ወንድም ሙላቱ በላቸው ነህ። ቤተ ሰባዊ የሆኑትን መረጃዎቼን ያሟላችሁልኝ ደግሞ እህቴ ወይዘሮ በካብቷ እና ወንድሜ አቶ ነጋሽ ወልደ ኪዳን ናችሁ። የሰጣችሁኝን መረጃዎች በትክክል እንደ ተጠቀምኩባቸው ተስፋ አደርጋለሁ። ለሁላችሁም አግዚአብሔር ይስጥልኝ።

ግርድፉን ጽሑፌን የሰለቅኽልኝ እና ትውስታዬንም አሁን ለአንባቢያን በቀረበችበት መልክ እንዳቀርባት ያገዝክኝ ጳውሎስ ፈቃዱ ነህ። ይህንን ስታደርግ ሰዓቶችን ብቻ ሳይሆን፣ ቀኖችን አቃጥለሃል። አንተ "ቢዝነስ ማን"፥ ተርጓሚ፥ ጸሐፊ፥ አገልጋይ፥ አስተማሪ እና ተማሪ ከመሆንህም በላይ፥ አባ ወራም ከሆንክ ገና አራት ወርህ ነበር። በዚህ ሁሉ መካከል ነው እንግዲህ

ለትውስታዬ ይህንን ያህል ጊዜ የለዋኽው። በሠርግህ ሰሞን ለህትመት የበቃችውን "የብርሃን አንጓዎች" የተሰኘች መጽሐፍህን በሰጠታ ስትሰጠኝ፥ "ለሽማግሌው ጓደኛዬ!" ብለህባታል። አኔ እንተን ምን እንደምልህ ገና አላወቅሁም። ምኞቴ ግን የቤተ ክርስቲያን ወጣቶች ሁሉ እንዳንተ ልጨኞች፥ ታታሪዎች እና ትጉሆች እንዲሆኑ ነው። እግዚአብሔር ይስጥልኝ - ፖል።

የትውስታዬን ረቂቅ አንብባችሁ መቅድሚን እና እስተያየቶችን ለአንባቢያን ክጻፋችሁልኝ ወገኖች ውስጥ ስድስታችሁን የመረጥኳችሁ "ውስጥ-ዐዋቂዎች" ስለ ሆናችሁ ነው። አንዳንዱ ትውስታ በእማኞች ፊት ቢወላ ይሻላል ብዬ ነው እንደዚህ ያደረግሁት። ሌሎቻችሁን የመረጥኳችሁ አስተያየታችሁ ሚዛን የሚደፋ "ጸሐፍት" አንደ ሆናችሁ ስለማውቅ ነው። ለእኔ እና ለአንባቢያን ለብም ቅርብ ናችሁ። ሁላችሁም ጊዜ ያልረከሰባችሁ ኢትዮጵያውያን ብት ሆኑም፥ ጥያቄዬን የተቀበላችሁት ግን በብዙ ደስታ ነበር። የለጣችሁኝን ብዙ እና እጅግ ጠቃሚ አሳቦች ለማካተት የምችለውን ሁሉ አድርጌአለሁ። ሳላካት ታቸው ስለ ቀሩት አሳቦቻችሁም ይቅርታ አለምናችኋለሁ። ሁላችሁንም እግዚአብሔር ይስጥልኝ እላለሁ።

ከበርም ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን።

አስተያየቶች

"ጣልቃ እየገባ" የተሰኘውን የመጋቢ (ጋሼ) በቀለን መጽሐፍ ረቂቅ እንዳነበብሁ ራሴን የጠየቅሁት አንድ ጥያቄ ነው - "የተጠየቅሁትን አስተያየት ለመጻፍ እኔ ትከከለኛው ሰው ነኝን?" የሚል። መጽሑፉንና አጻጻፉን የሚመጥን አስተያየት ለመጻፍ አልችልም ብዬ ስላሰብኩ ነው እንደዚህ የጠየቅሁት። ጋሼ በቀለንና ባለቤቱን እትዬ ገነትን የተዋወቅኋቸው በሚያዝያ ወር 1968 ዓ/ም ይርጋ ዓለም እያሉ ነበር። በትኩሱ የኢትዮጵያ አብዮት ወቅት፥ ለዕድገት በጎብረት ከዘመት ሁበት ከአዶ ሻኪሶ ለሙሉ ወንጌል ኮንፈረንስ ተጠርቼ ለመጣ፥ እንዳርፍ የተደረገው እነርሱ ቤት ነበር። በዚያን ጊዜ ሁለቱም አዳዲስ አማኞች ነበሩ። ሳያቸው ወደድኋቸው። ዲላ በነበሩ ጊዜም እየሄድሁ ለጥቂት ጊዜ አግኝቻቸዋለሁ።

እኔና ጓደኞቼ በእስር ላይ በቆየንባቸው ዓመታት፥ እነርሱም እየተመላለሱ ጠይቀውናል። አንደ ሌሎቹ ጠያቂዎቻችን ሁሉ፥ ጋሼ በቀለም ሊያየን በመጣ ቁጥር የወህኒ ቤቱን አጥር ተደግፎ ዕንባውን አፍስሷል። ዕምቅ መልእክት ባዘሉና ልዩ ጣዕም ባላቸው ደብዳቤዎቹም እጽናንቶናል። በንባብ የታነጽንባቸውን መንፈሳዊ መጽሔቶች በተከታታይ እየላከልንም አገልግሎናል። ከቁጥር ፣ እስከ 4 ተቀርጻው የነበሩትን የዝማሬ ካሴቶች በማሠራጨት ብቻ ሳይሆን፥ የሸያጩን ገንዘብ በጥንቃቄና በታማኝነት እየመዘገበ በማስቀመጥ እኛ ከተፈታን በኋላ ለቤተ ክርስቲናያችን አስረከቧል።

ጋሽ በቄ ወንጌል ስባኪና አስተማሪ እንደ መሆኑ መጠን፥ መልእክቶቹና ትምህርት አሰጣጡ ሁሌም ይመስጡኛል። ለመጀመሪያ ጊዜ ስብከቱን ያዳመጥኩት በጥር ወር 1970 ዓ/ም እዚያው ይርጋ ዓለም ሲሆን፥ የስብከቱ ርዕስ በዘፀ. 14፥13 ላይ የተመሠረተ "ቁሙ!" የሚል ነበር። አሁን በቅርቡ በግንቦት ወር 2004 ዓ/ም የለማሁት (ለመጨረሻ ጊዜ እንደማይሆን ተሰፋ አደርጋለሁ!) ስብከቱ ደግሞ በሕዝ. 3፥15 ላይ የተመሠረተና "በተቀመጡበትም ቦታ ተቀመጥሁ" የሚል ነው። ርዕሶቹ ትውስታዬን በቀላሉ የማይለቁ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።

ከዚህ በፊት የጻፋቸውን መጻሕፍት በጥሞና ያነበብኋቸው ቢሆንም፥ ይኼኛው ስለ ሕይወትና አገልግሎት ጉዞው ቀደም ሲል ያላወቅኋቸውንና አስገራሚ የሆኑ

ብዙ ጉዳዮችን እንዳውቅ አድርጎኛል። ወንድማችን ዘማሪ ደረጀ 'ዞር ብዬ ሳየው ያሳለፍኩትን፥ አባጣ ጎርባጣ ጉድጓድ ገደሉን ...' ያለውንም አስታውሶኛል። ጥልቅ ስለ ሆነ ጸጋው ልውል እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን። በዚህ መጽሐፉ የጋሼ በቀለ አጻጻፍ የመጨረሻ ዓይነት ይመስላል። "ትውስታው" በትንቢት ነው የተቋጨው። እንደ እውነቱ ከሆነ እዚህ ላይ የምለው ቸግሮኛል፤ እንደ ሰው መተከዜን ግን አልሸሽግም። ሁሉን ለሚያውቅና ለሚችል ጌታ ሁሉን አተዋለሁ።

ተስፋዬ ጋቢሶ (መጋቢ)

የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን (ሐዋሳ)

* * *

ዕድሜ መስተዋት ነው

በዕድሜ መከበር ጥቅሞች አሉት። ጥቅሞቹንም ቀደም ሲል ብዙ ውጣ ውረዶችን ተወጥቶ ባንቀላፋው በዮሴፍ፥ ኋላም በሦስት ዓርባዎቹ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች ለእግዚአብሔር ከብር ባዋለው በሙሴ፥ ዘልቆም በተከታታይ መንግሥታት ታሪክ ውስጥ በመገኘት የመፍትሔ ባለቤት በሆነው በዳንኤል፥ ኢየሱሰን አቅፎ "ባሪያህን አሰናብተው" በማለት አምላኩን በለመነው በስምዖን ሕይወት ውስጥ አይቼ ተጠቅሜባቸዋለሁ። በጊዜውም ዕድሜውን የለጣቸውን ልውል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

በእርግጥም በዕድሜ መከበር ጥቅም አለው። በመጋቢው ሕይወትም የማስተውሰው ይህንኑ ነው። እንዲህ በዕውቀት ለማደግ፥ ለማመዛዘን፥ የፊት የኋላውን ለማየት ያስቻለው በዕድሜ መከበሩ ነው።

በቀለ ወልደ ኪዳን በቀደሙት ዓመታት በርካታ መጻሕፍትን አስነብቦናል። ዘንድሮ ደግሞ ይኸው ግለ ታሪኩን አበረከተልን። በዚህም - ለው ሰው መሸ ተቱን፥ እንደ ኢየሱሰም "የሰጠኸኝን ሥራ ጨርሼ አከበርኩህ" ለማለት በሚያበቃው ሩጫ ላይ መሆኑን - የሚያሳይ ሰነድ ሰጠን። ራሱን ባየበት እኛም ራሳችንን እንድናይ፥ በሚያልፍ ዘመናችንም የማያልፈውን ሥራ በመሥራት እንድንዘልቅ ሰንቅ አስጨበጠን።

በቀለ ወልደ ኪዳን ነገርን ነገር እያነሳበት በዚህ ሕትመት ማግሥት እንደ ገና በመነሣሳት "የጣልቃ እየገባ"ን ከፍል ሁለት እንደሚያስነብበን ተስፋ አለኝ። ዕድሜ መስተዋት ሆኖት እንዲህ እንደ ጠቀመን፥ ቀሪውን ዘመኑንም ጌታ ለጥቅሙና ለጥቅማችን ያድርግልን።

ሰሜ ታደሰ (መጋቢ)

ቤዛ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን (አዲስ አበባ)

* * *

ጋሽ በቁ ድንቅ ተራኪ ነው። ከዚህ ቀደም ትንቢታዊ ታሪኮችን ደጋግሞ አስነብቦናል። አሁን ደግሞ የራሱን ግለ-ታሪክ ይዞ ብቅ አለ። ይህንን መጽሐፍ የጻፈው ልብን ከፍቶ የማስነበብ ባሕል ባልዳበረበት፥ ሰው ከነግለ-ታሪኩ ወደ መቃብር በሚወርድበት ድብቅ ማኅበረሰብ ውስጥ መሆኑን ሰናስብ ግርምታችንን የበለጠ ጨምሮታል።

ከጨቅላነት አሰከ ጉልምስና፣ ከከሀደት እስከ አገልግሎት ሹመት፣ ከትዳር ጥምረት እስከ ብቸኛነት፥ ባጠቃላይ የሕይወት ጉዞውን በውብ ቃላት ከሸኖ በብዕሩ ብሩሽ በኅሊናችን ሸራ ላይ ሥሎታል። በጋሽ በቁ ሕይወት ውስጥ ብዙ ሰዎች እንዳለፉ፥ አሁንም እንዳሉ አናውቃለን፤ ሆኖም ሁሉንም በኅሊታቸውን ሲያኅላ እንጂ እንዳቸውንም በድካማቸው ሲያሣቸው እናይም። ይህ የእግዚአብሔር ባሕርይ በውስጡ ተገልጦ በማየታችን ከመደነቅ በሻገር ትልቅ ትምህርት እግኝተንበታል።

በዚህ መጽሐፍ መደምደሚያ ላይ ጋሽ በቁ በ 75 ዓመቱ ጌታ እንደሚወስደው ቢነግረንም፥ እኛ ግን እግዚአብሔር ዕድሜን እንዲጨምርለት፥ እንደ ኢያሱና እንደ ካሌብ ባልደከመ ጉልበት እስከ ፍጻሜ እንዲያገለግል የዘወትር ምኞታችንም ጸሎታችንም ነው።

የሥነ-ጽሑፍ ድህነት በሰፈነበትና ሰው በእፀደ-ሥጋ እያለ ግለ-ታሪኩን በገዛ እጁ ጽፎ ማቆየት ባልተለመደበት አገር ውስጥ ጋሽ በቁ ከፋና ወጊዎቹ አንዱ ሆኖ ስለ ወጣ ደለታችን ወደር የለውም። ይህን መጽሐፍ የሚያነብ ሰው ሁሉ ስለ ራሱ ሳይጠይቅ፣ እሁን ያለበትን ሳይቃኝና ስለ ነገው ሳያስብ እንደማይቀር እምነታችን ጽኑ ነው።

በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር በሰው ሕይወት ውስጥ እንዴት ጣልቃ እንደ ሚገባና በደካማው ብርቱ፥ በትንሹ ትልቅ፥ ሥራ በመሥራት ከብሩን እንደ ሚገልጽ የሚያሳየውን፥ "ጣልቃ እየገባ" የተሰኘውን ይህን መጽሐፍ ሰው ሁሉ እንዲያነብ በአክብሮት እንጋብዛለን።

ኮ/ል ከፍሌ ስዩም እና ወ/ሮ ዘለቃ (ቃቂ) በቀለ

ሲልቨር ስፕሪንግ (ሜሪይላንድ)፤ አሜሪካ

* * *

ከጋሽ በቁና ከገኒ ጋር ከተገናኘን ይኸው እንግዲህ 26 ዓመት ሆነን። "በደጉበ እጉተዋወቃለን" ከምንላቸው ጥቂት ቤተ ሰቦች መካከል ናቸው። ገኒ አዲስ አበባ እያለች እቤታቸው በሄድንባቸው ጊዜያት ሁሉ ልባቸውንም ቤታቸውንም ከፍተው ነበር የሚያስተናግዱን። ቸሮችና ልብ የሚያሳርፉ ሰዎች ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉትን ታሪኮችና ከስተቶች - ከመገናኘታችን በፊት ያሉትን በጭውውት፥ ከዚያ ወዲህ ያሉትን በአካል - ከሞላ ጎደል እናውቃቸዋለን። ይሁን እንጂ ታሪኮቹና ከስተቶቹ ሁሉ እንደዚህ የተሳሰሩና በእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት የተደረጉ መሆናቸውን፥ ጋሽ በቁም እንደዚህ የንባብ፥ የጽሑፍና የግጥም ሰው መሆኑን አናውቅም ነበር። የአፕል ኮምፒውተር መሥራች የነበረው ሚቹ ስቲቭ ጆብስ በአንድ የምረቃ በዓል ላይ "CONNECTING THE DOTS" በማለት በሕይወቱ ያለፉትን እርሱ ግን የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ያላላቸውን ነገሮች እስታወሰን።

አናስተውሰውም እንጂ፥ እግዚአብሔር በሁላችንም ሕይወት ውስጥ ጣልቃ ይገባል። ይህንን ማለተዋል እንድንችል ይህ መጽሐፍ፥ ከእግዚአብሔር ጋር፥ በጣም ይረዳናል። በተጨማሪም መጻሕፍትን ማንቡበን ልምድ እንድናደርግ፥ የእግዚአብሔርን ድምፅ እንድንሰማ፥ የሕይወታችንን ገጠመኞች መዘግበን እንድንይዝ፥ ታማኞችና ትዕግስተኞችም እንድንሆን ያስተምረናል።

ወ/ሮ እስቴር ወልደ ሚካኤል እና ዶክተር-ኢንጂኔር ዳንኤል ቅጣው

በጋሽ በቀሰ "ጣልቃ እየገባ" መጀመሪያ "ሰው" የሆነውን ጋሽ በቀሰን አየሁ። በልጅነቱ የለበሳትን ጥብቆ ሳይቀር በዓይነ ልቡናዬ ሰበሰኩ። እለበሰኝ። የተሰያዩ ትውልድ አባላት ሆነን ሳለ በእረኝነቱ ዘመን የወላጆቹን ከብቶች እስጠበቅኝ። የአረኖ ገድሎች አብረን አደረግን። የአተራረኩ ጉልበት የሚጀ ምረዉ እዚህ ላይ ነው። ባሰታሪኩ ራሱን ቀላል (ባዶ) እድርጎ፣ አንባቢን ከጎኑ ያስቀምጣል። አንደ እኩያ ወንዝት አቅፎ ያወራል፣ የሌላውን ነፍስ ከራሱ ነፍስ ጋር ያቋጥራል። ሊላቀቁት ሲሹ እንኳን ከነፍሰያ ጋ ያሚግታል። ሬይሞንድ ካርቨር (1938 – 1988) የተባለ ደራሲ "ግሰ-ታሪክ የድሃ ሰው ታሪክ ነው" በሚለዉ አነጋገሩ ይታወቃል። ምን ለማለት አንደ ፈለገ አይገባኝም ነበር።

ጋሽ በቀሰ ከወሬ ፍጀታ በላይ ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ ሰብዓዊና መንፈሳዊ ብልጥ ግናዎች አንዳሉት አውቃለሁ። ታሪኩን በብልጥግናዎቹ ጀቡኖ አቅርቦልኝ ቢሆን ኖሮ በነፍሱ መቋጠሬ ቀርቶ ወደ ላይ እያንጋጠጥኩ ከእርሱ መማሩ በአሰለቸኝ ነበር። ዝቅ ብሎ አንደ ምድጃ ዳር ትረካ ሲያዋየኝ ግን ከዐመድና ከትቢያ የሚያነሳውን፣ ሰባራ ጠጋኙን፣ ፍርስራሽ (መቃብርም) ቆፋሪውን፣ የመደይዎች ወዳጅ የሆነውን የጌታ እምላኬን የምሕረቱን ባለጠግነት አሳየኝ። ይኼ ነው ባዶነት፤ ከቶስ ድኻ ልሸሸግ ቢልስ ምኑን ይሸሸገዋል!!? (በመንፈስ ድኻ የሆኑ... ብዬ ልቀጥል ነበር፤ የሰባኪዎቹን ሥራ መሻማት ይሆንብኛል።)

ጋሽ በቀለ አንደ ባለ አእምሮም - አንደ አግዚአብሔርም ሰው፣ አንዲህ ሆኖ ወደ አንባቢ መቅረቡ ወደ ፊት ሕይወታቸውን በጽሑፍ መልክ ሰሚያካፍሉን አንጋፋ አገልጋዮቻችንና የሕይወት ታሪክ ጸሐፊዎቻቸን ፊር የቀደደ ይመስለ ኛል። ግልጽነት፣ ቀጥተኛነት፣ ሽንገላ-አልበነት፣ ጎሊናዊ ሰሱነት፣ አርአያነት - ሰውነት፤ ... የተርከፈከፈበት አተራረክ ሰው ያበጀዉል - አሰከ ማዶው ትውልድ ድረስ። አኔን መቼም አንጠኛል።

ረዥም ዕድሜ ለጋሽ በቀሰ

ወንድዬ አለ.

ይህን መጽሐፍ ለማየት ብዙ ቄየን። ጭብጥ ሐሳቡ አንድ ሰው ከአከራሪ አማኝነት ወደ ከሀዲነት፣ ከከሀዲነትም በ"ምኑን ዐውቄነት" (agnosticism) ዐልፎ ወደ አማኝነት የተመለሰበት ታሪክ ትውስታ ነው፤ የአግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ደግሞ የእያንዳንዱ እርከን መሸጋገሪያ ሆኗል። የአንድ ግለ ሰብ ታሪክ ብቻ ግን አይደለም፤ የቤተ ክርስቲያንና የአገር ታሪክንም ዐቅፏል፤ የዘመን መስታዎት ነው። ጋሽ በቄ፣ "የሕይወት ታሪክህን ሰምን አትጽፍም?" ስለው፣ "የሕይወት ታሪክ አንዴት በልጅነት ይጻፋል?" ይለኝ ነበር፤ ታዲያ አሁን ማርጀቱን አመነ ማለት ነው?! የሆነስ ሆኖ አግዚአብሔር "ጣልቃ አየገባ" የሚታይበትን ታሪክ መርጦ ማቅረቡን የሚነግረን፣ የአግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት የሌለበት ምን ታሪክ አለውና ነው?! ምን አባቴ ዐውቃለሁ፤ መጽሐፉን ጠይቄታ! ጸሓፊው ድካሙንና ውድቀቱን ሳይቀር አውስቷል፤ ቁጭቱንም። በተለይ ካልተመለሱ ጥያቄዎች ጋር መኖሩን ማንበቤና "መልስ በኪሱ" አለመሆኑን ማወቄ አስደስቶኛል። ለካ ጋሽ በቄ እኛ ሰፈር ነው! አንኳንም መጽሐፉን ለማግኘት ብዙ ቄየን!

ጳውሎስ ፈቃዱ

ማውጫ

ይድረስ ለእንባቢዎች 17
መግቢያ 21

ምዕራፍ እንድ - ዐሥር አስጨናቂ ቀኖች 23
ሰባት ዓመታት ወደ ኋሊት
"አታደርገውም!"
ከዚያ በፊት፥ ዐሥራ ሰባት ዓመት
"እኔን ላከኝ!"
ለምን ይህን ያህል ዘመን?
አንቢተኛነትስ አልነበረም?
ጥሪው እየጠራ መጣ
ምን የሚሉት ፓስተር?
ያ ሁሉ ኢንቬስትሜንትሳ?

ምዕራፍ ሁለት - ከአከራሪነት ወደ አከራሪነት 63
ያላዋቂ እከራሪ
አለማወቅ አይደበቅ
ሳያምኑት ይከዱታል?
ዓርብ ዕሮብ
"የተነቃነቀ ጥርስ"
ከህደትንም ለካ ይካኑታል?
"አደንዛዥ ዕፅ"

ምዕራፍ ሦስት - "ሳያድጉ ማደግ ..." 97
ዱር ውስጥ አይደለን እንዴ?
"ምን ዐውቄን" ተዋወቅሁት
ናቲ እና ቶሚም?
ነፍስማ ነፋስዋ

ምዕራፍ አራት - ማለስለስ እና ማንኳኳት 115
በልጅነት ወራት
"ሃታ እሳ"
ትብብሩ እና መዝሙሩ

ገርማሜ ንዋይ፥ የማለስለስ አገልጋይ?
ሆሊይውድም፥ ከፊልሞቹ ባንዳንዶቹ
ዘፋኞቹ ዘማሪዎች
"እናንተ 'ማታዩኝ፥ እኔም 'ማላያችሁ"
ያልተሞተባቸው ሞቶች
በከቡር ሚኒስትር ሳይቀር
አያነብ አንባቢ
"ያባራሪው ያለህ ... !"

ምዕራፍ አምስት - ገነት ገባች 149
ተራከቧዊ ተዓቅቦ
የስለት ሚስት
ባንተ ያላረፈ፥ ምኑን ዓረፈ?
ጸሎት! ለሁለተኛ ጊዜ!!
ዶሪስ እና ብራያን ፋርገር
ተከትሏት ገባ? ወይስ አስከትሏት?
ይህም ሁሉ ሆኖ?
"ፍልስፍና ፍርስራሽ ላይ"
ለመመስከርም በስለት?

ምዕራፍ ስድስት - ሻካሮቹ ሽግግሮች 187
እብዮታዊት ኢትዮጵያ
"አልሰሜን 'ግባ!' በለው"
ካሣ እና አስካለ
"አስመሳዩ እና አደገኛው ጴንጤ"
"አበትናችኋለሁ!"
ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ
እየተነሡ ያሉ ጥያቄዎች
በሥነ መለኮቱም ሳይቀር
የሚዘናዊነት ያለህ!

ምዕራፍ ስባት - ገነት ወጣች 231
እያለማመደኝ ነበር እንዴ?
የሚያስገርሙ ጥንቃቄዎች
የማይመለሱ ጥያቄዎች
እንዴት እስቀድሞ ሳይናገር?
የሚጠረጥሩ ጥርጣሬዎች

የማይፈጸሙ ተስፋዎች
ተምሬአለሁም፥ አልተማርኩምም
የማይመረጡ አማራጮች
የገነት ሌጋሲዎች

ምዕራፍ ስምንት - ጣልቃ እየገባ 265
በትንሹም በትልቁም
የሙሉ ወንጌል አማኝ
ኤንጌቆስጤአዊ ክርስቲያን
ጥቂት ቃላት
የጨነገፈው የዕርቅ ሂደት
መዋዠቅ
የግዱ ዕርቅ
"ኖርማላይዜሽን ኮሚቴ"
ለመታረቅም ምክንያት ለሚሹ
ክፍተቱስ ተዘጋ?

ምዕራፍ ዘጠኝ - "ልብማ ልባሙ" 321
ስንት ዓመት ቢኖር?
ምን ቢሠራበት?
ፍጥሞ
ዕለተ ልደት፥ ዕለተ ሞት
የሚናገር እግዚአብሔር
ሰባት ወጣ፥ ሰባት ገባ
ሲያበቃ፥ በጣልቃ

አባሪዎች 345

ይድረስ ለአንባቢዎች

ወዳጇ መጋቢ በቀለ ለዚህ ለአራተኛው መጽሐፉ FOREWORD (መቅድም) እንድጽፍለት በጠየቀኝ ጊዜ ወዲያውኑ "እሺ" አላልኩትም ነበር። ወዲያውኑ "እሺ" ያላልኩበትን ምክንያትም በትክክል አላውቀውም። ምናልባት መቅድሙን እንድጽፍለት የጠየቀኝ ረቂቁን ሳያስነብበኝ በፊት ስለ ነበረ ይሆናል። መጽሐፉ MEMOIR (ትውስታ) እንደ ሆነ ገና ሲጀምረው ጀምሮ የነገረኝ ቢሆንም፥ በውስጡ ምንና ምን እንደ ያዘ ግን አላውቅም ነበር። ስለዚህም ዝርዝሩን ስለማላውቀው ጉዳይ በቅድሚያ ቃል መግባቱ አስፈርቶኝ ሲሆን ይችላል። ምናልባትም ከጸሐፊው ጋር ላለፉት 32 ዓመታት የቅርብ ወዳጅች ስለ ሆንን፥ የምጽፈው መቅድም ሐቀኛነት (OBJECTIVITY) ቢጎድለውስ? ከሚል ሥጋት የተነሣ ይሆናል። ወይም ደግሞ ከዚህ በፊት መቅድም ጽፌ ስለማላውቅ ብቻ ሊሆንም ይችላል።

መጋቢ በቀለ ምንም ዓይነት ግፊት አላደረገብኝም። ለውሳኔ ሳልቸኩል ጊዜ ወስጄ እንዳሰብበትና እንድጸልይበትም ብቻ ነበር ያሳሰበኝ። በእውነትም ነገሩን ለጥቂት ቀናት በውስጤ እገላበጥኩት። ሳልጸልይበትም አልቀረሁም። እግዚአብሔር ዕድሜውንና ዕድሉን ስጥቶ ለዚህ ካበቃን፥ ለመጋቢ በቀለ "ትውስታ" መቅድም ለመጻፍ ከእኔ የሚሻል ማን ይኖራል? ብዬ አሰብኩ። ከዚያም ፈቃደኛነቴን ገለጽኩለት። ፈቃደኛ በመሆኔ ሁሉታችንም ነበርን ደስ ያለን። በተለይም እኔ የመጽሐፉን ረቂቅ ካነበብኩ በኋላ ደስታዬ በጣም ጨምሯል። ምክንያቱም መጽሐፉን ከጠበቅሁት በላይ ጥሩ ሆኖ ስለ አገኘሁት ነው። ይህችን ጽሑፌን "መቅድም" ሳይሆን፥ "ይድረስ ለአንባቢዎች" ያልኳትም በዚሁ ምክንያት ነው። ስለ መጽሐፉ ብቻ ሳይሆን፥ ስለ እንባቢዎቹና ስለ ጸሐፊውም ጭምር ስለምናገርባት።

በሥነ ጽሑፉና በቋንቋው ረገድ እንደ ቀደሙት መጽሐፎቹ ሁሉ የተዋጣለት ቢሆንም፥ ይኸኛው መጽሐፉ ግን ግለ-ታሪክ በመሆኑ በይዘቱ ከቀደሙት ይለያል። አንደኛ፥ ስለ ግል ሕይወቱና በእገልግሎቱም ስላጋጠሙት ጉዳዮች በግልጽነትና ደግሞም በድፍረት ጽፏል። ይህም መጋቢ በቀለን ከዚህ በፊት

ከማውቀውም በላይ እንዳውቀውና ከማከብረውም በላይ እንዳከብረው አድርጎኛል። ሁለተኛም፥ በመጽሐፉ ውስጥ ያየሁት የእግዚአብሔር ታላቅነትና ታማኝነት በእውነት አስደንቆኛል። በብዙ የማውቀው ሲመስለኝ የነበረው ሰው፥ በሕይወቱና በአገልግሎቱ እግዚአብሔርን የማደንቅባቸውንና የማመሰግንባቸውን፥ ከዚህ በፊት የማላውቃቸውን ብዙ ምክንያቶች ነው በዚህ መጽሐፉ የጨመረልኝ።

ሦስተኛ፥ መጽሐፉ በተለይ ለወጣቶች በጣም እንደሚጠቅም ተረድቻለሁ። ወጣቶች ደቀ መዛሙርት ከሚሆኑባቸው መንገዶች መካከል እንዱ ቀድመ ዋቻው በዚህ መንገድ የተጓዙ ሰዎችን ታሪክ በማንበብ ነው። ይኸኛው ባለ ታሪክ ደግሞ ብዙ ወጣቶች በመድረክ አገልግሎቱ የሚያውቁትና የሚወዱትም ሰው ነው። ይህ ሰው ግን ለመሆኑ ማን ነበር? አሁንስ ማነው? ከትናንት እርሱነቱ ወደ ዛሬው ማንነቱ እንዴት ተሸጋገረ? መጋቢ በቀለ በዚህ መጽሐፉ ውስጥ ስለ ግል ሕይወቱና ስለ እገልግሎቱ ሁላችንም የማናውቃቸውን የእግዚአብሔርን ጣልቃ ገብነቶች፥ የራሱንም ደካማ ጎኖች፥ በፍጹም ግልጽነት በመተረክ ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

ይህም ብዙ ወጣቶች እግዚአብሔር በአንድ ሰው ሕይወት እንዴት እንደሚሠራና እንዴትስ ያንን ሰው ገንዘቡ እንደሚያደርገው ከቅርብ ርቀት እንዲያዩ ዕድል ይሰጣቸዋል። ከእግዚአብሔር ጸጋ ውጭ የሰው ብርቱ ያለመኖሩን፥ ይልቁንም ለከበረው መዝገብ ማስቀመጫነት የተመረጠው ዕቃ ተሰባሪው ሸክላ የመሆኑን እውነትነት ይገነዘባሉ። ብዙዎችም ከሌላ ከማናቸውም ምክንያት ይልቅ ከዚህ እውነት የተነሣ ብቻ ስለ ራሳቸው በእግዚአብሔር መታመንን ይማራሉ። ትውስታውን ሲጽፍ፥ የመጋቢ በቀለም ምኞት - እግዚአብሔርን ከማከበር ቀጥሎ - ይኸው ነው የሚመስለኝ። እንደ ተመኘውም በዚህ መጽሐፉ ይህንን ካተረፈ፥ እስከ ዛሬ በነበረው የመድረክ አገልግሎት ካተረፈው ይልቅ የበለጠ አተረፈ አላለሁ።

ከሚያነቧቸው ግለ-ታሪካዊ መጻሕፍት ከፍተኛውን ጥቅም የሚያገኙት ሰዎች፥ በእኔ አስተያየት፥ ቀደም ሲል ባለ ታሪኩን ወይም ስለ ባለ ታሪኩ፥ በመጠኑም ቢሆን፥ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ናቸው። ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም፥ ወዳጇን መጋቢ በቀለን በተመለከተ ጥቂት ነገሮችን ለእንባቢያን መግለጽ

አፈልጋለሁ፡፡ መጋቢ በቀለ ብዙ ነገሮችን የሚያውቅ፥ ጥሩ ሰባኪ፥ ጥሩ አስተማሪና ከብዙ ሰዎችም ጋር መልካም ግንኙነት ያለው አገልጋይ እንደ ሆነ የሚያውቁት ሁሉ የሚስማሙበት ይመስለኛል፡፡ የዚያኑ ያህል ደግሞ፥ ቆቅ (ጠርጣሪ፥ ብልጥ) ወይም የሚጠቅመውን ነገር ከሩቅ እያሰተዋለ በሰልት የሚንቀሳቀስ ሰው አደርገው የሚያዩትም አንዳሉ ዐውቃለሁ፡፡

እውነት ነው መጋቢ በቀለ ስለ ብዙ ነገሮች የሚያውቅና የሚተነትን ሰው ነው፡፡ አኗኗሩ ግን ከዚያ ይለይብኛል፡፡ ይህ አባባሌ በትክክል ይገልጸው አንደ ሆነ እርግጠኛ አይደለሁም እንጂ፥ ምንም አንደማያውቅ ሰው ይሆንብኛል ማለቴ ነው፡፡ ለምሳሌ ከሰው ጋር የሚያያይዘው ምንም፥ ከእግዚአብሔር ጋር የማያያ ይዘው ደግሞ እንድም ጉዳይ የለውም፡፡ በአመለካከቱ እዎንታዊ የሆነው እና ሁኔታዎችን ሁል ጊዜም በበጎ ጎናቸው በኩል ማየት የሚቀናው ከዚህ የተነሣ ይመስለኛል፡፡ ምድራዊ ነገር ብዙ የማያጓጓውም በዚሁ ምክንያት መሆን አለ በት፡፡ ይህ ባሕርዩ በዚህ መጽሐፉ ውሰጥ በብዙ ይስተዋላል፡፡ አንደዚህ ዓይነት ምስክርነት እንድሰጥ አልተጠየቅሁም፡፡ ከራሴም ጋር እየተሟገትኩ ነው ይህንን የጻፍኩት፡፡ ትውሰታውን የሚያነብቡ ሰዎች ስለ ጸሐፊው ይህንን ቢያውቁ ይጠቅማቸዋል ብዬ ስላሰብኩ ነው ሳላስፈቅድ ይሆንን ለመጻፍ የደፈርኩት፡፡ ይቅርታ፥ በቄ!

በእኔ እምነት፥ እግዚአብሔር በበቀለ ወልደ ኪዳን ሕይወት የሚሠራው ሥራ ገና አላለቀም፡፡ እርሱንና እኛንም የሚያሰደንቁን ነገሮች ገና በሕይወቱና በፊቱ ያሱ ይመስለኛል፡፡ ስለዚህም ይህንን መጽሐፉን ጽፎ ቢጨርሰውም አንኳን ከሕትመት ግን እንዲያዘገየው ደጋግሜ አሳስቢው ነበር፡፡ አርሱ ግን "እግዚአብሔር እሰካሁን ያደረገልኝን ልናገርና እንተ አንደምትለው ወደፊት የሚሆን ሌላ ነገር ካለ አሱ በጊዜው ይታያል" በሚለው ሐሳቡ ለለ ጸና፥ መጽሐፉ ታትሞ ይሸውና ከእጃችን ገብቷል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

በዘብህ ወርቅነህ

መግቢያ

ይህች፥ ላለመጻፍ ('ጻ' ትጠብቃለች) በብዙ የታገለችኝ መጽሐፍ ናት - ገና በአሳብ ደረጃ ሳለች ጀምሮ። ተጽፋ እስከ ተጠናቀቀችበትም ጊዜ ድረስ። ምናልባት ታትማ ከእንባቢዎች እጅ እስከምትገባም ጊዜ ድረስ ገና ትታገለኝ ይሆናል።

የምትታገለኝ ያለ ምክንያት አይደለም። "ስው፥ በተለይም ደግሞ ከርስቲያን ስው፥ እንዴት ስለ እራሱ ይጽፋል?" የሚለው አንደኛው ምክንያት ነው። አንዳንዶች እንደሚጻፍላቸው፥ አንዳንዶች እንደሚጽፉ፥ አንዳንዶችም መጻፍ ወይም ማስጻፍ እንዳለባቸው ዐውቃለሁ። የእኔ ምድብ ግን እንደዚህ ካሉት ሰዎች መካከል አይደለም።

ለወሬ የማይመቹ ነገሮችም አሉ። ነገሮቹ እግዚአብሔር ለከብሩ የሠራቸው ናቸው። ሆኖም ለጸሐፊው፥ በተለይም ደግሞ ለኢትዮጵያዊው ጸሐፊ፥ በሰዎች ፊት የሚያዋርዱት ይመስሉታል። "እርሱ ሊልቅ፥ እኔ ግን ላንስ" የሚለው መንፈሳዊ መርሕ - ሕይወቱ ቀርቶ ቋንቋውም እንኳን - ይተናነቀዋል። ሁለተኛው ምክንያት።

"ዘመኑ አልቆ የለም ወይ? ጌታስ ሊመጣ በደጅ አይደለም ወይ? በፊታችን ያለችውን ይህችን እጅግ አጭር ጊዜ ትውስታችንን በማውሳት እና/ወይም በማንበብ እንዴት እናባክናት?" የመጨረሻው ምክንያት።

በትግሉ ለማሸነፍ እና መጽሐፏን ጽፎ ለመጨረስ እራሴን የምሞግትባቸው ጠንካራ ምክንያቶች አሰፈልገውኛል - "መጽሐፏ ስለ እኔ አይደለችማ! ... መጽሐፏ ትንግርት ስለ አ'ረገልኝ ስለ እግዚአብሔር ናታ! ... 'እግዚአብሔርን እመስግኑ፤ ስሙንም ጥሩ፤ ሥራውንም በሕዝቦች መካከል ግለጡ። ተቀኙለት፤ ዘምሩለት፤ ድንቅ ሥራዎቹንም ሁሉ ተናገሩ' ተብሎ ተጽፏላ! እርሱ በጄኔራሎቹ ብቻ ሳይሆን፥ በተራ ወታደሮቹም ጭምር የሠራው ትንግርታዊ ሥራ ሞልቷላ! 'ለማይታወቀው ወታደር' (TO THE UNKNOWN SOLDIER) የሚባሉ ሐውልቶችም በጦርነት ባለፉ በብዙ አገሮች ውስጥ ተተክለዋላ!" የመጀመሪያው ምክንያት።

ላደረገልኝ ከዚያ ሁሉ ቸርነት ውስጥ ጥቂቱን እንኳን እንድመስከርለት ዕድል እንዲሰጠኝ ለብዙ ዓመታት ለምኜዋለኋ! "ለምኑ፥ ይሰጣችኋል" ያለው እርሱ፥ ጸሎቴን ሊመልስሳ! ማለቴ ሁኔታዎችን ሊያመቻቸልኝሳ! እየደጋገመ "ጻፍ!"፥ "ጻፍ!" ሊለኝሳ! መንፈሴንም ሊያነሣሣሳ! ሁለተኛው ምክንያት።

ሰመጽሐፏ የሚመከሩ፥ የሚማሩ፥ የሚጽናኑ እና የሚታነጹ ስዎችስ ይጠፋሉ? "እንግዲህ እነዚህን የመሰለስ ብዙ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን ... " ተብሎ የተጻፈው ስለ እነዚያ ብቻ ነውን? በእውነት ስለ እኛስ ግምር አይደለምን? ሦስተኛው ምክንያት።

አንዳንድ ወንድሞችም "እባክህን ግለ-ታሪክ ብጤ ነገር፥ ሕይወት ሕይወት የሚሸት ነገር ጻፍ" እያሉ ጎትጉተውኛል - ምን ልጽፍ እንደምችል እንኳን በቅጡ ሳያውቁ። አራተኛው ምክንያት።

ከነምክንያቶቹ ሁሉ በላይ ግን፥ "የጸጋ ሁሉ አምላክ" እርሱ አበረታኝ እና ጻፉት። ከብር ሁሉ ለእርሱ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን። አሜን።

መልካም ንባብ።

በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)

ምዕራፍ አንድ

ዐሥር አስጨናቂ ቀኖች

ቅዳሜ፣ መስከረም 20 ቀን 1993 ዓ.ም። ከሰዓት በፊት ፓስተር መርዕድን ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ላደርሰው ተገናኘን። ወደ አስራኤል ይበርራል። ትናንትና ምሽት ላይ ነበር ጠዋት አንድመጣ እና አውሮፕላን ማረፊያ እንዳደርሰው የጠየቀኝ። እየሄድን እያለ -

"ሰአረኛነት አገልግሎት ተመርጠሃል፤ መሪዎች ሰሞኑን ጠርተው ያነጋግሩሃል፤ አንተንም ቢሆን ጌታ ሳይናገርህ የቀረ አይመስለኝም" አለኝ። እኔም -

"እንተ ችግሬን ታውቀዋለህ አይደለም ወይ? እኔ ትዳሩ የፈረሰበት ሰው እኮ ነኝ፤ የእግዚአብሔርን ቤት ማስተዳደር አልችልም" አልኩት።

"እስቢበታለሁ፤ እንደኛ አልተፋታችሁም። ሁለተኛ ከዐቅምህ በላይ ሆኖብህ አንጂ አንተ ፈልገሽው የሆነ ነገር አይደለም" አለኝ። በዚሁ ተለያየን።

በዚያው ዕለት ከሰዓት በኋላ ፈረንሳይ ሌጋስዮን ባለው የጸሎት ቤታችን አገልግሎት ነበረኝ። አገልግሎቱን ጨርሰን እና ስእኔም ተጸልዮልኝ ሰንወጣ፥ ከአገልጋዮቹ አንዱ "ለእንተ መልእክት ያላት እኅት አለች፤ ልታነጋግርህ ትፈልጋለች" አለኝ።

"እሺ" አልኩት እና ከእንዲት እኅት ጋር አገናኘኝ።

"ቅድም ሲጸለይልህ ሳለ በራእይ ሦስት ቋጠሮችን አይ ነበር ... የመጀመሪያው የቆየ፥ በጌታ ፊት ብዙ ያለቀሰከበት ነው ... ሦስቱም ቋጠሮች ግን ተፈቱ" አለችኝ።

እንደ ጴንጤቆስጤአዊ ክርስቲያን፥ በእርነት አገልግሎት እንደሚያምንም ክርስቲያን - ቋጠሮ፥ ቀንበር፥ ዕንቆቅልሽ፥ አስራት - እና ከመሰሰሉት ቃላት ጋር ትውውቅ ብቻ ሳይሆን፥ ትንቅንቅም ኖሮኝ ያውቃል። "የምን ቋጠሮ ነው አሱ?" ብዬ ዐውቃለሁ ማለቴ ነው። "ቀራንዮ ያልፈታው ቋጠሮ አለ እንዴ?"

"በኢየሱስ 'እምን' እና 'አሜን' ያልሆነ (2ቆሮ 1፥18-20) ዕንቆቅልሽ ገና ቀርቷል እንዴ?"

ጰንጤቆስጤአዊው ክርስትና ልምምዳዊ ነው። ከ25 ዓመት በፊት ስተዋወቀው የተማረከኹስት ከዚህ ተጨባጭ ጎኑ የተነሣ ነበር። እየቆየሁ እና እስተምህሮ አዊ ጎኑን እየተረዳሁ ስመጣ ደግሞ፥ የተማረከሁለት ያ ተጨባጭ ጎኑ፥ ውበቱ ብቻ ሳይሆን ተግዳሮቱም ጭምር እየሆነ እግኝቼዋለሁ - እስከ ዛሬም ድረስ። ተግዳሮትነቱ ግን ክርስትና ልምምዳዊ ጎን ያለው ከመሆኑ ላይ አልነበረም። ተግዳሮትነቱ በእስተምህሮአዊው እና በልምምዳዊው ጎኖቹ መካከል መጠበቅ ያለበትን ሚዛን መጠበቁ ቀላል ሆኖ ካስመገኘቱ ላይ ነበር።

ሚዛን ያለ መጠበቅ ችግር ደግሞ እጅግ እሩቃችን በሆነው በስማያዊው ጉዳይ ይቅርና፥ እጅግ ቅርባችን በሆነው በምድራዊውም ጉዳይ፥ ምናልባት ሁላችን ነም፥ ሁልጊዜ እያንዳንደ ያስ ነገር ነው። ለምሳሌ በኤኮኖሚውና በፖለቲካው ጉዳይ "ቀኝ" እና "ግራ" ጎኖች ብቻ ሳይሆኑ፥ "ቀኝ እከራሪ" እና "ግራ እከራሪ" (FAR RIGHT AND FAR LEFT) የሚባሉ ጎኖች ጭምር እሉ አይደል? ከቶውንም በሁለቱ ጎኖች መካከል ያለው ውጥረት የዴሞክራሲያዊው ሥርዓት በጎ እና እስፈላጊ ጎን እንደ ሆነ ተደርጎ ይቆጠር የለም? አይ፥ ሚዛን ያለ መጠበቅ ችግር የሕዝበ ክርስቲያኑ እንጂ የክርስትና ሊሆን አይችልም።

ስለዚህም ልምምዳዊው ክርስትና እስከ አግዚአብሔር ሙላት ሁሉ ልክ ደርሶ ለመሞላት ቢደፍር፥ ከእስተምህሮአዊው ክርስትና እያፈነገጠ አይደለም። ወይም ደግሞ በዴድን ገነት በተጀመረ፥ የሞት እና የሽረት በሆነ፥ ጦርነት ውሰጥ እንደ ተሰለፈ፥ የሚዋጋው እውነተኛ ጠላት፥ የሚያዋጋውም እውነተኛ እዝማች አንዳለው ቢያምን የኢየሱስን "እምንነት" እና "አሜንነት" እያሳነሰ እይደለም።

እና ቋጠሮ እለ ማለት ነው? እንግዲህ "ወፍ እንደ አገሯ ትጮኻለች" አሉ። የሲሞንን "ሰንሰለት" (ሐዋ. 8፥23)፥ የጳውሎስን "መውጊያ" (2ቆሮ. 12፥7)፥ የጢሞቴዎስን "የሆድ ሕመም" (1ጢሞ. 5፥23) ምን ብለን እንጥራቸው? የእነዚህኞቹን ያህል የከበዱ ባይሆኑም፥ እኛም መላ የምናጣላቸውን አንዳንድ ፕሮጆቻችንን ምን ብለን እንጥራቸው? የእኔው ለዛሬ "ቋጠሮ" ተብሏል። እኔም ተቀብዬዋለሁ።

ከምንም የበለጠ ለረዥም ጊዜ በጌታ ፊት ያለቀስኩት ስለ አገልግሎት ጉዳይ ነው። ይህ ቋጠሮ ከሰዓት በፊት ፓስተር መርዕድ "... መሪዎች ስሞኑን ጠርተው ያነጋግሩሃል ..." ከሚለኝ የኦረኛነት አገልግሎት ጋር የተያያዘ ይሆን እንዴ? ከሆነ እግዚአብሔር አንዴት እድርጎ ይሆን የሚፈታው? ምክንያቱም እሱ ቋጠሮ ከሌላ ቋጠሮ ጋር የተቋጠረ ነው። ይህ ሌላ ቋጠሮ ደግሞ የትዳሬ ጉዳይ ነው። የመጀመሪያውን ቋጠሮ ያህል ባይሆንም፥ ይኸኛውም ቋጠሮ ብዙ ዓመታትን አስቆጥሯል። ሁለተኛው ቋጠሮ እሱ መሆን አለበት። ሦስተኛው ቋጠሮ ምን እንደ ሆነ እስከ ዛሬም ድረስ አልገባኝም።

ሰዎችን ለተጠሩለት የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ለመለየት መንፈሳዊ ሥልጣን ያለው በቤተ ክርስቲያን አጅ ነው። ቤተ ክርስቲያንም ይህንን ሥልጣኗን የምትተገብረው በሾመቻቸው መሪዎቿ አማካይነት ነው። እነርሱም በጸሎት እና እጆችን በመጫን ሥርዓት ሰዎችን በጌታ ለተጠሩለት አገልግሎት ይለያሉ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተደጋጋሚ የምናየው ይህንን ነው። የመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት በተሾሙ ጊዜ (ሐዋ. 6፥1-6)፤ በርናባስ እና ጳውሎስ ለተጠሩለት አገልግሎት በተለዩ ጊዜ (ሐዋ. 13፥1-3)፤ ጢሞቴዎስ በተለየ ጊዜ (1ጢሞ 4፥14)። የመለየቱ ሥነ ሥርዓት ሐዋርያቱ በወከሏቸው አገልጋዮች አማካይነት በተከናወነ ጊዜም (1ጢሞ. 5፥22)። እጅ በመጫን ሥርዓት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጅ ወደ ተጫነለት ሰው ይተላለፋሉ (ማር. 16፥18፤ 2ጢሞ. 1፥6)።

በብሉይ ኪዳንም ዘመን እንኳን ቢሆን፥ አሠራሩ አንደዚሁ ነው የነበረው። ለምሳሌ ሙሴ ኢያሱን በሾመ ጊዜ (ዘኁ. 27፥18-23)። በብሉይ ኪዳን ዘመን የመለየቱ ሥራ አብዛኛውን ጊዜ ይከናወን የነበረው "ቅብዐ ዘይት" በመቀባት ነበር። ለምሳሌ ሳሙኤል ሳኦልን እና ዳዊትን ባነገሣቸው ጊዜ (1ሳሙ. 10፥1፤ 16፥13)። የይሁዳ እና የእስራኤል ሸማግሌችም ዳዊትን ቀብተው በላያቸው ባነገሡት ጊዜ (2ሳሙ. 2፥4፤ 5፥3)። ቅብዐ ዘይቱ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። በአዲስ ኪዳንም ዘመን ቢሆን ለዚሁ ጉዳይ በአገልግሎት ላይ የሚውልበት ጊዜ አለ (ያዕ. 5፥14)።

ጌታ ኢየሱስ ራሱም ቢሆን ወደ አገልግሎቱ የገባው በጊዜው መንፈሳዊ ሥልጣን ባለው በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በመጠመቅ ነበረ (ማቴ. 3፥13-17)። ዮሐንስ እጁን አልጫነበትም፤ ቅብዐ ዘይትም አላፈሰሰበትም። ይሁን እንጂ

ከውሃው እንደ ወጣ ወዲያውኑ ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር መንፈስ በላዩ ሠውረዱ፥ "በአርሱ ደስ የሚለኝ ..." የሚል ድምፅም ከሰማይ መምጣቱ፥ ለአገልግሎቱ የተለየበትን የዚያን ሥርዓት በአግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት ያረጋግጣል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልጋዮችን ሲሾሙ የሚከተሏቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መመሪያዎች አሏቸው። ተሹዋሚው ሰው ለዚያ አገልግሎት በእግዚአብሔር ተጠርቷል ወይ? ተሹዋሚውን ሰው ለዚያ አገልግሎት ብቁ የሚያደርገው የተገለጠ ጸጋ አለው ወይ? ተሹዋሚው ሰው ቀደም ሲል በዚያ አገልግሎቱ የተገለጠ ፍሬ ታይቶበታል ወይ? ተሹዋሚው ሰው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲያሚሉ የሚጠበቁባቸውን መስፈርቶች ያሚላል ወይ? እነዚህ መስፈርቶች በብዙ የአዲስ ኪዳን ከፍሎች ውስጥ፥ በተለይም ደግሞ በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 እና በቲቶ ምዕራፍ 1 ውስጥ ተዘርዝረዋል። አስተምህሯዊ፥ ሥነ ምግባራዊ፥ አስተዳደራዊ እና ማኅበራዊ ይዘት አላቸው።

የእኔ ችግር እንግዲህ እዚህ ላይ ነው። እኔ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥4-5 ላይ "... የገዛ ቤተ ሰቡን በአግባቡ የሚያስተዳድር ሊሆን ይገባል። እንድ ሰው የራሱን ቤት ማስተዳደር ካላወቀበት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት አድርጎ ሊጠብቅ ይችላል?" የሚለውን መስፈርት አለሚላም። ትዳሬ ጥቂት ለማይባሉ ዓመታት እየተንገራገጨ ቆይቶ፥ ከጥቅምት ወር 1988 ዓ.ም. ወዲህ ግን ፈጽሞ ፈርሷል። ቀደም ሲልም ጀምሮ ገኑት የምትኖረው ከኢትዮጵያ ውጭ ስለ ነበረ፥ በዙሪያዬ ያሉ ሰዎች የሆነውን ነገር የሚያውቁበት መንገድ አልነበራቸውም። እኔና እርስዋም ብንሆን ከጥቂት የቤተ ሰባችን አባላት ጋር ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ከማንም ጋር አላወራነውም። ምንስ ተብሎ ይወራል? የምሥራች አይደል። ፓስተር መርዕድ "... እንደኛ አልተፋታችሁም ..." ሊለኝ የቻለው በዘህ ምክንያት ነው።

ሙቼም ለትዳር መፍረስ ኃላፊነቱ የሁለቱ ባለ ትዳሮች ነው። አሁን ጥያቄው፥ እንደዚህ ያለሁትን ሰው ቤተ ክርስቲያን "መጋቢ" አድርጋ ትሾመኛለች ወይ? ነው። ጥያቄው አሱ ብቻ ግን አይደለም። ለእኔ ከሱ ይልቅ የከበደኝ፥ እኔስ እሺ ብዬ እሾምላታለሁ ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። ከመለከረም 20 እስከ 29 ድረስ ያሉት ዐሥር ቀናት በእነዚህ ጥያቄዎች፥ በመልሶቻቸውና መልሶቻቸው በሚያስነሧቸው እንድምታዎች በእጅጉ የተጨነቅሁባቸው ነበሩ።

ከብዙ ዓመታት በፊት ጆን ሪድ በተባለ አሜሪካዊ ጋዜጠኛ የተጻፈ "ዓለምን ያንቀጠቀጡ ዐሥር ቀናት"[1] የተሰኘ መጽሐፍ አንብቤ ነበር። መጽሐፉ የሚያወራው እንደ ጎርነሳውያኑ አቆጣጠር በጎዳር ወር 1917 በልሼቪኮች በፔትሮግራድ (በኋላ ሌኒንግራድ) ሥልጣን በተቆናጠጡባቸው ዐሥር ቀናት ውሰጥ ስለ ተፈጸሙ ከሰተቶች ነው። ሌኒን ሰለዚያ መጽሐፍ በጻፈው መቅድም "... የዓለም ሠራተኞች ሁሉ ሊያነቡት የሚገባ መጽሐፍ ... በሚልዮኖች ቅጆች ታትሞ እና በሁሉም ቋንቋዎች ተተርጉሞ ላየው የምወደው መጽሐፍ ... " ብሎለታል።

የእኔዎቹ "ዐሥር አስጨናቂ ቀኖች" እንደዚያ የሚባልላቸው አይደሉም። ቢያንቀጠቅጡም እንኳን፥ እኔኑ ብቻ ነው። ምንድነው ማድረግ ያለብኝ? ጌታስ ምን እንዳደርግ ነው የሚፈልገው? መጸለይም፥ ማሰብም፥ እስከ አሁን የተጓዝኩትን ጉዞ ሁሉ ወደ ኋላ ተመልሼ መመርመርም፥ ነበረብኝ።

ሰባት ዓመት ወደ ኋሊት

ቅዳሜ፥ ሀዳር ፲፩ ቀን 1986 ዓ.ም። በጊዜው በነበረው አጠራር፥ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን "ሀ" መዘምራን የአዳር ጸሎት ነበራቸው። የአዳር ጸሎቱ የሚካሄደው በኮሎኔል ከፍሌ ሥዩም ቤት ሲሆን፥ በአግዚአብሔር ቃል እንዳገለግላቸው ደግሞ እኔን ጋብዘውኝ ነበር። አገልግሎቴ ወደ እኩለ ሌሊቱ ላይ ሲጠናቀቅ "ለጋሽ በቄ አንጸልይለታለን" ተባለና እኔን በመካከላቸው አድርገው፥ እነርሱ በዙሪያዬ ከብ ሠርተው፥ ሁላችንም ተንበረከከን። አየጸለይን እያለ ዘማሪ (አሁን መጋቢ ዶክተር) በድሉ ታንቁ እያየው ያለውን ራእይ ተናገረ። ወደ ቤቴ ከተመለስኩ በኋላ በማስታወሻ ደብተሬ ላይ ለእኔ እንደ ገባኝ አድርጌ የጻፍኩት፥ ለተነሣሁበት ጉዳይ አስፈላጊ ያልሆነው ተቀንሶለት፥ እንዲህ ይነበባል -

> ... ቀጣና ሁሰት ይወስደኛል ... የዱሮው የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ፥ ከዋናው በር ከፍ ብሎ ካለው ግድግዳ ላይ የሆኑ ጡቦች ወልቀዋል ... ስለዚህም ግንቡ ተቦድሷል ... እና ከዚህ የተነሣ የተፈጠረ ከፍተት አያለሁ ... በዚያ ከፍተት አማካይነት ከውስጥ ሰዎች ይወጣሉ፤ ከውጭም ችግሮች ይገባሉ ... ከፍተቱን መድፈን ይፈሊጋል ... እንዲደፍኑት ተፈልገው የሚመጡት ግን ሰዎች ናቸው ... ሰዎቹ የሚመጡት በአራት ዙር ነው፤ ሆኖም በአራቱም ዙሮች በመጡት ሰዎች ከፍተቱ አይደፈንም ...

> በመጨረሻ ላይ ጋሽ በቄ ይመጣል ... 'ይህ ምንድነው?' ብዬ ስጠይቅ የተሰጠኝ መልስ ... ብዙ ከሞከሩ በኋላ፥ ከመንገዳቸው ከጠቡና ከደከሙ በኋላ፥ ይፈልጉሃል ... አንተም ትገባለህ ... ከፍተቱም ይደፈናል ... ማዕበሉና ዥከቱ ሁሉ ጸጥ ይላል ...

የሚል ነው።

አገልግሎትን በተመለከተ ከዚያ ቀን በፊት ብዙ መልእክቶች ሰምቼ የማውቅ ቢሆንም፥ የዚያን ቀኑ መልእክት ግን በይዘቱ ከዚያ በፊት ከሰማኋቸው መልእክቶች ሁሉ ለየት ያለ ሆነብኝ። ከዘማሪ በድሉ ጋር እንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ አብረን እንሠራ ስለ ነበረ፥ ሰኞ ዕለት ጠዋት ሥራ ስንገባ ወደ ቢሮዬ አስጠራሁት እና እነጋገርኩት።

"... ሐሰተኛ ነቢይ ነህ እያልኩህ አይደለሁም ... ለእኔ እንደ ገባኝ ከሆነ ግን በቅዳሜ ማታው ራእይህ ውስጥ ያየኸው ያ ከፍተት የመጋቢ ወይም የሽማግሌ ቦታ ነው ... እኔ ደግሞ አንደኛ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሰለምሆን ሽማግሌ አልሆንም፤ ሁለተኛም የእንዲት አጥቢያ ቢተ ክርስቲያን መጋቢ ሆኜ እራሴን አይቼው አላውቅም፤ ጌታም መጋቢ እንደምሆን አልተናገረኝም ... እንተ ያንን ራእይ ከየት አመጣኸው?" አልኩት። በድሉ ጉዳዩን አላካበደውም -

"ጋሽ በቄ ... እትጨነቅ ... ራእዩ ከአግዚአብሔር ከሆነ ይመጣል ... ካልሆነ ደግሞ ይቀራል" ብቻ አለኝ። እኔም ስጠይቀው ተጨንቄ አልነበረም። ራእዩን እኔ የተረዳሁበት መረዳት ከእርሱ መረዳት ጋር ይስማማ ወይስ አይስማማ እንደ ሆነ ለማወቅ ነበር። እርሱ ግን ራእዩን አራሱ የተረዳበትን መንገድ ሰመግለጽም ሆነ ወይም የእኔን መረዳት ለማስተካከል ምንም ሙከራ አላደረገም። መልሱም መንፈሳዊ እና ትክክለኛ ነበረ። የሆነ በራሱ ወይም በጸጋ ሥጦታው የመተማመን ነገር አየሁበት። ደስ አለኝ፤ በውስጤም ባረከሁት። ልቤ ከማረቆም የተነሣ ነው መሰለኝ ነገሩን ወዲያውኑ ከውስጤ አወጣሁት። ነገሩም በእውነት ከውስጤ ወጣ - እስከ ... አ! እሱን ግን ስንደርሰበት።

"ኢታደርገውም!"

ኅዳር 24 - 27 ቀን 1991 ዓ.ም። የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የጀማ ሰብከተ ወንጌል በአዲስ አበባ ስቴድዬም አካሄደች። እንዳ

ንዶቻችን "ጀማ ሰብከተ ወንጌል" የምንለው "ክሩሴድ" በሚለው ቃል ላለመጠቀም ነው። በቃሉ መጠቀም ያልፈለግነው ቃሉ የሚያጭረው "የመስቀል ጦርነት" የተባለ፥ ጥሩ ያልሆነ ትዝታ ለላለ ነው። የአማርኛ እቻ ውም ይህንን ያህል ጥሩ ቃል ሆኖ አይደለም። እንዲያው "ቢቸግር" ነው። የተፈለገው "ብዙ ሰዎችን ሲላማ ያደረገ የወንጌል ሥርጭት" (MASS EVANGELISM) ወይም "የሜዳ ላይ የወንጌል ሥርጭት" (OPEN AIR EVANGELISM) ለማለት ነው። እነዚህ ደግሞ በአገራችን ገና በቅጡ አልተለመዱም።

ቤተ ክርስቲያኒቱ በራሰዋ እንደዚህ ያለ ከተማ-አቀፍ የሆነ የወንጌል ሥር ጭት እንቅሰቃሴ ለማድረግ ስትነሣ የመጀመሪያ ጊዜዋ በመሆኑ፥ በአገልጋዮችዋ እና በምዕመናኗ ዘንድ የተፈጠረው የደሰታ እና የመነሣሣት ሰሜት የተለየ ነበረ። እገልጋዮች ሁሉ በተለያዩ ግብረ ኃይሎች ተከፋፍለው ለብዙ ወራት ዝግጅት ሲያደርጉ ሰንብተዋል። ልጆች፥ ታዳጊዎች፥ ወጣቶችና ጎልማሶች ለሁለት ሳምንታት ያህል በከተማዪቱ ለምለክርነት ተሠማርተዋል። ቀኑ ቀረብ እያለ ሲመጣ በሥዕል የተደገፉ ማራኪ ማሰታወቂያዎችም በኢትዮጵያ ቴሌ ቪዥን እና ሬድዮ ተነግረዋል።

ዋናው አገልጋይ ከአሜሪካ የመጡት ዶክተር ሳሚይ ፕቲት ሲሆኑ፥ ከኢትዮጵያ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች አብረናቸው ነበርን። በእሰታድዬሙ አገ ልግሎት 4,150 ሰዎች ጌታን ተቀብለው የውሳኔ ካርድ ሞልተዋል። ብዙ ለዎች ክሕመማቸው ተፈውለዋል። ብዙዎችም ከአጋንንት አሰራት ተፈትተዋል። ቀደም ሲል በነበሩት የሁለት ሳምንታት የምዕመናን የምስክርነት ጊዜ ደግሞ በአስታድዬሙ አገልግሎት የውሳኔ ካርድ የሞሉትን ሦስት እጥፍ ያህል ሰዎች ጌታን እንደ ተቀበሉ ሪፖርት ተደርጎልናል። በተለይ የልጆቹ ምሰክርነት ብዙ ዎችን አለደንግጠ ነበር። "ደግሞ እናንተን ላክብን! ምን ሊመጣብን ይሆን?" ሲሉ የተደመጡ ጎልማሶች ነበሩ።

በዚህ አገልግሎት ውለጥ የአኔ ሚና አገልጋዮችን እና ምዕመናንን ሁሉ ለወንጌል ሥርጭት ለመቀሰቀሰ የተቋቋመውን ግብረ ኃይል ማስተባበር ነበር። ለነገሩ አንዳንድ ጉዳዮች ባለቤት ሳይበጅላቸው ቀርቶ እንዳይረሱ ለመጠንቀቅ ካልሆነ በስተቀር፥ የዚያን ጊዜው የሕዝቡ መነሣሣት የማንንም ማስተባበር የሚሻ ዐይነት አልነበረም። በሰፍራው ተገኝቶ የመዝሪያውን ፕሮግራም የዘገ በው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቃለ መጠይቅ ሊያደርግልኝ ጠየቀኝ። እኔም

ሦስበረ ኃይሎቹን ሁሉ አገልግሎት የሚያስተባብር ሌላ ሰው ከአኔ በላይ ስላለ፥ ቃለ መጠይቁን ለማድረግ ትክክለኛው ሰው እርሱ እንጂ እኔ እንዳይደለሁ አሰረዳሁ።

የቴሌቪዥኑ ሰው ግን "ቃለ መጠይቅ ማድረግ የምፈልገው ከአንተ ጋር ነው" አሰኝ። ከሰውዬው ጋር በመከራከር የማጠፋው ጊዜ አልነበረኝም። የመሪዎች ቡርድ ሰብሳቢ እና የግብረ ኃይሎቹም ሁሉ ዋና አሰተባባሪ ወደ ሆነው ወደ ፓስተር መርዕድ ሄድኩና ነገሩን ነገርኩት። እርሱም ያለ ምንም ማቅማማት ቃለ መጠይቁን ማድረግ እንደምችል ነገረኝ። የእርሱን ፈቃድ ካገኘሁ በኋላ ቃለ መጠይቁን አደረግን። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንም የራሱን ዘገባ እና የአኔን ቃለ መጠይቅ በምሽት ፕሮግራሙ አየር ላይ አዋላቸው።

ከዚያ ቀጥሎ በነበረው ሳምንት ይመስለኛል ወንድም ደረጀ አበበ ደወለልኝና በእርሱ አዘጋጅነት የምትታተመው "ሕይወት" መጽሔት በሚቀጥለው አትሚ ሰለ ጀማው ሰብከተ ወንጌል ዘገባ ይዛ እንድትወጣ ማሰባቸውን ነገረኝ። ከዘገባው ጋር በተያያዘ የሚፈልጓቸውን መረጃዎች በተመለከተም ከእኔ ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግ እንደሚፈልጉ ገለጸልኝ። "ሕይወት" አንጋፋ፥ በጊዜ ውም በጣም ተወዳጅ እና ተነባቢ የሆነች የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መጽሔት ነበረች።

እና የሚፈልጉትን መረጃ ለመሰጠት ደሰተኛ ሆንኩለት። ቃለ መጠይቁን በተመለከተ ግን ትክክለኛው ለው አኔ አለመሆኔን አሰረዳሁት። እንደ የኢት ዮጵያ ቴሌቪዥኑ ሰውዬ፥ ደረጀም 'እሻፈረኝ' አለኝ። አኔም እንደገና ወደ ፓስተር መርዕድ ሄድኩ። ፓስተር መርዕድም "አንተ ለምንድነው እንደዚህ ሳሳ የምታብዛው?" የሚል ዐይነት ነገር ተናገረኝ እና እንደገና ያለ አንዳች ማቅማማት ፈቀደልኝ። መጽሔቷም ዘገባዋን እና የአኔን ቃለ መጠይቅ ይዛ መ,ጋቢት 18 ቀን ወጣች።

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥኑን እና የሕይወት መጽሔቱን አጋጣሚዎች አዚህ ላይ ያነሣኋቸው፥ ከዚህ ቀጥሎ ለማነሣው ነገር ዳራ ስለሚሰጡልኝ ብቻ ነው። "ነገርን ነገር ያነሣዋል" ይባል የለ? በዚያ የጀማ ሰብከተ ወንጌል የቤተ ክርስ ቲያኒቱ አገልጋዮች እና ምዕመናን እጅግ ደለ እንደ ተሰኙ ከላይ ገልጫለሁ። አሳቡ ከተጠነሰሰበት ጊዜ አንሥቶ አገልግሎቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የሕዝቡ የልብ ትርታ አሱ ብቻ ሆኖ ነበር።

በጊዜው፥ በገንዘቡ፥ በዕውቀቱ፥ አንዲያው እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋ ሁሉ፥ ሳይሳተፍ የቀረ ሰው ያለ አይመሰለኝም - ከልጅ እስከ ዓዋቂ። እኔም ከተመ ደብኩበት ግብረ ኃይል ውጭ አስፈላጊ በመሰለኝ ወይም የተከፈተ በር ባገኘሁበት ሁሉ ዘው ዘው ብያለሁ። በአንዳንዶቹ በሮች ዘው ያልኩት ተጠ ይቄ ነው። ሳልጠየቅ ዘው ያልኩባቸው በሮችም አርግጠኛ ነኝ አይጠፉም። እንደዚያ በማድረጌም የተሠነዘረብኝ ውቀሳም ሆነ ወይም የተፈጠረ ሌላ ችግር አልነበረም።

ዕሑድ፥ መጋቢት 19 ቀን 1991 ዓ.ም። ከአስታድዬሙ ፕሮግራም ቀጥሎ በነበረው ሳምንት የጀማውን ስብከተ ወንጌል ለመገምገም አገልጋዮች ሁለት ጊዜ ተገናኝተናል። ዛሬ ከሰዓት በኋላ የተገናኘንው ወርኀዊ የሆነ የአገልጋዮች ሰብሰባ ስለ ነበረን ነው። በዕለቱ የተገናኘንበትን አጀንዳ አከናውነን ወደ ቤታችን ስንመለስ፥ እኔን ቤቴ ያደረሰኝ ወንድም ደመላሽ አይሸሽም ነበር። የመኖሪያ ሰፈራችን ይቀራረባል። ባልተቤቱ ሰፊ ጌታም አብራው ነበረች። የሰሞኑ ወሬአችን ስለ ነበረው የጀማ ስብከተ ወንጌል የሆነ የሆነ ነገር እየተባባልን ነበር የምንሄደው። በመሐሉ ሰፊ ጌታ -

"ለምን አንተን ፓሰተር እያደርጉህም?" ትለኛለች።

"ለምን አልሽ?" ስል አጠይቃታለሁ። የሆነ የሆነ መልሰ ትሰጠኛለች። ዝም አልኳት። እቤቴ ስደርስ ግን ልብሴን አወላልቄ እና ፒጃማዬን ለብሼ በቀጥታ ወደ ጸሎት ነው የሄድኩት። የሰፊ ጌታ ንግግር በጣም አሳዝኖኝ ነበር። እና ተንበረከከሁና -

> "ጌታ ሆይ! ሰፊ ጌታ 'ለምን ፓስተር እያደርጉህም?' የምትለኝ ምን ለማለት ፈልጋ ነው? ... ሹመት የምፈልግ ሰው መስያት ነው አይደለም? እኔ በጀማው ስብከተ ወንጌል ወቅት እዚህም እዚያም ዘው ዘው ያልኩት ሥራው እንዲቀላጠፍ ብዬ ነው ... ሹመት ፈልጌ አይደለም ... ቴሌቪዥኑም፥ መጽሔቱም ላይ የታየሁት ተገድጄ፥ ከወቅሜ በላይ ሆኖብኝ ነው ... እንዴት እንደዚህ ገመቶኝ?"

አልኩት። ደግሞ አሰብ አደረግሁና -

> "እንዴ? ... ሰፊ ጌታ ምን አጠፋች? ... በቅርብዋ ስላገኘችኝ ነው በግልጽነት የነገረችኝ ... እንጂ ሌሎች ብዙዎች ሰዎች ... እንደ ሰፊ ጌታ

> በቅርባቸው ሊያገኙኝ ያልቻሉ ሰዎች ... እንደዚሁ ገምተውኛል ማለት ነው ... ያደረግሁትን ሁሉ ... የቴሌቪዥኑንም፥ የመጽሔቱንም ... እራሴን ለማስተዋወቂያ እንዳደረግሁት መሰሏቸዋል ማለት ነው ... አዝናለሁ ..."

ስል ጨመርኩበት። ቀጠልኩናም -

> "እንዴ? ምን ይታወቃል? 'የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ ነው' ብለሃል ... ተንኮለኛው ልቤ እታልሎኝ ቢሆንስ? ... ያ ሁሉ ዘው ዘው ሳይታወቀኝ በእውነት ለታይታ ያደረግሁት ቢሆንስ? ... ለሹመት ፍለጋ የተደረገ ቢሆንስ?"

ወደሚል፥ የራሴን ተንሣሽነት ምክንያት ወደ መጠየቅ ተሸጋገርኩ።

ጸሎቴን ለጌታ በጽሑፍ ያቀረብኩባቸው ብዙ ጊዜያት በሕይወቴ አሉ። በተጥታ በጽሑፍ የጸለይኩባቸው ጊዜያት ግለቴ ነው። ይኸኛውን ግን እንደዚያ አይደለም የጸለይኩት። በቴፕም አራሴን አልቀረጽኩትም። ብዙዎቻችን ብዙ ጊዜ እንደምናደርገው ድምፄን አሰምቼ በንግግር ነው የጸለይኩት። ስለዚህ ከዚህ በታች በትዕምርተ ጥቅሰ ውስጥ ያስቀመጥኩትን ጸሎት ቃል በቃል እንደዚያ መጻለዬን እርግጠኛ አይደለሁም። ሆኖም የጸሎቴ ቅርጹም ሆነ ይዘቱ አሁን እንዳሰቀመጥኩት ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለኝም።

> "ጌታ ሆይ! እውነት ሰዎቹ እንደሚሉት ነኝ ወይ? ያደረግኩትን ሁሉ ያደረግኩት 'ዕወቁኝ፤ ፓስተር አድርጉኝ' ለማለት ነው ወይ? አንተ ምን ትላለህ?"

አልኩት። እግዚአብሔር ለጸሎቴ ከመቅጽበት መልስ ሲሰጠኝ ካየሁባቸው በቁጥር በጣም ውስን ከሆኑ ጊዜያት አንዱ ያ ቀን ነው። ጥያቄውን ከአፌ ባወጣሁበት በዚያው ቅጽበት፥ መልሱ ወደ ልቤ መጣ -

"እኔማ ነግሬህ የለም ወይ?"

"ምኑን?"

ወዲያውኑ የዘማሪ በድሉ ራእይ ታወሰኝ። ከ"ታወሰኝ" ይልቅ "ታየኝ" ብል ሳይሻል አይቀርም። ለመጀመሪያ ጊዜ - ከአምስት ዓመታት፥ ከአራት ወራት እና ከሰባት ወይም ከስምንት ቀናት በኋላ። "... ነግሬህ የለም ወይ?" ማለት ምን ማለት እንደ ሆነም አብሮ ገባኝ።

በኢንግሊዝኛ ቋንቋ "YOU DON'T MEAN IT!" ብዬ ከተንበረከከሁበት ተፈናጥሬ ተነሣሁ። ጮክ ብዬ ነው የተናገርኩት። "አታደርገውም!"፥ ወይም "የምርህን ሊሆን አይችልም!" ወይም "አትለኝም!" እንደ ማለት ነው።

"እገልግሎት ጥቅሙ ለራስ ነው" - በአገልጋዮች ዙሪያ ብዙ ጊዜ የሚለማ አባባል ነው። እውነት ነው፥ ሌሎችን ለናገለግል በተዘዋዋሪ እራሳችንን እያገለገልን መሆኑን እኔም አምንበታለሁ። እንደዚያ ባደረግን ጊዜ ሁሉ በውስጣችን የሚፈስለው የደስታ ስሜትም ነገሩ እውነት ለመሆኑ ምስክር ነው። እነዚያ "ከፉ" ዓመታት ዐልፈው፥ በኢትዮጵያም የከርስቶስ ወንጌል በአደባባይ የሚታ ወጅበት ዘመን መጥቶ በዐይኖቼ ለማየት በመብቃቴ፥ እኔም እራሴን እጅግ በጣም ዕድለኛ ሰው እንደ ሆንኩ አድርጌ ቆጥሬዋለሁ። በዚያ የጀማ ለብከተ ወንጌል እገልግሎት ውስጥ መሳተፍ በመቻሌ ደግሞ ልገልጸው ከምችለው በላይ በጣም ደስ ተሰኝቻለሁ። እግዚአብሔርንም በእጅጉ አመሰግኜዋለሁ።

እሁን የተሰማኝ ግን ደስታ ሳይሆን ድንጋጤ ነው። የደነገጥኩት ጨርሶ የረሳሁት እና በፍጹም ያልጠበቅሁት ነገር ስሰ ሆነብኝ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ቤቴ እና ሕይወቴ ከተመሳቀሉብኝ ገና ሦስት ዓመት ከአምስት ወር ገደማ ስለ ነበረ ሊሆንም ይችላል። "ሦስት ዓመት ከአምስት ወር? ... እጭር ጊዜ መሆኑ ነው እንዴ? ... በዚህን ያህል ጊዜ ውስጥ፥ ስው ከደረሰበት ከማንኛውም ዐይነት ከፉ ነገር ቢሆን እንዴት አያገግምም? ..." ሊባል ይችል ይሆናል። ለዚህ ጥያቄ እሁን መልስ መለጠት እያስፈልገኝም። አንባቢው መጽሐፏን እያነበበ ወደ ማገባደዱ ሲደርስ፥ መልሱን እራሱ ያገኘዋል።

ከዚያ በፊት፥ ዐሥራ ሰባት ዓመት

ከይርጋዓለም ተዛውረን ወደ ዲላ የመጣነው በሐምሌ ወር ኢጋማሽ 1968 ዓ.ም. ላይ ነው። ከዕለተ ዕሑዶቹ በአንደኛው እኔና ገነት ያመስከነው በእዋሳው (አሁን ሐዋሳ) ፊላደልፊያ (እሁን የሕይወት ብርሃን) ቤተ ክርስቲያን ነበር። ከሐዋሳ ነድተን አመሻሹ ላይ እቤታችን ስንደርስ ወንጌላዊ (በኋላ መጋቢ) ጻድቁ አብዶ እና ወንድም እዳነ ገብሬ ቁጭ ብለው ሲጠብቁን አገኘናቸው። እኔ በጊዜው ማስታወሻ (DIARY) የመያዝ ልምድ ስላልነበረኝ፥ ያች ዕለተ ዕሑድ መቼ እንደ ነበረች በጣም እርግጠኛ መሆን አልቻልኩም። ዝርዝሩን በምዕራፍ ስምንት ውስጥ እመለስበታለሁ።

ከወንጌላዊ ጻድቁ ጋር ይርጋዓለም እያለን እንተዋወቃለን። ከሚያገለግልባት ከባሌ ጎባ ሙሉ ወንጌል እማኞች ቤተ ክርስቲያን በመምጣት አገልግሎን ያውቃል። ከወንድም እዳነ ጋር ደግሞ ጅማ ተማሪዎች ሆነን እንተዋወቃለን። ከዐሥራ አምስት ዓመታት በፊት እኔ ሳውቀውም፥ እዳነ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ነበረ። እኔ ደግሞ በዚያን ጊዜ አከራሪ አርቶዶክስ ነበርኩ። ወንድም እዳነ ያንን አስታውሶ ነው መሰለኝ፥ የመጣው ወደ እኔ መኖሪያ ቤት መሆኑን ሲረዳ ተገረመ። እና በመደነቅ፥ በመተቃቀፍ እና በመሳሳም የታጀበ ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጥን።

ሥሜታችን ትንሽ እንደ ተጨዋወትን ገነት ሻይ እንዲቀርብልን አደረገች። ለሻዩ ሥመለሳኖ፥ "እሜን" ብለን፥ ካነነበስንበት ግን ገና ቀና ከማለታችን በፊት፥ ወንድም እዳነ ከፍ ባለ ድምፅ "ሃሌ ሉያ!" አለና በልሳን መናገር ጀመረ። እኔ ደነገጥኩ፤ ልቤ ለንጥቅ አለ። በልሳን የተናገረበት ጊዜ ምናልባት ከዐሥራ አምስት ሴኮንዶች የሚበልጥ አይመስለኝም። ከጨረሰ በኋላ እርሱም እኛም አንደ አቀረቀርን ዝም ብለን ለሴላ ዐሥራ አምስት ሴኮንዶች ያህል የቆየን ይመስለኛል። የእኔ ውስጥ የልሳኑን ትርጉም እየተጠባበቀ ነበረ። የሌሎቹም እንደዚያው ይመስለኛል።

ገነት እና እኔ ጌታን ካገኘን በዚያን ጊዜ ሁለት ዓመት በቅጡ እልሞላንም። ገነት ከጥቂት ወራት በፊት በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቃለች። በልሳን ትናገራለች፤ በልሳንም ትዘምራለች። እስከ ዛሬም ድረስ፥ በእርሷው ዐይነት ስው በልሳን ሲዘምር አልሰማሁም። ሜሎዲው እና ሪትሙ የመዝሙር መሆናቸውን ለይቼ ስጣወቅ የሚያስችለኝን ያህል ስለ ዜማ ዐውቃለሁ ስማለት እደፍራለሁ። በነገሩ በጣም ከመደነቄ የተነሣ በጸሎቷ ውስጥ በልሳን ስትዘምር በቴፕ የቀረጽኳት ጊዜም ነበረ።

እኔ ገና ነኝ። ቢሆንም እግዚአብሔር ሕዝቡን በልሳን እና በትርጉም የሚናገርባቸው ጊዜያት እንዳሉ ሁለታችንም እናውቃለን። ለዚህ ነው ወንድም እዳነ በኃይል በልሳን ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ፥ በጸሎት መንፈስ ውስጥ እንደ ሆንን ጸጥ ብለን በቆየንባቸው ጥቂት ሴኮንዶች፥ የእኔ ውስጥ ትርጉም እየተጠባበቀ የነበረው። ሆኖም ትርጉም አልነበረም።

የበለጠ ደነገጥሁ። ወንድም እዳነ ትርጉሙን ያልተናገረው መልእክቱ የቁጣ ስሰ ሆነ ይሆናል ብዬ እስበኩ። እግዚአብሔር ከተቆጣ ደግሞ፥ ሊቆጣ

የሚችለው ከእኔና ከገነት በስተቀር እዚያ ካለነው መካከል በሌላ በማንም ላይ ሊሆን አይችልም ብዬም ገመትኩ። ስምን እንደዚያ አንደ ገመትኩ አላውቅም። ምናልባት የቀሩት ሁስቱ አገልጋዮች ስስ ሆኑ ይሆናል። እገሌጋ የች "መላእከት" መስስው ይታዩን በነበረበት የትኩስ ፍቅር እና የመዳን ደስታ ወቅት ውስጥ ነበርን። ወንድም አዳነ ትርጉሙን ያልተናገረው፥ ነገሩ በጣም ከባድ ስለ ሆነ እሰፈርዶት መስለኝ። እና ተጨነቅሁ።

ሻያችንን እየጠጣን ትንሽ ተጨዋወትን። አዳነ በትምህርት ቤት ስስሚያውቀው ማንነቴ እንሥቶ አንዳንድ ነገር ተናገረ። ተሣሣቅን። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን የእኔ ልብ በመካከላችን በኃይል በተነገረው እና እስከ እሁን ትርጉሙን ባላወቅነው የልሳን መልእከት ላይ ነበር። ሁለቱ አንግዶች "ደኅና እደሩ" ብስውን ሊሄዱ ሲነሡ፥ ገነት እና እኔም ተከትለናቸው ከቤት ወጣን። በዚህ ጊዜ ቀሰ ብዬ ወንጌላዊ ጸድቁን ወደ ኋላ አስቀረሁትና -

> ... ወንድም አዳነ የቅድሙን መልእከት ያልተረጎመው እግዚአብሔር በእኔ እና በገነት ላይ ሰለ ተቆጣ መናገሩ ከብዶት ይመሰለኛል ... እኛ ግን ቁጣም ቢሆን ብንሰማውና ማስተካከል ያለብንን ነገር ብናስተካከል ይሻለናል ... ለምን ይደብቀናል? ... እባከህን ትርጉሙን እንዲነግረን ለምንልን

ሰል ተማጠንኩት። ወንጌላዊ ጸድቁ ሊያረጋጋኝ በብዙ ሞከረ። " ... የቁጣም ቢሆን የሌላ፥ አኔ በአካባቢው በአገልግሎት ላይ ሰላለሁ ለአኔ ይሆናል አንጂ ስለናንተ አይሆንም ... እትጨነቅ ..." እስከ ማለት ደረሰ። እኔ ግን አልሰማሁ ትም። ወንድም አዳነ እና ገነት ከአኛ በቅርብ ርቀት ቆመው እየተነጋገሩ ነበሩ። ወንጌላዊ ጸድቁ ወንድም አዳነን ከገነት ዞር አደረገውና ለብቻው እነጋገረው። ብዙም ሳይቆይ ደግሞ ወደ እኔ ተመለሰና "ትርጉሙ እልተስጠኝም" አንዳለው ነገረኝ።

መልሱ እንዲያውም ሌላ ጥያቄ ፈጠረብኝ።

> ... ትርጉሙ አልተሰጠኝም? ... እንዴት? ... ምን ማለት ነው? ... እኛ እንድናውቀው የሚፈልገው ነገር ከሌለው በስተቀር፥ እግዚአብሔር ዝም ብሎ ይናገራል? ... ያለ አንዳች ምከንያት? ...

ሁለቱን እንግዶች "እደሩ" አላልኳቸውም። የት እንዳረፉ አንኳን አልጠየቅኋቸውም። ሁለት የማውቃቸው ሰዎች፥ የእግዚአብሔር ስዎች፥ እኔ

ወደሃሞናዊበት ከተማ መጥተው፥ በእንግድነት ወደ ቤቴ ገብተው፥ በሌለሁበት ተተዓመጠው ሲጠብቁኝ ቆይተው፥ በማታ፥ ምናልባትም የሰዓት እላፊ በነበረበት ሁኔታ፥ "ደኅና እደሩ" ብስውን ወጥተው ሲሄዱ፥ ዝም ብዬ አየኋቸው። የዚህን ያህል ነበር የዞረብኝ ማለቴ ነው።

ይህ ከሆነ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፥ ወንድም አዳነ ለመንግሥት ሥራ እንደ ኮ/ ወደ ዲላ መጣ። ከሥራ ሰዓት ውጭ ስልከ ደወለና እቤት መሆናችንን አረጋግጦ ወዲያውኑ መጣ። የሞቀ ሠላምታ ተለዋወጥን። ሠላምታው ጋብ አንዳለ፥ ገነት እንደ ባልተቤትነቷ እንግዳ ለማስተናገድ ወዲያ ወዲህ ልትል ስትነሣ፥ ወንድም አዳነ ከለከላት። "በመጀመሪያ እንጸልይ፤ እስቲ መጽሐፍ ቅዱሰ አምጡልኝ" አለን። መጽሐፍ ቅዱሱ መጣ።

የዘረጠኝ ዓመቷ ራሔልም፥ ከአለታ ወንዶ ጀምሮ አብሮን ይኖር የነበረው ወንዱ ሠራተኞችን ደገፉ እና ሌቲ ሠራተኞችንም (አሁን ስሟ ጠፍቶኛል) ተጠሩና መጡ። ወንድም አዳነ ጸለየ እና ከእግዚአብሔር ቃል አካፈለን። ሲጨርስ ሁላችንም ለጸሎት ተንበረከከን። ጥቂት እንደ ጸለይን፥ ያ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ሰምቼው የነበረው ልሳን አሁንም መጣ። መቼም እርግጠኛ ልሆን አለችልም እንጂ፥ ልሳኑ ያው ቀደም ሲል የሰማሁት ልሳን ነው የሚመሰለኝ። ሣን ያውቃል? ይሆንም ይሆናል።

ልዩነት ቢኖረው የአሁኑ ልሳን ትርጉም ያለው መሆኑ ነው። እንደ ባልና ሚስት፥ ለግላችን የሆነ ትንቢት (PERSONAL PROPHECY) ሲመጣልን፥ ገነት እና እኔ የመጀመሪያ ጊዜአችን ነበር። አልጻፍኩትም፤ ቡቴፐም አለቀረጽኩትም። ሆኖም ይህ ከሆነ አሁን፥ ማለትም "ዐሥር አስጨናቂ ቀናት" ባልኩት ወቅት፥ ሐያ አራት ዓመታት ያለፉ ቢሆንም፥ ፊጽሞ አልረሳሁትም። ዮተባለውን ነገር ቃል በቃል በትከከል አስታውሳለሁ። ሌላው ቀርቶ በዚያ ምሽት ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በነበረው የመኖሪያ ቤታችን ሳሎን ውሰጥ የነበርነው ስድሰት ሰዎች፥ የተንበረከከንበትን ቦታ ሳይቀር በትከከል አስታውሳለሁ።

"ድምፄን እየሰማችሁ ብትከተሉኝ እመራችኋለሁ። ገና ብዙ ሰዎችን በአናንተ በኩል ወደ ቤቴ አስገባለሁ። ለዚህ አስነሥቻችኋለሁ።" ይኸው ነው። አጭር ለሳን፤ አጭር እና ግልጽ ትርጉም፤ ቢቃ። ጸሎቱን ጨርሰን ገና ቁጭ እንዳልን፥ ጸጥታውን የሰበርኩት እኔው ነበርኩ።

"አሁን የመጣው መልእክት ለማን ነው?" ስል ወንድም አዳነን ጠየቅሁት::

"መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ስሚመሰክርለት ሰው ነው::" የወንድም አዳነም መልስ በጣም አጭር እና ግልጽ ነበር::

ይህ መልእክት የመጣው በቁጥር ከአንድ በላይ በሆንን ሰዎች መካከል ነው:: "እየሰማችሁ"፥ "ብትከተሉኝ"፥ "አመራችኋለሁ"፥ "በአናንተ በኩል"፥ "አስነሥቻ ችኋለሁ" የሚሉት ቃላት የተነገሩት በብዙ ቁጥር ነው:: ተናጋሪውን ቀንሼ፥ በዚያ ከነበርነው አምስት ሰዎች መካከል፥ በቁጥር ከአንድ በላይ ሆነው እያሉ ነገር ግን በአንድነት የሚጠቀሱ ሰዎች አነ ማን ሊሆኑ ይችላሉ? ብዬ አሰቤለለሁ:: "ከእኔ እና ከገነት በስተቀር ሌላ አነ ማንም ሊሆኑ አይችሉም" ከሚል መደምደሚያ ላይ ነው የደረስኩት::

አሁን ግን ገነት አብራኝ የሰችም:: ምን ማለት ነው? ቀድሞውንም ተናጋሪው አግዚአብሔር አልነበረም ማለት ነው? ወይስ ገነት እና እኔ፥ ወይም ከሁለታችን አንዳችን፥ "... ድምፄን እየሰማችሁ ብትከተሉኝ ..." የሚሰውን ቅድመ ሁኔታ ሳናሚሳ ቀርተናል ማለት ነው? ወይስ? ... ወይስ? ... ሌሎችም ተያያዥ የሆኑ ብዙ ጥያቄዎች:: ነገር ግን ሁሉም መልስ የሌሳቸው ጥያቄዎች::

"እኔን ላከኝ!"

ዕሑድ ጥር 07 ቀን 1970 ዓ.ም:: ይህ ቀን የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ወርኀዊ ስብሰባ ቀን ነው:: ስብሰባው የሚካሄደው በአንጦጦ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ነው:: የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ፥ እንደ ተለመደው፥ በስደት ሳይ ነች:: ሆኖም በየወሩ የመጀመሪያ ዕሑድ ከሰዓት በኋላ የተበተነውን ምዕመኗን አንድትሰበስ ብበት የአንጦጦ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የራስዋን የመሰብሰብያ አዳራሽ ትሰቅቅላት ነበር::

የዚህ ወር የመጀመሪያ ዕሑድ የዋለው ጥር 7 ቀን ነው:: ከሰዓት በኋላ ስደተኞቹ የሙሉ ወንጌል ምዕመናን አንጦጦ ተገናኙ:: ገነት እና እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባዋ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ ተገኘን:: ከዲላ ተዛውረን አዲስ አበባ የገባነው ባለፈው ታሕሣሥ ወር ውስጥ ሲሆን፥ ስለ ስብሰባው የነገረን ወንድም (አሁን መጋቢ) ዓባይ ኃይሉ ነበር::

ስብሰባው ሞቅና ደመቅ፥ ዝማሬውም ነፍስን ከምድር የሚያላቅቅ፥ ወደ ጽርኅ አርያም የሚመነጥቅ ዐይነት ነበረ:: እንደዚህ ለመስለው ስብሰባ እና ዝማሬ ገነት እና እኔ ሙሉ በሙሉ እንግዳ አይደለንም:: በሐዋሳው የሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስቲያን አይተነዋል:: ገነት "በሾኔ ኮንፈረንስም" ላይ አይታዋለች:: ሰባኪው ማን፥ ስብከቱም ስለ ምን፥ እንደ ነበረ አሁን ትዝ አይሉኝም:: በጣም ትዝ የሚለኝ የጸሎት ጊዜው ነው:: በቁጥር ወደ አምስት መቶ የሚገመት ሕዝብ ቆሞ፥ ድምፁን ከፍ አድርጎ፥ በአንድነት ወደ እግዚአብሔር ይጮኽ ነበር:: በእንደዚህ ዐይነቱ "ጩኽት" የተሰናከልኩበት ጊዜ ነበረ:: እንደዚያ የሆነው ግን ከሁለት ተኩል ዓመታት በፊት ነው::

እንደዚያ እየተጸለየ እያለ ነው፥ አንዲት እኅት ከሌሎቹ ይልቅ ከፍ ባለ ድምፅ በልሳን መናገር የጀመረችው:: ወዲያውም የእርስዋ ድምፅ ከፍ፥ የጉባዔው ድምፅ ደግሞ በዚያው መጠን ዝቅ እያለ ሄደና የሚሰማው የእርስዋ ልሳን ብቻ እስከሚሆን ድረስ ቤቱ ጸጥ አረጭ አለ:: ልሳኑ ረዥም የነበረ ይመስለኛል:: ልሳኑ ሲያልቅ፥ በልሳን ተናጋሪዋ እኅት በኩል ይሁን ወይም በሌላ እኅት በኩል አላውቅም፥ ትርጉም መጣ::

እንኳን ሕዝቡን የማላውቀው እኔ፥ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ነባር የሆነ ሰውም ቢሆን ኖሮ ቀና ብሎ ተናጋሪው ሰው ማን እንደ ሆነ ስማየት ድፍረቱ የሚኖረው አይመስለኝም:: እንዳች አስደሳች እና አስፈሪ ድባብ በጉባዔው ላይ ወድቆ ነበር:: "የእግዚአብሔር ኩበር" ሲባል የሰማሁት ነገር ይህ ይሆን? ተናጋሪውን ሰው ማወቅ የሚቻለው በድምፁ ብቻ ነበር:: ያንን ማድረግ የሚችሉትም በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ የቆዩት ምዕመናን እንጂ የእኔ ብጤው እንግዳ ሊሆን አይችልም::

እንደ ልሳኑ፥ ትርጉሙም ረዥም የነበረ ይመስለኛል:: ሆኖም፥ እኔን ከሚመለከተኝ ነገር በስተቀር ሌላውን እንዱንም አላስታውሰውም:: ከአዳራሹም እንኳን አብሮኝ የወጣ አይመስለኝም:: በትርጉሙ ውስጥ አንድ ጥያቄ ተሰነዘረ:: ጥያቄውም በቀጥታ ከትንቢተ ኢሳይያስ 6፥8 ላይ የተወሰደ ነው - "ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል?" የሚል:: ይህንን ጥያቄ በሰማሁ ጊዜ በውስጤ ያስፈውን ነገር ለማስረዳት መሞከር እንዲያው መድከም ነው:: "ጦሽ" ብዬ የምፈነዳ እስኪመስለኝ ድረስ ማልቀሴን ግን አስታውሳለሁ::

አግዚአብሔር በጣም እሳዘነኝ:: በዚህ ሁሉ ሕዝብ መካከል ስው ያጣ፥ የተቸገረ፥ የሰው ደህ የሆነ መሰለኝ::

"እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል?" ስል ራሴንም፥ እግዚአብሔርንም ጠየቅሁ:: ጥያቄዬ ግን መልሰ የሚሻ ዐይነት እልነበረም:: እንዲያው የመገረም፥ ከመጠን በላይ የመገረም፥ ነበር:: ወዲያውም _

> እኔ ምንም አላውቅም ... እኔ ምንም እልችልም ... ነገር ግን እንተ የዚህን ያህል ሰው የተቸገርከ ከሆነ፥ ይህንን እንተ በሥጋም ሆነ በነፍስ ከሞት ያዳንከውን ሕይወቴን ልከለከልህ አልፈልግም ... ጌታ ሆይ፥ እነሆኝ፥ እንካኝ፥ እኔን ላከኝ ...

አልኩ::

ከገነት ጋር ጎን ለጎን ነው ተቀምጠን የነበረው:: እንደዚያ ስነፋረቅ እንኳን እርስዋ፥ በቀኝና በግራ፥ በፊት እና በኋላ፥ በአጠገቤ የነበሩ ሦስት አራት ስዎች ሳይሰሙኝ አይቀሩም:: እኔ ግን ሌላ ማንንም ሰው መስማት በምችልበት ሁኔታ ውስጥ እልነበርኩም:: በዚያን ዘመኑ የጴንጤቆስጤአውያን ጉባዔ ላይ በጸሎት ወቅት ማልቀስ እንግዳ ነገር እልነበረም:: ዐይኖቸ እርጥበት-አልባ አየሆኑ የመጡት ቆይቶ ነው:: ገነት እና እኔም ብንሆን ብዙ ጊዜ አልቅስን እናውቃለን:: በኀዘን እና በጸጸት ያለቀስንበት ጊዜ የነበረ ቢሆንም፥ በአብዛኛው ግን ዕንባችን የበረከት ነበር::

በዕለቱም ሆነ በሌላ ጊዜ፥ ገነት እና እኔ ስለዚያ ስብሰባ እንሥተን ያወራን አይመስለኝም:: እውርተንም ከሆነ ምን አንደ ተባበልን ትዝ አይለኝም:: ከብዙ ዓመታት በኋላ ከፓስተር እሳየቪኝ በርቪ ጋር ናይሮቢ፥ ኬንያ፥ ተገናኝተን ጥሪአችንን በተመለከተ ስለ የግል ልምምዳችን ስንጨዋወት፥ እር ሱም በዚያን ዕለት በዚያ ቦታ እንደ ነበረ እና ተመሰሳይ ነገር በሕይወቱ እንደ ዐለፈ ነግሮኛል:: ለንቱን ነገር ስጠይቅና ሰረዳ፥ ስንቱንም ነገር ሳሲታውስ፥ ስብዙ ዓመታት ከማንም ይልቅ በቅርቤ የነበረችው ስው በዚያን ዕለት፥ በዚ ያም መልእከት፥ ምን እንደ ተሰማት ጠይቄአት ሳልረዳ መቅረቴ ይገርመኛል::

ለምን ይህን ያህል ዘመን?

ጅማ፤ ዕሑድ መጋቢት 28 ቀን 1989 ዓ.ም:: ሥራዬን በፈቃዴ ለመልቀቅ ወስንኩ:: ሥራዬን የመልቀቁ ሂደት ግን እስከ ግንቦት 23 ቀን ድረስ ጊዜ

ወስዷል:: ከላይ ያነሣሁት ጥያቄ እና መልሰ በተካሄደበት ቀን እና ሙሉ ጊዜዬን ለመስጠት ውሳኔ ባደረግሁበት ቀን መካከል የዐሥራ ዘጠኝ ዓመታት፥ ከሁለት ወራት እና ከሦስት ሳምንታት ጊዜ ዐልፏል ማለት ነው:: ለምን እና እንዴት ነው ይህን ያህል ጊዜ ሊያልፍ የቻለው? ይህንን ጥያቄ ብዙ ጊዜ በመደጋገም እራሴን ጠይቄው ዐውቃስሁ:: ምክንያቶቼ ሆነው ያገኘኋቸው የሚከተሉት ናቸው:-

የመጀመሪያው "በቅድሚያ ለመንፈሳዊ እገልግሎት አስፈላጊ የሆነውን 'ኃይል' መቀበል አለብኝ" የሚል እንደ ነበረ በትከከል አስታውሳለሁ:: ጌታ አራቱ ሐዋርያቱን "እኔም አባቴ የስጠውን ተስፋ እልከላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስከትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" ብሏቸዋል (ሉቃ. 24፥49):: "መንፈስ ቅዱስ ከወረደ ስለ ቆየ፥ ያ የተባለው ለመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት ብቻ ነው" እንዳልል፥ "የተስፋውም ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ እንዲሁም ጌታ እምላካችን ወደ ራሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና" ይላል (ሐዋ. 2፥39):: ይኸኛው ጥቅስ ያለ ጥርጥር እኔን ያካትታል:: አዎን፥ ተስፋው ከተፈጸመ 2,000 ዓመት ሆኖታል:: ሆኖም እኔ የዚያ ተስፋ ተካፋይ ገና እልሆንኩም:: እመለከራለሁ፤ እሰብካለሁ:: ሙሉ ጊዜ መስጠት ግን ከመመለከር እና ከመስበክ ያለፈ ነገር እንደ ሆነ ነው ከመጀመሪያውም የነበረኝ መረዳት::

ረቡዕ መጋቢት 02 ቀን 1973 ዓ.ም. በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቅሁ:: ሁኔታው እንዴት እንደ ነበረ፥ ምናልባት በሌላ ርእስ እመለስበት ይሆናል:: ለእሁኑ ግን፥ በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቅሁ እና በልሳንም ከተናገርኩ በኋላ ለምን እንደ ዘገየሁ ብቻ ልናገር:: እንደኛ በመጠራት፥ በመውጣት እና በመለየት ('ለ' ትጠቢቃለች) መካከል የጊዜ ልዩነት ያለ፥ ሊኖር የሚችል፥ ወይም ሊኖር የሚገባ ይመስለኛል:: የጊዜው መርዘም እና ማጠር ከለው ስው ሊለያይ ይችላል:: በአንዳንዶች ዘንድ ጊዜው በጣም ከማጠሩ የተነሣ ልዩነቱ በግልጽ እስከ አለመታየት ሊደርስ ይችላል::

በምሳሌ ለማስረዳት ልሞክር:: ጴጥሮስ የተጠራው መቼ ነው? ማለቴ በዮሐንስ ወንጌል 1:41-43 ላይ በተጠቀሰው ወቅት ነው? ወይስ በሉቃስ ወንጌል 5፥1-11 ላይ በተጠቀሰው ወቅት? እኔ የዮሐንስ ወንጌሉ የተጠራበት፥ የሉቃስ ወንጌሉ ደግሞ የወጣበት ይመስሉኛል:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ስመልስው

"የወጣበት" ማለት "ሙሉ ጊዜውን የሰጠበት" ማለት ነው። የተለየው ግን በሉቃስ ወንጌል 6፥12-16 ላይ መሆኑ ግልጽ ነው።

ሙሴ በሕይወቱ ያለውን የእግዚአብሔርን ጥሪ ወደ መረዳት የመጣው በፈርዖን ቤተ መንግሥት ውስጥ ይኖር በነበረ ጊዜ ነው። ግብፃዊውን በገደለ እና ወንጮቹንም ሊያስታርቅ በሞከረ ጊዜ "... እግዚአብሔር በእርሱ እጅ ነጻ እንደሚያወጣቸው የሚያስተውሉ መስሎት ነበር፤ እነርሱ ግን አላስተዋሉም" ይላል (ሐዋ. 7፥25)። ይህም ማለት፥ በዚያን ጊዜ እርሱ ጥሪውን ያውቅ ነበረ ማለት ሲሆን፥ ወገኖቹ ግን ያንን ወደ ማስተዋል ገና አልደረሱም ነበር ማለት ነው። ሙሴ በዚያን ጊዜ ዕድሜው 40 ዓመት ነበር። ለጥሪው ታዞ የወጣው ግን ከሌላ 40 ዓመት በኋላ ነው። በመጠራት እና በመውጣት መካከል የምናገኘው ረዥሙ ጊዜ ምናልባት ይኸ ሳይሆን አይቀርም። በሙሴ መውጣት እና በሙሴ መለየት መካከል ግን የጊዜ ከፍተት አይታይም።

ሌላም እንድ ምሳሌ ልጨምር። ጳውሎስ የዳነውም ሆነ የተጠራው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ 9፥1-8 ላይ የተጠቀሰው ታሪክ በሕይወቱ በተፈጸመ ጊዜ መሆኑ እከራከሪ አይደለም። እርሱ እራሱ ያንን ልምምዱን በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ 22፥6-16 እና 26፥9-19 ላይ በተብራራ መልኩ ገልጾታል። በጀ፥ የወጣውስ መቼ ነበር? የተሻለው መልስ "ከተጠራ ከሦስት ቀናት በኋላ" የሚለው ይሆናል (ሐዋ. 9:9-18)። ምክንያቱም ከሐናንያ ጋር ከተገናኘ፥ ዐይኖቹ ከበሩለት፥ በውሃ እና በመንፈስ ቅዱስም ከተጠመቀ በኋላ፥ በሙሉ ጊዜው ጌታን እያገለገለ እንደ ነበረ እናውቃለንና (ገላ. 1፥11-24)። የተለየው ግን ከብዙ ዓመታት በኋላ፥ የእንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለበርናባስ እና ለእርሱ እጅ ጭነው በጸለዩላቸው ጊዜ ነው (ሐዋ. 13፥1-3)። በመጠራት እና በመውጣት መካከል የጊዜ ልዩነት የማናየው በማቴዎስ "ኬዝ" ነው (ማር. 2፥14)።

በመጠራት እና በመውጣት ወይም በመውጣት እና በመለየት መካከል ያለው ጊዜ የዝግጅት ጊዜ ነው - እግዚአብሔር የእገሌጋዩን ሕይወት የሚሠራበት። እግዚአብሔር የእገሌጋዩን እምነት የሚያሳድግበት። እግዚአብሔር እገሌጋዩን በቃሉ እና በመንፈሱ የሚያስታጥቅበት። እግዚአብሔር የእገሌጋዩን ጥሪ የሚያጠራበት፤ ማለትም ለአገልግሎቱ ቅርጽ እና ይዘት የሚሰጥበት። እግዚአብሔር የእገሌጋዩን የአገልግሎት ጸጋ እና የአገልግሎት ፍሬ የሚገልጥበት።

ይህ ጊዜ የእግዚአብሔር ሥራ ወይም እንቅስቃሴ በእገሌጋዩ ዙሪያ ብቻ የሚወሰንበት ግን አይደለም። እግዚአብሔር ሠራተኛውን ብቻ ሳይሆን የሥራውን መሰከም ጭምር፥ ተዋናዩን ብቻ ሳይሆን መድረኩንም ጭምር የሚያዘጋጅበት ጊዜ ነው። ይኸ የእግዚአብሔር የማዘጋጀት ሥራ በእገሌጋዩ ጠባራት እና መውጣት ወይም በእገሌጋዩ መውጣት እና መለየት መካከል ባሉት ጊዜያት ብቻ ተከናውኖ የሚጠናቀቅም አይደለም። እገሌጋዩ ከተለየ በኋላም በሕይወቱ እና በአገልግሎቱ የሚቀጥል ነው።

ከእነዚህ ምክንያቶች የተነሣ፥ ሙሉ ጊዜዬን የምሰጥበት ወይም ደግሞ ለአገልግሎት የምወጣበት ጊዜ፥ ለእኔ የተለየ ትርጉም ነበረው። ለምወጣበት ጊዜ ሰጥቼው የነበረው ከብደት ለጥሪዬ ከሰጠሁት ከብደት የሚያንስ እይመ ሰለኝም። በእንጦጦው ሰብሰባ ወቅት "እኔን ላከኝ" ልበል እንጂ፥ ጌታ በእርግጥ የጠራኝ መሆኑን ለማረጋገጥ፥ ከዚያም በኋላ ብዙ ጊዜ ወስዶብኛል። ብዙ ጸልዬአለሁ። የብዙ የእግዚአብሔር ሰዎችን ተሞክሮ አዳምጫለሁ።

እሱን ካረጋገጥኩ በኋላ ደግሞ፥ የምወጣበትን ጊዜ ለይቶ ለማወቅ የዚያኑ ያህል ተቸግሬአለሁ። "ወጥቼ ምን አደርጋለሁ?" ሊሚለው ጥያቄ ለራሱ በቀላሉ መልስ አላገኘሁለትም። ወደ ኋላ ተመልሼ ባለብኩት ቁጥር ብዙ ጊዜ እስቆኝ ያውቃል። "ለንት ስብከቶች መስበክ እችላለሁ?" ብዬ ያሉኝን የተዘጋጁ ሰብከ ቶች መቁጠር የሞከርኩባቸው ጊዜያትም ነበሩ። በጣም ጥቂት ሆነው ነው ያገኘኋቸው። እና በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ስብኬ የምጨርሳቸው መስለኝ።

ለመውጣት የቸኮልኩባቸው፥ የተቅበጠበጥኩባቸው፥ ጤና እና ዕረፍት ያጣሁ ባቸው ወቅቶችም ዐልፎ ዐልፎ ነበሩ። እንደዚህ ካሉት ወቅቶች በአንደኛው ከሰዓት በኋላ ሥራዬን ጥዬ ከቢሮ ወጥቼ እስከ መሄድ (WALK OUT እስከ ሚደረግ) ደርሻለሁ። ደግነቱ እርቄ አልሄድኩም። በመሥሪያ ቤቴ አቅራቢያ ወደ ነበረው ወደ ፓስተር መርዕድ ለማ ቤት ነበር የሄድኩት። እርሱም በዚያች ጉደኛ ከሰዓት በኋላ በቤቱ ውስጥ ነበረ። በሩን ከፍቶልኝ ስገባ "ምነው በሥራ ስዓት?" ያለኝ ይመለለኛል።

"ተውኩት!" አልኩት።

ግር አለው። ከላይ እለከ ታች፥ ከታች ደግሞ እስከ ላይ፥ ዝም ብሎ ተመለከተኝ።

"ምኑን ነው የተውከው?"

"ሥራውን ነዋ!"

"... ዛሬ ምን ሆነሃል? ... ደኅና እይደለህም እንዴ? ..."

"... እይ፥ ደኅና ነኝ"

"ታዲያ 'ተውኩት' የምትለው እሱ ምንድነው?"

"ሥራው ነዋ! በቃ! ተውኩት!"

እስከ አሁን እየተነጋገርን ያለነው የበሩን ደፍ ብቻ ገባ ብዬ፥ ግን ሁለታችንም አሱ ከወደ ውስጥ፥ እኔ ደግሞ ከወደ ውጭ፥ አንደ ቆምን ይመስለኛል::

"እንዴ? ... አስቲ ግባና ቁጭ በል ... ምንድነው እሱ የሆንከው?"

ተቀመጥኩ እና ላወራው ጀመርኩ:: "... ሥራውን ተውኩት! ... 'ቋቅ' ሊለኝ ደረሰ ... ስለዚህ በቃኝ ... ወጣሁ ..." ስል ደረደርኩለት::

"እኮ እንዴት አድርገህ ነው የተውከው? ... መሥሪያ ቤቱ አሰናበተህ ወይ? ... በእጅህ ያለውን ንብረት አስረከብክ ወይ?"

የሚለኝን እንዱንም አላደረግሁትም:: እንኳን ላደርገው ጨርሶም አላሰብኩትም እንጂ:: ጉድ እኮ ነው::

"... ታዲያ ልሙት እንዴ? ..."

"አ! ... እንዲህማ ከሆነ ውርደት አምሮሃላ! ... በፖሊስ ተይዘህ ... የፊጥኝ ታስረህ ትመለሳታለሃ! ... ያውም ከባንክ ነው ዝም ተብሎ ተወጥቶ የሚኬደው? ... የዚያን ሁሉ ሰው ሀብት እና ንብረት በትኖ? ... ወይስ የጌታን ሰም ለማሰደብ ነው? ... ወይስ የቅዱሳኑን ምስክርነት ለማበላሸት ነው?" መቼም ወረደብኝ:: ደግሞ እውነቱን ነበር:: እኔስ ይሀንን ሁሉ እንዴት ሳላስበው ቀረሁ? እሱስ ይሀንን ሁሉ እንዴት ዐወቀው?

"እና ... ቢቃ እኔ ልሙት ማለት ነው? ... አንድ አንጀራ ለመብላት?"

"ማን እንደ ሞተ አንተ ትሞታለህ?"

ትንሽ ቆየናም፥ አሳዘንኩት መስለኝ፥ "... ደግሞ እንጸልያለን ... ጌታ ጊዜውን እንዲያሳጥረው እንጸልያለን" አለኝ::

ተንበረከከሁና እጆቹን ጭኖ ጸለየልኝ:: እና ማንም ሳይሰማ፥ ሹልክ ብዬ ከቢሮዬ እንደ ወጣሁ፥ ሹልክ ብዬ ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ - በዚያችው ከሰዓት በኋላ:: ይህ የሆነው በ1973 ዓ. ም. ነው:: ወሩን እና ቀኑን አልያዝኳቸውም::

ከዘለሀ በተቃራኒው ደግሞ፥ ጌታን -

> ላገለግልህ በፍጹም አልችልም ... ቢሆንልኝ ኖር ደስ ባለኝ ነበር ... ነገር ግን አይሆንልኝም ... ቃልህን አላውቅም ... ለሰዎች ፍቅር የለኝም ... የምወደው እራሴን ብቻ ነው ... አንተን ማገልገል ቀርቶ መከተልም እንኳን የሚያስከፍለውን ዋጋ ለመክፈል በፍጹም ዝግጁ አይደለሁም ... የከበረውን ከተዋረደው ለይቼ አላውቅም ... በቃሌ ለመጽናት እቸገራለሁ ... ለሰይጣን ሽንገላ በቀላሉ እሸነፋለሁ ... ወዘተርፈ. ... ወዘተርፈ ...

ያለኩባቸው ጊዜያት ጥቂት አይደሉም:: ከቸኮልኩባቸው፥ ከተቅበጠበጥኩባቸው፥ ጤና እና ዕረፍት ካጣሁባቸው ወቅቶች ይልቅ እነዚህኞቹ በጣም ይበዛሉ::

በመጨረሻም የነኔት ጉዳይ እለ:: በእርግጥ ሁለታችንም ጌታን በሙሉ ጊዜአችን እናገለግለዋለን ብዬ ከመጀመሪያውም ቢሆን አልጠበቅሁም:: ሆኖም ቢያንስ እንዳችን በሙሉ ጊዜአችን፥ እንዳችን ደግሞ በትርፍ ጊዜአቸን ጌታን እብረን እናገለግለዋለን ብዬ በጣም ተስፋ ሳደርግ ነበር:: ስንጀምርም አብረን በማገልገል ነበር የጀመርነው:: በጣምም ደስተኞች ነበርን:: በጸሎቱ እና በምስክርነቱ አገልግሎት እርሷ ከእኔ ይልቅ እጅግ ትበረታ ነበር:: የስማናቸው የተለያዩ መልዕክቶችም ነበሩ:: ስለዚህም ከዛሬ ነገ አሳቧን ትለውጣለች ወይም ደግሞ አግዚአብሔር ይናገራታል የሚል ተስፋ አለመቁረጥ በውስጤ ነበር::

ያ ተስፋ አለመቁረጥ ለረዥም ጊዜ ከአኔ ጋር ቆይቷል:: መጋቢት 30 ቀን የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ አስገብቼ ነው፥ ሚያዝያ 19 ቀን፥ በዕለተ "ትንሣኤ" ለእርሷ ረዥም ደብዳቤ የጻፍኩላት:: ጨርሰን ከተለያየን ከአንድ ዓመት ከመን ፊቅ ያህል በኋላ ማለት ነው:: እንደኛ ሙሉ ጊዜዬን መስጠቴን ላስታውቃት:: ሁለተኛም አንደ ገና አብረን ለመኖር፥ አንደ ገናም አብረን ለማገልገል፥ ዕድል ይኖረን አንደ ሆነ ልጠይቃት:: አንደ አኔ "ለሙታን ሕይወትን በሚሰጠው" (ሮሜ 4፥17) የሚያምን ሰው ይቅርና፥ ሌላስ ተራ "አምንታዊ አሳቢ" ይህንን ያደርገው የለም?

እንቢተኛነትስ አልነበረም?

ይህም ሁሉ ሰበብ ይደርደር እንጂ፥ በእኔ በኩል እንቢተኛነት ፈጽሞ አልነበረም ብዬ አፌን ሞልቼ ለመናገር አቸገራለሁ። ጥሪዬ እና ሙሉ ጊዜ የምሰጥበት ጊዜም፥ ግልጽ ሆነውልኝ እያሉ ላለመታዘዝ ሰል ብቻ ጊዜ ማራዘሜን አላስ ታውሰም። ጌታን በሙሉ ጊዜዬ ላለማገልገል ሰል የዘገየሁበትን ጊዜ በፍጹም አላስታውሰም። ሆኖም ግን ወደ መጨረሻው ላይ "እለመታዘዝ በእኔ በኩል ሳይኖር አልቀረም" እንድል ያደረጉኝ ነገሮች ተከስተዋል። ሰው ደግሞ በተፈጥ ሮው ለራሱ ተሟጋች አንደ ሆነ የሥነ ልቦና ሊቃውንት ይናገራሉ። ሰለዚህ ይኸ "በጭራሽ አላስታውሰም" የምለው ንግግሬ፥ እሱ እለመሆኑን በምን ዐውቃለሁ? እንቢተኛነት በእኔ በኩል ሳይኖር አልቀረም ከምልባቸው ምክንያቶች ሦስቱን ቀጥዬ ልጥቀሳቸው።

ታኅሣሥ 16 ቀን 1989 ዓ.ም ከፓስተር አሳየኸኝ በርኸ ጋር ለአገልግሎት ወደ ጎንደር ሄድን። እርሱ በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ዋና ጸሐፊ ነበረ - የመጀመሪያው ዋና ጸሐፊ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ፕሮግራም መዛባት ስለ አጋጠመው ትንሽ ተንገላትተን እና አምሽተንም ነበር የገባነው። መኝታ የያዝነው ቋራ ሆቴል ነው። መኝታ ከያዝን በኋላ በዚያ ካሉት የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጋር ጥቂት የማይባል ጊዜ አብረን ማምሸት ነበረብን። እራታችንን በልተን ወደ መኝታችን ለንሄድ አኔ በጣም ደክሞኝ እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል። ሰለዚህም ዘወትር ከእንቅልፍ የምነቃበትን ሰዓት በእጅጉ አሳልፌ ከንጋቱ 11:00 ሰዓት ላይ ነው የነቃሁት። ሰነቃ ግን ከሕልም ነበር የነቃሁት።

ከአንድ የልጅነት ጓደኛዬ ጋር አንድ ትልቅ ሜዳ ላይ አብረን ቆመናል። ይህ የልጅነት ጓደኛዬ ማን አንደ ሆነ አላውቀውም። አብሮኝ እንደ ነበረ ብቻ እንጂ ፊቱንም አላየውም። የቆምነው ፊታችንን ከእኛ በተቃራኒ ባለው የሜዳው ዳርቻ በተከመረ ድንጋይ ላይ የሆነ ሥራ እየሠሩ ወዳሉ ሰዎች አዙረን ነው። አብሮኝ ያለው ጓደኛዬ ሄጀ ከእነዚያ ሰዎች ጋር አብሬ እንድሠራ የሚመክረኝ ወይም የሚለምነኝ ይመስለኛል። እኔ ግን ፈቃደኛ አይደለሁም። ለረዥም ጊዜ ከለመነኝ በኋላ፥ እንዴት እንደ ሆነ ሳላውቀው፥ እራሴን ሰዎቹ አጠገብ ቆሜ እገኘዋለሁ። የት እንደ ቀረ አላወቅሁም፥ ባልንጀራዬ ባጠገቤ አልነበረም።

ሰሦቹ ከሦስት አይበልጡም። ካቦ (አሠሪ) አላቸው። ካቦአቸውም በቁጣ "ትሠራ እንደ ሆነ ሥራ፤ ከእንግዲህ እንለምንህም" ይለኛል። ብዙ ድንጋዮች ተቆልለዋል። ትንንሽ ድንጋዮች ናቸው። ከእጄ ጡጫ ያናንሳሉ። የተለያየ ቅርጽ ነው ያላቸው። ከሠራተኞቹ እንዱን፥ ድንጋዮቹን ምን እያደረጓቸው እንደ ሆነ አጠይቀዋለሁ። ከድንጋዮቹ መካከል የሆኑ ዐይነት ድንጋዮችን እየመ ረጠ እንዳሉ ይነግረኛል። የመረጡአቸውንም ድንጋዮች ያሳየኛል።

ሃንበስ እልና ከድንጋዮቹ እንዱን በእጄ እንሥቼ እየዋለሁ። ካቦውን አቪ እንዳልለው ሥራውን አልወደውም። ዱሮ በልጅነቴ አሰረኞች (ዛሬ ታራሚ ሃኮች ነው የሚባሉት) ሲሠሩት ያየሁት ሥራ ዐይነት ነው የሚመስለኝ። አንቢ እንዳልለው ደግሞ ሰውዬውን እፈራዋለሁ። ድንጋዩን በእጄ እንደ ያዝኩት እና አሳቤም አንደዚህ እየዋለለ እያለ ነቃሁ። ሰነቃ "ሕያዋን ድንጋዮች" የሚል አሳብ ውስጤን ሞልቶት ነው የነቃሁት። በእንደኛ ጴጥሮስ 2፥5 ላይ የማው ሃው አሳብ ነው። ደነገጥኩ።

ከመኝታዬ ተነሣሁና ስለ ሕልሙም፥ ስለ ዕለቱ እገልግሎታችንም ጥቂት ጸለይኩ። ከዚያም ተጣጠብኩና ለባብሼ ከፓስተር አሳየኸኝ ጋር ቁርስ አብረን ልንበላ በተቃጠርንበት ሰዓት ወደ ሆቴላችን ሬስቶራንት ሄድኩ። ፓስተር አሳየኸኝ ቀድሞኝ ነበረ። "ደኅና እደርክ ወይ? ተኛህ ወይ? ድካሙ ወጣልህ ወይ?" ከተባባልን በኋላ ቁርሳችንን እየበላን እያለን "እረ አባክህን እሁን ሲኒጋጋ እንድ ሕልም አየሁ" አልኩት። ሊሰማኝ ዝግጁ የሚሆንበትን ያህል ጊዜ ከሰጠሁት በኋላ ሕልሜን ነገርኩት።

በእንድ በኩል የሙሉ ጊዜ አገልግሎትን በተመለከተ ከዚህ በፊት ከእርሱ ጋር ብዙ ተጨዋውተን ስለምናውቅ ነው ሕልሜን ልነግረው ነጻነት ያገኘሁት። በሌላም በኩል ሕልሙ በጣም ስለ አስደነገጠኝ ይመስለኛል። በዚያን ጊዜ በቅርቤ የማገኘው ሌላ ማንም ሰው ቢሆን እንኳን ሳልነግረው አልቀርም ይሆ ናል ብዬ አስባለሁ። ፓስተር አሳየኸኝ በጥሞና ካዳመጠኝ በኋላ፥ "ግልጽኮ ነው፤ ጊዜ ወስደን በዚህ ጉዳይ ላይ መጸለይ አለብን" አለኝ።

ይህ ከሆነ ከሁለት ወራት በኋላ፥ በትከክል ለመናገር ቅዳሜ የካቲት 15 ቀን፥ በኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት የወንጌል ሥርጭት እና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተከላ ክፍል ለወንጌላውያን የተዘጋጀ የሥልጠና ፕሮግራም ነበረ። ፕሮግራሙን የሚያስተባብረው የክፍሉ ኃላፊ

ወንጌላዊ በለጠ ህብተ ጊዮርጊስ ሲሆን፥ ከአሰልጣኞቹ አንዱ የሆንኩት እኔ ደግሞ የዚሁ ከፍል የአማካሪ ቦርድ አባል ነኝ። ሠልጣኞቹ ወንጌላውያን ከተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች የመጡ ናቸው። ቁጥራቸውን አላስታውሰውም፤ ከሃምሳ አስከ ሰባ ይሆኑ ይሆናል። በሦስት ዙር ልናሠለጥናቸው ዕቅድ ከያዝንላቸው ወንጌላውያን መካከል ይሽ አንዱ ዙር ይመስለኛል።

እኔ ሥልጠና ከምሰጥባቸው ሁለት ክፍለ ጊዜያት በመጀመሪያው ላይ፥ አሁን በትከከል በማለስታውሰው ምክንያት፥ በእነዚህ ሠልጣኞች መካከል ሙሉ ጊዜውን ያልሰጠ ሰው ካለ እጁን እንዲያሳየኝ ጠየቅሁ። አንድ ሰው እጁን አወጣ። የመጀመሪያው ከፍለ ጊዜ አልቆ ለሻይ ስንወጣ፥ ለወንጌላውያን በተዘጋጀ የሥልጠና ፕሮግራም ላይ ሙሉ ጊዜውን ያልሰጠ ሰው የተገኘበትን ምክንያት ወንጌላዊ በለጠን ጠየቅሁት። ያ ሰው የመጣባት አጥቢያ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ገና አንደሌላት፥ ሆኖም ሥልጠናው አንዲቀርባቸው ስላልፈለጉ የአጥቢያዋ ሽማግሎች ከመካከላቸው አንዱን መርጠው እንደላኩ ነገረኝ።

ሁለተኛው ከፍለ ጊዜ አልቆ የመዝጊያ ጸሎት ሲደረግ ከወንጌላውያኑ መካከል በአንደኛው በኩል አንዲህ የሚል መልእክት መጣ፡-

> ... ብዙ ጊዜ ... በብዙ መንገድ ተናገርኩህ ... አልሰማኝ አልክ ... አንግዲህ እንዴት አድርጌ ብናገርህ ነው የሚገባህ? ... መልእክ ልላከልህ? ... ከዚህ በኋላ አልናገርህም ... ይህ የመጨረሻዬ ነው ... ::

ይህ መልእክት ወይ ከአኔ ወይም ከዚያ ብቸኛ ሽማግሌ የእንዳችን ሊሆን ነው የሚችለው። ቀደም ሲል ከማውቃቸው ብዙ ምክንያቶች የተነሣ ደግሞ ከብቸኛው ሽማግሌም ይልቅ የእኔ ሊሆን ነው የሚችለው። ሲያቀብጠኝ የጠየቅሁት ጥያቄ ዕድሉን የዚህን ያህል አጥብቦብኛል። ፕሮግራሙ ተጠናቅቆ ወደ ቤቴ ስሄድ ለወንጌላዊ በለጠ "ሊፍት" (ሌሎች "ራይድ" ይሉታል) ሰጠሁት። እየሄድን አያለን "ጋሽ በቄ ... አንዴት ነው? ... ዎርልድ ቪዥን ተመቸቶሃል ወይ?" አለኝ። ሊለኝ የፈለገውን ለመረዳት ጊዜ አልወሰደብኝም።

"ከቅድሙ መልእክት ተነሥተህ ነው አይደል ይህንን የምትጠይቀኝ?" ስል ጠየቅሁት። መልስ አስኪሰጠኝ ድረስ ግን አልጠበቅሁትም።

> "እውነቱን ለመናገር ሙሉ ጊዜዬን ያልሰጠሁት ዎርልድ ቪዥን ስለ ተመቸኝ አይደለም ... ጌታን በሙሉ ጊዜዬ ከማገልገል ይልቅ የሚመቸኝ

> ሌላ ምንም ነገር የለም ... ሙሉ ጊዜዬን ያልሰጠሁት የጌታን ጊዜ በትከከል ስለ አላወቅሁ ብቻ ነው ... ጌታን ልቀድመው ስለማልፈልግ ብቻ ነው ... እርሱ 'ቢቃህ' በሚለኝ በማናቸውም ጊዜ ዎርልድ ቪዥንን ለመልቀቅ ዝግጁ ነኝ ... ዛሬም እንኳን ቢሆን

አለኩት።

"እንደዚህ ከሆነስ ጊዜ ውሰድና፥ ከከተማም ወጣ በልና፥ ጸልይ" አለኝ።

"ጊዜ የለኝም ... በቢሮ ሥራም፥ በአገልግሎትም፥ ተወጣጥሬአለሁ" አልኩት።

"እንዲያው ሦስት ቀንም እንኳን ቢሆን ጊዜ ሰጥተህ ለዚህ ነገር አልባት ማድረግ አለብህ"

> "ሦስት ቀን ቀርቶ አንድ ቀንም የለኝም ... የዚህን ያህል ጊዜ ካልሰጠሁት በስተ ቀር ጌታ እኔን ለመናገር ይቸግረዋል ብዬም አላስብም ... ባለሁበት ሁኔታ ውስጥ ሊመጣና ሊናገረኝ ይችላል ብዬ አምናለሁ"

አለኩት። ለእርሱ እንደዚህ ልበለው እንጂ በውስጤ ግን በጣም አዝኖለሁ። "ከዚህ በኋላ አልናገርህም ... ይህ የመጨረሻዬ ነው" የተባለ ሰው ሊያዝንበት በሚችለው ዐይነት ኅዘን አዝ ኖለሁ። ተስፋ መቁረጥም በብርቱ ተፈታትኖኛል በሚቀጥሉት ቀናት ሁሉ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ አያለሁ ለአገልግሎት ወደ ጅማ የምሄድበት መጋቢት 25 ቦን እየተቃረበ መጣ። ለዚያ አገልግሎት መጸለይ ነበረብኝ። እና ከዚያ ጋር አያይዤ ስለ አራሴም ጸለይኩ።

> "ጌታ ሆይ! 'አልናገርህም' ያልከው ሰው አንዴት ያገለግልሃል? ... የዚህን ያህል እስቸግሬሃለሁ ማለት ነው? ... ምናልባት የሚናገሩኝ ሰዎች ነገሬን የሚያውቁ ስለ ሆኑ ... ከሚያውቁት ነገሬ እየተነሡ የሚናገሩ ስለሚመስለኝ ይሆን እንደዚህ ያስቸገርኩህ? ... ነገሬን በማያውቅ ሰው በኩል ብትናገረኝ ለመስማትና ለመታዘዝ ይቀልለኝ ይሆን?"

ጅማ ነገሬን የሚያውቅ ሰው የለም። ከዐሥራ ዘጠኝ ዓመታት በፊት ገነት እና እኔ ብራያን እና ዶሪስ ፋርገርን ለማየት ጅማ ሄደን በነበረ ጊዜ፥ አዚያ ያሉ ወገኖች ባዘጋጁልን የጸሎት እና የአራት ምሽት ላይ ለገነት የተነበየላት ለማ የሚባል ነቢይ በዚያ እንደሚኖር ዐውቃለሁ። ስለ ገነት የተናገረው ትንቢትም

ትከከል አንደ ነበረ፥ ከብዙ ዓመታት በኋላ ገነት እራሷ በሆኑ በሆኑ ኢጋጣሚ ዎች ስታነሣው ሰምቻታለሁ።

ለማ ከመስከረም 03 እስከ 08 ቀን 1969 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብ ያተ ክርስቲያናት መሪዎች በናዝሬት ባይብል አካዳሚይ ባደረጉት የመጀመሪያ ኮንፈረንስ ላይ የተናገረው የትንቢት ቃል በጉባዔው መካከል አስነሥቶት ስለ ነበረው አሰጥ-አገባ በጊዜው ሰምቻለሁ። በዚያው ዓመት በወልመራ በተደረገ የወንጌላውያን ስብሰባ ላይም አግዚአብሔር የኮሚዩኒዝምን መንፈስ በኢትዮ ጵያ ላይ እንደሚሰብረው የተናገረውን ትንቢት በካሴት ተቀርጾ አግኝቼ ሰምቼ ዋለሁ። ከእነዚህ የትንቢት መልእክቶቹ የተነሣም በወቅቱ በጴንጤቆስጤስ ውያኑ አካባቢ በአገር አቀፍ ደረጃ ስሙ ተነሥቶ ነበር። "በእርሱም በኩል ብትናገረኝ አሰማሃለሁ" ስል በጸሎቴ ላይ አከልኩበት።

ዕሑድ መጋቢት 28 ቀን 1989 ዓ.ም. የጅማው ኮንፈረንስ የመጨረሻ ቀን ነው። ከምሣ በኋላ ባለው ፕሮግራም ላይ እገልግዬ ገና እንደ ተቀመጥሁ፥ አንድ ሰው ቀጥ ብሎ እኔ ወደ አለሁበት ወደ መድረኩ መጣና እንደሚፈልገኝ ነገረኝ። ተነሣሁና አብረውኝ ከተቀመጡት አገልጋዮች - ከፓስተር ኢቲቻ ነጋሣ እና ከወንጌላዊ (በኋላ መጋቢ) ታሪኩ ቴዎድሮስ - ትንሽ ዘወር ብለን ተነጋገርን።

"እንተ ሥራ እየሠራህ ነው አንዴ የምታገለግለው?" አለኝ።

"ምን ማለትህ ነው?" ስል ጠየቅሁት።

"አይ፥ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ነህ ወይስ የትርፍ ጊዜ? ማለቴ ነው" አለኝ።

"የትርፍ ጊዜ አገልጋይ ነኝ" አልኩት።

> አዚህ መድረክ ላይ ካየሁህ ከዓርብ ዕለት ጀምሮ 'ሞፊርህንና ቀንበርህን ጣልና ተከተለኝ በለው' ይለኛል፤ እኔ ደግሞ እንተ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ስለ መሰልከኝ መልእክቱ ለአንተ ሊሆን አይችልም በማለት ስከራከር ሰነበትኩ ... እውነኮ ቢብስብኝ ጊዜ ነው ለምን ጠይቄው ከአራሱ አፍ አልሰማም? ብዬ የመጣሁት ... አንግዲያውማ ስማ! '... እስከ አሁን አፍህን ማር ስለ ቀባሁልህ ነገር ጣፍጦልሃል ... እንቢ ብትለኝ ግን ከአሁን በኋላ ይመርብሃል' ይልሃል

አለኝ። ለማ ነበር። አርሱ ከዚህ በፊት መገናኘታችንን ፈጽሞ አያስታውሰም። እኔ ደግሞ ፊቱን ፈጽሞ አረስቼዋለሁ። አዚያው አብሬው እንደ ቆምኩ "እነዘ.ማ አልለውም፤ ደስ አያለኝ 'እሺ' አለዋለሁ" አልኩት። ማታ ባረፍንበት ሆቴል መኝታ ከፍሌ ውስጥ ሆኜ የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤዬን እርቅቄ እያረትኩ። ሰኞ ወደ አዲስ አበባ ተመልሼ፥ ማከሰኞ በጠዋት ቃቄ በኮምፒዩተር ተየበችልኝ እና አስገባሁት። መልእክቱ ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም ባይሆን፥ ሙሳኔም ትከከል ቢሆን ወይም ባይሆን፥ አሁን በእውነት ግድ አልነበረኝም።

ጥሪው እየጠራ መጣ

ሙሉ ጊዜዬን ከለጠሁ ጊዜ ጀምሮ በውስጤ ሦስት የጸሎት ጥያቄዎች ነበሩ። አንደኛው የአገልግሎት መስመሬን የሚመለከት ነው። ወንጌል መስበክ ደስ ይለኛል፤ ፍሬም አይበታለሁ። ማስተማርም ደስ ይለኛል፤ ፍሬም አይበታ ለሁ። የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት እና ጎብረቶች አንዴ በዚህኛው፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ በዚያኛው አንዳገለግላቸው ይጠይቁኛል። ጌታ ግን የጠራኝ በየትኛው አንዳገለግለው ነው? ቤተ ክርስቲያንስ በምትለየኝ ጊዜ ለየትኛው አገልግሎት ብላ ነው የምትለየኝ? እኔስ ከአንግዲህ በኋላ የበለጠ መትጋት ያለብኝ በየት ኛው የአገልግሎት መስመር ነው? በአጭሩ ወንጌላዊ ነኝ? ወይስ መጋቢ? ወይስ አስተማሪ? ይህንን ጉዳይ የጸሎት ርእስ አድርጌ ለብዙ ወገኖችም ሰጥቻቸዋለሁ።

ሁለተኛው ጥያቄዬ ከቤተ ክርስቲያን አሠራር ጋር የተያያዘ ነው። አባል እና አገልጋይ የሆንኩባት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አለችኝ። ሌሎችንም ብዙ ቤተ አምነቶች እና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ዐውቃለሁ። በሁሉም ዘንድ የተከ ፈተ የአገልግሎት በር አለኝ። በዚህ ረገድ ከፍተኛውን አስተዋጽዖ በሕይወቴ ያደረገው ለዐሥራ ሁለት ዓመታት ያህል ያገለገልኩበት ዎርልድ ቪዥን ነው። በአንዲት አጥቢያ ቢተ ክርስቲያን አባልነቴ እና በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት አገልጋይነቴ መቀጠል በጣም አፈልጋለሁ።

ባለው አሠራር መሠረት ግን የእኔም ሆነች የሌሎቹ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አንድ አገልጋያቸውን ለተጠራለት አገልግሎት ሲለዩ "የእኔ" ብለው አንጂ፥ "የሁሉም" ብለው አይደለም። ሊሆንም አይችልም። አገልጋዩ ከራሱ አጥቢያ ውጭ ማገልገል ቢኖርበት፥ ያ በፈቃድ እና በስምምነት ነው ሊሆን የሚችለው። ፈቃድ እና ስምምነትም የሚገኘው አንደ ቤተ አምነቱ መመሪያ

ነው። የቤተ እምነቱም መመሪያ በአብዛኛው በጊዜው እና በቦታው ላይ ባሉት ሰዎች ማንነት ነው የሚወሰነው። ሙሉ ጊዜ መሰጠቴ እስከ ዛሬ የነበረኝን ነጻነት ያለ ጥርጥር ያጠብበዋል። እና እንዴት ነው የማደርገው?

ሦስተኛው የጸሎት ጥያቄዬ ከቀደሙት ከሁለቱ ጥያቄዎቼ የሚነሣ ነው። ለሁለቱ ጥያቄዎቼ ግልጽ መልስ ሳላገኝ፥ የቤተ ክርስቲያኔ መሪዎች ቢጠሩኝና ወንጌላዊ ወይም መጋቢ ወይም አሰተማሪ ልናደርግህ እሰበናል ቢሉኝ ምን እመልሰላቸዋለሁ? ወይም እኔኑ እራሴን ምን እንድናደርግህ ትፈልጋለህ? ብለው ቢጠይቁኝ ምን እላቸዋለሁ? እነርሱ የሚሉኝን እሺ ብዬ ብቀበላቸው እና እነርሱ የሚሉኝ ግን ጌታ የሚለኝ ያልሆነ እንደ ሆነስ? እነርሱ የሚሉኝን እንቢ ብላቸውስ? በሁሉም በኩል፥ ማለቴ እሺም እንቢም በማለቱ በኩል፥ ነገሩን ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም።

ከብዙ ማውጣት እና ማውረድ በኋላ፥ መፍትሔ ሆኖ ያገኘሁት ነገር ለእኔም ለእነርሱም መጸለይ ብቻ ነው። እና በእውነት ጸለይኩ።

> "ጌታ ሆይ! በእነዚህ ጥያቄዎቼ ላይ አንተ ለእኔም ለመሪዎቼም ግልጽ የሆነ መልስ ከመስጠትህ በፊት፥ መሪዎቼ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊያነጋግሩኝ እንዳይጠሩኝ ከልከላቸው"

ብዬ ጸለይኩ። በእውነትም አልጠሩኝም። የጌታ መልስ ግን፥ ከላይ "እታደርገውም!" ባልኩት ንውሰ ርእለ ሥር ልናገረው እንደ ጀመርኩት፥ ከመጋቢት 19 ቀን 1991 ዓ.ም. ጀምሮ በተከታታይ መምጣት ጀመረ።

ቅዳሜ ነሐሴ 01 ቀን 1991 ዓ.ም። ካለፈው ረቡዕ ከሰዓት በኋላ ጀምሮ ናዝሬት ነኝ። የመጣሁት ለአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መዘምራን እና የመድረክ አገልጋዮች በተዘጋጀ የሥልጠና ፕሮግራም ላይ ከእሠ ልጣኞቹ አንዱ ሆኜ ነው። የታደምነው በድምሩ 600 ሰዎች ሰንሆን፥ የተገኘነው ግን 525 ገደማ ነበርን። ያረፍነውም፥ ሥልጠናው የሚካሄደውም፥ "በናዝሬት ሕፃናት ማዕከል እና ልማት ድርጅት" (ናሕማልድ) ግቢ ውስጥ ነው። ወንድም ደበበ ለማ (አሁን መጋቢ)፥ ወንድም መሰፍን ለማ እና መጋቢ ግርማ ቦጋለ ሦስታችን የምናድረው አንድ ከፍል ውስጥ እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል። ዘንግቼ ነው እንጂ፥ እንድ ሁለት ሌሎች አገልጋዮችም አብረውን የነበሩ ይመስለኛል። ሰንጫወት፥ ምለከርነት ሰንለዋወጥ እና ሰንጸልይ እምሽተን፥ የተኛነው ከሌሊቱ 7:30 በኋላ ነበር።

ጠዋት ልክ 11:30 ላይ ከእንቅልፌ ለነቃ ከሕልም ነው የነቃሁት። እጅግ በጣም ትልቅ ሊጣ ፈረሰ ላይ ተቀምጫለሁ። የፈረሱ መልክ መጋላ ወይም ጠይም ነው። ፈረሱ ላይ መቼ እና የት እንደ ወጣሁ ዐላውቅም። እንዴት ልወጣ እና ልሰመጥበት እንደ ቻልኩም አላውቅም። ምክንያቱም ፈረሱ ከትልቅነቱና ከሰራባነቱ የተነሣ እንዳች ከፍ ያለ ነገር ረግጬ ወይም ሰው ተሸክሞኝ ካልሆነ በስተቀር በራሴ ልወጣው እልችልምና ነው። የተቀመጥኩት ደግሞ ሰው በሚ ሰመጥበት የአካሉ ከፍል ላይ ሳይሆን፥ ከጭራው ትንሽ ከፍ ብሎ ከሁለቱ የኋላ እግሮቹ መጋጠሚያ፥ ከደንደሱ ጫፍ ላይ ነው። እቀማመጤ በፍጹም ምቾት አልሰጠኝም።

እነድ ዐሥር ሜትር ያህል ርቆ ከፊቴ ሌላ ፈረስ አለ። ሁለቱ ፈረሶች በመል ከም፥ በቁመትም፥ በሌጣነትም እንድ ዐይነት ናቸው። ልክ እኔ በዚህኛው ፈረስ ላይ በተቀመጥኩት ዐይነት፥ ከፊቴ ባለው ፈረስ ላይ ፓስተር መርዕድ ሥዩምጦአል። ቡላ ካፖርት ለብሷል። ከየት እንደምንመጣ፥ ወዴትስ እንደ ምነሄድ፥ አላውቅም። አለከ አሁን እንዴት እየተጓዝን እዚህ እንደ ደረሰንም፥ ማለቴ ፈረሶቹ እየጋለቡ ይሁን ወይም እንዲያው ዝም ብለው እየሄዱ፥ ደንገላሳ እየረገጡ ይሁን ወይም አሁን እያደረጉ እንዳሉት ሰምሶማ እየመቱ፥ አላውቅም።

የሚጨበጥም ሆነ የሚረገጥ እንዳች ነገር በላያቸው ለለሌለ፥ ፓስተር መርዕድ እና እኔ በእነዚህ ፈረሶች ላይ ለማድረግ የምንችለው ምንም ዐይነት ቁጥጥር የለም። ጋማቸውን እንኳን ለመያዝ ብንፈልግ አንደርለበትም። ጊዜው እኔ ባያግሁበት ገጠር "ከበት የሚገባበት" የምንለው ዐይነት ሰዓት ነው - ከቀኑ 11:30 ሰዓት ገደማ በኋላ። እየተጓዝን ያለነው ደግሞ በመንገድ ላይ አይደለም። ከበት የሚውልበት የግጦሽ ወይም ሁለት ሦስት ዓመት ጦም ያደረ ማሳ በሚመስል መሬት ላይ ነው። መሬቱ ከፊታችን የበለጠ ወጣ ገባ እና ገደላ ገደልማ እየሆነ የሚሄድ ይመስለኛል። ፈረሶቹ ፍጥነት እየጨመሩ ናቸው። የአግራቸው አጣጣል "ግራ፥ ቀኝ" እየተባሉ በሰልፍ እንደሚጓዙ ዐይነት በሥርዓት ነበር።

እጅግ በመጠኑ ፈረሰ ተቀምጬ ባውቅም፥ ሊጣ ፈረሰ ግን ተቀምጬ የማውቅ አይመስለኝም። መጋለብማ ሞከሬ አላውቅም ብል ይሻለኛል። እና እነዚህ ፈረሶች ቢሸመጥጡ እንዴት እንቆጣጠራቸዋለን? ባልሆነ ወይም በማይመች

መንገድ ቢሸመጥጡስ ወደ ትከከለኛው መንገድ እንዴት እንመልሳቸዋለን? ከላያቸው ብንወድቅ ዐጥንታችንስ ከየት መጥቶ ይለቀማል? በጣም አፈራለሁ። ወደ ፓሰተር መርዕድ በጩኸት አጣራ አና፥ "ኧረ እነዚህን ፈረሶች 'አንድ' እንበላቸው ... በኋላ የጣሉን እንደ ሆነ አጥንታችንም አይለቀምም ..." አለዋለሁ። በመካከላችን ያለው አርቀት መደማመጥ የሚከለከለንን ያህል አይደለም፤ ሆኖም አይሰማኝም። ከበስተ ኋላው ሌላ ሰው አንዳለም የሚያውቅ አይመሰለኝም።

ፈረሶቹ ፍጥነታቸውን በመጨመር ላይ ናቸው። መጋለብ ከመጀመራቸው በፊት አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ። ፈረሴ ፍጥነት በጨመረ ቁጥር፥ መውረድና በሕይወት መትረፍ የማይቻል ነገር እየሆነ ነው የሚመጣው። ሁለት ሦስት ጊዜ በጩኸት ወደ ፓሰተር መርዕድ ተጣራሁ። እርሱ ግን፥ አንዴት አንደ ሆነ አንጃ፥ ጨኸቴን በጭራሽ አይሰማም። ወደ ኋላው መለስ አንኳን አይልም። ቀስ አልኩ አና በፈረሱ ጭራ ላይ የኋሊት ሸ - ተ - ተ - ተ - ት ብዬ ከመሬቱ ላይ ዱብ አልኩ፤ ወደቅሁ። ፈረሱ ቆመ እና መለስ ብሎ እየኝ፤ የሣቀም መሰለኝ - የለው በሚመሰል ሣቅ። አኔም ከወደቅሁበት እየተነሣሁ እና ልብሶቼን እያራገፍኩ "ጣልከኝ አይደለም?" አልኩት። በአርሱ ለማሳበብ ብዬ አንጂ፥ አራሴ ነኝ የወደቅሁት።

አንደዚህ ሕልም ለፍቺ ያስቸገረ ሌላ ሕልም አጋጥሞኝ አያውቅም ማለት አችላለሁ። በተለያየ ጎኑ አያገላበጥኩ ልፈታው እና ላስፈታው ሞከሬአለሁ። ፈረሶቹ ምንድናቸው? አንደዚያ አሣር የሚያህሉ ፈረሶችስ? ሌጦች ፈረሶችስ? ልጓም የሌላቸው ፈረሶችስ? በፈረሶቹ ላይ በተቀመጥንበት የአካላቸው ከፍል መቀመጣችንስ? ጊዜው አየመሸ እና መንገዳችንም ገደላ ገደልማ አየሆነ መሄዱስ? በመካከላችን የነበረው አርቀት የዚያን ያህል አጭር ሆኖ አያለ መነጋገር አለመቻላችንስ? አኔ ከፈረሱ ላይ በዚያ ዐይነት ተንሸራትቼ መውረዴስ? ፓሰተር መርዕድ ዝም ብሎ ወደ ፊት መቀጠሉስ? ወዘተርፈ ... ወዘተርፈ ... ::

ወደ ትርጉሞቹ ውሰጥ አልገባም። ብቻ ቁ - ር - ጥ የአርሱን በሚመስል ፈረስ ላይ ተቀምጬ ከኋላው መከተሌ፥ አገልግሎቴ አንደ አገልግሎቱ ሳይሆን አይቀርም ማለት ሊሆን አንደሚችል ተደርጎ ተተርጉሞልኛል - በራሴም፥ በሌሎችም።

ሰኞ፡ መሰከረም 23 ቀን 1992 ዓ.ም። በሕልሜ አንድ ትልቅ ሜዳ ላይ ቆሜአለሁ። የሰው መልከ ለመለየት በማይቻልበት ርቀት ላይ ብዙ ሴቶች ከፊት ለፊቴ ቆመዋል። ሁሉም የአገር ልብሰ፥ ማለትም ነጭ ቀሚስ አና ነጠላ የለበሱ ሲሆን፥ ሁሉም አራሳቸውን ተከናንበዋል። አነርሱም ወደ አኔ፥ አኔም ወደ አነርሱ ነው የምናየው። አንደዚህ አሩቅ ለሩቅ አየተያየን አያለን፥ አንዲት ሴት ከመካከላቸው ትወጣና በሩጫ ወደ አኔ ትመጣለች። መጀመሪያ ላይ ሣያኔቷ አልተለየልኝም። አየቀረበች ስትመጣ ግን ሣራ ባዲ መሆኗን ዐወቅሁ።

አራሯጥዋ እጇቷን ወደ ፊት ዘርግታ ነው። ልትይዘኝ ነው የምትፈልገው። በዘህ ጊዜ አኔም ልያዝላት ባለመፈለግ መሮጥ እጀምራለሁ። ከአኔ ይልቅ አርሷ በፍጥነት አና በቁርጠኛነትም ነበር የምትሮጠው። ልትደርስብኝ እና ልትይዘኝ ስትል አጥፍ አልባታለሁ። ሦስት አራት ጊዜ እንደዚህ አጥፍ አያልኩ ስትይዘኝ አመለጥኳት። አየሮጥኩ አያለሁ ግን ማለብ እጀምራለሁ -

> ሣራ የማውቃት አኑት ናት ... የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባሎችም ነን ... ልትይዘኝ የምትፈልገው ለከፉ ሊሆን አይችልም ... ደግሞ የልጆች አናት ናት ... ለምንድነው አንደዚህ የማደከማት? ... ሰምን አልያዝላትም?

ነቃሁ። በግሌ ለጥቂት ቀናት ከጸለይኩበት በኋላ፥ ይህንን ሕልም ለአንድ የምቀርበው ወንድም ነገርኩት። "ከአጎቶች በኩል የሚመጣብህ ፈተና ይኖር ይሆናልና ተጠንቀቅ" አለኝ። አኔም -

> አንዴት? ሣራኮ አኑቴ ማለት ናት ... በዎርልድ ቪዥን ለብዙ ዓመታት አብረን ሠርተናል ... ልጃገረድ በነበረች ጊዜ አግዚአብሔር ትዳር አንዲሰጣት ብዙ ጸልዬላታለሁ ... አርሷም አፍኛ በመጣላት ጊዜ አግዚአ ብሔርን አንዳመሰግን በቁም ነገር ነግራኛለች ... ባሰቤቷን ዘገዬን፥ ትልቁን ልጇን ዮዳሄን ዐውቃቸዋለሁ ...

አለኩት። አርሱም "አይ ... ሣራ አራሰዋ ላትሆን ትችላለች አኮ ... የምትወክለው ለሎች ሴቶችን ሊሆን ይችላል ..." አለኝ። ትርጉሙ ብዙም አልተዋጠልኝም።

ኀሙት ቀናት ቆይቼ ደግሞ ለአኑት ሙሉ ዘለቀ ደወልኩላትና ይህንኑ ሕልም ነገርኳት። ልከ ነግሬአት አንደ ጨረስኩ፥ "ግልጽኮ ነው" አለችኝ።

"ምኑ ነው ግልጹ?" አልኳት።

"ሣራኮ አናትህ ናት" አለችኝ።

"ምን?" አልኳት በመገረም።

"ቃሉ አይልም አንዴ?" አለችኝ። አብርሃም "አባታችን" ከሆነ፥ ሣራ ደግሞ "እናታችን" መሆኗ ግልጽ ነው። በጊዜው ግን የታወሰኝ በገላትያ 4፥21-31 ላይ ስለ ሁለቱ የአብርሃም ልጆች እና ስለ ሁለቱ እናቶቻቸው የተጻፈው ነው "... የጨዋዪቱ ልጆች ነን አንጂ የባሪያዪቱ አይደሰንም" የሚለው።

"አዎ ይላል ... እና ... ?" ስል የበለጠ ማብራሪያ በሚፈልግ ድምፀት ለሙሉ መለስኩላት።

> እናማ እነዚያ ሴቶች ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ... ሁሉም ይፈል ጉሃል ... ሣራ ግን እናትህ ናት ... በአንተ ላይ የተለየ መብት አላት ... ለዚህ ነው ከመካከላቸው ተለይታ በመውጣት ያባረረችህ ... አንተ ግን እስከ ዛሬ ድረስ አጥፍ አጥፍ እያልከ አልያዝላት ብለህ አስቸግረሃታል ... አሁን ግን በቃ፤ ልትያዝላት ነው ...

አለችኝ።

በመደነቅ አፌን ከፍቼ ቀረሁ። የሕልሜን ትከከለኛ ትርጉም እንደ አገኘሁ ዐወቅሁ። አቤት አግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው የተለያየ ጸጋ! አቤት ሰዎች በጎብረት ሲሆኑ እና በተሰጣቸው ጸጋ አንዳቸው ሌላቸውን ሲያገለግሉ ያለው በረከት! ጌታን አጅግ አድርጌ አመሰገንኩት።

ይህ ከሆነ ከሁለት ሳምንታት በኋላ፥ ማለትም ጥቅምት 07 ቀን ሰኞ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የፋይናንስ ከፍል ሄድኩ። የሄድኩት የፋይናንስ ሥራ አስኪያጇ እኅት ፍሬ ሕይወት ማሞ (ሁላችንም ፍርዬ ነው የምንላት) ባሰፈው ቅዳሜ የሆነ ስብሰባ ላይ አግኝታኝ "እፈልግሃለሁ፥ ሰኞ ቢሮዬ አንድትመጣ" ብላኝ ሰለ ነበረ ነው። ፍርዬ ከመዛግብቷ ውስጥ የ3,000 ብር ቼክ አወጣችና "በል አዚህ ላይ ፈርምልኝና ይህንን ውሰድ" አሰችኝ።

"ምንድነው አሱ?" አልኳት።

"አንብበው" አሰችኝና ከቼኩ ጋር አባሪ የተደረገውን ሰነድ አሳየችኝ። "የ1991 ዓ.ም. የትራንስፖርት አበል በወር ብር 250.00 ሂሳብ" ይላል። ቀጠሰችናም "የመስከረም ወር 1992 ዓም. የትራንስፖርት አበል" የሚል ሌላ ሰነድ አወጣችና "አዚህም ላይ ፈርም ... አበሉ ከመስከረም ወር ጀምሮ 350.00 ብር

ሆኗል ... ከአንግዲህ በኋላ በየወሩ አየመጣህ በካሽ መውሰድ አለብህ" ብላ 350.00 ብር ከገንዘብ ከፋይዋ እንድቀበል ነገረችኝ።

"እንዴ ... ሳያነጋግሩኝ? ..." አልኳት።

"እባክህን ዝም በል እና ውሰድ" አለችኝ። ወሰድኩና ከቢሮዋ ወጥቼ ሄድኩ። ሚታ የመሪዎቹ ስብስብ ዋና ጸሐፊ ለነበረው ሰወንድም ዮሴፍ ኢማና ደወልኩለትና

> "የደወልኩልህ ስለ ተሰጠኝ የትራንስፖርት አበል ለማመስገን ነው ... ሆኖም ከተነጋገርን በኋላ ቢሆን አይሻልም ነበር ወይ?"

አለኩት። እርሱም መልሶ -

> "እኛም የወሰንነው ካነጋገርንህ በኋላ እንዲሰጥህ ነበር ... ይህንኑም ለፍርዬ ነግረናታል ... አልተግባባንም ነበር ማለት ነው ... ሰሞኑን እናነጋግርሃለን" አለኝ።

እንዳለኝም፥ የመሪዎች ስብስብ ሁለት ተወካዮች ሰሞኑን አነጋገሩኝ። እና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሆንኩ - በሰነድ ላይ ከመስከረም ወር 1991፥ በተግባር ግን ከጥቅምት 08 ቀን 1992 ዓ.ም. ጀምሮ።

ኑሮነበርግ (ጀርመን)፤ ሰኞ መጋቢት 25 ቀን 1992 ዓ.ም። ከጥር 21 ቀን ጀምሮ ጀርመን አገር ነኝ። ሰሦስት ወራት በአገሩ ዋና ዋና ከተሞች ባሉት የኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወርኩ አንዳስተምር በጎብረ ታቸው ተጋብዤ ነው የመጣሁት። በመካከሉ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ከየካቲት 23 አስከ 26 ድረስ በአዲስ አበባ አስታ ድዬም በምታደርገው ሁለተኛ የጀማ ስብከተ ወንጌል ላይ ለማገልገል፥ ለአንድ ሳምንት ኢትዮጵያ ደርሼ ተመልሻለሁ። የደርሶ መልስ የትራንስፖርት ወጭዬን የሸፈነው ወንድም ካሣዬ ኃይሌ ነበር። ከዕሑዱ አገልግሎት መልስ ማታ፥ ወደ ሆቴሉ ተመልሼ የሪከ ጆይነርን THE PROPHETIC MINISTRY[2] አያነበብኩ አመሸሁ። በጀርመን አገር አያስተማርኩት እና አሁን እያነበብኩትም ካለሁት ነገር ተነሥቼ ደግሞ ብዙ አሰብኩ -

> ... ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያለኝ አመለካከት በጣም አየጠነከረ አየ መጣ ነው ... በኢትዮጵያም ሆነ አሁን በጀርመን አየተዘዋወርኩ ስለ ቤተ

ሰኞ ሐምሌ 03 ቀን 1992 ዓ.ም። እኅት ሙሉ እመቤት ከበደ (በኋላ ሠንጊላዊት) በቤትዋ የጸሎት ሰብሰባ አዘጋጅታ ጋበዘችኝ። በጸሎቱ ሰብሰባ ላይ እኅት ውዴ ገ/ማርያም (በኋላ ወንጌላዊት)፥ እኅት ገነት ሦሪ (በኋላ ፓስተር)፥ ባለቤትዋ ወንድም ኤልያስ እንዳለ (በኋላ ፓስተር)፥ ወንድም በቀስ መንገሻ (ዘኍላ ወንጌላዊ)፥ ሙሉ እራስዋ እና እኔ ነበርን። እየጸለይን ሳለ፥ ገነት እንዲህ የሚል መልእክት አመጣች -

> ... አዲስ ነገር በፊትህ አለ ... ብዙ ጊዜ አብሮህ ስኖረው ችግር ... ዐንገትህን ላስደፋህ ነገር ... እኔ እራሴ መቋጫ አደርጋለሁ ... አንተ ዝም ብለ ሃል ... ለሚጠይቁህ፥ ለሚከሰሱህ፥ መልስ አልነበረህም ... በእውነትም መልስ አልነበረውም ... መልስ የነበረው በእኔ ዘንድ ብቻ ነው ... በዚህ ዓመት መቋጫ አደርጋለሁ ... ይህ የምታይበት ዓመት ነው ...

ገነት መልእክቱን "ለጋሽ በቄ" ብላ ነው መናገር የጀመረችው። ሆኖም በዚያ የነበረነው ሁሉት በቀሎች ስለ ሆንን፥ የተንበረከከነውም ጎን ስጎን ስለ ነበረ፥ ገነትም መልእክቱን ስትናገር በዚያኛው በቀለ እና በእኔ መካከል፥ ከበሰተ ኋላችን ቆማ ስለ ነበረ፥ መልእክቱ ለማንኛችን እንደ ሆነ እኔ እርግጠኛ አልነበር ነኩም። ስለዚህም ጸሎቱን እንደ ጨረስን ፊት ለፊት ጠየቅኋት። ወንጌላዊ ዙሪለ፥ "እይ፥ ይኸማ ላንተ ነው እንጂ ለእኔ አይደለም" አለኝ። ገነትም ክእርሱ ሥዘል እደረገች እና፥ "ጋሽ በቄ የምለው እንተን ነው፥ እርሱን በስሙ ብቻ ነው የምጠራው" አስችኝ። ውዴ ደግሞ "ጋሽ በቄን ልጠራው ስል አፌ ላይ 'ፓስተር' የሚል ይመጣብኛል፤ ፓስተር ልትሆን ነው እንዴ?" ስትል ጠየቀችኝ።

ምን የሚሉት ፓስተር?

ውዴ "በዕውቀት ቃል" እና "በፈውስ ስጦታ" በኢትዮጵያ ሁሉ ለማስተ የሚቻል ያህል የታወቀች እገልጋይ ነች። ለብዙ ዓመታት፥ በየለምንቱ ዓርብ በትተራው ጸሎት ቤታችን በእነዚህ "ስጦታዎቿ" በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተጠቃሚዎች ሆነዋል። ገነትም "ትንቢት በመናገር" ስጦታ እንደምታገልግል የሚናውቅ ሰዎች አሉን። የገነት መልእክት የመጣልኝ በጸሎት ውስጥ ነው። ውዴ ግን ዝም ብላ በጨዋታ መካከል ነው የተናገረችው።

እኔ ደግሞ መልእክት በዚህም ዐይነት ሊመጣ እንደሚችል ዐውቃለሁ። ክዚህ በፊት ያየኋቸውና የሰማኋቸው ነገሮችም አሉ። እንዳንዶቹን በዚሁ ምዕራፍ

ክርስቲያን የማስተምረውን ይህንን ትምህርት እኔ አራሴም ልኖረው አችል እንደ ሆነ እርግጠኛ አይደለሁም ... ታዲያ እነዚህን ስደተኞች ኢትዮጵያውያን ምን እድርጉ ነው የምላቸው? ... በዚህ መጽሐፉ ውስጥ ሪክ ጆይነር ስለ ትንቢት አገልግሎት እና ስለ ቤተ ክርስቲያን የጻፈው ነገር ሲበዛ ጤናማ ነው ... ግን እርሱ እራሱ የጻፈውን እየኖረው ይሆን ወይ? ... ሚኒስትሪይ እንዳለው ዐውቃለሁ ... እጥቢያ ቤተ ክርስቲያንስ አለው ይሆን ወይ? ... ክእጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑሰ ጋር ያለው ግንኙነት ጤናማ ይሆን ወይ? ...

ቤተ ክርስቲያን ሕያው የሆነች አካል (ORGANISM) ናት። ብልቶችዋም ሁሉ ሕያዋን ናቸው። ምንም እንኳን ዛሬ ጎልቶ የሚታየው መልኳ እንድም በቅርብ ሰንሆን የምንሰመው እና በሩቅ ሰንሆን የምንሳሰመው ሕንጻዊ፥ እንድም ደግሞ እካላዊነት የማይታይበት ተቅዋማዊ (INSTITUTIONAL) ብቻ ቢሆንም፥ ይህ ሰለ እጥቢያዋም (LOCAL) ሆነ ሰለ ጽርኅ አርያማዊዋ (UNIVERSAL) ቤተ ክርስቲያን እውነት ነው ... ታዲያ ይኸ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን እየወጣ ሚኒስትሪይ የሚጀምረው እገልጋይ ማንን ለማገልገል ብሎ ነው? ... በአካሏ ውስጥ ሳይሆኑ፥ በብልቶቿም ሁሉ ሳይገለገሉ፥ እንዴት ተደርጎ ነው የቤተ ክርስቲያን እገልጋይ የሚኮነው? ... ክብልቶቹ የሚፈለገው ጥሪታቸው ብቻ መሆኑ ነው? ... ነገ የእኔሰ እገልግሎት ምን መልክ ይይዝ ይሆን?"

ሲያላሰቡኝ በነበሩት በእነዚህ እና በተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ጸልዬ ተኛሁ። በሕልሜ ከእንዲት ልጅ እግር ጠይም ሴት ጋር ቆሜአለሁ። ስለ ምን እየተናገረችኝ እንዳለች አላውቅም፤ ብቻ ወላጅ እናቴ እንደ ሆነች ጭምር ነው የምትነግረኝ። እርስዋ ስራስዋ አርባም የምትደፍን እትመስልም። "መቼ ነው የወለድሽኝ? እማሆይ (እናቴ) የወለደችው አሰካለን (ታናሽ እኅቴ) እና ክእርሷ በኋላ ያሉትን (ካሣን፥ ነጋሽን እና አዘነጋሽን) ነው ማለት ነው?" አላታስሁ። መልሰ እትስጠኝም። በውሰጤ "ሰሚን እንኳን የማላውቀው ሴት እንዴት እናቴ ልትሆን ትችላለች?" እያልኩ አገረማስሁ። ወዲያውም "እሺ፥ ለመሆኑ ሰምሽ ማነው?" አላታስሁ። "ምልዕተ" ትለኛስች። ነቃሁ። ትርጉሙን ስመረ ዳት ምንም አልተቸገርኩም። "ምልዕተ" ማለት በግዕዙ "ሙሉ" ማለት ነው። ሙሉ ደግሞ ሙሉ ወንጌል አንጂ ሌላ ማን ልትሆን ትችላለች?

ዘይም ተከታዮች ማለት ነው። እማኞች ደቀ መዛሙርት የሚደረጉትም በስብከት እና በማስተማር አገልግሎት ብቻ አይደለም። በፈታቸው የሚሄዱ፥ በመካከላቸውም የሚኖሩ፥ የእግዚአብሔርን ቃል በሕይወታቸው በተግባር አየ ተረጎሙ የሚያሳዩአቸው ሰዎች ያስፈልጓቸዋል። ስለዚህ የመጋቢነት አገልግ ሎት የምሳሌነት አገልግሎት ነው ማለት ነው። መጽሐፉ አገልጋዮች ለምዕመ ናን ምሳሌ እንዲሆኗቸው ብቻ ሳይሆን፥ ምሳሌ የሚሆኑባቸውን አቅጣጫ ዎችም ሳይቀር ይጠቁማል። ለምሳሌ "... ነገር ግን ለሚያምኑት በንግግርና በኑሮ፥ በፍቅር፥ በእምነትና በንጽሕና አርአያ ሁንላቸው ..." ይላል (1ጢሞ. 4፥12)።

የወቅቱ የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ችግር የሚያስተምሩትን የሚኖሩ አገልጋዮች ቁጥር ከሚገባው በታች እጅግ በጣም አንሶ መገኘቱ ነው። በዓለም እና በቤተ ክርስቲያን መካከል ይህን ያህል ሊባል የሚቻል ልዩነት አለመታየቱ ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ አማኝ ከክርስቲያን የማይጠበቅ፥ ያልሆነ ያልሆነ ነገር ሲሆን የታየ እንደ ሆነ፥ "ወደ ዓለም ተመልሷል" ይባል ነበር። ዛሬ ዛሬ ግን ዓለም እራሷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብታ እና ተንሠራፍታ ስለ ተቀመ ጠች፥ "ወደ ዓለም መመለስ" የሚባል ቋንቋ ተረስቷል። እንደዚህ ባለ ጊዜ፥ ምሳሌነት የሌለው አንድ ሌላ አገልጋይ፥ "መጋቢ" ተብሎ ወደ ቤተ ክርስቲያን መድረክ ብቅ እንዲል ለምን ይደረጋል? ችግሩን ለማባባስ?

ያ ሁሉ ኢንቬስትሜንትስ?

በድምሩ ሃያ አራት ዓመታት ወደ ኋላ ተጓዝኩ። በመጀመሪያ የጥሪ ድምፅ ወደ ሰማሁበት ቦታ እና ጊዜም ደረስኩ። የሕይወት ጉዞ የሚጀምረው ግን ሰው ለእገልግሎት ሲጠራ አይደለም። የሕይወት ጉዞ የሚጀምረው ሰው ለደኅንነ ትም እንኳን ሲጠራ አይደለም። ከቶውንም ሰው ለደኅንነቱም ሆነ ለእገልግ ሎቱ ጥሪዎች አዎንታዊ ምላሽ እንዲሰጥ የሚያዘጋጁት ኹነቶች በሕይወቱ የሚከናወኑት ከዚያ በፊት ነው። "ከዚያ በፊት" ማለት ግን ከመቼ ጀምሮ ማለት እንደ ሆነ ለማወቅ ለእኛ አይቻለንም። ምክንያቱም ከእኛ ዕውቀት ውጭ በሕይወታችን የተከናወኑ መለኮታዊ ተግባሮች አሉና።

ለምሳሌ መጽሐፉ ለእገልግሎት ሳይሆን፥ ለደኅንነትም "መመረጥ" እና "መጠራት" የሚላቸው መለኮታዊ ተግባሮች አሉ። እነዚህ ተግባሮች እግዚአ ብሔር ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ በክርስቶስ በሕይወታችን ያከናወናቸው

ውስጥ ቀደም ሲል እንሥቻቸዋለሁ። እነዚህን ሁሉ ደማምሬ፥ በሁለቱ እጎቶች በኩል የመጡልኝ መልእክቶች ትክክለኛ እንደ ሆኑ እርግጠኛ ሆንኩ። በቅርቡ ሊሆን ያለ ነገር አለ ማለት ነው። "በዚህ ዓመት መቋጫ እደርጋለሁ" ማለት ሌላ ምንም ማለት ሊሆን አይችልም። ዓመቱ ሊያልቅ ደግሞ የቀሩት ሁለት ወራት ብቻ ናቸው።

ጥሪዬ ምን እንደ ሆነ፥ ሙሉ ጊዜዬን የምሰጣትም ቤተ ክርስቲያን ማን እንደ ሆነች፥ አሁን አሳምሬ ዐውቄአለሁ። ለሌሎቹም ጥያቄዎቼ ሁሉ መልስ አግኝ ቻለሁ። ያላወቅሁት አንድ ነገር ግን ገና ቀርቶኛል። መልስ ያላገኘሁለት እንድ ጥያቄ ግን ገና ቀርቶኛል - እሱም "ምን የሚሉት መጋቢ ነኝ?" የሚል ነው። ፓስተር ወይም መጋቢ ወይም እረኛ ተብሎ የሚሾመው ሰው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪ ነው። መንፈሳዊ መሪነትን በተመለከተ ጌታ ኢየሱስ ከሰጠን ሞዴሎች መካከል የሚከተሉት እራቱ ይገኛሉ፦

የሎሌ አገልጋይነት ሞዴል (ማቴ. 20፥25-28)

የእረኛ ሞዴል (ዮሐ. 21፥15-17)

የባለአደራ ሞዴል (ማቴ. 24፥45-51)

የምሳሌነት ሞዴል (ዮሐ. 13፥15)

እግዚአብሔር ሲያድነን ልጁን እንድንመስልለት ነው (ሮሜ 8፥29-30)። ልጁ ደግሞ አገልጋዮችን ሐዋርያ፥ ነቢይ፥ ወንጌላዊ፥ እረኛ እና አስተማሪ አድርጎ ለቤተ ክርስቲያኑ የሚሰጠው "የክርስቶስ እካል ይገነባ ዘንድ ቅዱሳንን ለአገልግ ሎት ሥራ ለማዘጋጀት" ነው (ኤፌ. 4፥11-13)።

መቼም ሁላችንም ከላይ በጠቀስኳቸው እና ባልጠቀስኳቸውም ሞዴሎች ረገድ ገና በማደግ ላይ እንደ ሆንን ይታወቃል። እኔ ግን እጅግ መሠረታዊ በሆነው የባል እና የሚስት አንድነት ላይ ችግር ያለብኝ ሰው ነኝ። ገና ያላደግሁበት ብቻ ሳይሆን፥ ምናልባት ከእንግዲህም ወዲህ የማላድግበት ጎን አለኝ ማለት ነው። ይህንን ምሰሌነት የጎደለውን ጎኔን ይዤ ምን የሚሉት መጋቢ ነው የምሆነው?

መጋቢነት በእመዛኙ አማኞችን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የማድረግ አገልግ ሎት ነው። ደቀ መዛሙርት ማለትም የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ተማሪዎች

ናቸው (ኤፌ. 1፥4)። ከእነማን እንደምንወለድ፥ የት እና መቼ እንደምንወለድ፥ ያሉት ኹነቶች "ዓለም ላይፈጠር" በተባለው ማዕቀፍ ውስጥ የሚካተቱ ይመስ ለኛል። በሥጋ ከመወለዳችን በፈትም ሆነ በኋላ፥ በሕይወታችን የሚከሠቱት ኹነቶች ሁሉ፥ ከርስቶስን ወደ እኛ ለማምጣት ባይሆንም፥ እኛን ወደ ከርስቶስ ለማቅረብ ግን ወሳኝ ሚና የሚጫወቱም ይመስለኛል።

ደኅንነትን ለመቀበል አንድ ሰው ንስሐ መግባት አለበት (ማር. 1፥15)። "ንስሐ" ማለት መመለስ ማለት ነው። ለመመለስ ግን ሰው እየተጓዘበት ያለው መንገድ እንደማያስሄደው እንዲገባው ያስፈልጋል። ያለዚያ ለምን ብሎ እየተጓዘበት ካለው መንገድ ይመለሳል? ደኅንነት የተዘጋጀው ከርስቶስን ለሚቀበሉ እና በስሙ ለሚያምኑ ሁሉ ነው (ዮሐ. 1፥12)። መድኀኒት የሚፈልጉ ግን የታመሙ ሰዎች ብቻ ናቸው (ማቴ. 9፥10-13)። ጤና እንደ ሆኑ የሚመስላቸው ሰዎች መድኀኒት አይፈልጉም። ምን ያደርግላቸዋል?

"ኑ! ዕረፍት ልስጣችሁ" የተባሉት ደካሞች እና ሸክም የከበደባቸው ለዎች ናቸው (ማቴ. 11፥28)። እንዳችም ሸክም እንደሌለባቸው የሚመስላቸው ሰዎች ግን ለዚህ ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ ሊሰጡ አይችሉም። በዚህ ምክንያት ነው ሰው ወደዚህ ዐይነቱ ግንዛቤ እንዲደርስ እግዚአብሔር እራሱ የሆኑ የሆኑ ነገሮችን በሰው ሕይወት ማድረግ ያለበት። ወይም ደግሞ ሰው አራሱ፥ አለዚያም ተፈጥሮ፥ ወይም ሁኔታዎች፥ ወይም ደግሞ ሰይጣን እና ከፉ ሰዎች የሆኑ የሆኑ ነገሮችን በሰው ሕይወት እንዲያደርጉ መተው ወይም መፍቀድ ያለበት። እኔ እነዚህን ነገሮች "የእግዚአብሔር ኢንቬስትሜንቶች" እያልኩ ስጠራቸው ነው ደስ የሚለኝ።

ኢንቬስትሜንት! ቃሉ ብዙ የሚታወቀው በአርሻው፥ በኢንዱስትሪው እና በአገ ልግሎት መስጫዎቹ የኤኮኖሚ ዘርፎች ዙሪያ ነው። "ልማታዊ" ቃል ነው። ልማት ግን በመሠረቱ ቁሳዊ እና አካላዊ ብቻ አይደለም። ልማት መንፈሳዊም ነው። አንዲያውም ለቁሳዊው እና ለአካላዊው ልማት መሠረቱ መንፈሳዊው ልማት ነው የሚሉ አሉ። እና እግዚአብሔር በሰው ሕይወት መንፈሳዊ ኢንቬስትሜንት ያደርጋል። ያ የእግዚአብሔር ኢንቬስትሜንት ነው ሰውን "የማያውቀውን አገር ናፋቂ" የሚያደርገው። ያ የእግዚአብሔር ኢንቬስት ሜንት ነው ሰውን ለንስሐ እና ለእምነት የሚያዘጋጀው ማለቴ ነው።

ያለዚያ ሰው የቱንም ያህል ቢሿጥ፥ በራሱ ጥረት ብቻ ወደ ንስሐ እና ወደ እምነት መድረስ አይችልም። እግዚአብሔር በሕይወቱ "ብርሃን ይሁን" ካለለ በስተቀር (2ቆሮ. 4፥3-6)፥ ሰው በጨለማ ውስጥ እንዳለ እንኳን ሊገባው አይችልም። ብርሃንን ለማየት፥ ሰው የእግዚአብሔር ብርሃን ያስፈልገዋል (መዝ. 36፥9)። እግዚአብሔር ለደኅንነትም ሆነ ለአገልግሎት የሚያዘጋጀን በሕይወታችን በሚያደርጋቸው በእነዚህ ኢንቬስትሜንቶቹ አማካይነት ነው እየልኩኝ ነኝ። እነዚህን ኢንቬስትሜንቶች በሕይወታችን የሚያደርጋቸውም፥ በሥጋ ከመወለዳችን ቀደም ሲል ጀምሮ ነው እያልኩም ነኝ።

በእነዚህ "ዐሥር አስጨናቂ ቀኖች" ውስጥ በብርቱ ካንገላቱኝ ጥያቄዎች አንዱ "እግዚአብሔር ሊያድነኝ፥ በመዳኔም ሊነግድበት እና ሊያተርፍበት ዐቅዶ ካለሆነ በስተቀር፥ ለምን ያንን ሁሉ በሕይወቴ ኢንቬስት አደረገ?" የሚለው ነው። እንደዚህ ለማለት ያስደፈረኝ፥ ኢንቬስትሜንቶቹ ብዙ እና ደግሞም ታላ ላት ሆነው ስለ ታዩኝ ነው። አሁን ግን ጥሪዬ ዕውቅና የማያገኝ ከሆነ፥ እንዴት አድርጎ ነው በእነዚያ ኢንቬስትሜንቶቹ ሊነግድባቸው እና ሊያተርፍባቸው የሚችለው? "አተርፍ ባይ አጉዳይ" መሆኑ አይደለም ወይ?

እነዚህ ኢንቬስትሜንቶች በሕይወቴ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነቶች ነበሩ - ሁሉም እንኳን ባይሆኑ እንዳንዶቹ። በጥንቃቄ አላለላሁትም እንጂ፥ ላሰላውም ደግሞ አልችልም እንጂ፥ ምናልባት አብዛኞቹ። ምናልባትም ሁሉም። ጣልቃ ገብነቶቹ ከመወለዴ በፈት - ቁጥሩ ለማይታወቅ ዘመን - ሲካሄዱ ነበሩ። በዚህ ረገድ እኔ በግሌ ራቅ ብዬ ወደ ኋላ ለመሄድ አልችልም። ምክንያቱም የአራቱን አያቶቼን እንኳን፥ ይቅርና ታሪካቸውን፥ ሙሉ ስማቸውንም አላው ቀውም። በአካል የማውቀው ደግሞ ከአራቱ አንዱን ብቻ ነው - ያውም እጅግ ለአጭር ጊዜ። ቢሆንም ታሪኩን ለማያያዝ፥ ምስሉንም ሙሉ ለማድረግ፥ ትንሽ ወደ ኋላ መለስ ማለት አለብኝ። ቢያንስ በቅድመ ልደቴ የመጨረሻ ምዕራፍ እና በድኅረ ልደቴ የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ያሳረፉትን አሻራ በመጠኑም ቢሆን ለመዘከር።

ማስታወሻ

1. John Reed, *Ten Days That Shook the World*, Penguin Books 1966.
2. Rick Joyner, *The Prophetic Ministry*, Morning Star Publications 1997.

ምዕራፍ ሁለት

ከአከራሪነት ወደ አከራሪነት

ከአራቱ እያቶቼ የማውቀው የአባቴን አናት አማሆይ አይመኩን ብቻ ነው። አብረውን ይኖሩ ነበር። የአምሰት ዓመት ልጅ ሆኜ ነው የሞቱት። የመርሐቤቴ ሰው ናቸው። ሲናገሩ "የጠባዝላው!"፥ "በጠባዝላው!"፥ ሲምሉም "የጠባዝላውን!" ማለትን ያበዙ ነበር ይሉኛል። ምናልባት ደብራቸው ይሆን ይሆናል። ታቦቱ ማን እንደ ሆነ ግን አላውቅም። የአይመኩን ቤተ ሰቦች - ከእርሳቸው፥ ከታላቅ ወንድማቸው ከደብተራ (በኋላ አባ) ወልደ ማርያም ዘወልዴ እና ከአንዲት አከሰታቸው በስተቀር - ሁሉንም "የጎዳር በሽታ" ይፈጃቸዋል። ቤታቸው ጨርሶ ወና፥ እርሰታቸውም ፈጽሞ ባድማ ይሆናል። አይመኩን ከቸነፈሩ የተረፉት እከሰታቸው ያሳድጓቸዋል።

ይህንን ታሪክ በልጅነቴ አናታችን ሰታወራው ሰምቻታለሁ። ነገር ግን ከልቤ ሆኜ አልሰማኋትም። "የወሬ እናቷ" አይመኩ ናቸው። እኔ ይህችን መጽሐፍ ለመጻፍ በምነሣ እና ማሰረጃ ማሰባለብ በምጀምርበት ጊዜ ደግሞ፥ እናቴ ከዚህች ዓለም በሞት ከተለየች ሁለት ዓመት ዐልፏታል። በልጅነታችን ከእናታችን የለማነውን ታሪክ እንደ ገና እንድትነግረኝ ታላቅ አጎቴን ማነጋገር ነበረብኝ። እርሷ ይህንን ታሪክ ከእናታችን አፍ ብቻ ሳይሆን፥ ከአማሆይ አይመኩም አፍ ሰምታዋለች። እርሳቸው በሚሞቱበት ጊዜ በዕድሜም ዐሥር ዓመት ሞልቷት ሰለ ነበረ፥ ሁሉንም እንኳን ባይሆን፥ አንዳንድ ነገሮችን ታሰታውሳለች።

አይመኩ በዕድሜ ትንሽ ከፍ ሲሉ፥ ወንድማቸኝ የተባሰ መንዜ በሚስትነት አንዲሰጡት አከሰታቸውን ይጠይቃል። እርሳቸውም አይመኩን ይዞ ወደ አገሩ የማይሄድ ከሆነ፥ ይልቁንም በባድማው የቤተ ሰባቸው እርስት ላይ የሚኖር እና ነፍስ የሚዘራበት ከሆነ፥ ሊለጡት ፈቃደኛ ይሆናሉ። ወንድማቸኝም በዚህ ቅድመ ሁኔታ ይሰማማና አይመኩ በሚስትነት ይዳሩለታል።

ሠንድማቸኝ ታይለኛም፥ ጨካኝም ሰው ነበር ይላሉ። አይመኩ የመጀመሪያ ለጃቸውን ወልደው ገና "ደማቸው ሳይጠፍ" ነው አሉ ጉልጓሎ ይዟቸው የወጣው። አራሷን ልጃቸውን ዛፍ ሥር አለተኝተው፥ እርሱ ሲያርስ እርሳቸው ሲነሰጉሉ አብረውት ይውላሉ። "አንዲህ አሳሬን ሳይ ምነው ዘመዶቼ በሕይ ወት ኖረው ባዩኝ ኖሮ" ሲሉ ልጃቸውን "ባዩሽ" አሏት ይባላል። አከታትለውም አበራሽን እና ወልደ ኪዳንን ይወልዱለታል።

ቱሰ በቀሰ ወናው ቤት እና ባድማው እርስት ነፍስ ዘራ። ወንድማቸኝም ዘመዶቹ ወዳሉበት ወደ መንዝ እና በዚያም ወዳለው የአባቱ እርስት መመላለስ ጀመረ። እንደዚህ ካሉት መመላለሶቹ በአንደኛው ወቅት ነው አሉ፥ አይመኩ ቱደም ሲል ዐይኑን ጥሎባቸው በነበረ አንድ ኮበሌ የተደፈሩት እና አራተኛውን ለጃቸውን ወልደ ቂርቆስን (ለው ሁሉ "ጨርቆሴ" ብቻ ነው የሚለው) ቅሪት የሆኑት።

እንደ ኢጋጣሚ፥ በዚያው ወቅት ወልደ ማርያም በትምህርት እና በቤተ ክርስቲ ያን እገልግሎት በየአገሩ ከሚዞሩበት ወደ መርሐቤቴ ይመለሳሉ። አይመኩ ብቸኛ ወንድማቸውን ሲያገኙ የሆኑትን ሁሉ ገልጠው፡ ይነግሯቸዋል። ወንድ ማኝኝ ከሄደበት በሚመለስ ጊዜ የሚከተለው ጣጣ ሁለቱንም እጅግ ያሳስባቸዋል። እና ወንድምና እኅት አጭር ምክክር ያደርጋሉ። ባዩሽ ሰድስት ዓመት ሞልቷት ሰለ ነበረ፥ እርለዋን እዚያው ሊተውዋት ይወስናሉ። አበራሽን በእጃቸው፥ ወልደ ኪዳንን በጀርባቸው፥ ጨርቆሴን ደግሞ በሆዳቸው ይዘው፥ ወልደ ማርያም ቀድሞም በቤተ ክርለቲያን አገልግሎት ወደሚያውቁት ወደ ወላሞ (አሁን ዎላይታ) አገር አብረው ይኮበልላሉ። ወልደ ኪዳን በዚያን ጊዜ የሦስት ዓመት ልጅ ነበረ ይላሉ።

ዘመኑሰ መቼ ይሆን? "የጎዳር በሽታ" በመባል የሚታወቀው ታሪካዊ ቸነፈር አዲስ አበባ የደረለው በጎዳር ወር 1911 ዓ.ም. ነው።[1] "የሐያኛው ከፍለ ዘመን መባቻ" የተባለው የብላታ መርሰዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ መጽሐፍ፥ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴን ዋቢ በማድረግ በኢትዮጵያ "የጎዳር በሽታ" እየተባለ የሚታወቀው በሽታ በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ላይ ዓለሙን ያዳረሰው፥ በታሪክ "እሰፓኒሽ ፍሉ" በመባል የሚታወቀው፥ የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ መሆኑን ይናገራል። ወረርሽኙ ብዙ የተጻፈበት ሲሆን፥ በዓለም ዙሪያ ከሃምሣ

ሚልዮን በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ሞት ምክንያት ሆኗል ይባላል፡፡ ይህም ቁጥር በጦርነቱ ከሞቱት ሰዎች ቁጥር ይልቅ በእጅጉ የበለጠ ነው፡፡

ጉስታቭ እሬን ደግሞ ወረርሽኙ ምዕራብ ወሊጋን ያዳረሰው እንደ ጎርጎሳውያኑ አቆጣጠር በመፀው ወራት (መስከረም - ጎዳር) 1918 እንደ ሆነ ጽፈዋል::[2] ይህም ማለት በእኛ አቆጣጠር ያው 1911 ዓ.ም. ማለት ነው:: ፕሮፌሰር ባህሩን ዋቢ ያደረገው "የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻም" ወረርሽኙ በምዕራብ ወሊጋ "ዱኩባ ቂሌንሳ" (የነፋስ በሽታ) ይባል እንደ ነበረ አስታውቆናል::

እንደ እኔ ምርምር ከሆነ፥ እይመኩ ለወንድማገኝ የተዳሩት ከጎዳር በሽታ በፊት እንጂ ከጎዳር በሽታ በኋላ ሊሆን አይችልም:: ትንሽ ዝቅ ብዬ በማነሣው ሌላ ምክንያት፥ ወልደ ኪዳንም የተወለደው ከጎዳር በሽታ ቀደም ብሎ እንጂ ከጎዳር በሽታ በኋላ ሊሆን አይችልም:: ለማናቸውም ደብተራው አጎቱ ወልደ ኪዳንን እንደ ልጃቸው አድርገው፥ የቤተ ክህነቱንም ትምህርት አስተምረው፥ አሳደጉት:: ለአባታችን በአባትነት፥ ለእኛም በአያትነት ስማቸው የሚታወቀው ወልደ ማርያም ናቸው:: ተኖሮ ተኖሮ አባቴ የባዩሽን ሞት በሚረዳበት ጊዜ፥ እኔ የዐሥራ አራት ዓመት ገደማ ልጅ ነበርኩ::

እናቴ ፈሰቀች ገብረ ሚካኤል ቢሻው ትባላለች:: እናቷ ዐፀደ እንደሚባሉ ብቻ ነው የማውቀው:: ፈሰቀች አልተማረችም:: ሆኖም ብዙ ነገር - በተለይም የአገር ታሪክ - ታውቃለች:: ስለ ንግሥት ዘውዲቱ እና ስለ ባላቸው ስለ ራስ ጉግሣ ወሌ አኗኗር እና አሟሟት፥ በልጅ ኢያሱ እና በራስ ተፈሪ መካከል ስለ ነበረው ሥር የሰደደ አለመተማመን እና አንዳቸው ሌላቸውን ለማጥፋት ዘወትር በሰልት ስለ መንቀሳቀሳቸው፥ አሳምራ ታውቃለች:: ስለ ሰገሌ ጦርነት፥ የሸዋው ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የወሎውን ንጉሥ ሚካኤልን እንዴት እንደ አታለሏቸው እና ድሉ የሸዋ እንደ ሆነ፥ "በኢያሱ ዳቦ ነው ትራሱ"፥ "በዘውዲቱ እሬሣ ጎትቱ"፥ "በተፈሪ የለም ፍርፋሪ" ይባል እንደ ነበረ መጀመሪያ የሰማሁት ከእርሷ ነው::

ስለ ማይጨው ጦርነት፥ "አርበኛ" እና "ባንዳ" በመባባል ሁለት ላይ ስለ ተከ ፈሉት ኢትዮጵያውያን ወንድማማቾች፥ በመጀመሪያ የሰማሁት ከእናታችን አፍ ነው:: የሰማሁትም በኋላ በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ተጽፎ ካነበብኩት ብዙም የተለየ አይደለም:: ለየት ያለ ታሪክ በምትነግረኝ ጊዜ፥ "እንደርሱ እይደለምኮ"

እላትና ተጽፎ ያንበብኩትን ልነግራት እሞክራለሁ:: በቀላሉ አትቀበለኝም፥ ዝርዝራቸውን በማላውቀው መስቀልኛ ጥያቄዎች ታጣድፈኛለች:: ስለ ማይ ጨው ጦርነት እና እሱን ተከትሎ እርሷ በነበረችበት አካባቢ የሆነውን፥ እራሷ ያለፈችበት ስለ ሆነ ታውቀዋለች:: ስለ ሰገሌ እና ስለ እንቺም ጦርነቶች፥ ስለ ራስ ጉግሣ እና ስለ ንግሥት ዘውዲቱ አሟሟት ለእኛ የነገረችንን የሰማቻቸው ግን ያለ ጥርጥር ከአባቷ መሆን አለበት::

አባቷ ሰገሌ ዘምተው በነበረ ጊዜ እንደ ተወለደች ነው የምትናገረው:: ከሰገሌ ጦርነት በኋላ ግን በማታውቀው ምክንያት (ዕድሜዋ ትንሽ ስለ ነበረ ይመስለ ኛል)፥ አባቷ እና ሌሎች ጥቂት ሰዎች ቤተ ሰቦቻቸውን እንሥተው ከሸዋ (ሰላሌ?) ወደ ገሙ ጎፋ (በኋላ ጋሞ ጎፋ) ተጓዙ:: በየት በኩል አድርገው እንደ ተጓዙ ለማወቅ ይረዳ እንደ ሆነ አላወቅሁም እንጂ፥ የጊቤን ሳይሆን፥ "የአሞን ሠንዘ በስልቻ ነው የተሻገርነው" ትላለች:: ከዚያም በጋርዱላ አውራጃ ከሚገኝ "ዱሮ" ከሚባል ቦታ ነዋሪ ሆኑ::

"የራስ ብር" የሚባለውን የመንግሥት ግብር ለመሰብሰብ፥ ከሆኑ ሹም ጋር ከሥላይታ መጥቶ በአካባቢው ይዘዋወር ከነበረው ከወልደ ኪዳን ጋር የተገናኙ ትና የተጋቡት በዚያን ጊዜ እና በዚያ ቦታ ነው:: "የራስ ብር" ስለሚባል ግብር እስከ አሁን ተጽፎ ያነበብኩት የለም:: እርሷዋ ግን "ጣልያን ኢትዮጵያን ሊወጋ እየተዘጋጀ ስለ ነበረ፥ ራስ ተፈሪ ለጠመንጃና ለጥይት መግዣ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ (እባወራ ማለት ሊሆን ይችላል) ላይ በነፍስ ወከፍ ይሰበሰቡት የነበረ የእንዳንድ ብር ቀረጥ ነው" ትላለች:: ታሪክ በጣም ስሜት ይሰጣታል::

ኢትዮጵያን በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ እየገፋ ከነበረው ከኢጣልያን ጦር በመሸሽ ላይ እያሉ ነው እናቴ ሁለተኛዋን ልጇን ነሐሴ 28 ቀን 1928 ዓ.ም. ጫካ ውስጥ የወለደቻት:: እራስዋ እናት አህል ሳትቀምስ፥ እራሰዋም ልጅ ሳትታጠብ፥ ሳትጠባ (ለምን ደግሞ ሳትጠባ?) ወይም ቅቤ ሳትልስ፥ ሁለት ቀን ያህል ሆነ:: ልጅቱ ባለመሞትዋ የተገረሙ፥ አብረዋቸው በመሸሽ ላይ የነበሩ አንድ ሰው፥ "ይህች ልጅ እስከ አሁን ካልሞተች ካብታም ናት ማለት ነው፥ እንግዲህ እርሰዋም ከሞት፥ እኛም ከዚህ መከራ ድነን ለቤታችን እንበቃለን" አሉ:: በዚያው "በካብቷ" ተባለች::

በእናቴ ቤተ ሰቦች በኩል ያለውን ታሪክ እንዳውቅ የረዱኝ በካብቷ እና ወንድሜ ነጋሽ ናቸው:: እነርሱ ካደጉ በኋላ ወደ እናታችን አገር የመሄድ (ነጋሽ

በሥራ ምክንያት እንዲያውም ደጋግሞ የመሄድ) እና ከዘመዶቿም ብዙዎቹን በአካል የመገናኘት ዕድል አጋጥሟቸዋል።

"አይመኩ ለወንድማገኝ የተዳሩት እና ወልደ ኪዳንም የተወለደው፥ ከጎዳር በሽታ በፊት እንጂ በኋላ ሊሆን አይችልም" ያልኩበትን ምክንያት አሁን ላስረዳ። በቅድሚያ ሁለት መንደርደሪያዎችን ላስቀምጥ። መንደርደሪያ አንድ ወልደ ኪዳን ፈለቀችን ያገባው ቢዘገይ በ1926 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ ነው ሊሆን የሚችለው። ምክንያቱም ወልደ ኪዳን እና ፈለቀች በ1928 መጨረሻ ላይ በካብቷን ከመውለዳቸው በፊት የመጀመሪያ ልጃቸውን ቀብረዋል። በዚያ ጊዜ ማግባት እና ማስወለድ፥ በመንግሥት መቀጠር እና ቀረጥ መሰብሰብ የቻለ ወንድ፥ በምንም ዐይነት ከጎዳር በሽታ በኋላ የተወለደ ሊሆን አይችልም።

መንደርደሪያ ሁለት በተለያዩ አጋጣሚዎች አባታችን እና እናታችን ሊጫወቱ እንደ ስማኋቸው፥ እርሱ እርሷን በዕድሜ 5 ዓመት ይበልጣታል። አናታችን የተወለደቸው አባቷ ሰገሌ ዘምተው በነበረ ጊዜ እንደ ሆነ ስትናገር መስማቴን ከላይ ጠቅሻለሁ። የሰገሌ ጦርነት የሆነውም ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም. ነው።[3] ይህም ማለት ከጎዳር በሽታ ሁለት ዓመት ቀደም ብሎ ማለት ነው። ስለዚህ አይመኩ ወንድማገኝን ያገቡት እና ወልደ ኪዳንም የተወለደው፥ ከጎዳር በሽታ በፊት እንጂ በኋላ ሊሆን አይችልም።

ከእነዚህ ሁለት መንደርደሪያዎች በመነሣት፥ የእኔ ድምዳሜ የአይመኩን ቤተ ሰቦች የፈጃቸው "የጎዳር በሽታ" አይደለም የሚል ነው። ታዲያ ምንድነው? የእኔ ምላሽ የአይመኩን ቤተ ሰቦች የፈጃቸው በጽናቱ "ከጎዳር በሽታ" ይልቅ እጅግ የከፋው፥ "ከፋ ቀን" በመባል የሚታወቀው እረሀብ ነው የሚል ነው። በኢትዮጵያ "ከፉ ቀን" በመባል የሚታወቀው እረሀብ የሆነው ከ1880 እስከ 1884 ለአራት ዓመታት ነው። ይህም ማለት ከ"ጎዳር በሽታ" ከ27 እስከ 31 ዓመት ለሚሆን ያህል ጊዜ ቀደም ብሎ ማለት ነው። የታሪከ ባለ ሞያው ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ እንዲህ ይላሉ፦

> ያገሪቱ ማዕከል ወደ ደቡብ እየተዘዋወረ ባለበት ሰዓት ኢትዮጵያን የረሀብ መቅሰፍት መታት። ባገሪቱ የውስጥም የውጭም ጉዳዮች ላይ አሻራውን ትቶ የሄደው ይህ ዐቢይ ማኅበራዊ ቀውስ ቀደም ብለን ለጠቀስነው የመስፋፋት ሂደት ግፊት ከሰጡት ኃይሎች አንዱ ነበር።

> ይሁን እንጂ ብዙ የተጠቃው ከፍል የስሜኑ ቢሆንም ከመዓቱ ያመለጠ ከልል አምብዛም አልነበረም። እንዲያውም ችግሩ ከኢትዮጵያም ከልል ዐልፎ በሱዳንና በሌሎች የምሥራቅ አፍሪቃ አገሮች ታይቶ ነበር ... በአጠቃላይም የዚህ ዘመን ረሀብ በሕዝብ ሕሊና የማይፋቅ ጠባሳ ትቶ ነው ያለፈው። "ከፉ ቀን" በሚል ስም እየተዘከረ የኋለኛ ዘመን ረሀቦችን ማመዛዘኛና ማነፃፀሪያ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል።[4]

አይመኩ የተወለዱት በ1884 ዓ.ም.፥ ማለትም "ከፉ ቀን" ሊወጣ ሊል ቢሆን እና ከወንድማገኝ ጋር የተጋቡትም በ15 ዓመት ዕድሜአቸው እንደ ሆነ ብንገ ምት፥ ሥስቱንም ልጆቻቸውን እስከ 1905 ገደማ ድረስ ሊወልዱላቸው ይች ላሉ። ይህም ስሌት፥ ወልደ ኪዳን በ1909 ወይም በ1910 አካባቢ የተወለደች ውን ፈለቀችን በ5 ዓመት ዕድሜ እንዲበልጣት በማድረግ በእንደኛው መንደር ደሪያችን ውስጥ ያለውን ጥያቄ ይመልሳል።

ታዲያ ፈለቀች እና በካብቷ "የጎዳር በሽታ" የሚለውን ከየት አመጡት? እሱን ቡተከከል አላውቅም። ከአይመኩ ያመጡት ግን አይመስለኝም። ፈለቀች እና በካብቷ "የጎዳር በሽታ" እና "ከፉ ቀን" በመባል የሚታወቁትን መጠሪያዎች እምታትተዋቸው ሊሆን ይችላል ብዬ ነው የማስበው። እንደኔ እንደኔ፥ በጎዳር በሽታ ወቅት አይመኩ በስሜን ሸዋ ሳይሆን በዎላይታ ነው የነበሩት።

አብዛኛውን የልጅነታችንን ዕድሜ ያሳለፍነው ከአናታችን ጋር ነው። አባታችን መጀመሪያ በመንግሥት ሥራ፥ በኋላም ደግሞ በንግድ ሥራ ምክንያት ብዙ ጊዜ በአገር አይቀመጥም ነበር። በመጨረሻም እኔ ዐሥራ ስድስት ዓመት ዕድሜ ላይ ስደርስ ሞተ። ያለ ምንም ገቢ ስድስት ልጆችን ማሳደግ፥ ከአነር ሱም አምስቱን ማስተማር፥ ለአናታችን የዋዛ ኃላፊነት አልነበረም። ሆኖም አርስዋም የዋዛ ሴት አልነበረችም። ጨው እና ጥጥ ከጅምላ ሻጭ በዱቤ እየወሰደች በቸርቻሮ ታጣራለች። ጥጥ እየፈተለች ነጠላ እና ጋቢ እያሠራች ትሸጣለች። ጥገት እያሠረች ወተቷን ታኮናትራለች። ጠላ ትጠምቃለች፤ "ያገር ተወላጅም" ታወጣለች።

ልጆቿም ዐቅማችን በሚፈቅደው ሁሉ እናግዛታለን። ድውር እናዳውራለን፤ የተዳወረውን ከሸማኔው እናደርሳለን። ውሃ ከምንጭ እንቀዳለን። ወንዝ ወር ደን ልብስ እናጥባለን። እንጨት እንሠብራለን። በጎች እና ከብቶች እናግዳ

ለን፡፡ ሣር እናጭዳለን፡፡ ወደ ገጠር ገባያዎች በምትሄድ ጊዜ እኔ አብሬአት እሄዳለሁ - ማከለኛ ቦዲቲ፣ ረቡዕ ጉልጉላ፣ ሐሙስ ዳልቦ፡፡ በካብቷ እና አለካለ ሌቶች የሚሠሩትን ሥራ ብቻ ሳይሆን፣ የወንዶቹንም ሥራ ይሠራሉ፡፡

ሥራ በምንፈታባቸው ምሽቶች ታሪክ ታወራናለች፤ ተረት ታጫውተናለች፡፡ አርሰዋ ልጅ በነበረችበት ዘመን ይዘፈኑ የነበሩ ዘፈኖችን ትዘፍንልናለች፤ የተለያዩ የአስክሲታ ዐይነቶችንም በአንገትዋ እና በትከሻዋ እየመታች ታሳየና ለች፡፡ ለማቸውንም ትነግረናለች - በውስጤ የቀረው ዋንጫ ልቅለቃ የሚባ ለው ብቻ ነው፡፡ "የንቅልፍ ያጀቡ ልጅ" የምትላት ገጸ ባሕርይ አለቻት፡፡ የአርሰዋ ፈጠራ እንዳይደለች ቢገባኝም፣ እስከ ዛሬም ድረስ ሌላ ለው ሲያነሣት አልሰማሁም፡፡ ሞያዋን በተመለከተ -

> የንቅልፍ ያጀቡ ልጅ የሠራችው ቂጣ
> ባርባ መሰቅሰቂያ ባምሣ ሰፈድ ወጣ፤
> አርሱን ዉጣ ዉጣ ቆማ ብታገሳ
> ሄደች የራስ በቅሎ አውታሩን በጥሳ፡፡

ዘመናይነቷን በተመለከተም -

> የንቅልፍ ያጀቡ ልጅ በጣም ሠለጠነች
> የብሩን አቡጀዲድ ጥለፉልኝ አለች፤
> ያውም በመኪና ጣት አይንካው አለች፡፡

ይህ የተዘፈነው የስፌት መኪና ከመምጣቱ ትንሽ ቀደም ብሎ ነው ትላለች፡፡ አንቅልፍ ወዳድነቷን በተመለከተ ደግሞ -

> የንቅልፍ ያጀቡ ልጅ ሂጂ ተኚንደሺ
> በራፉ እሰኪዘጋ ሱሪዬን ልበሺ፤
> ኡ! ኡ! የተባለ እንደሁ የት አባሽ ልትደርሺ፡፡

"የንቅልፍ ያጀቡን ልጅ" የሆነ ቦታ የማውቃት ሰው አለኩትመስለኝ ድረስ ነበር እናቴ በትረካዋ በውስጤ የሣለቻት፡፡

በቤታችን ሁላችንም ከእማርኛ ሌላ ዎላይትኛ እንናገራለን፡፡ ከበካብቷ በስተ ቀር ለእኛ ለልጆቹ ዎላይታ የተወለድንበት እና ለሁላችንም ደግሞ ያደግንበት አገራችን ነው፡፡ አባታችን፣ እናታችን እና በካብቷ አሮሚፋም ጭምር ይናገ

ራሉ፡፡ እባታችን አሮሚፋ መናገር የቻለው በአሮሞዎች መካከል ብዙ ስለ ኖረ ነው፡፡ በካብቷ ከወላጆቿ ተምራ ሲሆን፣ ለእናታችን ግን ሁለቱም ቋንቋዎች እሳቸን የፈታችባቸው ይመለሱኛል፡፡ እንዴት እንደ ሆነ እስከ አሁን አልገባኝም፣ ሁለቱንም ግን እቀላጥፋ ትናገራቸዋለች፤ ትዘፍንባቸዋለችም፡፡

ከአማርኛ ዘፈኖቿ ግጥሞች የአብዛኞቹን፣ ከአሮሚፋዎቹ ደግሞ የእንዳንዶቹን እስከ ዛሬም ድረስ በቃሌ ዐውቃቸዋለሁ -

> ሰላሌቲ ዳላታኒ፣
> ዱኩባ ላጴ ማል ሂማታኒ?
> ማጋላ ጃላታኒ፤
> ዚናሪ/ሺጉጢ ማሌ ማል ሂዳታኒ?

"ሰላሌ ተወልዶ፣ የልብ ሕመም (ፍቅር ለማለት ነው) ምኑ ይነገራል? ጠይም ያለይልኝ፤ ከዝናር/ከሸጉጥ በቀር ምን ይታጠቋል?" እንደ ማለት መሰለኝ፡፡

ሥራ ለሠራ ልቧ ያልደረሰ እንደ ሆነ "ላንፉ"፣ እበላሌ ደሰ ካላላት ደግሞ "ሳምብቻም ናረት" ትለኛለች፡፡ የከረምት ዝናብ ችክ ያለ እንደ ሆነ፣ "ወለሰ" ትላለች፡፡ እነዚህን ቃላት በእማርኛ መዝገበ ቃላት ውሰጥ ፈልጌ አግኝቻቸዋ ሰለሁ፡፡ ከ"ቅምብቻ" በስተቀር ግን፣ ሌሎቹን ሌላ ለው ሲጠቀምባቸው እስከ ዛሬ እልሰማሁም፡፡ ላንፉ የአገዳ አህል ወይም የአገዳ ሣር ቅጠል ነው፡፡ የእማርኛ ተረቶችዋማ እበዛዛቸው፡፡ ገነት አኔንም "እሮጊት ይመሰል ተረት ትወ ዳለህ" ትለኝ ነበር፡፡ እውነቷን ነው፤ ተረት እወዳለሁም፤ በመጠኑ አችላ ለሁም፡፡ አብዛኞቹን የተማርኩት ደግሞ ከእናቴ ነው፡፡

ያላዋቂ አከራሪ

እናታችን ሲበዛ "ሱፐርስቲሽየስ" ናት፡፡ ለቃሉ የአማርኛ እቻ አላገኘሁለትም፡፡ ድርጊቱን ለነግራችሁ ምን ማለቴ እንደ ሆነ ታውቁታላችሁ፡፡ ጉጉት ከፎኸች፣ ሙሻ ካላዘነ፣ ጨረቃ ስትወለድ ወደ ግራ ዘመም ብላ ከሆነ፣ ዓውሎ ነፋስ በኃይል ከነፈሰ፣ የሰኔ ልደታ ሰኞ ዕለት ከዋለች፣ መንገድ ስንሄድ - ግራ ይሆን ሃኝ አግራችንን አረላሁት - ካነቀፈን፣ ወዘተርፈ፣ ከፉ ነገር ሲመጣ ነው - ወይ በእኛ ቤት ላይ፤ ወይ በሰፈሩ ላይ፤ ወይም ደግሞ በአገሩ፣ በንጉሠ ነገሥቱ እና በመንግሥቱ ላይ፡፡ እነዚህ እምነቶች ባገሩ ላይ የተንሠራፉ እንደ ሆኑ፣ ማለቴ በብለይ የእናቴ አለመሆናቸውን፣ ዐውቃለሁ፡፡ በኋላ ላይ እየተረዳሁ እንደ

መጣሁትም፥ እንደ እነዚህ የመላለሱ እምነቶች የሌሉት ሕዝብ የለም። እንደ ዚያም ሆኖ፣ የእናቴ ከልኩ የሚያልፍ ይመስለኛል።

በእንድ ወቅት በቤታችን የሰይጣን ነው የሚባል ትንሽ ቁራጭ ቆዳም ነበረ። ሰይጣኑ "ዕጡን" ሳይይዘው አረስቶት፣ ሰው ይሁን አውሬ ድንገት ደረሰበት እና ወደ ሰይጣንነቱ መመለስ ላይችል ቀረ። እንደዚህ በሚሆን ጊዜ በሰይጣኑ እና በደረሰበት ሰው ወይም እውሬ መካከል ግጭት ሊፈጠር ይችላል። በግጭቱም ውስጥ ጭገር ይነጫል፤ ቆዳ ይቦጨቃል፤ ደም ይፈሰሳል፤ ጩኸት ይቀል ጣል። ማታ መኝታው ላይ ሆኖ የሰይጣኑን ጩኸት ለይቶ ያወቀ ሰው በማለዳ ወጥቶ አሰሳ ያደርጋል። የተነጨ ጭገር እና የተቦጨቀ ቆዳ እዚህም እዚያም ወዳድቆ ሊያገኝ ይችላል። የሰው ወይም የእውሬ የሆነውን ይተወውና የሰይ ጣኑ የሆነውን ያነሣዋል። የበለጠ ያቀጣጥነውናም ይቸበችበዋል - ፍቱን መድኀኒት ነው ትለናለች።

ወባ ክትንኝ እንደሚመጣ ተማሪ ቤት ያስተማሩንን በነገርኳት ጊዜ እናታችን የመጨረሻዋን ነው የሣቀችብኝ። ትምህርቱን እንደ ቂልነት፥ አስተማሪዎቻች ንንም እንደ ለየላቸው ቂሎች ነው የቆጠረቻቸው። "ወባ ቆሌ ናት ... ሰው ትመ ስላለች ... ፀጉርዋን ቀጥ አድርጋ ጎፈሬ ነው የምታበጥረው ... በሥሩ በቀጭኑ ገርዳሣ ታሥራለች ... ከቀሚሷ ሥር ሁል ጊዜም ሱሪ ትታጠቃለች ... በበረሃ ውስጥ ስትዘዋወር ያዩዋት ብዙ ሰዎች አሉ ... እንዳንዴ በሰም ጠርታ ታናግራ ቸዋለች ..." እቤት በሚኖር እና "ሙዳቸው" መልካም በሚሆን ጊዜ፥ አባታችን እንደዚህ ባለው የሚስቱ ንግግር የልግጫ ሣቅ ይሥቃል። ሚስቱም በተራዋ "... እ? ... የዳዊት አምላክ? ..." በማለት ታሾፍበታለች። እንደዚህ የምትለው እርሱ በንግግሩ ሁሉ ውስጥ "የዳዊት አምላክ ያውቃል" ማለትን ስለሚያበዛ ነው።

በቤታችን የሚከበሩ ወርኀዊ እና ዓመታዊ በዓላት አሉ - ልደታ፥ ባእታ፥ አቦዬ፥ ሥላሌ፥ ሚካኤል፥ ኪዳነ ምሕረት፥ ገብርኤል፥ ማርያም፥ ጊዮርጊስ፥ ተክለ ሃይማኖት፥ መድኀኔ ዓለም፥ በዓለ ወልድ፥ በዓለ እግዚአብሔር። ሆኖም በእኛ ቤት፥ እነዚህ በዓላት ከዕለታዊ ሥራችን የምንበዝንባቸው አልነበሩም። ገበሬዎች አይደለን እናርስባቸው። እጽዋማቱም - ከጽጌ እና ከሰኔ ጾም በስተቀር - በሁላችንም ይጾማሉ።

ማኅበራት እና ለንበቴዎችም ይጠጣሉ። አባቴ የጊዮርጊስን ለንበቴ፥ እናቴ ደግሞ የማርያምን ማኅበር እና የኪዳነ ምሕረትን ለንበቴ ይጠጡ ነበር። እኔም በአንድ ወቅት ከባልንጀሮቼ ጋር የሚካኤልን ማኅበር መጠጣት ጀምሬ ነበረ። ለንበቴ ሳምንታዊ ሲሆን፥ ማኅበር ወርኀዊ ነው። በተጨማሪም ለንበቴ ጽዋ የለውም።

የተኛው መቼ፥ ለማን እና ለምን እንደሚደረግ ለይቼ አላወቅሁም እንጂ፥ በቤታችን የሚደረጉ ሌሎች ነገሮችም አሉ። ዐልፎ ዐልፎ ወሰራ እና ጉበለማ ሥረዮች፥ ዐልፎ ዐልፎም ዳለቻ እና የጥቁር ቦሃ በጎች ይታረዳሉ። የሚገበርላቸ ውንም "ውቃቢዎች" ወይም "ዛሮች" ቢያንሰ ስማቸውን እናውቀዋለን - ሰዳር፥ ወሰን ጋላ፥ አዳል ሞቲ። እናቴ አቴቴም ታደርጋለች። እኛ ልጆቹ ለቅንጩው፥ ለእንቡሽቡሹ፥ በቅቤ ለሚቆላው ድፍን ቡና እና ለአቴቴዋ ለሚዘጋጀው ሌላ ሌላ ነገር ሁሉ ስንል፥ ቀኑን በናፍቆት እንጠብቀዋለን።

እናቴ አቴቴዋን በምታደርግበት ዕለት አባቴ በጊዜ ወደ ቤት አይገባም። በዕለቱ የሚደረገው ነገር ሁሉ ተደርጎ ካለቀ በኋላ ነው የሚመጣው። በዚያም ላይ ሦማምስ እና ሞቅ ብሎት ነው የሚመጣው። ተቃውሞውን የሚገልጥበት ቋንቋው መሆኑ ነው። በዚህ ምክንያት እርሱ በአገር የሌለ ካልሆነ በስተቀር፥ እናቴ አቴቴ የምታደርግበት ቀን በእኛ ቤት የሰላም ቀን ሆኖ አያውቅም።

"... ልጆችህን እንዳትፈጅልህ ብዬ ነው እንጂ ..." ትለዋለች። እሱ እንዳች አይመልስም። በድርጊቱ ተናግሮ ጨርሶታል። በተለይ እንድ ዓመት "... እንዲያውም አሁን አውጥቼ አጥልልህ ... እና ታርፈዋለህ ..." ብላ ተነሣች። ጠጨዋን ወደ ሙዳይዋ መልሳ እና ከሌላው ጓዟ ሁሉ ጋር ታቅፋት፥ በጨለማ በቅርቦችን ወደ ነበረው ወንዝ አቀናች። በካብቷ እና እኔ ከኋላ ከኋላዋ እየተከ ተልናት እንዳትጥላት ተማጠንናት። አባቴ ከነበረበት እልተነቃነቀም። ሰሚ አላገኘሁም እንጂ፥ በተለይ እኔ ዛቻዋን ተግባራዊ ከማድረጓ በፊት እንዲከተላት እና ወደ ቤት እንዲመልሳት ወትውቼው ነበር። ለደኅንነታችን ሠግቼ ወይም ለጨሌዋ አዝኜ ላይሆን፥ እናቴ ሰለ አላዘነችኝ ብቻ ነበር ያንን ያደረግሁት።

በየዕለቱ ጠዋት እና ማታ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተለመዱ ጸሎቶችን በቃሌ እየደገምኩ ነው ያደግሁት - በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ ... ነአኩተከ ... አቡነ ዘበሰማያት ... በለላመ

ቅዱስ ገብርኤል ... ጸሎተ ሃይማኖት ... ስብሐት ... የየዕለቱ ውዳሴ ማርያም ... አንቀጸ ብርሃን ... ወዘተርፈ:: ከጸሎት መጻሕፍት ላይ ደግሞ በየዕለቱ የማነብባቸው አሉ - መልከዓ ማርያም፥ መልከዓ ኢየሱስ፥ ትምሕርተ ኅቡዓት:: ከመ ዝሙረ ዳዊት አንድ ቀይ:: ዐልፎ ዐልፎ የሚነበቡም አሉ - መልከዓ ሚካኤል፥ ድርሳነ ሚካኤል፥ ቅዳሴ ማርያም፥ ተአምረ ማርያም፥ መልከዓ ጊዮርጊስ፥ ወዘተርፈ:: አናነብበውም እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስም በቤታችን ነበረ::

እኔ ብቻም አይደሰሁም - በካብቷም፥ የሁሳታችንን ያህል አይደለም እንጂ ታናሽ እኅቴ አስካለም፥ በዚህ ዐይነት ነው ያደግነው:: አባታችን በአገር የማይኖርበት ጊዜ እየረዘመ ስለ መጣ፥ በኋላ ላይ የተወለዱት ሁለቱ ወንድሞቼ እና አንዲ እኅቴ እኛ ባደግንበት መንገድ አላደጉም::

የቃል ድግምቱ፥ በተለይም የምሽቱ፥ የምወደው አልነበረም:: በዚያች አንዲት ከፍል የሣር ከዳን ቤታችን ውስጥ እኔ ፊቴን ወደ ግድግዳው እዙሬ ቆሜ ሳነበንብ፥ አባታችን እና እናታችን እያወሩ ወይም እራት እየበሉ ሊሆኑ ይች ላሉ:: ቀልቤ ወደ ጨዋታቸው ይሳባል:: ወይም የሚበሉት እራት ይሸተኛል:: እና ወይ ድግምቱ ይጠፋኛል፥ ወይም ደግሞ ለማሳጠር ስል የሆነውን ከፍል አድበስብሼ ለማለፍ ሙከራ አደርጋለሁ:: ለካ አባታችን በጨዋታው መካከል እየሰማኝ ኖሯል - "ላስከውኮ!"፥ "በል መልሰው!" ይለኛል:: ከየቱ ጋ መልሼ አንደምጀምረው ይደነጋገረኛል:: ያኔ "... ተንበርከከ ... እጅህን ዘርጋ ..." ይመጣል:: ከዚያም ወይ ቁንጢጥ፥ ወይ ኩርኩም፥ ወይ ቀበቶ፥ ይከተላሉ::

በካብቷ ዕቃ የምትፈልግ ወይም የምታነሣ መስላ በአጠገቤ በማለፍ፥ ሳይታወቅባት በጆሮዬ "ሹክ" ልትል እና ጫፉን ልታስጨብጠኝ ሙከራ ታደርጋለች:: ከተሳካልን ከመንበርከኩ እና እሱን ተከትሎ ከሚመጣው አበሳ ሁሉ እድናለሁ:: የጠዋቱ ድግምት የቀረልኝ እምስተኛ ከፍል ስገባ ነው:: "ለዕውቀቱ ያህል የእስከ አሁኑ ይበቃሃል" አለኝ አባቴ::

በቤታችን ዕሑድ ዕሑድ ቤተ ክርስቲያን ይሳማል:: ለምን አንደ ሆነ አንጂ፥ ይህ ግዴታ ግን ከእኔ በስተቀር ሌሎቹን ልጆች አይመለከታቸውም ነበር:: በአገር ያለ ከሆነ፥ ዕሑድ ማለዳ ላይ አባቴ ሁል ጊዜ ከእንቅልፍ ይቀሰቅሰኛል:: አንዳንድ ቀን እየሰማሁም እንዳልሰማሁ እሆንበታለሁ:: ገና አልነጋም እኮ! በዚያ ላይ ብርዱ:: በዚያ ላይ የእንቅልፉ መጣፈጥ:: ቢለኝ

በ.ሠራኝ፥ "አሬሣ ምስጋና ይጣ" እሆንበታለሁ:: እንደ ወለጋድኩ ሲገባው፥ ወይም ከልጅ ጋር እልህ ላለመጋባት ሲል፥ ወይም እሳዝኜው፥ እላውቅም፥ እኔን ይተወኝ እና እናቴን "ይህን ጋንድያሽን ቀስቅሽውና ቤተ ክርስቲያን እንዲመጣ" ብሏት ይወጣል:: ይህን ጠባዬን በዲቁና ማገልገል ስጀምር ነው የተውኩት::

እስከ ምን ድረስ እንደ ሆነ አላወቅሁም እንጂ፥ አባታችን የቤተ ክህነት ትም ህርት እንደ ተማረ እና በልጅነቱም በዲቁና እንደ አገለገሰ ዐውቃለሁ:: እንድ ጊዜ አብረን መንገድ ስንሄድ አብርሃም ቀድሞ ጣዖት ጠራቢ እንደ ነበረ፥ አንድ ቦን ግን የፀሓይን ጣዖት እየጠረበ ሳለ፥ ፀሓይ አራስዋ ፍጡር መሆንዋ ታወ ሰውና፥ "አምላከ ፀሓይ! ተናገበበኒ!" ብሎ እንደ ጸለየ ነገረኝ:: (የፀሓይ አምላክ! ተናገረኝ! ማለት ነው::) ከዚያም አግዚአብሔር ተገለጠለት እና ተናገረው:: በዘፍጥረት 12፥1-3 ላይ ያለውን መሆኑ ነው::

በለሊ ጊዜ ደግሞ አግዚአብሔር መላእክቱን ሊፈትናቸው ፈልጎ እንደ ተሠወረ ባቸው ነገረኝ:: መላእክቱ ግራ ተጋቡ:: ሳጥናኤልም በአጋጣሚው ለመጠቀም ፈልጎ "አምላካችሁ እኔ ነኝ" አላቸው እና ከመላእክቱ ሲሦው እውነት መስ ሎአቸው ሰገዱለት:: ገብርኤል ግን ተነሥቶ "ንቁም በበጎላዌነ፥ አስከ ንረከበ ለእምላከነ" አላቸው:: (አምላካችንን አስከምናገኘው ድረስ በየማንነታችን/በያለ ነበት እንጽና ማለት ነው::) በዚህም ንግግሩ ከሥስቱ አጅ የመላእክት ሠራዊት ውለቱን አጅ (ራሕ. 12፥4) ከስህተት አዳናቸው አለኝ:: የአብርሃምን እና የገብርኤልን ንግግር በግዕዙ ነው የነገረኝ:: አብርሃም እና መላእክቱ፥ አግዚአብሔር እራሱም ሳይቀር፥ የሚነጋገሩት በግዕዝ ቋንቋ ነበር የሚመስለኝ::

በመስከረም ወር 1953 ዓ.ም. ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወደ ጅማ ስሄድ፥ እንጓዝበት የነበረው አቶቡስ አበልቲ ላይ ይመስለኛል ለምሳ ይቆማል:: ከአቶቡሱ አብረውኝ ከወረዱት መንገደኞች አብዛኞቹ ወደሚገቡበት ሆቴል ተከትያቸው ገባሁ:: የነበረው ምሣ የዶሮ ወጥ ብቻ ነበር:: ተገኝቶ ነው? በጊዜው ከነበሩት ለስላሳ መጠጦች በአንዳቸው (ምናልባት አረንቻታ?) ማወራ ረጃነት፥ እጅግ ጣፍጦኝ በላሁት:: ወደ አቶቡሳችን ተመልሰን ጉዞ ልንጀምር ስንዘጋጅ፥ መንገደኞቹ ስለ በላነው ምሣ ጨዋታ ጀመሩ:: በጨዋታቸውም መካከል በከርስቲያኖቹ ከፍል የተለያየ ዐይነት ምግብ እንደ ነበረ፥ ሙስሊሞቹ ከፍል ግን ከዶሮ ወጥ በስተቀር ሌላ እንዳልነበረ ሲያነሡ ሰማሁ::

ጆሮቼ እየሰሙ ያሉትን ለማረጋገጥ፥ ከእኔ ጋር የበሉትን ሰዎች በዐይኖቼ ቃኘኋቸው። እውነትም በመሐላቸው ቆብ የደፉ እና የጠመጠሙ ነበሩባ ቸው። ሆኖም ቆቡ እና ጥምጥሙ የእኔዎቹ የሚደፉት እና የሚጠመጥሙት ዐይነት አልነበረም። የበላንበት ሆቴል ሁለት የመግቢያ በሮች እንደ ነበሩት፥ እንደኛው ክርስቲያኖች ሁለተኛው ሙስሊሞች የሚገቡባቸው እንደ ሆኑ ያለተ ዋልኩትም ከዚህ በኋላ ነው። ያለ ጥርጥር የሙስሊም ዶሮ ወጥ በልቻለሁ ማለት ነው። ያ ቅድም እንደዚያ እየጣፈጠኝ የገባው ዶሮ ወጥ፥ በገባበት ፍጥነት ካልወጣሁ ብሎ ተናነቀኝ። በብዙ ትግል፥ በሎሚ አረዳትነት ነው ለጊዜው ከመዋረድ የዳንኩት። ነገር ግን ጅማ ደርሼ፥ ቄስ ተዋወቁ፥ መጽሐፈ ቄደር አስከምጠመቅ ድረስ አግዚአብሔርን ዕድሜ እንዲለጠኝ ለመንኩት።

ክልቤ ነበር። ከዚህ በፊትም አንድ ጊዜ ይህንን የሚመስል አንድ ነገር አድርጌ አለሁ። በፍልሰታ ወቅት፥ አንድ ቀን ጠዋት ኪዳን አድርሼ ወደ ቤት በመመለስ ላይ እያለሁ፥ እንዲት ክልፍልፍ ዝንብ አንድ "ክፍት እፍ" ውለጥ ገባች። እጅግ አዘንኩ። ስድስት ሰዓት ገደማ ላይ ለቅዳሴ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስመለስ -

"ዛሬ ቅዳሴ አልገባም፥ ሌላ ዲያቆን ይፈልጉ" አልኳቸው ገባሬ ሠናዩን ቄስ።

"ለምን?" አሉኝ።

"አይ፥ እሱን አሁን አልነግርዎትም፤ ዛሬ ግን ቅዳሴ አልገባም" አልኳቸው። እርሳቸው ደግሞ "ካልነገርከኝ" ብለው ውጥር አደረጉኝ። አንደማይለቁኝ ሳው ቀው ነገርኳቸው። ምንም አላሉኝም፤ በጥያቄዬ መሠረት ሌላ ዲያቆን እንዲ ተካኝ ብቻ አደረጉ።

አለማወቅ፥ አይደበቅ

"ጅማ እርሻ ቴክኒክ ትምህርት ቤት" በነበርኩ ጊዜ ሚስተር ኢቫንስ የሚባል የፊዚክስ አስተማሪ ነበረን። እሜሪካዊው መምህራችን ስለ ኤሌክትሪክ ኃይል ሲያስተምረን፥ በዝናብ ወቅት መብረቅ እንዴት እንደሚፈጠር ነገረን። እኔም ክስተር ብዬ -

"እንደዚያማ ሊሆን አይችልም" አልኩት። ሚስተር ኢቫንስ አልተቆጣም። ረጋ ብሎ -

"ለምን?" አለኝ።

"ሙበረቅ የሚጥሉት አባታችን አቦዬ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው" አልኩት። አሁን በመገረም ሊመለከተኝ የጀመረው እርሱ ብቻ ሳይሆን፥ የክፍሉ ተማሪ ዎች ሁሉ ነበሩ። በዚያ የነበርነው ተማሪዎች የመጣነው ከዐሥራ አራቱም ጠቅላይ ግዛቶች ነው። እና የእኔን ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ዳራ የማይጋሩ ተማሪዎች ነበሩ። ባለ ተመሳሳይ ዳራዎቹን ያሰገረማቸው ግን ድፍረቴ መሆን አለበት።

"ያልካቸው አባታችሁ መብረቁን እንዴት እንደሚጥሉት አበክሀን ንገረን" አለኝ።

የፊለቀች ልጅ ከእናቴ የሰማሁትን ሱፐርስቲሽን በልበ ሙሉነት ነገርኩት። "ሰይጣን ዛፍ ወይም ሰው ሥር ይሸሸጥ እና በአቦዬ ላይ ምላሱን ያወጣባ ቸዋል። በዚህ ጊዜ አሳቸው ይናደዱ እና መብረቃቸውን ያምዘገዝገቡታል።"

ለእኔ ይሽ ተረት ተረት (MYTH) ሳይሆን፥ እውነት እውነት ነበረ። በዕድሜዬም እኮ ይህንን ያህል ልጅ አልነበርኩም፤ ዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ሆኖኛል። እንደዚህ ያሉ ሌሎች ብዙ ተረቶችንም ዐውቃለሁ። ተረቶቹም ሲያንስ ከማዝናናት፥ ሲበዛ ደግሞ እያዝናኑ ከማስተማር ያለፈ ፋይዳ እንደ ሌላቸውም ዐውቃለሁ። ይሽኛው ግን እንደዚያ አይደለም። ይሽኛው ለእኔ እውነት ነበረ። ሃይማኖቴ ነበረ።

ሚስተር ኢቫንስ መጀመሪያ ላይ የአእምሮዬን ጤንነት ሳይጠራጠር የቀረ አይ መስለኝም። ሆኖም ይህንን ነገር የበለጠ እንዳብራራለት ጥያቄ እየጠየቀኝ እና እኔም እየመለስኩለት ሁሉንም ክለማው በኋላ፥ ነገሩ የዕብደት እንደ አልሆነ ገባው። ወደ አፍሪቃ ለመሄድ ክአገሩ ሲነሣ ስለ ኋላ ቀር ባህላቸው የተለጠው መጠነኛ ሥልጠና ትክክለኛ ለመሆኑ በዚያች ዕለት ማሩም የሆነ ማለረጃ አገኘ - ከእንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የፊዚክስ ተማሪው። እኔም ብሆን አድሬ ውዬ፥ "እሺ፥ ግን ለምንድነው እቦዬ እና ሰይጣን ይህንን ድብብቆሽ የሚጫወቱት በዝናብ ወቅት ብቻ የሆነው?" ብዬ እራሴን ለመጠየቅ ችያለሁ።

በ1955 ዓ.ም. ክዕለታት አንድ ዕሑድ ቀን፥ በጅማ የእርሻ ቴክኒክ ትምህርት ቤት የለብስባ አዳራሽ ውስጥ ብርቱ የሆነ የሃይማኖት ክርክር ተደረገ። ለክርክሩ መነሻ የሆነው በዚያን ወቅት የተለያዩ ሃይማኖቶች ወደ ጅማ እና ወደ

ትምህርት ቤታችንም መማሪያ መጀመራቸው ይመስለኛል። ጴንጤቆስጤአ ዊው የስዊድን ፈላደልፊያ ሚስዮን በ1953 ዓ.ም. ወደ ጅማ መጣ። በዕቅድ ይሁን ወይም በአጋጣሚ አላውቅም፥ ሚስዮናውያኑም መኖሪያቸውን በትምህ ርት ቤታችን አካባቢ አደረጉ። የትምህርት ቤቱ ባልደረባ የነበረው ወንድም ሰለሞን ሉሉ በ2003 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ የዳግም ልደቱን 50ኛ ዓመት በቤዛ ኢንተርናሽናል ቤተ ክርስቲያን ባከበረበት ወቅት፥ በአነዚያ ሚስዮናዊያን ቤት ስብሰባ መካፈል ጀምሮ እንደ ነበረ ሊመሰክር ስምቼዋለሁ። ስክርክሩ መነሣት እንደኛው ምክንያት ሳይሆን አይቀርም።

ሁለተኛው ምክንያት የይሖዋ ምስክሮች እና ባሃኤዎችም ወደ ጅማ የገቡት በዚያው ጊዜ መሆኑ እና ከተማሪዎቹም እንዳንዶቹ እነዚህን አዳዲስ እምነቶች መከተል መጀመራቸው ይመስለኛል። ስብሰባውን ግን እንደ ጠራ ወይም ማን ሲመራው እንደ ነበረ አላውቅም። ነገር ግን ጥሪ ሳይተላለፍ ያ ሁሉ ተማሪ፥ በዕሑድ ቀን፥ እንዴት በአዳራሹ ውስጥ ሊገኝ ይችላል? ከዚያ በኋላም በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሃይማኖት ስብሰባ ማድረግ ፈጽሞ ስለ ተከለከለ፥ አስተዳደሩም ምናልባት ያንን ስብሰባ የጠራ እና ይመራም የነበረ አካል መኖሩን ደርሰበት ይሆናል። አርቶዶክሶች፥ ካቶሊኮች፥ ፕሮቴስታንቶች፥ አድቬንቲስቶች፥ የይሖዋ ምስክሮች እና በሃኤዎች በክርክሩ ንቁ ተሳታፊዎች ነበሩ።

በቁጥር የምንበዛው አርቶዶክሶቹ ስንሆን፥ ዋነኛው አፈ-ቀላጤአቸውም እኔው ነበርኩ ማለት እችላለሁ። ቅዳሜ ለዕሑድ አጥቢያ ከሌሊቱ 10:30 ላይ - ክአባቴ እንደ ተማርኩት - በየዶርማቸው እየዞርኩ፥ ሁሉንም ከእንቅልፋቸው እቀሰቅሳቸዋለሁ። ተጣጥበን እና ልብሳችንን ስብሰን፥ በላዩም ነጠላችንን አጣፍተን፥ በአቅራቢያችን ወደሚገኘው የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን እንሄዳለን። በበኩሌ ስሃይማኖቴ የቀናሚነት፥ የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት እና የኩራትም መንፈስ ይሰማኛል። ክቅዳሴ ውጭ ከዚያ ስንመለስ ደግሞ ቁርሳችንን በልተን፥ እንዳንዶቻችን ሚያዝያ 27 ትምህርት ቤት ወደሚካሄደው የ"ሃይማኖተ አበው" ስብሰባ እንሄዳለን። በትምህርት ቤታችን ውስጥ ሙስሊሞች ተማሪዎች የነበሩ ቢሆንም፥ በዚያን ዕለቱ ክርክር ውስጥ እንዳቸውም አልተሳተፉም።

ነበርክሩ የጦፈ ነበር። አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝ ኖሮ፥ ያን ዕለት በበኩሌ ምንም ክማ ድረግ - እስከ መሞትም ሆነ እስክ መግደል ድረስ - የምመስስ አይመስለኝም። በነዚርክሩ ላይ ክእኛ ክአርቶዶክሶቹ በስተቀር፥ ሁሉም - ባሃኤዎቹም እንኳን ሳያቀሩ - ክመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳሉ። እኛ የሆነ ነገር ለመጥቀስ ስንሞክር፥ "ዮነ ነው እንደዚያ የሚስው?" እንባላለን። በእኛ መካክል እንኳን ጥቅስ መሥገር የሚችል፥ መጽሐፍ ቅዱስ የያዘም ሰው አልነበረም።

በኋላ እንደ ተረዳሁት፥ ስመጥቀስ የምንሞክረውም ነገር መጽሐፉ ውስጥ የለም። ቢኖርም በተረታ-ተረቱ መጻሕፍት ውስጥ ነው ያለው። በመጮኽ እና እንዲያው ዝም ብሎ በመንጫርጫር የሆነ እንደ ሆነ ግን የሚያከለን አልነበረም። ለእኔ ያ ዕለት የእምነቴ መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን እና እኔም መጽሐፍ ቅዱሱን ጨርሶ የማላውቀው መሆኔን የተረዳሁበት ነበር። ዐፍሬ እና አዮርቅሬ ነበር ክአዳራሹ የወጣሁት። ስለዚህም "መጽሐፍ ቅዱስ" የሚባለውን መጽሐፍ ማግኘትን እና ማንበብን የመጀመሪያው ተግባሬ እደረግሁ።

ሳያምኑት ይክዱታል?

ልብ ወለድ መጽሐፍ እኑብ እንደ ነበረው ነው.መጽሐፍ ቅዱሱንም ስማንበብ ሃጀመርኩት - ክመጀመሪያው ገጽ። ሆኖም የመጀመሪያውን ምዕራፍ እንብቤ ሳልዘልቀው በፊት ነበር የተሰናከልኩበት። ያሰናከለኝም ብርሃን የመጀመሪያው ሦን፥ ፀሓይ ግን የአራተኛው ቀን ፍጥረት የመሆናቸው ነገር ነው።

"ይኽ እንዴት ያለው መጽሐፍ ነው እባካችሁ? ፀሓይ ሳትፈጠር ብርሃን ተፈ ጠረ ይለኛል እንዴ?" በማለት ነበር መገረሜን የገለጽኩት - ጮክ ብዬ። "ለካ በጤናውም አይደል ለዚህ ሁሉ የተለያየ ሃይማኖት መፈጠር ምክንያት የሆነው" ብዬም አሰብኩ። ካቶሊክ፥ አርቶዶክስ፥ እድቬንቲስት፥ የተለያዩ የፕሮ ቴስታንት ሃይማኖቶች፥ የይሖዋ ምስክሮች፥ ሁሉም ይህንኑ አንድ መጽሐፍ ነው የሚያምኑት። ከአንድ መጽሐፍ እንዴት ይህ ሁሉ ሃይማኖት ይወጣል?

ከኦሪት ዘፍጥረት 1፥19 አልፈ ማንበብ አላስፈለገኝም። መጽሐፉን የሁሉ የሆነች ሴት በምትጠራበት ሰም ጠራሁት። ክዚያ በኋላማ ቀደም ሲል ልብ ሳልላቸው ያሳስፍኳቸው አንዳንድ ነገሮችንም ማስታወስ ጀመርኩ።

ከሀነት ሰቀበል ቢበዛ የሰባት ዓመት ልጅ ብሆን ነው። የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ለቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ "አሁን ይህቺ ምን ታውቃለች

ብላችሁ ነው ያመጣችኋት?" አሉ። አስተማሪዎቼም "ብፁዕ አባታችን፥ እኛ ምንም እንልም፤ እርስዎ ይፈትኗት እና ዪዩዋት" አሏቸው። የማነብበው የሆነ መጽሐፍ፥ ከማነብበት ቦታ ላይ ተገልጦ ተሰጠኝ። አፈን የያዘኝ አልመሰለ ኝም። ጥቂት እንዳነብብኩ፥ "በቃሽ" አሉኝ። ከዚያ በኋላ ፈተና የተሰጠው ማንም ዕጩ አልነበረም።

ከህነት አንዲቀበሉ ተመርጠው ከእኔ ጋር የመጡት ሁሉ እኔ በታየሁበት ዐይን ታይተው ሁላችንም ተካንን። ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ "ያችን ትንሽ ተማሪ ሰጡኝ እና ወስጀ ላሳድጋት" ብለው ነበር ሊባል ለምቻለሁ። እናቴ፥ አሁን መጨረሻ ላይ የሆንኩትን ካየች በኋላ፥ "መልእከተኞቻቸውን አልቅሼ ለምኛ ቸው ነው ያን ጊዜ ያስቀረሁህ፤ እንዲህ አሁን ላይቀርልኝ" ብላኛለች። የደስ ደስ በቤታችን ጠላ ተጠምቆ፥ ዳቦ ተጋግሮ፥ በግ ታርዶ እና ድግስ ተደግሶ፥ ተበላ እና ተጠጣ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ አባቴ ማታ ማታ እቤት ሲገባ "ምሥጢር አሳዩህ ወይ?" እያለ ሊጠይቀኝ ጀመረ። ምሥጢር የሚባለው ነገር የሚታየው በቤተ ልሔም እና በመቅደስ ውስጥ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ። ምክንያቱም እኛ ምሥጢር ያላየ ነው ተማሪዎች መግባት የማንችለው ወደ እነዚህ ሁለት ቦታዎች ብቻ ነበር። በቤተ ልሔም ውስጥ ደግሞ ዘንዶ እና ነብር አሉ የሚባል ወሬ በእኛ በተማሪዎች መካከል ይናፈሳል። እስከ ዛሬ ድረስ ግን በዘንዶ ወይም በነብር ስለ ተበላ አንድም ሰው አልሰማንም። እውነት ቢሆን፥ አባቴ ለምን በየቀኑ "ምሥጢር አሳዩህ ወይ?" እያለ ይጠይቀኛል? መቼም በእነዚህ አራዊት አንድበላበት ቀርቶ፥ እንድደነግጥበትም እንደማይፈልግ እርግጠኛ ነኝ።

"የለም፥ አላሳዩኝም" አለዋለሁ።

"ለምን አያሳዩህም? ቆይ፥ ለመምሬ ኃይለ ማርያም እነግራቸዋለሁ" ይላል። መምሬ ኃይለ ማርያም የነፍስ አባታችን ናቸው።

በስንት ዓመቱ ምሕረት እንደ ሆነ አላውቅም፤ ለአስተርእዮ ማርያም (ጥር 21) ምሥጢር እንደማይ ተነገረኝ። በዕለቱ በጣም በማለዳ ደብረ መንክራት ተክለሃይማኖት ገዳም ስደርስ፥ ቀሳውስቱ ሁሉ ወደ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስለ ሄዱ፥ ከመምሬ ኃይለ ማርያም በስተቀር ሌላ ቄስ በሰፍራው አልነበረም። መቼም በዕለተ አስተርእዮ፥ ያውም በተክለሃይማኖት ገዳም፥ ቄስ ጎደለ ተብሎ

ጉዳሴ ሊታጎል አይችልም። ስለዚህ እኔው ወደ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሄጀ ለአባ መላኩ (በኋላ አባ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ) አንድ ቄስ እንዲልኩ እንድነግራቸው ተላከሁ።

የነደለው ተሚልዶ የቅዳሴውን ቅድመ ዝግጅት ለማጠናቀቅ ወደ ቤተ ልሔም ስንሄድ፥ የቤተ ልሔሙ በር ክፍት ነበረ። ሆዴን ፍርሃት ፍርሃት አለው። ወደ መምሬ ኃይለ ማርያም ተጠጋሁ። እርሳቸው ደግሞ ገና ከሩቅ እያለን ድምፃ ቸውን ከፍ አድርገው፥ "ኧረ በሩን ዝጉት!" አሉ እና በፍርሃቴ ላይ ፍርሃት ጨመሩብኝ። የበለጠ ተጠጋኋቸው። ወደ ልብሰ ተክህኗቸው ውስጥ ተወሸ ቅሁ። ቤተ ልሔሙ በር ላይ ስንደርስ ደቆን "ሳም" አሉኝ። ጎንበስ አልኩ እና ሦጨሞጭኩት። ቀጠሉናም "ተፈሥሂ አ ቤተ ልሔምን ድገም" አሉኝ። ሰያዙኝ ኮሰተር፥ ቆጣ እና ፈጠን እያሉ ነበር። ወትሮ የማውቃቸው ለው እለመስልህ አሉኝ። እኔም ድምፄን ከፍ አድርጌ "ተፈሥሂ አ ቤተ ልሔም" ብዬ በመጀመር ድግሙቴን እንበሰበልኩት።

ስንገባ በሁለት ትልልቅ ምድጃዎች ላይ የወይራ ፍልጥ ይንቀለቀላል። እኛ ከገባንበት በር በተቃራኒው በኩል፥ የማውቃቸው ብዙ ትልልቅ ሰዎች ፊታቸ ውን እኛ ወደ ገባንበት ወደ በሩ መልሰው፥ መደዳውን ተቀምጠዋል። የጠዋቱን ብርድ እየተከላከሉ መሆናቸው ነው። ምድጃዎቹ ያሉት በእነርሱ እና በእኛ መካከል ነው። መምሬ ኃይለ ማርያም "በል ወደ እነርሱ ሂድ" አሉኝ - በሚንቀለቀለው እሳት ውስጥ መሆኑ ነው። የማውቀው የ"ሠለስቱ ደቂቅ" ስዕል ሳይታየኝ አልቀረም። ቀና ብዬ "እውነትዎን ነው እንዴ?" በሚል ዐይን እየኋቸው። በቃላቸው አልመለሱልኝም፤ ግን እውነታቸውን እንደ ሆነ በሁኔታቸው እንዳውቀው አደረጉኝ።

ዐይኖቼን ከእርሳቸው ላይ አንሥቼ በዚያ ወደ ተቀመጡት ወደ ሌሎቹ ተመለከትኩ። ሁሉም ኩስትር አሉብኝ። በመጨረሻም በተለይ ወደ አባ ካሣ ተመለከትኩ። ለምን እንደ ሆነ እንጃ እንጂ፥ አባ ካሣ በጊዜው በዎላይታ ሶዶ ካሉት ካህናት ሁሉ በጣም የተከበሩት ይመስሉኛል። ጥምጥማቸው አራሱ ከሌሎቹ ካህናት ጥምጥም ይሰያል። በሥርዓት የተጠቀለለ እና በጣምም ረዥም ነው። በልብሳቸው ላይ ሁል ጊዜ ካባ ይደርባሉ። የሆነ ግርማ ሞገስ አላቸው። አባ ካሣም ልከ የሌሎቹን ዐይነት ፊት አሳዩኝ።

እንግዲያው "በቃ፤ መሆን ያለበት ነገር ነው ማለት ነው" ብዬ አሰብኩ። ምድጃው ሰፊ ስለ ሆነ፥ የእሳቱ ወላፈን ሳይገርፈኝም ሆነ የተንተረከከውን የወይራ ፍልጥ ፍህም ሳልረግጥ የምሻገርበት ምንም ዐይነት መንገድ አልነ በረኝም። አንዱን እግሬን አኑሣሁ እና ስዘረጋው፥ መምሬ ኃይለ ማርያም እጇን ለቀም አደረጉ እና በኃይል ወደ ኋላ መነጨቁኝ። ለጥቂት ከእሳቱ ተረፍኩ።

ቤተ ክርስቲያኗ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 17፥17 ላይ የተጠቀሰውን፥ በቀኃሥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም "ልጆችን በእሳት ማላለፍ" የተባለ የጣዖት እምልኮ፥ ትለማመድ ነበር ማለቴ አይደለም። በሁሉም ቦታ እንደዚያ የሚደረግም አይመ ስለኝም። በዚያም ቦታ ቢሆን፥ በሌላ ጊዜ እንደዚያው ላይደረግ ይችላል። ይኸኛው እንዲያው ቀልድ (FUN) ነበር። ታላላቆች ለዎች በአንድ ትንሽ ልጅ ላይ - ያውም በእግዚአብሔር ቤት - የቀለዱት መጥፎ እና አላስፈላጊ ቀልድ። ያንን ድርጊት በጊዜው የተረዳሁት፥ ዛሬም የምረዳው፥ "ቀልድ" እንደ ነበረ ብቻ ነው።

ቀልዱ እንደ አበቃ፥ በአንደኛው ምድጃ ላይ ትልቅ የገበር ምጣድ ተጣደ። በሁለተኛው ላይ ደግሞ በአከንባሎነት የሚያገለግል (በእጭሩ ተደርጎ ከተቀረጠ የበርሜል ክዳን የተሠራ ይመስለኛል)፥ ሙቀቱን ማቆየት እንዲችል ከጀርባው ላይ አፈር እና ዐመድ ይመሰሉኛል በወፍራሙ የተደበደቡበት፥ ለማንሣት እና ለማስቀመጥ እንዲያመች ደግሞ መያዣ የተበጀለት፥ ሌላ ዕቃ ተደፍቶ ተጣደ። ምጣዱ "ጽዱት"፥ አከንባሎውም "መድፍ" እንደሚባል ተነገረኝ። በኋላ እንደ ተረዳሁት አነዚህ በማዕዙ የዕቃዎቹ ስያሜዎች ናቸው።

ቤተ ልሔም የሚባለው ቤት ለጌታ እራት (ቅዱስ ቁርባን) የሚውለው ኅብስት እና ወይን የሚዘጋጁበት ቦታ ነው። "ቤተ ልሔም" የተባሰበት ምክንያት መለኮት የሆነው አምላክ፥ ለው (ሥጋ እና ደም) ሆኖ የተወለደባት ከተማ "ቤት ልሔም" ትባል ስለ ነበረ መሆን አለበት። ጽዱቱ እና መድፉ ኅብስቱን መጋገሪያ ናቸው። በጋሰው ጽዱት ላይ፥ የቡኸው ሙልሙሎች ከተደረጉ በኋላ፥ የጋለው መድፍ ይደፋብታል፤ በቃ።

በትልልቅ ከተሞች ውስጥ ባሉ የአርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት "ምሥጢር" የሚባለው ነገር ዛሬም ይኖር እንደ ሆነ እርግጠኛ አይደለሁም። ምክንያቱም ምንም አስፈላጊነት የለውም። ኅብስቱ በኤሌክትሪክ ወይም በጋዝ በሚሠራ

ምድጃ (OVEN) ሊጋገር ይችላል። ቤተ ልሔም ማለት የቤተ ክርስቲያን ወጥ ቤት (KITCHEN) ማለት ብቻ ነው። እና ነገሩን ሁሉ ማመሠጣጠር (MYSTIFY ማድረግ) ይቀራል።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ለጥምቀት በዓል እንድናገለግል በገንዘብ ተገዝተን መምሬ በቀለ የሚባሉ እንድ ቄስ እና እኔ ወደ አንድ የገጠር ቤተ ክርስቲያን ሄድን። ሦዙን ሰው ደብተራ ቸርነት ይባላሉ። የተነጋገሩት ከእናቴ ጋር ስለ ሆነ፥ በስንት ብር እንደ ገዙኝ አላወቅሁም። ብቻ ከአንድ ጠገራ ብር የሚበልጥ እያመስለኝም። የክተራ ዕለት (ጥር 10) በጠዋቱ ከሶዶ ተነሥተን እና ስንጓዝ ውሰን፥ ከቀኑ 10:00 ሰዓት ገደማ ከቦታው ደረስን። ሕዝቡ ተሰባስቦ ታቦት እስኪወጣ ድረስ ይጠብቃል።

እኔ በዚያ አገልግሎቴ ወቅት ታቦት ምን እንደሚመስል ለማየት በልቤ እስቤአ ለሁ። ዲያቆን ታቡቱ ወደሚቀመጥበት ወደ መንበሩ መቅረብ አይፈቀድለ ትም። ቄሱ መንበሩ ላይ እያገለገለ ባለበት ጊዜ፥ ዲያቆኑ በልብሰ ተከህኖው እንኳን የቄሱን ልብስ ተከህኖ እንዳይነካ የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። ሙቼም ሰው በባጋርዩ የተከለከለ ነገር ከልከ በላይ ትኩረቱን የሚሰብበት ፍጡር እንደ ሆነ ይታወቃል። ያ የገጠር ቤተ ክርስቲያን ስለ ሆነ እና እኔም ከከተማ የመጣሁ ዲያቆን ስለ ሆንኩ፥ በዐይኔ ታቦት ለማየት ያለኝ ዕድል ያን ሖን ነው ብዬ ወሰኛለሁ።

ቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳው የእንጨት እና የጭቃ፥ ጣራው ደግሞ የሣር ነው። ከውጭ ተመርጎ እና ተለስኖ እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል። ከውስጥ እንዲት እንደ ነበረ ግን የዚያን ያህል ትዝ አይለኝም። መምሬ በቀለ መንበሩ ላይ እያደረጉት ከነበረው ነገር ድንገት መለስ አሉና "ጎበዝ፥ ተዋረድን!" አሉ። በጊዜው ከመምሬ በቀለ ጋር በመቅደሱ ውስጥ እንድ ሌላ ቄስ እና ሁለት ዲያቆናት የነበርን ይመስለኛል።

ሁላችንም ደንገጥን። ሌላው ቄስ ይመስሉኛል "ምነው መምሩ?" ሲሉ ጠየቁ።

"ጽላቱ መንበሩ ላይ የለም" አሉ መምሬ በቀለ። እሁን ከማንኛቸውም በላይ የደነገጥኩት እኔ መሆን አለብኝ። ጽላቱ ከመንበሩ ላይ ተነሥቶ የት ይሄዳል? ግራ የሚገባ ነገር ነው እኮ! መምሬ በቀለ -

"ቶሎ ደብተራ ቸርነትን ፈልጉልኝ" አሉ። በዚያ ከነበርነው ሁለት ዲያቆናት የአካባቢው ልጅ የሆነው፥ ልብሰ ተክሕኖውን አውልቆ አስቀምጦ ደብተራ ቸርነትን ፍለጋ ወጣ። ብዙም ሳይቆዩ ፈላጊው እና ተፈላጊው ተከታትለው ገቡ። መምሬ በቀለም ያጋጠማቸውን እንግዳ ነገር እኛ እየሰማን ለደብተራ ቸርነት ተናገሩ። ደብተራ ቸርነትም ምንም ሳይደናገጡ -

"አይ መምሩ ... ሞኝ ነህ ለካ! ... የባላገር ታቦት መቼ መንበር ላይ ያድራል?" አሉ። አሁን ደግሞ የበለጠ ደነገጥኩ። ታድያ የት ነው የሚያድረው? ምን ጉድ ነው ዛሬ በጆሮቼ የምሰማው? ደብተራ ቸርነት አሁንም ቀጠሉና -

"ሌባው መች ያሳድረዋል?" አሉ። ከዚያም ወደ አንድ ጥግ ሄደው በግድግዳው እና በወለሉ መካከል ካለ አንድ መጋጠሚያ እጃቸውን ሰደዱት። እንደ አይጥ ጉድጓድ ከሚመሰል ሥርቻ ውስጥ፥ በግምጃ የተጠቀለለ ነገር አውጥተው ለመምሬ በቀለ ሰጡአቸው እና ወጥተው ሄዱ። ዐይኔን ማመን አልቻልኩም። በዚህ መሐል ታቦት ለማየት ያደረግሁትን ውሳኔ የረሳሁት ይመስለኛል። መምሬ በቀለ የሚያደርጉትን ነገር አድርገው ታቦቱን አከበሩ ("አከበሩ" ነው እንጂ "ተሸከሙ" አይባልም) እና ልንወጣ ስንል፥ ደብተራ ቸርነት ድንገት የሆነ ነገር እንደ ረሳ ሰው በችኮላ ወደ መቅደሱ ገቡ። እንደ ገቡም ዐይናቸውን መምሬ በቀለ አራሰ ላይ ተከሉ እና -

"አይ፥ አይ፥ መምሩ፥ አይሆንም፥ አይሆንም" አሉ። ደግሞ ምን ተፈጠረ ይሆን? በዚያ የነበርነው ሁላችንም ደብተራ ቸርነት "አይ፥ አይሆንም" ያሉበትን ምክንያት እስኪናገሩ ድረስ ጠበቅናቸው። እርሳቸውም የሚከተለውን አጭር ማብራሪያ ብቻ ለመምሬ በቀለ ሰጡአቸው - "ባላገር ትንሽ ታቦት አይወድም።" መምሬ በቀለ መልእክቱ ገብቷቸዋል ማለት ነው፤ ሌላ ምንም ጥያቄ አላቀረቡም። ወዲያው ታቦቱን ከራሳቸው ላይ አውርደው፥ ቦተጨማሪ ግምጃዎች በመጠቅለል የማተለቅ ሥራ ከሠሩበት በኋላ እንደገና "አከብረውት" እየጠበቀን ወደ ቆየው ሕዝብ ወጣን።

በልጅነት አእምሮዬም ቢሆን፥ እነዚህ ገጠመኞች ጤና አልሰጡኝም። የመጀመሪያውን "ብርቱው ሰው አራሱን በደካማው ድካም የሚያዝናናበት" ገጠመኝ ብዬ ብተወው እንኳን፥ ነፍስ ካወቅሁ በኋላ ግን እንዴት አድርጌ በታቦት እያመንኩ፥ ታቦት እያከበርኩ፥ ለታቦት እየሰገድኩ፥ እነዚያን ሁሉ

ኅሙታት እንደ ኖርኩ አላውቅም። በጊዜው ቃሉ በእኔ ዘንድ ታዋቂ ያልነበረ በ.ሆነም፥ "አከራሪ" ስለ ነበርኩ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው። "አከራሪ" (FANATIC) ማለት በራሱ እምነት ውስጥ ያለው፥ ያፈጠጠው እና ያዝጠጠው፥ ሰህተት ሁሉ ጨርሶ የማይታየው ሰው ማለት አይደል? በመላው ኅለም እርሱ እና የእርሱ የሆኑት ብቻ ትክክል ሆነው፥ ሌላው ሁሉ የተሳሳተ የሚመስለው ሰው አይደል - አከራሪ?

ያለፈውሰ ዐለፈ፤ የሆንኩትን ሁሉ የሆንኩት ባለማወቅ ነው ልበል። ከእንግዲህ በኑላ ግን እንዴት አድርጌ ነው እንደ ቀድሞዬ የምቀጥለው? እስከ መቼ ነው ትክክል እንዳይደለ የተረዳሁትን ነገር፥ ይሉኝታ በመፍራት ብቻ፥ ተሸክሜው የምጓዘው? ወይም "የአበቶቼ" በሚል ግብዝነት ታቅፈው የምኖረው? እሰከ መቼ ነው ያይደለሁትን እየሆንኩ፥ እራሴን እያታለልኩ ወይም ከራሴ ጋራ እየተጣላሁ የምኖረው? ከእንግዲህ በኋላ መጽሐፍ ቅዱሱን መጽሐፍ ቅዱሴ፥ የመጽሐፍ ቅዱሱን እግዜር እግዜሬ፥ የመጽሐፍ ቅዱሱንም ከርሰትና ከርሰትናዬ ለማድረግ ምን ምክንያት ቀርቶኛል?

እንደ እነዚህ ካሉት ጥያቄዎች ጋር እየታገልኩ የቆየሁት ለምን ያህል ጊዜ እንደ ነበረ በትክክል አላሰታውሰም። ለብዙ ወራት ግን አልነበረም። በዚያው ዓመት መጨረሻ ላይ ነው፥ "ከዛሬ ጀምሮ በቃኝ" ያልኩት። እንዲህ በቶሎ ውሳኔ ላይ እንድደርሰ ውጣትነቴም ሳያግዘኝ አልቀረም። ባጭሩ በ1955 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ከሃዲ ሆንኩ። ቀድሞውንም የማላውቀውን እና ሰለዚህም የማላምነውን መጽሐፍ፥ ቀድሞውንም የማላውቀውን እና ሰለዚህም የማላምነውን እግዚአብሔር፥ ቀድሞውንም የማላውቀውን እና ሰለዚህም ያልተቀበልኩትን የከርሰትና እምነት፥ አወለቅሁት እና ጣልኩት። ኋላ ላይ ከሃዲነቴን ያወጅኩበት መንገድ ደግሞ አላዋቂነቴን የበለጠ ያወቅሁበት እና ያሰታወቅሁበት ሆኖ አገኘሁት።

ዓርብ ዕሮብ

በዚያም ዓመት ትምህርት ቤት ሲዘጋ ወደ ቤተ ሰቦቼ አልሄድኩም። ላያቸው ብናፍቅም እንኳን፥ እናቴን "ለትራንስፖርት ገንዘብ ላኪልኝ" ላለማለት ሰል፥ ዘንድሮንም እዚያው ከርሜአለሁ። ትምህርት ቤታችንም በተማሪዎች የሚያሠራው የከረምት ሥራ አለው። የእርሻ ትምህርት ቤት አይደል? በጣም ሰፊ የእርሻ መሬት አለን። ከረምት ደግሞ የእርሻ ወቅት ነው። ከብቶችም፥

ዶሮችም፥ አሣሞችም አሉን። ሣሩ የሚታጨደው፥ ቤቶቹ ቀለም የሚቀቡት፥ ወንበሩ፥ ጋሪው፥ አልጋው፥ ወዘተርፈ የሚጠገነው፥ በአጠቃላይ ትምህርት ቤቱ ለሚቀጥለው የሥራ ዓመት የሚዘጋጀው በአኛው ጉልበት ነው። አንደ ትምህ ርቱ ወራት ሁሉ መኝታችንን እና ምግባችንን ትምህርት ቤቱ ይችለናል። ምን ያህል አንደ ነበረ ረሳሁት እንጂ፥ ትንሽ የኪስ ገንዘብም ይሰጠናል። በዚህ ምክንያት ብዙ ልጆች ነን ከረምቱን አዚያው የምናሳልፈው።

ከሃዲነቴን ለማወጅ የወሰንኩበት ቀን ዓርብ ነው። ያ ዓርብ የተባረከ ዓርብ መሆን አለበት። እንዴ? ጎሊናዬን መስማት፥ በጎሊናዬም መመራት የጀመርኩ በት የመጀመሪያው ቀን ሊሆንኮ ነው። ያን ዓርብ ዕለት ጠዋት፥ ቁርሴን የፍስክ ምግብ ልበላ ወስኛለሁ። ከዓለማየሁ ተፈራ እና ከክፍሌ ነጋሽ (አሁን ዶክተር) ጋር ገቢታችን ሳይ ተሰየምን። ሦስታችንም የሊዳም ልጆች ነን - ዓለማየሁ የክብረ መንግሥት፥ ክፍሌ የሃገረ ሰላም፥ እኔ ደግሞ የዎላይታ ሶዶ።

ሦስታችንም ደግሞ ዲያቆናት ነን። ቤተ ክርስቲያን ሳሚዎች፤ የሃይማኖተ አበውንም ስብስባ አዘውታሪዎች፤ በዚያም መዝሙር ዘማሪዎች፤ ቲያትር ሠሪ ዎች። ዶርማችንም አንድ ነው። በአነዚህ ምክንያቶች ይመስለኛል ጓደኝነታችን ትንሽ ጠበቅ ያለውና የምግብ ገቢታችንም አንድ የሆነው። በክረምቱ ወራት ብቻ ሳይሆን ዓመቱንም ሙሉ፥ ግድ ካላጋጠመን በስተቀር፥ አንድ ገቢታ ላይ ነው የምንበላው።

"የታል ቁርስ ያመጣኸው?" አሉኝ አንዳቸው።

"አኔ ዛሬ የፍስክ ምግብ ልበላ ነው" አልኳቸው። እንደርሱ የሚያደርጉ ብዙ ልጆች አሉ። ሙስሊሞች ወይም ፕሮቴስታንቶች ወይም ስለ ሃይማኖት ግድ የማይላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ከማክሰኞ ወይም ከሐሙስ አራታችን የተረፈ ውን የፍስክ ምግብ፥ ረቡዕ ወይም ዓርብ ቁርስ ላይ ይበሉታል። በቀለ ግን ምድቡ ከአነዚህ አይደለም። ዓለማየሁ እና ከፍሌ ጆሮቻቸውን ሊያምኗቸው አልቻሉም። በአጃቸው ወይም በሹካቸው ወይም በማንኪያቸው የያዙትን ሳይጎርሱ፥ የጎረሱትንም ሳያላምጡ ወይም ሳይውጡ፥ ዐይኖቻቸውን እንዳ ፈጠጡ ቀሩ። አኔም ሌላ ምንም ሳልናገር ከመካከላቸው ተነሣሁና ወጣሁ።

ሳህኔን ይዤ ኪችናቸን ውስጥ የፍስክ ምግብ ለሚፈልጉ ተማሪዎች የፈለጉትን እየሰጣቸው ከነበረው ክሽፍ ጋሽ ታምራት ፊት ስቆም፥ እርሱም ዐይኖቹን

ያመናቸው እልመሰለኝም። ሆኖም በረዥም ዓመታት የሥራ ልምዱ ብዙ የእኔን ዐይነት ተማሪዎች ያስተናገደ ሰው ስለ ሆነ፥ የነበረውን የፍስክ ምግብ ለጨልፎ ክዘረጋሁለት ሳህን ላይ ከማስቀመጥ በቀር ምንም አልተናገረኝም። ሃሣሰልባት በልቡ "ትዝብት ነው ትርፉ" ብሎኝ ይሆናል።

የፍስክ ምግቤን ይዤ መጣሁ እና አጠገባቸው ተቀምጬ ስበላ፥ ዓለማየሁ እና ከፍሌ አንዳች ቃል አልተነፈሱም። ቁርሳችንን ጨርስን ስንነሣ፥ ከፍሌ "ከዛሬ ጀምሮ ስምህን 'ካሊፎ' ብዬዋለሁ" አለኝ። ምን ሊለኝ እንደ ፈለገ ገብቶኛል። የምሩን ነበር። ሆኖም ዓርብ ዕሮብ መብላቴም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን መቅረቴ በባልንጀራነታችን ላይ ምንም ዐይነት መጥፎ ጥላ አላጠላም።

ከከፍሌ ጋር ለሠላሣ አምስት ዓመታት ያህል ሳንተያይ ኖረን፥ በቅርቡ ለሥራ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በነበረ ጊዜ ተገናኘን። እቤቱ አራት ጋብዞኝ ስንጨ ዋወት የጠየቀኝ የመጀመሪያው ጥያቄ "ካሊፎን ታስታውሰዋለህ ወይ?" የሚል ነበር። "መቼ እረሳሁት እና ነው የማስታውሰው?" ነበር መልሴ። ቆይቶ ስሙ የእርሱም የዓለማየሁም አንደ ሆነ ዐውቄአለሁ። ያላወቅሁት መቼ እና እንዴት እንደ ሆነ ብቻ ነው።

በወቅቱ በነበረኝ መረዳት፥ ዓርብ ዕሮብ መብላት ማለት ከሃዲ፥ ማለትም በእግዚአብሔር መኖር የማያምን ሰው መሆን ማለት ነበር። የወሰንኩትም ያንን ለመሆን ነው። ያደረግሁትን ሁሉ በባልንጀሮቼ ፊት በግልጽ ያደረግሁትም በዚሁ ምክንያት ነው። ሃይማኖቶች ሁሉ የሚገለጡባቸው የየራሳቸው የተለያዩ ሥርዓቶች እንዳሏቸው፥ ዓርብን እና ዕሮብን ከአንስሳት ተዋጽዖ የተዘጋጁ ምግ ቦችን አለመብላትም የካቶሊክ ወይም የአርቶዶክስ ክርስትና ከሚገለጥባቸው ሥርዓቶች አንዱ እንጂ፥ አራሱ ክርስትናው አለ መሆኑን በጊዜው የት ዓውቄ? "ያንቺ ቁም ነገርሽ ..." አንዲሉ፥ የእግዚአብሔር የራሱ ጎልውና ጥያቄ ውስጥ ለወደቀበት ሰው፥ ዓርብ ዕሮብ ተበላ እልተበላ ምኑ ነበር?

በጎላ ላይ፥ በተለይም ባሌ ጎባ እያለሁ፥ በጣም የምንዋደድ ሙስሊም ጓደኞች ነበሩኝ - ዓሊ ሣላህ እና ፋይሣል ሞሐመድ ይባላሉ። በጎባም ሆነ በሌላ ቦታ፥ በቢታቸውም ሆነ በቤቴ፥ እብረን በልተናል። "የክርስቲያን ሥጋ"፥ "የእስላም ሥጋ" የምንለው አልነበረንም። "የበሬ" ወይም "የበግ" ወይም "የዶሮ" የምን ለው ሥጋ ብቻ ነው የነበረን። አንዳንድ ሙስሊሞች የሆኑ የባንክ ደንበኞቼም

በረመዳን ወር በየምሽቱ ፆማቸውን ሲፈቱ ይጠሩኛል፤ አብረን እንፈጥራለን። እርግጥ እንደዚህ ማድረግ የጀመሩት፥ እኔ እንደዚህ ባሉ ነገሮች ችግር እንደ ሌለብኝ ካረጋገጡ እና ከምግበቻቸውም መካከል አንዳንድ በጣም የሚመቹኝ እንዳሉ ካወቁ በኋላ ነው።

"የተነቃነቀ ጥርስ"

በዚያው ዓመት ነው፥ ዓርብ ዕሮብን መብላት ከጀመርኩ በኋላ ብዙም ሳልቆይ፥ አቶ ተሾመ ዳጨውን ያወቅሁት። እንዴት ልተዋወቀው እንደ ቻልኩ ለማስታወስ ብዙ ሞክሬ አልተሳካልኝም። አቶ ተሾመ የሐረር መምሕራን ማሠልጠኛ ምሩቅ እና የደጃዝማች ከፍሌ ዳዲ ልዩ ጸሐፊ ነው ። ደጃዝማች ከፍሌ ማለት በጊዜው የንጉሠ ነገሥቱ የከፋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ የነበሩት ናቸው። ለዚህ ነው ከአቶ ተሾመ ጋር እንዴት እንደ ተዋወቅን ለማወቅ የፈለ ግሁትም፥ ለማወቅ ያልቻልኩትም። ምክንያቱም እርሱ ትልቅ ባለ ሥልጣን ሲሆን እኔ ደግሞ አንድ የዐሥራ እንደኛ ከፍልን ያጠናቀቀ ተማሪ ብቻ ነኝ። እርሱ ዕድሜውም እንኳን ባይሆን፥ ሥልጣኑ "አንቱ" ሊያሰኘው የሚገባ ሰው ነበረ። ሆኖም ሰውዬው በቀላሉ የሚቀርቡት፥ የሚወዱት እና "አንቱ" ሳይሉት የሚያከብሩት ዐይነት ሰው ነው የነበረው።

አቶ ተሾመ የሃይማኖት ውይይት መቀስቀስ እና ማድረግ በጣም የሚወድም፥ በጣም የሚችልም ሰው ነው። "እግዚአብሔር ከመጀመሪያው አባብን 'ተንኮ ለኛ' አድርጎ ለምን ፈጠረው?" አለኝ። "በሜድን ግነትስ ውስጥ 'መልካምንና ከፉን የሚያስታውቀውን' ያንን ዛፍ ለምን ተከለው?" አለኝ። "አዳም እና ሔዋን ከዚያ ዛፍ ፍሬ እንደሚበሉ እያወቀ ደግሞ ሰምን እንዳይበሉ አዘዛቸው?" አለኝ። እኔ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ይህንን አስቢውም አላውቅ። ምን ልመልስለት? "እግዚአብሔር ጠላቶቹን በገሃነመ እሳት ውስጥ ለዘላለም እያቃ ጠላቸው፥ እኛን ግን 'ጠላቶቻችሁን ውደዱ' ለምን ይለናል?" አለኝ። "ኢየሱስ ክርስቶስ አንዲትን የበለስ ዛፍ ያለወቅቷ ፍሬ ካላፈራች ብሎ እንዴት ይረግ ማታል?" (ማር. ፲፩፥12-14) አለኝ። ምን ልመልስለት? እግዚአብሔር ያሳያችሁ!

ይህ ያነሰኝ ይመስል፥ አቶ ተሾመ ዳጨው ከሮበርት ጂ. ኢንገርሶል ጽሑፎችም ጋር አስተዋወቀኝ። ቆይቶ ቆይቶ እንደ ተረዳሁት፥ ኮሎኔል ሮበርት ጂ. ኢንገርሶል ማለት በአንዳንዶች "THE GREAT AGNOSTIC"፥ በሌሎች

ደግሞ "THE GREAT INFIDEL" በመባል የሚታወቀው አሜሪካዊ ነው። አባቱ ከለመ ጥሩው ሪቫይቫሊስት ከቻርልስ ጂ. ፊኔይ ጋር በቅርብ አብሮ ያገለግል የነበረ ታዋቂ ፕሪስቢቴርያዊ ሰባኪ ነበረ። ሁሉንም ባላውቃቸውም፥ አቶ ተሾመ በጅማ አርሻ ቴክኒክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መካከል ሌሎችም ደቀ መዛሙርት ነበሩት። ምክንያቱም ከእኔ ጋር በተዋወቅን በዚያው ሰሞን የጅማ ልጅ እና የከፍል ጓደኛዬም የነበረው በላቸው ነጋሽ የኢንገርሶልን ሥጽሐፍ ይዞ አይቼዋለሁ።

በላቸው፥ የኢንገርሶልን መጽሐፍ ዜማ በተቀላቀለው እጠራር "MY BIBLE" እያለ ይጠራው እንደ ነበረ፥ እስከ መሳም እና እየታቀፈውም እስከ መተኛት ደርሶ እንደ ነበረም እስታውሳለሁ። ማንነቱን ያላወቅሁት እንድ ሌላ የትምህ ርት ቤታችን ተማሪ ደግሞ፥ ከእሜሪካውያን መምህሮቻችን በእንዱ በኩል ያመስለኛል መጽሐፉን ከአሜሪካ ድረስ እስከ ማስመጣት እንደ ደረሰም ሰምቻ ለሁ። ሁላችንንም ከኢንገርሶል ጋር ያስተዋወቀን አቶ ተሾመ መሆን አለበት። የእኔ ብጤ "ማሞ ቂሎች" ጭፍን እምነታቸውን እንዲጠይቁ እና እንዲመረምሩ ማድረግን የሕይወቱ ተልእኮ ያደረገ ሰው ነበረ መሰለኝ - አቶ ተሾመ ዳጨው።

ከሃዲ ከመሆኑ በስተቀር፥ አቶ ተሾመ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሀዲስ ዓለማየሁ "ፍቅር እስከ መቃብር" በተሰኘው ዝነኛ መጽሐፋቸው ያስተዋወቁንን ጉዱ ካሣን ይመስለኛል። ፍቅር እስከ መቃብርን እንብቦ ጉዱ ካሣን መውደድ ብቻ ሳይሆን፥ ጉዱ ካሣን መሆን ጭምር ያላስኘው ማን አለ? እኔን በተመለከተ፥ አቶ ተሾመ ተልእኮው ተሳክቶለታል ለማለት እችላለሁ። ምክንያቱም "ማሞ ቂሊዊ" የነበረው እምነቴ መነቃነቅ በጀመረበት በዚያው ዓመት ተንኮታኩቶ ወድቋልና። ከሆኑ ዓመታት በኋላ በላቸው በገዛ እጁ ሕይወቱን እንደ አጠፋ ሰምቻለሁ። ለዚያ እደጋ የአቶ ተሾመ እና የኮሎኔል ኢንገርሶል ትምህርቶች እንዳች አስተዋጽዖ አድርገው ይሆን? አላውቅም።

ከሀደትንም ለካ ይካኑታል?

ከሃዲ ለመሆን ከወሰንኩ በኋላ ብዙም ሳልቆይ ማስተዋል የጀመርኩት እንድ ነገር ቤኖር፥ ውሳኔዬ እንዲያው ዝም ተብሎ የተደረሰበት እንዳልነበረ ነው። ሣስ በቀስ እና ሳይታወቀኝ፥ ወደዚያ ውሳኔ እንድደርስ አስተዋጽዖ ያደረጉ፥

ቀደም ሲል ያገኘኋቸው፥ የተለያዩ ግንዛቤዎች በውስጤ ነበሩ። ለምሳሌ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሥነ ሕይወት (BIOLOGY) ትምህርት፥ በተለይም ደግሞ "አዝጋሚ ሰውጥ" (EVOLUTION) አንዱ ነው። በዚያ ደረጃ የሚለጠው የአዝጋሚ ለውጥ ትምህርት ይህንን ያህል የጠለቀ አልነበረም። ፊተና ለማለፍ ሰንል ካልሆነ በስተቀር፥ ተማሪዎቹም የምንማረውን ትምህርት የዚያን ያህል ቁም ነገር አድርገን አንወስደውም ነበር። ሆኖም ከሃዲ መሆን ስጀምር፥ ያም ትምህርት ትርጉም የሚሰጠኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ሳላውቀው ለከሃዲነቴ አስተዋጽዖ ያደረገው ሌላው ትምህርት፥ አሜሪካዊው የኢንግሊዝኛ ቋንቋ መምሕራችን ሚስተር ኢልየት ያስተዋወቀን የዑመር ኻያም "ሩብአያት" ነው። ዑመር ኻያም በዐሥራ አንደኛው እና በዐሥራ ሁለተኛው ምዕት ዓመት የኖረ ፋርሳዊ ባለ ቅኔ ነው። በአምነቱ "ሱፊ" ሙስሊም ነበረ ይባላል። የኤፊቆሮ (EPICURUS) ፍልስፍና ተከታይ ነበርም ይላሉ። ቅኔዎቹ "ሩብአያት" የተባሉት አያንዳንዳቸው ባለ አራት አራት ሥንኞች በመሆናቸው ነው።

ሚስተር ኢልየት የዑመር ኻያምን ቅኔዎች እጅግ አንደሚወዳቸው ግልጽ ነበረ። በኋላ ላይ እንደ ደረለኩበት፥ የሚያነብልን ከኤድዋርድ ፊትዝጀራልድ ትርጉም፥ ከሁለተኛው እትም ነው። ከዚያ የቅኔውን ምሥጢር ይተረጉምል ናል። በጣም መሰጫ ነበር። እና በእኔም ላይ የዑመር ኻያምን እና የቅኔዎቹን ፍቅር አሳደረብኝ።

ከሦስት ዓመት በኋላም የግሌ የሆነ የኤድዋርድ ፊትዝጀራልድ "RUBAIYAT OF OMAR KHAYYAM" ኖረኝ እና እነዚያን ቅኔዎቹን በቃሌ እስከምይዛቸው ድረለ ኮመኮምኳቸው። በ1950ዎቹ መጨረሻ ላይ ይመስለኛል፥ ፒያሳ አካባቢ "ዑመር ኻያም" የተባለ ሆቴል በተከፈተ ጊዜ፥ በኢንግሊዝኛ ቋንቋ በሚታተም አንድ ጋዜጣ ላይ የወጣው ማስታወቂያ "AT LAST OMAR KHAYYAM!" ይል ነበረ። ለእኔ ማስታወቂያው አራሱ ልዩ ትርጉም ነበረው። ምክንያቱም ኤፊቆሮአዊው ዑመር ኻያም ከዚህ ሕይወት እና በዚህም ሕይወት ከመደለት ውጭ፥ ለሰው ልጅ ሌላ ትርፍ አንደ ሌለው እጅግ ውብ በሆነ ቅኔ አስተምሮኝ ስለ ነበረ ነው።

አሁን በቅርቡ በ1999 በታተመው የአቶ ተሰፋዬ ገሠሠ "ዑመር ኻያም ... እና ሩብአያቶቹ" ውስጥ ያገኘኋቸው በ1B59ኙ የመጀመሪያ እትም ውስጥ የተካተ

ተትን 75ቱን ሩብአያቶች ብቻ ነው። የ1B68ቱ ሁለተኛ እትም 110 ሩብአያቶች ናቸው ያሉት። በሁለተኛው እትም ውስጥ ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ ለሚያምኑ ሁሉ የጻፈውን 27ኛውን ሩብአያት እንደሚከተለው ተርጉሜዋለሁ -

ለዚህኛው ለሚሯሯጡ፥
ወደዚያኛውም ለሚያንጋጥጡ፥
ሙአዚኑ[5] ይጮኻል፤ ከጨለማው ማማ ላይ -
"ቂሎች!
ወሮታችሁን እዚህም እዚያም አላይ"

ኦማን ከመልቀቄ በፊት በግሌ ያነበብኩት ሌላው መጽሐፍ የቮልቴይር CANDIDE ሲሆን፥ መጽሐፉን ያገኘሁት ከትምህርት ቤታችን ቤተ መጻሕፍት ነው። መጽሐፉ ከቮልቴይር ጽሑፎች ሁሉ በጣም ዝነኛ የሚባለው ሲሆን፥ ጸሐፊው በዚያን ዘመን በምዕራቡ ዓለም ታዋቂ ለነበሩት ሃይማኖቶች ሁሉ (ይሁዲነት፥ ክርስትና እና አሰልምና) ያለውን ንቀት እና ጥላቻ ያንጸባረቀበት ነው። የመጽሐፉ ዋና አሳብ "ሊኖሩ ከሚችሉ ዓለማት ሁሉ ይህ እጅግ በጣም የተሻለው ነው" (BEST OF ALL POSSIBLE WORLDS) የሚል ነው። "ዘመነ አብርኆትን" ካዋለዱት ወይም "ዘመነ አብርኆት" ካዋለዳቸው መካከል በግንባር ቀደምነት ከሚጠቀሱት ሰዎች አንዱ ቮልቴይር ነው።

ኦማን ከለቀቅሁ በኋላማ ምኑ ቅጡ? ጭንቅላት አላቸው የሚባሉት ሰዎች ሁሉ ከሃዲዎቹ ብቻ እስከሚመለሱኝ ድረስ ጽሑፎቻቸውን እያሳደድኩ አነበብኩ። የበረትራንድ ራሴልን WHY I AM NOT A CHRISTIAN፥ የጁልያን ሐክስሌይን RELIGION WITHOUT REVELATION፥ የአልደስ ሐክስሌይን BRAVE NEW WORLD፥ የማነው ስሙን MEN WITHOUT GODS፥ ወዘተ ተርፈ። በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ፥ ሁሉም የሚያነሡት አንድ ጥያቄ፥ "ሁሉን የሚወድ እና ሁሉን የሚችል አምላክ ካለ፥ ዓለሙ እንዴት እንደዚህ ሊሆን ቻለ?" የሚል ነው።

ይኸም ማንም የሚያስብ ለው ሊያነሣው የሚገባ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም በየትኛውም ሃይማኖት ቢሆን፥ አግዚአብሔር "ሁሉን የሚወድ" እና "ሁሉን የሚችል" አምላክ ነው። ማንም ሃይማኖተኛ ሊከደው የማይችለው እውነት ይኸም ዓለማችን ለመዘርዘር ከሚቻለው በላይ በሥቃይ የተሞላች መሆኗ

ነው። በሚሠቃዩትም መካከል ሊሥቃዩ እንዳች አስተዋጽዖ ያላደረጉ ሕፃናት፥ እናቶች እና ዐቅመ ደካማ አረጋውያን ይገኛሉ።

ለዚህ ነው የጥያቄው መልስ ቀላል፥ እጭር እና ግልጽ የሚሆነው - ወይ እግዚአብሔር የሚባል የለም። ካለም፥ ወይ ሁሉን አይወድም፤ ወይም ሁሉን አይችልም። ሁሉን የማይወድ እና ሁሉን የማይችል ከሆነ ደግሞ፥ እሱ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም። እንዲህ ያለውንም እግዚአብሔር ማንም አይፈልገውም - እኔን ጨምሮ። በዚህ ዐይነት ከህደትን ተካንኩ፤ ከአከራሪ አርቶዶክሰነት በቀጥታ ወደ አከራሪ ከሃዲነት ተሸጋገርኩ።

"አደንዛዥ ዕፅ"

ዘመኑ በኢትዮጵያ "የተማሪዎች ንቅናቄ" መጡዋጡዋፍ የጀመረበት ነበረ። ከተማሪዎቹ ንቅናቄ ጋር ያስተዋወቀኝ ተረፈ ወልደ ጻድቅ (በኋላ ዶክተር) ነበር ማለት እችላለሁ - "በዩኒቬርሲቲ ተማሪዎች ብሔራዊ አገልግሎት ፕሮግራም" ጅማ ተመድቦ መጥቶ በነበረ ጊዜ። ፕሮግራሙ የተጀመረው በ1956 ዓ.ም. ሲሆን፥ ዓላማውም ማንኛውም የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ከመመረቁ በፊት ለአንድ ዓመት በአገሪቱ ባሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመድቦ እንዲያገለግል ነው። ከተረፈም ጋር እንዴት እንደ ተዋወቅን አሁን ትዝ አይለኝም። ይገር ማል! ብዙ ነገር ነው የዘነጋሁት ማለት ነው።

ተረፈ በሚያዝያ 27 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው ብሔራዊ አገልግሎቱን እየሰጠ የነበረው። እኔ ባገኘሁት ጊዜ በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ እንደሚያገለግል እንደ ነገረኝ ነው ትውስ የሚለኝ። ዘመኑ 1955 ዓ.ም. መጨረሻ ወይም 1956 ዓ.ም. መጀመሪያ ነው። ያ ዓመት ከዚያ በፊት በየኮሌጆቹ የነበሩት የተማሪዎች ማኅበራት በብሔራዊ ደረጃ ለመደራጀት ጥያቄ አቅርበው የዩኒቨርሲቲውን አስተዳደር ይሁንታ ያገኙበትም ዓመት ነበር። ጥያቄአቸው ብሔራዊው የተማ ሪዎች ማኅበር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችንም እንዲያካትት ነው የነበረው። የተማሪዎቹ ማኅበር ንቅናቄውን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም የማዘመት ድብቅ ፍላጎት ነበረው ማለት ነው። ሆኖም ጥያቄው በዩኒቬርሲቲው አስተዳደር ተቀባይነት አላገኘም።[6]

ስለ ንቅናቄው በለፈው እንዲያስረዳኝ ተረፈን ያስገደደው ያ ድብቅ ፍላጎት መሆን አለበት። እየመለመለኝ የነበረ አይመስለኝም። ግንዛቤ እያስጨበጠኝ

እንደ ነበረ ግን ግልጽ ነው። ተረፈ ያስጨበጠኝ ያ ግንዛቤ መሆን አለበት እኔንም በዚያው ዓመት ለትምህርት ቤቴ "የተማሪዎች መመማከርት" መሪነት እንድወዳደር ያነሣሣኝ። ውድድሩ ተሣካልኝ። ሆኖም በዚያው ዓመት ከትምህ ርት ቤት ተባረርኩ። የተባረርኩበት ደብዳቤ የተጻፈው እንደ ጎርጎሳውያኑ አቆጣጠር መጋቢት 17 ቀን 1964 ነው። የተጻፈውም በኢንግሊዝኛ ቋንቋ ሆኖ "TO WHOM IT MAY CONCERN" (ለሚመለከተው ሁሉ) የሚል ነው።

በደ/በዳቤው ውስጥ የተባረርኩት ለአንድ ዓመት እንደ ሆነ፥ የተባረርኩትም በአር/ሻ ሚኒስትሩ በከቡር አቶ አካለ ወርቅ ሀብቴ ወልድ ትዕዛዝ መሆኑ ተመልከቷል። ከእንድ ዓመት በኋላ የመመለሴም ጉዳይ ቢሆን፥ የወደፊት ሁኔታዬ ታይቶ በከቡር ሚኒስትሩ እንደሚወሰን ተገልጾአል። ከትምህርት ቤት የተባረርኩት ረብሻ በማስነሣት እና ለሁለት ቀናት ነው መሰለኝ ትምህርት እንዲቋረጥ በማስደረጌ ነበር። ለረብሻው መነሣት እና ለትምህርቱ መቋረጥ ምክንያቱ ምን እንደ ነበረ እሁን በእውነት ጠፍቶኛል። ያልጠፋኝ እንድ ነገር ግን፡ የእኛ ረብሻ ተረፈ ካስተዋወቀኝ የተማሪዎች ንቅናቄ ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት ያልነበረው መሆኑ ነው።

ተረፈን ቀድሜው ነው ጅማን የለቀቅሁት ማለት ነው። ከዚያ በኋላም ቢሆን በጥንባር እልተገናኘንም። ሆኖም ከተማሪዎቹ ንቅናቄ እቀንቃኞች መካከል እነሱ እንደ ነበረ፥ በዚያም እስከ መጨረሻው እንደ ገፋበት ዐውቃለሁ። ከዐሥራ እንድ ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ እብዮት በፈነዳ እና በእብዮተኞቹም መካከል የነበሩት የመሰመር ልዩነቶች ይፋ በወጡ ጊዜ፥ እርሱ የተከተለው መሰመር የትኛው እንደ ነበረ ስምቻለሁ። በ1969 ዓ.ም. የትምህርት ሚኒስትር ሆኖ መሾሙን እና ብዙም ሳይቆይ እባል ከነበረበት የፖለቲካ ቡድን ዋና ዋና መሪዎች ጋር እብሮ መገደሉንም ተረድቻለሁ።

የተማሪዎቹ ንቅናቄ ዐሥር ዓመታት በማይሞላ እጭር ጊዜ ውስጥ ነበር የሁለ ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ያዳረሰው። ገና ከመጀመሪያው፥ ከ1960ዎቹ መጣቻ ገደማ ጀምሮ ነበር፥ በተማሪዎቹ ንቅናቄ መሪዎች መካከል የመሰመር ልዩነቶችም ሊስተዋሉ የጀመሩት። ልዩነቶቹ እየከረሩ እና እየጦዙ መጥተው፥ መጨረሻ ላይ ለእንድ ትውልድ እምሽከ ብሎ ማለቅ ምክንያት መሆናቸው ይታወቃል። በዚያ ሁሉ ውስጥ ግን የንቅናቄው መሪዎች፥ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ያልተለያዩባቸው ሁለት ጉዳዮች ነበሩ። ከእነዚ

ህም እንደኛው ሁሉም አገራቸው ተለውጣ ለማየት ጽኑ ፍላጎት ያላቸው እና ለዚያም የሚታገሉ መሆናቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሁሉም ከሃዲዎች መሆናቸው ነው።

የተማሪዎቹ ንቅናቄ በዚያን ጊዜ እንደ ለደድ አሳት ዓለሙን በሙሉ እያጥለቀለቀ የነበረው "የግራ ከንፍ" ንቅናቄ አካል ነው። የዚያ ንቅናቄ ርዕዮተ-ዓለምም ወይ ማርከሳዊ/ሌኒናዊ፣ አለዚያም ማርከሳዊ/ማኦዋዊ ነው። ከዚህ ርዕዮተ ዓለም ቀዳሚ ቀኖናዎችም አንዱ "ሃይማኖት ሕዝብን ማደንዘዣ ዕፅ ነው" (OPIATE OF THE PEOPLE) የሚል ነው። ስለዚህ የንቅናቄው መሪ ዎች ሁሉ ፍላጎት፣ አገሪቱ በሙሉ ሃይማኖት የተባለውን አደንዛዥ ዕፅ "አከ፣ እንትፍ" አንድትለው ነው። በዚህ ፍላጎታቸውም ብቻቸውን አይሆኑም፤ የተሸመ ዳጨው እና የእኔ ብጤ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ከጎናቸው ይቆማሉ።

በትከከለኛው መስመር ላይ መሆኔን ነው ሁኔታው ለእኔ ያመላከተኝ። ሃይማኖት የሚባል ነገር እያበቃለት ነው ማለት ነው። የነገው ዓለም ከሃይማ ኖት እና ከተጽዕኖው ፈጽሞ የጸዳ ዓለም ነው የሚሆነው ማለት ነው። አሁን እንደሚታየው ከሆነ ደግሞ፣ ይህ ሊሆን ያለበት ጊዜም እምብዛም እሩቅ አይደ ለም። የከሃዲዎቹ ካምፕ በሶቭዬት ኅብረት ጀምሮ ከአሁኑ፣ ማለትም አርባ ዓመት አንኳን ሳይሞላው፣ ምሥራቅ አውሮፓን እና ቻይናን ከአደንዛዥ ዕፅ አርነት አውጥቷቸዋል። አንዳንድ የአስያ፣ የላቲን አሜሪካ እና የአፍሪቃ አገሮ ችም አየተከተሉ ናቸው። በሴሎቹም አገሮች ውስጥ ቢሆን ከቀን ወደ ቀን እየፋመ እና እየጋመ የሚሄድ ንቅናቄ አለ። የኢትዮጵያም ወጣቶች የዚሁ ድል ነሺ ንቅናቄ አካል ሆነዋል። አንዴት ብሩኅ የሆነ ተስፋ ነው!

በእንደዚህ እያሰሁ ነበር፣ ሐምሌ 13 ቀን 1961 ዓ.ም. (JULY 20፣ 1969) አሜሪካ ሁለት ጠፈረተኞቿን ጨረቃ ላይ ያሳረፈችው። ጠፈረተኞቹ ወደ ምድር ሲመለሱ፣ የጨረቃን ኮረት ጭነው ተመልሰዋል። በዚያን ጊዜ የተሰማ ኝን የኢድናቆት እና የደስታ ስሜት በቃላት ለመግለጽ ይቸግረኛል። አንዲያው በአጭሩ አራሴ ላይ ወጣ፤ አስከረኝ፤ ማለቱ ይቀለኛል። ጨረቃኮ ከርቀቷ እና ከውበቷ የተነሣ ስንትና ስንት ባለቅኔ ስንትና ስንት ሥንኝ የቋጠረላት ናት። ወደ መመለከ የተቃረበችባቸው ሃይማኖቶችም ነበሩ። መቼም "ነበሩ" እንጂ ከእንግዲህ ወዲህ "አሉ" ሊባል ይቻላል እንዴ?

ያ'ከው እንግዲህ እርስዋ በሰው ልጆች ተረገጠች። ነገ አና ከነገ ወዲያ፣ የሴሎቹም እያንጋጠጥን የምናያቸው አካላት ሁሉ ዕጣ ይኸው ነው የሚሆ ነው። ዑመር ኻያም ከቅኔዎቹ በአንደኛው፣ ስለ ጨረቃ ሳይሆን፣ ጨረቃ እና ከሦከብቱ ሁሉ ስላሉበት "ሰማይ"፣ እንዲህ ነበር ያለው። ከተሰፋዬ ገሠሠ ትርጉም 52ኛዋ ሩብአያት ይህቻት -

ለዚህ ግልብጥ ቆሪ፣ ሰማይ ለምንለው
ከሥሩ ተደፍተን ፣ ቢጠን ለምናድረው
እጅህን አታንሣ! እሱም የሚኖረው
እንዳንተና እንደኔ ሲገለባበጥ ነው!!

የአፖሎ አስራ አንድ መንኮራኩር ጨረቃ ላይ ካረፈች እና ከዚያም በሰላም ከተመለሰች በኋላ፣ በዓለም ላይ እንደ ነበረ የሚቀጥል አንድም ነገር ሊኖር አይችልም። በጊዜው እኔም እንዲት ግጥም ጫጭሪ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያሳተማት በነበረች መጽሔት ላይ ለንባብ አብቅቻለሁ። የመጽሔቷ ስም "BANKERS' SPECTACLE" ይመስለኛል። ሙሉውን ግጥም እረስቼዋለሁ። አሁን፣ ከአርባ ሦስት ረዥም ዓመታት በኋላ፣ የባንኩን "አርቪም ቤት" (ARCHIVES) አስከ ማሰስ ድረስ ወደ ኋላ ለመመለስም አልፈለግ ሁም። ግጥሟን የቋጨኩባቸው የመጨረሻዎቹ ሦስት ስንኞች ግን አል ተረሱኝም - እንደዚህ ይላሉ፡-

... አለቀ፣ አመለጠ፤
ይኖራል ከ'ንግዲህ
በሕዋ-ሕው ጫካ እንደ ፊረጠጠ።

ማስታወሻ

1. መርሰዔ ኅዘን ወልደ ቂርቆስ፤ "የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፤ 1999 ዓ.ም. ገጽ 218።
2. ጉስታቭ አሬን፤ "Envoys of the Gospel in Ethiopia"፤ ጉስታቭ አሬን እና ቬርቡም እታሚ (ስዊድን)፤ 1999፤ ገጽ 349።
3. "የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ"፤ ገጽ 173።
4. ባሕሩ ዘውዴ፤ "የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1948 እስከ 1966"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፤ 1989።
5. "መአዚን" ለእስልምና እምነት ተከታዮች የሶላት (ጸሎት) ሰዓት መድረሱን ከመስጊዱ ማማ ላይ ሆኖ በዜማ በመጮኽ የሚያስታውቀው ሰው ነው።
6. ክፍሉ ታደሰ፤ "ያ ትውልድ - የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ታሪክ፤ ክፍል አንድ"፤ ኢንዲፔንደንት አሳታሚዎች፤ ዘመኑ አልተጠቀሰም፤ ገጽ 63።

ምዕራፍ ሦስት

"ሳያድጉ ማደግ ..."

እንዲህ እንደምጽፈው፥ ቀላል ቢሆን ኖሮ መልካም ነበረ። ሰው እንደ "አመለጠ" እና እንደ "ፈረጠጠ" የሚቀር ቢሆን ኖሮ ማለቴ ነው። ልኩ በማይ ታወቀው፥ ምናልባትም ልከ በሌለው፥ "በሕዋ ጫካ" ውስጥ ይቅርና፥ ተለከታ እና ተቆራርሳ ባለቀችው በጠባቧ ምድርም ላይ። ምድሯም እንኳን ትቅርና፥ ከመንደሮቿ በአንዱ ላይ። እንደዚያ ግን አይደለም። ቢያንሰ ለእኔ - በዚያን ጊዜ - እንደዚያ አልሆነም። ምከንያቱም የንባብ ሱሰኛ ሆኛለሁ። የጂያኖፑሎሰ መጻሕፍት መሸጫ መደብር ደንበኛ ነኝ። ደንበኛነቴ ከመደብሩ ሥራ አለኪያጅ ከፎቲ ጂያኖፑሎሰ ጋር አወዳጅቶኛል። መጻሕፍት በዱቤ ጭምር ይሸጥል ኛል። የምፈልጋቸው መጻሕፍት በመደብሩ ውስጥ ከሌሉ ከውጭ ያዝልኛል።

እኔ በምሠራበት በኢትዮጵያ ንግድ ባንኩ የአራዳ ጊዮርጊስ ቅርንጫፍ ያለው የአቨርድራፍት ብድሩ እንዲታደስለት በሚጠይቅበት ጊዜ፥ በሚያቀርበው የሂሣብ ሠነድ ላይ ስሜ በባለዕዳዎች ዝርዝር (ACCOUNTS RECEIVABLE) ውስጥ ይታያል። በዝርዝሩ ውስጥ ሰሜን ያዩ አንድ የብድር ከፍል ኃላፊ "ይኸ የእንተ ስም ነው ወይ?" ብለው የጠየቁኝ ጊዜ ነበረ። አንድ ተራ የባንክ ሠራ ተኛ፥ ለአንድ የመጻሕፍት መሸጫ መደብር፥ በሺዎች ለሚቆጠር ብር ባለ ዕዳ ሆኖ ሲያዩ ምን ያድርጉ?

ከዚያ በፊት ደግሞ የቤተ መጻሕፍት ወመዘክር፥ የአሜሪካ ዜና እገልግሎት ቤተ መጻሕፍት (U.S.I.S. LIBRARY) እና የሶቭዬት ኅብረት ቋሚ ኤግዚቢሽን ቤተ መጻሕፍት (SOVIET LIBRARY) ደንበኛ ነበርኩ - ለአንድ ዓመት ከትምህርት ቤት ተባርሬ በነበረበት ጊዜ። መጻሕፍት የምገዛበት ገንዘብም ባይኖረኝ፥ መጻሕፍት የማነብበት ጊዜ ነበረኝ ለማለት ነው። እና ከላይ በጠቀሰኳቸው መጻሕፍት ቤቶች ውስጥ አውል ነበር - ፎርጅ ባደረግሁት፥ 12ኛ ከፍልን እንደ አጠናቀቅሁ በሚያሳይ ዲፕሎማ - ፊተና ተቀምጬ እና ዐልፌ በገንዘብ ሚኒስቴር እስከ ተቀጠርኩበት እለከ ሐምሌ 23 ቀን 1956 ዓ.ም. ድረስ።

የሶሳሸት ኅብረቱን ቤተ መጻሕፍት የሚያዘወትሩት ሰዎች በዐይነ ቁራኛ ይታ ያሉ፡ ከትትልም ይደረግባቸዋል ሲባል አሰማለሁ። ይኸ ግን እንደ እኔ ዐይነ ዙን ተራ ተማሪ የሚያሳስብ ጉዳይ አይደለም። ለለዚህም ወደ ቤተ መጻሕፍቱ አመላለሰ የነበረው ያለ እንዳች ሥጋት ነበር። ቅጣቴን እንደ ጨረስኩ፥ ሥራ ዙን ለቅቄ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሻለሁ። ሆኖም ከሁለት ሣምንታት ያህል በኋላ በፈቃዴ እንደ ገና ጥዬው ወጥቻለሁ - እስከ ወዲያኛው።

የሚሰማ እና የሚያይ ሰው፥ የሚያስብ ለው፥ "አለቀ!" ወይም "አመለጠ!" ብሎ ሠላሰበጥ እንዴት ይችላል? በየቀኑ፥ በየለዓቱ፥ በየደቂቃው አዳዲስ መረጃ ያገ ሃል - ስለ ብዙ ነገሮች። "አለቀ"፤ "አመለጠ" ስለ ተባለውም ነገር ሳይቀር። ስለ ሁሉም ነገር። እና ነገሩ ሁሉ እንደ ገና ጥሬ ይሆንበታል። እንኳን ሲያ ልቅ፡ ለካ ገና አልተጀመረም። እንኳን ሊያመልጥ፥ ቀድሞውንም ለካ ገና አልተ ያዘም። የማንበብ ሐራዬን የማርካት ጥረቴን እየቀጠልኩ በመጣሁ መጠን፥ እኑንም ያጋጠመኝ እንደዚሁ ያለ ሁኔታ ነበር - ያልተመለሱ ጥያቄዎች፤ እርሰ በርሳቸው የሚጋጩ መረጃዎች፤ የያዝኩትን እውነት የሚያሰለቅቁ ሌሎች እውነቶች።

ዱር ውስጥ አይደለን እንዴ?

ያሀንን ሰሜቴን "ደማሙ ብዕረኛ"፥ አቶ መንግሥቱ ለማ፥ "አገሩ ገቢ" በተባለው ግጥማቸው እጅግ ውብ አድርገው ገልጸውታል -

ማወቅም ጫካ ነው ችምችም ያለው ዱር
ብርሃን፥ አንጸብርቆ ዐይን የሚሰውር
አዞ ሐረግ ያለበት እጅ እግር የሚያስር
አለ አሳብ አንበሳው፥ አጥንት የሚሰብር።
ማወቅም ጫካ ነው
አንድ ጊዜ ከገቡት የሌለበት መውጫ
አንድ ጊዜ ከያዘም የሌለው ማምለጫ።
መቶ ሺ መንታ ነው ይህ ጫካ መንገዱ
ያም ቢያስኬድ ያም ቢያስኬድ
መዳኛው ነው እንዲ።

የአቶ መንግሥቱ ለማን "የግጥም ጉባዔ" ያነበብኳት ገና ዎላይታ እያለሁ ነው - በ1951 ወይም በ1952 ዓ.ም። በታይፕ ራይተር ተጽፋ እና ተባዝታ ነበር ገባያ

ላይ የዋሰችው። አንዴት እጇ አንደ ገበች አላስታውስም። በጣም ነበር የወደድኳት። በውስጥዋ ያለው የሕይወት ምሥጢር ሊገባኝ የጀመረው ግን ገና አሁን ነው ማለት አችላለሁ። ታዲያ ያኔ ምኗን ነበር አንደዚያ በጣም የወደድኩላት? ቋንቋዋን? መሆኑ ነዋ! ግፋ ቢልም አንዳንድ ቀለል ቀለል ያሉ አሳቦችን የያዙትን ግጥሞቿን። የፍቅር ግጥሞችም አሏት። አቶ መንግሥቱ ያለ ጥርጥር አሁን እኔ አየሄድኩበት ባለው መንገድ ሄደዋል። አሁን እኔ እያጋጠ መኝ ያለው ችግርም አጋጥሟቸዋል።

ችግሩ መንገዱ "መቶ ሺ መንታ" መሆኑ ላይ ነው። ችግሩ መቶ ሺዎቹም መንታዎች መንገዶች ሁሉም የሚያስኬዱ መሆናቸው ነው። ታዲያ አቶ መንግሥቱ "መዳኛው ነው አንዱ" ያሉትን መንገድ፥ እሱን እንዴት ነው የማገኘው? በሁሉም ላይ እስከ "ጫፍ" ከተጓዝኩ በኋላ? እንደዚያ ለማድረግ እንዴት እችላለሁ? ማለቴ መቶ ሺ መንታ መንገድ ለመሞከር አንድ ሰው በቂ ጊዜ ከየት ያመጣል? እርሳቸውም "መዳኛው ነው አንዱ" አሉን እንጂ፥ አንዱ ግን የትኛው አንደ ሆነ አልነገሩንም። ለምን? እርሳቸውም ስለማያውቁት? ወይም ፈትፍ ተው ሊያነርሱን ሰላልፈለጉ?

በዚህ ወቅት ያነበብኳቸው መጻሕፍት፥ በዐይነትም በብዛትም፥ የዋዛ አልነበ ሩም። ልብ ወለዶቹን፥ ታሪኮቹን፥ ግለ-ታሪኮቹን እና ሌሎች ሌሎቹን ሁሉ ትቼ፥ ከአፍላጦን GREAT DIALOGUES አስከ አማኑኤል ካንት CRITIQUE OF PURE REASON ድረስ፤ ከሰረን ኪርክጋርድ EITHER OR እስከ ፍሬድሪሽ ኒቾ THUS SPAKE ZARATHUSTRA ድረስ። "ከ ... እስከ" ስላልኩ በእነዚህ መሐል ያሉትን ፈላስሞች መጻሕፍት በሙሉ አንብቤአ ቸዋለሁ ማለቴ አይደለም። ያነበብኳቸው ፈላስሞችም አንኳን ቢሆኑ፥ የጻፏቸውን ሁሉ አንብቤአቸዋለሁ ማለቴም አይደለም። ያንን ለማድረግ የአንድ ሰው ሙሉ ዕድሜስ ይበቃል አንዴ?

የፈላስሞቹ የፍልስፍና ይዘት ደግሞ የአንዱ ከአንዱ ይራራቃል። የአንዱም አንኳን ቢሆን ሁል ጊዜ አንድ አይደለም። ለምሳሌ ቀደም ሲል ያየነው የኤድዋርድ ፊትዝጀራልድ የሩብአያት ትርጉም፥ ኤፊቆሮነትን ጊዜአዊ-ደስታ-ፈላጊ ፍልስፍና ብቻ ያደርገዋል። ዋልት ዊትማን የተረጎማቸው የዑመር ኻያም ሌሎች ቅኔዎች ግን ከጊዜአዊ ደስታ ፈላጊነት ፈንጠር ያሉትን የኤፊቆሮነትን ሌሎች ገጽቶች ያሳዩናል።

ከዚህም ሌላ፥ እኔ የማነብበው አንዳገኘሁ ነው። አያነበብኩ ያለሁትም በግሌ እነጂ በአሰተማሪ እየታገዝኩ አልነበረም። ስለዚህም ፍልስፍኖቹን በየፊርጃ ቸው ላስቀምጣቸው አልችልም ነበር። የተለያዩ የፍልስፍና ፈርጆች እስከ መኖ ራቸውም ያወቅሁት ውዬ አድሬ ነው - ኤፊቆሮነት (EPICUREANISM)፥ ኢስጦኢከነት (STOICISM)፥ ጠርጣሪነት (SKEPTICISM)፥ ሰብአዊነት (HUMANISM)፥ ሕልውናነት[1] (EXISTENTIALISM)፥ ወዘተርፈ። በዚህ ረገድ የረዱኝም እነዚያው የማነብባቸው መጻሕፍት ነበሩ - የዊል ዱራንት THE STORY OF PHILOSOPHY፥ የዊልያም ኢበንስታይን GREAT POLITICAL THINKERS፥ የኤች. ጄ. ብላከሃም SIX EXISTENTIALIST THINKERS፥ የዊልያም ደ ዊት ሃይድ THE FIVE GREAT PHILOSOPHIES OF LIFE፥ ወዘተርፈ።

የሃይማኖታዊነት ወይም የተማልሎታዊነት[2] (MYSTICISM) ይዘት ካላቸው መጻሕፍት መካከል የሞሐመድ ፒክታልን THE MEANING OF THE GLORIOUS KORAN፥ የፒዮትር አውስፔንስኪይን IN SEARCH OF THE MIRACULOUS፥ የማነው ስሙን ZEN BUDDHISM፥ የጂአፍሬይ ፓሪንደርን THE WORLD'S LIVING RELIGIONS ማንሰቤን አስታው ሳሰሁ። ሌሎችም አሉ፤ አንዳንዶቹን በተገቢ ቦታቸው እነሣቸው ይሆናል። የአውስፔንስኪይን መጽሐፍ እንዲያውም በልዩ ትዕዛዝ ነበር ከውጭ ያስመጣ ሁት። አሉን መጽሐፍ በተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶች የነበሩ አንዳንድ ሕንዳውያን መምሕራን ካስሁበት ድረስ በመምጣት አየተዋሱኝ አንብበውታል - አንዱ ከሰሊላው እየሰማ።

ነቅጥቅ ካለው ዱር ውስጥ ነበር የገባሁት - መውጫው ሰጊዜው ከማይታ ወቅ። በድቅድቅ - "ዐይን ቢወጉ በማያሳይ" - ጨለማ ውሰጥ ነበር በዳበሳ እየተጓዝኩ ያለሁት። ከዕለታት አንድ ቀን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባልንጀራዬ ከነበረው ከዓለማየሁ ሸንቁጤ ጋር ስንጨዋወት፥ "ስለ አንተ ሕይወቱን በገዛ እጁ አጠፋ' የሚል መርዶ አንድ ቀን መስማቴ አይቀርም የሚል ሥጋት ሁል ጊዜ በውስጤ አለ" ብሎኛል።

ኅለማየሁ ለሥጋቱ በቂ ምክንያት አልነበረውም አልልም። ሆኖም አኔ እንደዚያ ያለ አሳብ በዚያን ጊዜ በፍጹም አስተናግጄ አላውቅም። ለምን ብዬ? እውነት ነው፤ ከአኔ በፊት ብዙ ሰዎች ለብዙ ዘመናት ከተናነቋቸው ታላላቅ የሕይወት

ጥያቄዎች ጋር መተናነቅ ጀምሬአለሁ - "... ለመሆኑ እኔ ማን ነኝ? ... ከየት ነው የመጣሁት? ... አዚህ ምን አደርጋለሁ? ... ወደ የትስ ነው የምሄደው? ..." ፈልጌም አይደለም አዚህ ዱር ውስጥ የገባሁት። እንዴት እንደ ገባሁበትም እንኳን አላውቀውም። አሁን ግን እንድ ጊዜ ገብቼበታለሁ። መውጫም የለኝም። እነዚህ ጥያቄዎች፥ የሆነ ቦታ፥ መልስ ሳይኖራቸው አይቀርም። በዚህ አካሄዴ ከቀጠልኩ፥ ከመልሶቻቸው ላይ መድረሴም አይቀርም። ዕድሜዬም ቢሆን ፍለጋዬን ለመቀጠል ይፈቅድልኛል። ለምን ብዬ ነው ሕይወቴን በገዛ እጇ የማጠፋው?

"ምን ዐውቄ"ን ተዋወቅሁት

"ያመጣል መንገድ ይወስዳል መንገድ፤
አንድ የሚጠላ አንድ የሚወደድ"

ይባላል አይደል? አዚያው ጂያኖፑሎስ መጻሕፍት መሸጫ መደብር ውስጥ ሆኜ ነው፤ የሆነ መጽሔት አነበብኩ። እና በዚያ ንባብ መንገድነት እንግዳ ነገር ወደ እኔ መጣ። እኔም ከዚያ በፊት ተጉዤበት በማላውቀው በዚያ አንግዳ መንገድ ነጎድኩ። ታሪኩ እንዲህ ነው። በደቡባዊ ሕንድ ይመሰለኛል የምትኖር እንዲት ሴት ከሆኑ ዓመታት በፊት በወሊድ ትሞታለች።

"ከሆኑ" ካልኳቸው ዓመታት በኋላ ደግሞ በሰሜናዊ ሕንድ ያችን "በወሊድ ሞተች" የተባለችውን ሴት ነኝ የምትል ሴላ ሴት ትገኛለች። ጉዳዩ ብዙ ቦታ ይደርሳል። ፖሊስም፥ ዳኛም፥ ጠበቃም ይገቡበታል። የሃይማኖት አባቶች፥ የሕግ እና የዩኒቬርሲቲ ሊቃውንትም ይጨመሩበታል። የሴትዮዋ ቃል በጥን ቃቄ ይመዘገባል። "ነኝ" የምትላት ሴት ሰም፥ የመኖሪያ አድራሻ፥ የወላጆች፥ የባል እና የልጆች ሰም ሁሉ በጥንቃቄ ይመዘገባል።

ከዚያ በኋላ ሴቲቱ በፖሊስ፥ በዳኛ እና በጠበቃ፥ በሃይማኖት አባቶች እና በዩኒቬርሲቲ ሊቃውንት ታጅባ ወደ ደቡባዊ ሕንድ ትወሰዳለች። ከቀናትም በኋላ ሴቲቱ በአድራሻነት ወደ አስመዘገበችው ሰፍራ ይደርሳሉ። ሴቲቱ ትኖር በት የነበረውን ሰፈር እና ቤት በትከከል ታሳያለች። ባሏን እና ልጆቿን ሁሉ በየሰማቸው ለይታ ትጠራቸዋለች። ልታውቀው ያልቻለችው አንድ ሰው ብቻ ነው። አርሱም ለአርሷ በወሊድ መሞት ምክንያት የሆነው ልጅ ነበር። ዛሬ ትልቅ ልጅ ሆኗል።

በአርሲ በኩል የቀረበላትን የምርመራ ፈተና በሚገባ ብታልፍም፥ "ባሴ" ያለ ችው ሰው ግን "ሚስቴ" አላላትም። "ልጆቼ" ያለቻቸው ልጆችም "እናታችን" አላሏትም። ምክንያቱም ይህች ሴት የሞተችውን ሴት አትመስልም ነበር። ይህ "ኬዝ" በሚገባ ዶኪውሜንት ተደርጎ እንደ ተቀመጠ ነው መጽሔቱ የዘገበው።

"ሪኢንካርኔሽን" ከሚባለው አምነት ጋር ፊት ለፊት የተገናኘሁት በዚህ ዐይነት ነበር። እንደዚህ ያለ ነገር ሊሆን ይችላል ብዬ ለማመን በፍጹም አልተዘጋጀ ሁም። "ኬዙ" በደንብ ዶኪውሜንት ተደርጓል ሰለ ተባለ፥ አውነትነቱን ለመጠ ራጠርም በቂ ምክንያት አላገኘሁም። ብቸል ኖሮ፥ ብድግ ብዬ ሕንድ አገር ብሄድ እና ነገሩን ሁሉ "ከፈረሱ አፍ" ብሰማ በወደድኩ። ብዙም ሳልቆይ በናሪዮያያም እንደዚሁ የሚመሰል ነገር ተከሰቶ አንደ ነበረ አነበብኩ። ሰለ ነገሩ የበለጠ ለማወቅ ያደረግሁት ሙከራም "ሪኢንካርኔሽን" መሠረታዊ አስተ ምህሮው ወደ ሆነው ወደ ሂንዱ ሃይማኖት መራኝ። ቀደም ሲል ከዜን ቡድ ሂዝም እና ከሎብሳንግ ራምፓ መጻሕፍት ጋር ንክኪ ሰለ ነበረኝ፥ ጫፍ ጫፉን ሰምቼው ነበር ማለትም እችላለሁ።

አንድ ከሰዓት በኋላ ደግሞ፥ ጂያኖፑሎስ መጻሕፍት መደብር ውስጥ እንዲህ ሆነ። ቢራ ቢሮ ከአበባ ወደ አበባ አንደምትዘል፥ እኔም ከመደርደሪያ ወደ መደርደሪያ እየተዘዋወርኩ አንዱን ሰጥል አንዱን ሳነሣ፥ በጊዜው ታዋቂ በነበረች "ዘ ሳይኮሎጂስት" በተሰኘች መጽሔት ላይ ያነበብኩት አንድ ማስታወ ሻያ ትኩረቴን አጅግ ሳበው -

> የሆነን ሰው እያየኸው ያለኸው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ግን ያንን ሰው ያለ ጥርጥር ከዚህ በፊት የሆነ ቦታ አይተኸዋል። በሆነ አካባቢ አያለፍክ ያለኸው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ሆኖም ያንን አካባቢ በእርግጥ የሆነ ቦታ ታውቀዋለህ። እንደዚህ ያለ ነገር አጋጥሞህ ያውቃል? እንግዲያው ከእኛ ጋር የምትገናኝበት ጊዜ ላይ ደርሰሃል

ይላል። ቁም ነገሩ ብቻ ሳይሆን፥ ማስታወቂያው አራሱ በጣም ነበር የማረ ከኝ። አሰታዋቂው ሰሙን እና በኢንግሊዝ አገር የሚገኝበትን አድራሻውን ሰጥቷል - "AMORC፥ ROSICRUCIAN ORDER" ይባላል። ከማስታወቂ ያው ጋር ሃይማኖታዊ ተቋም አለ መሆኑንም ጨምሮ ገልጾአል።

እኔ እንደዚያ ተለምዶኝ የሚያውቀው ብዙ ጊዜ ነው። እስታዋቂው ሃይማኖ ታዊ ተቋም አለ መሆኑም ተመችቶኛል። በተሰጠው አድራሻ ዕለቱኑም አንኳን ባይሆን በማግሥቱ ወይም በሣልስቱ፣ ጻፍኩላቸው። ወዲያውም የሆነውን እና ያደረግሁትን ነገር ለጓደኛዬ ለአበራ ፈቃዱ ነገርኩት። ከአበራ ጋር አብረን የምንሠራ ከመሆናችንም በላይ በጣም አንቀራረባለን፣ በእሳብም በጣም እንግባባለን።

አበራ ለካስ ያውቃቸው ኖሯል? የረዥም ጊዜ ተማሪአቸው ነው። እንደዚያ ስንቀራረብ እና ስንቱን ምሥጢር ስንከፋፈል፣ እንዴት ይህንን እንዳልነገረኝ ገረመኝ።

"ላይጽፉልህ ይችላሉ" አለኝ።

"ለምን?" አልኩት።

"የራሳቸው የሆነ መስፈርት አላቸው፤ ያንን ማሟላትህን በመጀመሪያ ያረጋግ ጣሉ" አለኝ።

"መስፈርቶቹ ምንድናቸው?" አልኩት።

አልነገረኝም። ከእነጋገሩ እኔን መጠየቅ ሳያስፈልጋቸው፣ ስለ እኔ ማወቅ የሚች ሉበት የሆነ መንገድ እንዳላቸው መለለኝ።

"እስቲ እንግዲህ እንተን ተቀብለው እኔን ሲጥሉኝ አናያለና" በማለት ቀለድኩበት።

አንድ ወር በማይሞላ ጊዜ ውስጥ እንደ ተቀበሉኝ ጻፉልኝ። ፎርም መሙላቴ ወይም አለመሙላቴ ትዝ አይለኝም። የተጠየቅሁትን ከፍያ ከፈልኩ እና የርቀት ተማሪአቸው ሆንኩ። የማነብባቸውን የተለያዩ ጽሑፎች እና መጻሕፍት ይልኩልኝ ጀመር።

ብዙም ሳይቆይ አበራ ጠቅልሎ ወደ ስዊድን ሄደ። ከግል መጻሕፍቱ መካከል የሎውረንስ አፍ አሬብያን SEVEN PILLARS OF WISDOM እና የቪክቶር ሁጎን LES MISERABLES ሥጦታ ሰጠኝ። በአንደኛው ላይ፣ እንደ ነርነሳው ያኑ አቆጣጠር ሚያዝያ 8 ቀን 1966 በጻፈልኝ ማስታወሻ፣ "... OUR SOULS INTERSECT IN COSMIC CONSCIOUSNESS ..." ብሎኛል። ምን ሊለኝ ፈልጎ ይሆን?

ከአበራ ሌላ፣ የ ROSICRUCIAN ORDER ተማሪዎች የነበሩ፣ ሁለት ሰዎች ዐውቃለሁ። አንደኛው በእንድ ወቅት የሥራ አስኪያጄቸን ጸሐፊ የነበረችው የወይዘሮ ፍቅሬ (የእውነት ስሟ አይደለም) ባለቤት ነው። ሰውዬው በአንድ በጣም ትልቅ የመንግሥት ድርጅት ውስጥ ሁለተኛ ሰው ነበረ። አንድ ቀን ወደ ሥ"ራው ለመሄድ ሲነሣ፣ አንድ የተጠቀለለ ነገር ለባለቤቱ ያሳያት እና "እባክሽን ጭኮሬ፣ ይህንን ነገር እንዳትነኪው፤ አደራ!" ብሏት አለቀምጦት ይሄዳል።

ጭኮሬ "ከፋፍቼ እስካየው ድረስ ቆረጠኝ፤ ልሞት ደረስኩ" አለችኝ። እና ከፈተ ችው። ሚታ፣ ሰው ሁሉ ከተኛ በኋላ፣ አሉ ብቻውን ሆኖ እና ሻማ አብርቶ፣ የሚያደርገውን የሆነ ሙከራ (EXPERIMENT) በሚመለከት የተሰጠው መመሪያ ነበር። መመሪያውን የሰጠው አካል AMORC ይባላል። "እቶ በቀለ፣ እንደዚህ የሚባል ስም ታውቃለህ?" አለችኝ። ባለቤቷ ዐልፎ ዐልፎ አራሱን እንደሚያያመውም ዐውቃለሁ።

ሁለተኛው ሰው ተለፋዬ አዱኛ ይባላል። የሲቪል አቪዬሽን መሥሪያ ቤት ባል ደረባ ሲሆን፣ የተገናኘነው ባሌ ጎባ ነው። ተስፋዬ ነገረ ሥራው ሁሉ ከሌሎች ሰዎች ለየት ያለ ነው። መጻሕፍት ማንበብ ይወዳል። ተጨባጭ ያልሆነ ነገር፣ በምናቡ ዓለም ውስጥ ካልሆነ በስተቀር የሌለ ነገር አንሥቶ ሞቅ ያለ ውይይት መክፈት ይችልበታል። WEIRD ልለው አልፈልግም። ብቻ ወደዚያ ይጠ ጋል። እንዴት እንደ ተገናኘን አላስታውስም፤ ነገር ግን በጣም ወዳጆች ሆነ ነበ። አኔም እንደርሱው ስለ ነበርኩ ይሆን እንዴ? አንድ ቀን፣ መኪና ውስጥ ያመሰለኛል፣ ተቀምጠን ስንጫወት የሆነ ነገር ተናገርኩ። የተናገርኩት ነገር ምን እንደ ነበረ አሁን ትዝ አይለኝም። የተናገርኩት ነገር የተስፋዬን ትኩረት ከሚገባው በላይ ሳበ። በመነጽሩ ውስጥ ትኩር ብሎ ረዘም ላለ ጊዜ ካየኝ በኋላ -

"ምን አልክ?" አለኝ። እኔም የተናገርኩትን ነገር ደገምኩለት። በመጨረሻም፣ ዥርጥ አድርጎ -

"አኑተ ማን ነህ?" ሲል ጠየቀኝ። ከጥቂት ጥያቄዎች እና መልሶች በኋላ ሁለታ ችንም የ"AMORC" ተማሪዎች አንደ ሆንን ተዋወቅን። በትምህርቱ ተስፋዬ ከእኔ ይልቅ ብዙ የገፋ ነበረ።

AMORC ምሕጻረ ቃል ነው። ሙሉ መጠሪያው "ANCIENT AND MYSTICAL ORDER OF ROSAE CRUCIS" ነው። እሞርክ ማኅበር (SOCIETY) ሲሆን፥ ዓርማው በመካከሉ ላይ የጽጌረዳ እበባ ያለበት መስቀል ነው። መስቀሉ የሰውን አካል ሲወክል፥ እበባው ደግሞ ከቀላል ወደ ውስብስብ በዝግታ እየተለወጠ (EVOLVE እያደረገ) የሚሄደውን የሰውን ነፍስ ይወክላል። ፍሪሜሰኖችም ምልክታቸው ይህንኑ የሚመስል ሰለ ሆነ፥ በሁለቱ መካከል የሆነ ዝምድና እንዳለ ይታወቃል። እንዲያውም የአሜሪካው ማኅበር አባሎቹ "ሜሰኖች" መሆን እንዳለባቸው ያሰቀምጣል። አሞርክ እንደ አይዛክ ኒውተን፥ ፍራንሲስ ቤከን፥ ረኔ ዴካርት፥ ቤንጃሚን ፍራንክሊን እና ቶማስ ጀፈርሰን ያሉ "ትልልቅ አሳቢዎች" (GREAT THINKERS) እባሎቻችን ነበሩ ይላል።

ከሁሉም ይልቅ ትልቁ እባላቸው ግን ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ "የፀሐይ ከፍሰ ጊዜ" በሚሉት ዘመን ከፍተኛው ሮዚከሩሽያን ነበር። የእርሱን ያህል በትምህርታቸው የተካነ ሌላ የለም ይላሉ። "ማስተር ጂሰስ" ይሉታል። የተማረው በሕንድ እና ቡቲቤት ነው ይላሉ - ዕድሜው ከ12 እስከ 30 ዓመት በነበረበት ጊዜ። ከላኩልኝ መጻሕፍት ውስጥ እንዱ ስለዚህኛው የኢየሱስ የሕይወት ዘመን የሚተርክ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ "የጨረቃ ከፍሰ ጊዜ" በሚሉት ዘመን ግንባር ቀደሙ ሮዚከሩሽያን ነው ይላሉ። ማኅበሩ በሪኢንካርኔሽን ያምናል። አባላቱን ከሞቱ ለዎች መንፈሶች፥ በተለይም ደግሞ "ከትልልቆቹ አሳቢዎች" መንፈሶች፥ ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ ያበረታታል። የሥጋን ሞት "ሽግግር" (TRANSITION) ብሎ ነው የሚጠራው።

እሞርክ ሲበዛ ምሥጢራዊ የሆነ ማኅበር ነው። ጅማሬው ከክርስቶስ ልደት በፊት 1500 ዓመት ላይ በግብፅ እንደ ነበረ ይናገራል። "ወደ አሜሪካ የገባነው በ1694 ነው" ይላል። ከዚያም ለተወሰኑ ዓመታት በንቃት ከተንቀሳቀሰ እና በጣምም ከተሳካለት በኋላ፥ እስከ 20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ድረስ የዘለቀ የ108 ዓመታት "የውጫዊ ዝምታ" ጊዜ መረጥን ይላል። የዝምታው ጊዜ ያበቃው እና በዚህ ስሙ የተመሠረተው በዶክተር ኤች. ስፔንሰር ሉዊስ እንደ ጎርጎሳውያኑ አቆጣጠር በ1915 ነው።

ዶክተር ሉዊስ ደግሞ ከ"ORDO TEMPLI ORIENTIS" (OTO) እና ከአሊስተር ክሮውሌይ ጋር ግንኙነት ነበረው። ኢንግሊዛዊው አሊስተር ክሮውሌይ እራሱን "እውሬ 666" በማለት እንደ ገና እስከ መለየም የደረሰ

ስው ነበር። ዶክተር ሉዊስ ማኅበሩን ሲመሠርት የOTOን ይሁንታ እግኝቶ ነበረ ይባላል። ከላይ ከጠቀስኳቸው መረጃዎች አብዛኞቹን ያገኘሁት ከማኅበሩ ኩተለየሁ ከብዙ ዓመታት በኋላ፥ ከአነርሱ ውጭ ከሆነ ምንጭ ነው።

ሠልስ ያጣሁላቸው ጥያቄዎች እየበዙ መጡ። "ከሃዲ" የመልስ ችግር የለበትም። ከሃዲ ለጥያቄ ሁሉ አጭር መልስ አለው - "እግዚአብሔር የለም" ይላል። "ክሞት በኋላ ሕይወት የለም" ይላል። "ቅዱስም ሆነ ርኩስ መንፈስ የሉም" ይላል። "የለም" ቀላል መልስ ነው። "የለም" የስነፍ መልስ ነው። "የለም" ከእነዚህ ሁሉ ግራ የሚያጋቡ አሳቦች ጋር መተናነቅ የማይፈልግ ሰው የሚሰጠው እጭር መልስ ነው። ከእንግዲህ እኔ "ከሃዲ" አይደለሁም። ቢያንስ ለሎኛ ከሃዲ አይደለሁም። ምክንያቱም ከዚህ ከሚታየው ዓለም በስተጀርባ የሆነ ሌላ ዓለም እንዳለ ሊመስለኝ ጀምሯል።

በለለ በኩል ደግሞ፥ "ሃይማኖተኛም" አይደለሁም። ሃይማኖት ማለት እምነት ማለት ነው። እኔ ደግሞ እምነት የለኝም። ምክንያቱም የሚታመን ምንም ነገር አላገኘሁም። ታዲያ ምንድነኝ? ምን እባላለሁ? "አላዋቂ" ነኝ! ከእንግዲህ "አላዋቂ" ነው መባል ያለብኝ። ማንነቴን የሚገልጸው ትክክለኛው ቃል እሱ ነው። በፍልስፍናው ዓለም እሱም የራሱ የሆነ ለም እንዳለው ዐውቃለሁ - "AGNOSTICISM" ይሰኛል። የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት "ኢታዋቂነት" ይለዋል። እንዲያው በቀላሉ "እነዚህ ነገሮች ከመታወቅ በላይ/ባሻገር ናቸው፤ ስለዚህም ማወቅ አልችልም" ማለት ነው። እሱን ነው "ምን ዐውቄ" ብዬ የተረጎምኩት።

እና "ምን ዐውቄ"ን ተዋወቅሁት። ዞሬ ዞሬ፥ እከራሪነቴን ብቻ ጥዬ፥ ወደ ተነሣሁበት ተመለስኩ ማለት ነው - BACK TO SQUARE ONE እንዲሉ። "ሳያድጉ ሚደግ ያዳግማል" እሉ? ከከሃዲነት ወደ ምን ዐውቄነት የተሸጋገርኩበትን ትክክለኛውን ጊዜ አላውቀውም። ምናልባትም ትክክሰኛ ጊዜ አልነበረ ውም ይሆናል። ምክንያቱም ከሃዲነቴም ሆነ ምን ዐውቄነቴ ሁለቱም ረዘም ላለ ጊዜ በሕይወቴ ሲካሄዱ የቆዩ ሂደቶች ውጤት ናቸው። ሁለቱም ሂደቶች የየራሳቸው የሆኑ ግብዓቶች ነበሯቸው። እንደዚያ ያሉ ሂደቶችም ጅማሬአቸው አና ፍጻሜአቸው መቼ እና የት እንደ ነበረ ቁርጥ አድርጎ መናገር ይከብዳል። በ,ኖስ ለእኔ ከብዶኛል። ብቻ በ1961 ዓ.ም. ጀምሮ የአግኖስቲኩቹን ካምፕ

ሳልቀላቀለው የቀረሁ አልመሰለኝም። እማኝ ባልሆንም፥ ከሃዲ ነኝ ማለትም ያቃተኝ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይመስለኛል።

ናቲ እና ቶሚም?

የዮሐንስ ወንጌሉን ናትናኤልን እና ቶማስን ነው "ናቲ" እና "ቶሚ" ያልኳቸው። ስለ እነዚህ ሁለት የከርሰቶስ ደቀ መዛሙርት ያወቅሁት ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው። ባወቅኳቸው ጊዜ ግን "እኔ እንደ ነበርኩት ነበሩ እንዴ?" የሚል ጥያቄ ተፈጥሮብኛል። ለምሳሌ ናቲ ከበለስ ዛፍ ሥር ምን እየሠራ እንደ ነበረ በትከከል ለመገመት የቻልኩ መስሎኛል - እያሰበ ('እየተመራመረ' ብል ይሻል ይሆን?) ነበር -

> ... ዓለም በከፋት ተሞልታለች ... ባለቤት ያላትም አትመስልም ... መምህሮቻችን ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ጽድቅ እና ስለ ኩነኔ ያስተማሩን ሁሉ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር በፍጹም አብሮ የሚሄድ አይደለም ... ሳንታሰል አልቀረንም ... ይህንን ሁሉ ዘመን? ... አቤት ኪሣራ! ... (ዮሐ. 1፥45-51)።

እንደዚህ እንድገምት የሚያደርገኝ ፊልጶስ መጥቶ "ሙሴ በሕግ መጻሕፍት፥ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉለትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል" ባለው ጊዜ፥ ናትናኤል የሰጠው መልስ ነው - "ከናዝሬት በጎ ነገር ሊወጣ ይችላልን?" አለው። ምን ማለቱ ነው? ሃይማኖታዊ ጥራት ባለበት በይሁዳ አውራጃ፥ በኢየሩሳሌም - በእግዚአብሔር ከተማ፥ በሊቃውንቱ መናኸሪያ - ተፈልጎ የታጣ በጎ ነገር፥ የቅይጦች መኖሪያ በሆነው በገሊላ አውራጃ፥ በናዝሬት ከተማ፥ በሸቃዮቹ መንደር፥ እንዴት ሊገኝ ይችላል?" ማለቱ ነበር።

ቶማስስ ቢሆን? በሙሉ ጊዜው፥ ማለትም "ሐዋርያ" ከተባለ በኋላ ጌታን በተከ ተለባቸው ሦስት ያህል ዓመታት ውስጥ እራት ጊዜ ያደረጋቸውን አጫጭር ንግግሮች የዘገበልን ወንጌላዊው ዮሐንስ ብቻ ነው። እርሱም ስለ ቶማስ በተናገ ረበት ቀዳሚ ዘገባው "ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ" ይለዋል (ዮሐ. 11፥16)። ዐዋ ቂዎቹ እንደሚሉት የዕብራይስጡ "ቶማስ" እና የግሪኩ "ዲዲሞስ" ሁለቱም ትር ጓሜአቸው "መንታ" ማለት ነው። ቶማስ መንትያ ወንድም ወይም እኅት እንደ ነበሩት ማረጋገጥ ግን አልተቻለም። ስለዚህም ይህ "መንታነት" የሕይወት መንገድ መንታነት፥ የአመለካከት መንታነት ሳይሆን አይቀርም የሚሉ አሉ።

በዮሐንስ የተዘገበልን የመጀመሪያው የቶማስ ንግግር የተደረገው ከአልዓዛር ሙታመም እና መሞት ጋር በተያያዘ ነው። አልዓዛር በታመመ ጊዜ እኅትማማ ቹቹ ማርያም እና ማርታ ወደ ኢየሱስ መልእክተኛ ላኩ። ኢየሱስ ግን የአልዓ ዛርን መታመም ከሰማ በኋላ በነበረበት ቦታ ሌላ ሁለት ቀናት ቆየ። ከዚያ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን "ወደ ይሁዳ እንመለስ" አላቸው። በዚህ ጊዜ ደቀ መዛ ሙርቱ "መምህር ሆይ፤ ከጥቂት ጊዜ በፊት አይሁድ በድንጋይ ሊወግሩህ እየፈ ለጉህ ነበር፤ እንደ ገና ወደዚያ ትሄዳለህን?" አሉት። ኢየሱስም "... ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቷል፤ እኔም ከእንቅልፉ ላስነሣው እሄዳለሁ" አላቸው። እነርሱም "ጉንፉ ከሆነስ ይድናል" አሉ።

አልተግባቡም ነበር። እርሱ የሚናገረው ስለ መሞቱ ሲሆን፥ እነርሱ ደግሞ ስለ ሙኾኙ እንደ ተናገረ መስሏቸው ነበር። ስለዚህ ነገሩን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ነበረበት - "አልዓዛር ሞቷል ... አሁን ግን ወደ እርሱ እንሂድ" አላቸው። በዚህ ጊዜ ነው፥ "ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ" ለተቀሩት ጓደኞቹ፥ "እኛም ሄደን ከእርሱ ጋር እንሙት" ያላቸው። ለምንድነው እንደዚህ ያለው? ግልጽ የሆነው ምክንያት ከጥቂት ቀናት በፊት አይሁድ ኢየሱስን በድንጋይ ሊወግሩት እየፈለ ጉት ስለ ነበረ ነው።

እውነት ነው፥ ያ እደጋ አሁንም አለ። አደጋው ያለውም በኢየሱስ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በደቀ መዛሙርቱም ላይ ነው። ቶማስም ከኢየሱስ ጋር ለመሞት ቆር ጧአል። የአልዓዛር ከሞት መነሣት ግን ለምን አልታይህ አለው? በኢየሱስ እገዛማሎት ከዚህ በፊት ሌሎች ሙታን ሲነሡ አላየም ይሆን? እነርሱንስ በላካ ቸው ጊዜ "... ሙታንን እስነሡ ..." ብሏቸው አልነበረም? (ማቴ. 10፥5-8)። እንድም ምውት፥ በአንዳቸውም እጅ፥ አልተነሣም ነበር ማለት ነው?

ቶማስ ሲናገር የምንሰማበት ሁለተኛው አጋጣሚ የተፈጠረው ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "... የምሄደው ሰፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው። ሄጀም ሰፍራ ካዘጋጀሁ ላችሁ በኋላ፥ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልመሰዳችሁ ዳግ መኛ እመጣለሁ። እኔ ወደምሄድበትም ሰፍራ የሚያደርሰውን መንገድ ታውቃላችሁ" ባላቸው ጊዜ ነው (ዮሐ. 14፥1-4)። ቶማስም "... ወዴት እንደ ሃምትሄድ እናውቅም፤ ታዲያ መንገዱን እንዴት ማወቅ እንችላለን?" አለ።

ለሦስተኛ ጊዜ ቶማስ ሲናገር የምናገኘው ኢየሱስ ከተሰቀለ፥ ከሞተ እና ከተቀ በረ ከሦስት ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱ "ጌታን እየነው እኮ!" ባሉት ጊዜ ነው (ዮሐ. 20፥24-25)። "በምስማር የተቸነከሩትን የእጆቹን ምልከቶች ካላየሁ፥ ምስማሮቹ በነበሩበት ቦታ ጣቴን ካላደረግሁ፥ በጎኑም እጄን ካላስገባሁ አላምንም" አላቸው። መጀመሪያ ነገር፥ ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ በተገለ ጠላቸው ጊዜ ቶማስ አብሯቸው ያልነበረው ለምንድነው? የትንሣኤው ወሬ ከጠዋት ጀምሮ በከተማው ሲወራ ነበር የዋለው። እንደዚያ ባለ ጊዜ እርሱ ከጓደኞቹ ተለይቶ የመጥፋቱ ምክንያት ምን ይሆን? ቀጥሎም አብሯቸው የኖረ፥ ደኅና እድርጎ የሚያውቃቸው ዐሥር ለዎች፥ በሐያ ዐይኖቻቸው "እየነው እኮ!" ሲሉት እንዴት "አላምንም" ይላቸዋል?

ቶማስ፥ የጓደኞቹን ብቻም ሳይሆን፥ የራሱንም ሁለት ዐይኖች ለማመን አልተ ዘጋጀም። "በሚስማር የተቸነከሩትን የእጆቹን ምልከቶች ካላየሁ፥ ሚስማሮቹ በነበሩበት ቦታ ጣቴን ካላደረግሁ፥ በጎኑም እጄን ካላስገባሁ አላምንም" ነው ያላቸው። ቶማስን "ለማመን ማየት እና መለማት የማይበቁት ለው" ሆኖ እናገ ኘዋለን። ቶማስ፥ ለማመን ከማየት እና ከመስማት በተጨማሪ "መንካትም" የሚያስፈልገው ሰው ነበር። ለምን ይሆን እንደዚያ የሆነው? ከዚህ ቀደም በዐይኖቹ እና በጆሮቹ ተታልሎ ይሆን እንዴ?

የመጨረሻው የቶማለ ንግግር በዮሐንስ ወንጌል 20፥28 ላይ የተመዘገበልን ነው። ይኸኛው አጋጣሚ የተከሠተው ሦስተኛው አጋጣሚ ከተከሠተ ከአንድ ሣምንት በኋላ ነው። ቶማለን ጨምሮ ደቀ መዛሙርቱ በቤት ውስጥ በነበሩ በት፥ በሮቹም በተቆለፉበት፥ ኢየሱስ መጣ እና በመካከላቸው ቆመ። "ሰላም ለእናንተ ይሁን" ካላቸው በኋላ፥ በተለይ ቶማስን "... ጣትህን ወደዚህ እምጣ፤ እጆቼንም ተመልከት፤ እጆችህን ዘርጋና በጎኔ አስገባ፤ እትጠራጠር፤ እመን" አለው። በዚህ ጊዜ ቶማስ "ጌታዬ፤ አምላኬም!" አለው ይላል።

ቶማስ ያን ዕለት የተመለሰለት በኢየሱስ ከሙታን መነሣት ላይ የነበረው ጥያቄ ብቻ አይመስለኝም። ያን ዕለት የተመለሰለት ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ በኢየሱስ "ጌትነት" እና "አምላክነት" ላይ ጭምር በውለጡ ሲጉላላ የኖረው ጥያቄ ነው የሚመስለኝ። እንዴ? ቶማስኮ አይሁዳዊ ነው። አይሁድ ሙታን እንደሚነሡ አስቀድመውምኮ ያውቃሉ (ዳን. 12፥2)። ነቢዩ ኤልሳዕ የሞተ

ልጅ ማስነሣቱን (2ነገ. 4)፥ ዐፅሙም ትኩስ ሬሳ ነፍስ እንዲዘራ ማድረጉን (2ነገ. 13፥21) ቶማስ ሳያውቅ አይቀርም።

ከ፫ጓደኞቹ ሦስቱ ሙሴ እና ኤልያስ ከምድር ላይ ከጠፉ ከስንት እና ስንት መቶ ኅሥታት በኋላ ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ እንዳየአቸው ሲያወሩም ላይሰማ አይቀርም (ማቴ. 17፥1-5)። እግዚአብሔር የሚኖረው በሰማይ እንደ ሆነ፥ ኢየሱስም ወደ ምድር የመጣው ከአባቱ ዘንድ መሆኑን እና ወደዚያውም እንደሚመለስ በተለያዩ ጊዜያት ሲናገር ቶማስ አብሮት ነበረ። እንዴ? ቶማስኮ ተራ ጣዖት አምላኪ አልነበረም።

ሆኖም ቶማስ "አምነሃል" የተባለው ከኢየሱስ ትንሣኤ በኋላ በሣምንቱ ነው - እሱ ዕሑድ በአገራችን "ዳግማይ ትንሣኤ" ለመባሉ ምክንያቱ ቶማለ ይሆን እንዴ? ቶማስ እለከዚያች ቀን ድረስ "አማኝ" አልነበረማ! ጴጥሮለ "አንተ ክርስ ቶስ የሕያው አግዚአብሔር ልጅ ነህ" ሲለው (ማቴ. 16፥16) አልሰማም? "ክርስ ቶስ" (መሲሕ) ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ትንሽም እንኳን ቢሆን ግንዛቤ አለነበረውም? አልዓዛርን ከሙታን ሲያስነሣውስ አላየም? - በሞቶ በአራተኛ ቀኑ? "ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፉ ሌሎች አያሌ ታምራዊ ምልከቶችን በደቀ መዛሙርቱ ፊት አድርጓል" ተብሎ ተጽፏል እኮ! (ዮሐ. 20፥30)

አይ፥ ቶማስ ለምቷል። አይ፥ ቶማስ አይቷልም። ግን እስከዚያች ቀን ድረስ ለክ እንደ ሰሙ ገና "መንታ" - ምን ዐውቄ፥ አግናስቲከ - የነበረ ነው የሚመስ ለኝ። ከሃዲ አይደለም፤ ይከተለዋልና። አማኝም አልሆነም፤ ገና "ጌታዬ፤ አምላኬ" አላለውምና። ለዚህ ነው የቶማስ ነገር ከተራ መጠራጠር ያለፈ የሚ ሆንብኝ። ከብዙ ዓመታት በኋላ ወንጌሉን ሲያጽፈው፥ መንፈለ ቅዱስም ስለ ቶማስ ወደ ዮሐንስ የሚያመጣቸው ትውለታዎች፥ የቶማለን ማንነት ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩት እነዚህ አራት ልዩ ገጠመኞች ናቸው። ያለ ምክንያትም አይመስለኝም።

ነፍስማ ነፋስዋ!

ሠ፤ ታርፋለች? ለማለት ነው። ባበጀንላት "ሣጥን" ውስጥ - ሣጥኑ ምን በኢያሳር፥ ምን ቢስማማን - መቼ በጅ ብላ ትቀመጥልናለች? እንዲያው ዝም ብላ ትነፍስዋለች እንጂ! በእነዚያ ዓመታት ነፋስዋ ነፍሴ ከምትነፍስባቸው አጋጣጫዎች አንዱ ግጥም መጻፍ ነበረ። በ1960 ዓ.ም. "የኢትዮጵያ ድርሰት

ማኅበር"[3] የግጥም ውድድር አዘጋጀ እና ተወዳዳሪዎችን በዜና ማሠራጫ ጋበዘ። ዜና ማሠራጫው ምን እንደ ነበረ ትዝ አይለኝም። ግጥሙ እንዲያሟላቸው የሚፈለጉ መስፈርቶች ነበሩ። የማሰታውሰው "ከ50 መስመር በማይበልጥ" መባሉን ብቻ ነው። አዲስ ግጥም ለመጻፍ በቂ ጊዜ አልነበረኝም። ስለዚህም በ1958 ዓ.ም. የጻፍኳትን ባለ 48 መስመር ግጥም መረጥኩ። አብራኝ ትሠራ የነበረችው ኪሮሰ መንገሻ በጽሕፈት መኪና ተየበችልኝ እና ላከሁላቸው።

<u>ሞናሊዛዬ ነሽ</u>

ሕልም ነው ያ ጊዜ
ሥራዬን ዘንግቼው፥
በሰሜት ጠንብዤ
አብሬሽ ያለፈው።

መዓት ነው ያ ምሕረት
ተቀምጠሽ እሳኔ፥
"ልጅነቴን ይቅጨው፥ እወድሃለሁ፥ ሙት!"
ስትይ የሰማሁሽ፥ ያየሁሽ በዐይኔ።

ያ አውነት ሐሰት ነው
ዓለም ባዶ ሆና፥ የምሠራው ባጣ፥
ዐይኖቼን ከድጌ፥ ገለጥ ሳደርጋቸው
አፍሽን ከአፌ ያጋጠመው ጣጣ።

ቅዠት ነው ያ ገሐድ
ዕንባሽ ክብለል ብሎ የገባው ካፋችን፥
"ደኅና ደሪ" ልልሽ፥ ልቆም፥ ትቼሽ ልሄድ
የቀረኝን ብርታት፥ ያለቸኝን ወኔ፥ ያደረጋት ውድም።

ኅዘን ነው ያ ደስታ
በአንቅልፌ ያሣቀኝ፥
ዕብደት ነው ያ ትዝታ
በውኔ ያስለቀሰኝ።

ሁሉድ ነው ያ ቃልሽ
"ተጋብተን አ'ኖራለን፤ ፍቅርን አንቀጫለን"
የሚለው መሐላሽ
"ሞት ነው የሚለየን!"

ተረት ነው ያ ታሪክ
ከነፉውን ከደጉ ልለይ ያልቻልኩበት፥
የመኖር ልምምድ፥ የመኖር ንትርክ
የማይሆነኝ ትምህርት።

ባለ ሕይወትነትሽ
ሣር፡ቋል በኔ ዘንዳ፥
ሥዕል ነሽ፥ ቅርጽ ነሽ
ለትሆኚኝ አትችይም፥ ዘመድ ወይም ባዳ።

ያህ የማይሞት ገላ
ያህ በድን ሰውነት፥
አያወፍር አይከሳ፥ አይጨከን አይራራ
ያለመኖር ውበት።

የፈጠሩሽ ቀቢው፥ ቀለሙ፥ ብሩሹ
ምን ነካቸውና?
እንዲህ አበላሹ
ሕይወት ነሱሽና?

ታውቂኝ አይምሰልሽ
እትሳሳች መውደድ፥
አላየኝም ዐይንሽ
ኅሊናሽ አይበድ።

የነፍሴ ቁራኛ
ብቻዮቴ የኛለሽ፥
ያሳቢ ጓደኛ
ሞናሊዛዬ ነሽ።

ግጥሜ በውድድሩ ሦስተኛ ወጣች። አንደኛ የወጡት፥ ምናልባት ከ200 መስመሮች በማያንሰው ግጥማቸው፥ "ጸሐፌ ትዕዛዝ" ነበሩ። መቼም ማንኛችንም ብንሆን አርሳቸውን ልናሸንፍ አንችልም። ሁለተኛ የወጣውን ሰው ስም እረሳሁት። አራተኛው በጊዜው በጣም ታዋቂ የነበረው ሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስ ነው። አሸናፊዎቹ በወወከማ አዳራሽ ሕዝብ በተሰበሰበበት ግጥሞቻችንን አነበብን። በማግሥቱ ነው መሰለኝ፥ የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር የበላይ ጠባቂ የነበሩት ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት "ጌቶቹ" ፊት አቀረቡን - ታላቁ ቤተ መንግሥት። ሰለ አገባባችን እና አወጣጣችን ቀደም ሲል ትንሽ ሥልጠና ብጤም ሰጡን።

ደጃዝማች ግርማቸው ሰለ ኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር እና አሁን በግርማዊነታቸው ፊት ሰለ ቀረብነው ሰዎች (ጸሐፌ ትዕዛዙ ከመጀመሪያውም ጀምሮ አብረውን አልነበሩም) አጭር መግለጫ ሰጡ። ንጉሠ ነገሥቱም ከጉዳዩ ጋር ጨርሶ ተያያዥነት የሌለውን ንግግር አደረጉልን። ትንሽም ተቆጡን - "ለምንድነው ታሪክ የማትጽፉት?" አሉን። እኔ ንግግራቸውን መከታተል አቃተኝ። የጃጁም መሰለኝ። ሣቅም አፈነኝ።

ከኢጋጣሚው ያገኘሁት ጥቅም "ፊታቸው ይፋጃል፤ ዐይናቸውንም ትክ ብሎ ማየት አይቻልም" ሲባል አሰማው የነበረውን "ተረት" ማስተባበል መቻሌ ብቻ ነበር። እጅ ነስተን ሰንወጣ፥ የኋሊት አንድንሄድ የተሰጠንን ትምህርት ዘንግቼው ከሁሉ ፊት ቀድሜ ወጣሁ። ደረጃውን በሩጫ መውረዴን እና ድምፄን አሰምቼ መሣቄን አስታውሳለሁ። ሻምበል አፈወርቅ ከኋላዬ መጣና አፌን በአጁ ግጥም አድርጎ ይዞ፥ "አንተ ልጅ፥ ታስጨርሰናለህ!" አለኝ።

ከበሩ እንደ ወጣን፥ ደጃዝማች ግርማቸው ደረሱብን እና "ጌቶቹ አልተረዱንም፤ ተመልሼ ማስረዳት አለብኝ" ብለውን ወደ ኋላ ተመለሱ። በግሌ ተረዱን አልተረዱን ግድ አልነበረኝም። የኢትዮጵያ ሬድዮ በምሣ ሰዓት ሥርጭቱ የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር ባዘጋጀው የግጥም ውድድር አሸናፊ ለሆኑ ሰዎች ንጉሡ ያደረጉትን - በበታው የነበርነው ሰዎች ያልሰማነውን - ንግግር አሰማን። ከዚያ በኋላ በቀጥታ የሚተላለፍ (ላይቭ) ካልሆነ በስተቀር፥ ዜና ማሠራጫዎች "ተባለ" አያሉ የሚናገሩትን አንዳንዱን ወሬ ማመን እየቸገረኝ መጥቶ ነበር።

የእኔ ግጥም ከነፎቶግራፌ በሐያ ሰምንተኛ ዓመት ቁጥር ስድሳ ሁለት አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ወጣች። እኔ ጋዜጣውን አላስቀረሁም። ግጥሞቼንም ካቃጠለኳቸው ይህችን መጽሐፍ በምጽፍ ጊዜ 35 ዓመታት ዐልፈውኛል። ምንም ሃሪ አልነበረችም ማለቴ ነው። በ1996 ዓ.ም. ወደ አሜሪካ ሰትሄድ የጋዜጣውን ቁራጭ የሰጠችኝ አኅቴ አዘነጋሽ ናት። እንደ ነገረችኝ ግጥሙን ከጋዜጣው ላይ ቀድዳ ያሰቀመጠችው ሌላዋ አኅቴ አስካለ ናት። ጋዜጣው የታተመበት ቀን ያለበትን የጋዜጣውን አካል ከተጣለው የጋዜጣው አካል ጋር አብራ ጥላዋለች ማለት ነው። ለዚህ ነው ወሩን እና ቀኑን ማወቅ ያልቻልኩት። ይህ በሆነ በጥቂት ወራት ልዩነት ይመስለኛል "ሞናሊዛዬ ነሽ" የተባለው የኮነላሁን ገሠሠ ነጠላ ዜማ ተለቀቀ። የግጥሙ ደራሲም ተወዳጁ የስፖርት ጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማ አንደ ሆነ ታወቀ።

ማስታወሻ

1. በቅንፍ ውስጥ በኢንግሊዝኛ የተጠቀሱትን የፍልስፍና ፈርጆች "ጠርጣሪነት"፥ "ስብእዊነት" እና "ሕልውናነት" ብሎ የተረጎማቸው የ"ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት" ነው። ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፤ 1978።
2. እንደ ላይኛው።
3. ማኅበሩ በሽለመኝ መጽሐፍ ላይ ያለው ማሕተም እንደዚሁ ነው የሚለው፤ የዛሬው ስያሜው "የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር" መሰለኝ።

ምዕራፍ አራት

ማለስለስ እና ማንኳኳት

መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ልብ በዕርሻ ቦታ ይመስለዋል። በትንቢተ ኢሳይያስ 5፥1-7 ላይ የእስራኤል ቤት በወይን ዕርሻ ተመስሎ እናገኘዋለን። ያም ዕርሻ መልካም የወይን ፍሬ ያፈራ ዘንድ ባለ ዕርሻው፥ ማለትም እግዚአብሔር፥ ሰለ አደረገለት ከብካቤ እናነባለን፦

> ለዕርሻነት ለምለም እና ኮረብታማ ቦታ መምረጡን፤
>
> መሬቱን መቆፈሩን እና ድንጋዩንም ለቅሞ ማውጣቱን፤
>
> ምርጥ የሆነውን የወይን ዘር መትከሉን፤
>
> ወይኑን ከእዕዋፍ መከላከያ ማማ በዕርሻው መከከል መሥራቱን።

በዚህ ምሳሌ መሠረት፥ የወይኑ ዕርሻ መልካም የወይን ፍሬ ያፈራ ዘንድ ሁለት ባለ ድርሻ አካላት አሉ ማለት ነው - ባለ ዕርሻው እና ዕርሻው እራሱ። ምሳሌው ባለ ዕርሻው ይህንን ሁሉ ከብካቤ ካደረገለት በኋላ፥ የወይኑ ዕርሻ መልካም ፍሬ ሳይሆን ኾምጣጣ ፍሬ ማፍራቱን ይነግረናል። ስለዚህም ባለ ዕርሻው በወይኑ ቦታ ላይ ሊወስድበት ያሰበውን የቅጣት እርምጃ በቅድሚያ ያስታውቀናል፦

> ዐጥሩን እነቅላለሁ፤ ለጥፋት ይጋለጣል፤
> ግንቡንም እፈርሳለሁ፤ መረጋገጫም ይሆናል።
> የማይኮተኮትና የማይታረም ጠፍ መሬት አደርገዋለሁ፤
> ኩርንችትና እሾኽም ይበቅልበታል፤
> ዝናብም እንዳይዘንብበት ደመናዎችን እዝዛለሁ።

ለዕርሻው ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በመዝራት ጊዜ ለዘሩ እና በመውቃ ትም ጊዜ ለሚወቃው አህል ጭምር፥ ከብካቤ እንደሚያደርግ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ከዚያው ከኢሳይያስ መጽሐፍ ላንወጣ ሌላ ምሳሌ እነሆ፦

> ገበሬ ሊዘራ መሬቱን ሲያዘጋጅ ያለማቋረጥ ያርሳልን?
> ጓሉን ሲከሰክስ፥ ዐፈሩን ሲያለሰልስ ይከርማልን?
> ዕርሻውን አስተካክሎ፥ ጥቁር አዝሙድና ከሙን አይዘራምን?
> ስንዴውንስ በትልሙ፥ ገብሱን በተገቢ ቦታው፥
> እጃውንም በተመደበው ስፍራ እይዘራምን? ...
> ጥቁር እዝሙድ በመውቂያ መሣሪያ አይወቃም፤
> ከሙን የሠረገላ መንኮራኩር አይሄድበትም፤
> ጥቁር እዝሙድ በበትር፥ ከሙንም በዘንግ ይወቃል።
> እንጀራን ለመጋገር እህል ይፈጫል፤
> ስለዚህ አንድ ሰው ለዘላለም እህል ሲወቃ እይኖርም።
> የመውቂያውን መንኮራኩር ቢያኼድበትም፥ ፈረሶቹ እይደፈጥጡትም።
> ይህ ሁሉ የሚሆነው በምክሩ ድንቅ በጥበቡ ታላቅ ከሆነው፥
> ከሰራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። (ኢሳ. 28፥24-29)

ይኸኛው ምሳሌ፥ እንደኛ የማሣው አዘገጃጀት እንደሚዘራው ዘር ዐይነት የተለ ያየ መሆኑን እና ሁለተኛ ደግሞ የእግዚአብሔር ቅጣቱም እንኳን ቢሆን እንደ ሥቃጩው ማንነት የሚለያይ መሆኑን ነው የሚነግረን - ለጥቁር እዝሙድ በትር፤ ለከሙን ዘንግ፤ ለእንጀራ እህል ደግሞ ወፍጮ። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ያለውን ጉዳይ በግል ሳይሆን በወል ያስኬደባቸው ጊዜዎች እና ሁኔታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች የሚያስተምሩን ግን፥ እግዚአብሔር በወል ሳይሆን በግል ከሰው ጋር ስለሚያደርጋቸው መስተጋብ ሮች ነው።

በአዲስ ኪዳንም ውስጥ ጌታ ኢየሱስ የሰውን ልብ በማሣ መስሎታል (ማቴ. 13፥1-23)። ማሣውንም "መንገድ ዳርማ"፥ "ድንጋያማ"፥ "እሾኻማ" እና "ጥሩ መሬት" በማለት በአራት ከፍሎታል። በአራቱም ዐይነት ማሣዎች ላይ "የእግ ዚአብሔር መንግሥት ቃል" የተባለ አንድ ዐይነት ዘር የተዘራባቸው ሲሆን፥ ለፍሬ የበቃው ግን "ጥሩው መሬት" ላይ የተዘራው ዘር ብቻ ነው። ችግሩ ከዘሩ ወይም ከዘሪው ሳይሆን ከማሣው እንደ ነበረ እንድንረዳ ነው የተፈለገው።

ለላም ምሳሌያዊ አነጋገር አለ፦ "እነሆ፤ በደጅ ቆሜ እንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ሰምቶ በሩን ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ ገብቼ ከእርሱ ጋር እበላለሁ፤

እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል" (ራእ. 3፥20)። ይህ "ደጅ/በር" የተባለ ነገር፥ ያው ከላይ "ዕርሻ"፥ "ማሣ"፥ "ዐፈር"፥ ያልነው የሰው ልብ መሆኑ ነው። እዚህኛው ምሳሌ ላይ ግን በቀደሙት ምሳሌዎች ውስጥ ያላየነው አዲስ አሳብ - ጊዜ - ተጨምሯል። በአንድ ሰው "በር" ላይ ይህ "ማንኳኳት" የተባለ ነገር የሚጀምረው መቼ ነው? የሚቀጥለውስ እስከ መቼ ነው? በቀደሙትም ምሳሌዎች ውስጥ ቢሆን - በውስጠ ታዋቂነት ነው እንጂ - የጊዜ ጉዳይ ነበረ። ዐፈሩን ለዘር ማዘጋጀት ወይም ማለስለስ "ጊዜ" ይጠይቅ የለም?

ይህንን "ጊዜ" ያልነውን አሳብ በሌላ ምሳሌም ውስጥ እናገኘዋለን። በሉቃስ 15፥1-7 ላይ ያልጠፉበትን 99 በጎች በሜዳ ላይ ጥሎ፥ የጠፋበትን አንድ በግ ለመፈለግ ስለ ሄደው "ባለ ብዙ በጎች" የሆነ ሰው እናነባለን። ባለ በጉ የጠፋውን በጉን የፈለገው "እስኪያገኝ ድረስ" ነው። መፈለግ፥ እስኪያገኙ ድረስ መፈለግ፥ ጊዜ የሚጠይቅ ሥራ ነው። ሂደት ነው።

ይህችን መጽሐፍ ለመጻፍ ስነሣሣ፥ እግዚአብሔር በሕይወቴ ያከናወናቸውን የማለስለስ እና የማንኳኳት ሂደቶች ወደ ኋላ ተመልሼ በጥንቃቄ እንዳስባቸው ተገድጃለሁ። ብዙ ነበሩ፤ ልዩ ልዩም ነበሩ። የወለዱትም ጊዜ ረዥም ነበረ። ስለዚህም በአካል አንድ ጊዜ በተጓዝኩበት በዚያ መንገድ ላይ በአሳብ ደግሞ ብዙ ጊዜ ተመላልሼበታለሁ።

መልስ ያላገኘሁላቸውን ብዙ ጥያቄዎችም ጠይቄአለሁ -

> "... በዚህ ጊዜ ... በዚህ ቦታ ... በዚህ ሁኔታ ... እግዚአብሔር በሕይወቴ ጣልቃ ባይገባስ ኖሮ? ... ይልቁንስ እንዲህ ሆኖ ቢሆንስ ኖሮ? ... እንዲህ ሆኖ ባይሆንስ ኖሮ? ... ይህን ያህል ጊዜ ባላገኝስ ኖሮ? ... ወዘተርፈ።"

ጎላ ጎላ ብለው የታዩኝን ሂደቶች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አነሣቸዋለሁ። በተቻለኝ መጠን እንደ ተከናወኑበት የጊዜ ቅደም ተከተል ላቀርባቸው እሞክራለሁ። አሰፈላጊ በሚሆን ጊዜ፥ የተከናወ ኑበትን ወቅትም እጠቅሣለሁ።

በምዕራፍ ሁለት እና ሦስት ውስጥ ያነሣኋቸው - ሁለቱ "ቀኝ" እና "ግራ" አከራሪነቶቼ፥ ከሃዲነቴ እና ምን ዐውቄነቴ - የዚሁ "ማለስለስ እና ማንኳኳት" ያልኩት ሂደት አካል ነበሩ። በጥም ከተቃጠለ ሰው በስተቀር፥ የቀዝቃዛ ውሃን ጥቅም የሚያውቅ ማን ነው? በጨለማ ውስጥ እየተደናበረ ከኖረ ሰው በስተ ቀር፥ የብርሃንን ልዩነት የሚረዳ ማን ነው? ያ ወቅት ለእኔ "በጥም የተቃጠ

ልኩበት"፤ "በጨለማ የተደናበርኩበት" ወቅት ነበር። ለእስራኤል ሕዝብ የሙሴ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያደርሳቸው ሞግዚት እንደ ሆናቸው ሁሉ (ገላ. 3፥23-25)፥ ለእኔም እነዚያ ሂደቶች ወደ ክርስቶስ እንድደርስ የረዱኝ ሞግዚቶቼ ነበሩ ለማለት እችላለሁ - ያ ግን ገና ከብዙ ሌሎች ሂደቶች በኋላ የሆነደርስበት ነገር ነው።

የልጅነት ወራት

የተወለድኩት መጋቢት 19 ቀን 1934 ዓ.ም. ነው። አባታችን ልጆቹ የተወለድን ባቸውን ቀኖች በዳዊቱ የውስጥ ገጽ ላይ ጽፎታል። አሁን የት እንደ ደረሰ አላውቅም እንጂ፥ ዳዊቱም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ነበረ። በመወለድ ለወላጆቼ አራተኛ ሰሆን፥ በማደግ ግን ሁለተኛ ልጃቸው ነኝ። ፊደል መቁጠር የጀመርኩት በአራት ዓመት ከአራት ወር ዕድሜ ላይ ነው። በኋላ እንደ ተረዳሁት፥ ተጨማሪዋ "ከአራት ቀን" በእኛ ቤት የምትታወቅ አልመሰለኝም።

መንግሥት ትምህርት ቤት መቼ እንደ ገባሁ አላውቅም። በካብቷን እየተከተ ልኩ "ልጃገረዶች ትምህርት ቤት" እሄድ እንደ ነበረ ግን አስታውሳለሁ። አስተማሪዋ ብዙነሽ ጥበቡ ትባላለች። በውስጤ ተሥሎ የቀረው የአንዲት በዕድሜዋ መካከለኛ፥ በቁመቷ መለስተኛ፥ ቀጭን እና ቁንጮ፥ የሆነች ሴት ሥዕል ነው። ትምህርት ቤቱ ብዙም ዕድሜ አልነበረውም። ወዲያው እነ በካብቷ ወደ ማጀት ተመለሱ፤ እኔም መንግሥት ትምህርት ቤት ገባሁ። የገባሁበት ትምህርት ቤት "የወንዶች ትምህርት ቤት" ወይም "የኢንግሊዝ ትምህርት ቤት" እየተባለ ነበር የሚጠራው።

ከአስተማሪዎቻቸን አብዛኞቹ ደብተሮች ነበሩ - አለቃ ወልደ ሩፌ፥ ደብተራ ገብረ መድኅን፥ ደብተራ ወንድማገኘ፥ አለቃ ተሾመ፥ አቶ መሐሪ፥ ግራ ጌታ ኃይሉ። አማርኛ ማንበብ እና መጻፍ፥ ደግሞም የአማርኛ ሰዋስው ያስተምሩ ነበር። ቀድሞም ቢሆን ዘመናዊ ትምህርት ሥር የሰደደ ስላልነበረ፥ ከአምስቱ ዓመት የኢጣልያን ወረራ በኋላ በአገሪቱ በጠቅላላው የመምህራን እጥረት እንደ ነበረ ይታወቃል። እኔ በገባሁበት ትምህርት ቤት እንደ ኢንግሊዝኛ ሰዋንድ፥ ሂሣብ እና ሳይንስ፥ ታሪክ እና ጂኦግራፊ፥ ጂምናስቲክ እና የእጅ ሥራ፥ ሥዕል እና መዝሙር፥ የመሳሰሉትን ዘመናዊ ትምህርቶች የሚያስተምሩ

መምህራን ቀስ በቀስ፣ እየዋሰ እና እያደረ ነበር የመጡት። ክፍተቱን በመሸፈን እስተዋጽዖ ያደረጉ ሁለት ሕንዳውያን መምህራንም ነበሩ።

ፊደል የሚያስቆጥሩት አስቃ ወልደ ሩፌ ስለ ሆኑ፣ አዲስ ተማሪ ስእርሳቸው ነው የሚሰጠው። እና እኔም ስእርሳቸው ተሰጠሁ። ሆኖም እኔ ፊደል ብቻ ሳይ ሆን፣ ንባብም ጭምር እሞክር ስስ ነበረ፣ አለቃ ወልደ ሩፌ ፊደል የማሰቆጠሩን እድካሚ ሥራ ስእኔ ሰጥተው፣ እርሳቸው ወይ ያንጎላጀሉ፤ ወይም ወዲያ ወዲህ ይላሉ። አባቴ በመንግሥት ሥራ ሄዶ ክቆየበት ሲመለስ፣ ስንተኛ ክፍል እንደ ደረስኩ ጠየቀኝ። እኔ "ክፍል" የሚባል ነገር እስክ መኖሩም አላውቅም ነበር። አለቃ ወልደ ሩፌ ክፍል መሆኔን እና ተማሪዎቹን ፊደል ሳስቆጥር እንደምውል ነገርኩት።

አባቴ አበደ። በማግሥቱ ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ አብሮኝ መጣ። ከአለቃ ወልደ ሩፌም ጋር ተጣላ። "እንዴት ቢሆን ነው ስመሆኑ አንድ ተማሪ ስዚህን ያህል ጊዜ ፊደል ክፍል የሚቆየው? እስክ መቼ ነው የእኔ ልጅ የእርስዎን ተማሪዎች ፊደል ሲያስቆጥር የሚኖረው?" በማለት ሲጮኽባቸው ትዝ ይለኛል። አለቃ ወልደ ሩፌ እንዳች የመለሱለት አልመሰለኝም። ያን ዕለቱኑ ወደ ሁለተኛ ክፍል ተዛወርኩ። ወሩን አላስታውስም፤ ዘመኑ ግን 1944 ዓ.ም. ነበር።

ዘመን መቁጠር የጀመርኩት በዚያ ዓመት ነው። አንድ ከሰዓት በኋላ ከትም ህርት ቤት ስመለስ፣ በቢታችን ወንድ ልጅ ተወልዶ ደረስኩ - "ህዳር 24 ቀን 1944 ዓ.ም." ብዬ በአእምሮዬ መመዝገቤን በትክክል አስታውሳለሁ። የአራተኛው ታናሽ ወንድሜ የልደት ቀን ነበር።

በቢታችን መጻሕፍት እንደ ጉድ ይነበባሉ። መጻሕፍት በቢታችን ያልነበሩበትን ጊዜ አላስታውስም። አዳዲሶችም በላይ በላዩ ይጨመራሉ። በዚያን ዘመን ለተማሪዎች በነጻ እንደሚሰጡት እንደ ዐውደ ንባብ፣ የእንስሳት አገልግሎት፣ ታሪክ እና ምሳሌ (ክአንደኛ እስክ ሦስተኛ መጽሐፍ)፣ ወዘተርፈ ያሉት ብቻ ሳይሆኑ፣ እንደ እነ የዕውቀት ብልጭታ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ የዓለም ታሪክ፣ ያሉ ትልልቅ መጻሕፍትም በቢታችን ነበሩ። የክበደ ሚካኤል መጻሕፍትማ ትርኒ ሞቹም፣ ግጥሞቹም፣ ልብ ወስዶቹም፣ አንዲያው ሁሉም ነበሩ ለማለት እችላለሁ።

ለዚህ ምክንያቱ አባታችን በመጀመሪያ የማዘጋጃ ቤት፣ ቀጥሎም የትምህርት ሚኒሰቴር ሠራተኛ የነበረ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ እንድናውቅ የነበረው ብርቱ ጉላጎት ይመስለኛል። መጻሕፍቱን ሁሉ ልጆቹ ሁሉ - በካብቷ፣ እኔ እና እስካስ እናንብባቸዋለን። የግጥም መጻሕፍቱን የምናነብባቸው በፍቅር እና በፍላጎት ስለ ነበረ፣ እየደጋገምን ነበር የምናነብባቸው። ግጥሞቹን በሞላ ቢቃላችን ይዘና ቸዋል። የማታነብበው እናታችንም እንኳን ሳትቀር እኛ ስናነብባቸው ክመስ ማት ብዛት እንዳንዶቹን በቃሷ ይዛቸዋስች።

አባቱ ዐልፎ ዐልፎ "ና፣ ጋዜጣ ታነብባስህ" እያስ ግድግዳው ላይ "በዘመናዊ ሞድ የወንዶች ጫማ ሰፊ" የሚል ትልቅ ጽሑፍ ወደ ተለጠፈበት ሱቅ ያወስደኛል። በኋላ እንደ ተረዳሁት ባስ ሱቆቹ ባቡ እና በጩ የሚባሉ ወንድ ማማቾች ናቸው። ባንያኖች ናቸው ሲሉ እስማለሁ። የማነብበው ጋዜጣ እንዲ ሰጡኝ ለእንዳቸው ይነግራቸውና፣ እኔን እዚያው ትቶኝ እርሱ ወደ ሚሄድበት ይሄዳል።

የእባቴ ምኞት ምን እንድሆንለት እንደ ነበረ አላውቅም። እኔ ግን ጋዜጦቹን ይቅርና፣ እንደ እነ ታሪከና ምሳሌ፣ የዕውቀት ብልጭታ፣ የመሳለሉት መጻሕ ፍትም እንኳን በውስጣቸው ያጨቋቸውን ታላላቅ ቁም ነገሮች ማስተዋል የጀመርኩት አሁን አሁን ዕድሜዬ ከገፋ በኋላ ነው።

"ሃታ አሳ"

ተወልጀ ባደግሁበት አቅራቢያ የሚኖሩ "ሃታ አሳ" (የውሃ ስው) የሚባሉ ሰዎችን ዐውቃስሁ። ያ መጠሪያ የተሰጣቸው ክውሃ በሰተቀር ጠላ ወይም አረቄ ስለማይጠጡ ነው። አብዛኞቹ የሰዶ ክተማ ነዋሪዎች እነዚህን ጠላ ወይም አረቄ የማይጠጡ ሰዎች "ጸረ ማርያም" ይሏቸዋል። ይኸኛው ሰያሜ ለምን እንደ ተሰጣቸውም ክልጅነቴ ጀምሮ ዐውቃለሁ። "የሱሳ እሳ" ሲባሉም ሰምቻለሁ። (የኢየሱስ ሰዎች ማለት ነው)። እነዚህ ሰዎች ሁሉም የአገሬው ሰው፣ ማለትም ዎላይቶች፣ ናቸው። በብዛት የሚገኙትም ክሰዶ ክተማ ወጣ ብሎ፣ በተስይም ደግሞ በአቶና ነው። አቶና የሚስዮኖቹ ሰፈር ነው። በሰዶ "ሐኪም ቤቱ" ያለው በአቶና ሲሆን፣ ሐኪሞቹም በሙሉ ፈረንጆች እና ሦላይቶች ናቸው።

በአቶና ሆስፒታል ለተመላላሽ ሕሙማን የሕክምና አገልግሎት መስጠት የሚጀመረው በየጠዋቱ መጽሐፍ ቅዱስ ከተነበበ እና ጸሎት ከተደረገ በኋላ ነው። በልጅነቴ ከቤተ ሰቤ አባላት እንዱ ታምሞ በአጃቢነት፥ ወይም ደግሞ እኔው አራሴ ታምሜ በታካሚነት ወደ አቶና ሆስፒታል የሄድኩባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው። ምንም እንኳን በጊዜው በእኔ ላይ ያስከተለው ምንም ዐይነት ለውጥ ባይኖርም፥ አቶናን በነበኝሁባቸው ጊዜያት ሁሉ በጸሎት አየተደገፈ የተነገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በጆሮዬ ወስጥ ፈስሷል።

እርሱም ብቻ አይደለም፤ የሚሰስ ባርሎውን "ብስኩት" ስመብላት እና ከፍራፍ ሬዎቿም ተደብቆ ለመቅጠፍ በየሳምንቱ ዕሑድ ወደ አቶና የሚሄዱ የዚያን ጊዜዋ ሶዶ "የእራዳ ልጆች" ነበሩ። ሚስስ ባርሎው የሰንበት ተማሪዎቿ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት በመጡ ቁጥር የምትሰጣቸው ሽልማቶችም ነበሯት። በአብዛኛው በተለያየ መጠን የተዘጋጁ የወንጌል ከፍሎች ናቸው። ደጋግመው ለሚመጡ ልጆች፥ ሽልማቶቹም ከፍ አያሉ ይመጣሉ። እኔም ከእነዚህ የእራዳ ልጆች ጋር አንድ ሁለቴ ወደ አቶና ሄጃለሁ።

ስሁለት ዓመታት በተከታታይ ወደ አቶና የሄድኩበት ሌላው አጋጣሚ የጸረ ማርያሞቹ የኮንፈረንስ ጊዜ ነው። ስስ ኮንፈረንሱ የነገሩኝ እና ይዘውኝ የሄዱት እነዚያው የእራዳ ልጆች ናቸው። ኮንፈረንሱ የሚካሄደው ቀኑን ሙሉ ቢሆንም፥ እኛ ግን የሄድነው በማታው ከፍለ ጊዜ ላይ ነበር። ያኔ ነው የኤሌከ ትሪከ መብራት ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት። ሕዝቡ ጉንዳን ነው። እኛ የሄድነው ለማየት እና ስማሸፍ ስለ ነበረ መቀመጥ አላስፈለገንም እንጂ፥ እንቀመጥ ብንል ኖሮም እንኳን መቀመጫ አልነበረም። ሣሩ ላይ ነው ሕዝቡ የሚቀመጠው። እንደ ጉድ ይዘምራሉ። ስብከቱም ሆነ መዝሙሩ በዎላይትኛ ነው። አንዳንዶች ደግሞ በየመሐሉ አየተነሡ የሆነ የሆነ ነገር ይናገሩ እና "ጌታን አመሰግኑልኝ" ይላሉ። "ምስክርነት" የምንለው ነገር መሆኑ ነው። ጉባዔው በእንድ ድምፅ "ጌታ ይመስገን!" ይላል።

"ጸረ ማርያሞቹ" በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁት "ፕሮቴስታንት" በሚለው ስያሜአቸው እንደ ሆነ ያወቅሁት ቆይቶ ነው። የራሳቸው የሆነ ትምህርት ቤትም በአቶና ስስ ነበራቸው፥ ከመካከላቸው የማውቀው ትልቅ ሰው ይቅርና ተማሪም እንኳን አልነበረም። ለመጀመሪያ ጊዜ ያወቅሁት ፕሮቴስታንት አቶ ተስፋዬ ባላ ይመስሉኛል - የትምህርት ቤታችን "ሐኪም" ሆነው በመጡ ጊዜ።

"የጠና ባለሞያ" የሚሰው አጠራር ያኔ አይታወቅም ነበር። የአርሳቸውን ሥምጣት ቀድሞ ይሁን ወይም ተከትሎ አላውቅም፥ ልጃቸው ብርሃኑ ተስፋዬም የትምህርት ቤታችን ተማሪ እና ባልንጀራችን ሆኗል።

ከአርሳቸው ቀጥዬ ያወቅሁት ፕሮቴስታንት ጋሼ ሙሉ መጀ ሳይሆን አይቀ ርም። እርሱም የትምህርት ቤታችን "ሐኪም" ነበረ። ወንድሙ ቄቻሞ መጀ ደግሞ የከፍል ጓደኛዬ ነበር። በኋላ ላይ፥ ጋሼ ሙሉ የሕክምና ሞያውን ትቶ የሕማ ተማሪ ሆኗል። ከዚያም በፓርላማ አባልነት፥ በተለያዩ እርከኖች በዳኝነት እና በጥብቅና ሞያ ለረጅም ጊዜ አገልግሏል። አቡቱ ዳና መጀ የዎላይታ ቃሰ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪ ናቸው - ቤተ ክርስቲያኗ ከተመሠረተች ከሦስት ዓመት ገደማ በኋላ[1] እና እኔ ከመወለዴ አምስት ዓመት ገደማ በፊት ጀምሮ።[2]

የአቶና የመጨረሻው ትዝታዬ ወደ ሰኔ ወር 1950 ዓ.ም. ያመጣኛል። አቡቱ በረጠና ታምሞ በሆስፒታሉ ተኝቷል። ደም ያስቀምጠዋል። በእኛ በቤተ ሰቦ ቹም ሆነ በሐኪሞቹ ዘንድ ይተርፋል የሚል ተስፋ ተቆርጦአል። ሐኪሞቹ ከእኛ ጋር በአባታችን አጠገብ ተቀምጠው በግራማፎን የመዝሙር ሸከላ ያጫ ወቱለታል። ከመዝሙሮቹ ሁሉ -

> ወንድሞቼ፥ እን-ገሥ-ግስ-
> የምንጠራበት ያ ቀናችን ሳይደርስ

የሚል አዝማች ያለው መዝሙር እንዴት አድርጎ እንደ አናወጠኝ አልረሳ ውም።

በመጀመሪያ ከሌሎች ጋር በመተጋገዝ አባቴን ወደ መጸዳጃ ቤት ሳመላልሰው፥ ለመነሣት ካቃተው በኋላም ከውስጡ የሚወጣውን ጥቁር እና ፖፖ ሙሉ ያም ስመለከተው፥ ወደ መጸዳጃው ቤት አየወሰድኩም ስደፋው፥ ፖፖውንም በውሃ ሳለቀልቀው፥ ከዚያ በፊት ተሰምቶኝ የማላውቀው የከንቱነት ስሜት ተሰ ማኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ይመስለኛል፥ አሰቀስኩ። "ጦሽ" ብዬ መፍረጤ አስከ ሚመስለኝ ድረስ አሰቀስኩ።

በዚያው ወቅት የከርስትና አባቴ የአቶ ተስፋዬ ዓሊ ልጅ እና አብሮ አደጌም የሆንችው ጌጤ የመጀመሪያ ልጇን ልትወልድ በጽኑ ምጥ ተይዛ በዚያው ሆስፒ ታል ተኝታ ነበረች። በጣም የምንቀራረብ ቤተ ሰቦች ከመሆናችን የተነሣ፥ የሞቱም ሆነ የልደቱ ጣር የሁለቱም ቤተ ሰቦች የጋራ ጣር ሆኖ ነበር። የእርሷ

ቤተ ዘመዶች እኛ ወዳለንበት፥ የአባታችንም አሲታማሚዎች አርሷ ወዳለችበት እንመላለሳለን። ሐኪሞቹ አባቴን ወደ ቤቱ እንድንመልሰው ነግረውን በታላቅ ኀዘን ከሆስፒታሉ ለንወጣ፥ ጌጤ ደግሞ ወንድ ልጅ ተገላገሰች። ሁላችንም ሰለ ተወለደው ሕፃን ደስ አለን፤ ሊሞት ስላለው ጎልማሳም እዘንን። በበኩሌ ከዝንጉርጉሯ ዓለም ጋራ በግል እና በግላጭ መተዋወቅ መጀመሬ ነበር። አባቴ በዚያው ቀን - ሰኔ 14 ቀን 1950 ዓ.ም. - አመሻሹ ላይ ሞተ።

በኋላ እንደ ተረዳሁት፥ በሽክላ ተቀርጾ የሰማሁትን ያንን ሕይወቴን ያነቃነቀ ያሬዳዊ ዝማሬ የዘመሩት መምሬ ለለሺ ወልደ ሚካኤል ናቸው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቄስ ነበሩ። ሲበዛ ድምፃዊ ናቸው። ያንን መዝሙር የዘመሩት ከሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር[3] ሚስዮናዊያን ጋር ከተገናኙ እና ሕይወታቸውን ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከሰጡ በኋላ ነው። ገነት እና እኔ ከእርሳቸው ጋር የመተዋወቅ እና አንዳንድ ጊዜም አብረናቸው የማገልገል ዕድል አግኝተናል።

ኤስ. አይ. ኤም. ለሚባለው የሚሰዮን ድርጅት ወደ ዎላይታ መግባት፥ ለቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም ለመጀመሪያ ጊዜ በደቡብ ኢትዮጵያ መመሥረት፥ እግዚአብሔር ምክንያት ያደረጋቸው ሰው ዶክተር ቶማስ ላምቤ ይባላሉ። በሞያቸው ሐኪም እና በደቡብ ምሥራቅ ሱዳን የአሜሪካ ፕሪስቢቴርያን ሚሲዮን መልእክተኛ ነበሩ። ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ከነበሩበት ከደቡብ ሱዳን ሊሆን፥ የገቡትም በኅዳር በሽታ የተነሣ ብዙ ሰው ያለቀባቸው የሰዮ (ደቡብ ምዕራብ ወለጋ) ገሸር (ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል) ባቀረቡላቸው ጥሪ መሠረት ነው።[4]

ቶማስ ላምቤ የኢትዮጵያን ዜግነት ከመቀበል አንሥቶ፥ በአገሪቱ ሃይማኖታዊ፥ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የመሳተፍ ጸጋ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ሰው ነበሩ። ሆኖም ወቅቱ ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን የወረረችበት በመሆኑ፥ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የአንዳንዶች ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ታማኝነት በጽኑ የተፈተነበት ወቅትም ነበር። ከዚህም የተነሣ፥ አንደ አንዳንዶቹ የኢትዮጵያውያን ሰሞች ሁሉ፥ የቶማስ ላምቤም ስም በበጎ ብቻ ሳይሆን በከፋም የሚነሣበት አጋጣሚ ተፈጥሯል። ወንድዬ ዓሊ "አሜሪካዊው ላምቤ"፥ "ኢትዮጵያዊው ላምቤ"፥ "ባይተ

ዋሩ ላምቤ"፥ እና "የመጨረሻው ጽዋ" በሚሉ ርእሶች ከፋፍሎ የእኚህን ሰው ታሪክ ለአማርኛ አንባቢያን ጥሩ አድርጎ በአጭሩ ዘግቦታል።[5]

በጎለም ዙሪያ ለብዙ ሚሊዮኖች ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው የኅዳር በሽታ፥ ለዶክተር ቶማስ ላምቤ ወደ ኢትዮጵያ መግባት እና ለወንጌል አገልግሎት ብም በምዕራብና በደቡብ ኢትዮጵያ መለፋፋት፥ ምክንያት ሆኗል። እንደ አንዳ ንሥቱ የኢትዮጵያውያን ስሞች፥ የቶማስ ላምቤን ሰም ጨምሮ እንደ አንዳን ሥቱም የውጭ አገር ሰዎች ስሞች፥ የ"ኅዳር በሽታ"ም ስም ባደረሰው ቁሳዊ ጥፋት ብቻ ሳይሆን፥ ባስከተለው መንፈሳዊ ልማትም ጭምር፥ ይነሣል። ታሪክ ግለትሰ ይኸው አይደል?

ያልተሞተባቸው ሞቶች

ዕድሜዬ ዐሥራ አምስት ዓመት አለከሚሞላ ድረስ፥ ሞት አምስት ጊዜ በላዬ አንዣቧል። እናቴ ከበካብቷ በፊት አንዲት ሴት ልጅ፥ ከእኔም በፊት አንድ ወንድ ልጅ ቀብራለች። በሰባት ዓመት ውለጥ ሁለት ልጅ ማለት ነው። በዚያ ተንድታለች። በትዳሯም ብዙ ደስተኛ እንዳልነበረች ሰትናገር ሰምቻታለሁ። ከቤተ ለቦቿም ርቃ "በሰው አገር" ነው የነበረችው። ማኩረፊያ የሚሆናት ዘመድ በቅርቧ አልነበረም። አና እኔን ማርገዟን ባወቀች ጊዜ ልታስወጣኝ ፈለገች።

በሰዎች ምክር፥ "እሬት አድምቼ፥ ደሙን በጣሳ ምልቼ፥ ጠጣሁ" ትላለች። አጥወልውላት እና አዙሯት እንደ ወደቀች፥ አራሷንም እንደ ሳተች ትናገራ ለች። ሽል ለማስወጣት ያደረገችው ነገር፥ ሕይወቷን ወደ ማጣት ሊያደርሳት ነበር። ያደረገችውን ነገር በሆነ መንገድ ያወቁ ለዎች፥ ተሯሩጠው "ማርከሻ ሠጉ" አደረጉላት። ብዙ ወተት እንዳጠጡአት መሰለኝ ለትናገር የሰማኋት። አርሷም ከሞት ተረፈች፤ እኔም በጤና ተወለድኩ።

ከዕሰታት አንድ ቀን ከበካብቷ ጋር ድልህ ሰርቀን በላን አሉ። በዕድሜ እርሰዋ ዘመነኝ እኔ ደግሞ ሦለት ዓመት አይሞላንም። አንዴ ከቀመስነው በኋላ ጣፊ ጠን መለለኝ፥ ሲያቃጥለን በላዩ ውሃ እየጠጣንበት፥ ማለሮ ሙሉ ድልህ በል ተን ጨረስን አሉ። እናቴ ከሄደችበት ስትመጣ፥ በካብቷ ታለቅሳለች፥ እኔ ተዝርፌአለሁ። የሆነውን ነገር ለማወቅ እናታችን ጊዜ አልወሰደባትም። ቤቱ

በድልህ ሽታ ታውዷል። ሆዴ ተቆዝሯል፣ ዐይኔ ተጎልጉሏል። ስኻፌጅ ይዝረበ ረባል፣ ትንፋሼ ቅትት ቅትት ይላል።

አቶ ብርሃነ መስቀል ተጠራ። እንደ መጣ እና የሆነውን ነገር እንደ ዐወቀ እኔን፣ በምን እንደ ሆነ እንጃ፣ ይዞኝ ወደ "ኢንግሊዞች ሐኪም ቤት" በረረ አሉ። "ከኢንግሊዞቹ ጋር አብሮ ይሠራ ነበር ... ኢንግሊዝኛውን ልከ እንደነሱው አኮ ነው የሚናገረው ... ፈረንጅ አገር አይደል የተማረው? ..." ትላለች እናቴ በኩራት - ስለ አርሱ በተነካ ቁጥር። ሐኪሞቹ ሆዴን ሙልጭ እድርገው አጠቡት አሉ። ውስጤ የገባው ድልህ አንድም ሳይቀር፣ በላይ ሳይሆን በታች፣ እንዲ ወጣ ተደረገ። "ሞተህ ነበር፤ ዕድሜ ስብርሃነ መስቀል በል፣ ተረፍከ" ትለኛለች።

አቶ ብርሃነ መስቀል እየስ፣ የአማሆይ እይመኩ ወንድም የአባ ወልደ ማርያም ልጅ ሊሆን፣ ያሳደጉት ግን "እየስ" የሚባሉ ሰው ናቸው። በነሐሴ ወር 1922 ዓ.ም. አገራችን ስትምህርት ወደ ግብጽ ከላከቻቸው ስድሳ ተማሪዎች መካከል እንዱ ነበረ። ተማሪዎቹ የተላኩት በግብፅ ቤተ ክርስቲያን በተሰጠ ስኮላርሺፕ መሠረት ነው። ተማሪዎቹ ካይሮ ሲደርሱ፣ ከእንድ የሃይማኖት ትምህርት ቤት አስገቧቸው እና ዐረብኛ ቋንቋ ተማሩ አሏቸው። በዚህ ጊዜ አብዛኞቹ በኢን ግሊዝኛ ወይም በፈረንሳይኛ ቋንቋ ካልሆነ በስተቀር በዐረብኛ ቋንቋ እንማርም ብለው ዓመፁ። ካመፁት እና ከዐሥራ አንድ ወራት ቆይታ በኋላ ወደ እገራቸው ከተመለሱት አርባ ተማሪዎች መካከል ብርሃነ መስቀል እየስ እንዱ እንደ ሆነ ብላታ መርስዔ ኀዘን ጽፈዋል።[6] አልተቀራረብንም እንጂ፣ እኔም በኋላ ላይ ከእርሱ እና ከልጁ ከተዘራ ጋር ተዋውቄአለሁ።

አንድ ቀን ከበካብቷ ጋር ተጣላን እና መጥፎ ስድብ ሰደብኳት። እናታችን በጊዜው እቤት አልነበረችም። ከሄደችበት ስትመለስ በካብቷ የሆነውን ሁሉ ነገ ረቻት። እናቴ ተቆጣች፤ በጣም ተቆጣች፤ እጅግ በጣም ተቆጣች። መታችኝ፤ በጣም መታችኝ፤ እጅግ በጣም መታችኝ። ቁጣው እና ዱላው እስከደከም ድረስ ስብዙ ስዓታት ቀጠለ። በመጨረሻ "ባለጌን ካሳደግ፣ የገደለው ጸደቀ አሉ" አለች እና ልትገድሰኝ ተነሣች። ገመድ ሸመቀቀች እና ከቤታችን ወጋግራ ላይ ይሁን ወይም የሆነ አግዳሚ ላይ እሰረችው። ከዚያ እኔን ካስሁበት እንሥታ እና ተሸከማ ወስዳ፣ ዐንገቴን ሸምቀቀው ውስጥ ስማስገባት ታገለች። እኔም "እልሞት ባይ ተጋዳይ" ሆኜ፣ ባስ በሌለ ኃይሌ ታገልኳት።

በካብቷ ኡኡታውን አቀለጠችው። ጊዜው ማታ ነው። ከሌሊቱ ሁስት እና ሦስት ሰዓት ሊሆን ይችላል። በጊዜ የተጀመረ ቁጣ እና ዱላ ነው እስከዚያ ሰኅት እና እስከ "ትሞታታስህ - እልሞታትም" ትግል የደረስው። እርስዋ በተደጋጋሚ አየተሸከመችኝ ወደ ገመዱ ስትወስደኝ፣ እኔም በተደጋጋሚ ከእጇ እያመለጥኩ ስወድቅ ወይም ስሮጥ፣ በካብቷም ጩኸቷን ስታቀልጠው፣ ብዙ የቶየን ይመስለኛል። ጩኸቱን የሰሙ የጎረቤት ሰዎች ቢደርሱም፣ በሩን ቀር ቅራ አላስገባም አለቻቸው። ቢለምኗት፣ ቢሷት ቢሠሯት፣ አምቢ አለች። ነውጭ በብዙ ትግል፣ ከውስጥ በበካብቷ ትብብር በሩ ተከፍቶ ሲገቡ፣ እኔ በጣም ደከሜ ነበር። እንድ ሌላ ሙከራ ስማድረግ ጊዜ አግኝታ ቢሆን ኖሮ አለቆልኝ ነበር። ዘመኑ 1945 ወይም 1946 ዓ.ም. ይመስለኛል።

እንዳታዝን ወይም ያቄምኩባት እንዳይመስላት በማሰብ፣ እናቴ በሕይወት እያለች ይህንን ነገር እንሥቼው አላውቅም። አሁንም ያነሣሁት እግዚአብሔር በሕይወቴ ያደረገውን ነገር የግድ መናገር ስለ አለብኝ ነው። ስለዚያን ዕለቱ ከስተት የገባኝ ነገር ቢኖር፣ እናቴ ያደረገችውን ነገር ሁሉ ያደረገችው ዐውቃ፣ ወድዳ እና ፈልጋ እንዳይደለ ነው። ይልቁንም በሕይወቷ ከነበረ፣ ብርቱ ከሆነ የረኩሳን መናፍስት ተጽዕኖ የተነሣ እንደ አደረገችው ነው የገባኝ። እቴቴዋን ከሁወች፣ ከቆረበች እና ስብዙ ዓመታት በምንኩስና ከኖረችም በኋላ፣ በእኔ ግሥት ከዚያ ተጽዕኖ ነጻ አልወጣችም። እንደበቷ ተይዞ ስለ ነበረ፣ በመጨረሻ ዎቷ ምድራዊ ቀኖቿ እግዚአብሔር በውስጥዋ ያደረገው ነገር ይኖር እንደ ሆነ ግን አላውቅም።

ሞት በላዬ ያንጣበበበት አራተኛው አጋጣሚ የተፈጠረው በ1947 ዓ.ም. ነው። ሰው ሁሉ በየጓሮው እና በየማሣው በቆሎ የሚዘራበት የየካቲት ወር ነበረ። እናታችን፣ ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ ወላጆቿን ስመጠየቅ ወደ አደገችበት አገር ሄዳለች። በካብቷ የደረሰች ልጃገረድ ስለ ነበረች፣ ነጋሽ ደግሞ ገና የሦስት ዓመት ልጅ ስለ ነበረ፣ ሁለቱን ይዛቸው ሄዳለች። ካሣ ከአከስታችን ከአበራሽ ጋር ድጉና ነው ያስው። በቤቱ ያለነው እኔ እና አስካስ ብቻ ነበርን - የዐሥራ ሦስት እና የዐሥር ዓመት ልጆች። ትታን የሄደችው ከእማማ ይሻሙ ጋር ቢሆንም፣ እማማ ይሻሙ ግን አሁን ከእኛ ጋር አልነበሩም። ከደጃችን ባስው ሉላ ቤት ውስጥ በኪራይ የሚኖሩ፣ ስሸመና ሥራ ወደ ሶዶ የመጡ፣ ሦስት የሚሆኑ የዶርዜ ብሔረ ስብ ተወላጆች ብቻ አሉ።

አንድ ቀን ጠዋት በቆሎ እንዘራለን ብለን አስካለ እና እኔ ተነሣን። ሁለት ጣት ያለው፥ በዎላይትኛ "ጢኬ" የሚባል መቆፈሪያ ይዘናል። አየተቀባበልን በዚያ ጢኬ መሬቱን ለንቆፍር፥ እንዴት እንደ ሆነ ሁሊታችንም ሳናውቀው፥ በአስካለ እጅ የነበረው ጢኬ አንድ ጣት ከመሐል አናቴ ጀምሮ ግንባሬ ድረስ አራሴን አረለው። ደም በደም ሆንኩ። አስካለ ጮኸች። ዶርዜዎቹ ጎረቤቶቻችን መጡ። የሆነውን ነገር ሲያዩ አፋፍሰውኝ ወደ ሐኪሞቹ መንደር ወደ አቶና ወሰዱኝ። ፀጉሬ ተላጭቶ፥ በቁስሉ ላይ መድኀኒት ተደርጎ እና ታሽጎ፥ በሌላ ቀን እንድንመጣ ታዝዘን፥ ወደ ቤት ተመለስን።

ቁስሉ ሞቀሞቀ። ለብዙ ወራት ወደ አቶና ተመላለስኩ። ትምህርት በአብዛኛው አያቋረጥኩ ዓመቱን ጨረስኩ። ሰለዚህም አምለተኛ ከፍል ደገምኩ። አሁን፥ ወደ ኋላ ተመልሼ ሳስበው፥ በውስጤ አንዳንድ ጥያቄዎች ይፈጠራሉ - "... እንዴት ቢሆን ነው የጢኬው ሁለቱም ጣቶች ሳይሆኑ አንዱ ጣት ብቻ የወጋኝ? ... እንዴትሰ ቢሆን ነው የጢኬው ጣት በቀጥታ አናቴ ውስጥ መተከል ሲችል፥ ከመሐል አናቴ አስከ ግንባሬ ድረስ ላዩን አርሶኝ ያለፈው? ..." "አትሙች ያላት ነፍስ" አሉ?

ከአራተኛው የሞት ማንኣበብ አገግሜ ብዙም ሳልቆይ ነበር አምለተኛው እና የመጨረሻው ማንኣበብ የተከሠተው። ጥቅምት 23 ቀን 1948 ዓ.ም. የጃንሆይ የዘውድ በዓል የብር ኢዮቤልዩ ነበረ። በትምህርት ቤታችን ለዚህ በዓል በሥዕል፥ በቅርጻ ቅርጽ እና በመዝሙር ዝግጅት ማድረግ የተጀመረው ካለፈው ዓመት ጀምሮ ነው። አንዳንድ ተማሪዎች አዲስ አበባ ሊላኩ እንደሚችሉ ሁሉ ተነግሮናል። እኔ ያለሁት በሥዕሉ እና በመዝሙሩ ዝግጅት ውስጥ ነበር። የዕለቱ ዕለት በዓሉ ቡተከበረበት በ"ደጃች በየነ ግቢ" እንደ ጉድ ዘመርን። በዓሉ በድንቅ ተከበረ። ወደ ቤት ስመለስ፥ እኔም ለብዙ ወራት ባስተኛኝ እና ለሞትም ባሠጋኝ ሕመም ታምሜ ወደቅሁ።

ለረዥም ጊዜ አህል በቅጡ አልቀመስኩም። አራሴንም አላውቅም ነበር። አባቴ "ልጅህ ሊሞት ነውና በነፍሱ ድረስ" ተብሎ ተላከበት። አልደረሰም፤ በፊን ታው ግን ለአባ መላኩ (በኋላ ፓትርያርክ ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ) ደብዳቤ ጽፎ ላከ። ደብዳቤው የደረሰው ከሞት ካፋረስኩ በኋላ ስለ ነበረ ይመስለኛል፥ እኔም አንብቤዋለሁ - "... አባታችን! እኔ ኃጢአተኛው እያለሁ ምንም የማያውቀው ልጄ እንዳይሞት አባከዎ ይጸልዩልኝ ..." ይላል። በአባቴ

ተማጽኖ መሠረት፥ አባ መላኩ ጸልየውልኛል። አቤታችን ድረስ በተደጋጋሚ እየመጡም አይተውኛል። እምለተኛ ከፍል ሰለሰኩ።

ትብብሩ እና መዝሙሩ

ቶማስ ላምቤ በየካቲት ወር መጨረሻ 1920 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ሲያቀኑ የአሜሪካ ፕሪሰቢቴርያን ሚሰዮን መልእክተኛ አልነበሩም። አራሳቸው የመሠረቱት "እቢሲንያን ፍሮንቲየር ሚሽን" የተባለ የሌላ አሜሪካዊ ሚሲዮን ድርጅት መልእክተኛ ነበሩ። ብቻቸውንም አልነበሩም። የእርሳቸውን የሚሰዮን ድርጅት "ሱዳን ኢንቲርየር ሚሽን" ከተባለ፥ በካናዳ ከተመዘገበ፥ የሚሰዮን ድርጅት ጋር አሰተባብረው አና ከሌሎች ሚስዮናውያንም ጋር ተባብረው ነበሩ።

በደቡብ ኢትዮጵያ የተሠራው መጠነ ሠፊ የወንጌል አና የልማት ሥራ፥ ከለሜን አሜሪካ የሆኑት የእነዚህ የሁለቱ የሚሰዮን ድርጅቶች አገልግሎት ውጤት ብቻ ግን አልነበረም። በአስተምህሮ ጭምር የሚለያዩ የብዙዎች ሚስዮን ድርጅቶች ትብብር ውጤት ነበር። በዚያ ትብብርም ውስጥ ዋነኛው ተዋናይ በ1940ዎቹ መጨረሻ ላይ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ የዘለቀው "ኖርዌጅያን ሉተራን ሚሰዮን" የተባለው አውሮፓዊ ድርጅት ነው።

የኖርዌጅያን ሉተራን ሚስዮን ወደ ደቡብ ኢትየጵያ ሲገባ፥ ሌሎች የሚስዮን ደርጅቶች አንዲተባበሩት ጥሪ አቅርቦላቸው እንደ ነበረ አና አነርሱም ለጥሪው አዎንታዊ ምላሽ እንደ ሰጡት የሚመለከሩ መጻሕፍት አሉ። ከተባበሩትም መካከል ከሉተራውያኑ የአይሰላንድ፥ የዴንማርክ፥ የፊንላንድ አና የፊሮይ የሚሰዮን ድርጅቶች ሲገኙ፥ ሉተራውያን ካልሆኑት መካከል ደግሞ የኤስ. አይ. አ.ም. አና የባይብል ቸርችሜንስ ሚስዮናዊ ማኅበር ይገኛሉ። ከዚህም ሌላ፥ ኖርዊጂያን ሉተራን ሚስዮን በደቡብ ኢትዮጵያ አገልግሎት ሲጀምር፥ አገልጋዮቹን የወለደው ከሌሎች አካባቢዎች አና ከሌሎች የሚለዮን ድርጅቶችም ጭምር ነበር።

እንደዚህ ካሉት አገልጋዮችም መካከል ከ"ምዕራብ አሮሞ የጋርዮሽ የወንጌል አንቅስቃሴ" የተወሰደው አና በኮንሶው የሚሰዮኑ ጣቢያ ያገለግል የነበረው አቶ ወልዴ ሹና አንዱ ነው። ወልዴ የታላቅ አኅቴ የበካብቷ የመጀመሪያ ባል ሲሆን፥ የተጋቡት በ1948 ዓ.ም. ነው። ወልዴ አና በካብቷ የተገናኙት፥ ቀደም

ሲል እንደ ጠቀስኩት፥ እናታችን ወላጆቿን ስመጠየቅ በካብቷን እና ነጋሽን ይዛ ወደ አደገችበት አገር ሄዳ በነበረበት ጊዜ ነው።

ከእንድ ዓመት ገደማ በኋላ በካብቷ የመጀመሪያ ልጇን ስመውለድ ወደ ወላጆቿ ቤት ስትመጣ፥ ባለቤቷ ወልዴ ደግሞ ስትምህርት ወደ አዲስ አበባ ሄደ። በካብቷ ስትመጣ ትልቅ የመዝሙር መጽሐፍ ይዛ ነበር የመጣችው። እና የፕሮቴስታንቶችን መዝሙር እስተማረችኝ። ሁሉም ትርጉሞች ናቸው። ዜማቸውም አገርኛ አይደለም። ሆኖም ግጥማቸውን በቃሌ ስመያዝም ሆነ ዜማቸውን ስማወቅ አልተቸገርኩም - "የጥንት እምባ"፥ "ወዳንተ ኢየሱስ ሆይ"፥ "ጎዘነተኛን የሚያጽናናው"፥ "ያ ታላቅ ሐኪም"፥ "እንተ የታመንክ"፥ "ንቁ ቁሙ ለኢየሱስ"፥ "ኢየሱስ ክርስቶስ የኔ ወዳጅ"፥ "ሰባኪው እስ ክንቱ ነው"፥ ወዘተርፈ።

የሚሰዮን መዝሙሮችን መውደድ እና መዘመር ቻልንበት እንጂ፥ በካብቷም ሆነች እኔ ግን አርቶዶክሶች ነው የነበርነው። በዚያኔዋ ደቡብ ኢትዮጵያ፥ አረማውያንን በወንጌል ስመድረስ ብዙ ዐይነት የሚሰዮን ድርጅቶች አብረው አገለገሉ። አሁን ደግሞ አርቶዶክሶቹም አብረናቸው ዘመርን። ጎብረት አራሱ መዝሙር አይደል? - የድምፅ ሳይሆን የሕይወት። የመንፈስ እና የነፍስ። ዮሐንስ ሳንድቬድ በዚያን ጊዜ በደቡብ ኢትዮጵያ ወንጌል ስለ ተሠራፍጨበት መንገድ የተረኩበትን መጽሐፍ "ተእምር በደቡብ አገር"[8] ብለው ሰይመው ታል። ትከክለኛ ሰያሜ ነው። አርግጥ በጊዜው የአኔ ጉዳይ ከመዝሙራቸው እንጂ ከመልእክታቸው አልነበረም። በማገለግልባት በአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ቢሆን፥ እንደዚያው ነበርኩ። ጉዳዬ ከያሬዳዊው ዜማ እንጂ፥ ከመልእክቱ አልነበረም ማለቴ ነው። መልእክቱንማ መቼ ሰምቼው?

ገርማሜ ንዋይ፥ የማለስለስ አገልጋይ?

"የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ" እየተባለ የሚጠቀሰው ከሥተት፥ በኢትዮጵያ በዐይነቱ የመጀመሪያው መሆኑን ብዙ የታሪክ ባለ ሞያዎች ይስማሙበታል። የዚያ ሙከራ ጠንሳሽ እንደ ሆነ የሚታመነው አቶ ገርማሜ ንዋይ ነው። ገርማሜ አሜሪካ ከሚገኘው የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ በማስተርስ ዲግሪ የተመረቀ እና በዚያም በነበረ ጊዜ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት የነበረ ሰው ነው። የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበ አዛዥ የነበሩት

ዮብሪጋድዬር ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ ታናሽ ወንድም ስለ ነበረ፥ መፈንቅለ መንግሥቱን ስማካሄድ መሣሪያ ያደረገው በዋናነት እኚህን ሰው ነው።

በትምህርት ክቆየበት ከአሜሪካ ወደ አገር ቤት ክተመለሰ በኋላ፥ ለገርማሜ ከተሰጡት ሥራዎች አንዱ የዎላይታ አውራጃ ገዢነት ነበረ። አንዳንድ ሰዎች የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ገርማሜን ክፍተኛ የመገናኛ ችግር በነበረው እንደ ዎላይታ ባለው የገጠር አውራጃ የመደበው ኮሚዩኒስታዊ ዝንባሌ እንዳለው ያውቅ ስለ ነበረ፥ ሌሎችን እንዳይበክል ምሑራኑ በብዛት ክሚገኙበት አካባቢ ለማራቅ ሲል ነው ይላሉ። ገርማሜ ግን የዎላይታ አውራጃ ገዥ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ብዙም ሳይቆይ፥ ለተጎዳው የጎብረተሰቡ ክፍል የሚጠቅሙ እንዳንድ አርምጃዎችን መውሰድ ጀመረ።

ከወሰዳቸው አርምጃዎች መካከልም ጭሰኞችን ክባለ አርስቶች መሬት ላይ አያነሣ የመንግሥት ይዞታ በሆነ ቦታ ላይ ማስፈሩ እና የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ መጀመሩ ይጠቀሣሉ። ክዳሞታ ተራራ ላይ ውሃ በቦይ ወደ ሶዶ ክተማ አስገብቶ እንደ ነበረም እስታውሳለሁ። የሰፈራው ፕሮግራም ተግባራዊ ሊደረግ እንደ ተጀመረ ወዲያው ነበር ተቃውሞ ያስነሣበት። ትልልቆቹ ባለ አርስቶች ተወካዮቻቸውን መርጠው እና እቤቱታቸውን ተብትበው ጽፈው ወደ ይርጋ ዓሰም እና ወደ አዲስ አበባ ላኩ።

በመሠረተ ትምህርቱ ዘመቻ በ1951 ዓ.ም. ክረምት ላይ የሰባተኛን ክፍል ያጠናቀቁ ተማሪዎች ለሁለት ወራት በአስተማሪነት እየተቀጠሩ በየገጠሩ ተላኩ። ይቹኛውም ዘመቻ ቢሆን በዎላይታ ክዚያ ዓመት በኋላ ስመቀጠሉ አርግጠኛ አይደለሁም። ለነገሩ ገርማሜ አራሱም ቢሆን በዚያ የቆየበት ጊዜ በጣም አጭር ነው የሚመስለኝ።

በወር ሐያ ብር ደመወዝ እየተከፈላቸው ለሁለት ወራት ክተቀጠሩት አስተማሪዎች መካከል አንዱ እኔ ነበርኩ። በዚያን ጊዜ እንደ ዛሬው በየክፍሉ ሰባ እና ስማንያ ተማሪዎች አልነበሩም። ስለዚህም አስተማሪዎቹ ቁጥራችን በጠቅላላው ሐያም የሚሞላ አይመስለኝም። መኖሪያችን እና ቀለባችን ክአንድ የአገር ሽማግሌ ቤት ይሆናል። የመንግሥት ተቀጣሪዎች ብንሆንም፥ የአገር ሽማግሌ ሦቹ ክልጆቻቸው እንደ አንዱ አድርገው በቤታቸው እንዲያኖሩን ተጠይቀው ስምምነታቸውን ሰጥተዋል።

እኔ የተመደብኩበት አካባቢ የኪማ ይባላል። የምኖርበት ቤት ባለቤት በዕድሜ ከእኔ የሚበልጡም የሚያንሡም ብዙ ልጆች ያሏቸው ትልቅ ሰው ሲሆኑ፥ የፐሮቴስታንት እምነት ተከታይ ናቸው። ዕሁድን የኪማ አሳልፌ ሰለማላውቅ፥ በቤተ ክርስቲያናቸው መደበኛ የአምልኮ ፕሮግራም ላይ ተገኝቼ አላውቅም። ከሳምንቱ ቀኖች ውስጥ በአንደኛው ምሽት ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚ ካሄድ ፕሮግራም አላቸው። ቤተ ሰቡ ሁሉ በዚያ ፕሮግራም ላይ ይገኛል። እኔም እንደ ቤተ ሰቡ አባልነቴ አብሬአቸው እሄዳለሁ።

በቤታቸው ውስጥ ደግሞ በየምሽቱ ከአራት በፊት የጸሎት፥ የመዝሙር እና የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ጊዜ አለ። የቤተ ሰቡ አባል ስለ ሆንኩ፥ በእነዚህም አካፈላለሁ። ይዘምሯቸው ከነበሩት መዝሙሮች መካከል በተለይ አንዱ እስከ ዛሬ ድረስ በልቤ እና በአፌ ላይ አለ - ከነቃሉ እና ከነዜማው። ከአራቱ ቁጥሮቹ መካከል የመጀመሪያው እነሆ፦

> የኔ ክህ የሱስ ሆይ አወድሃለሁ፤
> ስላንተ ያለምን ደስታ ትቻለሁ።
> ቅዱስ አምላኬ ሆይ ሁን መድኃኔቴ፥
> እጅግ የምወድህ ቸሩ ወዳጄ።

ቆይቼ ለማወቅ እንደ ቻልኩት፥ ይህ መዝሙር ዊልያም ፌዘርስቶን ገና ለጋ ወጣት (TEENAGER) በነበረ ጊዜ "MY JESUS I LOVE THEE" በሚል ርእስ የጻፈው የኢንግሊዝኛ መዝሙር ትርጉም ነው። ዜማውም ያው ኢንግሊዝኛው የሚዘመርበት ዜማ ነው። መዝሙሩን ወደ አማርኛ ቋንቋ የመለሱት እና ለአገራዎቹም ያስተማሯቸው ሚስዮናውያኑ ናቸው። ሚስዮና ውያኑ በሄዱባቸው አገሮች ቋንቋዎች ሁሉ ተተርጉመው በዓለም ዙሪያ ከሚዘ መሩት ብዙ የኢንግሊዝኛ መዝሙሮች መካከል አንዱ ይኸ መዝሙር ነው። የመዝሙሩን ቅኔ ከጣዕሙ እና ከለዛው ጋር ወደ አማርኛ ቋንቋ ማስተላለፍ ባይሆንላቸውም፥ የተርጓሚዎቹ ጥረት ግን ያስደንቃል፦

> My Jesus I love Thee, I know Thou art mine;
> For Thee all the follies of sin I resign;
> My gracious Redeemer, my Saviour art Thou;
> If ever I loved Thee, my Jesus, 'tis now.

ሆሊይዉድም፥ ከፊልሞቹ ባንዳንዶቹ

እኔ በነበርኩባት ጊዜ፥ የጅማ ከተማ በጣም ጥሩ ከሚባሉት የኢትዮጵያ ከተሞች አንዷ ነበረች። አንዳንዶች እንዲያውም ከአዲስ አበባ እና ከአስመራ ተነሥሎ በሦስተኝነት ደረጃ ያስቀምጡአታል። የቢንቧ ውሃ ነበራት። ዋና ዋና መንገዶቿ ብቻ ሳይሆኑ ብዙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶቿም በአሰፋልት የተሠሩ ነበሩ። ቁጥራቸውን ባላውቀውም፥ የከተማ አቶቡሶችም ነበሯት። በተለይም ደግሞ በእኔ ብጤ ወጣቶች ዘንድ እጅግ ተወዳጅ እና ተፈላጊ የሆኑት ሲኒማ አና ዳንስ ቤትም ነበሯት።

በትምህርት ቤታችን ግቢ ውስጥ ዓርብ ምሽት ላይ አልፎ አልፎ ትምህርታዊ አና ዶኪዩሜንታሪ የሆኑ ፊልሞችን እናያለን። ወይም ደግሞ ተማሪዎቹ በየከፍ ላችን ወይም በየብሔረ ሰባችን ተቧድነን የምናዘጋጃቸውን የድራማ እና የዘፈን ትርኢቶች እንመለከታለን። እነዚህን እና እነዚህን በመሳሰሉ መዝናኛዎች ባልተያዙት ዓርቦቻችንም ወደ ከተማ መሄድ እና ፊልም ቤት መግባት እንችላለን።

በጅማው ሲኒማ ቤት ("ሲኒማ ኢትዮጵያ" ነበር ይባል የነበረው መሰለኝ) ካየኋ ቸው ፊልሞች መካከል፥ አሁን እየጻፍኩበት ካለሁት ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላ ቸው አንዳንድ ፊልሞች ትዝ ይሉኛል። ለምሳሌ "THE TEN COMMAND-MENTS"፥ "THE SILVER CHALICE"፥ "BEN HUR"፥ "THE ROBE"። እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች ላይ የተመሠረቱ ፊልሞች ናቸው። በጣም ታዋቂም ፊልሞች ናቸው። እኔም ተዝናንቼባቸዋለሁ ወይም በጊዜው በነበረው አነጋገር "ENJOY አድርጌአቸዋለሁ።" የኋለኞቹን ሦስቱን፥ መጻሕፍቱንም ላጭምር እንብቤአለሁ።

BEN HURን ያየን ምሽት ከከፍል ጓደኞቼ መካከል መኮንን ጆቴ (በኋላ ዶክተር) አብሮኝ ነበረ። ወደ ዶርም ከተመለስን በኋላ፥ በተደራራቢዎቹ አልጋ ዎቻችን ላይ እርሱ ከላይ፥ እኔ ከታች ሆነን ተኛን። ምክንያቱ አልገባኝም፥ መኮንን ግን አሁንም አሁንም "እ-ህ-ህ" ይላል። ሲበዛብኝ ጊዜ ጠየቅሁት -

"ምን ሆነሃል?"

"አባክህን በጣም አዝኛለሁ!"

"ምነው? ምን ተፈጠረ?"

"አላየኸውም እንዴ ያለቀውን ለው? እንዴት ምን ተፈጠረ ትለኛለህ?"

"እኔ በእውነት አላየሁም፤ የምን ሰው ነው ያለቀው? የት? መቼ?"

"ምን ትቀልዳለህ? ምን ሰው ተርፏል? BEN HURን አብረን አይደለም እንዴ ያየነው?"

አሁን ገባኝ። መኮንን በፊልሙ ውስጥ ያየውን ሁሉ እውነት አድርጎ ወስዶታል ማለት ነው። "SHOW BUSINESS" ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ገና አልገባውም ማለት ነው። ላለረዳው ሞከርኩ። በፍጹም ሊረዳኝ አልቻለም።

"አዚህ አትምህርት ቤታችን ውስጥ እኔና እንተ ሠርተን ለሌሎች አንደምናሳየው ቲያትር ማለት አኮ ነው" አልኩት።

"በባሕሩ ላይ የተነሣው ማዕበል፥ በባሕሩ ውስጥ የሰጠሙት አነዚያ ሁሉ ለዎች፥ ጦርነቱ እና በጦርነቱ የሞቱት ሰዎች፥ በጠቅላላው ያየነው ያ ሁሉ ነገር ቲያትር ነበረ፥ ውሸት ነበረ፥ ነው የምትለኝ?" ሲል እምርሮ ጠየቀኝ።

"እዎ፥ እኔን ካላመንከ ሌሎቹን፥ አነ ... ን ጠይቃቸው" አልኩት - ፊልም ብዙ የሚያዩ እና ስለ ፊልምም ብዙ የሚያውቁ ተደርገው የሚገመቱትን የከፍል ጓደኞቻችንን ስም እየጠራሁለት። የጠየቃቸው ይመስለኛል። "ሁለተኛ ፊልም የሚባል ነገር አላይም፤ ውሸት አላይም" አለኝ በሌላ ቀን።

"አይ፥ ውሸት አኮ አይደለም፤ ከብዙ ዓመታት በፊት በእውነት የሆነ ታሪክ አኮ ነው፤ ያንን ታሪክ ነው በፊልም ሠርተውት አንድናየው ያደረጉት" አልኩት። ውሳኔውን ለመቀየር ብዙ ጊዜ የወሰደበት አልመሰለኝም። ከዚያ በኋላ ከመኮንን ጆቴ ጋር አብረን ሌሎች ፊልሞችን አይተናል። በአገራችን ሕዝባዊው አብዮት በፈነዳባቸው በመጀመሪያዎቹ ዓመታት፥ ዶክተር መኮንን ጆቴ የሸዋ ከፍለ አገር አስተዳዳሪ ተደርጎ ነበር። ሆኖም ብዙም ሳይቆይ በ1970 ዓ.ም. ተገድሏል።

ዘፋኞቹ ዘማሪዎች

በጅማ የእርሻ ቴክኒክ ትምህርት ቤት፥ ተማሪዎች ጠዋት ከእንቅልፋችን የምንቀሰቀሰው በሙዚቃ ነበረ። ከአራት በኋላም ለጥናት ላይብረሪ መግባት እስከሚገባን ጊዜ ድረስ እንደዚያው በሙዚቃ እየተዝናናን እንቆያለን። ከመቶ

ዘጠና ዘጠኝ በላይ፥ ዘፈኖቹ በሸክላ ላይ የተቀረጹ፥ የኢንግሊዝኛ ዘፈኖች ነበሩ። የዘፈኑ ወይም የሙዚቃው ዐይነት የሚወሰነው በዕለቱ "ዲጄ" ነው። ሥራው አንጂ፥ "ዲጄ" (DISC JOCKEY) ምሕጻረ ቃሉ በዚያን ዘመን እዩታወቅም። ዲጄው ከእኛ ከተማሪዎቹ መካከል ለዚያ አገልግሎት በፍላጎታቸው ስማቸውን ካስመዘገቡት፥ ለዚያ ሳምንት ወይም ለዚያ ዕለት የተመደበው ተማሪ ነው። ሙዚቃውን የምንሰማው በየመኝታ ቤታችን፥ ወይም ሃጣብ ቤት፥ ወይም ግቢው ውስጥ ካሉ ከተመረጡ አካባቢዎች አንዱ ጋ ሆነን ነው - ዕድሜ ለቴከኖሎጂይ፥ በቀጭኑ ሽቦ።

በዚያን ጊዜ ስማቸው ከገነነው ዘፋኞች እና ዘፈኖቻቸው መካከል ብዙዎቹን ወውቃቸው ነበር ማለት አችላለሁ - ፍራንክ ሲናትራ፥ ኤልቪስ ፕሪስሊይ፥ ፓት ቡን፥ ጂም ሪቭስ፥ ሃሪይ ቤላፎንቴ፥ ከሊፍ ሪቻርድ፥ ሊትል ሪቻርድ፥ ናት ኪንግ ኮል፥ ቢ. ቢ. ኪንግ፥ ሬይ ቻርለስ፥ ወዘተርፈ። ከሴቶቹም እነ ዶሪስ ዴይ፥ ማሃሊያ ጃክሰን፥ አሬታ ፍራንክሊን፥ ወዘተርፈ። ከምንለማቸው ሙዚቃዎች አንዳንዶቹ "NEGRO SPIRITUALS" የሚባሉት ናቸው። ዘፈን ሳይሆኑ፥ ለካ መንፈሳዊ መዝሙሮች ነበሩ።

ዘማሪዎቹ ዘፋኞች "ኔግሮቹ" ብቻም አልነበሩም። ከነሬጫቹም ነበሩብቸው። ከእነዚህም ነጮች መካከል አንዳንዶቹ መዝሙር የሚባል ነገር አይደለም ዘምረው፥ ሰምተውም እያውቁም፥ የምላቸው ዐይነት ዘፋኞች ነበሩ። "ዘፈን እና መዝሙር ለይቼ አላውቅም ነበር ማለት ነው?" አስከምል ድረስ አራሴን ታዝቤዋለሁ። ለምሳሌ በዚያን ጊዜ ከኤልቪስ ፕሪስሊይ "ዘፈኖች" መካከል እንዱ እና በጣምም የምወደው የነበረው "CRYING IN THE CHAPEL" ነው። የዘፈኑን ግጥሞች በሙሉ በቃሌ ዐውቃቸዋለሁ። ከኤልቪስ ጋር አብሬ እና ብቻዬንም ለግሌ ለረዥም ዘመን ዘፍኜዋለሁ።

"CRYING IN THE CHAPEL" ዘፈን ሳይሆን፥ መዝሙር መሆኑን ያወቅሁት ግን ብዙ ዓመታት ካለፉ እና እኔ እራሴም አማኝ ከሆንኩ በኋላ ነው። ግጥሞቹ ሲበዛ ግልጽ ነበሩ። ጥቂቶቹ ቁጥሮች እነሆ፦

You saw me crying in the chapel;
The tears I shed were tears of joy;
I know the meaning of contentment;
Now I'm happy with the Lord.

Every sinner looks for something;
That will put his heart at ease;
There is only one true answer;
He must get down on his knees.
You'll search and you'll search;
But you'll never find;
A way on earth
To gain peace of mind.
Take your troubles to the chapel;
Get down on your knees and pray;
Your burdens will be lighter;
And you'll surely find the way.

በትምህርት ቤታችን ውስጥ ሀብቴ አውአሎም የሚባል ተማሪ ነበረ። የኢንግሊዝኛ ዘፈኖችን እንደ ጉድ ይዘፍናቸዋል። ከፀጉር አበጣጠሩ ጀምሮ ነገረ ሥራው ሁሉ የኤልቪስን ይመስላል። አንድ ዓመት፥ በልደት በዓል ወቅት፥ ሀብቴ ጥቂት ተማሪዎችን ስበስበን እና "CHRISTMAS CAROLS" (የልደት መዝሙሮች) አስጠናን። በዋዜማው ዕለት ምሽት ላይ በአሜሪካውያኑ መም ሀሮቻችን ቤቶች እየዞርን ዘመርንላቸው - SILENT NIGHT, DECK THE HALL, JINGLE BELLS, JOY TO THE WORLD ወዘተርፈ። የፈረንጅ "ሆያ ሆዬ" መሆኑ ነው። የአበሻው አልቢቃኝ ብሎ!

"እናንተ 'ማታዩኝ፤ እኔም 'ማላያችሁ"

አውንም እዚያው ጅማ ነኝ። በትምህርት ቤታችን ውስጥ በአምነታቸው ፕሮቴስታንቶች የሆኑ ብዙ ተማሪዎች አሉ። ከዶርሜ ልጆች መካከል እንኳን ታደስ ቀነዓ፥ አዲሱ በየነ፥ ዘርዓ ኢዘዝ (በኋላ ዶከተር)፥ ያዕቆብ ፍስሐ (በኋላ ዶከተር)፥ የለየላቸው ፕፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ነበሩ። የእነዚህኞቹን ያህል ያልለየላቸው፥ በተለይም የኤርትራ እና የወለጋ ልጆች የሆኑ፥ ሌሎችም ነበሩ። ያሉን ስምንት ዶርሞች ሲሆኑ፥ በየዶርሙ ያለነው ተማሪዎች ቁጥር ደግሞ ቢበዛ ሐያ አምስት ነው። በዚህች ሰሌት ብቻ እንኳን ብንሄድ፥ ቢበዛ ሁለት መዶ ከምንሆነው ተማሪዎች መካከል ቢያንስ 15% ያህሉ ፕሮቴስታንቶች ነበሩ ማለት ነው።

እነዚህ እምነታቸውን ያለ ጥርጥር ከወላጆቻቸው ነው የወረሱት። ዕሑድ በመጣ ቁጥር አንዳንዶቻቸው መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ይዘው፥ ሌሎቹም ባዶ እጆቻቸውን ሆነው፥ ወደ "ቸርች" ሲሄዱ አያቸዋለሁ። ከዚህ ያለፈ ግን የሚታይ ነገር አልነበራቸውም። ለምሳሌ ሲጸልዩ፥ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ሲያነቡ፥ ወይም ሲዘምሩ፥ ወይም ሲመለከሩ፥ አይቻቸው የማውቅ አይመስለኝም። እና ከርስትናቸው፥ ልክ እንደ እኔው ከርሰትና፥ የዕሑድ ብቻ የነበረ ይመስለኛል። ንባቡም፥ ጸሎቱም፥ አምልኮውም በሳምንት አንድ ቀን - ዕሑድ። ከዕሑድ እስከ ዕሑድ ባሉት ቀናት ግን - ዓለማዊ።

እንዳንዶቹ እዚያው ጅማ ሊያሉ ነው እምነታቸውን የጣሉት - ልክ እኔ የራሴን እንደ ጣልኩት። እንደዚህ ካሉት መካከል አንዱ ታደሰ ቀነዓ ነው። ዕልም ያለ ዓለማዊ ነበር የሆነው። ቆይተው፥ ወደ ዓሰማያ ኮሌጅ ከሄዱ በኋላ፥ ወይም ደግሞ የሥራውን ዓለም ከተቀላቀሉ በኋላ የጣሉም አሉባቸው። እንደነዚህ ካሉት መካከል ደግሞ ታምሬ ሐዋንዶ (በኋላ ዶከተር) አንዱ ነው። እነዚህን ሁለቱን በሰም የምጠቅሥበት ምክንያት እንደኛ የእነርሱ ነገር "እገር ያወቀው፥ ዐሐይ የሞቀው" በመሆኑ ነው። ሁሰቱም የደርግ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች ነበሩ። ሁሰተኛው ምክንያት ግን፥ ሁሰቱም ከመሞታቸው በፊት ጥለውት ወደ ነበረው የልጅነት አምነታቸው ተመልሰው የተገናኘን በመሆናችን ነው።

ከብዙ ዓመታት በኋላ፥ ከሁለቱም ጋር የተገናኘነው በናይሮቢ (ኬንያ) ሲሆን፥ የተገናኘነውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር። እኔ የሄድኩት ለአገልግሎት ስለ ነበረ፥ አገልግሎቱን ጨርሼ ከመድረኩ ላይ እስከምወርድ ድረስ ታማሦ መጠ በቅ ከባድ ሆኖባቸው እንደ ነበረ ነው ሁሰቱም የነገሩኝ። ታደስ ለረዥም ጊዜ የደርግ አሰረኛ ነበር። ከዚያ እስራት በሕይወት ተርፎ፥ ያም ሁሉ የሰቆቃ ዘመን ዐልፎ፥ እንደ ገና ለሙተያየት ሙቢቃት የሚፈጥረው የተሰየ ሰሜት አለ። እሱ ሳያንሰን ደግሞ፥ ከሃዲውን እኔን ችሩ እግዚአብሔር ወደ እራሱ አምጥ ኖኝ፥ የተዉትን እነርሱንም መሐሪው እግዚአብሔር ወደ አራሱ መልሷቸው፥ በቤቱ ውስጥ መገናኘት መቻል የሰውን ነፍስ በቋንቋ ሊገለጽ በማይችል ደስታ ያሰከራታል። እና ተቃቀፍን፤ እየሣቅን አለቀስን፤ እያለቀስንም ሣቅን።

በጅማ ሚያዝያ 27 ትምህርት ቤት ይካሄድ የነበረውን የሃይማኖተ አበው ማኅበር ስብሰባዎች እካፈል እንደ ነበረ ቀደም ሲል ጠቅሻለሁ። በሃምሳዎቹ አጋማሽ ላይ፥ በዚያ ማኅበር ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ከነበሩት ወጣቶች መካከል

አንዳንዶቹ እየጣሉን ወደ ሚሰዮኖቹ ሰፈር ሄደዋል። በስብሰባዎቻችን ላይ ባጣኋቸው ጊዜ፥ "እነ እንትና የት ሄዱ? ምነው እይቻቸው አላውቅ?" ብዬ መጠየቄን አስታውሳለሁ። ያን ጊዜ ነው ወደ ሚሰዮኖቹ ሰፈር እንደ ነጎዱ የተነገረኝ። ሊገባኝ አልቻለም። ምን ማለት ነው? ጥለውን ከሄዱት መካከል እንዴ መሠረት እንደሸው ነበረች። አባቷ መምሬ እንደሻው የፓርላማ ተመራጭም ነበሩ። ይህንን ጉድ እልሰሙም ማለት ነው? ወይስ ሰምተው ዝም አሏት?

በአገራችን ዐይነ ሥውራን (ዛሬ 'ማየት የተሣናቸው' ነው የሚባሉት) ምጽዋት ሲለምኑ፥ ዐይናሞቹ እንዲራሩላቸው ለማድረግ የሚጠቀሙበት የመለመኛ ቋንቋ አለ - "እናንተ የምታዩኝ፤ እኔ የማላያችሁ።" እሱን አባባል ነው ትንሽ እዚዙሬ ለዚህ ክፍል ርእስ አድርጌ የተጠቀምኩበት - "እናንተ 'ማታዩኝ፤ እኔም 'ማላያችሁ።" በዚያን ጊዜ በአንድ ትምህርት ቤት ተማሪነት ወይም ደግሞ በሃይማኖተ አበው ማኅበር አባልነት ካወቅኋቸው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ጋር የነበረን ግንኙነት የሁለት ዐይነ ሥውራንን ግንኙነት ነበር የሚመስለው ማለት እችላለሁ። እኔ በአነርሱ ዘንድ ያለው ብርሃን (ያለ ከሆነ) አይታየኝም፤ ሰለዚህም የሚያዩትን ለማየት ፍላጎት የለኝም። እነርሱም በእኔ ዘንድ ያለው ጨለማ አይታያቸውም። ስለዚህም ያየነውን እናሳይህ አይሉኝም።

በክቡር ሚኒስትር ሳይቀር

በ1957 ዓ.ም. እንድ ዕሑድ ቀን፥ የሆነ ወሬ ሰማሁ። የወሬ አባቴ ያንን ቀን ጠዋት ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የተመለሰ፥ ጓደኛዬ ነው። እሱ ጓደኛዬ እንዲት ቆንጆ ልጅ ወዶ መከነፍ ጀምሯል። መከነፍ ስለ ጀመረም፥ ምንም እንኳን በእምነቱ "ስመ አርቶዶክስ" ክርስቲያን ቢሆንም፥ ልጅቱ ወደምትሄድበት ወደ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ይመላለሳል። በጊዜው እርሱ እና እኔ አብረን እንኖር ነበር - የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ በነበረችው በይርጋ ዓለም። እርሱ የቡና ቦርድ፥ እኔ ደግሞ የአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ባልደረቦች ሆነን።

እና ይህ ጓደኛዬ ያን ዕሑድ ዕለት መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሰማውን እንድ ማስታወቂያ ነገረኝ። ማስታወቂያው "በሚቀጥለው ዕሑድ በዚህ ቦታ ቃለ እግዚአብሔርን የሚያስሙት ከቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም፥ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የፖስታ ቴ.ቴ. ሚኒስትር ናቸው። ስለዚህ ሌሎችንም

ሰዎች እየጋበዛችሁ ይዛችኋቸው እንድትመጡ እና የበረከቱ ተካፋዮች እንድት ሆኑ" የሚል ነው።

ይህንን ወሬ እንደ ሰማሁ፥ ወዲያው ወደ እኤምሮዬ የመጣው እላብ "ምን ዐይነት ጉድ ነው? ሚኒስትር ደግሞ ምን ይስብካል?" የሚል ነው። ይሁን እንጂ፥ ማስታወቂያውን በተመለከተ ውሳኔ ለማድረግ ምንም ጊዜ አልወሰደብኝም። ዕሑድ መጥቶ ወደ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ እና ከቡር አቶ እማኑኤልን ለመስማት ቸኮልኩ። አንዳይደርስ የለም ዕሑድ ደረሰ። ጓደኛ የም ለለማው ማስታወቂያ በመታዘዝ "የጣለውን ግዳይ" አስከትሎኝ በለዓቱ በቦታው ደረስን። ከቡር አቶ እማኑኤልን ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ያየኋቸው ያን ዕለት ነው።

በሺዎች ባይሆን በመቶዎች የሚቆጠሩ ስብከቶችን ከዚያ በኋላ ሰምቻለሁ። ከሰማኋቸውም ስብከቶች ውስጥ የማስታውሳቸው በጣት የሚቆጠሩ አሉ። በጣት ከሚቆጠሩት ከአነዚያ ስብከቶች አንዱ፥ በዚያች ዕሑድ በይርጋ ዓለም መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሰማሁት የከቡር አቶ እማኑኤል አብርሃም ስብክት ነው - የመጀመሪያዬ ስለ ነበረም እንደ ሆነ እንጃ። የስብከቱ ርእስ "አማዚአብሔር የታሪከ ባለቤት ነው" የሚል ነበር። ሰባኪው በዚያ ስብከታቸው በአንድ በኩል እኔ የማውቃቸውን እንዳንድ ታሪካዊ ከስተቶች ይጠቅሳሉ። በሌላ በኩል ግን እኔ በፍጹም የማላውቀውን፥ እግዚአብሔር በአነዚያ ታሪካዊ ከስተቶች ውስጥ ጣልቃ የገባባቸውን እና የዘላለም ዕቅዱን እውን ያደረገባቸውን ሁኔታዎች ያስረዳሉ።

ለምሳሌ ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት አነሡ እና ሂትለር ከስድስት ሚልዮን በላይ አይሁዳውያንን እንዴት አንደ ጨፈጨፈ ተረኩ። የእስራኤል መንግሥት በመካከለኛው ምሥራቅ ከተመሠረተ ገና 16 ዓመቱ እንደ ሆነም ተናገሩ። እነዚህ እኔም የማውቃቸው ታሪኮች ናቸው። ቀጠሉ እና ግን፥ አይሁዳውያን ከ11,900 ዓመታት ረዥም ዘመን በኋላ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እንዲመለሱ፥ ከ16 ዓመት በፊትም መንግሥታቸውን እንደ ገና በስፍራው እንዲያቋቁሙ፥ ግድ ይላቸው ዘንድ አግዚአብሔር የተጠቀመበት መሣሪያ የሂትለር ጭፍጨፋ ነበር አሉ። የታሪኩን ይሽኛውን ጎን እኔ በፍጹም አላውቀውም። ከቡር አቶ እማኑኤል በሰበከታቸው ትኩረቴን ሳቡት። "የሠራ አካላቴ ጆሮ ብቻ" ሆኖ ሰማኋቸው።

ለአኔ እግዚአብሔር "እሩቅ ብእሲ" ነው የነበረው። ስለ አርሱ የሰማኋቸው ነገሮች ሁሉ አንድም ዱሮ ዱሮ ያደረጋቸው፥ አንድም ደግሞ ገና ወደ ፊት፥ በፍርድ ጊዜ፥ የሚያደርጋቸው ናቸው። እግዚአብሔር አምና ወይም ትናንትና፥ ዘንድሮ ወይም ዛሬ፥ እንዲህ እና እንዲህ አደረገ ሲባል ለምቼ እላው ቅም። እግዚአብሔር ዛሬም እንደ ጥንቱ በአንድ ግለሰብ ወይም በአንድ ሕገር ታሪክ ውስጥ ጣልቃ ይገባል የሚለው የከቡር እቶ እማኑኤል ስብከት፥ አግዚ እብሔርን የትናንት ብቻ ላይሆን፥ "የአሁን" ጭምር አደረገብኝ። በማለረጃነት የተጠቀለው ታሪከም በአኔው ዕድሜ የተፈጸመ አውነተኛ ታሪክ መሆኑ ያለ ጥርጥር እስገረመኝ። ሆኖም ነገሩ ሁሉ ከዚያች አፍታ ወይም ከዚያች ቀን አላለፈም። ወዲያው እረሳሁት ማለቴ ነው። ወደ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንም ከዚያች ዕሑድ በኋላ እልተመለስኩም።

አያነብ አንባቢ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለማላየት እንደ ሞከርኩት፥ ሁሉንም ዐይነት ፊልም ነው የማየው፤ ሁሱንም ዐይነት መዝሙር እና ሁሉንም ዐይነት ዘፈን ነው የምለማው። አሁንም በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ለማሳየት እንደ ሞከርኩት፥ ካየኋ ቸው ፊልሞች ውስጥ እይቻቸውም ያላየኋቸው ነበሩ። ከሰማኋቸው መዝሙ ሮች እና ዘፈኖችም ውስጥ ሰምቻቸውም ያልለማኋቸው ነበሩ። ያነበብኳቸውን መጻሕፍት በተመለከተ ያለው ሁኔታ ግን - ከቁጥራቸው መብዛት የተነሣ - ያየኋቸውን ፊልሞች እና የሰማኋቸውን ዘፈኖች በተመለከተ ካለው ሁኔታ ሁሉ የባለ ነው።

በዚሁ ምዕራፍ፥ "የልጅነት ወራት" በሚለው ርእስ ሥር "በቤታችን መጽሐፍ እንደ ጉድ ይነበባል" ማለቴን አለታውሳለሁ። በልጅነቴ ካነበብኳቸው መጻሕፍ ትም ውስጥ፥ "የሰው ልብ" እና "ወዳጄ ልቤ" የተባሉትን መጻሕፍት በመንፈ ሳዊ ይዘታቸው ተደንቄባቸው አንደ ነበረ አለታውሳለሁ። እግረ መንገዴን፥ "የሰው ልብ" የተባለው መጽሐፍ በመጀመሪያ የተጻፈው በጎርጎሳውያኑ እቆጣ ጠር በ1732 በፈረንሳይኛ ቋንቋ ሲሆን፥ ከዚያ በኋላ ወደ ብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ሦስት የሰው ልብ ሥዕሎች እሉት። የመጀመሪያው የኃጢአተ ኛውን ሰው ልብ የሚያሳይ ነው። በተለያዩ እራዊት እና እንስሳት ተሞልቷል። ሁለተኛው በኃጢአቱ የተጸጸተውን ሰው ልብ ነው የሚያሳየው። እራዊቱ እና

እንስሳቱ ከለውዬው ልብ ውስጥ ሲወጡ ያሳያል። ሶስተኛው ያመነን ሰው ልብ የሚያሳይ ሲሆን፥ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ውሏል።

መጽሐፉን ወደ እማርኛ ቋንቋ የተረጎመው ማርቲን ፍላድ ነው።[9] ጆናታን ማርቲን ፍላድ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት በጎንደር አካባቢ የነበረ፥ የእማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እና ሲሎች መንፈሳዊ ጽሑፎችን በማሠራጨት፥ እንዲሁም ፈላሾችን በወንጌል በመድረስ ረገድ እግዚአብሔር በድንቅ የተጠ ቀመበት የ"ፒልግሪም ሚስዮናውያን" መልእክተኛ ነበረ። በኢትዮጵያ እና በእንግሊዝ መንግሥታት መካከል በተፈጠረው አለመግባባት፥ አፄ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉትን ደብዳቤ ወደ ሎንዶን የላኩት በማርቲን ፍላድ እጅ ነበር። ማርቲን ፍላድም ለደብዳቤአቸው ምላሽ ይዞ መመለሱን ለማረጋ ገጥ ሲሉ፥ ባለቤቱን ፓዎላይንን እና ልጆቿን በመያዣነት አጠገባቸው እስቀር ተዋቸው ነበር።[10]

በዚያ የልጅነት ወራት ያነበብኳቸው መንፈሳዊ መጻሕፍት ግን "የሰው ልብ" እና "ወዳጄ ልቤ" ብቻ አልነበሩም። ለምሳሌ በ1892 ዓ.ም. በጎበረ ጊዮርጊስ ትርፌ "የክርስቲያን መንገድ" በሚል ስያሜ ወደ አማርኛ የተተረጎመውን የዮሐንስ ቡንያንን "PILGRIM'S PROGRESS" አንብቤአለሁ። ሰድስተኛን ይሆን ለባተኛን ክፍል ስጨርስ ከአንድ እስተማሪአችን በሽልማትነት ነበር ዮተሰጠኝ። የተሸለምኩበትን ምክንያት እና የሸለመኝን አለተማሪአችንን አሁን አረስቼዋለሁ። በዚያው ጊዜ እካባቢ "ተግሣጽ እና ምክር" የተባለውን የዘመ ንፈስ ቅዱስ አብርሃን መጽሐፍም አንብቤአለሁ።

ይሁን እንጂ፥ የእነዚህ መጻሕፍት መልእክታቸው በፍጹም አልገባኝም ነበር ማለት አችላለሁ። የዚህን አባባሌን ትክክለኛነት የሚያሰረዳልኝ ጥሩ ምሳሌ "ሐተታ መናፍስት ወሳውደ ነገሥት" በተባለው፥ በሌላኛው የዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ መጽሐፍ ያደረግሁበት ነገር ነው። መጽሐፉን ያኔ በልጅነቴ ወራት ካነበብኩት በኋላ ተመልሼ አላየሁትም። ሆኖም ጸሐፊው መጽሐፉን የጻፉበት ምክንያት፥ እንባቢዎች "ዓዋቂ ነን"፥ "መጽሐፍ አንገልጣለን"፥ "ኮክብ እንቆጥራለን" በሚሉ ሰዎች አንዳይታለሉ ለማስጠንቀቅ አንደ ሆነ በመጽሐፉ ቸው መግቢያ ላይ የተናገሩ ይመለለኛል። አኔ ግን መጽሐፉን የተጠቀምኩበት ለዚያ፥ ጸሐፊው "እንባቢዎች እንዳይታለሉ" ላሉት ጉዳይ ነው። የራሴንም ሆነ የባልንጀሮቼን ኮኮብ ለመቁጠሪያ ተገለገልኩበት።

የኢንግሊዝኛ መጻሕፍት ማንበብ የጀመርኩት ጅማ ከሄድኩ በኋላ ነው። የንባቡን መንገድ የመራኝ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የጠቀስኩት የኢንግሊዝኛ መምህራችን ሚስተር ኢልየት ነው - የ10ኛ ክፍል ተማሪ በነበርኩ ጊዜ። መጻሕፍት እንድናነብና ስለነበብነውም ሰለ አያንዳንዱ መጽሐፍ ሪፖርት እንድንጽፍ አዘዘን። ለአንድ መጽሐፍ የተያዘው ከፍተኛ ነጥብ 8 ነበር። ከፍተኛውን ነጥብ ሊያስጡ የሚችሉ መጻሕፍት በስም ተለይተው ተሰጥተውናል። ነጥባቸው ከዚያ በታች የሆነውንም መጻሕፍት እንድናውቃቸው አድርጓል። አንድ ተማሪ በዚህኛው ትምህርት ላለመውደቅ በድምሩ ስንት ነጥብ ማምጣት አንደ ነበረበት አሁን ትዝ አይለኝም፤ ሆኖም ከ50 በታች ይመለስኛል።

ስለዚህ አንድ ተማሪ 8 ነጥብ ያላቸው 7 መጻሕፍት ማንበብ አለበት ማለት ነው። ነጥባቸው ቀለል ቀለል ያለ መጻሕፍት ለማንበብ ከመረጠ ደግሞ ወደ 10 መጻሕፍት ማንበብ ይኖርበታል። ለማንበብ የተሰጠው ጊዜም አንድ ሴሜስተር፥ ማለትም 18 ሳምንት፥ ብቻ ነው። እኔ ነጥቡ ከፍ፥ ጥራዙ ግን አነስ ያለ መጽሐፍ ለማንበብ ነው የፈለግሁት። ይህንን መስፈርቴን የሚያሟላልኝ መጽሐፍ ስፈልግ፥ የአላን ፔተንን "CRY THE BELOVED COUNTRY" አገኘሁ። አነበብኩት እና ሪፖርቴን ጽፌ አስገባሁ። ከአንድ ሁለት ቀናት በኋላ ሚስተር ኢልየት ወደ ቢሮው ጠራኝ። 45 ደቂቃ ያህል አሰቀምጦኝ፥ የመጽሐፉን አሳብ ፈጽሞ አንደ ሳትኩት፥ የአንድን መጽሐፍ አሳብ ላለመሳት ወደ ፊት መጽሐፍ ሳነብ እንዴት ማንበብ አንደ አለብኝ፥ ረጋ ብሎ አስረዳኝ።

በመጨረሻም "CRY THE BELOVED COUNTRY"ን አንደ ገና እንዳነበበው እና ሌላ ሪፖርት አንድጽፍ አዞኝ ከቢሮው ወጣሁ። መጽሐፉን አርሱ ባስረዳኝ መንገድ አነበብኩት እና ከቀድሞው ሪፖርቴ ፈጽሞ የተለየ ሌላ ሪፖርት ጻፍኩ። ሚስተር ኢልየት ሙሉ ነጥብ ሰጠኝ። "EXCELLENT!" የሚል አስተያየትም ወረቀቴ ላይ ጻፈበት መስለኝ። በጣም ተበረታታሁ፤ ተደፋፈርኩም። ቀጥዬ ያነበብኩት የቪክቶር ሁጎን "LES MISERABLES" ነበር ይመስለኛል። ትልቅ መጽሐፍ ነው። ግን ደፈርኩት። ስንት ነጥብ አንዳገኘሁበት አሁን ትዝ አይለኝም፤ ሙሉ ነጥብ አግኝቼበት ሊሆንም ይችላል።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የኢንግሊዝኛ መጽሐፍ ማንበብ "HOBBY" (ጊዜ ማሳለፊያ) ሳይሆን "DUTY" (ሥራ) ሆነኝ እና ቀረ። ማንበቤን በቀጠልኩ መጠንም፥ ቋንቋውን ብቻ ሳይሆን፥ አሳቦችንም የመረዳት ዐቅሜ አየጨመረ መጣ። ወደ

ኋላ ላይ፥ ዕድሜ ለመዝገበ ቃላት፥ አሳቡ ጠጥሮብኝ ካልሆነ በስተቀር፥ ሦንቋው ጠጥሮብኝ ሳልረዳው የቀረ መጽሐፍ አላጋጠመኝም ማለት እችላለሁ። አሳብ ደግሞ - ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው - ዛሬም ቢሆን ብዙ ጊዜ ነው የሚጠጥርብኝ።

የሚገርመው ግን፥ አሳባቸውም ሆነ ቋንቋቸው ሳይጠጥርብኝ፥ እንዲሁ ያልተረዳኋቸው መጻሕፍት አሉ። እንብቤአቸውም ያላነበብኳቸው መጻሕፍት አሉ። በሚስተር ኢልየት ቋንቋ "አሳባቸውን ፈጽሞ የሳትኩት" መጻሕፍት አሉ ማለቴ ነው። አንደዚህ ካሉት መጻሕፍት መካከል የሚከተሉትን ልጠቅሳቸው እችላለሁ: የቅዱስ አውገስጢኖስ "CONFESSIONS"፥ የቶማስ ኤ ከምፒስ "OF THE IMITATION OF CHRIST"፥ የሮላንድ ኤች. ቤይንቶን "HERE I STAND: A LIFE OF MARTIN LUTHER"፥ ወዘተርፈ። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ "ከላሲካል" ከሚባሉት መካከል ናቸው። የገዛኋቸው በአንዳንድ መጻሕፍት ላይ ሲደነቁ ስለ አየሁ ነው።

ከታዋቂ የልብ ወለድ መጻሕፍት ጋር ሁነኛ ትውውቅ ያለው አንባቢ ሁሉ፥ ያለ ጥርጥር ስመ ጥሩዎቹን የሩለያ ጸሐፍት ሌዎ ቶልስቶይን፥ ፊኦዶር ዶስቶየፍስኪን እና አሌክሳንደር ሶልዘኒትሲንን ያውቃቸዋል። የእነዚህን ታዋቂ ደራሲያን ጽሑፎች በሙሉ አንብቤአቸዋለሁ ብዬ ለመናገር አልደፍርም። ሆኖም አብዛኞቹን ሳላነብባቸው አልቀረሁም ለማለት እችላለሁ። መጽሐፎቻቸውን በእጅጉ አወድዳቸዋለሁ። የጽሑፋቸው አወቃቀር፥ የአሳባቸው ጥልቀት፥ የታሪካቸው አሳካከ፥ የገጸ ባሕርያቱ አቀራረጽ፥ የቋንቋቸው ውበት፥ ሲበዛ ይመስጠኛል - ባሬም።

አንዳንዶቹን ከአንድ እና ከሁለት ጊዜ በላይ አንብቤአቸዋለሁ። አንደ ሀዲስ ዓለማየሁ "ፍቅር እለከ መቃብር" ማለት ነው። ሆኖም፥ ጸሐፊዎቹ ወይ አውነትን በመፈለግ ላይ የነበሩ፥ ወይም ደግሞ የሚፈልጉትን አውነት ያገኙ፥ በከር ስትና እምነታቸውም ሁሉም ሥር የሰደዱ መሆናቸውን በጽሑፎቻቸው ውስጥ ለማስተዋል አልቻልኩም። ለምን? ለምሳሌ ሀዲስ ዓለማየሁን "ፍቅር እለከ መቃብር" ውስጥ አግኝቻቸዋለሁ። ሩስያውያኑንም ደራሲያን መጻሕፍቶቻቸው ውስጥ ማግኘት እንደሚቻል በኋላ ላይ ተገንዝቤአለሁ። ሆኖም እኔ አላገኘኋቸውም።

ባሌ ጎባ በነበርኩ ጊዜ፥ ከኤስ. አይ. ኤም. ሚስዮናውያን ጋር የሥራ ግንኙነት ነበረኝ። የልደት ወይም የትንሣኤ በዓል በሚሆን ጊዜ በጣቢያቸው መንፈላዊ ፊልሞች ያሳያሉ። እኔንም ይጋብዙኛል፤ እኔም እሄዳለሁ። ለእንድ ሁለት ዓመት ያህል እንደዚህ ያደረግን ይመስለኛል። ነገር ግን ያየኋቸው ፊልሞች ሁሉ፥ ከታዩበት አዳራሽ እኔ ስወጣ፥ እነርሱም ከውስጤ ይወጣሉ።

በአንድ ወቅት "FIRE ON THE MOUNTAIN" የተባለ መጽሐፍ አውሰውኝ እንብቤአለሁ። መጽሐፉ የመጀመሪያዎቹ የኤስ. አይ. ኤም. ሚስዮናውያን በዎላይታ ወንጌልን በሰበኩ ጊዜ የሆነውን ሁኔታ ነው የሚተርከው። በመጽሐፉ ውስጥ በስም ከተጠቀሱት ቦታዎች እና ሰዎች መካከል አንዳንዶቹን ዐውቃቸዋለሁ። መጽሐፉ እሰደናቂ ከሚባሉት ከአንዳንድ ያነበብኳቸው ልብ ወለድ መጻሕፍት ይልቅ የበለጠ አስደናቂ ነው። መጽሐፉን ካነበብኩት በኋላ ግን፥ ላዋለኝ ሚስዮናዊ በምመልስለት በዚያው ጊዜ፥ ያነበብኳቸው አስደናቂ ታሪኮች ከውስጤ ጠፍተዋል።

አዚያው ባሌ ጎባ በነበርኩ ጊዜ፥ ሚስተር ሜኖን የሚባል ሕንዳዊ ጓደኛ ነበ ረኝ። በአዝማች ደግለሃን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቋንቋ መምህር ነው። ዘንግቼ ካልሆነ በስተቀር፥ ከእኔ ጋር በተዋወቅንበት ጊዜ በኢትዮጵያ ከአምስት ዓመታት ላላነሰ ጊዜ ቆይቷል። ሆኖም አንድ ጊዜም ለዕረፍት ወደ አገሩ የተመለሰ አልመሰለኝም። መቼም በአገሩ ሚስት እና ልጆች ባይኖሩት አንኳን፥ ወላጆች እና ሌሎች ቤተሰቦች ላይኖሩት አይቀርም። እንደ ነገረኝ እና እኔም እንደማየው (የባንክ ሠራተኛ ስለ ሆንኩ ማለት ነው)፥ ገንዘብ ልኮላቸው አያውቅም። ከኢትዮጵያዊቱ የቤት ሠራተኛው ደጋግሞ ወልዷል። የወር ገቢው አነርሱን ለማስተዳደር እና እርሱንም ለማዝናናት አትበቃውም - በዚያን ዘመኑ እጅግ ርካሽ የጎባ ኑሮም!

አልፎ አልፎ፥ በልደታ እና በጊዮርጊስ ስሞን፥ የጎባን መጠጥ ቤቶች ከሚስተር ሜኖን ጋር አብረን እንጎበኛቸዋለን። አንድ ቀን ለብታ ይሆናል። በሌላ ቀን ይሰከራል። አሁንም በሌላ ቀን ይወደቃል። ሚስተር ሜኖን "Bekele, hell has no bottom" ይለኛል። "ገሃነም ወለል የለውም" እንደ ማለት ነው። ዝም ብሎ ወደ አዘቅት መውረድ ብቻ ነው ማለቱ ነው። ሚስተር ሜኖን ሃይማኖ ተኛ አይደለም። እኔ እስክማውቀው ድረስ፥ ምንም ዐይነት ሃይማኖት የለ ውም። እንድ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ሲመለስ ግን አንድ መጽሐፍ በሥጦታ

አመጣልኝ። የኒኪይ ክሩዝ "RUN BABY RUN" ነበረ። እውነተኛ ታሪክ ነው።

ዴቪድ ዊልከርሰን በተባለ የወንጌል ሰባኪ እማካይነት፥ እግዚአብሔር በኒው የርክ ከተማ ጋንግስተሮች መካከል የሠራውን አስደናቂ ሥራ የሚተርክ መጽ ሐፍ ነው። መጽሐፉ፥ ዘፋኝ የነበረው ፓት ቡን በዋና ተዋናይነት የሚጫወ ትበት፥ "THE CROSS AND THE SWITCH BLADE" የተባለ ተወዳጅ ፊልም ተሠርቶበታል። እነበብኩት። ሆኖም "ለሰሚው ግራ" የሆነ ነገር ነው ያጋጠመኝ - መጽሐፉ ስለ ምን እንደሚያወራ እንኳን አልገባኝም። የላይንስ ወይም የፍልስፍና መጽሐፍ አይደለም። ታሪኩ የእውነት ከመሆኑ በስተቀር፥ እንደ ሌሎቹ ልብ ሰቃይ (SUSPENSE) መጻሕፍት - መጠጥ እና ወሲብ፥ ድብድብ እና ድራግ፥ ፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ - የሞሉበት መጽሐፍ ነው። ግን አልገባኝም።

"ያባራሪው ያለህ! ..."

ሁለት ሂደቶች ናቸው በሕይወቴ እየተካሄዱ ያሉት። እየተካሄዱም ያሉት ጎን ለጎን ሳይሆን፥ ላይ እና ታች ፥ ወይም ፊት እና ኋላ ሆነው ነው። እነዚህን ሁለት ሂደቶች "ከእግዚአብሔር የሚያርቁ" እና "ወደ እግዚአብሔር የሚያ ቀርቡ" ልላቸው እችላለሁ። ከላይ ወይም ከፊት ያለው ከእግዚአብሔር የሚያ ርቀው ሲሆን፥ ከታች ወይም ከኋላ ያለው ግን የሚያቀርበው ነው። የላይኛው ወይም የፊተኛው ጉልህ ነው - ይታያል። ጩዋኺ (VOCAL) ነው - ይሰማል፤ ከእኔ አልፎ ለሌሎችም። ያኛው ግን እንኳን ለሌላ፥ ለእኔው ለራሴም እይታይ፤ ድምፁም አይሰማ። መካሄዱ ቀርቶ እስከ መኖሩም አይታወቅ።

እነዚህ ሁለት ሂደቶች ይከተሉኛል ወይስ እከተላቸዋለሁ? እያባረሩኝ ናቸው ወይስ እያባረርኳቸው? እየተሰደድኩ ነኝ? ወይስ እየተሳደድኩ? በዚህ ወቅት ከጻፍኳቸው ግጥሞች ውስጥ የምትከተለዋ ለዚህ ጥያቄዬ መልስ የምትሰጥ ይመስለኛል። ስሚን እረስቼዋለሁ። ከሚከተሉትም ሰንኞች በስተቀር ሌላውን እረስቼዋለሁ -

ቁራ "ቋ!"፥ "ቋ!" አለ፤
ሰማይ ደም መሰለ፤
ወፎቹ ተንጫጩ፤
ብርሃን መጣ - ነጩ!

ሊሮጥ፥
ሊሸመጥጥ፥
ሰው ከሰውነቱ -
ነጋለት ሌሊቱ::
ባልጋው ላይ ተንጋሎ፥
በጨርቅ ተጠቅሎ፥
ሳይነግሩት ሲሰማ፥
ሲአስተውል በጨለማ፥
ድንገት ያየውና፥ ሰው ኢምንትነቱን -
ይጠላል እራሱን::

ሰው እንደዚህ ሊለማው ሲጀምር ጥሩ አይደለም:: አደገኛ ሁኔታ ላይ ነው ያለው ማለት ነው:: ቀደም ሲል ያነሣኋቸው እቶ መንግሥቱ ለማም፥ በዚህ "ዝቅታ ነጥብ" በኩል አልፈዋል ይመስለኛል:: "ሕይወት" ብለው በሰየሙት ግጥማቸው:-

ራሴም፥ ጥያቄዬም፥ የሕይወት ደቂቃ
የሕይወት ኬክሮስ፥ ነን፥ አለቀ፥ በቃ!

ብለው ነበር:: ያሉት እውነት ነው:: ሆኖም ይህ እውነት በሚዛናዊ ልቦና እና እንዲሁም በትሕትና - አ! በእግዚአብሔርም ረድኤት - ካልተያዘ በሰተቀር፥ እንዴ እንደዚህ ሊሰማው የጀመረ ሰው፥ ቀጥሎ ምን ሊያደርግ እንደሚችል መገመት ያለቸግራል::

ለምንድነው ከእግዚአብሔር የሚያርቀው ነገር ሁሉ በቀላሉ የሚገባኝ? ለምን ድን ነው ከባዱን ፍልሰፍና ሁሉ ሳይቀር በቀላሉ የምረዳው? በአንጻሩ ግን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበው ቀላሉ ነገር ሁሉ - ፊልም፥ መዝሙር፥ ዘፈን፥ መጽሐፍ፥ ወዘተርፈ - ፈጽሞ የማይገባኝ? ትውስ እለክማይለኝ ድረለ ፈጽሞ የሚ ረሳኝ? በኋላ ላይ፥ ለእነዚህ ጥያቄዎቼ ያገኘሁላቸው መልሶች ሁለት ናቸው:-

የመጀመሪያውን መልስ በ2ኛ ቆሮንቶለ 4፥3-4 ላይ ነው ያገኘሁት - "ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ፥ የተከደነው ለሚጠፉት ነው:: የእግዚአብሔር እምሳል የሆነውን፥ የክርስቶስ የክብሩን ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳውሮአል::" "የዚህ ዓለም እምላክ" የተባለው ሰይ

ጣን ነው:: እና ሰይጣን በልቦናዬ ላይ ግርዶሹን ጋርዶብኝ ነበረ ማለት ነው:: በሥጋዊውም ባይሆን፥ በመንፈላዊው ግን በእርግጥ "ማየት የተሳነው" ሰው ነበርኩ ማለት ነው::

ሁለተኛውን መልስ በማቴዎስ 13፥18-19 ላይ ነው ያገኘሁት - "እንግዲህ የዘሪውን ምሳሌ ለሙ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት ቃል ሰምቶ ከማያሰተውል ከማንኛውም ለው ልብ ውለጥ ከፋው መጥቶ የተዘራውን ዘር ይነጥቃል:: ይህ እንግዲህ በመንገድ ዳር የተዘራው ዘር ነው::" በዚህ ጥቅስ መሠረት፥ የእኔ ልብ ያለ ጥርጥር "መንገድ ዳርማ" ነበር ማለት ነው:: በልቤ ማሣ ላይ የሚዘራውን ዘር ወዲያው የሚለቅመው "ክፋው" (THE EVIL ONE) ነበረ::

በዚያ ሁሉ ረዥም ጊዜ፥ በልቤ ላይ ክነበረው "ግርዶሽ" የተነሣ የማላይ፥ ክልቤ "መንገድ ዳርማ"ነት የተነሣም የማላስተውል ብሆንም፥ ከታች ወይም ከኋላ እየ ተካሄደ የነበረው፥ "ማለለለለ እና ማንኳኳት" ያልኩት ሂደት ግን ባለማቋረጥ እንደ ቀጠለ ነበር - ድምፁን እጥፍቶ:: እንደዚህ እንድል የሚያስደፍረኝ፥ በእንድ በኩል ቃሉ ነው፡-

ሐሳቤ እንደ ሐሳባችሁ፤
መንገዴ እንደ መንገዳችሁ አይደለምና ይላል እግዚአብሔር::
ሰማያት ከምድር ከፍ እንደሚሉ፥
መንገዴ ከመንገዳችሁ፥
ሐሳቤም ከሐሳባችሁ እንዲሁ ከፍ ያለ ነው::
ዝናምና በረዶ
ከሰማይ ወርዶ፥
ምድርን በማራስ፥ እንድታበቅልና እንድታፈራ
ለዘሪው ዘር፥ ለበላተኛም እንጀራ እንድትሰጥ ሳያደርግ፥
ወደ ላይ እንደማይመለስ ሁሉ፥
ከአፌ የሚወጣውም ቃሌ፥
በከንቱ ወደ እኔ አይመለስም፤
ነገር ግን የምሻውን ያከናውናል፤
የተላከበትንም ዐላማ ይፈጽማል:: (ኢሳ. 55፥8-11)

በሌላም በኩል፥ እንደዚህ እንድል የሚያለደፍረኝ፥ መጨረሻ ላይ ሆኖ የታየው ነገር ነው:: ክሕንዳዊው ወዳጄ ከሚስተር ሜነን ጋር፥ በታሕሣሥ ወር 1965

ዓ.ም. እኔ ከባሌ ጎባ በተቀየርኩ ጊዜ ተለያየን። ከሰድሰት ዓመታት በኋላ አዲስ አበባ ላይ ለንገናኝ፥ ሁለታችንም ጴንጤዎች ሆነን ነበር - እርሱ ባሌ ጎባ፥ እኔ ደግሞ አለታ ወንዶ/ይርጋ ዓለም ሳለን። ታሪኩ እጅግ አስደናቂ ነው። የእርሱን እንዲነግረን፥ ለእርሱው አተውለታለሁ። የእኔውን ግን ከጥቂት ገጾች በኋላ እንደርሰበታለን። እስክዚያው፥ እንደ ቋጠርኳት እና ከላይ እንደ ጠቀስኳት ስንኝ፦

ልፍጥ፤
ልሸምጥጥ፤
ሳሳድድ፤
ልሳደድ፤
"ያባራሪው ያለህ!
የት ታደርሰኛለህ?"

ትእምርተ ጥቅሱ ውስጥ ያለውን የሰማሁት ከእናቴ ነበር - ዱሮ፤ በልጅነቴ። እሁን ግን ውሰጡ ነኝ። መጀመሪያ ላይ እንዲህ የተባለበትን ምክንያት ባላው ቀውም እንኳን።

ማስታወሻ

1. ቤተ ክርስቲያኗ የተመሠረተችበት አድርጌ የቆጠርኩት በዎላይታ የመጀመሪያዎቹ ዐሥር ሰዎች የተጠመቁበትን 1926 ዓ.ም. ነው። ወንድዬ ዓሊ፥ "የእኩለ ሌሊት ወጣታ"፥ ሚያዝያ 1992 ዓ.ም.፥ ገጽ 17።
2. ዳና መጃ አማኝ የሆኑት በ1929 ዓ.ም. ነው። በቀለ ገሙ (ተርጓሚ)፥ "ጠረጋ"፥ 1986 ዓ.ም.፥ ገጽ 14።
3. ከኢትዮጵያ ውጭ "BIBLE CHURCH MEN'S MISSIONARY SOCIETY (BCMS)" በመባል ይታወቃል።
4. "የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ"፥ ገጽ 302 (የግርጌ ማስታወሻ)።
5. ወንድዬ ዓሊ፤ "የእኩለ ሌሊት ወጣታ"፤ ሚያዝያ 1992 ዓ.ም. ገጽ 79-94።
6. "የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ"፥ ገጽ 391።
7. የሐንስ ሳንድቬድን በመጥቀስ ፈቃዱ ጉርሜሣ ኩሣ እንደ ጻፈው፤ "የወንጌል እምነት እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ"፤ መካነ ኢየሱስ የምሥራች ድምፅ ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ አዲስ አበባ ጃንዋሪ 1999 ዓ.ም. ገጽ 318-324።
8. ዮሐንስ ሳንድቬድ፤ "ተአምር በደቡብ አገር፤ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የደቡብ ኢትዮጵያ ሲኖዶስ የአርባ ዓመት ታሪክ"፥1988?
9. ዶሪስ ቤንሰን፥ "The Most Valuable Thing": አሳታሚ እና ቀን አልተ ጠቀሰም፡ ገጽ 65።
10. ጉስታቭ አረን፥ "Evangelical Pioneers in Ethiopia"፥ ገጽ 95-96።

ምዕራፍ አምስት

ገነት ገባች

"Enter Genet" እንዲሉ። ወደ ባሌ ጎባ የሄድኩት በ1961 ዓ.ም. በመጋቢት ወር የመጀመሪያ ሳምንት ውስጥ ይመስለኛል - ከሁለት ሳምንታት ገደማ በኋላ ለሚከፈተው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ "የገንዘብ እና የሂሳብ መዝገብ ያዥ" ሆኜ። በቅርቡ የጎባ ከተማ በጋ ከከረምት በሚያስኬድ የጠጠር መንገድ ከአዲስ አበባ ጋር የተገናኘ ቢሆንም፥ እኔ የሄድኩት ግን በአውሮፕላን ነበረ። ከአውሮፕላኑ ወርጄ፥ ሻንጣዬን በአንድ የኑልበት ሠራተኛ አሸከሜ፥ ከአውሮፕላን ማረፊያው የከተማው ዋና መንገድ ብቻ ከሚሰየው ከአቶ ይልማ እሞሣ ሆቴል መኝታ ያዝኩ። ከሶዶው፥ ከጅማው እና ከአዲስ አበባው አውሮፕላን ማረፊያዎች ሌላ ገና ያላየሁ ቢሆንም፥ የዚያን ጊዜዋን ጎባ ያህል የአውሮፕላን ማረፊያው እንብርቱ ላይ የሆነ ሌላ ከተማ ያስ አይመስለኝም።

የባንኩን ቅርንጫፍ ለመክፈት በምናደርገው ቅድመ ዝግጅት የሚረዱን ሻለቃ (በኋላ ጄኔራል) በቀስ ጉደታ የሚባሉ የጠቅላይ ግዛቱ የፖሊስ አዛዥ ስለ ሆኑ፥ እርሳቸውን እንዳገኛቸው አዲስ አበባ ባሉት እስቆቹ ተነግሮኛል። ስለዚህ ምሣ ከበላሁ እና የሥራ ሰዓት አስኪደርስ ድረስ ከጠበቅሁ በኋላ ወደ ሻለቃ ቢሮ ለመሄድ ተነሣሁ። አቶ ይልማ መንገድ ከሚያሳየኝ አንድ ልጅ ጋር አገናኘኝ። ለመንግሥት ባለ ሥልጣኖች፥ ስታዋቂ ነጋዴዎች እና ለእንዳንድ የከተማው ነዋሪዎች የተዘጋጁ የጥሪ ካርዶች በካርቶን ሳጥን ውስጥ ይዣለሁ። የጥሪውን ካርዶች የማሠራጨቱን ሥራ የሚያሰፈጽሙልን ሻለቃ በቀስ ናቸው።

ከሆቴሉ ስንወጣ፥ አቶ ይልማ ያገናኘኝ ልጅ ካርቶኑን እንዲይዝልኝ ሆነ። ሆኖም እንድ ሃምሳ ሜትር ያህል እንደ ሄድን በግድ ተቀበልኩት። ምክንያቱም መንገዱ በጣም ጭቃ ነው። እግር ማሳረፊያ የሚሆን ቦታም የለው። ይኸ ልጅ ካርቶኔን እንደ ያዘ ከወደቀ፥ የጥሪ ካርዶቻችን አለቀላቸው ማለት ነው። የድጡም ሆነ የመንደባለሉ እደጋ ያሰው ከአርሱ ይልቅ በእኔ ላይ እንደ ሆነ አላ ጣሁትም። መንገዱንም ሆነ ጭቃውን ከእኔ ይልቅ አርሱ አሳምሮ ያውቀ

ዋልና። ቢሆንም፥ እነዚህን ካርዶች ተሸከሞ፥ በዚያ መንገድ ላይ ተጉዞ፥ በሰላም ከሻለቃ ቢሮ ለማድረስ ከራሴ የበለጠ የማምነው ማንም ሊኖር እይች ልም። መውደቅም ካለ እራሴው ብወድቅ ነው የጎሊናው ወቀሳ የሚቀልልኝ። መንገዱ ረዥም የነበረ ቢሆንም፥ ሳልወድቅ ነበር የደረስነው። ተመስገን ነው።

ሻለቃ በቀስ ቢሮ ሰገባ በድንጋጤ ከው ነበር ያልኩት። የሻለቃው መቀመጫ ያለው በበሩ ትይዩ፥ ከጓላቸው ወዳለው ግድግዳ በጣም ቀርቦ ነው። በበሩ እና በእርሳቸው መካከል ሰፊ ከፍት ቦታ አለ። ወንበራቸው ምን ዐይነት እንደ ነበረ ትዝ አይለኝም። ጠረጴዛቸው ግን ትልቅ ነው። ከፍሉ በሙሉ ሳጋቱራ ተጎዝጉዘቦታል። "ሳጋቱራ ተጎዝጉዘቦታል" ከማለት ይልቅ "ሳጋቱራ ተከምሮበ ታል" ማለት ይቀልላል። እንደዚህ ያለ ነገር አይቼ አላውቅም። በአንጨት መሰንጠቂያ ውስጥ አንኳን የዚያን ያህል ብዙ ሳጋቱራ የሚገኝ አይመሰለኝም። የአንድ ጠቅላይ ግዛት የፖሊስ አዛዥ ሳጋቱራ ቁልል ውስጥ ምን ይሠራሉ? ብዙም ሳልቆይ ሳጋቱራ የአካባቢው የጭቃ መከላከያ መሆኑን ተረድቻለሁ።

ሻለቃ በቀለ ከመቀመጫቸው ተነሥተው እና እጃቸውን ዘርግተው ከጨበጡኝ በኋላ -

"ተቀመጥ" አሉኝ።

"እሺ" ብዬ ለእንግዶች ከተዘጋጁት ወንበሮች አንዱን ስቤ ተቀመጥኩ።

"እልቅስ እልቅስ እይደል አሁን የሚልህ?" አሉኝ፥ ገና ንግግር ሲጀምሩ። ሰውዬው ፖሊስ ብቻ ሳይሆኑ፥ ሳይኮሎጂስትም ጭምር መሆን አለባቸው። እንዴት ዐወቁብኝ? በተከከል እልቅስ አልቅስ አያለኝ ነበር። ገና አቶ ይልማ ሆቴል ውስጥ፥ ወደግርፍበት ከፍል ስገባ ነው ሆድ ሊብሰኝ የጀመረው። አሁን እየዘነበ ባይሆንም፥ ወደ ሻለቃ ቢሮ በመጣሁበት መንገድ ላይ ያየሁት ያ ሁሉ ማጥ የዋዛ ዝናብ የፈጠረው እንዳይደለ ተረድቻለሁ። ፀሐይ እትታይም፤ ይቀዘቅዛል፤ የጨፈገገው ቀን ነው። ስለ ጎባ የዓየር ጠባይ ምንም ዐይነት ጥናት አላደረግሁም።

"እም!" አልኳቸው።

"ጎባ ምን እንደሚባል ልንገርህ?"

"ምን ይባላል?"

"ሲገቡ በእንባ! ሲወጡም በእንባ!"

"ሲገቡ በእንባ የሚባልበት ምክንያት ይገባኛል። ሲወጡም በእንባ ለምን እንደ ሚባል ግን አልገባኝም።"

"ሲገቡ ይጠሉት እና አሁን አንተ እንደ ሆንከው ይሆናሉ። በኋላ ደግሞ ይለምዱት እና፥ የጠሉትንም ያህል ይወድዱት እና፥ ሲወጡም ያለቅሳሉ።"

"እኔን በተመለከተ የፊተኛው እንጂ የኋለኛው አውነት እንደማይሆን እርግጠኛ ነኝ።"

ትክክለኛ እና እጅግም ወቅታዊ ከሆነው፥ ከዚህ የሻለቃ በቀለ አረጋጊ መከፈቻ (ICE BREAKER) በኋላ፥ ወደ መጣሁበት እና በፈታችን ወዳለው የባንኩ ቅርንጫፍ ምረቃ ፕሮግራም ተመለስን። የምንነጋገረውንም ሁሉ ተነጋገርን እና ወደ ሆቴሌ ተመለስኩ።

ጎባ ሦስት ዓመታት ከዘጠኝ ወራት ቆይቻለሁ። ከዓመቱ ውስጥ በጠቅላላው ወደ ዘጠኝ ወራት ይዘንባል። በጋው እና ከረምቱ ተለይቶ አይታወቅም። ጭቃ ነው። ጭቃው እህያ ከነጭነቷ ሲያስምጥ፥ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው፥ ሁለት ወፍራም እጠናዎች በአህያዋ የፊት እና የኋላ እግሮች አካባቢ ከሥሯ አስገብ ተው፥ በሽክም ሲያወጧት አይቻለሁ። ብርድ ነው። ፍሪጅ አያስፈልግም። የገበለ እንጀራ ይበላል። ሁሉ ዐይነት አልኮል፥ የማር እና የኮሶ አረቄም ጭምር፥ ይጠጣል። ከብቶቹ ጠስኝ ይበላሉ። ሥጋቸው እና ወተታቸው ለጉድ ይጣፍጣል። ትንኞች እና ዝንቦች የሉም። ልጆች ጉንፋን ሳይዛቸው ያድጋሉ። ጎልማሶች ረዥም ዕድሜ ይኖራሉ።

ጃንሆይ ጎባን የጎበኙ ጊዜ፥ "ዕድሜአቸው 126 ዓመት ነው" መሰለኝ የተባለ አንድ ሽማግሌ ሰው "እኔ ያንተ እሽከር" እያሉ በሰለሰ ድምፃቸው ሲፎክሩ ሰም ቻቸዋለሁ። በጣም ሰፊ በሆነ ዳሰ ውስጥ ግብር እየተበላ ነበረ። ጉልበት ያላቸው ሰዎች ወደ ፊተኛው የዳሉ ከፍል እየሄዱ፥ ለንጉሥ በሚታዩበት እና በሚለሙበት ቦታ እየተንጎራደዱ ያቅራራሉ፥ ይፎከራሉ። ያልኳቸው ደካማ ሽማግሌ ግን ከኋላ፥ እኔ ከተቀመጥኩበት አካባቢ፥ ትንሽ እንደ መንጎራደድ እያሉ፥ እንኳን ከፊት ላሉት፥ በቅርባቸው ላለነውም በቅጡ በማይሰማ ድምፅ ፎከሩ። ማንም እያዳመጣቸው እንዳልነበረ እንዴት እንዳወቁት እንጃ፥

"ተፈሪ፥ ምሣህ ይቀራል እንጂ ኩርፊያው ምንድነው?" ብለው፥ እዳራሹን ጥለው ውልቅ አሉ። በኋላ ተለምነው ተመለሱ እና ከንጉሡ አካባቢ ተቀም ጠው ምሣቸውን በሉ። ገንዘብ እና ልብሰም ተሸለሙ።

ሻለቃ በቀለ እንዳሉትም ጎባን በጣም ለምጀዋለሁ፤ ወድጀዋለሁም። ለቅቄው ስወጣ አለቅሰ እንደ ሆነ ወደ ፊት ይታያል። ሁለት ዓመት ከቆየሁ በኋላ፥ "ጎባ ክረምት ገባ" በሚል ርእስ የጻፍኳት እና ከአዲስ ዘመን ወይም ከዛሬዬቱ ኢት ዮጵያ ጋዜጦች በአንደኛው ላይ የታተመችው ግጥሜ የመልመዴን ልከ ሳታሳብቅብኝ እትቀርም። የማሰታውሰው የሚከተሉትን ስንኞቿን ብቻ ነው፦

... ስንት ዓመት ዘነመ?
ስንት ዓመት ጨለመ?
ዐለት እያራሱ፥
ዐፈር እና ደንጊያ እያግበሰበሱ፥
ዋቤ እና ገናሌ ስንት ዓመት ፈሰሱ?
ተሜ ትሄዳለች
ደብተሯን ሸጉጣ፥
ጭቃ መርገጥ ቀፏት፥ ታጉረመርማለች -
"እበሳ ነው ጣጣ!"
የቆመበት ዐጥንት
የለበሰው ሥጋ፥ የደረበው ሸማ፥
ይህ ጭቃ መሆኑን፥ ባይነግሩት ይሆናል፥
ባያውቀው፥ ባይሰማ።

የመጀመሪያዎቹ አምስት ስንኞች ሳንሱሩን አላለፉም መስለኝ ጋዜጣው ላይ ሳይታተሙ ቀርተዋል። ይኸም ፖለቲካ መሆኑ ነው?

ተራከቢዊ ተዓቅቦ

ፍቅር ደጋግሞ ይዘኝ ያውቃል። የመጀመሪያው የያዘኝ በ1949 ዓ.ም.፥ ዕድሜዬ ዐሥራ አምስት ዓመት ከመድፈኑ በፊት ነው። በዚያን ጊዜዋ የሰዶ ከተማ "እጣቢ" የምንላቸው፥ ገንዘብ እየተከፈላቸው የሰዎችን ልብስ የሚያጥቡ ወን ዶች ነበሩ። የሚያጥቡበት ወንዝ ቀደም ሲል እንኖርበት በነበረው መሬታችን ላይ ነው የሚወርደው። እንድ ቀን በዚያ በኩል ሳልፍ፥ እንዲት ወጣት ልጅ

ልብስ ታጥባለች። እያጠበች ደግሞ እንደ ጉድ ትዘፍናለች። መጀመሪያ ላይ የሳበኝ አዘፋፈንዋ ነበር። ዐይኖቼ ያንን ሰርቅርቅ ድምፅ ወደሚያወጣው አፍ፥ አንገት፥ ደረት፥ ወዘተርፈ እያሉ ወደ ታች እና ወደ ላይ ሁለንተናዋን ቃኙት። መልእክ አይቼ አላውቅም፤ ግን ከዚህች ልጅ ይልቅ ሊያምር አይችልም። የሆነ የስንበት ቀን ነበረ መሰለኝ፥ ያን ዕለት አዚያ ወንዝ ላይ ከእኔ እና ከዚያች ልጅ በስተቀር ሌላ ሰው አልነበረም።

አጠባዋን ጨርሳ እስከምትሄድ ድረስ ፈዝዤ ሳያት እና ስሰማት የቆየሁ ይመስለኛል። እኔም የራሴን ልብሶች እዚሁ ወንዝ ላይ አንጨፍጭፌ ዐውቃ ለሁ። የታወቁት አጣቢዎችም እዚሁ ወንዝ ላይ የከተማውን ልብስ ሁሉ ሲያ ጥቡ ብዙ ጊዜ አይቻቸዋለሁ። እንደዚህች ልጅ፥ ልብስ የሚያጥብ ሰው ግን አይቼ አላውቅም። ልብሱን የምታሽበት አስተሻሸት፥ የምታለቀልቅበት አለቃ ለቅ፥ የምትጨምቅበት እጨማመቅ፥ እንቅስቃሴዋ ሁሉ የተለየ ነው። የሆነ ቄንጥ አለው። እሱም እራሱ ዘፈን ነበር። ከአርሱ ይልቅ ደግሞ የዘፈንዋ! ከዘፈንዋ ደግሞ የድምፅዋ! ከድምፅዋ ደግሞ የግጥሞችዋ! ምን ጉድ ነው እሱ? በውስጤ እንደ ነበረ በማላውቀው፥ "እፍላጦናዊ ፍቅር" ልበለው?፥ ነፍሴ ተቀሰቀሰች - ለመጀመሪያ ጊዜ።

በሌላ ቀን፥ ያችን ልጅ በመንገድ ላይ ስትሄድ አየኋት። ስላምታ ልሰጣት ድፍረት አልነበረኝም። ብቻ በሩቁ ስከተላት ቆይቼ የምትገባበትን ቤት እየሁት - መጠጥ ቤት ነው፤ ጠጅ ቤት። ደግሞ በሌላ ቀን በሆነ በዓል ሰሞን በዚያ ቤት ደጅ ሳልፍ፥ በቤቱ ውስጥ ሰዎች ሲዘፍኑ ሰማሁ። አሁን አላመነታሁም - ዘው ብዬ ገባሁ። ዘፈን ሰሰማ የሚያደርገኝን አላውቀውም ነበር። እንደ ገባሁም ዘፋኞቹን ተቀላቀልኩ። በቁጥር ጥቂት የእኔ ብጤ ልጆች የነበሩባቸው ቢሆንም፥ አብዛኞቹ ግን ጎረምሶች ነበሩ። ልጅቱም እዚያው መካከላችን ነበረች። እህል ውሃ ሳንቀምስ፥ እንዲሁ ስንዘፍን ዋልን። ወደ ቤታችን ለመ ሄድ ስንነሣ፥ "ነገም ኑ!" አለችን - ልጅቱ። "ወየው ጉድ፥ ጠይቀሽ ነው?" አልኩ - በልቤ። አሁን ስሟንም ዐውቄዋለሁ - "በቀለች" ነው የምትባለው። "በቀለች ... በቀለች ... ::" ስሟ እራሱ እንደ ዘፈኗ ነው የሆነብኝ - ተሰምቶ የማይጠገብ።

በማግሥቱ ከማንም ቀድሜ የደረስኩት እኔ ነበርኩ። ብቻዬን መግባቱ አሳፍ ሮኝ ወዲያ እና ወዲህ ሰል ትንሽ ጊዜ ገደልኩ። ሁለት እና ሦስት ልጆች

ሲጨማመሩልኝ፥ ገባን። ከተጨማመሩልኝ መካከል አበራ ገብረ መስቀልን አስታውሳለሁ። እርሱ ጥሩ ዘፋኝም ነበር። ከእኔም ጋር በደንብ እንተዋወ ቃለን። አሁን በቅርቡ፥ ለገብርኤል በዓለ ንግሥ ቁልቢ በሄደበት፥ በዚያው በያዘው የጦር መሣሪያ እራሱን አጠፋ። ከጠዋቱ እራት ሰዓት ገደማ ሲሆን በቱ ሞላ። ከጎረምሶቹ መካከል እንዱ፥ ከሆኑ ጠና ካሉ ሴት ጋር ሲንሾካሾክ እየሞለሁ። እንደዚያ ባለ የሞቀ ዘፈን ውስጥ እያለሁ፥ ምናልባት አውራጁም እኔው እራሴ ልሆን እችላለሁ፥ እንዴት ዐይኖቼ ሌላ ነገር መከታተል እንደ ቻሉ አይገባኝም።

ሰውዬው ገንዘብ ከኪሱ አውጥቶ ለሴትዮዋ ሲሰጣቸው እየሁት። ትንሽ ቆየት ብሎ፥ ያች ልጅ ከመካከላችን ተነሥታ ወደ ጓዳ ገባች። እሁንም ትንሽ ቆየት ብሎ፥ ጎረምሳውም ከመካከላችን ተነሥቶ በዋናው በር በኩል ወደ ውጭ ወጣ። በሙሉ ልቤ እየዘፈንኩ ነኝ። ዐይኖቼ ግን ሳላዝዛቸው የሰዎቹን እንቅስ ቃሴ ይከታተላሉ። ትንሽ ቆይቶ፥ ከመካከላችን ወጥተው የሄዱት ሁለት ሰዎች፥ እንዱ ከሌላው ትንሽ ዘግየት ብለው፥ በየወጡበት በር ወደ መካከላችን ተመለሱ። በዚያን ጊዜ፥ የሄዱበት ጉዳይ ገባኝ። ምነው ባላየሁ ኖሮ! ዘፈኑን እቋርጬ ተነሣሁ እና ወደ ቤቱ ሄድኩ። የዚያን ዕለቱን ውሎ እና አዳር፥ ውሎ እና አዳር አይበለው። ትንሽዋን ልቤን ፍቅር ብቻ ሳይሆን፥ ቅናትም አጋያት - እሁንም ለመጀመሪያ ጊዜ።

በ1947 ዓ.ም. ይመስለኛል፥ ልብስ ማጠቢያው ወንዝ በሚወርድበት መሬታችን ላይ በምንኖር ጊዜ፥ ከሴት ጋር የተያያዘ እንድ መጥፎ አጋጣሚ አግኝቶኛል። ግርማ ሀብተማርያም የሚባል የልጅነት ጓደኛ ነበረኝ። የእንድ ሰፈር ልጆች ነን። ግርማ በዕድሜ ጥቂት ዓመታት ይበልጠኛል። አንድ ቀን ከብቶች እያገድን አያለ፥ ከቢታቸው ሳይሆን አይቀርም፥ አብራው ከመጣች አንዲት ልጅ ጋር "እንተኛ" አለኝ። "ሞኝ እንደ መከሩት"፥ "እሺ" አልኩት። እርሱ አስቀ ድሞ ተኛ። ከዚያ በፊት ልምድ አለው እንደ ሆነም እላውቅም፥ ቻለበት። "ቂካ ውስጥ ይሁን እንጂ፥ የምናደርገውን ሁሉ እየተያየን ነበር የምናደርገው። "አሁን ያንተ ተራ ነው" አለኝ እና ልጅቱን ለቀቀልኝ። እኔ እንደ ግርማ ሳልችልበት ቀረሁ። እምቢ አለኝ። በጊዜው ምንም እልመሰለኝም ነበር።

ለሁለተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ሙከራ ያደረግሁት ከሰምንት ዓመታት በኋላ፥ ጅማ እያለሁ ነው። ያን ጊዜም፥ ልከ እንደ መጀመሪያው ጊዜ፥ እምቢ አለኝ።

በሶዶ፥ በጅማ፥ በይርጋ ዓለም፥ በአዲስ አበባ፥ በጎባ "ልጃገረድ ጓደኞች" ነበሩኝ። ሆኖም፥ አንዚያ ሁሉት ገጠመኞቼ ካሳደሩብኝ ፍርሃት የተነሣ፥ ከእነዚህ ጓደኞቼ መካከል ከአንዳቸውም ጋር ተራክቦ ስማድረግ አልደፈር ኩም። ዕድሜዬ እየጨመረ ሲመጣ ግን፥ ነገሩም እያሳሰበኝ መጣ። ከማሳሰ ብም አልፎ እያስጨነቀኝ እና ጤናም እየነሣኝ መጣ።

ከልጅነቴ ጀምሮ አራስ ምታት እና ነሰር ያዘወትሩኛል። በየወቅቱ በገባያ ላይ የዋሉትን የአራስ ምታት ኪኒኖች አየቃምኩ ነው ያደግሁት ማለት አችላለሁ። ጎባ እያለሁ፥ ከዕለታት አንድ ቀን በኃይል ነሰረኝ። ሁል ጊዜ ነው የሚነሰረኝ፤ ያን ዕለት ግን ከወትሮው በተለየ ዐይነት በኃይል ነሰረኝ ማለቴ ነው። ደንበ ኞችን የምናስተናግድበት አይደለም አንጂ፥ የሥራ ሰዓት ነው የነበረው። አለቃዬ አቶ ሙሉጌታ ዱባለ ደነገጠ። አፍንጫዬን በጥጥ ወትፎ እና በባንኳ ላንድ ሮቨር መኪና ውስጥ እንገቴን ወደ ማጅራቴ አስግጌ ተቀምጬ፥ ይዞኝ ወደ ጎባ ሆስፒታል በረረ። በጊዜው በጎባ ሆስፒታል ዶክተር ዴኮቭ የሚባል ቡልጋሪያዊ ሐኪም ነበር። "አስቸኳይ ታካሚ" ተደርጌ ተወሰድኩ። ዶክተር ዴኮቭ የደም ግፊቴን ለክቶ አየ እና ከፉኛ ደነገጠ።

"እንዴት እንደዚህ ሊሆን ይችላል?" አለ በመገረም።

"ምንድነው የሆነው?" አለው አቶ ሙሉጌታ።

"የደም ግፊቱ ሁለት መቶ ከምናምን በአንድ መቶ ከምናምን ነው" አለው። "ከምናምን" ያልኩት ከመቶዎቹ በላይ ያሉትን ቁጥሮች ስላልያዝኳቸው ብቻ ነው። ሊያስብ ይመስለኛል፥ ትንሽ ክቆየ በኋላ ደግሞ፥ "የተበጠሰው የሆነ ቦታ ያስ ሥር ቢሆን ኖሮ፥ አደገኛ ይሆንበት ነበር" አለው። መድኀኒት አዝዘልኝ እንደ ሆነ ትዝ አይሰኝም። ሥጋ እና ጨው እንዳልበላ፥ ቡና እንዳልጠጣ አንደ አዘዘኝ በትክክል አስታውሳለሁ። ያስገረመኝ ግን የሚቀጥለው ትዕዛዙ ነው - "አብዝተህ ከሴት ጋር ተራክቦ አድርግ።" ከፍርሃት እና ከጭንቀት የተነሣ ልሞከረው በማልደፍረው፥ በዚህ ዐይነቱ የሐኪም ትዕዛዝ ሥር እያለሁ ነበር፥ ከወይዘሪት ገነት ሀብተ ማርያም ጋር የተገናኘሁት።

የስእለት ሚስት

ገነት ወደ ጎባ የመጣችው በ1964 ዓ.ም. ሁለተኛ አጋማሽ ውስጥ ነው። ቆይቼ አንደ ተረዳሁት፥ ባለፉት ሦስት ዓመታት እርስዋም በራስዋ ውጣ-ውረዶች

ውስጥ አልፋለች። ከሐዋሣ ወደ ጎባ የተላከችው ከእንዲት ዘመዳቸው ዘንድ ሆና እንድታርፍ እና እንድታገግም ታስቦ ነው። ምናልባትም፥ ሊያጋጥሟት ከሚችሉ ከሴሎችም ውጣ-ውረዶች አንድትሰወር ጭምር ነው። እንደ ዕድል ሆኖ፥ ጎባ ገብታ ብዙም ሳትቆይ በጠቅላይ ግዛቱ የጤና ጥበቃ ጽሕፈት ቤት ውስጥ በጸሐፊነት ተቀጠረች። እኔ አላውቀውም እንጂ፥ "እንደ ዕድል" ላይ ሆን፥ ቅድመ ዝግጅትም የነበረ ሊሆን ይችላል - ያረፈችባቸው ዘመዷ የጤና ጥበቃ ሠራተኛ ነበሩ።

አዚያ ስትሠራ ነው ከእኔ ጋር የተዋወቅነው - የባንክ አገልግሎት ፍለጋ ወደ ቢሯቸን በመጣች ጊዜ። ከትውውቃችን በኋላ ብዙም ላልታገሥ ነው፥ እንድ ቀን አመቺ ቦታ ላይ ሳገኛት ያስቆምኳት እና ጓደኛዬ አንድትሆን የጠየቅኋት። አንድ ሁለት ወራት ደጅ ያስጠናችኝ ይመስለኛል። መስከረም 16 ቀን 1965 ዓ.ም. ገነት እኔን እና ወይዘሪት አልማዝ ሻረውን ከምትኖርበት ቤት ምሳ ጋበዘ ችን። አልማዝ ከጅማ ጀምሮ ጓደኛዬ የነበረው የኃይሉ ሻረው እኅት ስትሆን፥ በዘያን ጊዜ በባሌ ጠቅላይ ግዛት በደን እና ዱር አራዊት ጥበቃ መሥሪያ ቤት ውስጥ በኤከስፐርትነት የሚሠራውን ወንድሟን ኃይሉን ለማየት ነው ከምትማ ርበት ከሐዋሣ የመጣችው። እነ ኃይሉ እና ገነት የአስላ ልጆች ስለ ሆኑ፥ ቀደም ሲል ጀምሮ ይተዋወቃሉ።

ያን ዕለት ኃይሉ በከተማው ባይኖር ነው ይመስለኛል፥ ምላው ላይ አብሮን አልነበረም። እየተጫወትን ቆንጆ ምሳ በላን። በልተን ከጨረስንም በኋላ አየተጫወትን እስከ ዐሥር ስዓት ገደማ ድረስ ቆየን። ከዚያም፥ ዕስቱ የደመራ በዓል ስለ ነበረ፥ የፈረስ ጉግሥ ለማየት ወደ ፈረስ መጋለቢያ አብረን ወጣን። ፈረስ መጋለቢያው የአውሮፕላን ማረፊያው ነው። እና አስከ በዓሉ ፍጻሜ ድረስ ደስ የሚል ጊዜ አብረን አሳለፍን። ከፈረስ መጋለቢያው እያለን ነበር፥ "ጓደኛ ሁኚኝ" የሚለውን ጥያቄዬን እንደ ተቀበለችው ገነት የነገረችኝ - ሴቶች ብቻ በሚናገሩበት፥ በዚያ ቃል-አልባ ቋንቋቸው።

ደስታ እና ፍርሃት በተቀላቀሉት ስሜት ነበር ያን ዕለት ማታ ወደ ቤቴ የተመለስኩት። ያች ዕለት፥ ከገነት ጋር የፍቅር ግንኙነት የጀመርኩባት ተደርጋ ልትወሰድ ትችላለች። ልጅቷን ያስ ጥርጥር ልቤ ወዷታል። እርስዋም ጓደኛዬ ለመሆን ፈቃደኛ ሆናለች። ደስ ብሎኛል፤ ደግሞም አዝኛለሁ። እንደኛ፥ ይህንን ግንኙነት በምጀምር ጊዜ እኔ ከባሌ ጎባ ወደ አስታ ወንዶ መዛወሬ ተነግ

ሮኖል። የሚተካኝን ለው በመጠበበቅ ላይ ነው ያለሁት። ገነት ይህንን ገና አላወቀችም። በምታውቅ ጊዜ ምን ትላለች? እንደዚህ ዐይነቱ ግንኙነትስ የት ይደርሳል? ሁለተኛ አና ከሁሉም በላይ፥ የአሁኑ ፍቅር ከከዚህ በፊቶቹ ፍቅሮቼ በምን ይለያል? በተራከቦ ልቋጨው ካልቻልኩ በለተቀር፥ ይሽኛውም የሚጠብቀው የከዚህ በፊቶቹ ዐይነት ዕጣ አይደለም ወይ?

በእንድ በኩል ለእነዚህ ጥያቄዎቼ እጥጋቢ መልስ ሳላገኝላቸው፥ በሌላ በኩል ደግሞ ከገነት ጋር የጀመርኩት ግንኙነት ከፍላጎቴ አና ከቁጥጥሬም ውጭ አየጦዘ አንደ ሄደ፥ ታሕሣሥ አጋማሽ ላይ ጎባን ለቀቅሁ። ሻለቃ በቀለ ጉደታ (እኔ ጎባን በምለቅበት ጊዜ ኮሎኔል) ጎባን መጀመሪያ በረገጥኩ ዕለት ከነገሩኝ ተረት ባይብለ፥ የማያንስ ነገር ነበር የደረሰብኝ። እርግጥ፥ ዕንባ እፍሰሼ አላለቀሰኩም። ለምን አንደ ሆነ አላውቅም፥ እንባ በቀላሉ የሚወጣው ዐይነት ሰው አልነበርኩም።

"ስለማታለቅስኮ ነው" ትለኝ ነበር እናቴ፥ በልጅነቴ አባቴ መትቶኝ መትቶኝ ለምን አልጠቅምህ እንደሚለው ስታስረዳኝ። "እኅትህን (አለካለን ማለቷ ነው) አታያትም? ገና በእጁ ሳይነካት ትጮኻለች፥ ትንፈራፈራለች። 'ጋሼ? ጋሽዬ? ስሞትልህ፥ ዐፈር ስበላልህ' ትለዋለች። ይተዋታል። እንተ የሆነ ጋግርት አለ ብህ መስለኝ፥ መልሰህ ዐይንህን ታጉረጠርጣለህ፤ ሰው እልህ ታሰይዛለህ" ትለኛለች። እና በዚያችም ዕለት ለገነት እጆቼን አውለብልቤላት ወደ አውሮ ፕላኑ ውስጥ ሰገባ፥ ዕንባ እልወጣኝም።

ጥቂት ቀናት እዲስ አበባ ከቆየሁ በኋላ፥ አናቴን ለማየት ወደ ዎላይታ ሄድኩ። ገነትም ለጥምቀት ከጎባ መጣች። እና ለሌላ ዐሥር ቀናት ያህል እናቴ ቤት አብረን ቆየን። ከዚያ እኔም እዲስ የባንክ ቅርንጫፍ በእለታ ወንዶ ለመከፈት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ለለ ነበረብኝ፥ እርሷም ዕረፍትዋ አየተገባደደ ለለ ነበረ፥ ሐዋሣ ድረስ እብረን መጣን። እንድ ሦለት ቀናትም በሐዋሣ አብረን የቆየን ይመስለኛል። በእነዚህም ቀናት ውስጥ፥ በሐዋሣ ያሉትን ዘመዶቿን ሁሉ ተዋወቅኋቸው - በመጀመሪያ ገና ሁለት ዓመት ተኩል ያልሆነውን ልጇን ጌዲዎንን፥ ቀጥሎም እኅቶቿን ሰናይትን አና ፍሬ ሕይወትን፥ አከሰቷን ወይዘሮ ጤናዬን አና ባለቤታቸውን በጅሮንድ እሉላን፥ የሰናይትን ባለቤት ታደለን፥ ወዘተርፈ። ከዚያ እርሷ ከጌዲዎን ጋር ትንሽ መቆየት ለለ ነበረባት፥ ትቻት ወደ አለታ ወንዶ ሄድኩ።

ስንለያይ ለፋሲካ እለታ ወንዶ እንደምትመጣ ነገረችኝ። ከባድ የቤት ሥራ ሰጠችኝ። ብዙ ማስብ፥ ብዙ ማውጣት እና ማውረድ፥ ብዙም መጨነቅ ነበረ ብኝ። ምንድነው የማደርገው? "አትምጪ" ልበላት? እውነቱን ለመናገር፥ እንደዚያ የምልበት ዐቅም አልነበረኝም። ግንኙነቱን ላቋርጥ? እንዴት አድርጌ? አብዛኞቹን ቤተ ሰቦቿን ከተዋወቅኋቸው በኋላ? ዝም ልበላት እና ትምጣ? እንዴት አድርጌ ነው ዝም የምላት እና የምትመጣው? በአእምሮ እና በአካል፥ ጠናማ ወንድ ነኝ። ሆኖም ከዐሥር ዓመታት በፊት፥ ጅማ አየለሁ፥ ከእንዲት ሲተኛ አዳሪ ጋር ባደርኩበት ሴሊት አሳፋሪ የሆነ ነገር አጋጥሞኛል። አሁንም እንደዚያው ቢሆንብኝስ? ትዳር ያለ ተራከቦ ይሆናል?

በወርኅ የካቲት፥ ከምሽቶች በአንዱ ምሽት፥ አድርጌው የማላውቀውን እንድ ነገር አደረግሁ። እሰቤበት፥ ትርፍ እና ኪሣራዬን አስልቼ፥ ያዋጣኛል ብዬ፥ ያደረግሁት ነገር እይደለም። የጭንቀቴ ጭካኔ ነበር ወደዚያ ጥግ ያደረሰኝ ብል ይሻለኛል። በማላውቀው ኃይል ተነድቼ ያደረግሁት ነገር ነበር ብል ደግሞ የበለጠ ወደ አውነቱ እጠጋለሁ። ባንክ በተከራየልኝ መኖሪያ ቤቴ ሳሎን ውስጥ ተንበረከከሁ - በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ። ተንበርከኬም -

> "እግዚአብሔር የምትባል ካለህ!" አልኩ። "ገነትን በጣም ወድጃታለሁ! ... እርስዋ ሚስቴ ... ጌዲዎንም ልጄ እንዲሆኑ እፈልጋለሁ ... በእኔ ዘንድ ያለውን ይህንን ችግር አስወግደህልኝ ... እኔን እና ገነትን ባል እና ሚስት ብታደርገን ... በሕይወቴ ከገነት በስተቀር ሌላ ሴት ላትኖር ቃል እገባልሃለሁ። ... ደግሞ ሁለታችንንም እባከህን ያንተ አድርገን።"

ቤቱ ውስጥ ያለሁት ብቻዬን ለለ ነበረ፥ ድምፄን እስምቼ ነበር የተናገርኩት። የኑካኝን ነገር አላውቅም፥ ሰቅሰቅ አያልኩ እያለቀስኩም ነበር የተናገርኩት። ያደረግሁት ነገር "ጸሎት" ወይም "ስእለት" የሚባለው ነገር እንደ ሆነ የገባኝ ከሦስት ዓመታት በላይ ቆይቼ ነው። ከሁለት ተኩል ወራት በኋላ፥ እንደ ተናገረችው ገነት ለፋሲካ እለታ ወንዶ በመጣች ጊዜ፥ ተራከቧዊው ተዓቅቦ ከላዬ ተነሣልኝ - ለእንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ። ደስታዬ ወለን አልነበረውም።

የቆይታዋ ጊዜ ሲያበቃ፥ በሰኔ ወር መጨረሻ ላይ ሥራዋን ለቅቃ እና ጠቅልላ እንደምትመጣ ተሰማምተን፥ ገነት ወደ ጎባ ተመለሰች። ከሁለት ወራት በኋላ አብረን መኖር ጀመርን - እማኝ የለም። ፊርማ የለም። ሰማኒያ የለም። የማዘ

ጋጃ ቤት ወይም የቤተ ክርስቲያን የምስክር ወረቀት የሰም። ሆኖም፥ ከእነዚህ ሁሉ የሚበልጥ፥ ሌላ ነገር አሰ። ያም ሌላ ነገር፥ "ቃል" የምሰው ነገር ነው።፥ "ሰእሰት" ወይም "ኪዳን" ብዬውም ዐውቃለሁ። በኋላ ላይ፥ ሁሉንም የጠቀ ሰልኩት ግን "እግዚአብሔር!" በሚሰው ነው። "እማኝ፥ ፊርማ፥ ወዘተርፈ"፥ ያልኳቸው ነገሮች አያስፈልጉም እያልኩ አይደሰሁም። ያስፈልጋሉ። በጣም ያስፈልጋሉ። እኛ አልነበሩንም ማሰቴ ነው። እነዚያ - ቃል ወይም ኪዳን ወይም እግዚአብሔር ያልኳቸው - በሌሉበት፥ እነዚህ የሚፈይዱት ነገር አይኖርም ማለቴም ነው።

ባጉተ ያላረፈ፥ ምኑን ዓረፈ?

የዚህን ርእሴን አሳብ ያገኘሁት ከታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ከቅዱስ አውገስጢኖስ መጽሐፍ ነው - "እቤቱ ሰራስህ ሠርተኽናል፤ በእንተ እስከሚያርፍም ድረስ፥ ልባችን (ነፍሳችን?) ሳያርፍ ይኖራል"[1] (ትርጉም የራሴ)። እኔ እስክ ማውቀው ድረስ፥ ከቅዱስ አውገስጢኖስ እባባሎች ውስጥ፥ የዚህኛውን እባባሉን ያህል በብዙ ሰዎች እየተጠቀስ፥ በብዙ ቦታ ያነበብኩት ሌላ እባባል የሰም። በእኔ እጅ በገባው የመጀመሪያው የመጽሐፉ ትርጉም ውስጥ፥ እባባሉ ያሰው ከዐሥራ ሦስቱ መጻሕፍት በመጀመሪያው ውስጥ ሲሆን፥ ከመጀመሪያውም መጽሐፍ በመጀመሪያው ገጽ የመጀመሪያ ዕሩብ ነው - ስለ ሰውዬው ገና ብዙ ከማንበቤ በፊት ሰማለት ነው።

ቅዱስ አውገስጢኖስ ባይሰውም ኖሮ፥ አባባሉ በእኔ ሕይወት እውነት ሲሆን የጀመረው ከገነት ጋር ከተጋባን በኋላ ብዙም ሳልቆይ ነው። ከገነት ጋር ባልና ሚስት በመሆናችን ደስታዬ ወሰን እንዳልነበረው ከላይ ገልጫለሁ። ከዚያ በፊት በውጭ ባለ-ብዙ ወዳጅ ብሆንም፥ በውስጤ ግን በጣም ብቸኛ ነበርኩ። ለሚያዩኝ ሁሉ በጣም ደስተኛ ሰው ብመስልም፥ በውስጤ ግን ፍርሃት እና ጭንቀት መሸገው ነበር። በፈለጉ ጊዜ ሁሉ ከምሽጋቸው ይወጡ እና ያሳድዱ ኛል። ሮጬ እና ሸሽቼ ላመልጣቸው አልቻልኩም። እንዴ? አራዊቱ እና አንስሳቱ፥ አዕዋፉ እና ዓሦቹ፥ ዝንቦቹ እና ሴሎች ሌሎቹ፥ በደመ ነፍስ የሚያከናውኑት ተፈጥሯዊ ተራክቦ አኮ ነው እኔን ያቃተኝ። እና ብዙ ብዙ ነገር አሳስቦኛል። ማንም ሲገምተው እንደሚችለው፥ እሱ ችግር አሁን ከእኔ በመለየቱ በጣም ደስ ብሎኛል።

ደስታዬ ግን፥ መስሎኝ እንደ ነበረው፥ ወሰን የሌለው አልሆነም። በአሰታ ወንዶ የሚኖሩ የይሖዋ ምስክሮች ወደ እኔ እና ወደ ቤታችን መጡ። በኩተ ሳው ውስጥ የማውቀውን እንድ ትልቅ ሰው፥ የባንካችንም ደንበኛ የሆነ ሰው፥ ተከትሰው ነበር የመጡት። በአዲስ አበባ የሚኖር የእንድ ባልንጀራዬንም ሰም ጠርተው ነበር የመጡት። እና እሰማስተናገድ አልቻልኩም። እነርሱ ሲመጡ፥ መልስ ያላገኘሁሰት የሕይወት ጥያቄም ነፍስ ዘራ። ከእከራሪ አርቶዶክሰነት እስከ አከራረ ከሃዲነት፥ እስክ ምን ዐውቄነት፥ እስከ ሮዚከሩሽያንነት ለዐሥር ዓመታት ያንገላታኝ ጥያቄ "ሰባት እራሱን" ሆኖ እንደገና መጣብኝ። "እፎይ!"፤ "ዐረፍኩ!" ያልኩት ሰው፥ ሰንኮፉ ያልተነቀለሰት ሕመሜ ይኸው አገረሸብኝ።

ላለፉት ሁለት ዓመታት ያህል፥ ከሮዚከሩሽያኖቹ ጋር አልተጻጻፍኩም። መጀመሪያ ላይ ገንዘብ ስለ ቸገረኝ ነበር መጻጻፍ ያቋረጥኩት። እጇ እንደ ረጠበ፥ ግንኙነቴን እንደምቀጥል ነው በአሳቤ የነበረው። በመሐሉ ገነት ገባች እና ሁሉንም ነገር አስረሳችኝ። ይኸው አሁን አስታዋሾች መጡ - የይሖዋ ምስክሮች። ከጅማ ጀምሮ ነው የማውቃቸው። ጀማሪዎችን ስለ እምነታቸው የሚያ ስጠኑባትን "THE TRUTH that leads to ETERNAL LIFE" የተባለች አነስተኛ መጽሐፍ እና ሌሎችም ጥቂት መጽሐፎቻቸውን አንብቤአለሁ። ባሌ ንባ እያለሁ፥ ከሁለት ዓመት ያህል ላላነሰ ጊዜ፥ "AWAKE!" የተባለውን መጽ ሔታቸውንም እንዲሁ በተከታታይ አንብቤአለሁ።

ደስታ ማሞ ነበር መጽሔቱ በቋሚነት እንዲደርሰኝ ያደረገው። ሳይከፍልበትም የቀረ አይመስለኝም። ከላይ "በአዲስ አበባ የሚኖር አንድ ባልንጀራዬ" ያልኩት እርሱን ነው። ከደስታ ጋር የምንተዋወቀው ከምላይታ ጀምሮ ነው። ትውው ቂም በወላጆቻችን የጀመረ ነው። ደስታ አንድ ዓመት ይቀድመኛል እንጂ፥ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለጥቂት ዓመታት እብረን ተምረናል። ከደስታ ጋር እዲስ አበባ ውስጥ እብረን ኖረናል - እነርሱ ቤት። እርሱ ኮካ ኮላ ኩባንያ ተቀጠረ እንጂ፥ የገንዘብ ሚኒስቴርን ፊተና እብረን ነበር የተፊተንነው። የባንኩንም ፈተና እብረን ነው የወሰድነው እና የተቀጠርነው። እኔ ወደ ባሌ ንባ ስዛወር ነበር፥ እርሱም ወደ ነጌሌ ቦረና የተዛወረው። ደስታ ስለ ሃይማኖት ብዙም ግድ ያለው ልጅ አልነበረም። እንዴት እንደ ሆነ ሳላውቀው፥ የይሖዋ ምስክር ሆነ።

"ሆነ" ብቻም ሳይሆን፥ ሌሎችንም መመልመል ጀመረ። ከተመለመሉለትም መካከል እምሳለ አሸንጎ አንዷ ናት። እምሳለ የብሥራት ሚስት ስትሆን፥ ብሥራት እና ደስታ ደግሞ የታላቅ እና የታናሽ ልጆች ናቸው። ብሥራት ማለት ለእኔ ታላቅ ወንድሜ እንደ ማለት ነው። ከጅማ ተባርሬ ወደ አዲስ አበባ በመጣሁ ጊዜ፥ ያለሁበትን ቦታ ፈልጎ እና አግኝቶ፥ ወደ ቤቱ የወሰደኝ እርሱ ነው። በእነር ውስጥ ገቢ ዋና መሥሪያ ቤት ተመድቤ ወደ ሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት እስከ ሄድኩበት ጊዜ ድረስ አብሬው ኖሬአለሁ። ከዚያ በኋላ የእርሱ እና የእምሳለ ቤት፥ ለእኔም ቤቴ ሆኖ ቀርቷል። ለመጀመሪያው ወንድ ልጃቸው ለሳምሶን የክርስትና አባት እድርገውኛል። ከዲላ ወደ አዲስ አበባ በተዛወርንም ጊዜ፥ ገነት እና እኔ ለሰምንት ወራት ያህል እነ ብሥራት ቤት አብረን ኖረናል።

"... እምነት፥ ተስፋ፥ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው" (1ቆሮ. 13፥13) የሚለው የመጽሐፍ ቃል እንዴት እውነት እንደ ሆነ የተረዳሁት እነ ብሥራት ቤት እንኖር በነበረ ጊዜ ነው። በቤቱ ውስጥ የነበርነው የሁለት የተለያዩ እምነቶች ተከታዮች ብንሆንም እንኳን፥ በመካከላችን ምንም ዐይነት ልዩነት አልነበረም። ብሥራት እና አምሳለ ሲበዛ ጥሩ ሰዎች ነበሩ። እኛም፥ በምድር ላይ አለ የምንለውን መልካም ነገር ከምንመኝላቸው በስተቀር፥ እንደዚህ ላሉ ጥሩ ሰዎች ልናደርግላቸው የምንችለው አንዳች ነገር አልነበረንም። ስለዚህም እነርሱ እና ልጆቻቸው የሕይወት እራስ የሆነውን ክርስቶስን እንዲያውቁ ዘወትር እንጸልይላቸው ነበር።

እግዚአብሔርም ጸሎታችንን ሰምቷል። እምሳለ ጌታን ተቀብላ፥ በሕይወቷም ፈጽሞ ተለውጣ፥ ከዐሥራ አንድ ዓመታት በፊት ወደ ጌታዋ ሄዳለች። እኔ እስከማውቀው ድረስ፥ ከዘጠኙ ልጆቻቸው መካከል ቢያንስ ስምንቱ በጌታ ናቸው። ብሥራት የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቆራቢ አባል ነው። ጸሎታችን፥ ቀድሞውንም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን እንዲቀይር ሳይ ሆን፥ "መንገድ እና እውነት ሕይወትም ነኝ" ያለውን (ዮሐ. 14፥6) ክርስቶስን በእምነት እንዲቀበለው ብቻ ነበር። ብዙ መንገዶች እና ብዙ አዳኞች በሚሰ በኩበት፥ ክርስቶስን ሳይቶ ለማወቅ ያለውን ችግር፥ ያለፍኩበት ስለ ሆነ፥ ዐውቀዋለሁ። እና በእርሱ በኩል ልቤ ገና አላረፈም።

ወደ እለታ ወንዶው ቤታችን የመጣው የይሖዋ ምስክሮች አገልጋይ ግርማይ ይባላል። "ፓዮኒር" ነው። "ወንጌላዊ" እንደምንለው መሆኑ ነው። ብሩክሊን፥ ነው ዮርክ (ዋናው ማዕከላቸው ያለበት)፥ ሄዶ የሠለጠነ እንደ ሆነ ተነግሮ ኖል። ለጥቂት ቀናት ወደ ቤታችን ተመላልሶ ሊያስተምረን ሞክረ። አብዛኛው ጊዜአችን የሚያልፈው ግን ከእኔ ጋር በምንነጥመው ክርክር ነበር ማለት እችላለሁ። ገነት ታኪታት። "እኔ ጭቅጭቅ አልፈልግም፤ ስለዚህ ግርማይ ሁለ ተኛ ወደ ቤታችን ባይመጣ ይሻላል፤ አንተ መማር ከፈለግህ፥ ሌላ ቦታ አየተገናኛችሁ መማር ትችላለህ" አለችኝ።

ገላገለችኝ ማለት ነው። "ገነት እንደዚህ አለችኝ" ሳልለው፥ ትምህርቱን ማቋ ረጥ እንደምፈልግ ለግርማይ ነገርኩት። ግርማይ ግን በቀላሉ ሊለቀኝ ዝግጁ አልነበረም። ከእርሱ በስተ ኋላ የደስታ እጅ የነበረም ይመስለኛል። ደስታ "በቀለ ከዚህ ሁሉ ክርክር በኋላ እንዴ ቢያምን፥ ጥሩ የይሖዋ ምስክር ይወጣ ዋል" ብሎ ያስባል ይመስለኛል። ስለዚህም የሄድኩበትን ቦታ ሁሉ በሄድኩበት አካባቢ ላሉት የይሖዋ ምስክሮች ይጠቁምብኛል።

"እንድ ዕድል ስጠኝ እና እንነጋገር" አለኝ ግርማይ። "እሺ" አልኩት እና ለአንድ ቀዳሚ ከሰዓት በኋላ ተቃጠርን። የምንገናኘውም እኔ ቢሮ እንዲሆን ተስማ ማን። ያን ከሰዓት በኋላ ግርማይ ሦስት እራሱን ሆኖ መጣ። ሌሎቹ ሁለቱ ከአዲስ አበባ ነበር የመጡት። አንደኛው እንዲያውም የማውቀው፥ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባልደረባ ነበር።

የተለያዩ መጻሕፍትም ይዘው ነበር የመጡት። እውነቱን ለመናገር፥ ያን ዕለት ብዙ ጥያቄዎቼን መልሰውልኛል። በእንድ ነጥብ ላይ ብቻ ነበር የተፋረስነው - "ኢየሱስ ዳግመኛ መጥቷል" አሉኝ። እኔም፥ ምንም ቢሆን በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሰማሁት ትምህርት እርሾው በውስጤ ነበረና በዚህ መስማማት አቃተኝ። ከብዙ ንትርክ በኋላ፥ ከቀኑ 12:00 ሰዓት ገደማ ላይ ተሰነባበትን። ጓዛቸውን ሰብስበው፥ ከቢሮዬ ወጥተው ሄዱ። እኔም ብቻዬን ቢሮዬ ውስጥ ቀረሁ።

ያን ዕለት በእውነት ድከም አለኝ። የተለያየነው ቀሰል ባለ ነጥብ ላይ ቢሆን ኖሮ፥ ዝም ብዬ እምኜላቸው ዐርፈው ነበር። "ኢየሱስ ዳግመኛ መጥቷል" የሚለው ትምህርታቸው ግን ተናነቀኝ። ስለ መምጣቱም ሆነ ስለ አለመምጣቱ ምንም የማውቀው ነገር ኖሮኝ አይደለም። እንዳሉት መጥቶስ ቢሆን?

"ባለፈው ጊዜ ስትመጣ፥ እኔ አልነበርኩም:: ስለዚህም MISS አደረግ ሁህ:: አሁን ደግሞ፥ ለሁለተኛ ጊዜ፥ እንዴት MISS አደርግሃለሁ? IT IS NOT FAIR"

አልኩ - ድምፄን አሰምቼ:: በጣም አዘንኩ:: በማን ላይ እንደ ሆነ አላውቅም እንጂ፥ በጣምም ተቆጣሁ:: እንደዚያ ብቻዬን ለነጋገር፥ እንድ አሳብ መጣብኝ:: እነዚህ የይሖዋ ምስክሮች ምንድናቸው? ምንድነው የሚያምኑት? ስለ እነርሱ ማን ሊያስረዳኝ ይችላል? ጥያቄውን በውስጤ ገና ከመጠየቄ፥ መልሱን ደግሞ ወዲቅሁት - ስለ እነርሱ ሊያስረዳኝ የሚችለው ሚስዮናዊው ሰውዬ ነው:: እርሱ መቼም ቴዎሎጂይ (የእማርኛ አቻው "ሥነ መለኮት" መሆኑን በኋላ ነው ያወቅሁት) ተምሯል:: እርሱን ነው መጠየቅ ያለብኝ:: የዚህን ጥያቄዬን መልስ ሳላገኝ ዛሬን ማደር አልችልም::

የባንኳን ቮልክስዋገን መኪና አስነሣሁ እና ወደ ሚስዮኑ ጣቢያ አቀናሁ:: ሰዓቱን በትከክል አላስታውስም፤ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ካለፈ ወዲያ መሆኑን ግን እርግጠኛ ነኝ:: በቀን ሄጀበት ወደ ማላውቀው ቦታ፥ በማታ!

ጸሎት! ለሁለተኛ ጊዜ!!

ከግቢው በር ላይ ሰደርሰ የጥበቃው ሠራተኛ አነጋገረኝ:: ወዴት እንደምሄድ ነገርኩት:: የሚሰዮናዊው ቤት የትኛው እንደ ሆነም ጠየቅሁት:: ከመኪናዬ ወርጄ፥ በሩን ሳንኳኳ፥ የከፈተልኝ ሚስተር ፋርገር እራሱ ነበር:: ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ሠራተኛ በመሆኔ፥ ከሚስተር ፋርገር ጋር ከዚህ በፊት አንድ ጊዜ ተገናኝተናል - ወደ ቅርንጫፍ ባንካቸን፥ ምናልባት ፊርማውን እንዲሰጥ፥ ይዘውት በመጡ ጊዜ:: በማታ በሩን ያንኳኳው ሰው የባንኩ ሥራ አስኪያጅ መሆኑን ባየ ጊዜ፥ ሚስተር ፋርገር ተገርሚል::

"እዶ በቀለ፥ What a surprise! ('ምን አግር ጣለህ!' እንደ ማለት)፥ እያለ እጁን ዘረጋልኝ:: ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጥን - በሩ ላይ እንደ ቆምን::

ቀጠለናም፥ "Come in, please" አለኝ፥ በሩን በሰፊው እየከፈተልኝ:: ገባሁና ተቀመጥኩ:: የእኔን እና የቤተ ሰቤን ጤንነት ጠየቀ:: ስለ ሥራዬም ጠየቀኝ:: ለጥያቄዎቹ ሁሉ አጫጭር መልሶች ሰጠሁት:: እኔም በተራዬ ስለ እርሱ እና ስለ ቤተ ሰቡ ጤንነት ጠየቅሁት:: ስለ ሥራው ግን አልጠየቅሁትም:: ምን

ብዬ ነው የምጠይቀው? "ሚስዮናዊነት እንዴት ነው?" ብዬ? "ሕዝቡ ደኅና እየተሰበከላችሁ ነው ወይ?" ብዬ? ኧይ፥ እንደዚህ ብዬማ አልጠይቅም:: ሚስ ዮናውያኑ ለበኩ አልሰበኩ፥ ሕዝቡም ተሰበከላቸው አልተሰበከላቸው እኔ ምን ቸገረኝ? ምንስ ያገባኛል?

የሚሰተር ፋርገር መኖሪያ ቤት መጠነኛ፥ ግን ጽዱ የሆነ የጭቃ ቤት ነው:: ከአራቱ ግድግዳዎች አብዛኛው ከፍል በመደርደሪያዎች፥ መደርደሪያዎቹም በመጻሕፍት ተሞልተዋል:: ከሩቁ የሚታዩኝ አንዳንድ መጻሕፍት ትኩረቴን ሳቡት:: ከሚስዮናዊ ቤት ይገኛሉ ብዬ የማልጠብቃቸው ዐይነት ነበሩ - ለም ሳሌ የፒተር ድራከር የማኔጅሜንት መጽሐፍ:: ከመቀመጫዬ ተነሥቼ ወደ መደርደሪያዎቹ ሄድኩ እና መጻሕፍቱን በቅርበት መመልከት ጀመርኩ - የታሪክ፥ የፍልሰፍና፥ የሊትሬቸር፥ የኤኮኖሚክስ፥ የአስተዳደር፥ የሂሣብ፥ የሃይማኖት፥ ወዘተርፈ:: ሚስዮናውያን ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው ውጭ ሌላ መጽ ሐፍ የሚያነቡ መስሎኝ አያውቅም:: "ሚስዮናውያን መጽሐፍ ያነብባሉ ማለት ነው?" አልኩኝ - በሆዴ::

በዚያ ምሽት ወደ ሚስዮናዊው ቤት የሄድኩበትን ምክንያት ሊማንሣት ምቹ ሁኔታ ተጠባበቅሁ:: ምቹ ሁኔታ ግን አልመጣ አለ:: "ስለ የይሖዋ ምስክሮች ልጠይቅህ ነው የመጣሁት" ማለት ከበደኝ:: "አሳፈረኝ" ብል ነው ትክክል የም ሆነው:: እኔን የሚያከል ሰው፥ እንዴት ብሎ ነው አንድን ሚስዮናዊ ስለ ሃይ ማኖት የሚጠይቀው? እርሱ "መስበክ" ሥራው ስለ ሆነ፥ ሊሰብከኝ መጀመሩ መቼም አይቀርም:: ባይሆን ያን ጊዜ የእርሱን ስብከት እስታከኬ፥ የእራሴን ጥያቄ አቀርብለታለሁ ብዬ ነበር ያሰብኩት:: እርሱ ደግሞ እንኳን ሊሰብከኝ፥ "መንፈሳዊ" ሊባል የሚችል ዐይነት ወሬም አላነሣብኝ አለ::

ሻይ እና ኩኪስ ለማቅረብ ካልሆነ በስተቀር፥ ዶሪስ ባለቤቷ እና እኔ ወደ ተቀመጥንበት ሳሎን ብቅ አላለችም:: ከመሸ ወደ ቤታቸው የመጣው ሰው፥ የሆነ ሽክም በልቡ ላይ የከበደው ሰው ሳይሆን እንደማይቀር ጠርጥራ መሆን አለበት:: እንደዚህ ያለው ሰው ከባለቤቷ ጋር የቆይታ ጊዜ እንዲያገኝ ሁለቱን ለብቻቸው ተወቻቸው:: ሰውየው "ኩራት አራቱ" የሆነው "እበሻ" መሆኑን አላወቀችም:: ባለቤቷ ደግሞ እንግዳው ሰው የመጣበትን ጉዳይ እንዲናገር ግፊት ሊያደርግበት አልፈለገም:: ስለዚህም በመካከላችን፥ ፈረንጆቹ እንደሚ

ሉት፥ "ስለ አየሩ ከማውራት" ያለፈ ነገር አልተነሣም። ተሰፋ ቆርጬ፥ የዶሪስን ኩኪስ በልቼ እና ሻይዋን ጠጥቼ፥ "ደኅና አደሩ" ብዬአቸው ወደ ቤቴ ሄድኩ።

ያን ሌሊት ግን በፍጹም መተኛት አልቻልኩም። ከጎኔ ወደ ጀርባዬ፥ ከጀርባዬ ወደ ሌላው ጎኔ፥ ከዚያ ወደ ደረቴ፥ ከዚያ እንደ ገና ወደ ጎኔ፥ ስገለባበጥ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት አለፈ። ፊጽሞ እራሷን ጥላ፥ ከጎኔ የለላም እንቅልፍ የተኛችውን ሚሱቴን ቀናሁባት። "ምነው እንዲህ እንደ አንቺ ብሆን ኖሮ" አልኩ በውስጤ። ውስብስብ ባልሆን ኖሮ ማለቴ ነው። አዎ፥ ው-ስ-ብ-ስ-ብ-ሉ-ብ ብያለሁ። ውሌ እስከሚጠፋ ድረስ ተወለሳስቢአለሁ። ገነት አላዘነችኝ። ከዚህ ጣፋጭ እንቅልፏ እንዳልቀሰቅሳት ፈራሁ። እና ቀስ ብዬ ከጎኗ ተነሣሁ እና በጓሮው በር ወደ ውጭ ወጣሁ።

ሌሊቱ ጨረቃማ መሆን አለ መሆኑ ትዝ አይለኝም። ጨረቃማ፥ ደማቅ ጨረቃማ፥ ሆኖም ቢሆን ኖሮ እኔ ላየው አልችልም ነበር። የፍቅር ምሽት ነው ጨረቃማ ምሽት። የፍቅር ምሽት ከውጭ ጨረቃማም ባይሆን ከውስጥ ጨረቃማ ነው - ሙሉ ጨረቃማ! ያ ምሽት ግን ለእኔ የፍቅር ምሽት አልነበረም። ውስጤ ጨልሟል። ድ-ቅ-ድ-ቅ ብሷል። ከጨለማው ጫፍ ደርሻለሁ። ከዚያ ወዲያ ያለውን ማን ያውቃል? በግቢው ውስጥ ወደዚያ እና ወደዚህ ተመላለስኩ። ቆምኩ። እንጋጠጥኩ። አቀረቀርኩ። አለ መቀመጤን ብቻ ነው በትክክል የማስታውሰው። በመጨረሻም በግቢው ውስጥ ወደ ነበረው የመታጠቢያ ከፍል ገባሁ። መብራቱን ሳበራው ከፈት ለፊቴ ባለው የግድግዳ መስተዋት ውስጥ አራሴን አየሁት።

"ምስኪን በቀለ!" አልኩት በመስተዋቱ ውስጥ በትዝብት ዐይኖች መልሶ የሚያየኝን ሰው። "ከሰዎች ጋር በመከራከር ዕድሜህን ፈጀኸው ... ከእንተ ይልቅ በድንጋይ ... በእንጨት ... የሚያምን ሰው ይሻላል!" አልኩት። ሳናግረው ላለሁ፥ የቀኝ እጇን የሌባ ጣትም የቀሰርክብት ይመስለኛል። በትዝብት ዐይኖች ከላይ አስከ ታች እያየሁት እያለሁ፥ ድንገት መብራቱን አጠፋሁ እና ተንበረከከሁ። አሁንም አሰቤ፥ ልንበርከክ እና ልጸልይ ብዬ፥ ያደረግሁት ነገር አይደለም። መብራቱን ያጠፋት የእኔ እጆች፥ የተንበረከኩትም የእኔ ጉልበቶች ይሁኑ እንጂ፥ የሆነ ነገር በቁጥጥሩ ሥር አድርጎኝ ነበር ለማለት እችላለሁ። በቁጥጥሩ ሥር አድርጎኝ የነበረው ያ ነገር ነው፥ ያደረግኹትን ሁሉ ያስደረገኝ። ቆይቼ እንደ ተረዳሁት፥ ያን ሌሊት የታጠፉት ጉልበቶቼ ብቻ አልነበሩም። ያን

ሌሊት የታጠፈው፥ በዋነኛነት፥ ውስጤ ነበረ። ያን ሌሊት የተሰበረው እኔነቴ ነበረ። ያን ሌሊት፥ በዚያ ዐይነት፥ እጁን ሊለጥ ፈቃደኛ የሆነው ፈቃዴ ነበረ።

አሁንም፥ በሰአለቴ ጊዜ ጠርቼው እንደ ነበረው፥ ልከ እንደዚያው ነበር የጠራሁት -

> "እግዚአብሔር የምትባል ካለህ! ... እኔ ደከመኝ! ... የይሖዋ ምስክር ልሆን ነው! ... ላይ ... መንገዱ እሱ አይደለም ... መንገዱ ሌላ ነው ... የምትለኝ ከሆነ ... ላሳየኝ!"

አልኩት። ድምፄን አለምቼ ነው እንደዚያ ያልኩት። ጮክ ብዬም ሳይሆን አይ ሳርም። በቀኝ እጄ፥ የተንበረከከሁበትን መሬት በጥፊ በማጮል ጭምር ነበር "ላሳየኝ!" ያልኩት። ይህችኑ ብቻ ተናግሬ፥ ከተንበረከከሁበት ተነሣሁ እና እየተፈናጠርኩ ወደ መኝታዬ ሄድኩ። ጸሎት መጸለዬን አሁንም አላወቅሁም። መጣራቴን እንጂ፥ ጥሪዬን የሚሰማ አንዳለ አላወቅሁም። ያደረግሁትን ሁሉ የማደርገው በማሰተዋል ሳይሆን፥ እንዲያው በደመ ነፍስ ዐይነት ነበር። ጎኔ አልጋውን ከመንካቱ፥ ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰደኝ። ገነት የሆነውን ሁሉ አላወቀችም።

በማግሥቱ ዕሑድ ረፈድ አድርጎን ነው ከእንቅልፋችን የተነሣነው። ተጣጥበን፥ ቁርስ እየበላን እያለን፥ "እስኪ ዛሬ ወደ ሚሰዮን ጣቢያ እንሂድ" አለችኝ - ገነት። ለእርሷ ገና አልነገርኳትም እንጂ፥ እኔ ትናንትና ማታ እዚያ ነበርኩ። አሁንም እሱን ሳልነግራት፥ ዝም ብዬ ብቻ "ለምን?" አልኳት። እርሷም ዝም ብላ ብቻ "መዝሙር እንሰማለን" አለችኝ። በዚያ ዘመን "የብሥራት ወንጌል ሬድዮ ጣቢያ" የሚባል ነበረ። ፕሮግራሞቹ ሁሉ ከ"ኢትዮጵያ ሬድዮ ጣቢያ"ው ይልቅ ተመራጭ ነበሩ። መዝሙርም ያዘምራሉ። ብዙ ሰው - እኛም እንለማቸው ነበር። "እሺ" አልኳት እና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተያይዘን ወደ አለታ ወንዶው የኤስ. አይ. ኤም. ግቢ ሄድን።

አቶ ገነነ ሃሜሶ እየሰበከ ነበር። አርፍደን ነው የደረስነው ማለት ነው። ሰዓታቸውንም አናውቀውም። አቶ ገነነ እየሰበከ ያሰው በሲዳምኛ ቋንቋ ነው። እኛ ደግሞ ሲዳምኛ አንለማም። አሱም ቢሆን ከአምስት አድስት ደቂቃ በኋላ አለቀ። አቶ ገነነ ሲጨርሰ በአማርኛ አንድ መዝሙር ዘመረ። በጊዜው የተያዘ ለኝ የመዝሙሩ አዝማች ብቻ ነበር፦

ዘምራለሁ፥ ዘምራለሁ፥ ለየሱስ ለሞተልኝ፤
ዘምራለሁ፥ ዘምራለሁ፥ እስከ ዘለዓለሙ።።

እቶ ገነነ ሲቀመጥ ሚሲተር ፋርገር ተነሣ እና የሆነ የሆነ ነገር በእማርኛም በኢንግሊዝኛም ተናገረ። ያንን ያደረገው ገነት እና እኔ አንዳች ነገር ላንለማ እንዳንወጣ በማሰብ እንደ ሆነ ገብቶኛል። ሆኖም እኔ በበኩሌ በዚያች ዕሑድ ምንም ነገር አልሰማሁም። ከአዳራሹ ወጥተን፥ ከበሩ ላይ ቆመን ሰላምታ ስንለዋወጥ፥ ሚሰስ ፋርገር ገነትን እና እኔን "ለምን ቤታችንን አናሳያችሁም?" አሉችን። ተያይዘን ባሰፈው ምሽት እኔ ወደ አመሸሁበት ቤታቸው ሄድን።

እንደዚህ ባለው ጊዜ ሰዎች የሚነጋገሯቸውን "ተራ ንግግሮች" ከተለዋወጥን በኋላ፥ ዶሪስ እና ገነት ወደ ወጥ ቤት ገቡ። እኔ እና ሚስተር ፋርገር ሳሎን ቀረን። ልቀመጥበት ከነበረው ወንበር ላይ አንድ መጽሐፍ ቀድሞኝ ተቀምጦ አል። የሃል ሊንድሴይ "THERE IS A NEW WORLD COMING!" ነው። አነሣሁት እና ላነብበው ጀመርኩ። ዶሪስ እና ገነት ሻይ እና ኩኪስ ይዘው ሲመጡ፥ ሳሎኑ በጸጥታ ተውጧል።

"አቶ በቀለ፥ መጽሐፍ ማንበብ ትወዳለህ ወይ?" አለችኝ፥ ዶሪስ።

"አዎ፥ በጣም እወዳለሁ" አልኳት።

"የያዝከው መጽሐፍ ላለፈው የትንሣኤ በዓል በስጦታ ከውጭ የተላከልኝ ነው። ውሰደው እና አንብበው። እኔ ከአንተ በኋላ አነብበዋለሁ" አለችኝ። "አሁን ማንበቡን ተወት አድርግ እና ከእኛ ጋር ሁን" ማለቷ እንደ ሆነ ገብቶኛል። መጽሐፍ ከያዝኩ በሰዎች መካከል መሆኔን እረሳለሁ። አንድ ጊዜ ከገነት ጋር ምሳ ሰንበላ፥ በቅርቤ የነበረ መጽሐፍ አንሥቼ ያዝኩ እና ምሳውን እና በዙሪያዬ ያለውን ሁሉ አረሳሁት። በመብረቅ ፍጥነት፥ ገነት መጽሐፉን ከእጄ ነጥቃ ወዲያ ማዶ አሽቀነጠረችው። ከግድግዳው ጋር አላተመችው። ደነገጥኩ። መጽሐፍ አንዳንዴ እንደ ጣውንትም ሊታይ ይችላል ይመስለኛል። በሚሰተር ፋርገርም ቤት ይህ መጥፎ አመሌ ተንጸባረቀ። ምን ይሻለኛል?

የእነ ሚሰተር ፋርገር ቤት ቆይታችን ተጠናቆ ወደ ቤታችን እንደ ተመለስን፥ ምሳችንን በላን እና የሚሰሰ ፋርገርን መጽሐፍ ይዤ ቁጭ አልኩ። "THERE IS A NEW WORLD COMING!" የዮሐንስ ራእይን መጽሐፍ የሚያስተነትን የጥናት መጽሐፍ ነው።

እነሆ፤ በደመና ይመጣል፤ የወጉት እንኳ ሳይቀሩ፥ ዐይን ሁሉ ያየዋል፤ የምድርም ሕዝቦች ሁሉ ከእርሱ የተነሣ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎ! ይህ ሁሉ ይሆናል፤ አሜን (ራእ. 1፥7)

የሚለውን ክፍል ሲያብራራው፥ ኢየሱስ ዳግመኛ የሚመጣው በአካል እንደ ሆነ እና ዓለሙም ሁሉ እያየው እንደ ሆነ፥ ያን ጊዜ ላለመኑበት ሰዎች የታላቅ ዋይታ ጊዜ እንደሚሆን ይናገራል። ከአዲሰ ኪዳን ውስጥ ሌሎች ጥቅሶችንም በማስረጃነት ይጠቅሳል። ትዝ የሚለኝ "... ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያያችሁት ኢየሱስ፥ ልክ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለሳል" የሚለው ነው (ሐዋ. 1፥11)። የይሖዋ ምስክሮችም ቢሆኑ፥ "መጥቷል" ነው እንጂ፥ "እየታየ ነው ዳግመኛ የመጣው" አላሉም። እየታየ ካል መጣ፥ ዳግመኛ አልመጣም ማለት ነው። ነገር ግን በመጀመሪያ እነዚህን ጥቅሶች ለራሴ ማንበብ አለብኝ።

ከጥቂት ወራት በፊት፥ የመጀመሪያውን የራሴ የሆነ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የሰጠኝ "ፓዮኒር" ግርማይ ነው። ጥቅሰ ማውጣቱን አላውቅበትም። በማውጫው እየታገዝኩ፥ ከብዙ ፍለጋ በኋላ ጥቅሶቹን አገኘኋቸው እና ለአራሴ አነበብኳቸው። በትክክል ሃል ሊንድሴይ እንደሚለው ነው የሚሉት። ከዶሪስ መጽሐፍ ጋር ቢበዛ ለአንድ ሰዓት ቆይቼ ቢሆን ነው፥ "የይሖዋ ምስክር አልሆንም" ብዬ ሰወሰን። ምነው ከሃያ አራት ሰዓት በፊት እነዚህን ጥቅሶች ዐውቄአቸው ቢሆን ኖሮ! ምናልባት የትናንትናው ከርከራችን ሌላ መልክ ይኖረው ነበር ይሆናል። ተቆጨኹ። ለማታው "ጸሎቴ"፥ መልሱ እንዲህ በፍጥነት መምጣቱን ለማሰተዋል ግን፥ አሁንም ገና ነበርኩ።

ዶሪሰ እና ብራያን ፋርገር

ከርሰቶሰ ወደ ሕይወቴ ሲመጣ፥ ይዟቸው የመጣ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወቴ ቁልፍ እና ወሳኝ የሆነ ሚና የተጫወቱ ሰዎች ናቸው። ምናልባትም ያንን ቁልፍ እና ወሳኝ የሆነ ሚና ሊጫወት የሚችል፥ ከእነዚህ ሰዎች በሰተቀር፥ ሌላ ማንም ሰው አልነበረም ሊሆን ይችላል። የእግዜሩን አላውቅም፥ በእኔ እይታ ግን፥ እንደዚህ ካሉት ሰዎች መካከል የመጀመሪያዋ ገነት ስትሆን፥ ሁለተኛው ሚሰተር ፋርገር ነው። የገነትን በሌላ ርእሰ እመለስ በታለሁ።

ሚስተር ፋርገር እኔን ካገለገለባቸው እገልግሎቶች "ትልቁ" የምለው፥ እኔን ከመንፈሳዊ መጻሕፍት ጋር ማስተዋወቁን ነው። ሚስተር ፋርገር ያዋሰኝ የመጀመሪያው መጽሐፍ የስመ ጥሩው APOLOGIST፥ የ ሲ. ኤስ. ሉዊስ "ግለ ታሪክ" የሆነው "SURPRISED BY JOY" ነው። በመጽሐፉ መግቢያ ላይ፥ ጸሐፊው እንዲህ ይላል፦ "ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በከፊል ከከሃዲነት ወደ ክርስቲያንነት እንዴት እንደ ተሸጋገርኩ እንድናገር የሚቀርቡልኝን ጥያቄዎች ለመመለስ ሲሆን ... መጽሐፉ ሙሉ ግለ ታሪክ ሳይሆን፥ ዓላማው እንዴት እንደ ተሰወጥኩ መተረክ ነው።" ልክ አንደዚህች፥ እንደ እኔው "ትውስታ" ማለት ነው። እና ለጉድ ተረከው።

የመጽሐፉን 14ኛ ምዕራፍ "ቼክ ሜት" ብሎ ስይሞታል። በቼዝ ጨዋታ "ቼክ ሜት" የሚባለው፥ ከተጫዋቾቹ እንደኛው "ንጉሡን" ማዳን በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ሲወድቅ ነው። እዚያ ደረጃ ላይ ሲደረስ፥ ንጉሡ ይማረካል። ንጉሡ ሲማረክ፥ ጨዋታው ያልቃል። እርሱን ወደ ክርስቲያንነት ለማምጣት፥ እግዚአብሔር ልክ እንደ እሸናፊው ቼዝ ተጫዋች እንደ ሆነበት ነው ሉዊስ በ14ኛው ምዕራፍ ውስጥ የሚናገረው። መላወሻ፥ መፈናፈኛ አሳጣው። "ቼክ ሜት!" ሲለው የጀመረው፥ "ENGLISH LANGUAGE AND LITERATURE" የሚባል የዩኒቨርሲቲ ኮርስ እየወሰደ በነበረበት፥ በ1922 ነበር። በክርስቶስ እምላከነት እና አዳኝነት ያመነው ግን ስፕቴምበር 28 ቀን 1931 ነው። እንዲያው በደፈናው "በፈጣሪ እማኝ" (THEIST) ብቻ ሆኖ ለመቅረት፥ ለዘጠኝ ዓመታት ነበር የተሸሉከለከው።

ስለዚህም ከራሱ ተሞክሮ፥ የከሃዲዎቹን የመከራከሪያ ነጥቦች በሙሉ ያውቃቸዋል። እና እንድ በእንድ እያነሣቸው፥ በፊቴ አደባያቸው። ልክ ገበሬ እህል ሲወቃ፥ ውቂያውን በመንሹ ሰንፋስ እንደሚስጠው እንደዚሁ ነበር ያደረጋቸው። ሰበብ እስባቦቼን በሙሉ ማለት አችሳሰሁ፥ በእውድማ ላይ እንደሚ ወቃ እህል ወቃቸው። አምነትን በተመለከተ፥ ከየት ተነሥቼ የት እንደ ደረስኩ ሚስተር ፋርገር የሚያውቀው ነገር የለም። በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ካልሆነ በስተቀር፥ በምንም ዐይነት እንደዚህ ያለ መጽሐፍ ሊያውሰኝ አይችልም። ወይስ በዚያች ምሽት ጭውውታችን ውስጥ፥ ሳይታወቀኝ ትንሽ ፍንጭ ስጥቼው ነበር ይሆን?

ሚስተር ፋርገር ያዋሰኝ ሁለተኛው መጽሐፍ፥ የዚሁ የሲ. ኤስ. ሉዊስ "MERE CHRISTIANITY" ነው። ታዋቂው ጂኔቲሲስት እና የHUMAN GENOME PROJECT መሪ የነበረው፥ ዶክተር ፍራንሲስ ኮሊንስ፥ "THE LANGUAGE OF GOD" በተባለው መጽሐፉ ውስጥ ስለ "MERE CHRISTIANITY" እንዲህ ብሏል፦ "በዚህ ዝነኛ (legendary) የኦክስፎርድ ምሑር የተሠነዘሩትን ምሑራዊ (intellectual) ሙግቶች በስፋታቸው እና በጥልቀታቸው ስማብ ላላት እየታገልኩ፥ የመጽሐፉን ገጾች ማገላበጥ በጀመርኩባቸው በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ፥ የእምነትን ኢተአማኒነት ለማስረዳት ያዋቀርኳቸውን የአራሴን መከላከያዎች ሁሉ የልጅ ጨዋታ ሆነው አገኘኋቸው ... ሉዊስ ተቃውሞቼን፥ እንዳንዴ እንዲያውም ገና በቅጡ ቅርጽ ያልሰጠኋቸውንም ሁሉ፥ ያውቃቸዋል።"[2]

ሚስተር ፋርገር ካስተዋወቀኝ ጸሐፍት መካከል የ"ኮ ABRI FELLOWSHIP"አቹ፥ ፍራንሲስ ሼፈር እና እዝ ጊነስ ይገኙባቸዋል። እነዚህም፥ የሲ. ኤስ. ሉዊስን ያህልም ባይሆን፥ በጣም የታወቁ እፖሎጂስቶች ናቸው። በታሪክ ስለ ታወቁ እና ስለ ተፈጸሙ ትንቢቶች የሚናገሩ እንድ ሁለት መጻሕፍትም አስነብቦኛል። እነዚህ መጻሕፍት በሕይወቴ የሠሩት ትልቅ ሥራ፥ መጽሐፍ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ እንዳምን ማድረጋቸው ነው። በጌታ በኢየሱስ ከርስቶስ ከማመኔ በፊት ነበር፥ መጽሐፍ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ያመንኩት።

ካመንኩ በኋላ ደግሞ፥ ሚስተር ፋርገር ለመንፈሳዊ ሕይወቴ ዕድገት በሚጠ ቅሙኝ ሌሎች ዐይነት መጻሕፍት አጥሰቅልቆኛል። ከብዛታቸው የተነሣ፥ አነዚህን መዘርዘር አልችልም። እንዲያው ባጭሩ፥ ከአርተር ፒንክ GLEANINGS፥ ከጂ. ካምፕቤል ሞርጋን ድንቅ መጻሕፍት፥ ኪጀን ስቶት BASIC CHRISTIANITY፥ ወዘተርፈ ጋር ያስተዋወቀኝ ሚስተር ፋርገር ነው። እንደ THE NEW BIBLE DICTIONARY, THE NEW TOPICAL TEXT BOOK, CRUDEN'S CONCORDANCE እና THE NEW SCOFIELD REFERENCE BIBLE ያሉት፥ መጽሐፍ ቅዱሱን በግል ስማጥናት የሚረዱ መጻሕፍት፥ እጄ እንዲገቡ ያደረገውም ሚስተር ፋርገር ነው።

ከሚስተር ፋርገር ጋር የነበረን ግንኙነት እርሱ እና እኔ አለታ ወንዶ እብረን በነበርንበት ጊዜ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። እብላጫው ግንኙነታችን የነበረው

እንዲያውም አለታ ወንዶን ከለቀቅሁ በኋላ ነበር ማለት ይቻላል። እኔ ይርጋ ዓለም፥ ዲላ እና አዲስ አበባ፥ እርሱ ደግሞ አለታ ወንዶ፥ ጅማ እና አዲስ አበባ በነበርንባቸው ዓመታትም ግንኙነታችን አልተቋረጠም ነበር። ከእኔ ድካም የተነሣ፥ ምናልባትም ደግሞ የአግዚአብሔር ፈቃድ ስላልነበረ፥ አልዘለቀም አንጂ፥ ብራሴልስ (ቤልጅዬም) በሚገኘው INTERNATIONAL CORRESPONDENCE INSTITUTE የርቀት ትምህርት አለጀምሮኝም ነበር። እርሱ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የተቀዋሙ ተጠሪ ነበረ። የመጀመሪያዎቹ ተመዝጋቢ ተማሪዎች ደግሞ ሚቹ ሺመልስ ወዳጆ እና እኔ የነበርን ይመስለኛል።

ተከትሷት ገባ? ወይስ አስከትሷት?

ከርሰቶለ ወደ ሕይወቴ ሲመጣ ይዟቸው ከመጣ፥ በመንፈሳዊ ሕይወቴ ቁልፍ እና ወሳኝ ሚና ከተጫወቱ ሰዎች መካከል፥ የመጀመሪያዋ ገነት ናት ብያለሁ። ይህንን አባባሌን ለማብራራት፥ ትከሰኛው ጊዜ እና ቦታ፥ ይኸ አሁን የደረስኩበት ይመስለኛል። ከላይ "ተራከቢዊ ተዓቅቦ" በሚል ርእሰ ሥር ለተናገርኩት ነገር፥ አንባቢ ምን ትርጉም እንደሚሰጠው አላውቅም። አንዳንዶች "የሥነ ልቦና ትንታኔ አባት" (FATHER OF PSYCHOANALYSIS) በመባል የሚታወቀውን የዚግመንድ ፍሮይድን ፊለማ ይከተሉ ይሆናል።

ፍሮይድ ከሰው ዘር ሁሉ ታሪክ በለተ ጀርባ "ያልነቃ" (SUBCONSCIOUS) እና አርሱ "ወሲባዊ" የሚለው አእምሮ እለ ይላል። እንደ ፍሮይድ፥ የዓለምን ታሪክ እያሽከረከረ ያለው ወሲብ ነው። የእርሱን ፊለማ የሚከተሉ ሰዎች አኔንም፥ "ገና 30 ዓመት ሳይሞላህ፥ ወሲብ ማድረግ ባለመቻልህ ወደ መጨነቅ፥ ጤናም ወደ ማጣት፥ በመጨረሻም ጻሎት እና ስእለትም ወደ ማድረግ መድረስህ፥ የፍሮይድን ትንታኔ ትከከለኛነት ያረጋግጣል" ሊሉኝ ይችሉ ይሆናል። እኔ ዕውቀቱ ለለሌለኝ፥ የፍሮይድን ትንታኔ ለማጽደቅም ሆነ ለመኮነን አልቃጣም። ለእኔው ጉዳይ እኔ የምስጠው ትንታኔ ግን፥ ፍሮይድም ሆነ ደቀ መዛሙርቱ ሊለጡ ከሚችሉት ትንታኔ ፈጽሞ የተለየ ነው።

ከገነት ጋር በተያያዘ፥ እራሴን የጠየቅኋቸው ጥያቄዎች ብዙ ናቸው። አሁን ለደረስንበት ጊዜ እና ቦታ ተገቢ ከሆኑት ጥያቄዎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፦ ከገነት በፊት ሌላ ሴት እንዳላውቅ የሆንኩት ለምንድነው? ከእርሰዋ በፊት ሌላ ሴት እንዳላውቅ በሆንኩባቸው ሂደቶች ውስጥ የእግዚአብሔር እጅ

ይኖርበት ይሆን ወይ? የዚህ ጥያቄ መልስ "አዎን" ከሆነ፥ ለምን? የእግዚአብሔር እጅ ያልነበረበት ከሆነ ደግሞ፥ ተራከቢዊው ተዓቅቦ ያንን ለእለት እስከ ምሳልበት ጊዜ ድረስ ብቻ ለምን አብሮኝ ቆየ? ያንን ለእለት ባልሳል ኖሮ፥ ችግሩን የማለወግድበት ሌላ መንገድ አይኖረኝም ነበር ማለት ነው?

የእነዚህን ጥያቄዎቼን መልሶች ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱሴን ብዙ እገላብጫለሁ። ጸልያለሁ። በብዙም አስቤአለሁ። እና የደረስኩበት መልስ፥ ገነት በእኔ ሕይወት ውስጥ "ማለስለስ እና ማንኳኳት" ላልኩት ምዕራፍ መቋጫ እና ከዚያ ለሚቀጥለውም የሕይወቴ ምዕራፍ መከፈቻ ነበረች የሚል ነው። በሲ. ኤስ. ሉዊስ ቋንቋ፥ ገነት ለእኔ የአግዚአብሔር "ቼክ ሜት" ነበረች የሚል ነው። በምዕራፍ አራት ውስጥ ባየነው የ"ማለስለስ እና ማንኳኳት" ሂደት ሁሉ ውስጥ፥ በእልኸኛነቴ እንደምቀጥል እግዚአብሔር አስቀድሞ ያውቅ ነበር። ስለዚህም ይህችን "መጫወቻውን" (ካርዱን እንዲሉ) ለዚህ ጊዜ፥ ማለትም ለመጨረሻው ዙር፥ አቆይቷት ነበር። በዙሩ መጨረሻ ላይ በግሩም ሁኔታ ተጠቀመባት እና "በመዘረር" አሸነፈኝ።

ከሌሊቶች በአንዱ፥ ዓሣ እጥማኝ ጴጥሮስ ዓሣ አልጠመድልህ አለው። የእጁን መዳፍ ያህል አሳምሮ የሚያውቀውን የገሊላን ባሕር ጓዳ ጎድጓዳ ሁሉ አስሶ፥ በብዙ ዓመታት ተሞክሮው ያካበተውን ዘዴውን ሁሉ ጨርሶ፥ ዓሣ ማጥመድ አቃተው። ሌሊቱ ነግቶ፥ ጥረቱም አብቅቶ፥ ታንኳውን ምድር ላይ አውጥቶ፥ መረቡን እያጠበ እያለ ጌታ በተለይ ወደ እርሱ ታንኳ መጣ። ከምድር ፈቀቅ እንዲያደርጋት ለመነው እና በታንኳው ላይ ተቀምጦ ሕዝቡን አስተማረ። ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ፥ ጴጥሮስ ታንኳውን ወደ ጥልቁ ፈቀቅ እንዲያደርጋት እና ዓሣ ለመያዝ መረቡን እንዲጥል አዘዘው። መረቡ እስኪቀደድ ድረስ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዘ። ከዚያም ታንኳውን ወደ ምድር አድርሶ እና ሁሉን ትቶ ተከተለው (ሉቃ. 5፥1-11)። ጌታ ወደ ጴጥሮስ ሕይወት የገባው ዓሣውን ተከትሎ ነው አለከትሎ?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሐናን ማሕፀን "ዘግቶት" ነበር ይላል (1ኛ ሳሙኤል 1፥5)። የሐና ማሕፀን የተከፈተው፥ ሐና ያንን አስደናቂ ስእለት በተሳለች ጊዜ ነው፦ "... የአገልጋይህን መዋረድ ተመልከተህ ብታሰበኝና አገልጋይህን ሳትረሳት ወንድ ልጅ ብትሰጣት፥ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ለእግዚአብሔር አስጠዋለሁ ..." (ቁጥር 11)። እንደ ድፍረት አይቆጠርብኝ እንጂ፥ ሐና ያንን

ስለለት እለከ ተሳለችበት ጊዜ ድረስ፥ እግዚአብሔር እርስዋን በመሐንነት የሚያለጨንቅበት የተለየ ምክንያት የነበረውም ይመለለኛል::

የዔሊ ልጆች ምናምንቴዎች እና እግዚአብሔርን የማይፈሩ ነበሩ (2፥12):: ዔሊም እጅግ እርጅቶ ነበር (2፥22):: ዘመኑ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ የሆነበት እና ራእይም የማይታይበት ነበር (3፥1):: እንደዚህ ባለ ዘመን፥ ተተኪው ትውልድ ምን ተስፋ አለው? ማን፥ እንዴት አድርጎ ያሳድገዋል? ስለዚህም እግዚአብሔር እራሱ፥ ከታች ጀምሮ እያስተማረ እና እየኮተኮተ የሚያሳድገው፥ ሕፃን ልጅ የምትሰጠው እናት እየፈለገ የነበረ ይመለለኛል:: ሐና እግዚአብሔር የሚለጣትን ወንድ ልጅ መልሳ ለእግዚአብሔር ልትለጠው ተሳለች:: እግዚአብሔርም "በአንድ እፍ" አላት እና ወዲያው ሳሙኤልን ሰጣት:: እርሷም ለሕፃኑ ልጇ ሳትሳሳ ስእለቷን ፈጸመች (1፥21-28):: እግዚአብሔር ወደ ሐና ሕይወት የገባው መካንነቷን ተከትሎ ነው እስከትሎ?

እንድ ሌላ ታሪክ ልጨምር:: "... የጌራራ ንጉሥ አቢሜሌክ መልእክተኛ ልኮ ሣራን ወሰዳት:: እግዚአብሔርም በአንድ ሌሊት ወደ አቢሜሌክ መጥቶ 'እነሆ፤ በወለድሃት ሴት ምክንያት ምውት ነህ፤ እርሷ ባለ ባል ናት' አለው:: አቢሜሌክም ገና አልደረሰባትም ነበርና ... 'አንተ ይህን ያደረግኸው በቅን ልቦና መሆኑን ዐውቄአለሁ፤ በእኔም ላይ ኃጢአት እንዳትሠራ የጠበቅሁህና እንዳትነካትም ያደረግሁት ለዚሁ ነው' አለው (ዘፍ. 20፥1-7 ሥርዝ የተ ጨመረ):: ከዐውዱ መረዳት እንደሚቻለው፥ ሣራ በአቢሜሌክ ቤተ መንግ ሥት ቢያንስ ጥቂት ቀናት አለቆጥራለች:: አቢሜሌክ ወድዷት ነው ሣራን ያስ ወሰዳት:: ግን ገና አልደረሰባትም:: ለምን? ሊነካት እንዳይችል ተደርጎ ነበር - "ምውት" ሆኖ ነበር::

እግዚአብሔር በዚያን ዘመን በጴጥሮስ፥ በሐና እና በአቢሜሌክ እንደዚያ ካደረገ፥ በዚህ ዘመን ደግሞ በበቀለ እንደዚህ እንዳያደርግ ምን ይከለከለዋል? እና ማን ነው በመጀመሪያ ወደ ሕይወቴ የገባው? ገነት? ወይስ ጌታ? መጨረሻ ላይ ከሆነው ነገር ቅደም ተከተል አንፃር ብቻ ከታየ፥ ቀድማ የገባችው ገነት ናት:: እሱ ግን፥ የታሪኩ መጨረሻ እንጂ የታሪኩ መጀመሪያ አይደለም:: ታሪኩ ከጀመረ ቆይቷል:: በጣም ለረዥም ዘመን ወደ ኋላ ይሄዳል:: በጌታ እና በገነት መካከል፥ እርስዋ በሌለችበት እና ያለ እርሷም ዕውቀት የተደረገ የሆነ ስልታዊ ቅንጅት (STRATEGIC ALLIANCE) ነበረ - ልኬን ለማሳያ፥

ፈቃዴን ለመርቻ፥ በሬን ለማስከፈቻ:: ጉልበቴን ለማስበርከክ፤ ንጉሤን (እኔነቴን) ለመማረክ::

ይህም ሁሉ ሆኖ?

ሰው ሲ. ኤስ. ሉዊስን፥ ፍራንሲስ ሼፈርን፥ አዝ ጊነስን፥ ወዘተርፈ ካነበበ በኋላ፥ እነዚህንም መጻሕፍት እጅግ ከወደዳቸው በኋላ፥ በጌታ በኢየሱስ ክርስ ቶስ ለማመን ጊዜ ሊወለድበት ይችላል? ሰው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ከተረዳ እና ካመነ በኋላ፥ ሕይወቱን ለጌታ ከመሰጠት ሊዘገይ ይችላል? ሰው በሰባት ወራት ልዩነት ውስጥ ሁለት ጸሎቶችን ጸልዮ እና ሁለቱም ጸሎቶቹ በድንቅ ሁኔታ ተመልሰውለት፥ ጸሎት መጸለዩንም ሆነ የጸሎቱን መልስ መቀበሉን ፈጽሞ ሊረሳ ይችላል? ይገርማችሁ ይሆናል፤ እኔ ግን እንደዚያ ነበር የሆንኩት::

ይህችን ምዕራፍ ለመጻፍ ቅድመ ዝግጅት በማደርግበት ጊዜ፥ ካናዳ የሚኖረ ውን ሚስተር ፋርገርን ሁለት ጥያቄዎችን በኢ-ሜይል ጠየቅሁት:: አንደኛ "እንተ ወደ እለታ ወንዶ የመጣኸው መቼ ነበር?" ሁለተኛ "እንተ በዚያን ጊዜ የዕለት ሁኔታዎችን የምትጽፍበት ማስታወሻ (DIARY) ሳይኖርህ አይቀርም እና ለመጀመሪያ ወደ ቤትህ የመጣህበት ቅዳሜ ምሽት መቼ ነበር?" ሚስተር ፋርገር በማግሥቱ መለሰልኝ:: ከቀድሞ ጀምሮ፥ የሆነውን ሁሉ ለልጆቻቸው እና ለልጅ ልጆቻቸው ለማቆየት በሚል ዓላማ፥ የዕለት ሳይሆን "የሳምንት ሁኔታ" ይጽፉ እንደ ነበረ ገለጸልኝ:: እነዚያ ጽሑፎች እሁን ተሰባስበው ብዙ ቅጾች እንደ ወጣቸው እና እንደ ተጠረዙም ነገረኝ::

በቅጽ 3 ገጽ 132 ላይ፥ እንደ ጎርነሳውያኑ አቆጣጠር በ1973 በኢትዮጵያው አዲስ ዓመት የመጀመሪያ ቀን እለታ ወንዶ እንደ ገቡ ተመዝግቧል:: መስከረም 1 ቀን 1966 ዓ.ም. ማለት ነው:: አሁንም በቅጽ 3 በገጽ 134 ላይ "የባንኩ ቮርንጫፍ ሥራ እስኪያጅ ቅዳሜ ሰፕቴምበር 29 ቀን 1973 ምሽት ላይ ወደ ቢታችን መጣ" ተብሎ ተጽፏል:: ይኸ ደግሞ በዚያው ዓመት መስከረም 19 ወይም 18 ማለት ነው:: በገጽ 133 ላይ ደግሞ "የአንተ እና የገነት ቆንጆ ፎቶግራፍ አለ" አለኝ:: በዚያን ጊዜ እንደዚህ ያሉ ማስታወሻዎችን የመያዝ ልምድ ስላልነበረኝ፥ እነዚህ ለእኔ በጣም ጠቃሚ መረጃዎች ነበሩ:: እኔ ነገሩ ከሆነ ከ37 ዓመታት በኋላ ነው እያለታወስኩ የምጽፈው:: እርሱ ግን ነገሩ በሆነ ቢረዝም በአንድ ሳምንት ዕድሜ ውስጥ ነው ጽፎ ያስቀመጠው::

እነዚህ መረጃዎች፥ ከሚስተር ፋርገር ጋር የተገናኘነው በመለኮታዊ ቀጠሮ ነው የሚለውን እምነቴን የበለጠ አጠናከረውልኛል። እኔ "መጨረሻዬ" ላይ በደረስኩበት በዚያ ምሽት፥ ሚስተር ፋርገር በአለታ ወንዶ ገና ሦስት ሳምንታት እንኳን በቅጡ አልሞላውም ነበር። እግዚአብሔር በቀጥታ ለእኔ ሲል በዚያን ጊዜ እንደ ላከው ነው የምረዳው። እግዚአብሔር በአንዲት ግራ የተጋቦች፥ ገናም የበለጠ ግራ ልትጋባ ባለች፥ ነፍስ ዙሪያ የመጨረሻውን ከበባውን እያደረገ እንደ ነበረ ነው የማስተውለው።

> በምድረ በዳ በጥማት፥
> የነፋስ ጩኸትም በሞላበት ውድማ አገኘው፤
> ከበበው፥ ተጠነቀቀለትም፤
> እንደ ዐይኑ ብሌን ጠበቀው።
> ንስር ጫጩቶቹን እንደሚያወጣ፥
> በእነርሱም ላይ እንደሚሰፍፍ
> ክንፎቹን ዘርግቶ ወሰዳቸው፥
> በክንፎቹም አዘላቸው።
> እግዚአብሔር ብቻውን መራው፤
> ከእርሱም ጋር ሌላ አምላክ አልነበረም።

ተብሎ እንደ ተጻፈው ማለት ነው (ዘዳ. 32፥10-12)።

እርግጥ፥ በዚህ ወቅት ለማመን የዘገየሁት ለማመን ካለመፈለግ የተነሣ አልነበረም። እንደ ሰው ሳየው፥ ለመዘግየቴ ዋነኛው ምክንያት፥ ማድረግ ያለብኝን አንድ፥ ሁለት፥ ብሎ የሚያሰረዳኝ ሰው በአጠገቤ ስላልነበረ ይሆናል። ሚስተር ፋርገር ፈጽሞ ስብከኝ አያውቅም። እግዚአብሔር ቀጠሮ የያዘልኝ ሊሰብክኝ ከማይፈልግ ሰው ጋር ከሆነ፥ ወደ አራሱ ሊያመጣኝ የፈለገበት መንገድ፥ የሰብ ከቱ መንገድ ባይሆን ይሆናል። ገነት እና እኔ በዚያች ዕሑድ ወደ እነ ሚስተር ፋርገር ቤተ ክርስቲያን የሄድን ቢሆንም እንኳን፥ ያ የመጀመሪያችን እና የመጨረሻችንም ነበር።

መስከረም 19 ወይም 18 ቀን 1966 ዓ.ም. ከሚስተር ፋርገር ጋር ተገናኘሁ። በማግሥቱ ዕሑድ የሃል ሊንድሴይን መጽሐፍ ማንበብ ጀመርኩ። መጽሐፉን አንብቤ ሳልጨርስ፥ የይሖዋ ምስክር ላለመሆን ወሰንኩ። ከዚያም ሌሎች

መጻሕፍትን አነበብኩ። እነዚያም መጻሕፍት፥ መጽሐፍ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብዬ እንዳምን አደረጉኝ። ይህ ሁሉ እጅግ መልካም ሆኖ እያለ፥ ጌታን የተቀበልኩት ግን መቼ ነው? ሕይወቴን ለክርስቶስ የሰጠሁት እና እርሱንም መከተል የጀመርኩት ግን መቼ ነው?

ሰው፥ ካለመዳን ወደ መዳን፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን፥ ከኩነኔ ወደ ጽድቅ፥ ከዲያብሎስ ልጅነት ወደ እግዚአብሔር ልጅነት፥ የሚሻገራት ቀጭን መስመር አለች። ሰው አሷን መስመር የሚሻገራት ከኃጢአቱ ንስሐ ገብቶ፥ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ነው። ጌታ እራሱ ለኒቆዲሞስ "ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" ብሎታል (ዮሐ. 3፥3)። ሰው ዳግመኛ የሚወለደው ደግሞ ጌታን ሲቀበል ነው (ዮሐ. 1፥12-13)። እና እኔ ታዲያ መቼ ነው ዳግመኛ የተወለድኩት? እዎ፥ ስለ ክርስቶስ ዐውቃለሁ። ሆኖም ስለ ክርስቶስ ማወቅ እና ክርስቶስን እራሱን ማወቅ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ስለ ዳግማዊ ምኒልክ ብዙ ዐውቃለሁ። እርሳቸውን ግን በጭራሽ አላውቃቸውም።

ክርስቲያን ከሆንኩ በኋላ የጻፍኳቸው፥ ከመቃጠል የተረፉ፥ ግጥሞች አሉኝ። ከእነዚህም የመጀመሪያው "ፍልስፍና ፍርስራሽ ላይ" ብዬ የሰየምኩት፥ በጥቅምት ወር 1967 ዓ.ም. የጻፍኩት ነው። እሱ ግጥሜ ነው ጌታን መቼ እንደ ተቀበልኩ ፍንጭ የሰጠኝ። ሚስተር ፋርገር የሚያውሰኝን እነዚያን ግሩም መጻሕፍት እያነበብኩ፥ መጽሐፍ ቅዱሱም የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ እያመንኩ፥ ጌታን ግን ሳልቀበለው፥ ለሌላ አንድ ዓመት ያህል ቆይቻለሁ ማለት ነው። በዚህ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሞቼ ቢሆንስ ኖሮ? የምሄደው ወዴት ይሆን ነበር? ማለቴ ነው። እንደዚያ ባይሆንማ፥ ታዲያ "እነሆ፤ ትክክለኛው ሰዓት አሁን ____ ነው፤ የመዳንም ቀን አውን ለምን ተባለ? (2ቆሮ. 6፥2 ሥርዝ የተጨመረ) የነበርኩበት ድንዛዜ እቤት ብርታቱ! ጌታም እኔን የታገሠበት፥ እቢት ትዕግሥቱ!

ግጥሙን ከጻፍኩት በኋላ፥ በብሥራተ ወንጌል ሬድዮ ዘወትር መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስተምሩ ለምስማቸው፥ ለእቶ ተስማ ደምሴ ላከሁላቸው። ለእርሳቸው የላክሁት፥ እንደኛ ትምህርታቸውን በጣም ስለምወደው ነው። ሁለተኛ እርሳቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ መሆናቸውን ስምቻለሁ። እና አንድ ከሃዲ

የነበረ የባንክ ሠራተኛ፥ አማኝ በመሆኑ ደስ ይላቸዋል በማለት ነው። ሦስተኛ ግጥሙን ከሬድዮው ፕሮግራማቸው በአንደኛው አንዲነበብ አንዲያደርጉልኝ ነበር። ይህንኑም በሸኚ ዐይነት ደብዳቤ ገልጬላቸዋለሁ ይመስለኛል። ሆኖም ግጥሙ አልተነበበም። ከብዙ ዓመታት እና ከአቶ ተሰማም ጋር በደንብ ከተዋወቅን በኋላ፥ ግጥሜን ምን አንዳደረጉት ጠይቄአቸው ነበር። በፍጹም እንዳልደረሳቸው ነው የነገሩኝ። አምኛቸዋለሁ። ትንሽ ከረካከሜአት፥ ይህቻት፦

ፍልስፍና ፍርስራሽ ላይ

ፍልሰፍኖቼ ሁሉ
"ፍልስፍኖቼ" ልበላቸው እንጂ፤
ምንም እንኳን፥ እንዳቸውም ከኔ ባይፈልቁ
ሁሉም ቢሆኑ ቅጂ።
እና ፍልስፍኖቼ ሁሉ
ሰርክ ሲተናነቁ፤
እንዳቸውም አልቀሩ
ሁሉም አለቁ።

ዕርቀ ሰላም በመሐላቸው ወርዶ
አብረው ይኖሩልኝ ይመስል፤
ዘወትር እነርሱን ስሸመግል -
የምይዘው፥ የምጨብጠው አጥቼ፤
"ባንድ ራስ ሁለት" ሳይሆን
ሠላሣ "ምላስ"[3] አወጥቼ።

ባንድ ፊት
ሳይንስ በከሰተው ሁሉ ማመን የምወድ፤
በሌላ ፊት ሳይንስ ከሣቴ-እውነት እንጂ
ገባሬ-እውነት እንዳይደለ የማልከድ።
ባንድ ፊት "የጦጣ ዘር ነኝ"
የምል ዳርዊናዌ፤
በሌላ ፊት የማይገባኝ

ያለ ሰበብ የሆነ ጠንቅ ጎላዌ።
ባንድ ፊት "የሰው ዘር ነኝ! ያለም ዜጋ!"
የምል ደፋር
የቀለምን፥ የቋንቋን፥ ቅጥር ጥሼ፤
የእምነትን አድሞ፥ የባሕልን ባጥ አፍርሼ።
"የወንዜ ልጅ ወገኔ"፥ ስል ወዲያው ልገኝ
መሬቷ ላይ የውሸት ወሰን ሜሬ፤
"ብሔረተኛነት" የሚሉት
የወፍ ጎጆ ወንከሬ።
ባንድ ፊት ለው እካባቢውን አልፎ
ሕዋን እና ሕዋውያንን ገና እሸንፎ
ለጥቅሙ እንዲያውላቸው
ለምችቱ፤
የማልጠራጠር ቦችሎታው
በማያልቀው ብልሃቱ።
በሌላ ፊት የሰው ዘር
አንድ ጊዜ፥ አንድ ቦታ፥ ዱሮ -
ቀምሶት የነበር
የተሟላ፥ ፍጹም ኑሮ -
አልረሳህ ብሎት
ዕረፍት እጥቶ
በትዝታው፥ በሰቀቀኑ -
ከሚዋትት በቀር፥ በሕይወታዊ-ቅጽበት ዘመኑ
እራሱን እና እካባቢውን ገዝቶ
መኖር የሚችል፥ የማይመለስ ከቶ።
ባንድ ፊት ስለ ነጻነት፥ ስለ እኩልነት
የምሰፈልፍ፥ የተባለውን ሁሉ የማስተጋባ፤
"ከምን ነጻ?" በሚል ሙግት
ወዲያው መልሼ፥ ራሴን በራሴ፥ ግራ ላጋባ።

ከልጁ በላይ እናቱ፥ ታላቅ ወንድሙ፥ መምህሩ
ከናትዬዋ በላይ ባልዬው፥ ጎረቤቱ፥ ማኅበሩ

ከባልዬው በላይ አሠሪው፥ ጎብረተ ሰቡ
ካሠሪው በላይ መንግሥቱ፥ መመሪያው፥ ደንቡ
ከመንግሥቱ በላይ መንግሥታቱ፥ ዓለም-አቀፍ ፖለቲካ
ዓለም-አቀፍ ኤኮኖሚ - ያንን ሰጠኝ፥ ይህን እንካ
ከመንግሥታቱ በላይ ሬድዮ፥ ቴሌቪዥን፥ ጋዜጣ
"ፓብሊክ አፒንዬን" - ሥልጣኔ አመጣሹ ጣጣ::
ከዚያ ሁሉ በላይ አይራሬ ተፈጥሮ
በጠኔው፥ በቁንጣኑ፥ በምጡ
በሳተ ገሞራው፥ በምድር አንቀጥቅጡ
እያፈራረቀች በምትቀጣው ዓለም
በፀሐዩ፥ በዝናቡ፥ በነፋሱ፤
ትልቁ ጥያቄ "ነጻነት" ከሆነ
"ከምን ነጻ?" ነው መልሱ::

እንዲህ በተራራቁ፥ ልዩነታቸውን ሊያጠቡ
ሊቃረቡ፥ ሊገናዘቡ
በማይችሉ፥ ችኮ አሳቦች መሐል፥ ነፍሴ ተወጥራ
አለው ጠፍቶኝ፥ እደርገው ገብቶኝ ግራ
ስቀርበው የሚርቅ
መልኩን፥ ሰሙን፥ የሚዘባርቅ
ምትጎታዊ ግብ በርቀት እያስተዋልኩ
በማይራመዱ እግሮቼ ተውተረተርኩ
አልፍ፥ አፎይ! ግን አላልኩ::
ደኅና ሰንብት! ትካዜ
የሚሹትን ሳያውቁ የመፈለግ
አንዲያው የመቅበዝበዝ አባዜ::

በሞተ ምኞት አፈሳ
በተቀበረ ተስፋ መካን ላይ እያቀረቀርኩ
የሌለ ድምፅ ላዳምጥ
የማይሰሙ ጆሮቼን ቀሠርኩ
ደኅና ሰንብት! ከንቱነት
ከየት መጥተው፥ ወዴት እንዲሄዱ አለማወቅ

"ሕይወት" በሚሠኝ ወጥመድ ተይዞ
"ዓለም" በሚሉት ወህኒ መማቀቅ::

ከመፀነሱ
እስከ መፍረሱ
ለጉልቁ-ወ-መሳፍርት እጋጣሚዎች
ለተዳረጉት ነፍሱ
"ባለቤቷ እኔ ነኝ" ባይ
ምንኛ ግብዝ ነው እርሱ
በራስ መታመን ደኅና ሁና!
በሞገዱ ላይ
ምን ሥልጣን አለው ጣና?

ለበጎ እና ለከፉ መለያ
ለልክ እና ለሰህተት ማረጋገጫ፤
ለሕይወቱ መመሪያ
ቋሚ ዕቅድ፥ ዘላቂ እቅጣጫ
የሌለው
በድቅድቅ ጨለማ፥ በዳበሳ የሚጓዝ ሰው
አሰገድዶ
ወይ እግባብቶ
ሌሎችን አስከትቶ
ይመራኛል አልልም
ወደ ድል፥ ወደ እርካታ፤
ደኅና ሰንብት!
ከንቱ አለኝታ::

የባቢሎን፥ የግሪክ፥ የሮማ፥ ሥልጣኔዎች
ምን ቢረቁ፥ ምን ቢደምቁ
ሰው-ሠራሽ ነጥሮች
መውደቅ ነበረባቸው፥ ወደቁ::
የኛይቱም ትወድቃለች፥ እንደ ቀደሙቱ
መካከለኛው ምሥራቅ ቢሆን ምክንያቱ

ኢንፍሌሽን፥ ወይም ፖሉሽን
ወይም ፖፑሌሽን ኤክስፐሎሽን
እኮ ምንድነው ሥጋቱ?
ደኅና ስንብት! መታወከ፤
ሰዎች መሣሪያ አንጂ፥ ሠሪም አይደሉ ታሪክ::

ግዙፍ ሕጸጽ አለበት
"ተፈጥሮ ጥንተ-ዓላማ የለውም" ማለት
አምን ላይ ቆሞ አማትሮ
ያዩዋል?
ንድፍ እንዳልነበረው ተፈጥሮ?
ማነው ደስተኛ? ለምን?
ከዓሣ አንበሪ እና ከዓሣ?
ከበግ ግልገል እና ከጥንብ አንሣ?
አይሻለንም ነበር? ወዲያ ቀርቶብን አለምሮ
ፀጉራችን ባልተሸለተ ኖሮ?

"አይሻለንም ነበር?" አልኩ እንዴ?
አወይ ጉዴ!
ይሻል አይሻል
መጥፎ ይሁን ወይም ጥሩ
ላለምክንያት፥ አለምክንያት ተሠራሁ የሚል
አንደምን ሊያውቀው ነው ዳሩ?
"ናቹራል ሴሌክሺን" ደኅና ሁኚ!
አበባና ዐይን፥ አክናፍና አንጎል ሸላሚ፤
ሊሆን አይችልም፥ ደደብና ደንባራ አጋጣሚ::

እና ፍልስፍኖቼ አለቁ
ውሰጤ ጭጭ፥ አረጭ ማለት ጀመረ፤
ግብግባቸው አበቃ
መራገጫቸው መሆኔ ቀረ::
ይህ ዕረፍት እና ጸጥታ
ለካ ኖሮታል የራሱ ጣጣ፤

ባዶነት ደግሞ በተራው
በቁሜ ሊውጠኝ ቃጣ::
እና አንድ ቀን፥ ተነሣሁና
ፍልስፍኖቼ ከተዋደቁበት ሜዳ
ገባሁ፥ ቁስላቸውን ላጠና
ማን በማን፥ ምኑ ላይ፥ እንደ ተጎዳ::

"ፍጹም ፍልስፍና ስሻ፥ ሳልጎለምስ አርጅቼ
በስንት ድካም ያገኘኋችሁ፥ ኢፍጹማን ጣዖቶቼ
የምታዛልቁኝ መስሎኝ፥ ብከተላችሁ ተግቼ
ላንዴ እንኳን ክፉ ቀን ሳታስገፉ
ከመልዮን መንታ መንገዶች መሐል ጥላችሁኝ
እንዲህ ካጠገቤ ትጠፉ?
አዚቹ ቆሜ - በኔ፥ በናንተ፥ በሕይወት - ሳፈዝ
ይመሸ እንደ ሆን አንጂ፥ ይደነግዝ
በመልዮን መንታ መንገዶች ሙከራ
አላበድኩም ከእንግዲህስ ልሠማራ"

እያልኩ ስናገር ለተዋቁበት
ለተዋደቁበት እውድማ፤
ድንገት ቢታየኝ አወቅሁት
የውነት እምነቴ ይኸውማ!
በሕይወት ፍቺ ፍለጋ
እንዲያ ስባዝን ጠፍቶ ከርሞ፤
ፍልስፍኖቼ ፍርስራሽ ላይ፥ አሁን
እጆቹን ዘርግቶ ቆሞ::
በፍቅር ዐይኖቹ እያየኝ
"ና! አንተ ደካማ!" አለኝ::[4]
ለይቼ ዐወቅሁት በቃሉ
በቀራንዮው ቁስሉ::

ለመመሰከርም በሰአለት?

ለለ እነዚያ ሁለት ጸሎቶቼ ያስታወስኩት ጌታን ካወቅሁ ከሁለት ዓመት ገደማ በኋላ ነው። ለለ መጸለዬም ሆነ የጸሎቶቼን መልሶች ስለ መቀበሌ ፈጽሞ አረስቼ ነበር። እነርሱንም ከፉው "ከመንገድ ዳርማው ልቤ" ላይ ነጠቃቸው ማለት ነው? ባስታወስኳቸው ጊዜ ግን፥ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ነበር የሆንኩት። ሁለቱም እስቤ እና እቅጇ የጸለይኳቸው ጸሎቶች እልነበሩም። ሁለቱም ተነድቼ የጸለይኳቸው ጸሎቶች ነበሩ። የነበረችባቸው ሁኔታዎች ገፍተዋት እና ገፈታትረዋት ጥግ ያስያዟት ነፍሴ፥ በ"እልሞት ባይ ተጋዳይ" ሲቃ የጮኸቻቸው የመጨረሻ ጩኸቶቿዋ ነበሩ። ሁለቱም፥ "እግዚአብሔር የምትባል ካለህ!" ተብለው ነበር የተጸለዩት። በእግዚአብሔር የማያምን ሰው ጸሎቶች። ጸሎት መሆናቸውን ያላወቀ ሰው ጸሎቶች። ይሁኑ እንጂ፥ እግዚአብሔር የሰማቸው እና በድንቅ የመለሳቸው ጸሎቶች።

እነዚያ ጸሎቶች፥ በእኔ እፍ እና በእማርኛ ቋንቋ ይጸለዩ እንጂ፥ የእኔ ነበሩ ብዬ መናገር እግዚአብሔርን መበደል ሆኖ ይለማኛል። እነዚያን ጸሎቶች በአፌ ላይ ያኖረ እግዚአብሔር እራሱ እንደ ሆነ ነው የማምነው። ሆን ብዬ ነው፥ "በአፌ ላይ ያኖረ" የምለው። ምክንያቱም፥ እነዚያ ጸሎቶች ከልቤ መውጣታቸውን እርግጠኛ አይደለሁም። ሰው እንድን ነገር አለቦ ሊያደርገው አይደል "ከልቤ" የሚለው? እኔ ግን፥ የጸለይኩበት ቋንቋ አማርኛ በመሆኑ ለወሬ እይመችም እንጂ፥ "በልሳን" እንደ ጸለይኩ ያህል ነው የሚመሰለኝ። በምንም ዐይነት፥ እኔ እንደዚያ ያሉ ጸሎቶች ልጸልይ አልችልም። ከየት አምጥቼ? ከማን አይቼ? ወይስ ሰምቼ?

የማልወደውን እና የማልለማማበትን ነገር እግዚአብሔር አስደረገኝ እያልኩ አይደለሁም። በፍጹም! በጣም ትከክል እና መሆን የነበረበትን ነገር ነው ያስደ ረገኝ። በዚያን ጊዜ ላደርገው የምችለው፥ ከጸሎት ውጭ፥ ከጸሎት የተሻለ፥ ሌላ ምንም ነገር አልነበረኝም። ሞት እና ሽረት ጠርዝ ላይ ነኝ። እንደዚያ በቋፍ ያለ ለው፥ ወደ እግዚአብሔር ከመጮኽ የተሻለ፥ ሊያደርገው የሚችለው ሌላ ነገር የለውም። እኔ ግን ያንን፥ ላደርገው አይደለም፥ ላስበውም እንኳን አልችልም ነበር ማለቴ ነው። እግዚአብሔር፥ ጣልቃ ገብቶ፥ ስላለደረገኝ እንጂ።

ታዲያ ዘግይቼም ቢሆን፥ እግዚአብሔር እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንደ አደረገልኝ አስተዋልኩ። ባስተዋልኩም ጊዜ፥ እግዚአብሔር የዋለልኝ ውለታ መለል ብሎ ታየኝ። በእንድ ጊዜ፥ ከሥጋ እና ከነፍስ ሞቶች ነበር የታደገኝ። በደስታ እና በምሰጋና ተሞላሁ። በባለ ዕዳነት ሰሜት OVERWHELMED ሀ"ንኩ። (መቀላቀሊን ይቅር በሉኝ። በአብላጫው ከእኔ አለማወቅ፥ በአናሳው ደግሞ ከቋንቋው ደህንት ነው ሊሆን የሚችለው) ይህንን ነገር አንድ ቀን ሠመስከር ይኖርብኛል ብዬ አመንኩ። መቼ? እና እንዴት? በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ብዙ አሰብኩ፤ ብዙም ጸለይኩ። በመጨረሻ ላይ የደረሰኩበት ውሳኔ፥ ከገነት ጋር በትዳር ለዐሥራ አምስት አመታት አብረን ከኖርን በኋላ የሚል ነው።

"ለምን ዐሥራ አምስት ዓመታት?" ከቁጥሩ ጋር የተያያዘ፥ ምንም የተለየ ምክን ያት የለኝም። ትንሽ በዕድሜ ከገፋን እና ምራቅ ከዋጥን በኋላ ብናደርገው ጥሩ ይሆናል ብዬ አሰቤአለሁ። በመንፈሳዊ ሕይወታችንም ትንሽ ከበለልን በኋላ ቢሆን፥ ምስክርነታችን ከብደት ይኖረዋል ብዬ ገመቻለሁ። ትዳሮች ሁሉ በመ ጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ውስጥ ያጋጥማቸዋል ሲባል የምሰማቸውን ተግዳሮቶች ካለፍናቸው በኋላ ብንናገር ያምርብናል ብዬማሰሁ። ማንም "የልጅ ነገር" እድርጎ እንዲያይብን አልፈለግሁም። አለከዚያ እጸልያለሁ። ለገነትም እነግራታለሁ።

በሚቀጥሉት ዓመታት ውስጥ፥ ስለምሰጠው ስለዚህ ምስክርነት ስጸልይም ሳሰ ብም ነበር የቆየሁት። በቅርብ የምናውቃቸውን፥ በቁጥር 100 ገደማ የሚሆኑ ሰዎች፥ በምቹ ስፍራ እንሰበሰባለን - ቢያንስ ለግማሽ ቀን። በ40 ጀምሬ ነው ቀስ በቀስ ወደ 100 የደረስኩት። ምሳ እንጋብዛቸዋለን። መዝሙር አብረን እንዘምራለን። ቃለ እግዚአብሔርንም አብረን እንሰማለን። ከዚያም እግዚ አብሔር ያደረገልኝን ታላቅ ነገር እመሰክርላቸዋለሁ። በመጨረሻም አብረን ጌታን እናመሰግነዋለን። ሌላ ምን እመልስለታለሁ? ወይስ ምን አከፍለዋለሁ? (መዝ. 116፥12-14)

እግዚአብሔርም ይህንን ዕድል እንዳይነፍገኝ አጥብቄ ለምኜዋለሁ። "እንዲህ ብታደርግልኝ፥ እንዲህ አደርግልሃለሁ" እላልኩትም። ሰእለት የሚባለው እሱ ከሆነ፥ አልተሳልኩም። ሆኖም በእነዚህ ዓመታት ውስጥ፥ ይህንን ጉዳይ በተመ

ለከተ ያሰብኩት ነገር ሁሉ፥ ለእግዚአብሔርም የተናገርኩት ነገር ሁሉ፥ ቢደማመር ከሰአሰት እንደማይተናነስ ሆኖ ነው ለእኔ የሚሰማኝ። እና ይህንን ስእሉቴን ለመከፈል ሳደርግ የነበረውን የአእምሮ ዝግጅት እያጠናቀቅሁ እያለሁ፥ ያልጠበቅሁት ነገር ተከሠተ።

የገነት እና የእኔ ትዳር 15 ዓመት የሚሞላው በሚያዝያ ወር 1980 ዓ.ም. ነው። ትዳራችን እዚያ ከመድረሱ በፊት ግን፥ በምዕራፍ አንድ ውስጥ እንደ ተናገርኩት፥ መንገራገጭ ደረሰበት። እኔም እግዚአብሔር ያደረገልኝን ታላቅ ነገር ለመመስከር እሰቤው የነበረውን አሳብ በመጀመሪያ እዘገየሁት፤ በኋላም ትዳሩ ሲሠረዝ፥ አሳቡም አብሮ ተሠረዘ። እግዚአብሔር ግን፥ አሁንም የጸሰይኩትን ጸሎት መለሰልኝ። መልሱ ይህች መጽሐፍ ናት። ይህችም መጽሐፍ፥ እኔ ለመመስከር ከሰመንኩትም ሆነ ካሰብኩት ይልቅ እጅግ ሰፊ ናት። በእጭሩ፥ በእኛ እንደሚሠራው እንደ ኃይሉ መጠን ናት። ሰለዚህም በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ፥ በዘመናት ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ ክብር ይሁን፤ አሜን (ኤፌ. 3፥20-21)።

ማስታወሻ

1. Edward B. Pusey (Translator)፥ "Confessions of St. Augustine", Cardinal edition, 1952. P 1
2. FRANCIS COLLINS, "The Language of God", Pocket Books, 2007 p 21.
3. ቀላማጅ ሰዎችን ለመግለጽ የምንጠቀምበት፥ "ባንድ ራስ ሁለት ምላስ" የሚል ብሂል በገራችን አለ።
4. ኢየሱስ ክርስቶስ (ማቴዎስ 11፥28)

ምዕራፍ ስድስት

ሻካሮቹ ሽግግሮች

1967! ጉደኛ ዓመት። በአገሪቱ ላይ፣ በየአቅጣጫው የተቀሰቀሰው ነውጥ፣ ንጉሠ ነገሥቱን ከዙፋናቸው ላይ እስከ ማውረድ የደረሰበት። እንደዚያም አድርጎ፣ "በቃኝ" ያላለበት። በኢትዮጵያ "ዘውዳዊ" እገዛዝ፣ ከዝንተ ዓለም በኋላ፣ "ጎብረተሰባዊነት" በተባለ ሌላ ዐይነት እገዛዝ የተተካበት። መሬት "ላራሹ" የሆነበት። "ባለ ርስት"፣ "ጉልተኛ"፣ "ጭሰኛ" የሚባሉት ስያሜዎች፣ በቅርስነት ወደ ቤተ መዘክር ያቀኑበት። በየፍርድ ቤቱ የተከፈቱት በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ እርስት-ነክ ፋይሎች ሁሉ የተዘጉበት እና ወደ "እርሺም ቤት" (ARCHIVES) የተመለሱበት። ገበሬውን እንዲያነቁ እና እንዲያደራጁ በዐሥሮች ሺሆች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ የዘመቱበት።

በአደባባይ እና በይፋ "እግዚአብሔር የለም" የተባለበት። የሽግግር ዓመት - በአገር አቀፍ ደረጃ። የሽግግር ዓመት - ለእኔ ደግሞ በግለሰብም ደረጃ። የከር ስቶስ ተከታይ የሆንኩበት ዓመት አይደል? ጉደኛ ዓመት! 1967።

ኢትዮጵያውያን ሁሉ "አድኅሪ" እና "ተራማጅ"፣ "በዝባኝ" እና "ተበዝባኝ"፣ "ጨቋኝ" እና "ተጨቋኝ" ተብለው "መደብ" በሚሉት ሁለት ጎራ ብቻ የተከፋፈሉበት። በሴቱ እና በወንዱ፣ በተማረው እና ባልተማረው፣ በሲቪሉ እና በመለዮ ለባሹ፣ በእሮሞው እና በአማራው፣ በበላዩ እና በበታቹ፣ በፈረሱ እና ቢጋሪው፣ መካከል ያለው ማናቸውም ዐይነት ልዩነት ዕውቅና የተነፈገበት። የሰው ሁሉ መጠሪያ "ጓድ" ወይም "ጓዶች" ብቻ የሆነበት። በኢትዮጵያ በሕግ፣ በሥልጣን እና በኃይል የተደገፈ፣ የሥር-ነቀል ነውጥ እና የሥር-ነቀል ለውጥ የመጀመሪያ ዓመት።

አገሪቱ እንዳለች አፈፍ አለች እና ተነሣች - ከዚህ ማዶ ወደዚያ ማዶ፣ ከትናንት ወደ ነገ - ልትሻገር። ለዝንተ ዓለም ከኖረችበት እና ከምታውቀው፣

ትኖሪበታለሽ ወደ ተባለችው እና ገና ወደማታውቀው ልትሻገር። ለመታጠቅም ጊዜ አልነበራት። ቅሏን፣ ጨርቋን ሰማንያትም ፋታ አላገኘች። ስለዚህ ቀን ስታስብ አይደል ዘመንዋን ሁሉ የፈጀች? ይህንን ቀን ስትናፍቅ አይደል እንዲህ የሰለሰለች? እንዲህ ከስውነት ተራ የወጣች? ለዚያ ለዚያማ ልጆቿ አሉ። ለትጥቋ፣ ለቅሏ እና ለጨርቋ፣ ልጆቿ አሉ። ይህንን አነርሱ አስበውበታል። ይህንን እነርሱ ተዘጋጅተውበታል። እርስዋ መኾኗት ብቻ ነው ያለባት። ከእንግዲህ የምታባክነው ጊዜ መች ተርፏት?

ሆኖም፣ ገና ሳትራመድ ነበር ፈጽሞ ያልጠበቀችው ነገር ያጋጠማት። ገና አግሯን ስታነሣ ነበር ፈጽሞ ያልጠረጠረችው ችግር ፊት ለፊት የተጋፈጣት - መሻገሪያ የለም! ድልድይ አልተዘረጋም! እጅብ! ዛሬን ሳይረግጡ፣ ከትናንት ወደ ነገ እንዴት ይሻገሯል? ዛሬ ግን ለካ ገና አልተሠራም። ስለ ትናንት ጽልመ ትነት ወሬ ሲጠረቅ፣ ስለ ነገ ብሩኅነት ከበሮ ሲደለቅ፣ ለካ ዛሬ ተረስቶ ኖሯል። ለመንገድ እንዳች ዝግጅት አልተደረገም። እና እግሮቿን ከምን ላይ ታሳር ፋቸው? እንዴ እንደ ሆነ ተነሥታለች፤ ተመልሳ እትቀመጠው ነገር። እንዴ እንደ ሆነ እግሯን እንሥታለች። ወደ ኋላ እትመለሰው ነገር! አሁን እንግዲህ እንዴት ትሆነዋለች? አይጣል እኮ ነው!

ከላይ ያልኩት ሁሉ እውነት ነው፤ ደግሞም ፈጠራ ነው። ታሪካዊ ነው፤ ደግሞም ምናባዊ ነው። እውነታ፣ ከፈጠራ ይልቅ የበለጠ፣ ፈጠራ ይመስላል ያለው ማን ነበር? ከላይ ላልኩት ነገር እውነታነት ግን ማስረጃ መስጠት ያስፈልገኛል። ማስረጃ ምን ገዶ! ይኸው! "... የተማሪና የመንግሥት ፍጥጫ እየከረረ ይምጣ እንጂ የ1966ቱ አብዮት ሁለቱም ባልጠበቁት ሰዓትና ሁኔታ ነበር የፈነዳው። ሥርዓቱም የፍጻሜውን መቃረብ አልተረዳም ነበር። ለዓመታት የታገሉት ተማሪዎችም ያን የጠሉትን ሥርዓት በምን እንደሚተኩት ገና እውጠንጥነው አልጨረሱም ነበር።"[1]

"የየካቲት አብዮት ያን በመሰለ ስፋቱ፣ ያን በመሰለ ግለቱና ፍጥነቱ፣ በእንደዚያ ያህል ተደራራቢነቱና ደግሞም፣ በእንደዚያ ዐይነቱ - በወዲህ እጅግ በጣም ግልጽ በሆነው ሕዝባዊ አብዮታዊ መልኩ፣ በወዲያ ደግሞ እጅግ በጣም ውስብስብ በሆነው ግሥጋሴ በነጎደ ጊዜ - ማንንም ይሁን ማንን እየሰባበረ 'ሠርገኛ መጣ፣ በርበሬ ቀንጥሱ' እንደሚባለው ዐይነት ያራወጠው ሆነ።"[2]

"... ድርጅቱ የሠራዊቱን አስኳል በማደራጀት ላይ በነበረበት ወቅት ነው ይጠብቀው የነበረው አብዮታዊ ዓመጽ ሳይታሰብ በ1966 ዓ.ም. የፈነዳው:: በ ... ዙሪያ የተሰባሰቡት ቡድኖች የፈሩት ሁሉ ደረሰ:: የአገሪቱ ተራማጅ ኃይል የሕዝቡን ትግል በጭራነት እንደሚከተሉ በማያጠራጥር መንገድ በመረ ጋገጡ፥ የቀረው አማራጭ፥ የተቻለውን ሁሉ ጥረት አድርጎ ከሁኔታው ጋር ለመራመድ መሞከር እንደ ሆነ ታመነበት ... ::"[3]

"እውነት እና ደግሞም ፈጠራ፥ ታሪካዊ እና ደግሞም ምናባዊ" ላልኩት ነገር ድጋፍ እንዲሰጡኝ ነው ከላይ የጠቀስኳቸውን ሦስት ማስረጃዎች የደረደር ኩት:: የመጀመሪያው ጥቅስ ከታሪክ ባለ ሞያው ከፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ መጽሐፍ ነው የተወሰደው:: የሚቆጥሉት ሁለቱ ደግሞ፥ የዚያ አብዮት መሪ ለመሆን እርስ በርሳቸው እልህ አስጨራሽ ትግል ያካሄዱት፥ በመጨረሻም እርስ በርሳቸው የተጠፋፉት፥ የሁሰቱ ማርክሳዊ/ሌኒናዊ ፓርቲዎች - የመኢሶን እና የኢሕአፓ - መሥራች መሪዎች ስለ ፓርቲዎቻቸው ከጻፏቸው መጻሕፍት ነው የተወሰዱት::

ሁለቱም ባለ ድርሻ አካላት የሚሉት አንድ ነገር - የሆነው ነገር ሁሉ፥ በቂ ዝግጅት ወይም መሰናዶ ከማድረጋችን በፊት - ድንገት ሆነብን ነው:: አዋላጇ በቅርብ በሌለችበት፥ እትብቱን መቁረጫው ችግሬም ሆነ ወይም ማበቻው ፈትል በእካባቢው ባልነበሩበት፥ ሕፃኑን ስመጠቅሰያም "ጨርቅ" ባልተሰናዳ በት፥ የእንሽርት ውሃው ድንገት ፈሰሰ፥ ምጡም ድንገት ደረስ፥ ልጁም በጭንቅ ላቱ ሳይሆን በእግሮቹ ሊወጣ ገሰገሰ፥ እንደ ማለት ነው:: የታሪከም ትዝብት፥ ከላይ እንዳየነው፥ ይኸው ነበር:: እና መሰየ ለባሹ የጎበረተሰብ ከፍል "ታሪክ የጣለበትን አደራ" ተረከበ:: "ነጠቀ" ብል ነው ብዙዎች ደስ የሚላቸው - ያስ አስነጣቂ፥ ነጣቂ ያስ ይመስል::

አብዮታዊት ኢትዮጵያ

"አብዮታዊት" - ምን ማለት ነው? ከዚያ ጊዜ በፊት እንደዚህ የምትባል "ኢትዮ ጵያ" እንደ ነበረች አልሰማንም:: እንደዚህ የምትባል ኢትዮጵያ ከዚያ ጊዜ በፊት በአርግጥ አልነበረችም:: የማርከሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት "አብ ዮት" የሚለውን ቃል ሲተረጉም "አበየ ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም አሻፈረኝ አለ፥ አምቢ አለ ማለት ነው" ይላል:: ሲያብራራውም

"በአንድ ነገር፥ ከስተት ወይም ሂደት ውስጥ ያሉ ቅራኔዎች ተካረው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርሱ የሚፈጠር መሠረታዊ ለውጥ ..." ይሰዋል:: በአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል የተዘጋጀው የ"እማ ርኛ መዝገበ ቃላት"ም ይህንኑ ትርጉም ነው የሚያስተጋባው:: ስለዚህ "አብዮ ታዊት ኢትዮጵያ" ማለት የአበየች፥ አሻፈረኝ ያለች፥ እምቢ ያለች፥ ኢትዮጵያ ማለት ነው::

ኢትዮጵያ፥ "አምቢ!"፥ "አሻፈረኝ!" ያለችባቸው ጊዜያት ከዚያ በፊት በታሪካ ውስጥ አልነበሩም እንዴ? ነበሩ እንጂ:: ከአንድም፥ ከሁለትም፥ ከሦስትም ጊዜ በላይ ነበሩ እንጂ:: ሆኖም እነዚያኞቹ እምቢኞቿ አንድም ከውጭ ስመጣ ወራሪ ጠላት የተሰጡ ምላሾች ነበሩ:: አንድም ደግሞ የአንዱ አካባቢ መስፍን ሰሌላው አካባቢ መስፍን፥ የአንዱ አካባቢ ንጉሥ ሰሌላው አካባቢ ንጉሥ "አልገበርም!"፥ "አልገዛም!" ያሉባቸው ነበሩ:: አዎ፥ የሕዝቡ የሆኑ እምቢኞች ነበሩ - በጎጃም፥ በባሌ፥ በደራሳ (በኋላ ጌዴኦ):: ሆኖም ከመከራው ጽናት እና ከዘመኑ እርዝመት አንፃር ሲታዩ "ነበሩ" የሚባሉ ያህል አልነበሩም::

ይኸኛው ግን ስፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለንጉሠ ነገሥቱ እና ስመሳፍንቱ፥ ስጦር አዛዦቹ እና ስአሠሪዎቹ፥ ሰምስሰኔው እና ሰባለባቱ፥ ወዘተርፈ፥ የሰጠው የ"አንገብርም!"፥ የ"አንገዛም!" ምላሽ ነው:: በጎሹው እና በተጎሹው መደቦች መካከል ያሉት ቅራኔዎች ሲከርሩ እና ሲካረሩ፥ ሲጦዙ እና ሲጡዋጡዋዙ ኖረው፥ በመጨረሻ የተበጠሱበት ነው - የኢትዮጵያ አብዮት!

አብዮት፥ በወጣትነት ዕድሜ ውስጥ በነበርን ጊዜ ሲመስለን እንደ ነበረው፥ "ደስ የሚል ነገር" አይደለም:: በአብዮት ወቅት፥ ሕግ እና ሥርዓት የጨቋኞች የመጨቆኛ መሣሪያዎች ናቸው ተብለው ወዲያ ተሸቀንጥረው ይጣላሉ:: ሃይ ማኖት፥ ሞራል እና ሥነ ምግባር አድኅሪያን ስፈውን ሕዝብ "ቢጭኑት አህያ ቢቀመጡት ፈረስ" ስማድረግ የሚጠቀሙባቸው ሰከ እና ልጓም፥ እምቢ ነገር እና እርካብ እንደ ሆኑ ተቆጥረው ይወገዳሉ:: የአንድ ሕዝብ የማንነቱ መሰያ የሆነው ባህሉም እንኳን ይሻራል:: በሚወገዱት ነባር እሴቶች ቦታ የሚተካው "አብዮት" የተባለ ነገር ብቻ ነው - "አብዮታዊ" አመለካከት፥ "አብዮታዊ" ባህል፥ "አብዮታዊ" ሕግ፥ "አብዮታዊ" ሥነ ምግባር፥ "አብዮታዊ" እርምጃ፥ ወዘተርፈ:: ሕዝብ መግባቢያ ቋንቋውን ያጣል:: እጅግ አስፈሪ ምስቅልቅል ይፈጠራል::

ከአገሪቱ የረዥም ዘመን ታሪክ ጋር ሲነጻጸር፤ የ"አብዮታዊት ኢትዮጵያ" ዕድሜ እርዝመት አዚህ ግባ የሚባል አይደለም - ዐሥራ ሰባት ዓመት ብቻ ነበር። ሆኖም ገና ከአሁኑ፥ ካለፈ ገና ሃያ እምስት ዓመት እንኳን ሳይሞላው፥ ከሦስት ደርዘን የማያንሱ ጥራዞች ተጽፈውበታል። ለአማርኛ አንባቢዎች ከቀረቡልን ውስጥ፥ አኔ እስከማውቀው ድረስ፥ ኢህአፓ እራት (ያ ትውልድ)፥ መኢሶን አንድ? (ከላይ የተጠቀሰው)፥ ደርግ አንድ (የኮሎኔል መንግሥቱ ኃ. ማርያም "ትግላችን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ፥ ቅጽ አንድ")፥ ኢሕአዴግ አምስት (ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ)፥ የዮሐንስ ሙሉጌታ "አጥፍቶ መጥፋት" አንድ ጥራዝ፥ የዘነበ ፈለቀ "ነበር" ሁለት ጥራዝ፥ የግነት አየለ አንበሴ "የሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ትዝታዎች" ሁለት ጥራዝ፥ በድምሩ ዐሥራ አምስት።

እኔ በሰም ለጠቀስኩት ለእያንዳንዱ መጽሐፍ፥ በስም ያልጠቀስኳቸው ሦስት ሦስት ያህል ሌሎች መጻሕፍት ሳይኖሩ አይቀሩም - በአገር ልጆች እና በውጭ አገሮች ጸሐፊዎችም የተጻፉ። በአንድ በኩል በጣም ብዙ ነው። ባለፈ በዚህ ችን ታህል እጭር ጊዜ ውስጥ፥ ይህንን ያህል ብዙ ሰው የጻፈበት፥ አጭር ቀርቶ ረዥም ጊዜም፥ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የነበረ አይመስለኝም። ከተጻፉት መጻሕፍት ውስጥ አብዛኞቹ የአሸናፊነት እና የሰኬት ወሬ የሚያወሩ አይደሉም። በተቃራኒው በእብዮተኞቹ፥ በተለይም ደግሞ በእብዮቱ መሪዎች፥ መካከል ስለ ነበረው የአለመግባባት፥ የመለያየት፥ የመጠላላት፥ የመጠፋፋት፥ የዕልቂት፥ የዋይታ፥ የሰቆቃ ታሪክ የሚያወሩ ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ በጣም ብዙ የሚባልም አይደለም። ገና ሊጻፍ ካለው ጋር ሲነጻጸር ማለቴ ነው። ስለዚያ ወቅት የሚጻፈው ታሪክ ገና እንደ ተጀመረ እንጂ፥ እንደ አልተገባደደ ከሁኔታው ያስታውቃል። ጸሐፊዎቹ ብዙ ናቸው። አብዛኞቻቸውም የታሪክ ባለ ሞያዎች አይደሉም። ሁሉም በእነዚያ ዓመታት በየነበሩባቸው ጥጋ ጥጎች የሆነውን ነገር ነው የሚተርኩት። ያ አብዮት ያላመሰቀለው የኢትዮጵያዊ ሕይወት እና ቤት አልነበረማ! ያልገደለ ወይ ያላሰገደለ ወይም ያልተገደለ፥ ያልገረፈ ወይ ያላስገረፈ ወይም ያልተገረፈ፥ ያላሰረ ወይ ያላሳሰረ ወይም ያልታሰረ፥ ያላሳደደ ወይ ያልተሰደደ፥ ያላስለቀሰ ወይ ያላለቀሰ፥ ያልፈከረ ወይ ያላስፈከረ ወይም ያልተፈከረበት፥ አልነበረማ! እና፥ እስከ አሁን ወደ ሰው ጆሮ ያልደረሰ ብዙ ጉድ ገና ሳይወጣ አይቀርም።

የታሪክ ባለ ሞያዎቹማ ሥራዎቻቸውን ገና ለሕትመት ያደረሱም አይመስለኝም። እውነተኛ መረጃ ለማግኘት፥ የሚያገኙዋቸውን መረጃዎች ለማመሳከር፥ በትክክል ለማየት፥ የደፈረሰው ሁሉ እስኪጠል እና እስኪጠራ ይጠብቃሉ ይመስለኛል። እነዚያ ዓመታት ለኢትዮጵያዊ ሁሉ የቅዠታዊ ድንጋጤ (TRAUMATIC) ዓመታት አልነበሩ? ከዚያ ቅዠታዊ ድንጋጤ እስከ ዛሬም ድረስ ገና ያልነቁ ብዙ ኢትዮጵያውያን በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ አሉ አይደል? እንደዚህ ባለ ሁኔታ ውስጥ፥ ግራ ቀኙን እና ፊትና ኋላውን ያገናዘበ ታሪክ መጻፍ ቀላል እንደማይሆን እገምታለሁ። ደጉ ነገር፥ ተስፋ ሰጭው ነገር፥ ሌላ ትውልድ ደርሷል። በዚያ ቅዠታዊ ድንጋጤ ውስጥ ያላለፈ ሌላ ትውልድ ደርሷል። በወሬ ወይም በታሪክ ካልሆነ በስተቀር፥ ያንን ጉድ በዐይኖቹ ያላየ ሌላ ትውልድ ደርሷል። ተመስገን ነው።

ለዚህኛው ትውልድ፥ የዚያን ዘመን ጉድ ማውራቱ እራሱ ትከክል ነው ወይ? የሚል ጥያቄም ሊነሣ ጀምሯል። ለምን ኋሊናውን እናቆሽሽበታለን? የሚሉ አሉ። በእንዳንድ ጀርመናውያን፥ ለአዲሱ ጀርመናዊ ትውልድ ስለ ሂትለር፥ ስለ ናዚ ፓርቲ፥ ስለ "ሦስተኛው ራይኽ"፥ ስለ "ሆሎኮስት"፥ ስለ ጥቁር ሸሚዝ ለባሾቹ "ኤስ ኤስ" (SCHUTZSTAFFEL) መናገር እና መጻፍ እያስፈልግም እንደሚባለው ዐይነት ማለት ነው። ይኸኛው ትውልድ ባልሠራው በደል ሲከሰስ እና ሲወቀስ እንዲኖር፥ እንገቱን እንዲደፋ፥ እንዲያፍር፥ እንዲሸማቀቅ ማድረግ ትከክል አይደለም እንደሚባለው ማለት ነው።

በአንድ በኩል እውነት አላቸው። ትውልዱ ባልነበረበት ዘመን፥ አባቶቹ በሠሩት ወይም በተሠራባቸው ግፍ ምክንያት፥ ኋሊናው "ቶርች" መደረግ የለበትም። ምን በወጣው? በሌላ በኩል ደግሞ ይህ አባባል፥ ያለፈ ታሪክ በፍጹም መነገር ወይም መጻፍ የለበትም ማለትስ ትከክል ነው ወይ? የሚልም ጥያቄ ያስነሣል። ታሪክ መነገሩ ወይም መጻፉ ትከክል ነው ከተባለ፥ ከታሪክ ውስጥ መልካም መልካሙ ብቻ እየተመረጠ ይነገር ወይም ይጸፍ ማለትስ ትከክል ነው ወይ? የሚል ሌላ ጥያቄም ያስከትላል። ይኸ እንግዲህ ለመሆኑ "እይነገር" ወይም "እይጻፍ" የሚለውን እሳብ እራሱን፥ በሥራ ላይ ማዋልስ ይቻላል ወይ? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ሳናነሣ ነው።

የዚህኛው ጥያቄ መልስ "እይቻልም" ነው። ሰው አሳቡን ወይ በንግግር፥ አለዚያም በጽሑፍ፥ ወይ በዜማ፥ አለዚያም በምስል፥ ብቻ በሆነው እና

በተመቸው መንገድ እንዳይገልጽ ማድረግ በመሠረቱ አይቻልም። ተሞክሮ፥ ተሞክሮ፥ ሳይቻል የቀረ ነገር ነው። እንኳን ዛሬ፥ ዓለም ግሎባዊት በሆነችበት ዘመን ቀርቶ፥ ዱሮ በ"ድንጋይ ዳቦ" ዘመንም አልተቻለም። ዛሬማ የዴሞክራሲ ያዊ መብት ጉዳይም ተጨምሮበታል - አመለካከትን እና አሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት። መረጃ የመቀበል እና የመስጠት፥ የማወቅ እና የማላወቅ መብት።

አንደዚያ ካልሆነስ ሰው ከታሪክ አንዴት ይማራል? ሰው ከታሪክ ካልተማረስ ምን ተስፋ አለው? ያለፈውን ጥፋት አንዳይደግም ምን ይከለክለዋል? ቅራኔ ዎች ከርረው እና ተካርረው ከፍተኛ ደረጃ ላይ አንዳይደርሱ፥ አንዳይጦዙ እና እንዳይበጠሱ፥ አብዮት እንዳይፈነዳ፥ አልም ካለው የሥርዓት አልበኝነት ማጥ ውስጥ አንዳንዘፈቅ፥ የአርስ በርስ አልቂትም አንዳይከተል እና አንዳይሰፍን ማድረግስ አንዴት ይቻላል? የጥፋቱ አዙሪትስ አንዴት ይሰበራል? በብልጠት እና በጉልበት? አይ፥ አሱማ ታየኮ! ተደጋግሞ ታየኮ! ታሪክ ሌላ ምን ወሬ አለውና!

"አልሰሜን 'ግባ!' በለው"

ስመ ጥሩውን ደራሲ፥ ክበደ ሚካኤልን፥ አላየኋቸውም ብል ነው የሚሻለው። በደርግ ዘመን፥ ሆቴል ይኖሩ በነበረ ጊዜ፥ ለእንዲት እጭር አፍታ ነበር ያየኋ ቸው። ሆኖም የማውቃቸው፥ የማውቃቸው፥ ሰው ይመስሉኛል። አፈን የፈታ ሁት በእርሳቸው ግጥሞች አይደል? - ብርሃነ ጎሊና፥ የዕውቀት ብልጭታ፥ የትንቢት ቀጠሮ፥ የቅጣት ማዕበል፥ አኒባል፥ ሮሜዎና ዡልየት፥ ወዘተርፈ። ይህንን ክፍል ስጽፍ ትዝ ያለኝ፥ በ"ታሪክና ምሳሌ እንደኛ" መጽሐፋቸው ውስጥ ያነበብኩትን፥ "እዝማሪና የውሃ ሙላት" የተባለውን ግጥማቸውን የቋ ጩበት አሳብ ነው። ብዙ ጊዜ፥ ብዙ ቦታ ነው፥ ይህንን ግጥማቸውን አና፥ ከዚህ ግጥማቸው የተነሣ፥ አርሳቸውንም የማነሣቸው።

> አስኪ ተመልከተው ይህ አወራረድ፤
> ያልሰማው ሲመጣ የሰማው ሲሄድ፤
> ድምጡን አያውካካ መገሥገሡን ትቶ፤
> ማን ይሰማኝ ብለህ ትደክማለህ ክቶ።

በዚያ ጉደኛ ዘመን እኔን ሊያጋጥመኝ የጀመረው ሁኔታ ይህንን ነበር የሚመ ስለው። ወንዙ ከመውረድ ተግ አይልም። የአዝማሪውን መግሳ የሰማው ውሃ ላንድ አፍታም አይቆምም። ዝም ብሎ ወደ ታች ይፈስሳል። ክወደ ላይ የሚ መጣው ውሃ ሁል ጊዜም አዲስ ነው። ሁል ጊዜም እንግዳ ነው። ምዕራፍ አምስትን ስደመድም አንደ ተናገርኩት፥ እኔ ክዐሥራ አንድ ዓመታት የክህደት እና የምን ዐውቄነት ሕይወት ወጥቼ በክርስቶስ ያመንኩት እና ክርስቶስን መከተል የጀመርኩት በ1967 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ሆነ። እኔ "ክርስቲያን" ሆ'ፔ "አፎይ" ያልኩበት ያ ወቅትም፥ በዙሪያዬ ያሉ ብዙ ሰዎች "እግዚአብሔር የለም"፥ ሃይማኖትም "ሕዝብን ማደንዘዣ ዕጽ ነው" በማለት "አፈፍ" ብለው ከተነሡበት ወቅት ጋር ተገጣጠመ።

እና ክውስጥ እና ክውጭ ግብ ግብ ተነሣ። ከውስጥ የመጀመሪያውን ግብ ግብ የቀሰቀሰችው እናቴ ናት። "የአባትህን ሃይማኖት ትተህ ሌላ ሃይማኖት ውስጥ አንደ ገባህ ሰምቻለሁ። በእስቸኳይ ይህንን አዲስ ሃይማኖትህን ካልተውከ እና መተውህንም በደብዳቤ ካላስታወቅሽኝ በስተቀር እኔ አራሴ መጥቼ አስተው ሃለሁ" የሚል ደብዳቤ ጻፈችልኝ።

ስእናቴ መልስ መስጠት ነበረብኝ። ስለዚህም ረዥም ደብዳቤ ጻፍኩላት። በደብዳቤዬም ውስጥ፥ ላለፉት ዐሥራ አንድ አመታት ለእርሷ አንደ መሰላት እኔ ክርስቲያን እንዳልነበርኩ፥ ይልቁንም አልም ያልኩ ክሃዲ አንደ ነበርኩ ነገርኳት። እሁን የገባሁትም እርሷ አንደ ፈራችው ሌላ ሃይማኖት ውስጥ እለ መሆኑን፥ ይልቁንም አውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ መሆኔን፥ ክርስቲያን ማለትም የክርስቶስ ተከታይ ማለት መሆኑን (ሐዋ. ፲፩፥26) አብራራሁላት።

በሌላ ጊዜ "ሃይማኖተኛነትን ትተህ ይልቁንስ ወደ ትግሉ ዓለም ብትገባ አይሻል ህም ወይ?" የሚል ጥያቄ ያዘለ ደብዳቤም ጽፋልኛለች። ደብዳቤውን የሚጽፉ ላት አኅቶቼ እና ወንድሞቼ ስለ ሆኑ፥ አሳቡ የእርሷ ሳይሆን የእነርሱ ሊሆን አንደሚችል ጠርጥሬአለሁ። የጻፉትን መልሰው ሲያነቡላት፥ ያችን ክፍል ይዘ ሏታል። ደፍረው ካነበቡላትም፥ አሳቡ የእርሷ ካልሆነ በስተቀር ታስሠርዛቸዋ ስች። ብዙ ደብዳቤዎች ጽፈላት ስለማውቅ እርሷ ያላሰችው አንዲባል አንደማ ትፈልግ እሳምሬ ዐውቃለሁ። ፖለቲካ የቱን ያህል ስሜት አንደሚስጣት ስለ ማውቀውም፥ አሳቡ የእርሷ የአራሷ ቢሆንም አያስገርመኝም። ይልቁንም ሃይ ማኖት እና ትግል አብረው አይሄዱም ያሉችውን ነገር ክየት አመጣችው?

የውጭው ግብ ግብ በአብዛኛው ከትኩሶቹ ከሃዲዎች ጋር ነበር። እነዚህ ደግሞ ከህደታቸውን ለራሳቸው ቢይዙት ኖሮ ባልከፋ። የሚፈለገው ግን ከህደቱ እንዲሰፋፋ እና ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን ጭምር ሰለ ነበረ ይሰብኩታል። ስብከታቸውን መቀበል ያለመቀበሉን ለእኛ ለተሰባኪዎቹ የሚተውልን ቢሆኑ ኖሮ፥ መስበካቸውም እንኳን ባልከፋ። እነርሱ ግን ከመሰበክም እልፈው፥ ሰብከታቸውን ሰው ሁሉ እንዲቀበለው ግልጽ እና ልዩ ልዩ ጫና ያደርጋሉ። መከራከሩ ምንም ፋይዳ ስለ ሌለው፥ ብዙውን ጊዜ ዝም እላቸዋለሁ። አንዳንዱ "እላዋቂ ከሃዲ" ግን ያበሣጨኛል። እና እናገራለሁ።

የሚነሡት ክርክሮች እንዲያው "ጉንጭ አልፋ" ናቸው። አንዳንዶቹ ካድሬዎች ሶሻሊዝም ከሌሎቹ ፍልሰፍናዎች ሁሉ እጅግ የተሻለ መሆኑን ሊያሳምኑኝ ይሞክራሉ። ስድሣ ዓመታት ባልሞላ ዕድሜው፥ የመደብ ልዩነትን በማጥፋት፥ ሰው በሰው የማይበዘበዝበትን ሥርዓት በማምጣት፥ ሶቭዬት ኅብረትን ልዕለ ኃያላን መንግሥት በማድረግ፥ እነዚያን ሁሉ ቻይናውያን እብልቶ እና እጥግቦ በማሳደር ያስገኘውን ስውጥ በማሰረጃነት ይደረድራሉ። ኢትዮጵያ ኋላ ቀር፥ ደሀ እና እንደዚህ ጎሰቋላ የሆነችው፥ ሥርዓተ መንግሥቷ ሶሻሊዝም ባለ መሆኑ እንደ ሆነ ይነግሩኛል።

በዚያ ሂደት ውስጥ ሰለ ተከፈለው ዋጋ ግን አያነሡም። በጆሌፍ ሰታሊን እና በማኦ ዜዶንግ ዘመነ መንግሥታት ስላለቁት የሶቭዬት ኅብረት እና የቻይና ዜጎች ግን አያነሡም።[4] አሰከነ እካቴው፥ ሃያኛው ምዕት ዓመት "የዕልቂት ምዕት ዓመት" ስለ መባሉ የሰሙ አይመስሉም። ቀደም ሲል በነበሩት ዐሥራ ዘጠኝ ምዕት ዓመታት ውስጥ የደረሰው ዕልቂት ሁሉ ተደምሮ፥ በእንዱ በሃያኛው ምዕት ዓመት ውስጥ ብቻ ከደረሰው ዕልቂት ጋር ሊተካከል እንዳልቻለ፥ ለዕልቂቱም ከፍተኛውን አስተዋጽዖ ያደረጉት በምዕት ዓመቱ ውስጥ ከተካሄዱት ሁለት የዓለም ጦርነቶች ይልቅ፥ በየአገሩ የተደረጉት ሶሻሊስት አብዮቶች መሆናቸውን የሰሙ አይመስሉም።

ያለቁት ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም እኮ! ካለቁት ሰዎችም እብዛኞቹ፥ እጅግ እብዛኞቹ፥ ጸረ እብዮተኞች አልነበሩም። ተራ ሰዎች፥ ደሆች ሰዎች፥ የአገራቸውን መሻሻል የሚፈልጉ እና በአገራቸው መሻሻል የሚጠቀሙ ሰዎች ነበሩ። ብዙዎቹ እንዲያውም ከአብዮቱ ጎን የተሠለፉ ነበሩ። እንዴ? ሰውጡ የተፈለገው ሕዝቡ የተሻለ ሕይወት እንዲኖር ሰማድረግ ነበር እኮ! በሂደቱ ውስጥ

ግን፥ የዚህን ያህል ሕዝብ ዕልቂት ካሰከተለ፥ ደግሞም የዚህን ብዙ እጥፍ የሚሆን ሕዝብ በፍርሃት እና በሥጋት እንዲኖር ካደረገ፥ ግዙፍ ችግር አለ ማለት ነው። ይልቁንም እነዚህ መንግሥታት፥ ከሥልጣን ካወረዷቸው መንግሥታት ይልቅ እጅግ በከፋ ሁኔታ፥ "ፊለጭ ቆራጭ" እየሆኑ ነው ማለት ነው። እንድ ዐይነት ባርነት፥ በሌላ እና እጅግ በከፋ ዐይነት ባርነት፥ እየተተካ ነው ማለት ነው።

እንዳንዶቹ ሰው እግዚአብሔርን እና የሞራል ሕጎቹን ሁሉ ወዲያ ጥሎ፥ አራሱን በራሱ አስተካከሎ፥ አካባቢውን ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር አውሎ፥ መኖር ይችላል ይላሉ። ጀርመናዊውን ፍሬድሪሽ ኒቸን አያውቁትም ልበል? ከእንድ መቶ ዓመታት በፊት "እግዚአብሔር ሞቷል!" ብሎ ያስተማረውን? እግዚአብሔር የሌሰበት የሞራል እና የሥነ ምግባር ሕግ ለመደንገግ፥ ሰውንም "ልዕለ-ሰው" (SUPERMAN) ለማድረግ፥ ፎክሮ የተነሣውን? ብዙም ሳይቆይ ግን ሕይወቱ በዕብደት የተደመደመውን? የኒቸ ደቃ መዝሙር ነበር የሚባለው አዶልፍ ሂትለር፥ የመምህሩን ፍልስፍና እንዴት በሥራ ላይ እንዳዋለው እና ውጤቱም ምን እንደ ነበረ አልሰሙም ልበል?

አንድ ጊዜ ተከሰሼ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ እደራጅ ከሚሽን (ኢሠፓኦኮ) ካዛንቺስ ካለው ቀጣና ጽሕፈት ቤት ቀርቤለሰሁ። ከሱ "በሥራ ሰዓት መጽሐፍ ቅዱስ ትሰብካለህ፤ የምትሠራበትን መሥሪያ ቤት የውይይት ከበብ ታዳከ ማለህ፤ ለሥራችን ዕንቅፋት ሆነሃል" የሚል ነበር። እኔም ለሚያነጋግረኝ ካድሬ "በሥራ ሰዓት መጽሐፍ ቅዱስ አልሰበከሁም፤ የውይይት ከበቡንም እላዳ ከምኩም፤ ይልቁንም እናንተ በዚያ ካስቀመጣችኋቸው ከእንዳንዶቹ በተሻለ በውይይቱ እሳተፋለሁ፤ እናንተ የፖለቲካ ሥራችሁን በትጋት እንደምትሠሩ፥ እኔም መንፈሳዊ ሥራዬን በትጋት እሠራለሁ፤ ይኸ ለእናንተ ሥራ ዕንቅፋት ከሆነ፥ ልረዳችሁ አልችልም" አልኩት። የሚያሰሩኝ መስሎኝ ነበር። ሆኖም ለሁለት ሰዓት ያህል በጥሞና እና በግልጽ ከተነጋገርን በኋላ፥ ያ ካድሬ በሰላም አሰናብቶኛል።

አሁን በደረሰንበት፥ ስለ ሶሻሊዝም ፍልስፍናም ሆነ ወይም ያንን ፍልስፍና ሰለ ተከተሉት መንግሥታት ስኬታማነት ወይም አለስኬታማነት መናገርም ሆነ መከራከር እያስፈልገንም። "አገር ያወቀው፤ ፀሐይ የሞቀው" ጉዳይ ሆኗል። ከዚያ ፍልስፍና የተነሣ በሳይቤርያ፥ በሞንጎልያ፥ በከምቦድያ፥ በኢትዮጵያ፥

ወዘተርፈ፥ በሰው ዘር ላይ የተፈጸሙት አሰቃቂ ወንጀሎች ለዓለም ሁሉ ግልጽ ሆነዋል። እውነት ነው፥ "በእግዚአብሔር እናምናለን!" የሚሉ መንግሥታት በሕዝቦቻቸው ላይ ግፍ ሠሩ። ያ ግፍ አንገፍግፏቸው፥ "እኛስ በእግዚአብሔር እናምንም!" ብሰው የተነሡ መንግሥታት ደግሞ በሕዝቦቻቸው ላይ የበለጠ ግፍ ሠሩ። ከግፍ ወደ በለጠ ግፍ። የግፍ አዙሪት። በኃጢአት የወደቀው ሰው ዕጣ ፈንታ!

ካሣ እና አስካለ

ከቤተ ሰቤ አባላት መካከል፥ ግብ ግብ ያጋጠመኝ ከእናቴ ጋር ብቻ አልነበረም። ከሌሎችም፥ በተለይም ደግሞ ካሣ እና አስካለ ከተባሉት ወንድሜ እና እኅቴ ጋር ጭምር ነበር። እብዮቱ ሲፈነዳ ካሣ በጥቁር አንበሳ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪ ነበር። እንደኛ ደረጃን ዎላይታ፥ ሁለተኛ ደረጃን ደግሞ በጀኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ነው የተማረው። ኮሌጅ ሲገባ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት ተሸላሚ ነበር። እርሱ እና እንደርሱ ያሉ ተሸላሚዎች በየወሩ አንድ መቶ ብር ይሰጣቸው ነበር። ካሣ ከትምህርቱ በሰተቀር ሌላ ነገር አያውቅም። ከትምህርት መጻሕፍቱም ውጭ፥ ጋዜጣም እንኳን ቢሆን፥ አንብቦ የሚያውቅ አይመሰለኝም።

የዕድገት በኅብረት ዘመቻ በታወጀ ጊዜ ለመዝመት ፍላጎት አልነበረውም። ዘመቻውን በመቃወም ሳይሆን፥ ትምህርታችንን ከጨረስን በኋላ ቢያዘምቱን አይሻልም ወይ? የሚል አሳብ ነበረው። ከውጭ የመጡት አስተማሪዎቻችን ይሄዱብናል። ስንመለስ እንደ እነርሱ ያሉ ጥሩ መምህራን ላናገኝ እንችላለን የሚል ከፍተኛ ሥጋት ነበረው። ብዙ ጊዜ በስልክ ተወያይተናል። እኔ ሁል ጊዜም "ይህ በአገር የመጣ ጉዳይ ነው። ከባልንጀሮችህ ጋር ዘመቻውን ዘም ተህ፥ ግዳጅህን ተወጥተህ ሰትመለስ፥ አገር እንደ ሆነ ትሆናለህ እንጂ በተለይ ለእንተ ተብሎ የሚደረግ አንዳች ነገር ላይኖር፥ ለምን በከንቱ ትጨነቃለህ?" ነበር የምለው። አልቀረም፥ "የሕክምና ኮሌጅ" ተማሪዎችም ወደ መጨረሻው ላይ ዘመቱ።

ካሣ የዘመተው ሰሜን ሸዋ ነው። የቦታውን ልዩ ስም እርግጠኛ መሆን አልቻልኩም። መሐል ሜዳ፥ ኮረማሽ፥ አንኮበር የሚባሉ ቦታዎች ተጠርተው ልኖል። ለሰንት ወራት በዚያ እንደ ቆየ ባላውቅም፥ ለብዙ ወራት እንዳልሆነ

"ገን እርግጠኛ ነኝ። ዘመቻውን ትቶ ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሰ (EVACUATE አንዳደረገ) ሰማሁ። እርሱ ብቻ ይሁን ይህንን ያደረገው ወይም ሌሎቹም ዘማቾች ጭምር ይሁኑ የማውቀው ነገር አልነበረም። አይደውልልኝም ወይም አይጽፍልኝም። ያገኙታል ብዬ ለማሰባቸው ሰዎች ሁሉ እንዲደውልልኝ አልከበታለሁ። እነርሱም የሚነግሩኝ ሊያገኙት እንዳል ቻሉ ነው። የምሰማቸው ተባራሪ ወሬዎች ሁሉ ደስ የሚያሰኙኝ አልሆኑም። የሆነ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ሳይገባ እንዳልቀረ እና ጊዜውንም ሁሉ ለዚያ ድርጅት አገልግሎት እያዋለው እንደ ሆነ ገምቻለሁ።

እንደዚያ ላለመዝመት ሲፈልግ የነበረ ልጅ፥ እንደዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ፥ እንዴት የዚህን ያህል ለውጥ ሊታይበት ቻለ? የሚል ብርቱ ጥያቄ ተፈጠረብኝ። በዚህም በዚያም ብዬ እንድ ቀን በሰልክ አገኘሁት። ምንም ሳልለው፥ ወደ እኔ እንዲመጣ እና ለጥቂት ጊዜ እንዲያርፍ ብቻ ጠየቅሁት። ለመምጣት ዝግጁ በሚሆንበት ጊዜ ደውሎ እንደሚነግረኝ ገለጸልኝ። ከምን ያህል ጊዜ በኋላ እንደ ሆነ እላስታውሰም፥ ደወለልኝ እና መጣ። ጊዜው ሚያዝያ መጨረሻ 1968 ዓ.ም. ይመስለኛል። አንድ ሦስት ቀን እንደ ቆየ፥ ቤት ውስጥ ምን ሲሠራ እንደሚውል ገነትን ጠየቅኋት። "ምን እንደሚጽፍ አላውቅም፥ ነገር ግን መኝታ ቤቱ ውስጥ ሆኖ ሲጽፍ ነው የሚውለው" አለችኝ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ ወጣ ወጣ ማለት ጀመረ።

አንድ ቀን እንዲያውም በፈቃዱ አሉላን ለምሳ ቤታችን ይዞት መጣ። በፈቃዱ ግራዝማች አሉላ የሚያሳድጉት የዘመዳቸው ልጅ ነው። የዘመተው ከሐዋሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፥ የዘመተውም ዳሌ ወረዳ ውስጥ ነበር። ዳሌ የይርጋ ዓለም ከተማ ያለባት ወረዳ ነች። እንዴት እንደ ተገናኙ እና በመካከላችን ያለውን ዝምድና እንዴት ሊደርሱበት እንደ ቻሉ እግዚአብሔር ይወቀው። እርሱ በሌለበት፥ እኔ እና ገነት መኝታ ቤቱን በርብረን የሚጽፈውን ወረቀት እገኘን እና አነበብነው። እርሱ የዘመተበት ዘመቻ ጣቢያ ዘማቾች ዘመቻውን ለማቋረጥ ያስተላለፉት ውሳኔ ነው። እሱን ነው አየገለበጠ በዚህ አካባቢ ላሉ ሌሎች ዘማቾች የሚያሰራጨው።

አንድ ቀን ቀጠሮ እድርገን ተገናኘን እና ተነጋገርን። እንድንነጋገር የጠየቅሁት እኔ ነበርኩ። "ሰለ እገርህ እና ስለ ሕዝብህ እንዲህ 'ያገባኛል ባይ' መሆንህን እወድልሃለሁ። ለአገሬ እና ለሕዝቤ ይጠቅማል ለምትለው የፖለቲካ ቡድን

አባል መሆን፥ በሕይወትህም የፈለግኸውን ማድረግ መብትህ ነው። ነገር ግን አሁን ባለንበት ሁኔታ - ከፖለቲካ ቡድኖቹ በስተጀርባ ያሉትን መሪዎች ማንነት ገና በቅጡ ባላወቅንበት፥ ፕሮግራሞቻቸውን እንኳን ለማስተያየት አና ከዚህኛው ይሽኛው ይሻላል ለማለት ባልቻልንበት፥ ነገሮች ሁሉ ገና ድፍርስ በሆኑበት - ያንተ ተሳትፎ ይህንን ያህል መሆኑ ትንሽ የበዛ አይመስልህም ወይ?" አልኩት።

ለጥያቄዬ ቀጥተኛ መልስ አልሰጠኝም። ስለ ኩባ አብዮት፥ ስለ ፊደል ካስትሮ፥ ስለ ቼ ጉቬቫራ፥ ስለማው የኖርኩትን ዲስኩር ደሰኮረልኝ። ገነት እና እኔ "ጴንጤዎች" በመሆናችን፥ የራሔልን እእምሮ በዚህ ዕድሜዋ በሃይማኖት በመበከላችን፥ ሰላደረሰንባት ከፍተኛ ጉዳት አሰገነዘበኝ። በተራማጅ ኃይሎች ተይዘን እና ታስረን እንደ ነበረ መስማቱን፥ "ሊገድሏችሁ ሲገባ በሰላም የለቀቋችሁ በሥልጣን ላይ ያሉት የመደብ ኢጋሮቻችሁ (የመንግሥት ባለ ሥልጣናትን ማለቱ ነው) ካደረጉባቸው ተጽዕኖ የተነሣ ነው፤ እቋማችሁን የማታስተካክሉ ከሆነ ግን ሞት አይቀርላችሁም" በማለት አስጠነቀቀኝ። የማውቀው ወንድሜ፥ ያ ትሑቱ እና ሰው አከባሪው ካሣ፥ አልመሰልህ አለኝ። እንደዚህ ሲናገር ሰምቼው አላውቅም። ምን አገኘው ይባላል?

በውስጤ አጅግ እየተገረምኩ፥ ንግግሬን ግን ቀጠልኩ። በመጀመሪያ ስለ ምክሩ እና ስለ ማሰጠንቀቂያው አመሰገንኩት። በመቀጠልም በጣም ረጋ ብዬ፥ ማንም ወላጅ ልጁን በራሱ የሃይማኖት ሥርዓት እንደሚያሳድግ፥ እኔ እና ገነትም ልጃችንን በራሳችን የሃይማኖት ሥርዓት ማሳደግ መብታችን መሆኑን ገለጽኩለት። ሞት የሚገባን ስለ መሆናችን የሆነ እንደ ሆነ ግን፥ እኛ ሕይወታችንን አንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር የሰጠን መሆናችንን፥ ክእኛና እኛን ከሚገድሉን መካከል ቀዳሚው ማን እንደሚሆን የሚያውቀውም እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ነገርኩት። ይኸ የመጨረሻ ዕድሌ ሲሆን እንደሚችል በማሰብ፥ ልለው የፈለግኹትን ሳልለው ንግግራችን ወደ ጠብ እንዲያመራ አልፈለግሁም።

ንግግሬን ቀጠልኩ። "ለጥያቄዬ መልስ አልሰጠኸኝም። እኔ እስከማውቅህ ድረስ፥ አንተ ክትምህርትህ ውጭ ሌላ ነገር አታውቅም ነበር። ትምህርታችሁን አቋርጣችሁ መዝመታችሁ የቱን ያህል አስጨንቆህ እንደ ነበረ አስታውሳሁ። ከዘመታችሁ ይህን ያህል ወራት እንኳን በማይሞላ ጊዜ ውስጥ፥ ዘመቻውን

በመቃወም ጥላችሁ ተመለሳችሁ። እንደዚህ ባለ አጭር ጊዜ ውስጥ፥ ክጥቂት የ"ዴሞክራሲያ"[5] አትሞች እና ምናልባትም ክጥቂት አብዮታውያን መጻሕፍት ያለፈ አንብበህ ሊሆን አይችልም። አነዚህ ደግሞ አሁን እንተ እንደ ደረስክበት ያለ አቋም ላይ ለመድረስ በቂ አይመስሉኝም።

"እንደምታውቀው የፖለቲካ ሳይንስ እንደ ጤና ሳይንስ 'የጠራ' (PURE) አይደለም። የሚመራበትም የጠራ ሕግ እና ሥርዓት የለውም። ስለሌለውም ነው የፈረንሳይ፥ የቦልሼቪክ እና የቻይና አብዮቶች ሕዝቦቻቸውን ያንን የሚያክል ከፍተኛ ኪሣራ ያስከፈሏቸው። እኛ ክአነርሱ ተሞክሮ ትምህርት በመውሰድ፥ የምንፈልገውን መልካም ነገር በተቻለ መጠን በአነስተኛ ኪሣራ ለማምጣት ፕሮት ማድረግ የለብንም ወይ? አሁን የአገራችን አብዮታዊ ንቅናቄ በደረሰበት ደረጃ፥ የዚህን ያህል እራስህን ለአንድ የፖለቲካ ቡድን መሰጠትህ (COMMITTED መሆንህ) ትንሽ አልቸኮልክም ወይ?" አልኩት።

የሰጠኝን መልስ በአውነት በትክክል አላሰታውሰውም። ላሰታውሰውም ደግሞ አልችልም። ምክንያቱም የረባም፥ የተያያዘም አልነበረም። "እራምባ እና ቆቦ" እንደሚባለው ዐይነት ነበረ። ባቀረብኩለት ዐይነት ጥያቄዎች ላይ አስቦ የሚያ ውቅም አልመስለኝም። እኔንም የተረዳኝ፥ አገሩን እንደሚወድ እና ለአገሩም መልካም እንደሚመኝለት ሰው አድርጎ አይደለም። ያም እንኳን ቢቀር፥ እርሱን እንደሚወደው እና ስለ እርሱ ግድ እንዳለው ታላቅ ወንድሙ አድርጎም እንኳን አይደለም። እኔም በልቤ ጨርቁን ብቻ እንዳልጣለ እንጂ፥ በእውነት እንደ አበደ ሰው ቆጠርኩት። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እስካለ ድረስ፥ በፍጹም ልን ግበባ እንደማንችል ገባኝ። ሁለታችንም ዝም ዝም ብለን ጥቂት እንደ ቆየን -

"ክዚህ በኋላ ወዴት ለመሄድ ታሰባለህ?" አልኩት። ዝርዝሩን አልነገረኝም፤ ሆኖም፥ እናታችንን ለማየት ወደ ዎላይታም ለመሄድ እንደሚያስብ ነገረኝ።

"እንግዲያውስ አንድ ነገር ልለምንህ" አልኩት።

"ምን?" አለኝ።

"እናታችንን ካየሃት በኋላ ቶሎ ብለህ እካባቢውን ለቅቀህ ብትወጣ ... አሁን እዚህ እኔ ቤት ሆነህ እንደምታደርገው፥ እርሷም ቤት ሆነህ የፓርቲህን ሥራ ባትሠራ ... እርሷንም በዚህ ዕድሜዋ ጣጣ ውስጥ ባትጨምራት" አልኩት።

አሺም አምቢም አላለኝም። ከአንድ ሁለት ቀናት በኋላ ከእኛ ዘንድ ሄደ። በወጉ እንኳን አልተሰነባበትንም።

የፈራሁት ጣጣም አልቀረም፣ ደረሰ። በ1969 ዓ.ም. ወደ ታሕሣሥ ወር ላይ ይመሰለኛል አናቴ፣ ወንድሜ ነጋሽ እና እኅቴ እዘነጋሽ ተይዘው መታሠራቸውን ሰማን። ልንጠይቃቸው አሰብን አና በአንድ የሳምንት መጨረሻ ላይ ገነት እና እኔ ከዲላ ተነሥተን ሐዋሣ ሰንደርሰ፣ ሐዋሣ ያሉት ቤተ ሰቦቻችንን፣ እሥረኞቹን ወደ ሐዋሣ ኢያመጡአቸው ሰለ ሆነ እናንተ መሄድ ኢያስፈልጋ ችሁም እሱን። ለካ ካሣ የእናታችንን ቤት የኢሕኢፓ ምሽግ አድርጎት ኖሯል። በጊዜው የተለያየ ወሬ ይነፍሰ ስለ ነበረ፣ የሆነውን ነገር በትክክል ለማወቅ አልቻልኩም ነበር። አሁን ግን፣ "ያ ትውልድ ቅጽ ሁለት" እና "ከናይሮቢ እስከ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት"[6] የተባሉት ሁለት መጻሕፍት ዝርዝሩን በተሻለ ሁኔታ እንዳው ቀው እረድተውኛል።

የኢሕኢፓ የበላይ አመራር ወታደራዊ ማሠልጠኛ ቤዝ በአሞ ሸለቆ ለመመሥ ረት ይወሰናል። ከመስከረም ወር 1969 ዓ.ም. ጀምሮ፣ በዚያ ቤዝ የሚሠለጥ ኑት እና የሚያሠለጥኑት ሰዎች ከአዲስ አበባም፣ ከአሲምባም፣ ከሌሎች ቦታዎችም ወደ ዎላይታ መጓጓዝ ይጀምራሉ። ከዕለታት አንድ ቀን፣ በመጓጓዝ ላይ የነበሩ ሰዎች እና የጦር መሣሪያዎች በመንግሥት ኃይሎች እጅ ይወድ ቃሉ። እንዳንዶቹ ሲያዙ ወይም ሲገደሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ያመልጣሉ። በጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሳምንት ውሰጥ እኔ ከምሠራበት የዲላ ንግድ ባንክ እሩብ ሚልዮን ብር ዘርፎ የጠፋው፣ የባንኩ ገንዘብ ያዥ የነበረው ሰው በመካ ከላቸው ይገኛል። ሊነጋጋ ሲል የእናታችን ቤት ይከበባል። ከቤተ ሰቦቼ እንደ ተረዳሁት፣ ይህ ከመሆኑ እንድ ሠላሣ ደቂቃ ቀደም ብሎ፣ ካሣ ከቤት ወጥቶ ሄዷል። በቤቱ ውስጥ የተገኙት አናቴ፣ ወንድሜ እና እኅቴ ተይዘው ታሠሩ።

ኢሕኢፓ የአሞ ሸለቆውን ቤዝ ለመመሥረት በመስከረም ወር 1970 ዓ.ም. ሁለተኛ ሙከራ አድርጓል። ድርጅቱ ለቤዙ ምሥረታ እና ለሌሎችም ሥራዎቹ ወጭ የሚያደርገው ገንዘብ ያስፈልገው ሰለ ነበረ፣ ይኸው ገንዘብ ከሻሸመኔ ንግድ ባንክ አንዲዘረፍ የፓርቲው የኢንተርዘን ኮሚቴ ይወሰናል። ዘረፋው በኅሐሴ ወር 1969 ዓ.ም. የመጨረሻው ቅዳሜ ዕለት ይከናወናል። ድርጅቱ ለዘረፋው ከሠማራቸው ሃያ ሦስት ወጣቶች መካከል ዐሥራ አንዱ በዚያው ዕለት ይሞታሉ። ዘረፋው በሚፈጸምበት ዕለት በቴሌኮሚዩኒኬሽን መሥሪያ

ቤት፣ የሻሸመኔው ሪጅን ውሰጥ፣ በሱፐርቫይዘርነት ትሠራ የነበረችው አስካለ ደግሞ በአካባቢው ሁሉ የሰልከ ግንኙነት አንዲቋረጥ እድርጋለች ሲባል ሰምቻለሁ። አሰካለ፣ እንደሚመለሰኝ ካሣ የመለመላት፣ ከቤታችን ሁለተኛዋ የኢሕኢፓ አባል ነበረች።

እንደ መጀመሪያው ሁሉ፣ የቤዝ ምሥረታው ሁለተኛ ሙከራም አልተሣካም። ከቡድኑ አባላት አራቱ በገበሬዎች ተያዙ። ሰምንቱ በወረዳው አስተዳዳሪ በሚ መራ ኃይል ተይዘው፣ እጆቻቸውንም የኋሊት ታሰረው፣ ከገደል እፋፍ ላይ ከነሕይወታቸው እሞ ወንዝ ውሰጥ ተጣሉ። ቀኑ መስከረም 28 ወይም 29 ሳይሆን አይቀርም። ከተጣሉት መካከል እንዱ ካሣ ነው።

እዮ ሐርቃ "ዶ/ር ካሣ" ከማለታቸው በስተቀር (ገና ዶክተር ሰላልሆነ)፣ የ"ሰማ ዕታቱን" ሰም በዝርዝር በመጻፍ የበኩላቸውን መታሰቢያ ሊያስቀሩላቸው ሞክ ረዋል። የወሬ ነገር፣ በዚያው ሳምንት ነበር መገደላቸውን እና ያሰገደላቸውን ሰው ሰም የሰማሁት። እሰገደላቸው የተባለውም ሰው የማውቀው ሰው ነው። የእዮ ሐርቃን መጽሐፍ እስከ እነበብኩበት ጊዜ ድረስ ግን፣ አንደ ተገደሱ እና ከሞቱ በኋላ እሰከሬናቸው በአሞ ወንዝ ውሰጥ እንደ ተጣለ ነበር የመሰለኝ።

እኛ ከዲላ ተዛውረን ወደ አዲስ አበባ ከመጣን በኋላ አስካለ ቤቷ እንደ ተፈተሸ፣ የጦር መሣሪያ እና የኢሕኢፓ ሰዎች በቤቷ ውስጥ ተደብቀው እንደ ተገኙ፣ እርሷም በቁጥጥር ሥር እንደ ዋለች ሰማን። ብዙም ሳይቆይ ወደ አዲስ አበባ አመጡአት እና በከፍተኛ 19 ውሰጥ ታሠረች። እንደ እግዚአብሔር ቸርነት፣ እኛም አንኖርበት የነበረው የአዮ ብሥራት ቤት የሚገኘው በዚሁ ከፍ ተኛ ውሰጥ ብዙም ሳይርቅ ነበር። እና ገነት በእግሯ እየተመላለሰች የአስካለ የየዕለቱ ሰንቅ አቀባይ ሆነች። ከገባችበት ነገር ከብደት የተነሣ፣ አስካለ በሕይ ወት ትተርፋለች የሚል ተስፋ ማንኖችንም አልነበረንም። ሆኖም አግዚአብ ሔር ይመሰገን እና ተረፈች።

እንዴት ልትተርፍ እንደ ቻለች ጠይቄአት ዐውቃለሁ። "ታማኝ ለመሆን ብዬ፣ እልናገርም ብዬ፣ ነዋ ያንን ሁሉ መከራ የበላሁት" አለችኝ። "ልጆቼን ጥዬ ልሰደድ ሁሉ ዝግጅት አድርጌ ጨርሼ ነበርኮ!" አለችኝ። ሦስት ትንንሾች ልጆች ነበሯት። ትልቋ ምናልባት የዐሥር ዓመት ትሆን ይሆናል። የመሰጠቷ መጠን በጣም አስገረመኝ።

"ታዲያ በመጨረሻ እንዴት ልትናገሪ ቻልሽ?" አልኳት።

"እንድ ቀን አንድ ቡል ይዘውልኝ መጡ፤ አያፈዘብኝ የኮድ ሰሙን እና የኮድ ስሜን ነገረኝ። ሌሎችንም እኔ እና እርሱ ብቻ የምናውቃቸውን ጉዳዮች እንደ ቀልድ አወራልኝ። 'ስትራከቸራችን፥ ሌላውም ሁሉ ነገር ተበልቷል፤ ተይው፤ አትድከሚ' አለኝ። ያንን ሁሉ መሥዋዕትነት የከፈልኩት እና የምከፍለው እንደዚህ ላለ ቡል ነው ብዬ በፍጹም አስቤ አላውቅም ነበር" አለችኝ።

"ቡል ስትይ ምን ማለትሽ ነው?" አልኳት።

"ቡል አታውቅም? ... በቃ ቡል ነበር ... አንዲያው ወደል ... በፍጹም አረሃብ እና ውሃ ጥም ምን እንደ ሆነ እይቶ የማያውቅ ወደል ነበር ... ለቀናት ያለ አፍኝ ጥሬ እና ውሃ እንደዚያ እየተንገላቱ የታገሉትን እና የሞቱትን ወንድሞቼን አሰብኳቸው ... ያን ጊዜ ነው በኢሕአፓ ፈጽሞ ተሰፋ የቆረጥኩት" አለችኝ።

አስካለ ወደ ዝዋይ ተዛውራ በዚያም ለሆነ ያህል ጊዜ ታስራለች። በመጨረሻም ተፈትታ ወደ ሥራዋ ተመልሳለች። ወደ አዲስ አበባም ተዛውራለች። ለሆነ ያህል ጊዜ ቆይታ ደግሞ የሌላ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆናለች። የትኛው ፓርቲ እንደ ሆነ በውል አላወቅሁትም። ምናልባት የአራሱ የመንግሥት ፓርቲ ሳይሆን እንደማይቀር እገምታለሁ። እንደ ገና ወደ ፖለቲካ መመለሷ አስገር ሞኛል። ሆኖም፥ እርሷ ያለፈችበትን ሁኔታ ዝርዝሩን ስለማላውቀው፥ ማለቴ ምን አስብለዋት ወይም ምን ዐይነት ግዴታ አስገብተዋት በሕይወት እንደ ለቀቋት ስለማላውቀው፥ አልፈረድኩባትም።

የደርግ መንግሥት ከወደቀ በኋላ፥ ለአገልግሎት ወደ ኬንያ ከተመላለስኩባቸው ጊዜያት በአንደኛው፥ ከመድረክ ላይ ሰወርድ አንድ ሰው ከጉባዔው መሐል ተነሥቶ መጣ እና ከፊት ለፊቴ ቆመ።

"ይህንን ሰው ታውቀዋለህ?" አለኝ። ትከ ብዬ አየሁት፤ ሆኖም ላስታውሰው አልቻልኩም።

"ይቅርታ ያድርጉልኝ፥ እኔ እዘነጋለሁ" አልኩት።

"አስቲ ደህና አድርገህ እየው" አለኝ። ደህና አድርጌ ላየው ሞከርኩ። ሆኖም አሁንም ምንም ማስታወስ አልቻልኩም።

"ይቅርታ ያድርጉልኝ፤ እኔ እንደዚህ ያለ ድካም አለብኝ፤ ሰው እዘነጋለሁ" አልኩት፥ በድጋሚ።

"አገሌ የሚባል ሰው አታውቅም?" አለኝ የገዛ ስሙን ጠራልኝና።

"አገሌ? ... አገሌ አገሌ?" በማለት እኔ ደግሞ ስሙን ከነአባቱ መልሼ ጠራሁለት።

"አዎ" አለኝ። ጢሙን ተላጭቶ ይሁን ወይም አላድጎ ኖሯል ያላሉተኝ። አሁን መልኩ መጣልኝ። እነካሣን ከነሕይወታቸው አሞ ወንዝ ውስጥ አስጥሏቸዋል የሚባለው ወረዳ አስተዳዳሪ ነው። እጁን ዘርግቶ ሊያቅፈኝ መጣ። እኔም እጆቼን ዘርግቼ ላቅፈው ሄድኩ። የውነት፥ ከልባችን ተቃቅፈን ተሳሳምን። እዚያው እንደ ቆምን፥ እንዴት እንደ ወጣ እና እንዴትስ ወደ እምነት እንደ መጣ ጠየቅሁት። ሠርከ እያስደነቀኝ የሚኖረውን የእዳኜን ሥራ ነገረኝ።

እንደ ነገረኝ፥ ኢሕአዴግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረባት ዕለት ነበር እርሱ የአራት ኪሎን ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ለቅቆ የወጣው። በወጣባት በዚያችው ቅጽበትም ነበር፥ ሕይወቱን ለጌታ የስጠው። ከዚያ በየት እና እንዴት አድርጎ "እዚህ እንዳደረሰኝ፥ እርሱ አረኽም ታሪክ ነው" አለኝ። ስለ እነካሣ አሟሟት የሰማሁት ወሬም ሆነ ያነበብኩት ታሪክ፥ እውነትም ይሁን ሐሰት፥ በዚህ ወንድሜ እና በእኔ መካከል በከርስቶስ የተመሠረተውን ይህን እንድነት ሊያናጋው በፍጹም አይችልም።

"እስመሳዩ እና አደገኛው ጴንጤ"

የዲላውን ባንክ መዘረፍ ካነሣሁት አይቀር፥ ትንሽ ነገር ላከልበት። የገንዘብ ለውጡ እዋጅ ሣታ ሊታወጅ ቀኑን፥ የባንክ ቅርንጫፎች ሥራ አስኪያጆች ነገ አዲስ አበባ ገብተን እንድናድር በስልክ ታዘዝን። ገንዘብ እንደሚለወጥ የምና ውቀው ነገር አልነበረም። ከሁሉም ዐይነት ኖቶች በቂ ገንዘብ ከዋናው ካዝና አወጣን እና ለካሼሩ አስረከብኩት። ከዚያ ሥራዬን አጠናቅቄ ለነገ መንገድ ለመዘጋጀት በጊዜ ወደ ቤቴ ሄድኩ።

ሣታ እዋጁ ሲነገር፥ ከነገ ጀምሮ ባለ 100 እና ባለ 50 ብር ኖቶች ገቢ ብቻ እንጂ ወጭ እንደማይሆኑ ዐወቅሁ። ስለዚህ ካሼሩን አፈላልጌ እንደ ገና ወደ ቢሮ መግባት እና የተረከባቸውን ባለ 100 እና 50 ብር ኖቶች ወደ ዋናው

ካዝና መመለሰ ነበረብን። በአራተኛው ቀን ይመስለኛል፥ ገነት እና እኔ ከአዲስ አበባ ስንመለስ፥ የዲላው ባንክ ተዘግቷል፤ ጉዳዩ ከማይመለከታቸው ከጥቂቶች በስተቀር፥ ሠራተኞቹ በሙሉ ታስረዋል። ገንዘብ ቤቱ ታሽጓል።

የባንኩን ቅርንጫፍ ሥራ ለማስጀመር፥ የታሸገው ገንዘብ ቤት መከፈት፥ ከታሠሩትም ሠራተኞች አንዳንዶቹ መፈታት ነበረባቸው። ገንዘብ ያዥም ከሌላ ቦታ መምጣት ነበረበት። እና ከፖሊስ፥ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ከባንኩም የበላይ መሥሪያ ቤት ተወካዮች በተገኙበት ካዝናዎቹ ሁሉ ተከፍተው፥ መዛግብት እና ሰነዶች ሁሉ ታዩ። ካሹም ተቆጠረ። በእኔ እና በካሼሩ መካከል ርከክቡ በትከክል ነው የተደረገው። ዘራፊው ይዞ የሄደው ገንዘብ እርሱ በአንድ ቀን ውስጥ ከለበሰበው ባለ 100 እና ባለ 50 ብር ኖቶች ላይ ነበር።

የዘረፋውን ሁኔታ ለማጣራት ከአዲስ አበባ ይመሰሰኛል የመጣ አንድ ወጣት መርማሪ ነበር። "ሻምበል ነው" ሊባል ለምቻለሁ። ምርመራውን አጠናቅቆ ከተመለሰ ከወራት በኋላ በዎላይታ የተከሠተውን የኢሕአፓ አንቅስቃሴ ለመመርመርም ይኸው ሰው ይላካል። በምርመራው ሂደት የዲላውን ባንክ የዘረፈው ሰው በዚያ አንደ ነበረ ይደርስበታል። ወደ አናታችን ቤት ሲሄድም፥ የዲላውን የባንክ ቅርንጫፍ ሥራ አሰኪያጅ ፎቶግራፍ ግድግዳ ላይ ተሰቅሎ ያያል። በባንኩ በቀለ እና በኢሕአፓው ካሣ መካከል ያለውንም ዝምድና ጠይቆ ይረዳል። የሆነ ነገር ሸተተው።

አንድ ቀን ሰናይት ከሐዋሳ ትደውል እና ዛሬ ዲላ አመጣለሁ ትለናለች። ሰናይት የገነት ታላቅ እኅት እና የከፍለ አገሩ አስተዳዳሪ ጸሐፊ ናት። ስለ ባንኩ ዘረፋም ሆነ ስለ ዎላይታው ጉዳይ ከእኔ የተሻለ ታውቃለች። ሆኖም እኔን በዝርዝር ጠየቀችኝ። እኔም የማውቀውን ሁሉ ነገርኳት። እርሷም "በባንኩ ዘረፋ ውስጥ የበቀለ አጅ አለበት ... ጴንጤነቱ ሆነ ተብሎ ለማወናበጃ የተዘጋጀ ሽፋን ነው ... የባንኩን ዘራፊ ወደ ዎላይታ የላከው እና እናቱ ቤት ውስጥ እንዲደበቅ ያደረገው አርሱ ነው ..." ይባላል አለችን። አኛም "አውነቱን አንደ ሆነ አግዚአብሔር ያውቀዋል ... እንግዲህ እኛ ከመጸሰይ በስተቀር ሌላ ምን ለማድረግ አንችላለን?" አልናት። በዚህ መነሻነት እንደ ሆነም አላውቅም፥ በጥቅምት ወር 1970 ዓ.ም. ነው ይመስለኛል ወደ አዲስ አበባ መዛወሬ የተነገረኝ - በዲላ ገና አንድ ዓመት ከሦስት ወራት ብቻ አንደ ቆየሁ።

በአንድ ወቅት በዲላ ከተማ ውስጥ የቤቶች አሰሳ ይደረጋል። ከሚታሰሱት ቤቶች መካከል አንዱ የባንኩ ሥራ አሰኪያጅ መኖሪያ ቤት ነበር። ቤታቸው የሚታሰሰው ሰዎችም ከያሉበት አየተለቀሙ ይታሰራሉ። አሰሳውን በበላይነት የሚመራው በጊዜው "የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት" በመባል ይታወቅ የነበረው አካል ነው። ቀደም ብሎ የባንኩ የውስጥ ኡዲተር የነበረው ሰው በታጠቁ ሰዎች ታጅቦ ወደ ቢሮዬ መጣ እና እንደምፈለግ ነገረኝ። አሁን ሥራ ላይ ሰለ ሆንኩ ልመጣ እንደማልችል ነገርኩት። ሄደ እና አሰሳውን በበላይነት ለሚመራው ሰው ሪፖርት አደረገ ይመስለኛል፥ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በቁጥር ከቀድሞው የበዙ ታጣቂዎችን አስከትሎ ወደ ባንኩ መጣ።

"ጓድ በቀለ፥ ለምን ታስቸግረናለህ? ለጥያቄ እንፈልግሃለን ነው እኮ የምንልህ" አለኝ በቁጣ። የእርሱም ስም በቀለ ነው - በቀለ ገደቹ። እኔም "ጓድ በቀለ፥ አላስቸገርኩም፤ አልመጣምም አላልኩም። እኔ ያልኩት በመጀመሪያ በእጃችን ተበትኖ ያለውን የሕዝብ ገንዘብ በሥርዓት አንቁጠር እና ሂሳቡን አንዝጋ ነው። አንተም ሆንክ እኔ የሕዝብ እና የመንግሥት አገልጋዮች ነን። አሁን ብትወሰደኝ ነገ በእጄ ያለውን የሕዝብ እና የመንግሥት ንብረት እንዳስረከብ መልሰህ ታመጣኛለህ። ሰለዚህ ያን ጊዜ የምንሠራውን ሥራ አሁን ትንሽ ላቃልልህ" አልኩት።

"አይቻልም፤ አሁን ነው ይዘንህ ልንሄድ የምንፈልገው" አለኝ።

"ጓድ በቀለ፥ ችግር እኮ የለውም። ባንኩ ሁለት በሮች ናቸው ያሉት። ሁለቱም በሮች በታጣቂዎች ይጠበቁ። እኔ ሂሳቤን ልዝጋ። የሕዝብ አገልግሎት እንዳይ ቋረጥ ደግሞ ለሌላ ሰው ላስረከብ። ከዚያ በኋላ ትወስደኛለህ" አልኩት።

"እይቻልም" አለኝ።

"እንግዲያው እኔም ይህንን ሳላደርግ ልመጣ አልችልም። የወደድከውን ማድረግ ትችላለህ" አልኩት እና ወደ ሥራዬ ተመለስኩ። ትንሽ አለብ አደረገ እና በሩ ላይ አንድ ሁለት ታጣቂዎችን አቁሞ ሄደ። እኔም ሥራዬን ቶሎ ቶሎ ብዬ አጠናቀቅሁ እና የባንኩ አገልግሎት እንዳይተጓጎል ካሸሩን ገንዘብ ላስረከ ብህ ሰለው "አልረከብም" አለኝ። "ኧረ ተው" ብለውም፥ "ዋስትና በሌለበት እንደዚህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ገንዘብ ልቀበል እና ልከፍል አልችልም፤ የፈለጉትን ያድርጉኝ" አለ። ላስገድደው አልችልም። የገንዘብ ካዝናዎቹን

ቆላልፌ፥ አንዳንድ ሰነዶችን የማስቀምጥበትንም ካዝና እና የባንኳን ላንድ ሮቨር መኪና ቁልፎች አንድ ላይ ከሌላ ቦታ ቆለፍኩባቸው። ከዚያ አብረውኝ የሚሠሩትን ስዎቹ "አይዟችሁ" ብዬአቸው ለሚጠብቁኝ ታጣቂዎች አጄን ሰጠሁ።

ገነት አንደ ነገረችኝ፥ ቤቴን ሲፈትሹ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የጌዴዎናውያን አዲስ ኪዳኖች ተገኙ። ከእነርሱም ውስጥ ምን ያህሎቹን እንደ ሆነ አላስታውስም ገነት በማግሥቱ ይዛቸው መጥታ አብረውኝ ለታሠሩት ሁሉ አደለቻቸው።

ባንኩ ለሥራ ሳይከፈት ሲቀር፥ ጉዳዩ የእውራጃው አስተዳዳሪ ወደ ነበሩት ወደ ሻለቃ ደሰዬ ትኩ ደረሰ። አርሳቸውም አሣሪዎቼን ጠርተዋቸው፥ "የባንኩን ሥራ አስኪያጅ ደግሞ ለምንድነው ያሠራችሁት?" ሲሉ ጠየቋቸው። እነርሱም "ከዚህ በፊት ባንኩን አስዘርፏል። ቀንደኛ ኢሕአፓ የሆነ ወንድም አለው። እርሱም ጴንጤ ነኝ የሚለው ለማስመሰል ነው። ገና ያልታወቀበት አደገኛ ስው ነው" እንዳሏቸው ሰማሁ።

ሻለቃ ደሰዬም፥ "ባንኩ ሲዘረፍ እርሱ እዚህ አልነበረም፤ ይልቁንስ አንተ እራስህ (አዲተሩን) እዚህ አልነበርከም እንዴ? እርሱ አራት ኢሕአፓ ለመሆኑ ማስረጃ ካላችሁ ንገሩኝ፤ ወንድሙ ኢሕአፓ ነው የምትሉት ግን እርሱን ለማሠር በቂ ምክንያት አይደለም። አሁን ፍቱት እና ባንኩ ሥራውን ይጀምር። አለበለዚያ ለሚፈጠረው ችግር ተጠያቂዎቹ እናንተ ትሆናላችሁ" አሏቸው።

በማግሥቱ ወደ ረፋዱ ላይ ይመለሰኛል ተፈታሁ እና ወደ ሥራዬ ተመለስኩ። ከአምስት ይሁን ከስድስት ዓመታት በኋላ ከዚያ ወጣት መርማሪ ጋር አለመራ ተገናኝተናል። እንዲያውም አብረን "ሻይ ቡና" ያልንም መስሎኛል። "አስመ ሳዩን እና አደገኛውን ጴንጤ" እስከ አሁንም ድረስ እየተከታተለው ይሆን እንዴ? ከሆነም ያለመስማነዋል እንጂ አያሰነቅፈውም። እንደ ተወራው ሆኜ ካገኘኝ፥ በስለላ ታሪክ ውስጥ አንድ ድል ሰአራሱም ለአገርም ያስመዘግባል።

ተራው ደረሰ እና "ጓድ በቀለ ገደቹም" በይርጋዓለም ወሕኒ ቤት ታሠረ። ካድሬ ከመሆኑ በፊት አዲስ አበባ በትምህርት ላይ ነበር። በቤተ ክርስቲያንም ያገለግል ነበር። አባቱ ደግሞ የዲላ ጢኖ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ነበሩ።

እርሱ የ"ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዚያዊ ጽ/ቤት" ካድሬ ሆኖ እንደ ተመለመለ እና የጌዲኦ አውራጃ ተጠሪ ሆኖ መመደቡ እንደ ተሰማ፥ አንድ ዕሑድ ቀን በጉባዔ ነገሩን ተናግረው ለልጃቸው የጸሎት እርዳታ ሲለምኑለት በቦታው ነበርኩ። ይርጋዓለም ታሥሮ በነበረ ጊዜ ያመልከው እና ያገለግለውም ከነበረው ጌታ ጋር ታረቀ። በጊዜው በይርጋዓለም ወህኒ ቤት በእሥር ላይ ከነበሩት ከእነ ተሰፋዬ ጋቢሶ ጋር በጣም ይቀራረብ እንደ ነበረ፥ ከእርሱ ሳይሆን ከእነርሱ ስምቻለሁ። ዛሬ በካናዳ ይኖራል፤ በዚያም ከነፍስ እና ከሥጋ ሞት የታደገውን ጌታ ያገለግላል ሲባል ሰምቻለሁ።

"አበትናችኋለሁ!"

አስካለ "ልጆቼን ጥዬ ልሰደድ ሁሉ ዝግጅት አድርጌ ጨርሼ ነበርኮ!" አለችኝ - በ1970 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ። የኢትዮጵያውያን ሰደት ያኔ ጀምሮ ነበር ማለት ነው። ኢሕአፓዎች፥ "ቀኝ መንገደኛ" የሚል ስም የተሰጣቸው መኢሶኖች፥ ሌሎችም ነገሩ ያላማራቸው፥ መሰደድ ጀምረው ነበር። ተሣከቶላት ቢሆን ኖሮ አስካለም የደርግ መንግሥት ካሳደዳቸው ብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያን መካከል አንዲ ትሆን ነበር።

በስማኒያዎቹ አጋማሽ ላይ በናይሮቢ ያገኘሁት ሁለተኛው ስው ተሳከቶላቸው መሰደድ ከቻሉት ኢትዮጵያውያን መካከል እንዱ ነው። እርሱን የደርግ መንግሥት አላሳደደውም። እርሱን የደርግን መንግሥት ያሳደደው የኢሕአዴግም መንግሥት እንኳን ገና አላሳደደውም። እርሱ "ማንም ሳያሳድደው በፊት የነዘ ነሊናው ያሳደደው ስው ነበር" (ምሳ. 28፥1)።

ከአስካለ አፍ ስለ ስደት በሰማሁበት ጊዜ፥ ስለ ኢትዮጵያውያን መሰደድ ከተነገረው ትንቢት ጋር ትውውቅ አልነበረኝም። እኔ ባለኝ መረጃ፥ ትንቢቱ ሊነገር የጀመረው በ1957 ዓ.ም. በናዝሬት ነው። በመጀመሪያ የተነገረውም በጸጋዬ ካብትይመር አፍ ነበር። ጸጋዬ ካብትይመር በዝማሬ አገልግሎቱ የሚታወቅ፥ እስከ ምክትል ሚኒስትርነት ማዕረግ ይመስለኛል ደርሶ የነበረ፥ አሁን በሁለት ሺሆቹ ውስጥ ወደ ጌታው የተለበሰበ ወንድም ነው። ትንቢቱን በሚናገርበት ጊዜ ግን ገና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሲሆን፥ የተናገረውም እንደ እርሱው የዓፄ ገላውዴዎስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በተሰበሰቡበት ጉባዔ ነበር።

ትንቢቱ ከዚያ በኋላ በተለያዩ ቦታዎች እንደ ተነገረ ዐውቃለሁ። ምናልባት ከዚያም በፊት የተነገረባቸው ቦታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እኔም ከደረስኩ በኋላ በየቦታው ሲነገር ሰምቻለሁ። ይህ የኢትዮጵያም፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጉም ታሪክ ሰለ ሆነ፥ ከ1957 ዓ.ም. በፊት ሲነገር የሰሙ ወገኖች ካሉ ይህንን ሬኮርድ ማረም እና ማስተካከል ይችላሉ። ይህንን ጉዳይ ከዚህ ቀደም በጻፍኳቸው በሦስቱም መጽሐፎቼ ውስጥ እንዛሥቼዋለሁ ይመስለኛል።

ከኢትዮጵያ ውጭ በዞርኩባቸው ቦታዎችም ሁሉ በስብከት ወይም በትምህርት መልክ ብዙ ጊዜ አነሣዋለሁ። ይህንን የማደርገው አገርን የሚመለከት፥ በእኛው ዕድሜ የተነገረ እና በእኛው ዕድሜ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ የተፈጸመ ትንቢት በመሆኑ ነው። ትንቢቱን ተናጋሪዎቹ ኢትዮጵያውያኑ ብቻ ላይሆኑ የተለያዩ የውጭ አገር ሰዎች ጭምር መሆናቸውም የበለጠ ትኩረት አንድ ስጠው አድርጎኛል።

የኢትዮጵያውያኑ ወደ ዓለም ሁሉ መበተን ዓላማው ወንጌል እንዲሠራጭ እና ብዙዎች እንዲድኑ ለማድረግ እንደ ሆነ ነው ትንቢቱ የሚናገረው። ትንቢቱ ሲነገር የነበረው፥ ኢትዮጵያ ኤርትራንም ታካትት በነበረበት ጊዜ መሆኑንም ለእንባቢያን ማስታወስ የሚያስፈልገኝ ይመስለኛል። እንደማየው እና ደግሞም እንደምሰማው ከሆነ፥ አሁን ኢትዮጵያውያኑ የሌሉበት የታወቀ አገር መኖሩን አጠራጠራለሁ። አሁንም እንደማየው እና ደግሞም እንደምሰማው ከሆነ፥ ኢትዮጵያውያኑ በቁጥር ጥቂት በርከት ብለው ያሉበት፥ ነገር ግን የአበሾች ቤተ ክርስቲያን የሌለበት፥ አገር መኖሩንም የዚያኑ ያህል አጠራጠራለሁ።

እና ይኸ እጅግ አስደናቂ ነገር ነው - ዓርባ ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የተነገረ እና የተፈጸመ፥ ደግሞም በመፈጸም ላይ ያለ፥ ትንቢት። የመደነቅ ዐቅም የሚያንሰው ለው ካልሆነ በስተቀር፥ በዚህ የማይደነቅ ኢትዮጵያዊ ወይም ኤርትራዊ ሊኖር እንዴት ይችላል?

> ... እስቲ እንደ እኔ ማን አለ? ይናገር ... ገና ወደ ፊት ምን እንደሚሆን፥ ይናገር፤ በፊቴ ያስረዳ፤ ስለሚመጣውም ነገር እስቀድሞ ይናገር። አትፍሩ፤ አትደንግጡ፤ ይህን አልነገርኋችሁምን? ቀድሞስ አላሳወቅኋ ችሁምን? ስዚህ እናንተ ምሰክሮቼ ናችሁ። ከእኔ በቀር ሌላ እምላክ አለን? ፈጽሞ! ወይም ሌላ ዐለት አለ? የለም! ማንንም አላውቅም (ኢሳ. 44፥7-8)።

ብተናው እውን ስለሚሆንበት ሁኔታ የተባለ ነገር አልነበረም። ከላይ እንዳልነው ሁኔታው ሊታይ እና ሊታወቅ የጀመረው ከዐሥራ ሁለት ዓመታት በኋላ ነበር። ስደቱ ሲጀምር ምክንያቱ ፖለቲካዊ ነበር። "ፖለቲካዊ" በሚለው ቁረጃ ውስጥ የዕድገት በጎብረት ዘመቻው፥ ነጭ እና ቀይ ሽብሩ፥ አብዮታዊ እርምጃው፥ መንደር ምሥረታው እና ሠፈራው፥ ጦርነቱ እና ብሔራዊ ውትድ ርናው፥ ወዘተርፈ፥ ይካተታሉ። ትንሽ ቆይቶ ድርቅ እና እረሃብ በእነዚህ ላይ ተጨምረዋል። የ1970ዎቹ ድርቅ እና እረሃብ በሙቶ ሺሆች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን መሰደድ፥ ከዐሥር ሺህ በላይ ለሚሆኑ "ቤተ እሰራኤላውያንም" ከዘመናት ሰደታቸው ወደ እባቶቻቸው አገር መመለስ ምክንያት ሆነዋል።

የብተናው ዓለማም እውን ሰለሚሆንበት ሁኔታ የተባለ ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር ግን ቅድመ ዝግጅቶች ማድረጉን ማስተዋል ይቻላል። መጀመሪያ ላይ ኢትዮጵያውያኑ በብዛት የተስደዱት ወደ ጎረቤት አገሮች፥ ማለትም ወደ ሱዳን፥ ኬንያ እና ጅቡቲ ነበር። በኬንያ የተጠናከረ የቤተ ክርስቲያን እባቶች ከምችት ነበር። አቶ ሙላቱ በላቸው እንደ ነገረኝ፥ እርሱ በግንቦት ወር 1969 ዓ.ም. በሥራ ተዛውሮ ወደ ኬንያ ሲሄድ፥ አቶ ሚልዮን በስጠ እና አቶ አሸናፊ ዘውገ ቀድመውት በዚያ ነበሩ። ብዙም ሳይቆይ፥ አቶ ኃይሉ ወልደ ሰማያት፥ አቶ ብርሃኑ ደረሰ፥ ዶ/ር ቤተ መንግሥቱ፥ አቶ ተስፋሁን አማደው እና ሌሎችም መጡ። አቶ አሸናፊ እና አቶ ተስፋሁን የሄዱት በትምህርት ሲሆን፥ የተቀሩት በኬንያ ያሉት በሥራ ምክንያት ነበር። ሆኖም ተማሪዎቹም ትምህርታቸውን ሲጨርሱ እዚያው ሥራ ጀመሩ።

በናይሮቢ የኢትዮጵያውያን ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ጉበረት ቤተ ክርስቲያን መሠረት ተጣለ። አገር ቤት በነበሩ ጊዜ፥ አቶ ኃይሉ ከመካነ ኢየሱስ ሲሆኑ፥ አቶ ሙላቱ እና አቶ ብርሃኑ ከቃለ ሕይወት ናቸው። አቶ ሚልዮን ከመሠረተ ክርስቶስ ሲሆኑ፥ አቶ አሸናፊ፥ ዶ/ር ቤተ እና አቶ ተስፋሁን ከሙሉ ወንጌል ናቸው። አቶ ኃይሉ ሉተራዊ ሲሆኑ የተቀሩት መጥምቃዊ ናቸው። አቶ አሸናፊ፥ ዶ/ር ቤተ እና አቶ ተስፋሁን ጴንጤቆስጤአዊ ሲሆኑ የተቀሩት አይደሉም።

እነዚህ ሰደተኞች እልነበሩም። ሰደተኞቹን እንዲቀበሉለት እና እንዲያነሳሳሉ ለት እግዚአብሔር አስቀድሞ የላካቸው መልእክተኞቹ ነበሩ። ምንም እንኳን በመካከላቸው ከላይ የጠቃቀሰኳቸው ዐይነት የቤተ ክርስቲያን ዳራ እና

የአሰተምህሮ ልዩነቶች ቢኖሩም፥ ስለሚያገለግሉት ሕዝብ ሲሉ፥ ልዩነቶቻቸውን አቻቻሉ።

ወደ ሱዳን እና ወደ ጅቡቲ የተሰደዱት ከርስቲያኖች በመጀመሪያ ላይ አርስ በርሳቸው እና ባስጠለሏቸው እብያተ ከርስቲያናት እገሌጋዮች ነበር የሚገለገሉት። ዐልፎ ዐልፎ የሚነበኙአቸው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ኢት ዮጵያውያን ያልሆኑም አገልጋዮች ነበሩ። ከእነዚህም መካከል በተለይ እቶ መለሰ ወጉ (በኋላ ዶከተር) ይጠቀሣል። ትምህርቶችን በሥነ ጽሑፍ፥ በካሴት እና በሬድዮ በማሰራጨት፥ ጥያቄዎቻቸውን በመቀበል እና በመመለስ፥ አልፎ እልፎ በአካልም በመገኘት በፍቅር እና በትጋት አገልግሏቸዋል። ቆይቶ ከአገር ቤትም እንዳንድ አገልጋዮች ሊነበኙአቸው ችለዋል።

በተመሳሳይ እና/ወይም በተከታታይ ጊዜያት፥ በሌሎች የአፍሪቃ አገሮች፥ በአውሮፓ፥ በሰሜን አሜሪካ፥ በመካከለኛው ምሥራቅ፥ በአስያ፥ በአውሰት ራልያ እና በኒውዚላንድ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ከርስቲያናት ተተክ ለዋል። እነዚህ የዳያስፖራ አብያተ ከርስቲያናት የተተከሉባቸው ሁኔታዎች በየራሳቸው ትንግርታዊ ናቸው። ጊዜውን ሰጥቶ የሚያጠናቸው እና የሚጽ ፋቸው ሰው ይጠብቃሉ።

የ1,700 ዓመታት ዕድሜ ያላት ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ቤተ ከርስቲያን በዘመኑ ፍጻሜ ላይ ወደ ዓለም-አቀፋዊ ሚስዮናዊነት የተሸጋገረችበት እስገዳጅ ሁኔታ ያለ ጥርጥር ትንግርታዊ ነው። በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሚስዮናዊ የነበረች ቢሆንም፥ ያ ግን ከፖለቲካ ሥልጣን ጋር በእጅ እና ጓንትነት የተደረገ ሚስዮ ናዊነት ነበረ። የሚጻፈው ታሪክ፥ እግረ መንገዱንም ቢሆን፥ ትንቢቶች ወደ ታሪክነት ስለሚቀየሩበት ሂደትም ያሳየናል።

ቀደም ሲል ከአፍሪቃ ናይሮቢን እንደ ምሳሌ ጠቅሻለሁ። አሁን ደግሞ ከአው ሮፓ አንድ ሰበዝ ልምዘዝ። በኢትዮጵያ ሚስዮናዊት የነበረችው ሞሪን እና ባለቤቷ ወንጌላዊ ካሣዬ ደገፉ ወደ ኢንግሊዝ አገር የሄዱት በ1966 ዓ.ም. በንጉሥ ዘመነ መንግሥት ነበር። አሳባቸው የነበረው፥ ካሣዬ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቱን እንደጨረሰ ወዲያውኑ አገልግሎታቸው ወዳለበት ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ነበር። ነገር ግን በዚያው ዓመት የኢትዮጵያው አብዮት ስለ ፈነዳ እና ሞሪንም የውጭ አገር ሰው ስለ ሆነች፥ የመመለስ ዕቅዳቸውን ለማዘግየት ተገደዱ።

ይህ ከሆነ ከአምስት ዓመታት በኋላ፥ ከወንጌላዊ ካሣዬ ጋር አገር ቤት የሚተዋ ወቁ አራት ወጣት ከርስቲያኖች ለትምህርት ወደ ኢንግሊዝ አገር መጡ። እነርሱም ዶከተር ብርሃኑ ሀብቴ፥ ዶከተር ሚልከያስ ሻሜቦ፥ ወንድም (በኋላ ዶከተር) ተከሥተ ተከሉ እና እኅት ተናኘ ለማ ናቸው። እነዚህ በኢንግሊዝ ምድር የመጀመሪያውን ኮንፈረንሳቸውን በሚያዝያ ወር 1972 ዓ.ም. ለፈረን ጆቹ የትንሣኤ በዓል አደረጉ። ዶከተር ብርሃኑ ሀብቴን በዋቢነት ልጥቀስ፡-

> ዘመኑ 1980 ዓ.ም. ወቅቱም ደግሞ የጌታ ኢየሱስ ከርስቶስ ትንሣኤ የሚከበርበት ጊዜ ነበር። ይህንኑም በዓል ለማክበር ፕሬስተን በሚገኘው በወንድም እርገጤ እና በእኅት ሞሪን ቤት፥ በቤቱም ባለቤቶች አስተባባሪ ነት፥ ሁለት ወገኖች ከለንደን፥ አንድ ከበርሚንግሃም፥ አንድ ከማንቼ ስተር፥ እኔ እና ሌሎች ሁለት ወንድሞች ደግሞ ከግላስጎ፥ በድምሩ ዘጠኝ በመሆን ተገናኘን።[7]

በኮንፈረንሱ ላይ ካሣዬ፥ ሞሪን እና እርገጤ የነበሩ ከሆነ፥ ድምሩ ዶከተር ብርሃኑ እንዳለው ዘጠኝ ሳይሆን ዐሥር ነው የሚሆነው። ዶከተር ብርሃኑ ከላይ የተጠቀሰውን ምስከርነት በሰጠበት በዚያው መጽሔት ላይ፥ ወንጌላዊ ካሣዬ ደግሞ ለየት ያለ ምስከርነት ሰጥቷል። አንደ ወንጌላዊ ካሣዬ ከሆነ፥ ዘጠኝ ሰዎች የተገኙት በኮንፈረንሱ ላይ ሳይሆን፥ በፈረንጆቹ ጎዳር ወር እና በእኛው 1972 ዓ.ም. ውስጥ በነበረ አንድ የሳምንት መጨረሻ፥ በእነ ወንጌላዊ ካሣዬ ቤት በተደረገ ጎብረት ላይ ነው። በዚያ ጎብረት ላይ እኅት እጅጋየሁ በየነ የነበረች ሲሆን፥ በኮንፈረንሱ ላይ ደግሞ ወንድም መለሰ መርጊያ ነበረ።

የማንኛቸው ምስከርነት ነው ትከከል? የሚለውን ጥያቄ አላነሣም። የፈለግሁት ኢትዮጵያውያን ወደ ኢንግሊዝ አገር አየመጡ መሆናቸውን እና እየመጡ ያሉበትን ጊዜ ለማሳየት ነው። አየመጡ ባሉትም መካከል ወንጌላውያን ከርስቲያኖች መኖራቸውን እና እነዚህም በያሉበት መገናኘት መጀመራቸውን ለማመልከት ነው። በዚህችው መጽሔት ላይ ካገኘሁት የወንድም ጌታቸው ዘርጋው ምስከርነት ደግሞ አለፍ አለፍ ብዬ ልጥቀስ፡-

> እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር በ1981 መስከረም ወር ላይ (በእኛ 1974 ማለት ነው) በሳውዝፖርት እነ ወንድም ካሣዬ ደገፉ ስብሰባ ያደርጉ ስለ ነበረ እኔንም ጋብዘውኝ በዚያ ስብሰባ ላይ ተገኝሁ። በስብሰባው ላይ

የነበሩትና ትዝ የሚሉኝ እኅት ሞሪን ደገፉ፥ እኅት አብረኸት፥ እኅት ኪዳን እና ዶክተር አብርሃም ነበሩ።

... ከአገራችን እንደ መጣን አካባቢ ቀደም ብለን አገር ቤት የምናውቃቸውን ... አፈላልገን አግኝተን ነበርና ሌሎች ወገኖችን ጨምረው ሊጠይቁን እንኖርበት ወደ ነበረው ሪዲንግ ከተማ መጡ። ይህም የሆነው እንደ ኤውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1982 ይመስለኛል። በዚያም አብረን ጌታን አመሰገንን፤ ደለም አለን። በሪዲንግ እናመልከባት የነበረችው ቤተ ክርስቲያንም በታላቅ ፍቅር አስተናገደችን ...

ታዲያ አነዚያ በለንደን ያሉ ወገኖቻችን በመኖርያ ቤት ውስጥ በመገናኘት ጌታን ያመልኩ ነበር። ግን የሚለበሰቡት በየሣምንቱ ይሁን ወይም በየወሩ የማስታወሻ ማህደሬ አያስታውስም። የተረዳሁት ግን ሌሎች ወንድሞችና እኅቶች ከለንደን ውጭ እንዳሉና ሁሉንም የሚያገናኝ ስብ ሰባ በቅርቡ እንደሚደረግ ነበር። በዚያም ስብሰባ እንድንገኝ ተጠርተን ስለ ነበር ሄደን አገኘናቸው። በዚያም ጌታን አመሰገንን፤ ደስም አለን። ...

ብዙም ሳይቆይ "ታላቁ የኢትዮጵያ እረሃብ" በ1984-85 (በእኛ 1977-1978) በብዙኅን የመገናኛ መሣሪያዎች ሊነገር ጀመረ። በዚያን ጊዜ ለምን እየተገናኘን ለአገራችን አንጸልይም? በሚል አሳብ በተለያዩ ቤቶች እየተዘዋወርን መጸለይ ጀመርን። ከዚያም በ ... መሰብሰብ ጀመርን። ለአገራችን ለመጸለይ ታቅዶ የነበረው ስብሰባም፥ ለካ ሊመጣ ላለ፥ በጌታ አሳብ ውስጥ ለነበረ ሰውን የመድረስ ረኀቡም ዕቅዱ፥ ጥንስስ እንደ ነበረ አሁን ካለፈ በኋላ ማስተዋል ይቻላል።

የሎንዶን ቤተ ክርስቲያን ቀደምት ምዕመናን እንደ ወላጆቻቸው የሚያዩት ወንድም ጌታቸው ዘርጋውን እና ባለቤቱን ጽጌ ዘበርጋን ነው። ጌታቸው በነሐሴ ወር ኢጋማሽ 1973 ዓ.ም. ነው ኢንግሊዝ አገር የገባው። ትንሽ ቆይቶ ጽጌ እና ልጃቸው ማኅሌት መጡ። ጌታቸው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሩቅ እና በአገር ቤት ሳለ የማቴማቲከስ መምህር ነበረ። ከአገር ለመውጣት ሲያ ሰቡ፥ የጌታቸው እና የጽጌ ዕቅድ ወደ አሜሪካ ለመሄድ ነው የነበረው። ሆኖም፥ አቅደውት እንደ ነበረው ወደ አሜሪካ አልሄዱም። በሎንዶን ለመቅ ረታቸው ብቸኛው ምክንያት፥ በዚያ እየተጀመረ ያለው የእግዚአብሔር መንግ ሥት አገልግሎት ነበር።

ከሚያገኙአቸው ኢትዮጵያውያን ወንጌላውያን ከርስቲያኖች መካከል አብዛኞቹ የሚያጽናናቸው እና የሚያበረታታቸው ሰው የሚያስፈልጋቸው ዐይነት ናቸው። እማኞች ካይደሉትም መካከል ቢሆን፥ መንፈሳዊ ምክር እና የጸሎት ድጋፍ የሚሹት ይበዛሉ። በዕድሜአቸው ልጆች የሆኑ እና ተመልካችም በቅርብ የሌላቸው ሞልተዋል። እነዚህን ሁሉ ጥሎ ወደ አሜሪካ ለመሄድ ልባቸው እምቢ አላቸው። ጌታቸው "የተማሪ አገልጋይ"፥ ጽጌ ደግሞ እየሠራች የቤተ ሰቧ ደጋፊ ሆነች። ሁለት የእኅቷን ልጆችም ከአገር ቤት እስመጥታ ማሳደግ እና ማስተማር ጀመሩ። ሁለት መኝታ ቤት ባላት የመንግሥት አፓርትሜንት ቤታቸው ውስጥ ነው አምስት ሆነው የሚኖሩት። በዚያች ቤታቸው ውስጥ ግን ሌሎች እምስት ሰዎች ያህል እየተጨመሩ የሚያድሩባቸው ቀናት ጥቂት አልነበሩም።

ከአገር ቤትም ሆነ ከውጭ አገር ወደ ሎንዶን የሚሄዱ አበሾች የጌታቸው እና የጽጌ አድራሻ ነው የሚሰጣቸው። እንግዶቹን ተቀብሎ በቤታቸው ማሣረፍ፥ ከተማውን ማሳየት እና ማስለመድ፥ እየያዙአቸው በየሱቁ መዘር እና ዕቃ ማጋዛት፥ ተግባራቸው ነው። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ቤታቸው "ሪፐብሊክ" የሚል ሰም ወጥቶለታል። ሪፐብሊክ ማለት ንጉሥ ወይም ንግሥት የሌለበት፥ ሥልጣን ድምፅ መስጠት በሚችሉ ዜጎች ሁሉ እጅ የሆነበት ሥርዓተ መንግ ሥት ማለት ነው። ቃሉን በጣሙን ታዋቂ ያደረገው አፍላጦን ሲሆን፥ የተፈ ጠረውም "ሬ" = የሆነ ነገር፥ እና "ፐብሊካ" = የሕዝብ ወይም የጋራ የሚል ትርጉም ካላቸው ሁለት (የላቲን?) ቃሎች ነው። በእነ ጌታቸው ቤት ያለው ሁሉ የባለቤቶቹ እና የእንግዶቹ የጋራ መጠቀሚያ ነው ለማለት ነው። ለቤታ ቸው ይህንን ስም ያወጣችው ልጃቸው ወይዘሪት (በኋላ ዶክተር) ማኅሌት ጌታቸው ናት።

ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ፥ ጌታቸው ለረኀም ጊዜ ሥራ አላገኝም ነበር። አቅደውት እንደ ነበረው ወደ አሜሪካ ለመሄድ፥ ያም ካልሆነ ወደ አገራቸው ለመመለስ በብርቱ የተፈተኑበት፥ በጣም መጠነኛ የነበረውን ጓዛቸውንም ሸክፈው የተነሡበት ጊዜ ነበረ። ያንን ያደረጉት ግን በጣም በተከፈለ ልብ ነበር። ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን አደራ ምን ያድርጉት? በግላቸው እና ከሌሎችም ጋር በመሆን በዚህ ጉዳይ ላይ ወደ እግዚአብሔር ጮኽዋል።

"ሌሎች" ከተባሉትም መካከል አንዱ ይህ ጸሐፊ ነው። በመጨረሻም "አንተ አንደምታደርገን አድርገን አንጂ፥ መንጋህን በትነን የትም አንሄድም" ሲሉ ወሰኑ። ዛሬ በሺሆች የሚቆጠሩ ምዕመናን እና ከሁለት ደርዘኖች የሚበልጡ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በታላቋ ብሪታንያ አሉ። እናቲቱ ቤተ ክርስቲያን በመሐል ሎንዶን በራስዋ ካቴድራል ውሰጥ ታመልካለች። ሦስቱ ልጆቻቸው እራሳቸውን ችለዋል። ሪፐብሊኩም የግል ንብረታቸው ሆኗል።

ከናይሮቢ እና ከሎንዶን ያየናቸው ናሙናዎች ከሞላ ጎደል በሌሎች አገሮች እና በሌሎች ከተሞች የተመሠረቱትን የዳያስፖራ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ይወክላሉ። ዐቅሙ በኖረኝ እና ቢያንሰ ስለማውቃቸው ሁሉ በተረከሁ። በሁሉም ቦታዎች አግዚአብሔር ፈር ቀዳጅ አድርጎ ያስቀመጣቸው፥ የሚጸልዩ እና የሚ መሰከሩ፥ ሰዎች ነበሩ። በሁሉም ቦታዎች የአግዚአብሔርን ልጆች በብዙ መሥዋዕትነት አየተንከባከቡ የሚያሳድጉ ወንዶች እና ሴቶች ሞግዚቶች ነበሩ። አንደ አነ ዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል ያሉ "ቤቴን" እና "ምቾቴን" ሳይሉ በየአገሩ እየዞሩ ሕዝቡን የሚጎበኙ፥ የሚያሰተምሩ እና የሚመከሩ የበሰሉ አገልጋዮችም ነበሩ።

ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ

ሌላ ሸግግር፤ ሌላም ሻካራ። ሌላ ነውጥ፤ ሌላም ለውጥ። የኢትዮጵያውያኑ መበተን ከደርግ ዕድሜ ማከተም ጋር አብሮ አላከተመም። ልብ አንድንለው የምፈልገው ይህንን ነው። በኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥትም፥ ይኸው ለሃያ አንድ ዓመታት፥ እንዲያውም ተጠናክሮ ቀጥሏል። "ብሔረ ሰባዊነት" (ETHNI CITY) እና የፖለቲካ አለመቻቻል በሰበብ እሰባብነት ተደጋግመው ይጎዛሉ። ቀዳሚውን ሰፍራ የሚይዘው ግን ኤኮኖሚያዊው ሰደት ነው። የመካከለኛውን ምሥራቅ አገሮች እያጥለቀለቁ ያሉትን ኢትዮጵያውያት ያጤኗል። ትንቢቱም የሚለው "እበትናችኋለሁ" እንጂ፥ "እሳድዳችኋለሁ" አልነበረም። ሰደት ከመበ ተኖዎቹ መንገዶች አንዱ ብቻ መሆኑ ነው።

ብሪስቤን በምትባል የአውስትራልያ ከተማ ብርሃኔ ተድላ መርሃ የሚባል ወንድም አለ። በዚያ የሚኖሩት የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ወንጌላውያን ከርሰቲ ያኖች እንደ አባታቸው ነው የሚያዩት። ብርሃኔ በዕድሜው ሃምሳዎቹ አጋማሽ ላይ የሚገኝ የትግራይ ልጅ ነው። እንዲት እኅት እና ሦስት ወንድሞች ነበ

ሩት። አባታቸው ሲሞቱ ወንድሞቹን ለማሳደግ ሲል የራሱን ትምህርት አቋርጦ "የድኅማ አሰተማሪ" ሆነ። የኢትዮጵያ አብዮት ሲፈነዳ ትልቁ ወንድሙ "ኢዲዶ" (የኢትዮጵያ ዴሞከራሲያዊ ኅብረት?) የሚባለውን ፓርቲ ተቀላቀለ። አስከ ዛሬ ድረስ ያ ወንድሙ በሕይወት መኖሩን ወይም መሞቱን አያውቅም። "አንደ ወጣ ቀረ" ይላል። ምን ያድርግ? "ሞት" ለማለት አይመችማ። በጊዜው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የነበሩ ሁለት ወንድሞቹ ደግሞ ሕወሐትን ተቀ ላቀሉ። እና ሁለቱም በትግሉ ውስጥ ተሠውተ።

አርሱ በገበሬዎች አደራጅነት የመንግሥት ሠራተኛ ሰለ ነበረ፥ የኢሠፓ አባል መሆን ነበረበት። "በጊዜው አንደ እኔ ያለ የትግራይ ልጅ፥ ወይ ከዚህ ወይ ከዚያ ሳይሆን መኖር አይችልም ነበር" ይላል፥ የነበረውን ሁኔታ እያስታወሰ። ደርግ ሲወድቅ እና ኢሕአዴግ ሲገባ፥ ሊከተለው የሚችለውን ጣጣ በመፍራት ወደ ጂቡቲ ተሰደደ - ባለቤቱን ወይዘሮ ውብነሽን፥ ፋና እና ዕሌኒ ከሚባሉት ሁለት ሴቶች ልጆቹ ጋር አገር ቤት ትቶአቸው። በጂቡቲ አያለ ደግሞ፥ አንደ አርሱው ሸሽተው ጂቡቲ ከገቡ የደርግ ባለ ሥልጣኖች መካከል በአንድ ሁለቱ ላይ የመግደል ሙከራ አድርገሃል ተብሎ በጂቡቲ መንግሥት ተያዘ እና ታሰረ። "ከድጡ ወደ ማጡ" ይሏል ይኸ ነው። የደም ግፊት በሽታ ያዘው።

ብርሃኔ በታሰረበት ከፍል ውስጥ ታደሰ ኃ/ማርያም የሚባል ሌላ አስረኛ ነበር። ታደሰ የደርግ ደኅንነት ሠራተኛ ነው የነበረው። ደርግ ሲወድቅ ከአንድ የሥራ ባልደረባው ጋር በመሆን ከአዲስ አበባ ወደ ድሬ ዳዋ የሚበር የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ጠልፎ ነው ጂቡቲ የገባው። እና የጂቡቲ መንግሥት አው ሮፕላን በመጥለፍ ወንጀል ያዘው እና አሰረው። ታደሰ ብዙዎቻችን የምናው ቃት፥ ከቀድሞዎቹ "ጴንጤዎች" መካከል የሆነች፥ ወይን አሸት የምትባል አኅት አሰቸው። የእለግድ ሙላት ባልተቤት። በተደጋጋሚ ሰለ ጌታ ሲነገረው የኖረ ሰው ነበር ለማለት ፈልጌ ነው። ታደሰ ጅቡቲ ማረሚያ ቤት ሲገባ "ጴንጤ" ሆነ። ታደሰ መለከረለት እና ብርሃኔም ጌታን ተቀበለ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሕይወቱ ፈጽሞ ተለወጠ። ለዐሥር ወራት ከታሰረ በኋላ፥ እነዚያን የደርግ ባለ ሥልጣኖች ለመግደል በተደረገው ሙከራ ውስጥ እጁ አንደሌለበት በመረጋገጡ፥ በነጻ ተለቀቀ።

ብርሃኔ ሰለ ጌታ ቸርነት አውርቶ አይጠግብም። "እንድ ቀን ፓሰተር ባደግ በቀለ በሲሼልስ ሬድዮ ሲሰብክ ሰማሁት። ስብከቱን ሲጨርስ የሚያማቸው

ለዎች አብረውት እንዲጸልዩ ጠየቀ እና እኔም አብሬው ጸለይኩ። 190/130 የነበረው የደም ግፊቴ ወዲያውኑ ወደ 130/90 ወረደ" ይላል። እንደ ነገ ስለሚፈቱ እሥረኞች "ለማመስገን በተሰበሰብንበት፥ ጌታ በመንፈስ ቅዱስ አጠ መቀኝ" ይላል። እንድ ጊዜ፥ "ጌታ ሆይ! እኔ ወደ አገሬ ለመመለስ አልችልም፤ ባለቤቴ እና ልጆቼም ጀቡቲ መምጣት አይችሉም። እውለትራልያ የሚባል አገር ውሰደኝ እና በዘመኔ ሁሉ አገለግልሃለሁ ብዬ ተሳልኩ" አለኝ። አንድ ምሽት አራት ሆነን ስንጸልይ፥ "ስእለት የተሳልከ ሰው አለህ ... ጌታን እንዲህ አድርግልኝ እና እንዲህ አደርግልሃለሁ ያልከ ሰው አለህ ... በሰዓቱ አደርገዋለሁ ይልሃል" የሚል መልእክት መጣ አለኝ።

ጀቡቲ በገባ በአንድ ዓመት ከመንፈቅ፥ ከእሥር ቤት ከወጣም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይመስለኛል፥ ሁሉ ነገር አልቆ አውስትራልያ የገባው። ባለቤቱ እና ልጆቹም መጡለት። እርሱም እንደ ተሳለው፥ ጌታን በደለታ ያገለግላል። ሆኖም ግን ያዝናል። ዕድሜአቸው ከሰማንያ ዓመት በላይ የሆነ፥ "ብርነሽ ወልደ ማር ያም" የሚላቸው ወላጅ እናቱ አገር ቤት ናቸው። ሌላዋ ወላጅ እናቱ - ኢትዮጵያም - በብዙ ሺህ ማይል እርቀት ላይ ነው ያለችው። ሁለቱንም ሳያያቸው ከሐያ ዓመታት በላይ ሆኖታል።

በከተማ እና በገጠር እየተሠሩ ስላሉት መንገዶች፥ እየተገነቡ ስላሉት ሕንጻዎች፥ በአፋር ሳይቀር ለለ ተከፈተው ዩኒቬርሲቲ፥ ስለ ዕርሻው፥ ስለ ሕዳሴው ግድብ፥ ወዘተርፈ፥ እየደጋገመ ይጠይቀኛል። የማውቀውን እነግረዋ ለሁ። በጆሮቹ ብቻ አይደለም፤ ዕንባ ባቀረሩ ዐይኖቹም ጭምር ነበር የሚ ሰማኝ። ዛሬ ብርሃኔ ሕይወት ብዙ ያለተማረችው፥ እመለካከቱ ስማያዊ የሆነ ሰው ነው። ሁለቱንም እናቶቹን በጣም ይናፍቃል። ለመምጣት ግን ይፈራል ይመስለኛል። የብርነሽ አራተኛ ወንድ ልጅም እንደ ወጣ ሊቀር ነው ማለት ነው? እርሷም ሳታየው ልትሞት ነው ማለት ነው? እቤቱ! ምሕረት እለምናለሁ - ከእንተ፤ ከሰውም።

ፋና ብርሃኔ የዚምባቡዌአዊው የብሌሲንግ ጊጂማኒ ባልተቤት ናት። ፋና እና ባለቤቷ የብሪስቤኗ ሂልሶንግ ቤተ ክርስቲያን አባላት ሲሆኑ፥ በእሁሾቹ ቤተ ክርስቲያንም ውለጥ ያገለግላሉ። ስለ አፍሪቃ፥ በተለይም ለለ ኩሽ ነገድ (ኢትዮጵያ? ጥቁር አፍሪቃ?) አንሥተን ስንጨዋወት፥ ብሌሲንግ በመዝሙር 68፥31 ላይ የተመሠረተውን የዚምባቡዌአዊቷን የኦሲቭያ ቻራምባን መዝሙር

አሰማኝ። እንደ ጎርጎሳውያኑ አቆጣጠር ጥቅምት 30 ቀን 1998፥ በላቲን አሜሪካዊ አገር በጓቴማላ የተናገረችውን የሲንዲይ ጀኮብሰን ትንቢትም ሰጠኝ። ሲንዲይ ትንቢቱን የተናገረችው ከላቲን አሜሪካ አገሮች በተሰባሰቡ የጸሎት አገልጋዮች ጉባዔ ላይ ነበር። እንደሚከተለው ተርጉሜዋለሁ። በኢንግሊዝኛው ሲያነቡት ለሚፈልጉም፥ አሪጅናሉን በአባሪነት አለቀምጬላቸ ዋለሁ (አባሪ ሁለትን ይመልከቱ)።

> ወንዙ በዚምባቡዌ ውስጥ ሲፈስስ ነው፤ እና ጋይለኛ ፈረሰኛ ውሃ፥ ገስ ጋሽ የሆነ ፈረሰኛ ውሃ፥ ብዙ ዓሦችም አያለሁ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመከፋፈል ምሽጎች እንዳሉ እና የወንድሞች ከሣሽ ነፍሳትን ተሰፋ ለማስቆረጥ ሲተጋ እያለሁ። የዲቦራ ቅባት ያለበት የሴቶች ሠራዊት በም ድሪቱ ላይ የተምማል። በጸሎታቸው በሞላዋ ዚምባቡዌ ላይ እንደ መረብ ይሆናሉ። በጋይለኛ ቅባት ሴቶቹ ይቀድማሉ፤ ወንዶቹም ይከተ ላሉ። ከጥንት ጀምሮ የነበሩ ዙፋኖች፥ እሰከ ጎሣዎች ድረስ የሚወርድ ሥር የሰደደ የዘረኛነት መንፈስም ሲገረሰሱ፥ ጥቁሮች እና ነፎች ሲተራረቁ አያለሁ። ዚምባቡዌን እንደ ዕንቁ እጠቀምባታለሁ፤ በመል ካም ምርቶቿ ዓለምን ለመመገብ የበኩሏን እሰተዋጽዖ ታደርጋለች። በእርስ በርስ ጦርነት አማካይነት የመጣባትን እርግማን አግዚአብሔር ይሰብራል ... እርግማኑ ይሰበራል። (ስለ ዚምባቡዌ ምንም እላውቅም) መልካም የሥጋ ከብቶች ይደልቡባታል። እዳዲስ ፋብሪካዎች ይቋቋ ማሉ። ዚምባቡዌ አፍሪቃውያንን እንደ ገና አንድ የሚያደርግ የዕርቅ እገልግሎት አላት። የዕርቅ ቅባት በመላዋ ዚምባቡዌ ላይ ይሆናል። ወደ ኋላ እንደምትሄዱ ዐይነት ቢመሰልም እንኳን፥ ለውጡን አትፍሩት። እኔ ለእናንተ ዓለማ አለኝ። ሰይጣን እየተሳካለት እንዳለ ይመስለዋል፤ እኔ ግን በክፍተኛ ስፍራዎች ላይ ያለውን ከፋት እገልጣለሁ። አትፍሩ። ሰይ ጣን ጦርነት ሊያስነሣ ይሞከራል፤ ይኸ (የጸሎቱ) ሠራዊት ግን ጦርነቱን እና ደም መፋሰሱን ለማስቆም ያገለግላል። ከሌሎች አገሮች ጋር የጋራ ስምምነት ይደረጋል። ዚምባቡዌ እንደ ስዊትዘርላንድ ለአገሮች ፈውስ በማምጣት፥ የቀደሙ ነገሮችንም ለመስበር ታገለግላለች። አገራችሁ በደባ ውስጥ አልፋለች፤ አግዚአብሔር ግን ያድሳታል ...

በዚያ የጸሎት አገልጋዮች ጉባዔ ላይ ከዚምባቡዌ የመጣ ሰው የነበረ አይመለለኝም። እዎ! በአፍሪቃ መከራዎን ብዙ ነው። ሆኖም ለበጎ ነው። ትን

ቢቶቹ ሁሉ እንደዚያ ነው የሚሉት። ፍጻሜአቸውንም እያየን ነው - ቢያንስ ስለ ኢትዮጵያ የተነገሩትን። የዚምባቡዌውንም እንጠብቃለን።

እየተነሡ ያሉ ጥያቄዎች

"ስደት እርግማን እይደለም ወይ?" ብለው የሚጠይቁ ኢትዮጵያውያን አሉ - የሚያምኑም የማያምኑም፤ በአገር ውስጥም ከአገር ውጭም። ለምንድነው እንደ በረከት ተደርጎ የሚታየው? ይላሉ። አንድ ሰው ወደ ሆነ የውጭ አገር ለመሄድ ቪዛ ሲመታለት "እንኳን ደስ አለህ/አሰሽ" የሚባለው፥ የምስጋና ፕሮግራም የሚዘጋጀው፥ ስምንድነው? ይላሉ። እንደዚህ እንዲጠይቁ የሚያስገድዷቸው ሚዳዊም፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊም ምክንያቶች አሉ። እንደኛው ኢትዮጵያ ውያኑ በተሰደዱባቸው አገሮች (ባተሰይም በአንዳንድ የዓረብ አገሮች) ውስጥ እየደረሰባቸው ያለው ከፍተኛ አንግልት ነው። ሁለተኛው በአሪት ዘዳግም 28፥15-68 ውስጥ ከተዘረዘሩት እርግማኖች መካከል በተለይ በቁጥር 36-37 ላይ እንዳሉት ያሉቱ ናቸው። እንዳንዶች እንዲያውም እንደዚህ ዐይነቱን ስደት መንግሥት በሕግ ማስቆም አለበት እስከ ማለት ይደርሳሉ።

እንደዚህ ባለ፥ ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶችን በሚመለከት ጉዳይ ላይ፥ አስተያየት ለመስጠት እኔ ዕውቀቱ የለኝም። ሆኖም መንግሥት ዜጎቹ በብዛት በሚሄዱበት አገር ያለው ነባራዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል - በተለይም አሳሳቢ ሁኔታዎች ያሉ ከሆነ - ዜጎቹ ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ሊያውቁ የሚችሉበት መንገድ እንዲፈጠር ቢያደርግ ጥሩ ይመስለኛል። ሌላ ችግር ከሌለበት በስተቀር፥ አሰፈላጊ በሚሆንበትም ጊዜ ቶሎ ይደርስላቸው ዘንድ፥ ዜጎቹ በብዛት ከሚሄዱባቸው አገሮች መንግሥታት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ቢመሠርት ትም ጥሩ ነው። ከዚህ ባለፈ ግን፥ የሚሄዱበት አገር መንግሥት እስከ ተቀበላቸው፥ የመግቢያ እና የሥራ ፈቃድም እስከ ሰጣቸው ድረስ፥ ዜጎቹ የት መሄድ እንዳሰባቸው እና የት መሄድ እንደሌለባቸው መንግሥት ሊወስንላቸው የሚገባ አይመስለኝም።

ለመሆኑ ስደታችን እግዚአብሔር ያቀደው ነው ወይስ የፈቀደው? አቅዶት ከሆነ ለምን አቀደው? ፈቅዶትም ከሆነ ለምን ፈቀደው? ይኸ ከኹነቶች በስተ ጀርባ ያለውን ምክንያት ለመረዳት የሚሞከር ጥያቄ ነው። መልሱ ግን እንደ ጥያቄው ቀላል አይሆንልንም። ምክንያቱም ጉዳዩ ከእግዚአብሔር ሉዓላዊነት

እና ከሰው ነጻነት ጋር የተያያዘ ነው። ከኤኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ሁኔታዎችም ጋር ቁርኝት አለው። በተረፈ በዘዳግም 28 ውስጥ የተዘረዘሩት በረከቶች እና እርግማኖች በተለይ ለእስራኤል የተነገሩ ነበሩ። እነዚያን በረከቶች እና እርግማኖች ቃል በቃል ወስደን ለሌሎች አገሮች ልናውላቸው የምንችል አይመስለኝም። እንደ ከርስቲያን፥ ልንመራ የሚገባን በእግዚአብሔር መንፈስ ነው (ሮሜ 8፥14)። ወደ አሜሪካ መሄድ በራሱ በረከት፥ ወደ ዓረብ አገር መሄድም በራሱ መርገም ሊሆን አይችልም።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ስደት የሚለው ነገር አለ? አዎ፥ አለ። በመጀመሪያ ግን ስደትን እና ምርኮን እንለያቸው። ለምሳሌ ይሁዳ ለሰባ ዓመታት ወደ ከለዳውያን ምድር የሄደው ተሰድዶ አይደለም፤ ተማርኮ ነው። የተማረከውም ወድዶ አይደሰም፤ ተገዶ ነው። በከነዓን ምድር እረሃብ በሆነ ጊዜ አብርሃም ወደ ግብፅ ተሰድዷል (ዘፍ. 12፥10)። ያዕቆብም ስባ አራሱን ሆኖ ወደ ግብፅ ተሰድዷል። የተሰደደውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር (ዘፍ. 46፥2-4፥27)። በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ወላጆቹ ኢየሱስን ይዘው ወደ ግብፅ ተሰድደዋል (ማቴ. 2፥13-15)። ጌታ ደቀ መዛሙርቱን "በአንድ ስፍራ ሲያሳድዷችሁ ወደ ሌላ ሽሹ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ የእስራኤልን ከተሞች ሳታዳርሱ የሰው ልጅ ይመጣል" ብሏቸዋል (ማቴ. 10፥23)። እነርሱ ግን የሄዱት "እስከ ፈንቄ፥ እስከ ቆጵሮስና እስከ አንጾኪያ ..." ድረስ ነበር (ሐዋ. 11፥19)። ከእስራኤል ውጭ ማለት ነው።

> ... እያንዳንዱ የራሱን ውሳኔ ልብ ብሎ ይወስን" (ሮሜ 14፥5) ... "እንግዲያስ ስለ እነዚህ ነገሮች ያለህ እምነት በእንተና በእግዚአብሔር መካከል የተጠበቀ ይሁን፤ ትከከል ነው ብሎ በተቀበለው ነገር ራሱን የማይኮንን የተባረከ ሰው ነው (ሮሜ 14፥22)።

እነዚህ ጥቅሶች የሚናገሩት ስለ ስደት ባይሆንም፥ መርሕ ሊሆኑን የሚችሉ አሳቦችን ይዘዋል። አንደኛ፤ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ "ኃጢአት" በማይሳቸው እና አከራካሪ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ፥ እያንዳንዱ ከርስቲያን ለየራሱ ነው መወሰን ያለበት። እንደዚህ ባሉ ጉዳዮች ላይ የጅምላ ውሳኔ አይሠራም። የግል ውሳኔአችንም ቢሆን ግራ ቀኙን ያገናዘበ እና በጥንቃቄ የተደረሰበት መሆን ነው ያለበት። ሁለተኛ፤ ውሳኔአችን ሰላም የሚሰጠን መሆን አለበት። ማለትም የኅሊና ወቀሳ የሚያስከትልብን መሆን የለበትም።

በስደት ያሉትን የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በተመለከተ፥ ተደጋግሞ ሲነሣ የምስማው ሌላው ጥያቄ በብሔር መደራጀት ለምን ያስፈል ጋል? ከአገሬው ሕዝብ ጋር ተቀላቅለን፥ በየአገሩ ባሉት ነባር ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አባላት ሆነን ለምን እናመልክም? የሚል ነው። ይኸ ጥያቄ በ1960ዎቹ መጨረሻ ላይ በናይሮቢዋ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ተነሥቶ እንደ ነበረ እቶ ሙላቱ በላቸው አጫውቶኛል።

ቀደም ሲል በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ስማቸውን የጠቀስኩት አነዚያ የበለሉ አባቶች በጉዳዩ ላይ በጥሞና ካስቡበት እና ከተመካከሩበት በኋላ የደረሱበት ውሳኔ "ሁላችንም የአገሩ ሕዝብ በሚያመልከባቸው አብያተ ክርስቲያናት ቋሚ አባል መሆንም ሆነ በየዕሑዱ እየተገኘን አብረን ማምለክ አንችላለን። ነገር ግን የራሳችን የሆነ ጎብረት ደግሞ ሊኖረን ያስፈልጋል" የሚል ነበር። እንደዚህ አንዲወለኑ ያስገደዳቸው ዋናው ምክንያት ቋንቋ ነው። ኬንያውያኑ ያሚያመል ኩት ወይ በኢንግሊዝኛ፥ አለዚያም በኪስዋሂሊ ነው። ከኢትዮጵያውያኑ ስደተ ኞች መካከል ደግሞ አብዛኞቹ ኢንግሊዝኛ የሚይስሙ ሲሆኑ፥ አንዳቸውም ኪስዋሂሊ አይችሉም።

ከአገሬው ሕዝብ ጋር አብረው መዘመር እንዴት ይችላሉ? የሚነገረውን ቃለ አግዚአብሔርስ እንዴት ይስማሉ? ለሚጸለየውስ ጸሎት እንዴት አሜን ይላሉ? ስደቱ ከጀመረ አሁን ሠላሳ አምስት ዓመት የሞላው ቢሆንም፥ በብሔር ለተደ ራጁት አብያተ ክርስቲያናት አሰከ ዛሬም ድረስ እንደዚያው መቀጠል ዋነኛው ምክንያት ቋንቋ ነው። ለምን? ቢባል እንደኛ ከላይ እንዳነሣነው፥ መበተኑ ተጠ ናክሮ ቀጥሏል። ሁለተኛ ዛሬም ቢሆን ወደ ውጭ አገሮች ከሚፈልሰው ኢትዮ ጵያዊ መካከል አብዛኛው የሚሄድበትን አገር ቋንቋ በቅጡ እያውቀውም።

ይህ እደረጃጀት ስደተኛውን ጎብረተሰብ በወንጌል ለመድረስ አጅግ ጠቅሟል የሚል ሌላ መከራከሪያ ነጥብም አለ። በብዙዎች ግምት በዳያስፖራው ወንጌላ ውያን አብያተ ክርስቲያናት ካሉት ምዕመናን ውስጥ አስከ 90% የሚሆኑት ከአገር ከወጡ በኋላ ወደ እምነቱ የተጨመሩ ናቸው። አጎዙ ከዚህ ይብለጥም ይነስም፥ አብያተ ክርስቲያናቱ በብሔር ባይደራጁ ኖሮ የዚህን ያህል ዕድገት ማስመዝገብ ይችሉ ነበር ወይ? የሚለው ጥያቄ አብሮ መጠየቅ አለበት። እውንም በጥናት ላይ የተመሠረተ መልስ የለም። ሆኖም የብዙዎች ግምት

ከአገር ቤት ሲወጡ እማኞች የነበሩት ኢትዮጵያውያን በየሄዱባቸው አገሮች ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ገብተው፥ ተበታትነው እና ተውጠው ቀር ተው ቢሆን ኖሮ፥ ለዚህን ያህል ሕዝብ ሊተርፉ በፍጹም አይችሉም ነበር የሚል ነው። እንዳንዶች እንዲያውም፥ እንኳን ለሌሎች ሊተርፉ አብዛኞቹ የራሳቸውንም ሕይወት ጠብቀው ለማቆየት አይችሉም ነበር ይላሉ።

ይህም ደግሞ እውነት ነው። ከአገራቸው ለመጀመሪያ ጊዜ፥ ለዚያውም በስደት፥ የወጡ ሕዝብ ናቸው። እንዳንዶቻቸው ከአገር ቤት ሲወጡ ከእንድ ሞት ያመለጡ ቢሆኑም እንኳን፥ በመንገድ ላይ ግን ሁለት እና ሦስት ሞት ያጋጠማቸው አሉባቸው። ፍርሃቱ እና ሥጋቱ፥ ድንጋጤው እና ግራ መጋባቱ ገና እልለቀቃቸውም። ያልተሟሉ አካላዊ እና ሥነ ልቦናዊ ፍላጎቶች አሏ ቸው። ከሁሉም ይልቅ የልባቸውን የሚነግሩት፥ የሚሰማቸው እና የሚረዳ ቸው ሰው የሚፈልጉ ሆደ ባሾች ናቸው። በቅጡ በማይሰሙት እና በቅጡም በማይናገሩት ቋንቋ እግዚአብሔርን እያመለኩ ለምን ያህል ጊዜ በሕይወት መቆየት ይችላሉ? መንፈላዊውን እና ሥነ ልቦናዊውን ሐሩር፥ አረሃብ እና ጥም፥ ነፍሳቸው እስከ መቼ መቋቋም ትችላለች?

በምድር ላይ እንዳለ አንደ ማንኛውም ጉዳይ፥ በብሔር የመደራጀትም ጉዳይ አዎንታዊ ብቻ ሳይሆን፥ አሉታዊ ጎኖችም እንዳሉት ብዙዎች ይስማማሉ። መፍትሔው አሉታዊ ጎኑ ከአዎንታዊ ጎኑ ጋር እንዳይተካከል፥ ይልቁንም በተቻለ መጠን በጣም እነስተኛ እንዲሆን፥ ማድረግ ነው ይላሉ። ከአሰከ አሁኑ ተሞክሮአቸው በመነሣትም፥ የመቀላቀል ነገር በመጀመሪያው ትውልድ ስደተኛ (FIRST GENERATION DIASPORA) ዘመን የማይሞከር፤ በሁለተ ኛው ትውልድ ስደተኛ ዘመን ግን የማይቀር ነው ይላሉ። ከአውሮፓ እና ከእስያ ወደ አሜሪካ የፈለሰውን የመጀመሪያ ትውልድም በምሳሌነት ይጠቅ ሳሉ። ጀርመኖች፥ ስዊድኖች፥ እርመኖች፥ ቻይኖች፥ ወዘተርፈ፥ መጀመሪያ ላይ እንደ እኛው ነበሩ። ለብቻቸው፥ በቋንቋቸው ነበር የሚያመልኩት። ዛሬ ግን ልጆቻቸው እና የልጅ ልጆቻቸው በጥሩ ሁኔታ ተቀላቅለዋል ይላሉ።

በሥነ መለኮቱም ሳይቀር

ሽግግሩ ሻካራ የሆነው በመንፈሳዊውም ረገድ ጭምር ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካጋጠሚት ውስጣዊ ተግዳሮቶች ሁሉ እጅግ የከበዳት በዴሞክራ

ቲከ ሥርዓተ መንግሥት ውስጥ መኖር፣ ማምለክ እና ማገልገል ሳይሆን አይቀርም። ፍቅሯ፣ እንድነቷ እና ጎብረቷ የተፈተነው፣ በፈተናውም አይወድቁ እወዳደቅ የወደቀቸው በዘውዳዊው ወይም በጎብረተሰባዊው ሥርዓተ መንግሥት ዘመን አይደለም። በዴሞክራሲያዊው ሥርዓተ መንግሥት ዘመን ነው። ይህንን የምለው ስለ ወንጌላውያኑ እብያተ ክርስቲያናት ብቻ አይደለም። ስለ "ብሔራዊዋ" ቤተ ክርስቲያንም ጭምር ነው። ለዚህ ነው "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን" ያልኩት። እነዚያ ቀድሞውንም ቢሆን፣ ከሞላ ጎደል፣ በስደት ላይ ነበሩ። ይህችኛዋ ግን እስከ ዛሬ ድረስ ተዘልላ ነበር የኖረችው። እንዴት እንደ ዚህ ሊሆን ቻለ? መቼም ምክንያቶች አሉ።

እንደኛ፤ ዴሞክራሲይ ለኢትዮጵያዊ እንግዳ የሆነ ሥርዓት ከመሆኑ የተነሣ ይመስለኛል። ቃሉ እና ትርጓሜው በብዙዎች ዘንድ፣ በተለይም ደግሞ በተማ ረው ከፍል ዘንድ፣ በደንብ ይታወቃሉ፤ ይወደዳሉም። የማኅበራዊ ሊቃውንቱ ጥሩ አድርገው ሊፈትቱት እና ሊያብራሩት ይችላሉ። "ሊፈትቱት እና ሊያብራ ሩት ይችላሉ" ማለት ግን እነርሱ እራሳቸው ጥሩ ዴሞክራቶች ናቸው ማለት ላይሆን ይችላል። ባይሆኑም ደግሞ ልንፈርድባቸው አይገባም። ከየት አምጥተ ውት ጥሩ ዴሞክራቶች ይሆናሉ? በባህላችን ውስጥ የሌለ ነገር! ያላደግንበት፣ ያልኖርንበት፣ ያልተቃኘንበት ነገር! የእኛው ምን ተብሎ እንደሚጠራ ሞያዊ ስያሜውን አላውቀውም፤ ይኸ "እኔ ያልኩት ካልሆነ" ብለን ድርቅ የምንለው ነገር፤ እሳቦቹን ጥለን ባስ እሳቦቹን ጥምድ የምናደርገው ነገር፤ እና የመሳሰለው።

ሁለተኛ፤ በቀደሙት ሁለት ዘመነ መንግሥቶች እማኞች የነበሩ ሰዎች፣ "ያኔ በመካከላቸው በሙላት እንደ ነበረ እና ዛሬ ግን ፈጽሞ እንደሌለ" የሚመ ስከሩለትን "ፍቅር እና እንድነት" በተመለከተ፣ መለስ ብለን እንደ ገና ልናጤነው የሚገባ ነገር ያለ ይመስለኛል። ያኔ ፍቅር እና እንድነት አልነበሩም እንልም። እንዳንዶቻችን በትንሹም ቢሆን እይተነዋል። ያላየነውም ብንሆን "የወይን ምስከሮቹን" ለማስተባበል እንሞክርም። እንድ ነገር ማለት ግን በእርግጥ እንችላለን - ያ ፍቅር እና እንድነት የተፈተነ አልነበረም። ከእግዚአ ብሔር ነበረ? አዎ! ንጹሕ ነበረ? ምን ጥያቄ አለው! ውብ ነበረ? ያለ ጥርጥር! ሆኖም ግን፣ ገና ያልተፈተነ እና ስለዚህም ያልበሰለ ነበረ። በዕውቀት ላይ የተመሠረተ አልነበረም ማለቴ ነው። ሰዎቹ እኮ አሁንም አለን። ያኔ የነበረው

ሁኔታ ነው እሁን የሌለው። ፍቅራችን እና እንድነታችን ነው ከሁኔታው በላይ መሆን ያቃተው። ለምን እቃተው? ቀድሞውኑ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ስላልነበረ ይመስለኛል።

ለዚያ ፍቅር እና እንድነት እስተዋጽዖ ያደረጉ ምክንያቶችም ነበሩ። እንዱ የምዕመናኑ ዕድሜ ነው። ምዕመናኑ ወጣቶች ነበሩ። በመንጋ እብሮ መንጎድ ከጎልማሶች ይልቅ ወጣቶች እንደሚቀልላቸው ለማወቅ የሥነ ልቦና ባለ ሞያ መሆን የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ሌላው የምዕመናኑ ቁጥር ነው። ምእመ ናኑ ጥቂቶች፣ እንዴ በጣም ጥቂቶች፣ ነበሩ። በስም፣ በአድራሻ ይተዋወቃሉ። ይገናኛሉ፤ ይጠያየቃሉ። የሆነውን እና እየሆነ ያለውን ነገር ሁሉም ያውቃሉ ማለት ይቻላል። በሚሆነውም ነገር ሁሉ ውስጥ፣ ከሞላ ጎደልም እንኳን ቢሆን፣ ሁሉም ይሳተፋሉ።

እሁንም ሌላው የጊዜው ሁኔታ ነው። ጊዜው የነጻነት - እንድ ሰው ከመንጋው ተለይቶ በግሉ ብዙ ማድረግ የሚችልበት - አልነበረም። ጊዜው የስደት እና የመከራ ነበረ። መከራ ደግሞ - በተለይም የጋራ የሆነ መከራ - መከረኛቹን ያስተሳስራል። እሁንም ሌላው የወቅቱ "መንፈሳዊ ከባቢ እየር" (SPIRITUAL ATMOSPHERE) ሁኔታ ነው። በወቅቱ የነበረው መንፈሳዊ ሁኔታ "የሁል ጊዜው" (NORMAL) እልነበረም። ወቅቱ የ"መንፈሳዊ መነቃቃት" (REVIVAL) ነበረ። በሪቫይቫል ወቅት በሰው ሕይወት የሚሆነው አብዛኛው ነገር "ልዕለ ተፈጥሯዊ" (SUPERNATURAL) ነው - ጸሎቱ ቢባል፤ መዝሙሩ ቢባል፤ ምስከርነቱ ቢባል። የሪቫይቫል ጊዜ፣ ከሌላው ጊዜ ይልቅ፣ እግዜእብ ሔር ለሰዎች የሚገኝበት ጊዜ ነው፤ እግዚአብሔር ወደ ሰዎች የሚቀርብበት ጊዜ ነው (ኢሳ. 55፣6)። ከላይ የጠቀስኳቸው እነዚህ እራቱም ሁኔታዎች ዛሬ የሉም።

ሦስተኛ፤ ግሎባዊነት። ዓለሚ መንደር መሆኗ። ከእኛ ወደ ሌሎች የሚሄዱት እና የሚመጡት፣ ከሌሎችም ወደ እኛ የሚመጡት እና የሚሄዱት ቁጥር እጅግ መጨመሩ። የትም ሳንሄድ፣ እዚሁ ሆነን፣ የትም የሚሆነውን መስማት እና ማየት መቻላችን። የሳተላይት ቴሌቪዥን እና የኢንተርኔት እገልግሎት ተጠቃ ሚዎች መሆናችን። ሰብዙ እዳዲስ እስተሳስቦች እና እደራረጎች መጋለጣችን። ይህንን እና ይህንን የመሳሰለውን ነገር ነው ግሎባዊነት ያልኩት።

ይህ ታዲያ አዲስ ነገር ነው አንዴ? እንደዚህ ያለ ነገር ቀድሞስ አልነበረም እንዴ? ከቶውንስ እንደዚህ ያለ ነገር ያልነበረበት ዘመን ነበረ እንዴ? ሊባል ይችላል:: መልሱ ባጭሩ "እንደዚህ ያሰ ዘመን አልነበረም" ነው:: ይህ ዘመን፥ ከነስሙ፥ "ዘመነ መረጃ" ነው የሚባለው - በዓለሙ ሁሉ:: "ኢንፎርሜሽን" አዎን ቀድሞም ነበረ፤ "ዘመነ ኢንፎርሜሽን" ግን አልነበረም::

እኛ ኢትዮጵያውያን ስለ እንድ ነገር የምንስማው እና የምናውቀው ነገሩ ከሆነ ከረዥም ጊዜ በኋላ ነበር:: ተማሪ ቤት ገብተን እና ተምረነው ወይም በመጻሕፍት ተጽፎ እንብበነው ነበር:: አሁን ግን በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ ሳናልፍ፥ ነገሩ ሲሆን ወዲያው እንሰማዋለን:: ነገሩ ሲታወቅ እኛም ወዲያው እናው ቀዋለን:: ተማሪ ቤት መማባት፥ የመጻሕፍትን ገጾች ማገላበጥ ሳይኖርብን፥ አንማረዋለን::

የሁሉም ኢትዮጵያዊ መረጃ የማግኘት ዐቅም እዚህ ደረጃ ላይ አለመድረሱን አላጣሁትም:: ሆኖም አሁን እየተንደረደርንበት ባለው ፍጥነት ከቀጠልን (አለመቀጠልም የምንችል አይመስለኝም)፥ የጥቂት ዓመታት ጉዳይ ነው የሚሆነው:: መሠረታዊ የከርስትና ትምህርት ቢሆን፥ የደቀ መዝሙርነት ትምህርት ቢሆን፥ የአገልግሎት ትምህርት ቢሆን፥ ሌላ ሌላውንም ቢሆን፥ ምዕመናኑ ሁሉንም ከዚያው ያገኙታል - ከሳቴላይት ቲቪው እና ከመረጃ መረብ::

ለምሳሌ ስለ "ለቀቅተኛ" (LIBERAL) ሥነ መለኮት ለመሰማት ብዙ ዓመታት ወስዶብን ነበር:: ስለ "ነጻነት" (LIBERATION) ሥነ መለኮት ለመስማት እና ለመተግበር ግን የዚያን ያህል ብዙ ዓመታት አልወሰደብንም:: በቋንቋ ዙሪያ በመካከላችን ዐልፎ ዐልፎ የተከሠቱት አለመግባባቶች የዚያ ውጤቶች ናቸው:: ስለ "ዐውዳዊ" (CONTEXTUAL) ሥነ መለኮት ለመሰማት እና ለመ ሰበክ ምንም ያህል ጊዜ አልወሰደብንም:: ደሆቹን የአፍሪቃ ምዕመናን በተመለ ከተ፥ "የብልጽግና ወንጌል" የሚባለው ከዚህ ጎራ ሊፈረጅ ይችላል:: "ትንቢ ታዊ" (PROPHETIC) ሥነ መለኮት የሚባለውንም ለመሰበክ ጊዜ አልወሰደብ ንም:: ቤተ ከርስቲያን፥ አንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት፥ ለሕዝብ እና ሰመንግሥ ታት ሁሉ "ትንቢታዊ ድምፅ" (PROPHETIC VOICE) መሆን አለባት ሲባል ብዙ ጊዜ የምንስማው በዚህ ምክንያት ነው:: ስለ "ሴቴአዊ" (FEMINIST) እና ስለ "መግዛት" (DOMINANCE) ሥነ መለኮትም፥ ልንስማ ጀምረናል::

የሚዛናዊነት ያለህ!

የምንለማው እና የምናየው ሲበዛ፥ ሸግግሩም አብሮ ይበዛል:: ሸግግሩ ሲበዛ፥ ሻካራውም አብሮ ይበዛል:: ሸግግሩን ማለቅም እንደማንችል ሁሉ፥ ሻካራነቱ ንም ቢሆን ማለቀረት አንችልም:: ሻካራነቱ ጨርሶ የማይለማቸው ቢኖሩ፥ እነርሱ ምናልባት የወቅቱ ትውልድ አባላት ብቻ ይሆናሉ:: ሻካራነቱ ለእነርሱ የማይሰማቸው ማነጻጸሪያ ስለ ሌላቸው ነው:: የሚያውቁት ይህንኑ ያሉበትን ወቅት ብቻ ስለ ሆነ ነው:: አባቶች እና እያቶች የሆኑት ግን፥ "እዬ ዱሮ!"፥ "እዬ በእኛ ዘመን!" ማለታቸው አይቀርም:: ነጮቹም እኮ "THE GOOD OLD DAYS" ይላሉ:: እንደዚያ ሲሉ ግን OLD DAYS ሁሉ፥ GOOD DAYS ነበሩ ማለታቸው አይደለም:: በአገራችን "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" እንደሚባለው ነው:: ማታው "እንኳን ዶሮ፥ የሰም ሽሮ" የሚባልበት እንደሚሆን በቅድሚያ እየታወቀም:: ይኸ እንዲያው የአነጋገር ፈሊጥ ነው - ሚዛናዊነት የጎደለው ፈሊጥ::

እንደዚህ ማለት ግን ሻካራውን ያነሰ ሻካራ ማድረግ አንችልም ማለት አይደ ለም:: ሻካራውን ያነሰ ስለ ማሻከር እንጂ ስለ ማለሰለስ የማልጽፈው ሆነ ብዬ ነው:: ሻካራውን "ለስላሳ" ማድረግ የሚደረሰበት ግብ አልመሰልህ ሰለሚለኝ ነው:: በመሠረቱ ለፍጹምነት መሥራት እና ከራስም ሆነ ከሌሎች ፍጹምነትን መጠበቅ ጥቅም እንዳለው ይገባኛል - በደረሰንበት አረከተን እና እጆቻችንን አጣጥፈን እንዳንቀመጥ ያነሣሣናል:: ሆኖም አውነታው እሱ ብቻ እንዳይደለ አለመዘንጋትም ደግሞ ያስፈልገናል - በራሳችንም ሆነ በሌሎች ተሰፋ እንዳንቆ ርጥ ይረዳናል:: "... ከፊቴ ወዳለው አዘረጋለሁ" ያለው ሐዋርያ ነው፥ እንደዚያ ያለበት ቀለም ሳይጠፍፍ፥ "... ሆኖም በደረስንበት በዚያ እንመላለስ" ደግሞ ያለው (ፊል. 3፥13፥16):: እና ወደ ፊት በመዘርጋት እና በደረሰንበት በመመ ላለስ መካከል ሚዛናዊነት ያስፈልገናል::

ሁለተኛ፤ ሚዛናዊነትን መጠበቅ ያለብን በሁለት አገሮች ዜግነታችንም መካከል ነው:: በምድር ላይ መኖራችን እና የእንዲት ምድራዊት አገር ዜጎች መሆናችን ምንም ጥያቄ የሌለበት ነገር ነው:: ከከርስትና ጋር አብሮ ሩጫ ጀምሮ የነበረው "ኖስቲሲዝም" የተባለ የግሪከ ፍልስፍና መንፈስን ከሥጋ ለመለየት በኃይል ነበር የሮጠው:: ምንም እንኳን "መንፈስ ነን" የሚሉ "አልስሜ" ከርስቲያኖች ዛሬም ያሉ ቢሆንም፥ ፍልስፍናው ግን ሩጫውን ጨርሶ ሜዳውን ከለቀቀ

ቆይቷል። አሁን አሁን ደግሞ "ሥጋዊ " እና "ምድራዊ" ብቻ ሊያደርጉን ከመሸ ወዲያ ሩጫ የጀመሩ ትምህርቶች ያንጎተቡናል። የእነዚህኞቹን ትምህርት እን ዳንድ ጸሐፍት "ምድር ተኮር" ይሉታል። ሆኖም እኛ የምድራዊት አገር ዜጎች ብቻ እይደለንም። "... አገራችን በሰማይ ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም እዳኝ፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን" (ፊል 3፥20)።

ከየመድረኩ ከምንሰማቸው አንዳንድ ትምህርቶች፥ በገባያ ላይ እየዋሉ ካሉትም አንዳንድ መጻሕፍት የምንረዳው፥ በምድራዊው ዜግነታችን እና በሰማያዊው ዜግነታችን መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቅ ለብዙዎቻችን ቀላል አለመሆኑን ነው። አሁን ደግሞ ምድርን "የመግዛት ሥነ መለኮት" የሚያቀነቅኑ መምህራን ብቅ ብቅ እያሉ ናቸው። "ወንድሞች ሆይ፤ ሐሳቤ እንዲህ ነው፤ ዘመኑ እጭር ነው፤ ከአንግዲህ ሚስት ያላቸው እንደሌላቸው ሆነው ይኑሩ። የሚያለቅሱ እንደማያለቅሱ፥ ደስተኞች ደስ እንደማይላቸው ይሁኑ፤ ዕቃ የሚገዙም የገዙት ነገር የእነርሱ እንዳልሆነ ይቁጠሩ፤ በዚህ ዓለም ነገር የሚጠቀሙም እንደ ማይጠቀሙበት ይሁኑ፤ የዚህ ዓለም መልክ ዐላፊ ነውና" (1ቆሮ. 7፥2-31)። ይህ ለማንኛችንም ቢሆን ቀላል "አያዎ" (PARADOX) እይደለም።

"አያዎ" - እንደ "መቼት" - በቅርብ ጊዜ የተፈጠረ የእማርኛ ቃል ነው። ሁለቱም የሁለት ሁለት ቃላት ጥምሮች ናቸው። አያዎ የ"አይ" እና የ"እዎ"፥ መቼት ደግሞ የ"መቼ?" እና የ"የት?"። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያለው አያዎ ምንድ ነው የሚለን? አናግባ? አዎ! ሙሉ ልቦችንንስ ትዳራችን ላይ እንጣለው? አይ! አናልቅስ? ማልቀስ ካለባችሁ፥ አዎ! በጎዘንስ አንቆራመድ? አይ! ደስ ይበለን? አዎ! በደስታስ እንፍነከነክ? አይ! ለኑሮ የሚያስፈልጉንን ነገሮች አንግዛ? አዎ! ነፍሳችንስ ከንብረታችን ጋር ትጣበቅ? አይ! በዚህ ዓለም ውስጥ በሚገኙ፥ ለሰው ጠቃሚ በሆኑ ነገሮች ሁሉ እንጠቀም? እዎ! ሆኖም ግን ...

ይህ አያዎ ለምን አስፈለገን? አነዚህ ሁሉ የምድር፥ የዚህች ዓለም መልክ፥ ስለ ሆኑ ነው። የዚህች ዓለም መልክ ደግሞ ዐላፊ ስለ ሆነ ነው። "ክርስቶስን ተስፋ ያደረግነው ለዚህች ሕይወት ብቻ ከሆነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ የምናሳዝን (በቀ.ኃ.ሥ. ትርጉም 'ምስኪኖች') ነን" (1ቆሮ. 15፥19)።

ሦስተኛ። በአስተምህሮ እና በኑሮ መካከል ሚዛናዊነት ያስፈልገናል። "ራሴላስ የአበሻ መስፍን"[3] በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ራሴላስ እና ኢምላከ የተባሉ ሁለት ምናባዊ ገጸ ባሕርያት አሉ። ራሴላስ ካለባት ከልል በስተቀር ስለ

ውጭው ዓለም እንዳች የማያውቅ መስፍን ነው። ሆኖም በውጭ ስላለው በጎ እና ክፉ ብዙ የሕይወት ተሞክሮ ካለው ከኢምላከ የለማው ነገር፥ የውጭውን ዓለም ለማወቅ ብርቱ ፍላጎት አላደረበት። በኢምላከ መሪነት፥ ራሴላስ በተድላ እና በደስታ ከሚኖርባት ጠባብ ዓለሙ፥ ብዙ ወርቅ ይዞ፥ ከአጎቱ ከኒቅያ ጋር ይጠፋል። አሁን በግብፅ ይገኛሉ። ከዕለታት አንድ ቀን ራሴላስ በመንገድ ላይ ሲሄድ፥ በተከፈተው ደጅ እንዲገቡ ሰውን ሁሉ የሚጋብዝ ማስታወቂያ ያለበት ሰፊ እዳራሽ ያይ እና ዘው ይላል። አንድ ሰው በተለያዩ የሕይወት ተሞክሮዎች ላይ ትምህርት እየሰጠ ነበር።

ራሴላስ በትምህርቱ እጅግ ይመሰጣል። በር ላይ ይጠብቀው እና መምህሩ ሲወጣ፥ አንደ እርሱ ያለውን "የእውነተኛ ጥበብ ባለቤት" የሆነ ሰው ለመገብ ኘት እንዲፈቀድለት በትህትና ይጠይቃል። መምህሩ ጥያቄውን ላለመቀበል ባንገራገረ ጊዜ፥ ራሴላስ አንድ ከረጢት ወርቅ እጁ ላይ ያስቀምጥለታል። መም ህሩ የራሴላስን ስጦታ ደስታ እና መገረም በተቀላቀሉት ስሜት ይቀበላል። ከኢምላከ ጋር ሲገናኙ፥ ራሴላስ ለማወቅ የሚያስፈልገውን ሁሉ ሊያስተምረው የሚችል መምህር ማግኘቱን፥ ይህንን ሰው መሪው ሊያደርገው እና እርሱም ደቀ መዝሙሩ ሊሆን መወሰኑን ይነግረዋል። ኢምላከም "የሞራል መምህራንን ለማመንም ሆነ ለማድነቅ አስቲ አትቸኩል፤ እነርሱ ሲናገሩ አንደ መላአከት፥ ሲኖሩ ግን እንደ ሰው ነው" ይለዋል። ይህችን እባባል ፍለጋ ነው ይህንን ሁሉ መንገድ የዞርኩት።

በመንፈሳዊው መስክ፥ እንደ ራሴላስ እና አንደዚያ መምህር የመሳሰሉ ብዙ ሰዎች አሉ - ቂሎች እና የሚያቄሏቸው ሰዎች ማለቴ ነው። በአገራችን "ከመጠ ምጠም መማር ይቅደም" ይባላል። ምን ማለት ነው? ሳትማሩ እትጠምጥሙ፥ "መምሩ" (መምህሩ) እትባሉ ማለት ነው። ጥሪው አንኳን ቢኖራችሁ፥ ሳት ማሩ እና በቂ ሊባል የሚችል ያህል የውስጥ እና የውጭ ዝግጅት ሳይኖራችሁ፥ በሆነ ስም - ወንጌላዊ፥ መጋቢ፥ ነቢይ፥ ሐዋርያ፥ ቢሾፕ፥ ወዘተርፈ፥ - ለመጠ ራት እትቸኩሉ ማለት ነው። የጠመጠመ ሁሉ የተማረ አይምሰላችሁ ማለ ትም ነው። ምከሩ ለሚያቄሉት ብቻ ሳይሆን፥ ለቂሎቹም ጭምር ነው። እንደ ኢምላከ ያሉ መካሪዎችን አያሳጣን። ከፍተኛው ኃላፊነት ያለው ግን በመምህራኑ ላይ ነው - የሚያስተምሩትን ይኑሩ። ባሕርያቸው ማዕረጋቸውን ይመጥን።

ሚዛናዊነትን በተመለከተ ላነሣው የምፈልገውን የመጨረሻ ነጥብ፥ "የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል" የሚለው የእገራችን ተረት ጥሩ አድርጎ ይገልጽልኛል። የረጋ ወተት ቅቤ እይወጣውም። ይህ ተረት እውነት እይደለም። ይህንን ተረት እውነት ነው ብዬ፥ እንዴት ተቀብዬው እንደ ኖርኩ እገረማለሁ። የተናጠ ወተት ነው ቅቤ የሚወጣው። አይ፥ የተናጠ ወተትም ቅቤ እይወጣውም። እና? እናማ ቅቤ የሚወጣው የረጋ እና የተናጠ ወተት ነው። "የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል" ለንል፥ ግማሽ እውነት ነው የተናገርነው። "የተናጠ ወተት ቅቤ ይወጣዋል" ብንልም፥ ግማሽ እውነት ነው የተናገርነው። ሙሉው እውነት "የረጋ እና የተናጠ ወተት ቅቤ ይወጣዋል" የሚለው ነው። በብዙ ረገድ፥ ግማሽ እውነቶች በየግላችን እና በየቤተ ክርስቲያናችን ሞልተዋል።

አብያተ ክርስቲያናት የቆየው፥ የደለበው፥ ባህላቸው እና ወጋቸው (TRADITION) የሚያስፈልጋቸው ቦታ እና ሁኔታ ሊኖር ይችላል። የማንነታ ቸው መገለጫ ነውና። ከዚያ የበለጠ ግን፥ አብያተ ክርስቲያናት ተሐድሶ ያለፈ ልጋቸዋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር የእንድ ትውልድ ብቻ ሳይሆን፥ የትው ልዶች ሁሉ አምላክ ነውና። ጌታ ኢየሱስ ያስተማረበት ቋንቋ አስራኤላውያን በጊዜው ይናገሩበት የነበረው አራማይስጥ ነበር። "አባቶቹ" የተናገሩበት እና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉበት የዕብራይስጥ ቋንቋ አልነበረም። አዲስ ኪዳንም የተጻፈው ጌታ ባስተማረበት በአራማይስጥ ቋንቋ ሳይሆን፥ በጊዜው በስፋት ይነገር በነበረው በጽርዕ (ግሪክ) ቋንቋ ነው። የእማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችንም አራት ጊዜ ተተርጉሟል። እንደዚህ የሚደረገው "ቃሉ" በየጊዜው ላለው ትውልድ መናገር እንዲችል (RELEVANT እንዲሆን) ለማድረግ ነው። በመዝሙሩ እና በአምልኮ ዘይቤውም እንደዚያው ነው።

በመሠረታዊው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ላይ ካልሆነ በሰተቀር፥ በሌሎች ጉዳዮች ላይ "አለመቸከል" (STUCK አለመሆን) መልካም ነው። ግሎባዊነትን በሁለት እጆቻችን እናቅፈውም፤ ፈጽመንም ደግሞ አንገፋውም። የነጻነት ሥነ መለኮት ወይም ዐውዳዊ ሥነ መለኮት ልንሰብክ የሚያስፈልግበት ጊዜ እና ቦታ ሊኖር የችላል። "የብልጽግና ወንጌልም" ሙሉ በሙሉ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው አላልንም - የምንሰብከው የ"ድነት" እንጂ፥ የ"ድህነት" ወንጌል እይደለ ምና። ትንቢታዊ ሥነ መለኮትም በእርግጥ ያስፈልገናል። እግዚአብሔር ለለ ዛሬ ብቻ ሳይሆን፥ ስለ ነገም የሚገደው እና የሚናገር እምላክ ነውና። የሁል

ጊዜ እና የሁሉ ቦታ (UNIVERSAL) የሆኑ እውነቶች እሉ፤ ዐውዳዊ (CONTEXTUAL) የሆኑ እውነቶችም ደግሞ አሉ። አንዱን ለማንሣት፥ ለላውን መጣል እያስፈልገንም። የሚዛናዊነት ያለህ!!

ሣስታወሻ

1. ባሕሩ ዘውዴ፥ "የኢትዮጵያ ታሪክ፥ ከ1848 እስከ 1966"፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፥ 1989 ገጽ 239-240።
2. እንዳርጋቸው አስግድ፥ "በእጭር የተቀጨ ረዥም ጉዞ፤ መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ"፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፥ 1992 ገጽ 124።
3. ከፍሉ ታደሰ፥ "ያ ትውልድ፥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ታሪክ፥ ክፍል አንድ"፥ ኢንዲፔንደንት አሳታሚዎች፥ ዘመን አልተጠቀሰም፥ ገጽ 162።
4. በጊዜው በሶቭየት ኅብረት እስከ 20 ሚልዮን በቻይና ደግሞ እስከ 35 ሚልዮን ሕዝብ እንደ አለቀ የሚናገሩ ጽሑፎችን እንብቤ ነበር። አሁን ከዚያን ጊዜው ይልቅ የተሻሉ ጥናቶችን ለማድረግ ሁኔታው አመችቷል። በእነዚህ የተሻሉ ጥናቶች መሠረት፥ እጎዙ ወደ 60 እና ወደ 77 ሚልዮን አድጓል።
5. ዴሞክራሲያ "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ" (ኢሕአፓ) ልማን የነበረች መጽሔት/ጋዜጣ ናት።
6. ሐርቃ ሐሮዬ አዳ፥ "ከናይሮቢ እስከ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት"፥ መስከረም 1997 ዓ.ም.
7. "የምሥራች"፤ በብራታንያ የኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን፥ ለ27ኛው ዓመት ክብረ በዓል የተዘጋጀች መጽሔት JULY 2007 VOL 3።
8. GEORGE BIRKBECK HILL, "Johnson History of Rasselas Prince of Abyssinia" Oxford at the Clarendon Press, First edition 1887. Im pression of 1960. ይህ መጽሐፍ በሲራክ ወልደሥላሴ ኅሩይ ወደ አማርኛ ከተመለሰ ቆይቷል። በልጅነቱ ያነበብኩት ቢሆንም አሁን ግን ላገኘው ስላልቻልኩ የኢንግሊዝኛውን ማመሳከሪያ ሰጥቻለሁ።

ምዕራፍ ሰባት

ገነት ወጣች

Exit ገነት እንዲሉ። እኔም ሆንኩ በቅርብ የሚያውቋት ሰዎች ሁሉ፥ ገነትን የም ንመድባት "በጣም ጥሩ" ከሚባሉት ሴቶች መካከል ነው። "እጅግ በጣም ጥሩ" ያላልኩት፥ ገነት ይበዛባታል ብዬ ሳይሆን፥ "እበዛኸው" እንዳልባል ፈርቼ ነው። ከዚያም በላይ ደግሞ፥ ገነት "ዴንጤ" ናት። እብረን ነው ጌታን የተቀበልነው። የሚታይ ለውጥ ነው ሁለታችንም የተስወጥነው። በመንፈስ ቅዱስ በመጠ መቅ፥ ገነት ከአራት ዓመት ከመንፈቅ በላይ ትቀድመኛለች (እባሪ እንድን ይመልከቱ)። በመንፈስ ስለ መዘመሯ በምዕራፍ አንድ ጠቅሻለሁ። በእለም ሮም ደግሞ ትዘምራለች። ድምፃዊ ናት። ታስዘምራለችም። ፕሮግራም ትመራ ለች፤ ቃልም ታካፍላለች።

በኑሯችንም እጅግ ደስተኞች ነበርን። በባል እና በሚስት መካከል እንግዳ ያይደለውን "ተራ ግጭት" እንኳን፥ ገነት እና እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተናገድ ነው ከተገናኘን ከእምስት ዓመታት በኋላ ነው። ለዚያ ግጭት ሰበቡን የሰጠኋት እኔ ብሆንም፥ እርሷ ደግሞ ከልክ በላይ አጦዘችው። በኋላ እንደ ሰማነው፥ የዚያን ዓመቱን "የሾኔ ኮንፈረንስ" ከተካፈሉት ከርስቲያኖች መካከል፥ ወደ ቤታ ቸው ሲመለሱ የሆነ የሆነ ከባድ ችግር ያጋጠማቸው ሌሎችም ነበሩ አሉ። "የበቀል መንፈስ" ከሚባለው የርኩሳን መናፍስት አሠራር ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅሁት በዚያ አጋጣሚ ነበር ለማለት እችላለሁ።

የ1969ኙን ኮንፈረንስ ለመካፈል ገነት ወደ ሾኔ ትሄዳለች። እርሱ ኮንፈረንስ በደቡቡ የሙሉ ወንጌል ቀጣና የተዘጋጀ የመጀመሪያው "የሾኔ ኮንፈረንስ" ይመ ስለኛል። ገነት የሄደችው ብቻዋን ሳይሆን፥ በቅርብ ጊዜ ጌታን የተቀበሉት በዕድሜ እጅግ ጠና ያሉ፥ አንዲት እናት ይዛ ነው። እኚያ እናት፥ ገነት እና እኔ የምናውቃት የእንዲት አጎት እናት ወይም አያት የነበሩ ይመስለኛል። እርሷ ከሄደች በኋላ፥ እኔ ደግሞ የዲላ ቃለ ሕይወት ቤተ ከርስቲያን መዘምራን ሾኔ

ለመሄድ ፈልገው፥ ለትራንስፖርት የሚሆናቸው ገንዘብ እንደ ተቸገሩ ሰማሁ። እና በሌዎንቺና ለዲላ - ሾኔ ደርሶ መልስ የሚሆናቸውን ገንዘብ ሰጠኋቸው። በዚያን ጊዜው የትራንስፖርት ታሪፍ ሲሰላ፥ በጣም ትንሽ ገንዘብ ነበር። ሙሉ ውን የስጠኋቸውም እንኳን እይመስለኝም። የጎደላቸውን የሞላሁላቸው ነው የሚመስለኝ።

መንገደኞቹ ሰኞ ከሰዓት በኋላ ተመለሱ። እኔም የሥራ ስዓት እንደ እለቀ ወዲያው ወደ ቤት ሄድኩ - ወሬ ለመስማት ቸኩያለሁ። ገነት ኮንፈረንስ ለመካፈል ይህንን ያህል እሩቅ መንገድ ብቻዋን ሰትሄድ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር። ከዚያ በፊት እንድ ጊዜ ለሌላ ኮንፈረንስ ከይርጋዓለም ወንዶ ገነት ሄዳ የነበረ ቢሆንም፥ በዚያ ኮንፈረንስ ላይ ችግር ተፈጥሮ ከይርጋዓለም የሄዱቱ በማግስቱ ትተው ተመልሰዋል። በሾኔ ስለ ነበራቸው የበረከት ጊዜ፥ ብዙ ደስ ደስ የሚሉ ነገሮች አወራችኝ። የሾኔውን አባባ ጸጋዬን በስም ያወቅኋቸው ያኔ ነው። እቶ ተስፋ ወርቅነህንም (እሁን መጋቢ ዶክተር) በስም ያወቅሁት ያኔ ነው። በኮንፈረንሱ ላይ የዮሐንስ ራእይን መጽሐፍ ያስተምር ነበር። ገነት እና እማማ በትምህርቱ እጅግ በጣም ተደንቀዋል። ስንጨዋወት ቆይተን፥ ከዚያም እማማን በመኪና እቤታቸው አድርስናቸው ተመለስን።

በመንገድ ላይ እያለን ይሁን ወይም እቤት ከደረስን በኋላ ትዝ አይለኝም፥ የዲላ ቃለ ሕይወት ቤተ ከርስቲያንን መዘምራን በተመለከተ ያደረግሁትን ነገር ነገርኳት። "ጎሽ፥ ደግ አደረግህ" ትለኛለች ብዬ ነው የጠበቅሁት። እርሷ ግን ቡተቃራኒው ቱግ አለች። ነገሩ እንዴት እንደዚያ ሊሆን እንደ ቻለ ለማስረዳት ሞከርኩ። በሞከርኩ ቁጥር፥ ቁጣዋ እየጨመረ የሚመጣ ሆነ። ደነገጥኩ እና ዝም አልኩ። ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ፥ እንደዚህ ያለ ነገር በፍጹም አጋጥሞን አያውቅም። የመጀመሪያችን ነበር። ቁጣዋ አልበርድ አለ። እየጋለ እና የበለጠም እየጋለ መጣ። ከምሽቱ እንድ ሰዓት ገደማ የጀመረ፥ እስከ ሦስት ሰዓት አልበረደም። ትናገራለች፤ ትናገራለች፤ ትናገራለች። ቢቸግረኝ፥ እርሷን ሳሎን ትቻት፥ መኝታ ቤት ገባሁ እና ጥቅልል ብዬ ተኛሁ። ትንሽ ቆየት ብላ መጣች እና "በቀለ!" አለችኝ።

"አመቤት" አልኳት።

"መሄዴ ነው ..." አለች። ደነገጥኩ። ጆሮቼን ማመን አቃተኝ። ከአልጋው ላይ ወረድኩ እና አፊት ለፊቷ ቆምኩ።

"ምን አልሽኝ?" አልኳት::

"እሄዳለሁ ነው ያልኩህ" አለችኝ::

"የት ነው የምትሄጂው?"

"ቢቃ! ... እሄዳለሁ!"

እንዴት ግራ እንደ ተጋባሁ፥ እንዴት ድንግርግር እንዳለኝ፥ እንዴት እንደ ዞረ ብኝ መግለጽ አልችልም:: "እንዴ? ... ገነት ... ምን ነካሽ? ... አሁንኮ ከምሽቱ (ይሆንን ያህል) ሰዓት ነው ..."

"ይሁን! ... ግድ የለህም ..."

"እንዴት ግድ የለኝም? ምን ማለትሽ ነው?"

"አሁን ሌላውን ነገር ተወው ... እኔ ግን መሄድ አፈልጋለሁ"

"እሺ ... መሄዱን ትሄጃለሽ ... ግን ይንጋ ... እና ጠዋት እኔ እራሴ የፈለግሽበት አደርስሻለሁ"

"አይ ... እኔ ዛሬ እዚህ ቤት አላድርም ... ይልቅስ አሰናብተኝ"

"እንደዚያ ከሆነ ... እንግዲያውስ ... ዝም ብለሽ ሂጂያ ... አኔን ለምን ታናግሪኛለሽ?"

"የምትሰጠኝን ስጠኝ!"

"ኦ! ... እሱ ነው እንዴ ጥያቄሽ? ... ይቅርታ ... አልገባኝም ነበር ... ታዲያ እኔ ምን አንድሰጥሽ ፈለግሽ? ... በቤቱ ውስጥ ያለው ሁሉ ያንቺ አይደል እንዴ? ... ሁሉንም ይዘሽ መሄድ ትችያለሽ"

እርሷ እዚያው አንደ ቆመች፥ እኔ ወደ አልጋዬ ተመልሼ፥ ጥቅልል ብዬ፥ ተኛሁ:: እንደዚህ ያለ ጉድ አይቼም፥ ሰምቼም አላውቅም:: ልጅቱ ምን ነካት? ሻንጣ ስታወርድ፥ ቁም ሳጥን ስትከፍት፥ ልብሶች ስታወጣ፥ ወደ ላይ ወደ ታች ስትል፥ ቤቱን ስታተረማምስ ይሰማኛል::

ተነሣሁ እና ልጀልይ ተንበረከከሁ:: የሆነ ነገር ወደቀብኝ:: ድምፄን ከፍ አድ ርጌ ጮኽኩ፤ አለቀሥኩ፤ ተንሰቅሰቄ አለቀሰኩ:: መጮኽ ይብዛብኝ አንዴ?

ማልቀስ ይብዛብኝ እንዴ? አሁን የት ብላ ትሄዳለች? አውሬ ቢበላትስ? ሌላ ችግር ቢያገኛትስ? ምን ይባላል? ሰው ምን ይላል? እኔስ ነገ ጠዋት የሰው ዐይን ምን ብዬ አያለሁ? ምንስ ብዬ አወራለሁ? ጌታ ሆይ! ምን ጉድ ነው የመጣብኝ? ጮኽኩ፥ አለቀስኩ፤ ጮኽኩ፥ አለቀሰኩ::

ጩኸቱ እና ለቅሶው ሲያባራልኝ፥ በቤቱ ውስጥ ቅድም የነበረው ማተረማመስ ሁሉ እሁን አይለማም:: ጸጥ ብሏል:: ምን እያደረገች ይሆን? ሄደች ይሆን እንዴ? በጋቢዬ እንደ ተጠቀለልኩ፥ ከተንበረከከሁበት ሳልነሣ፥ ዝም ብዬ ማዳ መጥ ጀመርኩ:: ትንሽ እንደ ቆየሁ፥ የለቅሶ ድምፅ ሰማሁ:: ቀሰ ብዬ፥ ከንብ ነቤን ገልጬ፥ ድምፁን ወደ ሰማሁበት ዞር አልኩ:: ተንበርከካለች:: በሳምንት ሁለት ቀን - ረቡዕ እና ዓርብ - በአብዛኛው ተንበርከካ ከምትውልባት እና ተኝ ታም ከምታድርባት የጸሎት ምንጣፏ ላይ:: ምንድነው የማየው? ምን ማለት ነው? ቅድም እንደዚያ፤ እሁን ደግሞ እንደዚህ:: እሳቢን ቀየረች? ወይስ ከቤት ከመውጣቷ በፊት የመጨረሻ ጸሎት እያደረገች ነው? አልገባኝም:: ዝም ብዬ በተንበረከከሁበት ቆየሁ::

እንቅስቃሴ ሰማሁ ... ከተንበረከከችበት ተነሣች ማለት ነው ... እኔ ወዳለሁበት እየመጣች ነው ... አጠገቤ ከደረሰች በኋላ ለትንሽ ጊዜ ዝም ብላ ቆመች ... በመጨረሻም፥ በጣም በሚያሣዝን ድምፅ ... "በ-ቀ-ለ" አለችኝ::

በጋቢዬ እንደ ተጠቀለልኩ እና እዚያው አንደ ተንበረከከሁ፥ "እመቤት" አልኳት::

"ይ-ቅ-ር-ታ እ-ድ-ር-ግ-ል-ኝ ... ምን እንደ ነካኝ በእውነት አላውቅም ... በጣም አ-ዝ-ና-ለ-ሁ" አለች::

ከተንበረከከሁበት ተነሣሁ:: ጋቢዬን ወደዚያ ጣልኩት እና በሁለት እጆቼ አቀፍኳት:: እርሷም አቀፈችኝ:: ተቃቀፍን፤ ተላቀስን፤ ተሣሣቅንም:: ቀሪውም ሌሊት የበረከት ሆነልን:: ያ ከሆነ እሁን ዐሥራ ስምንት ዓመታት ዐልፈዋል:: እንባቢው ከምዕራፍ እንድ ንባቡ እንደሚያስታውሰው ገነት እና እኔ አሁን አብረን አይደለንም:: እርሷ የምትኖረው በኢትዮጵያ ሳይሆን በአሜሪካ ነው:: የሄደችው ጥር 21 ቀን 1982 ዓ.ም. ይሁን እንጂ፥ ከእኔ ለመለየት መወሰኗን ያስታወቀችኝ ግን ጥቅምት 18 ቀን 1988 ዓ.ም. ጠዋት 3:00 ሰዓት ላይ ነው - በሰልከ:: ዕለቱ ዕሑድ ነበር:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ልወጣ፥ መኝታ ቤቴ

ውስጥ የመጨረሻ ዝግጅት እያደረግሁ ነበርኩ። ላም በረት ሙሉ ወንጌል አገልግሎት አለኝ። ስልኩ ያለው ሳሎን ስለ ሆነ፥ ያነሣችው ሠራተኛችን እመቤት ናት። የመኝታ ቤቴን በር እንኳኳች እና "እትዬ ይፈልጉዎታል" አለችኝ። ስልኩን ከእመቤት ተቀበልኩ።

"እስከ አሁን እንዴት አልወጣህም?" አለችኝ።

የምሄድበት ቤተ ክርስቲያን ቅርብ መሆኑን ነገርኳት።

> "የደወልኩት እንኳን ጌዴዎንን ፈልጌ ነበር ... ወደ ዋና ሄዲል እሉ ... ለደብዳቤህ ገና መልስ አልጻፍኩም ... ደስ የሚያሰኝህ፥ ልትሰማ የምትፈልገው ዐይነት ወሬ የለኝም ... ለዚህ ነው ጨንቆኝ እስከ አሁን ድረስ ያል ጻፍኩልህ ... እስቲ ስሞኑን እሞከራለሁ"

አለችኝ። ምንም አላልኳትም። ለማለትም አልተመቸኝም - እመቤት ቤት እያጸዳዳች በአጠገቤ ነበረች። ቀኑን ሙሉ ግን ሳስብ ዋልኩ። ልትጽፍልኝ የፈለገችው እና ጨንቋት እስከ አሁን ድረስ ያልጻፈችው "የፈታችኝ" መሆኗን ለመናገር ነው። ወደዚህ ውሳኔ ላለመድረስ፥ ለብዙ ዓመታት ከእራሷ ጋር ያደረገችውን ትግል ዐውቃለሁ። ከአምስት ተኩል ዓመታት በፊት ወደ አሜሪካ የወለዳትም ይኸው ትግል ነው። "እንዴት ብዬ በምታገለግልበት አገር?" ብላኝ ነበር። ከእራሷ ዐልፎ፥ ከሚቀርቡን ወዳጆቻችን መካከል አንዳንዶቹን እንዲጸልዩላት ለትለምናቸውም በጆሮቼ ሰምቻታለሁ። እስከ አሁን ድረስ የተጨነቀቸው አይበቃትም? ለምን ከዚህ በላይ አስጨንቃታለሁ?

ወደ ማምሻው ላይ እኔ እራሴ ከቢሮዬ ደወልኩላት እና "ጠዋት ለማውራት ስላልተመቸኝ ነው አሁን የምደውልልሽ ... የዚህን ያህል ስላስጨነቅሁሽ እዝናለሁ ... ልትይኝ የፈለግሽውን ዐውቄዋለሁ ... ስለዚህ ደብዳቤ መጻፍ አይኖር ብሽም ... ቤቱንም መሥራት ከእንግዲህ አስፈላጊ አይሆንም" አልኳት።

"አይ ... ቤቱማ ይሠራ ... በአንተ ሰም ቢሠራ በእኔ በኩል ምንም ችግር የለውም" አለችኝ። "እንዴት ይሆናል?/እንዴት አይሆንም?" በመባባል ትንሽ ከተከራከርን በኋላ መጨረሻ ላይ በእርሷ አሳብ ተስማማን።

"ለደብዳቤህ ገና መልስ አልጻፍኩም" ያለችው፥ ባለፈው መስከረም 02 ቀን አንድ ደብዳቤ ጽፈላት ስሰ ነበረ ነው። በብዙ ጸሎት እና በብዙም ጥንቃቄ

ነበር ያንን ደብዳቤ የጻፍኩላት። 12 ገጽ ደብዳቤ ለመጻፍ ምናልባት 24 ገጽ ቀዳድጀለሁ። ደብዳቤው የያዘው በአብዛኛው የቤተ ስብ ወሬ ነው። ከዚያም ባለፈው ዓመት እግዚአብሔር ስላደረገልን ዋና ዋና ነገሮች ያወራል። በዓመቱ ውስጥ በታወቁ የጋብቻ አማካሪዎች የተጻፉ ብዙ መጻሕፍት ማንበቤን እና ያገኘሁባቸውን ጥቅም፥ በአሁኑ ዓመት የጋብቻ የምለከር ወረቀት ለማውጣት እና ልትሠራ ያሰበችውን ቤት ለማስጀመር ማቀዴን ይገልጻል። በመጨረሻም የእርሷን አሳብ ይጠይቃል። "ልትሰማ የምትፈልገው ዐይነት ወሬ የለኝም" ያለችው መሆኑ ነው - የእርሷ አሳብ።

ለሆነው ነገር ወይም ስተፈጠረው ችግር የእንበሳውን ድርሻ እኔ እንሣለታለሁ። የእንበሳው ድርሻ ከተነሣለት በኋላ የሚቀረው የማን የማን እንደሚባል አላውቅም እንጂ፥ መቼም ገነትም የእራሷን ድርሻ ማንሣቷ አይቀርም። እግዚአብሔር እና ሰይጣን ድርሻ ይኖራቸው እንደ ሆነ፥ ከኖራቸውም የእነርሱ ድርሻ ምን እና የቱን ያህል እንደሚሆን አላውቅም። ብዙ ጥያቄዎችን ግን ጠይቄአለሁ።

እያለማመደኝ ነበረ እንዴ?

ከገነት ጋር ከመጋባታችን በፊት ለዘጠኝ ዓመታት በሥራ ዓለም ብቻዬን ኖሬ አለሁ - እዲስ አበባ፥ ይርጋዓለም፥ እንደ ገና እዲስ አበባ፥ ባሌ ጎባ፥ እሰታ ወንዶ። በቤት ሠራተኛም፥ አለ ቤት ሠራተኛም። ከገነት ጋር ከተጋባን በኋላ ግን፥ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጌ ትቼዋለሁ። ነገረ ሥራው ሁሉ እልም ብሎ ጠፍቶብኛል። ማድ ቤት ገብቼ፥ ከቤት ሠራተኛ ጋር ተነጋግሬ አላውቅም ነበር ለማለት እችላለሁ። ለምሳሌ ምግብ ለብቻዬ መብላት አልችልም ነበር - ሆቴል ቤትም እንኳን ቢሆን። ስለዚህም ከዐቅም በላይ ካልሆነብን በስተቀር፥ ለሥራ ወደምሄድበት ሌላ ከተማ ሁሉ ከገነት ጋር ተያይዘን ነው እንሄድ የነበረው።

በ1974 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ ወደ አስመራ ተቀየርኩ። ገነት አብራኝ ለመሄድ የማትችልባቸው በቂ ምክንያቶች ነበሩ። የማታ ትምህርት እየተከታተለች ነበረች። ስትሠራበት የነበረው "የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የመተባበር ጉባዔ" የቦርድ ስብሰባ ቁልፍ ጉዳና ቴምሣ እና ዋና ጸሐፊው አቶ ሽምሱዲን አበዶ ሁለቱም ታስረዋል። ጽሕፈት ቤታቸው የነበረበትን የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ሕንጻ መንግሥት በቅርቡ ወርሶታል። ስለ

ዚህ የጽሕፈት ቤቱ ሰነዶች የት የት አንዳሉ የምታውቅ አርሷ ብቻ ናት። ድን ገት የሆነ ነገር ቢፈለግ ወይም አንድ ጥያቄ ቢመጣ፥ ማን መልስ ይሰጣል? ከመኖሪያ ቤት እና ከልጆች ትምህርት ቤት ጋር፥ የአስመራው ዝውውሬ ለሁለት ዓመታት ብቻ ከመሆኑም ጋር፥ የተያያዙ ሌሎች ምክንያቶችም ነበሩ።

ብቻዬን ወደ አስመራ የመሄዴ ነገር ቁርጥ መሆኑ ሲታወቅ፥ የገነት ጥያቄ "አሁን አንግዲህ እንዴት ትሆነዋለህ?" የሚል ነበር። "ብቻህን ሙበላት እን ኳን አትችል" ማለቷ ነበር። ነገሩ ሁለታችንንም እጅግ አሳስቦናል። ምንም ማድረግ ግን አንችልም። ገነት ደግማ ደግማ ነበር "አሁን አንግዲህ አንዴት ትሆነዋለህ?" የምትለው። አንዳንድ ጊዜ እኔን ነው የምትጠይቀኝ። አብዛኛውን ጊዜ ግን ለአራሷ ነው የምትናገረው። ጥያቄዋ ለእኔ በሚሆን ጊዜ ሁሉ፥ መልሴ "አንግዲህ አግዚአብሔር ያውቅልኛላ" የሚል ብቻ ነው። ሌላ ምን ማለት አችላለሁ? አግዚአብሔርም በአውነት ዐወቀልኝ።

ሐሙስ የካቲት 18 ቀን፥ አስመራ የገባሁ የዕለቱ ዕለት፥ ገና ከአውሮፕላን ማረፊያ ተቀብሰውኝ ከማርፍበት ሆቴል በር ላይ ሲያወርዱኝ፥ ከወንጌላዊ (አሁን መጋቢ) አሸናፊ ዘማት ጋር ተገናኘሁ። ከአሸናፊ ጋር የምንተዋወቀው ከይርጋ ዓለም ጀምሮ ነው። በዚያችው ዕለት ምሽት ከወገኖች ጋር አገናኘኝ። አብረናቸው መንፈሳዊ ጥሮግራም ተካፈልን። የተስፋዬ ጋቢሶን "ሕዝብን አበዛህ" በትግርኛ አንደ ጉድ ዘመሩት። በጋራም ጸለይን። ለአኔም ጸለዩልኝ። ጠቅላላው የአስመራ ቆይታዬ ፈር በዚያች የመጀመሪያ ምሽቴ ተቀደደ ማለት ነው። አንድ አሳብ ወረደ። በጣም ደስ አሰኝ። እጅግም ተጽናናሁ። አግዚአብ ሔርንም አመሰገንኩ።

ከምተካው ሰው ጋር ርክክብ ጨርሰን የባንኩን መኖሪያ ቤት ስረክብ፥ የቤት ሠራተኛውን አበራሽንም አብሬ ተረክብኳት። ሁለተኛ አሳብ ደግሞ ወረደ። አበራሽ የአከሉም ልጅ ነች። ሽጋ ጠባይ አላት። በስላም ነው አብረን የኖር ነው። በጣም ነበር የተመቸችኝ። ከአስመራ ስዛወር፥ አኔም በተራዬ ለተካኝ ሰው አስረክቤአታሰሁ። በአርሱ ዘመን ነው መሰለኝ፥ አንዲያውም ባንኩ ሠራተኛው አድርጎ እንደ ቀጠራት ሰምቻለሁ። ይገባታል።

አስመራ በቆየሁባቸው ሃያ ስምንት ወራት ውስጥ ገነት አንድ ጊዜ፥ ጌዴዎን ሁለት ጊዜ ወደ አስመራ፥ እኔም አንድ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ መጥተን ተመልሰ

ናል። በመሠረቱ የመሐል አገር ሰዎች ወደ ኤርትራ የሚላኩት በዘመቻ መልክ ስለ ነበረ፥ ቤተ ሰብ ይዞ የመሄድም ሆነ በጉብኝት ስም የማስመጣት ጥያቄ አይነሣም። እንደዚህ ማድረግ የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ፥ በራሳቸው መንገድ ነው ማድረግ የሚችሉት። በራሳቸው መንገድ ማለትም፥ ወይ አራሳቸው ቲኬት ቆርጠው በኢትዮጵያ አየር መንገድ፥ አለዚያም ደግሞ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለ ሥልጣኖች ጋር በመነጋገር በአንቶኖቭ አውሮፕላን በነጻ ማስመጣት ነው የሚችሉት ማለት ነው። ከጦርነቱ የተነሣ፥ የዮበስ ትራንስፖርት በጊዜው አልነበረም።

ገነትን እና ጌዴዎንን ግን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው ቲኬት ገዝቶላቸው የላከልኝ። የአስተዳደር ከፍል ሥራ አስኪያጁ አቶ ሥዩም ሐጎስ ነው እንደዚያ ያደረገልኝ። ከሌላ ባለ ሥልጣን ጋር ተማክሮ አንደ ሆነ አላወቅሁም። እንደ ዚያ ስለ ተደረገለት ሌላ ሰውም አልሰማሁም። አኔ ወደ አዲስ አበባ የመጣሁት የውጭ ምንዛሪ ለማድረስ ነበር - በሥራ ምክንያት ማለት ነው። ከአናቱ ጋር አብሮ በመጣ በዓመቱ፥ ጌዴዎንን በራሴ መንገድ ወደ አስመራ አምጥቼው፥ ሁለተኛ ክረምት አብሮኝ አሳልፏል። የአስመራውን ግዳጁን አንደ ጨረስኩ ደግሞ፥ ባንኩ ለሌላ ስድስት ወራት ወደ ምዕራብ ጀርመን ልኮኛል።

አነዚህን ነጥቦች የማነሣቸው፥ አንደኛ ከገነት ተለይቼ የቆየሁበት ጊዜ፥ ሁለታችንም አንደ ፈራነው አልሆነም ለማለት ነው። ይልቁንም የብዙ በረከት ጊዜ ነበር የሆነልኝ ለማለት ነው። የአስመራ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክር ስቲያን አባል ሆኛለሁ። የጸሎት - የብዙ ጸሎት፥ የፍቅር - የብዙ ፍቅር፥ የዝማሬ - የብዙ ዝማሬ አና የአገልግሎት ጊዜ ነበረን። በቤት አበራሽ አለች። በቢሮዬም ብዙ ሰላም አለ። ገነት አስመራ መጥታ አንድ ክረምት አብረን አሳል ፈናል። ጌዴዎን ሁለት ክረምት አብሮኝ ቆይቷል። አኔም አንድ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ መጥቼ፥ ለአንድ ሳምንት ያህል አብሬአቸው ቆይቻለሁ። በተለያዩ ምክን ያቶች ወደ አስመራ የሚመጡ የማውቃቸው የመሐል አገር ሰዎችም ነበሩ - ኮሎኔል አየለ ገበየሁ፥ አቶ መስፍን ለማ፥ ዶክተር አታላይ ዓለም፥ ዶክተር ሩት ለ.ካሣ፥ ፓስተር መርዕድ ለማ፥ ወዘተርፈ።

ሁለተኛ፥ አንደማይቀርልኝ የሚያውቀውን "ብቸኛነት"፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እያለማመደኝ ነበር አንዴ? ብዬ መጠየቄን ለመናገር ነው። በምዕራብ ጀርመ ንም የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መሠረት አየተጣለ ነበረ። ወንድም

ተወልደ ዮሐንስ ለትምህርት ከኢትዮጵያ መጥቶ ከባለቤቱ ከገነት ጋር በቦኹም ይኖራል። ወንድም አማኑኤል ደበሳይ (አሁን መጋቢ) እና ባለቤቱ ፀዳል ከኤርትራ ተሰድደው በፍራንከፈርት ተቀማጮች ሆነዋል። ዶክተር እሸቱ ጉርሙ (አሁን መጋቢ) ትምህርቱን ጨርሶ ከኪዩባ ሲመለስ ፍራንከፈርት ላይ ቀርቷል። ቀድሞ የሙሉ ወንጌል አማኝ የነበረ ቢሆንም፥ አብዮቱ ሲፈነዳ እም ነቱ ተናጋበት። ኪዩባ ሲደርስ ደግሞ ለየለት። ፍራንከፈርት ላይ በቀረ ጊዜ ግን ወዲያው ወደ ጌታ ተመለሰ። አሁን በፍራንከፈርት የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ነው።

የሚያስገርሙ ጥንቃቄዎች

ከገነት ጋር ስለ መለያየታችን ለመናገር ስነሣ፥ መነሣት የሚገባኝ እግዚአብሔር ስላደረገልን ጥንቃቄዎች በመናገር ነው። እግዚአብሔር ስላደረገልን ጥንቃቄ ዎች በመናገር መነሣት የምፈልገው፥ እግዚአብሔር መለያየታችንን አጽድቆል ናል ለማለት አይደለም። ያለዚህ ጥንቃቄው አንኳን በአገልግሎት፥ በሕይወ ትም መቆየት መቻሌ እጅግ አጠራጣሪ እንደ ነበረ ለመናገር ነው። "እያለማ መደኝ ነበረ አንዴ?" የሚለውን ጥያቄዬን ያስቀደምኩትም በዚሁ ምክንያት ነው። እንደዚያ ጊዜውን እና ሁኔታውን እመቻችቶ ብቸኝነትን ባያለማምደኝ ኖሮ፥ አሆን የነበረው ምን ይሆን? ለማለት ነው። አጅግ የበዛልኝን ምሕረቱን እና ቸርነቱን በመናገር አለመነሣት፥ እግዚአብሔርን መበደል ስለሚሆንብኝ ነው።

ገነት ወደ አሜሪካ ስትሄድ፥ ራሔል የ23፥ ጌዲዎን የ19፥ ዮሴፍ ደግሞ የ5 ዓመት ነበሩ። እርሷን ከማጣታችን በስተቀር፥ ቤተ ሰቡ አንዳለ ነበር። ሙሉ ቤትም ነበር ትታልን የሄደችው። እርሷ እየገዛች ያጠራቀመቻቸውን የቤት ዕቃዎች አለከ ዛፊ ድረስ፥ ሰብረንም እንኳን ገና አልጨረስናቸውም። የጤፍ፥ የቅቤ፥ የሥጋ፥ የሽንኩርት፥ ወዘተርፈ፥ ደንበኞች ነበሯት። ከአንዳንዶቹ ጋር እኔንም እንኳን አስተዋውቃኛለች። እኔ የማላውቃቸውን ደግሞ ራሔል ታው ቃቸዋለች። እና ሰረዝም ጊዜ ነበር በዚያው ዐይነት የቀጠልነው።

የቤት ሠራተኞችንን እመቤትን ያመጣቻት ገነት ናት። እርሷ ከመሄዷ በፊት እመቤት ለሁለት ዓመታት ያህል አብራን ኖራለች። እርሱ ብዙ አላስገረመ ኝም። ገነት ሁል ጊዜም ቢሆን የቤት ሠራተኞች ይዋጡላታል። ምናልባት

ከሁለት ሠራተኞች በስተቀር፥ እመቤትን ጨምሮ ሁሉንም ደግሞ ወደ ጌታ አምጥታቸዋለች - በ17 ዓመታት ውስጥ ማለት ነው። በጣም ትመቻቸዋለች ይመስለኛል። እርሷም፥ ስለ አንዳቸውም ቢሆን "እልተመቸችኝም" ስትል ሰምቻት አላውቅም። እመቤት በጣም ጥሩ ልጅ ናት። ከሁሉም በላይ ከልጆቹ ጋር በጣም ስምም ናት። ዮሴፍን አንደ ልጇ ነው የምታየው። ማንኛችንም ብንሆን አንድናለከፋው አትፈቅድልንም። ይህ ለእኔ ትልቅ ዕረፍት ነበር።

እኔ ከቤት ውስጥ ይልቅ ከቤት ውጭ የማላልፈው ጊዜ ይበልጣል። በሥራ እና በአገልግሎት ምክንያት፥ ከአገር ውጭ የምሄድባቸውም ጊዜያት ትንሽ አል ነበሩም። ገነት ከሄደች በኋላ ለ16 ዓመታት አመቤት አብራን ኖራለች። በመጋቢት ወር 1998 ዓ.ም. ወደ ጌታ በሄደች ጊዜ ነው የተለየችን። በዚያን ጊዜ ራሔል እና ጌዲዎን የየራሳቸውን ትዳር መሥርተዋል። ትዳር ከመመሥ ረታቸው በፊትም ሆነ በኋላ፥ አነርሱም ሆኑ ዮሴፍ፥ ከእመቤት ጋር አንድም ቀን ተጣልተው አያውቁም። በጣም የሚዋደድ የአንድ ቤተ ሰብ አባላት ሆነን ነው አብረን የኖርነው። እመቤትም ሆነች አነርሱ፥ "ቤታቸው" ያለበትን ሁኔታ ይረዱ ነበር ማለት ነው። ይህም "ቤታቸው"፥ አለከ አሁን ከደረሰበት የበሰጠ መናጋት ወደ ፊት እንዳይደርስበት የየበኩላቸውን ጥንቃቄ ያደርጉለት ነበር ማለት ነው። እግዚአብሔር ይባርካቸው።

ገነት ወደ አሜሪካ ለመሄድም ሆነ ከእኔ ለመለየት ስትወስን፥ እኔ የዎርልድ ቪዥን ሠራተኛ ነበርኩ። ዎርልድ ቪዥን ብዙዎች እንደሚያውቁት፥ በተፈጥሮ አና በሰው ሠራሽ ችግሮች የተነሣ ሕይወታቸው የተጎሣቆለ በመቶ ሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን በዓለም ዙሪያ የሚረዳ ከርስቲያናዊ የሆነ ድርጅት ነው። በዎርልድ ቪዥን ውስጥ፥ በዓለም ዙሪያ ስላለው የሰዎች ጉስቁልና ብዙ ይነገራል፤ ብዙም አንሰማለን። የሚነገረው አና የምንሰማው ስለ ሰዎች ሥጋዊ ጉስቁልና ብቻም አይደለም፤ ከአብዛኞቹ ሥጋዊ ጉስቁልናዎች በስተ ጀርባ ስላለው መንፈሳዊ ጉስቁልናም ጭምር አንጂ። አሉም ጉሰቁልና ከሥጋዊው ጉስቁልና ይልቅ፥ የዚህን ያህል አጥፍ ሊባል የማይቻል ያህል፥ እጅግ የከፋ ነው።

ቅዳሜ ጥቅምት 02 ቀን 1978 ዓ.ም. የዎርልድ ቪዥን ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ዕብናት (ጎንደር) የገባሁበት ቀን ከሰዎች ሥጋዊ ጉስቁልና ጋር ፊት ለፊት የተያየሁበት ቀን ነበረ። ወይዘሪት ገነት ከበደ የመጠለያ ካምፖቹን

እያዞረች ስታስነበኘኝ፥ ስሜቴ አሸነፈኝ እና አለቀስኩ። ኩሩ የነበሩ ለዎች ተዋ ርደው፥ የራሳቸው ቤት እና ንብረት የነበራቸው ሰዎች ተሰድደው፥ በሌማታ ቸው እንጀራ እጥፈው ወጥ ጨልፈው ይበሉ የነበሩ ለዎች እንደ ትንሽ ልጅ የፋፋ ገንፎ በትንሽ ዕቃ እየተሰፈረላቸው፥ ሲበሉ ማየት ያስለቅሳል። በአረሃቡ ምክንያት ወላጆቻቸውን፥ ልጆቻቸውን፥ ባሎቻቸውን፥ ሚስቶቻቸውን፥ በሞት የተነጠቁ በመካከላቸው ሞልተዋል። ዐፈር ለማልበስ ጉልበት ጎድ ሏቸው፥ የሚወዷቸውን ሰዎች እሬሣ እንደ ዋዛ ነገር፥ ከመንገድ ዳር ለእውሬ ጥለውት የሄዱም አሉባቸው። የእንዳንዶቻቸውን ታሪክ ከአፋቸው እየሰማሁ፥ ከዚያም በኋላ ብዙ ቀን አልቅሻለሁ።

አብረነው ለለምንውል እና ስለምናድር፥ ሕመም (PAIN) እና ዕንባ በኃጢአት የወደቀው ዓለም ዕጣ ፈንታ የመሆኑ ግንዛቤ በአብዛኞቻችን ዘንድ በኃይል አለ። በዎርልድ ቪዥን ብዙ የሚጸለየው በዚህ ምክንያት ነው። በዎርልድ ቪዥን ጸሎት የምንተነፍሰውን አየር ያህል ሆኖልን ነበር ለማለት አደፍራለሁ። በሕይወቴ ላይ እንደዚያ ያለ አደጋ የደረሰው፥ እንደዚህ ባለ "ከባቢ አየር" (ATMOSPHERE) ውስጥ ሆኜ ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፥13 ላይ የተጻ ፈውን "ቃል" ለመረዳት ምቹ ሁኔታ ነበር -

> "በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብ ሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋች ሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ፥ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል"

በግሌ የደረሰብኝ ፈተና ከምችለው በላይ ያልሆነውም ሆነ፥ ወይም በፈተናው ውስጥ መታገሥ የቻልኩት በዚህ ምክንያት ነው።

ሌላም ጎብረት ነበረኝ። በትንሽ ቁጥር የጀመረ እና ቀስ በቀስ ያደገ ጎብረት ነው። በጎብረቱ ውስጥ አብረውኝ ካሉት ወንድሞች እና እኅቶች ጋር የቤተ ሰብ ያህል እንቀራረባለን። ወደ አሜሪካ ከመሄዴ በፊት ገነትም የጎብረቱ አባል ነበረች። በገነት እና በእኔ መካከል አለመግባባት በተፈጠረ ጊዜ፥ በእርሷ ጥያቄ ሽምግልና የገቡ እና ያለታረቁን ሰዎች በውስጣቸው አሉባቸው። ለጸሎት እና ለአገልግሎት ከሁሉም ጋር በሳምንት ቢያንስ አንድ ጊዜ እንገናኛለን። ከአንዳን ዶቹ ጋር ደግሞ በሳምንት ሁለቴም ሦስቴም እንገናኛለን። አብረውኝ የሚሠ

ሩም አሉባቸው። ከእነርሱ ጋር ደግሞ በሳምንት አምስት እና ስድስት ቀን እንገናኛለን ማለት ነው።

ለምልጃ እና ለምስጋና እንዲያመቻቸው፥ ለጎብረቴ አባላት ገነት ወደ አሜሪካ ከሄደችም በኋላ ለላለንበት ሁኔታ በየጊዜው አስታውቃቸዋለሁ። ይወዱናል፤ ያለ ማቋረጥም ይጸልዩልናል። ምክር በሚያስፈልገኝ ጊዜ ይመከሩኛል። ተግሣጽ በሚያስፈልገኝም ጊዜ በፍቅር ይገሥጹኛል። ከዚያ ጎብረት አባላት ጋር፥ እስከ ዛሬም ድረስ፥ ቤተ ሰብ እንደ ሆንን ቀርተናል። ሕይወቴ እና አገልግሎቴ፥ እስከ ዛሬም ድረስ፥ በጸሎታቸው ይሸፈናል።

የእኔን ሕይወት እና አገልግሎት ከጥፋት ለማዳን፥ እግዚአብሔር እኔን ስለ ከበበባቸው ስለ እነዚህ እና ልዘረዝራቸው ለለማይቻለኝ ጥንቃቄዎቹ ሁሉ እጅግ አድርጌ አመሰግነዋለሁ። ቅዱሳኑንም እግዚአብሔር ይባርካቸሁ እላ ለሁ። ሆኖም፥ መገረሜም ደግሞ አልቀረም - እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ ጥን ቃቄ ያደረገልኝ ለምን ይሆን? ከዚህ ሁሉ ጥንቃቄው ጋር እንደዚህ የሆነ፥ ይህ ሁሉ ጥንቃቄው ባይኖር ኖሮ ምን ሊሆን ነበር ማለት ነው?

የማይመለሱ ጥያቄዎች

ይህም ሁሉ ይሁን እንጂ፥ ጥያቄዎች - አ! በጣም ብዙ እና በጣምም ከባድ ጥያ ቄዎች - ደግሞ ነበሩ። ከእንዳንዶቹ ጥያቄዎቼ ጋር ሲነጻጸር፥ "እያለማመደኝ ነበር እንዴ?" የሚለው ጥያቄ በጊዜው ከጠየቅኋቸው ጥያቄዎች ሁሉ ምናልባት በጣም ቀላሉ ሳይሆን አይቀርም። ለእንዳንዶቹ ጥያቄዎቼ እስከ ዛሬም ድረስ መልስ አላገኘሁላቸውም። ለእንዳንዶቹ ደግሞ አለከ ወዲያኛውም ድረስ መልስ የማገኝላቸው አይመስለኝም። ለምሳሌ "ለምን?" ብያለሁ። በተለያዩ ጊዜያት፥ እየደጋገምኩ፥ "ለምን?"፥ "ለምን?" እያልኩ ጠይቄአለሁ። ይህን ጥያቄ የሠነዘርኩት በአብዛኛው ወደ እግዚአብሔር ነበር። ለምን እንዲህ እንዲሆን ፈቀድከ? የገነት የእራሷ፥ የእኔ እና የእነዚያ ሁሉ ቅዱሳን ጸሎት ለምን ሳይመለስ ቀረ?

በጣም ብዙ ለዎች ነበሯ የጸለዩልን። በጣም ብዙ ሰዎች፥ ደግሞ ለረዥም ጊዜ፥ የጸለዩለት እንደ እኛው ያለ ሌላ ትዳር የለም ብዬ እስከ ማሰብ አደርሳለሁ። "ለረዥም ጊዜ" ማለት፥ ከመለያየታችን በፊት ለዐሥር ዓመታት ያህል ማለት ነው። መለያየታችንን ካወቁም በኋላ ተስፋ ያልቆረጡ ሰዎች አሉ። በሚጸልዩ

ልን ሰዎች መካከል፥ እኛንም ሆነ ስለ እኛ ምንም የሚያውቁ ሰዎች አሉባቸው። እነዚህ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ሽከም የተቀበሉ ሰዎች ናቸው። እንዳይረሳው፥ የገነትን ሰም በቁም ሳጥኑ መስታወት ላይ ለጥፎ በየዕለቱ እንደሚጸልይላት የነገረኝ ስው አለ። ፈጽሞ የማያውቋት፥ ነገር ግን ገነትን በቤተ ሰባቸው ቋሚ የጸሎት ርእሳቸው ያደረጓት ሰዎችም እንዳሉ ዐውቃለሁ። እንደዚህ የማይመለስ ከሆነ፥ ለምን ለእነዚያ ሁሉ ሰዎች ይህንን የሚያህል የጸሎት ሽከም ስጠ?

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የማውቃቸውን አንዳንድ መለኮታዊ እውነቶች ለመረዳት ወይም እርስ በርሳቸው ለማስታረቅ እጅግ የተቸገርኩበትም ጊዜ ነበር። ለምሳሌ፥ "... ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ ... እናውቃለን" የሚለው ጥቅስ (ሮሜ 8፥28) ብዙ ጊዜ የሰበከሁበት ነው። አሁን ግን ጥያቄ ተፈጠረብኝ። "ፍቾ" እንዴት ለበጎ ሊሆን ይችላል?

"ባሎች ሆይ፤ ከርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፥ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ" ይላል (ኤፌ. 5፥25)። ይኸ ግልጽ ነው፤ ይገባኛል። መለስ ብሎ ግን "ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አባቱንና እናቱን፥ ሚስቱንና ልጆቹን፥ ወንድሞቹንና እኅቶቹን፥ የራሱንም ሕይወት እንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም" ይላል (ሉቃ. 14፥26)። ምን ማለት ነው? ከርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት የምወዳትን ሚስት፥ እንዴት አድርጌ ነው የምጠላት? ለእንዳንዶች የድፍረት ንግግር ሊመስለቸው ይችል ይሆናል፤ የድፍረት ንግግር እንዳልነበረ ግን እርሱ ያውቃል - "አንተ ሚስትህን እስከ ሞት ድረስ ወደሃታል፤ ዐቅም ስላለህም ያንን ያህል መንገድ ተጉዘህ፥ ያንንም ያህል ዋጋ ከፍለህ መልሰህ የራስህ አድርገሃታል። ዐቅም በሌለኝ በእኔ ትዳር ላይ ግን - እንደማያውቅ ሰው - ለምንድን ነው እንደዚህ የጨከንከው?" ያልኩበትም ጊዜ ነበረ።

ከሁሉም ይልቅ በጣም ያሰቸገረኝ ጥቅስ ሮሜ ፲፥36 ላይ ያለው ነው። "ሁሉም ከእርሱ፥ በእርሱ፥ ለእርሱ ነውና" ይላል። እንዴት ሊሆን ይችላል? እግዚአብሔር በግልጽ "ፍቾን አጠላለሁ" ብሎ የለም ወይ? (ሚል. 2፥16) ገነትን እና እኔን እግዚአብሔር አጋባን እንጂ አላፋታንም። ስለዚህ ፍቻቾን ከእርሱም፥ በእርሱም፥ ለእርሱም ሊሆን አይችልም። ታዲያ ከማነው ልበል? ከገነት እና ከእኔ ነዋ! ከእኛ ካለፈም፥ ከሰይጣን ነዋ!

እንዴት ሊሆን ይችላል? እርሱን በማናውቀው ጊዜ፥ በፈቃዱ እና በፈቃዳችን ተጠቅሞ ወደ ትዳር ያመጣን እግዚአብሔር፥ አሁን እርሱን በምናውቀው ጊዜ፥ በፈቃዱ እና በፈቃዳችን ተጠቅሞ ለምን ትዳራችንን አላዳነውም? ሁለታችንም ጸልየናላ! የገዛ እጁ የሠራችው ቤት በእኔ እና በገነት ድካም፥ ወይም ደግሞ በሰይጣን ብርታት፥ ወይም ደግሞ በእኛ ድካም እና በሰይጣን ብርታት ቅንጅት፥ ሲፈርስ ለምን ዝም አለ?

ለሰዎች እና ለሰይጣንስ ቢሆን ፈቃድ የተሰጣቸው የእግዚአብሔርን ዕቅድ እና ዓላማ "ዐፈር ዲሜ" እስከሚያበሉት እስከዚህ ድረስ ነውን? ከሆነስ፥ ለምን? ስለ እግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና ስለ ሰው ነጻነት ያነበብኩት እና ስሰጠው የኖርኩት ትንታኔ ሁሉ አሁን ምንም ሊረዳኝ አልቻለም። ለካ ምንም የማላው ቀውን ነገር ኖሯል እንደዚያ ስለፈልፍ የኖርኩት?

ለምን? የሚለው ጥያቄዬ የተሠነዘረው ግን ወደ እግዚአብሔር ብቻ አልነበረም። ወደ አራሴ እና ወደ ገነትም ጭምር ነበር። ለምን ለገነት ጥሩ ባል ልሆናት አልቻልኩም? እንደዚህ ያለ አደጋ ሊመጣ እንደሚችል ለምን አስቀድሜ አልገመትኩም? ፍላጎቷን ለመረዳትና የማያግባቡንን ጉዳዮች ለመፍታት ለምን የበለጠ ጥረት አላደረግሁም? የመንፈሳዊ እማካሪዎችን ወይም የባለሞያ እማካሪዎችን እርዳታ እንድንሻ ለምን አላግባባኋትም? ለምን ከጸምኩት እና ከጸለይኩት የበለጠ አልጸምኩም እና አልጸለይኩም? እርሷስ ብትሆን፥ ለምን ኪታገሠችኝ በላይ አልታገሠችኝም? ለምን "ይህንን እና ይህንን ድካምህን እሻሽል፥ አለዚያ ግን ..." አላለችኝም? ለምን እስከዚህ ድረስ ፈጽማ ተስፋ ቆረጠችብኝ?

እንዴት አስቀድሞ ሳይናገር?

"በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለአገልጋዮቹ ለነቢያት ሳይገልጥ፥ ምንም ነገር አያደርግም" የሚለውን ቃል ዐውቃለሁ (አሞ. 3፥7)። እንደዚህ ማለት፥ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ፥ ሁሉን ነገር፥ ለሁሉ ሰው አስቀድሞ ይናገራል ማለት እንዳይደለም እገነዘባለሁ። ሆኖም፥ ሕይወቴን የሚያናጋ፥ ይህንን የሚያህል ትልቅ አደጋ እየመጣብኝ እንደ ሆነ ደግሞ እግዚአብሔር አሳምሮ ያውቃል። ለምን ታዲያ በቅድሚያ አላስጠነቀቀኝም? ቃሉ የሚለው "ምንም ነገር አያደርግም" ስለ ሆነ፥ ያልተናገረኝ ይህንን ነገር ያደረገው እርሱ ስላልሆነ ነው? ወይስ እርሱ አስጠንቅቆኝ፥ እኔ ግን ሳላስተውል ቀርቻለሁ?

በ1969 ዓ.ም. ዲላ እያለን ያጋጠመኝ ነገር አለ። አንድ ሰሞን በየጠዋቱ ቢሮ ስንገባ፥ ጆሮ ጭው የሚያደርግ ወሬ ሊወራ አንሰማለን። "ማታ እኮ የሆኑ ሰዎች እገሌ ቤት ገብተው" ይባል እና ከዚያ ቀጥሎ መሳት ይወራል። በማግ ስቱ ደግሞ "እገሌን እጅ እና እግሩን አስረው ወይም ጠብመንጃ ግንባሩ ላይ ደግነው፥ ሚስቱን ወይም የደረሰች ሴት ልጁን አፊቱ ደፈሯት" ይባላል። ወሬው አውነት ይሁን ወይም ሐሰት የት ተብሎ ይጣራል? ጊዜው የአብዮት ሰለ ሆነ፥ አንደዚህ ያለ ነገር አይደረግም ማለትስ እንዴት ይቻላል? ጌዴኦች ደግሞ በኢትዮጵያ ምድር በጣም የተጨቆኑ ሕዝቦች ናቸው። አንዳንድ ባለ አርሰቶች ጭሰኞቻቸውን የሚያሰሩበት የራሳቸው አሰር ቤት ሁሉ ነበራቸው ይባላል። አነዚህ ገበሬዎች ያመፁ እንደ ሆነ፥ ዓመፃቸው በተጨቆኑት ጭቆና መጠን ነው የሚሆነው። እና ወሬውን ላለማመንም ይቸግራል።

እንደዚህ ዐይነቱን ወሬ በሰማሁበት ሰሞን፥ ከሌሊታት በአንዱ ሌሊት አሳብ ገባኝ። ሚስቴ ቆንጆ ናት። የማንንም ቀልብ ትቀልባለች። እነዚህ ሰዎች ወደ አኔስ ቤት የመጡ እንደ ሆነ ምን አደርጋለሁ? ተጨነቅሁ። የአውነት ተጨነ ቅሁ። ቀስ ብዬ ከጎኗ ተነሣሁ እና ወደ ላሎን ሄድኩ። እና ተንበርከኬ ጸለ ይኩ። ከልቤ ጸለይኩ። ጭንቀቴን ሁሉ ለእግዚአብሔር ነገርኩት። አየጸለይኩ እያለሁ፥ በውስጤ ድምፅ የሰማሁ መሰለኝ። ጸጥ አልኩና ማዳመጥ ጀመርኩ።

"ምንህ ናት?"

"ምንህ ናት? ... ሚስቴ ናታ!"

"ከየት አመጣሃት?"

"ከየት አመጣሃት? ... ከየት አመጣታለሁ? ... አንተ ነሃ የሰጠሽኝ"

"ምን አድርገህላታል?"

"ምን አድርገህላታል? ... ኧረ አኔ ምንም አላደረግሁላትም"

"እሺ፥ ለአኔስ ምኔ ናት?"

"ለአንተ? ... ለአንተማ ልጅህ ናት"

"አኔስ ምን አድርጌላታለሁ?"

"አንተ? ... አህአ ... አንተማ ሞተህላታል"

"ዝምድናዋ ለማን ይበልጣል? ለአንተ ወይስ ለአኔ?"

"ዝምድናዋ? ... ዝምድናዋማ ለአንተ ነው የሚበልጠው"

"አና፥ አሁን አንተ ምን ልታደርግላት ትችላለህ?"

"አኔ? ... አኔማ ምን ላደርግላት እችላለሁ? ... የሚያሰጨንቀኝስ ይኸው አይ ደል? ... ምንም ላደርግላት አለመቻሌ?"

"አኔሰ?"

"አንተ? ... ወይ ጉድ ... አንተማ ሁሉን ልታደርግላት ትችላለህ"

"በል አንግዲያው፥ መልሰ እና ለአኔ ስጠኝ"

ጥያቄውን የምሰማው በውስጤ ነው። መልሱን እሰጥ የነበረው ግን በእፌ ነው። አያንዳንዱን ጥያቄ እመልሰ የነበረውም ረጋ ብዬ ካሰብኩበት በኋላ ነበር። ጥያቄ እና መልሱ መጨረሻ ላይ ስደርስ አለቀሰኩ። በእግዚአብሔር ባለመታመኔ በአራሴም እጅግ አዘንኩ። አፌን አውጥቼም ለእግዚአብሔር ተናገርኩ -

> "ይህች ሚስቴ ለአኔ የአንተ ከቡር ስጦታ ነች። አኔ አንደዚህ ዐይነቱን ከቡር ስጦታ የምደብቅበት ቦታ፥ የምጠብቅበትም ጉልበት የለኝም። ስለ ዚህ ይኸው አሁን መልሼ ለአንተ አደራ አሰጣታለሁ እና ተረከበኝ"

አልኩ። ከልቤ ነበር ይህንን ያልኩት። ሆኖም፥ ከልቤ የሰጠሁትን ይህንን አደራ ከእጆቹ መልሼ የወሰድኩበት ጊዜ ጥቂት የሚባል አይደለም። ከቶውንም እኔም እንደ ሰጠሁት፥ አርሱም እንደ ተቀበለኝ ያልመሰለኝ ጊዜ ሁሉ ነበረ።

በታሕሣሥ ወር 1970 ዓ.ም. ከዲላ ወደ አዲስ አበባ በተዛወርን ጊዜ፥ የይርጋ ዓለምን ቤተ ክርስቲያን ለመሰናበት ሄድን። ዕለቱ ዕሑድ ነው - በዲላ የመጨ ረሻው ዕሑዳችን። አብረናቸው አመለከን። ፕሮግራሙን የሚመራው የባሌ ነባው ወንጌላዊ በለጠ ሀብተ ጊዮርጊስ ነው። ገነት እና አኔ ከመድረኩ ጎን፥ ጎን ለጎን ተቀምጠናል።

ፕሮግራሙ በጸሎት ተጀምሮ፥ በአንድ መዝሙር ጌታን እምልከን ጨርሰን እንደ ሆነ እርግጠኛ አይደለሁም፤ የሆነ ነገር ወደቀብኝ። ቀስ ብዬ ጀምሬ እጅግ ጮክ ብዬ እሰከ ማልቀስ ደረስኩ። እየተንዘፈዘፍኩ፥ ለረዥም ጊዜ እለ

ቀስኩ። ወንጌላዊ በሰጠ አምልኮውን ማስቆም ነበረበት። ጉባዔውንም በሙሉ ከመዝሙር ወደ ጸሎት መመለስ ነበረበት። በእኔ ዘንድ ብርቱ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ መቃተት ነበረ። ከፊታችን - ማለትም ከእነርሱም ከእኛም ፊት - የሆነ የማይመች ነገር ያለ መሰለኝ። በኋላ ላይ በአገር አቀፍ ደረጃ ስሰ ታውቀው "የይርጋዓለሙ ስደት" እጀማመር መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ እንዲህ ሲል ጽፏል -

> በ1970 ዓ/ም አጋማሽ ላይም በምዕመናን ላይ ቀላል የማይባል ስደት ደርሶአል ... ሚያዝያ 21 ቀን 1971 ዓ/ም ሁለቱ አገልጋዮች ገብተዋል - ፓስተር ተሾመና ፓስተር ኃይሉ። አሁን ሁለት አገልጋዮች ቀርተናል - አስቻለውና ተስፋዬ። ቀጥሎስ? ... ሰኔ 16 ቀን 1971 ዓ/ም ቅዳሜ ... ጥቂት የከተማው ወጣቶች ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ በሩጫ ወደነበርንበት ቦታ መጡ። እንዳንዶቹ ቆመጥ ይዘዋል ... [1]

ከ1972 ዓ.ም. መጨረሻ ገደማ ጀምሮ ፓስተር መርዕድ ስማ፥ ወንጌላዊ ደሣለኝ ደምሴ፥ ወንጌላዊ (በኋላ መጋቢ) ክንፈ ሚካኤል ደበል፥ አኅት ዓለም ብሰራት፥ አኅት ምሕረት በርሄ እና እኔ ሆነን በአንድነት የምናገለግልበት አንድ ጉብረት ነበረን። አገልግሎቱ በተጀመረ ጊዜ ይካሄድ የነበረው በአኅት አልጋነሽ አሰፍሐ ቤት ነበር። በኋላ የሰው ቁጥር በጣም ስለ በዛ ወደ ኖርዌጅያን ሉተራን ሚሲዮን ግቢ ተዛወረ። አሁን ካዛንቺስ መካነ ኢየሱስ የሚባለው ማኅበረ ምዕመናን ቀድሞ ይሰበሰብበት በነበረው አዳራሽ ውስጥ መሰብሰብ ጀመርን።

ይህንን ያመቻቹልን ከይርጋዓለም ጀምሮ ይተዋወቁ እና ይቀራረቡ የነበሩት ፈኒሸዋ ሚስ ራትሻ አኮላ እና የእኔዬቱ ገነት ነበሩ። የዚያ ጉብረት ስብሰባ ከታህ ሣሥ ወር 1973 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ልደታ እና ወደ ዑራኤል (አሁን ካዛንቺስ) መካነ ኢየሱስ ተዛወረ። በዑራኤል የትምህርት ጊዜ፥ በልደታ ደግሞ ስመንፈስ ቅዱስ ሙላት የጸሎት ጊዜ እናደርጋለን። በሳምንት ሁለት ቀናት። አስተባባሪ ዎቹ ስሰ አገልግሎቱ ስመጸስይ በየሳምንቱ እኅት ብርቱካን ቤት እንገናኛለን። አንድ ምሽት በነበረን የጸሎት ጊዜ፥ ወደ አስመራ መዛወሬን ነገርኳቸው እና እንዲጸልዩልኝ ጠየቅኋቸው። ሲጸለይልኝ ያየችውን ራእይ ምሕረት በሌላ ቀን ነገረችኝ።

> "ብቻህን ክህ ... በአንድ በተዘረጋ የእጅ መዳፍ ላይ ዝም ብለህ ትራመዳ ለህ ... መዳፉ ምድረ በዳ ከሚመስል አንድ ቦታ ላይ አስቀመጠህ ...

> አሁንም ዝም ብለህ ትሄዳለህ ... በድንገት ያላየኸው ትልቅ ጎርፍ ይመጣ ብሃል ... እንዳየኸው ግን ትዘል እና ከጎርፉ ወዲያ ማዶ ከአንድ ጉብታ ስፍራ ላይ ካለ ዛፍ ሥር ትቆማለህ ... ጎርፉም ብዙ ሳይቆይ ያልፋል"

የየካቲት 14 ቀን ማስታወሻዬ ደግሞ እንዲህ ትላለች -

> "ዛሬ በአኅት እንዳልሽ ቤት ነው የዋልነው - ከጠዋቱ 5:00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 2:00 ሰዓት ገደማ ድረስ። 18 ያህል ሰዎች ነበርን። ስመስብሰባችን ምክንያት የሆነው የእኔ ወደ አስመራ መቀየር ነው። በዚያ የእግዚአብሔርን ቃል ተካፈልን። ምሣችንን በላን። እንደ ተለመደው ጸለይን - ለገነት እና ለእኔም ተጸለየልን።

> ወደ አስመራ መቀየሬ ከታወቀ ጀምሮ እንደዚህ ዐይነት ነገር በተደጋጋሚ ተደርጓል። በመጀመሪያ በአቶ ብርሃኔ እና በአኅት ፍቅርተ ቤት። ከዚያ በአኅት ምሕረት ቤት። አሁን ያዘጋጁት አብረውኝ ያገለግሉ የነበሩ ወን ድሞች እና እኅቶች ናቸው። ገነት እና እኔ ተንበርከክን እጅ ተጫኖልን ተጸልዮልናል። ከዚያ በዑራኤል መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን። ያንን ያዘጋጁት ደግሞ በዚያ ይገለገሉ ከነበሩት ሰዎች መካከል የተውጣጡ በቁጥር ሠላሳ ገደማ የሚሆኑ ሰዎች ናቸው። ስጦታም ተበርክቶልናል።

> እናቴን ልሰናበት ዎላይታ ሄጄ በነበረበት፥ የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ጉባዔ በሙሉ ቆሞ ጸልዮልኛል። እነ ተስፋዬን (ተስፋዬ ጋቢሶ) ለመሰናበት ወደ ይርጋዓለም ወጎኒ ቤት በሄደኩበትም ጥቅስ ተሰ ጥቶኛል - ዘፍጥረት 28፥15። እንደሚጸልዩልኝም ዐውቃለሁ።

> ነገሩ እጅግ ከመብዛቱ የተነሣ ግራ ገብቶኛል። ለምንድን ነው ይህ ሁሉ የሚሆነው? ስዎች በሥጋቸው ስለሚወዱኝ ነው? ይህንን ያህል ሊደረግ ለት የሚገባ እገልግሎት ኖሮኝ ነው? አይመስለኝም። ሰዎች በሥጋቸው ተገፋፍተው፥ በይሉኝታም እንኳን ተገድደው እንደዚህ ሊያደርጉ እንደ ሚችሉ ብገምትም፥ ምናልባት የእግዚአብሔርም እጅ በነገሩ ሊኖርበት ይችላል ብዬ ደግሞ አስባለሁ። ታዲያ ለምን ይህ ሁሉ እንዲሆን እግዚ አብሔር አደረገ? ምን ሊናገረኝ ይፈልጋል? ምን እንዳስተውል ይፈልጋል? ይህ ሁሉ "አይዞህ"፥ ይህ ሁሉ "እትፍራ"፥ ይህ ሁሉ "እኔ ከአንተ ጋር ነኝ" ለምን? ከፊቴ ምን አለ?

ከእንዳልሽ ቤት ሰንወጣ ወንጌላዊ ደሣለኝ አብሮን ወጣ እና ሊነግረን የሚፈል ገው ጉዳይ እንዳለው አጫወተን። "ታዲያ ለምን እኛ አንሸኘህም እና አታወራ ንም?" አልኩት። "እሺ" አለኝ እና መኪናችን ውሰጥ ገባ። ወደ አብዮት (አሁን መለቀል) አደባባይ እየነዳሁ እያለ -

> "... ይህ ሁሉ እየሆነ ያለው ለምን እንደ ሆነ አላውቅም ... ሁል ጊዜ መል ካም የሚመስለውን ነን ብቻ ግን አትዩ ... ምናልባት ችግር ያጋጥማችሁ ይሆናል ... ምናልባት ብቸኛነት ... በአገልግሎት ነቀፋ ... የልብ ሰብ ራት ... ወዘተርፈ ... በዚያን ጊዜ ይህንን አስቡ ... ከፍታን ብቻ ሳይሆን ዝቅታንም ጠብቁ ..."

አለን። "ትንቢት ነው" አላለንም እንጂ፣ የተናገረው ትንቢት ነበረ።

የሚጠረጥሩ ጥርጣሬዎች

እንደ አተር፣ ባቄላ እና ሽንብራ የመሳለሉትን አህሎኞ በአሸትነታቸው ለንበላ ቸው፣ ከላያቸው ያለውን ገለፈት በጥርሳችን እናነሣለን። እሱ ድርጊታችን "መጠርጠር" ይባላል። የሚጠረጥሩ ያልኩት አሱን ነው። "ጥርጣሬዎች" ያል ኩት ግን አንድ ነገር የሆነበትን ትከከለኛ ምከንያት ባለማወቅ፣ "ስለዚህ ይሆን?"፣ "ስለዚያ ይሆን?" እያልን የምንቸገረውን ነው። ገነት ሰትለየኝ እኔ እንደዚያ ሆኛለሁ። ልትጽፍልኝ አሰባ የነበረውን ደብዳቤ - በእኔው "ልትይኝ የፈለግሽውን ዐውቄዋለሁ፣ መጻፍ አያስፈልግሽም" ባይነት ሳትጽፍልኝ ቀርታ ለች። እኔም ምንም እንኳን የማይመቿትን ድካሞቼን ባውቃቸውም፣ ከእኔ ለመለየት የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ያደረሳትን ምከንያት ከአፏ ሳልሰማ ቀርቻ ለሁ። እና የተለያዩ ምከንያቶችን ጠርጥሬለሁ። ጥርጣሬዎቼም መልሰው እኔኑ ጠርጥረውኛል። ከአፏ ለምቼ ቢሆንም ኖሮ በእነዚህ ጥርጣሬዎቼ መጠርጠሬ አይቀርልኝም ነበር ይሆናል።

ገነት አስተዋይ፣ አርቆ አሳቢ እና ጠንካራም ሠራተኛ ነች። ብርቱ የሆነ፣ አራሷን እና ኑሮዋን የማሻሻል ፍላጎት አላት። አኔም እንደ እርሷ ብሆን አልጠላም ነበር። ግን አይደለሁም። ግድ አያስገደደኝ ካልሆነ በሰተቀር፣ ከውስጤ በሆነ ተነሣሽነት ተነሥቼ የማደርገው ብዙ ነገር የለኝም። አዲስ አበባ እንደ መጣን፣ ቤት ለመግዛት ፈለግን እና አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ አንድ ቤት አየንን። ቀብድ ከፈልን። ቤቱን ሊሸጥልን የነበረው ሰው ግን አታለለን።

ገንዘባችንን ወሰዶ ጠፋ። ገነት እንከለሰው አለቸኝ፤ እኔ ደግሞ ነገሩን ችላ አልኩባት። ገነት ከሰውዬው ባላነሰ፣ በእኔ እንደ ተበሣጨችብኝ ትዝ ይለኛል። ከዚያ በኋላም፣ ቤት ሰለ መግዛት ወይም ቤት ሰለ መሥራት ብዙ ጊዜ እንሥ ታብኖለች። እኔ ግን አልተንቀሳቀሰኩላትም። እንደዚህ ዐይነቱ ድካሜ ይሆን በእኔ ተሰፋ ያስቆረጣት?

ማኅበራዊ ግንኙነት ሌላው የገነት ጠንካራ ጎን ነው። ሰዎችን በቀላሉ ታውቃ ቸዋለች። ከምታውቃቸውም ሰዎች ሁሉ ጋር በቀላሉ ትቀራረባለች። አማኝ ወይም ዓለማዊ ብላ ልዩነት አታደርግም። ትጠይቃቸዋለች፤ እነርሱም ይጠይ ቋታል። እኔ ደግሞ ሻጉራ ብጤ ነኝ። ብቻዬን መሆን እወዳለሁ። ከለዎች ይልቅ ከመጻሕፍት ጋር የበለጠ ጊዜ ባሳልፍ እመርጣለሁ። የታመመ መጠየቅ፣ የወለደ መመረቅ እና የመሳሰለው ነገር ብዙ አይሆንልኝም። በሠርግ እና በለቅሶም ቦታ የምገኘው በመከራ ነው።

አንድ ጊዜ፣ አንዲት ጓደኛዋ ልትጠይቃት አቤታችን መጣች። ሲጨዋወቱ ቆይተው፣ ወደ ቤቷ ለመሄድ ስትነሣ፣ ገነት "በመኪና ሸኛት" አለቸኝ። እኔ ሆዬ ደግሞ "እልችልም" አልኳት። እና ልጅቱ በእግሯ ይሁን ወይም በታከሲ ሄደች። ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ "ያን ዕለት ነበር ልፈታህ የወሰንኩት" ብላኛለች - ገነት። ያንን ውሳኔዋን ነው አሁን በሥራ ላይ ያዋለችው? ወይሰ የአሁኑ ስለ ሌላ ድካሜ የሆነ፣ ሌለ ውሳኔ ነው?

ሌላ ወንድ አፍቅራ ይሆን? አሰመራ እና ምዕራብ ጀርመን በነበርኩ ጊዜ፣ ከሞላ ጎደልም ቢሆን፣ ለሦስት ዓመታት ያህል ተራርቀን ቆይተናል። ወደ አሜሪካ ከመጣችም በኋላ መራራቁ ቀጥሏል። በእነዚህ ከፍተቶች ውሰጥ ሌላ ወንድ ወደ ሕይወቷ አስገብታ ይሆን? እንደዚህ ያለው ጥርጣሬ፣ ሚሰቱን የሚያፈቅር ማንም ወንድ የሚፈተንበት ጥርጣሬ ነው። እንደ ገነት ያለች ቆንጆ፣ ብዙ ሰው የምታውቅ እና ከብዙም ሰው ጋር በቀላሉ የምትግባባ ሴት ደግሞ፣ ለእንደዚህ ዓይነቱ ጥርጣሬ በጣም የተጋለጠች ናት። ወደ አሜሪካ ገና እንደ ሄደች፣ እኔም ሦስት ጊዜ በየዓመቱ ተመላልሼ፣ ለእንዳንድ ወር ያህል አብሬአት ቆይቻለሁ። እውነቱን ለመናገር፣ እንድጠረጥራት የሚያደርገኝ ምንም ምልክት አላየሁም። እንደዚያ ያለ ነገር ቢኖር ኖሮ፣ እኔን ፈትታ የወደደችውን ለው እንዳታገባሰ ምን ይከለክላታል?

ከርስትናዋ እንደሚከለከላት ዐውቃለሁ። ብቸኛነት ይህንን ያህል ከብዷት እንደ ሆነ ማለቴ ነው። ያለዚያ ደግሞ እኔን "አሜሪካ እንድትመጣ እና አብረን እንድንኖር እፈልጋለሁ" የማለት አማራጭ አላት። እንድ ጊዜ፥ "ወደ አሜሪካ ለመምጣት ትፈልጋለህ ወይ? የሥነ መለኮት ኮሌጅ እና ስኮላርሺፕ ላፈላልግ ልህ ወይ?" ብላ ጠይቃኝ ነበር። "ጠቅልለህ ወደ አሜሪካ እንድትመጣ እፈል ጋለሁ" ማለቷ ነበር ይሆን እንዴ? በሕይወቴ ከገነት ጋር አብሮ ከመኖር የበለጠ የምፈልገው ሌላ ነገር የለኝም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመሳትም የበለጠ የምፈራው ሌላ ነገር የለኝም። በዚህ ረገድ፥ እግዚአብሔር "እንዲህ አለኝ" የምለው የጠራ ምሪት ባይኖረኝም፥ ልቤ ካለበት በፍጹም አልተንቀሳቀስም። ወደዚያ በሄድኩባቸውም ጊዜያት ቢሆን፥ የቆይታዬ ጊዜ እጅግ ይረዝም ብኖል። እዚህ ያለውም ነገር ሁሉ እጅግ ይናፍቀኛል። ከዚህም ሁሉ በላይ፥ ሦስቱም ልጆቻችን ያሉት ከእኔ ጋር ነው። ለማን አተዋቸዋለሁ? "እግዚአ ብሔር ይስጥልኝ፥ አልመጣም" አልኳት።

ከእኔ ለመለየት የወሰነችውን ውሳኔ መቀበል አልነበረብኝም ይሆን? አሳቧን ለማለለወጥ መሞከር ነበረብኝ ይሆን? ስናይት (ታላቅ እኅቷ) ከአሜሪካ ደውላ ልኝ፥ እንደዚያ እንዳደርግ መከራኝ ነበር። ያደረገችውን ነገር የነገረቻት ገነት አራሷ ናት። ከዚያ በፊት ሁለት ጊዜ ያህል እንደዚያ አድርጌአለሁ። አንዱን በዚህችው በለናይት ምክር። ተሳከቶልኝም ነበር። ትንሽ ላግደረድራት ይገባኝ ነበር ይሆን? ምን አለበት? ትዳሬ ከመፍረስ የሚድን ከሆነ፥ ከዚያ የሚበልጥ ነገር ባደርግ ምን አለበት?

ትዳሩ ከፈረሰ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ፥ ለአገልግሎት ወደ አሜሪካ መሄድ ነበረብኝ። ደወልኩላት እና "በአሜሪካ መንግሥት ዘንድ ያለው የእንቺ የግል ታሪክ የሚለው ምንድነው? - ያገባች? የፈታች? ወይስ የተለያየች?" ስል ጠየቅ ኋት። "የፈታች" ነው የሚለው አለችኝ። ከዚያ ማለፍ አልቻልኩም፤ ዝም አልኩ። ይህንን ጥያቄ የጠየቅሁበት ሌላም ምክንያት ነበረኝ። በዚያው ሰሞን ፓስፖርቴን ማሳደስ ነበረብኝ። ፎርሙን በምሞላበት ጊዜ፥ ስለ ቤተ ሰቤ ሁኔታ የምጠየቀውን ጥያቄ ምን ብዬ መመለስ እንዳለብኝ እርግጠኛ መሆን ፈልጌአለሁ።

ፎርሙ የሚጠይቀኝን ጥያቄ "የፈታ" ብዬ መለስኩ። እውነቱ እሱ ነው። ለማን ነው የምዋሸው? የኢምግሬሽኗ ሠራተኛ "ፓስተር" የሚለውን ማዕረጌን

እና "የፈታ" የሚለውን የቤተ ሰቤን ሁኔታ ከፎርሙ ላይ አየች እና፥ "የት ቤተ ክርስቲያን ነዎት?" አለችኝ። "ሙሉ ወንጌል" አልኳት። "እናንተም?" አለች። ጥያቄውን እንደ ዘበት ነው የወረወረችው - ከእኔ ይልቅ፥ ሰገዛ አራሷ የተናገረ ችው ነው የሚመስለው። ለእኔስ ቢሆን ኖሮ፥ ምን ልመልስላት እችላለሁ? ምን እፍ አለኝ?

ገነት "ጣዖት" ሆናብኝስ ይሆን? ይስሐቅ ለአብርሃም እንደ ሆነው ማለት ነው። እግዚአብሔር በመካከላቸው ጣልቃ መግባት ነበረበት። የሚወደውን፥ እንዱን ልጁን፥ ይስሐቅን እንዲሠዋለት አብርሃምን ጠየቀው (ዘፍ. 22፥2)። ብንያምም ለራሔል እንደ ሆነው ማለት ነው። ዮሴፍን ስትወልድ "ስሙንም፥ 'እግዚአብ ሔር ሌላ ወንድ ልጅ ጨምሮ ይስጠኝ ስትል፥ ዮሴፍ አለችው" ይላል (ዘፍ. 30፥24)። ዮሴፍ ማለት "ጨምሮ ይስጠኝ" ማለት ነው። ስሙ የወጣው ለለ ዮሴፍ ሳይሆን፥ ስለ ብንያም ነበር።

ዮሴፍን ከወለደች በኋላ ራሔል ልጅ ሳትወልድ ለ15 ዓመታት ያህል ቆይታ ለች። ለምን ለዚህን ያህል ጊዜ እዘገየባት? መሻቷ እስኪጠራ ድረስ ይሆን? በምትወልደውም ጊዜ ስም የምታወጣለትን ያህል ዕድሜ ብቻ ለምን ሰጣት? ሌላ ወንድ ልጅ የምትሻበት ምክንያት የጠራ ስላልነበረ ይሆን? "የሕመሜ ልጅ" (ዘፍ.. 35፥18) አለችው እና ለዘለቄታው ተለየችው። ገነትም እንድትለየኝ የሆነው ለዚህ ይሆን? ጌታን እስቀንቼው (1ቆሮ. 10፥22) ይሆን? ማለቴ ነው። ማን ያውቃል? እነዚህ ከብዙ ፍሊጋ በኋላ የሚገኙ ነገሮች ጣዖት የመሆን ጣጣ አለከትለው ነው የሚመጡት - ከላይ በራሔል እና በአብርሃም እንዳየነው። እና አፈራለሁ።

የማይፈጸሙ ተስፋዎች

እኔ በእምነቴ ጴንጤቆስጤአዊ ከርስቲያን ነኝ። ይህ ጴንጤቆስጤአዊነቴም፥ በአገልግሎቴ ብቻ ሳይሆን፥ በግል ሕይወቴም ጭምር ከእኔው ጋር አብሮ በብርቱ ተፈትኗል። ለፈተና ከዳረጉኝ ነገሮችም እንዱ ትዳሬ ነው። ይህንን ከፍል ለጽፍ፥ ማስታወሻዎቼን እውጥቼ ስለ ትዳሬ ትንቢት የተናገሩልኝን ቅዱ ሳን ቆጠርኳቸው። በዐሥራ ስድስት ዓመታት ውስጥ ዐሥራ ዘጠኝ ስዎች ናቸው። በመካከላቸውም፥ ትንቢት በመናገር ለጠታቸው በእማኞች ዘንድ ብቻ ሳይሆን፥ በዓለማውያንም ሁሉ ዘንድ የሚታወቁ ሦስት ስዎች፥ ሁለት ሁለት

ጊዜ የተናገሩልኝ ደግሞ እምስት ሰዎች አሉባቸው። ይህም የመልእክቱን ቁጥር ሃያ እራት ያደርሰዋል። የመልእክቶቹ ሁሉ ይዘት እንድ - እግዚአብሔር ትዳር ህን ይፈውሳል፤ እግዚአብሔር ትዳርህን ይባርካል - የሚል ዐይነት ነው። ትዳሬ ግን ፈርሷል። ምን ማለት ነው?

ጴንጤቆስጤአዊ ክርስቲያን ልሁን እንጂ፥ "እግዚአብሔር ብሏል" እየተባለ፥ የሚባለውን ሁሉ ዝም ብዬ የምቀበልም ሰው አይደለሁም። የተጻፈውንም እን ኳን ለማመን እና ለመታዘዝ በብዙ የምቸገር ደካማ ሰው ነኝ። በተደጋጋሚ ወደ እኔ ለመጣው የእገልግሎት ጥሪ ምላሽ ለመስጠት የቱን ያህል ጊዜ እንደ ወለደብኝ፥ በምዕራፍ እንድ ገልጫለሁ።

ሐሙስ መጋቢት 25 ቀን 1978 ዓ.ም. ገነት የማሕፀን ዕጢ ለማሰወጣት በቅዱስ ጳውሎስ ሆሰፒታል አፐሬሽን እደረገች። በዚያን ዕለት ጠዋት እኔ ወደ ሆስፒታል አልሄድኩም። አራሴን ፈርቼው እንጂ፥ እንደዚያ ባለው ጊዜ እጠባቧ መሆን ይገባኝ እንደ ነበረ እጥቼው አይደለም። አፐሬሽኑን የሚያደር ገው ዶክተር መኮንን ሲሆን፥ የቅርብ ወዳጃችን ዶክተር ሩትም አብራው ነበረች። ረፋዱ ላይ ዶክተር ሩት ደወለችልኝ እና "ዶክተር መኮንን 'ማሕፀኗ ተበላሽቷል፥ በሙሉ መውጣት አለበት' ይላል። ምን ይሻላል?" አለችኝ። "እንደ ባለ ሞያ፥ እርሱ መደረግ አለበት የሚለውን ሁሉ ያድርግ" አልኳት።

የሆነውን ነገር ለጊዜው ለገነት ላንነግራት ዶክተር ሩት እና እኔ ተማክርን። ሆኖም ምክራችን የዘለቀው ለጥቂት ቀናት ብቻ ነበር። በወጣላት የማሕፀን ዕጢ ላይ ምርመራ (HISTOPSY) ተደርጎ ከካንሰር ነጻ መሆኗ ሲታወቅ ሁለቱንም በእንድነት እንድትለማቸው ሆኗል። እንደኛው ያለ ጥርጥር ቢያሳዝናትም፥ ሁለተኛው ግን ያለ ጥርጥር ደስ አሰኝቷታል። እርሷንም ብቻ ሳይሆን እኛንም ሁላችንን ነበር ደስ ያሰኘን። ሰው በመጀመሪያ በሕይወት ሲኖር እይደል ሰለ ሌላ ሌላው ሁሉ የሚያሰበው?

በዚያው ሰሞን በእንድ፥ እኔ እዘውትሬ በማገለግልበት የእኅቶች ስብሰባ ላይ፥ የሆነውን ነገር ነገርኳቸው እና "እግዚአብሔርን አመስግኑልኝ" አልኳቸው። ከእነዚያ እኅቶች መካከል እንድ ሁለቱ፥ "እግዚአብሔር ሌላ አዲስ ማሕፀን እንደሚገጥምላት እናምናለን" አሉ። እና ጉዳዩን የምሸቱ የጸሎት ርእሳችን እደ

ረጉት። እኔም ያለ ፍላጎቴ እብሬአቸው ጸለይኩ። እንደዚህ ካለው የዋሕነት፥ እንደዚህም ካለው መልካም ምኞት የተነሣ፥ የሚሠሩ ስሕተቶች አሉ።

እንደ "ሎጎሱ" የእግዚአብሔር ቃል፥ እግዚአብሔር ለገነት አዲስ ማሕፀን ሊገጥ ምላት እንደሚችል አምናለሁ። ሆኖም፥ እንደ "ሬማው" የእግዚአብሔር ቃል፥ እንደዚያ እንደሚያደርግ እልነገረንም። ሎጎሱ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ያለው ቃሉ ሁሉ ነው። ሬማው ግን ለገነት እና ለእኔ የሆነው "የጊዜው ቃል" ነው (ምሳ. 25፥11)። እርግጥ እነዚህኞቹ እኅቶች "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እን ደዚህ ይላል" አላሉም።

የሰማኋቸው ትንቢቶች ሁሉ እንደዚህ ያሉ ነበሩ ማለቴ ግን እይደለም። ከእግ ዚአብሔር ናቸው ብዬ በሙሉ ልቤ የተቀበልኳቸው ደግሞ ነበሩባቸው። ለምሳሌ፥ በኅዳር ወር 1985 ዓ.ም. ገነት ዘንድ ነበርኩ። ወደ ገነት የሄድኩት ለሥልጠና እንድ ወር ያህል ከቆየሁበት ከሲንጋፖር ነው። ሲንጋፖር ሆኜ ብዙ ሳስብ እና ብዙም ስጸልይ ነበርኩ፦

> ገነት ከኢትዮጵያ ከሄደች ሦስት ዓመት ሊሞላት ነው ... እኔ ግን ኢትዮ ጵያ ነው ያለሁት ... ላያት ወደ አሜሪካ ስመላለስ አሁን ሦስተኛዬ መሆኑ ነው ... እሰክ መቼ እንደዚህ እንቀጥላለን? ... ይኸ ምን የሚሉት ዐይነት ትዳር ነው? ... በዚህ መራራቅ መካከል፥ ከሁለታችን እንዳችን አንድ ነገር ብንሆን፥ ቅዱሱን ስምህን ልናስነቅፍ አይደለም ወይ? እግዚአብሔር ሆይ፥ በድለንህም እንኳን ቢሆን፥ አባክህን ይቅር በለን ... አባክህን በቃችሁም በለን

ገነት ካለችበት ስደርስ፥ በአሜሪካ ያሉ መጋቢያን በዓመታዊ ኮንፈረንሳቸው ላይ ነበሩ። ዕሑድ ኅዳር 06 ቀን (November 15/92) እነ ገነት ቤተ ክርስቲያን አገለገሉ። በጣም ጥሩ የጸሎት ጊዜ ነበረን። ሦስት መጋቢያን በጉባዔው ፊት ቆመው፥ የጸሎት ጥያቄ ያላቸው ሁሉ ወደ ፊት እየወጡ እጅ እየተጫነ ይጸለይላቸው ነበር። እኔ እና ገነት አልወጣንም። በተለያየ ቦታ ተቀምጠን የየራሳችንን ጸሎት እየጸለይን ነበርን። እኔ ያንኑ የሲንጋፖሩን ጸሎቴን ነው የምጸልየው - እንዳቀረቀርኩ፥ ድምፄንም ሳላሰማ። ምርር ያለ ለቅሶም እያለቀስኩ ነበር የምጸልየው። አንድ ለው ትከሻዬን መታ መታ አደረገ። ቀስ ብዬ ቀና አልኩ። ከሦስቱ ፓስተሮች አንዱ ነበረ። ተነሥቼ

አንድቆም በምልከት ተናገረኝ። ተነሣሁ እና ቆምኩ። እኔ ብቻ እንደምለማው አድርጎ -

> አሁን በልብህ ያለብከውን፥ ለማንም ያልተናገርከውን፥ ሰምቼሃለሁ ... እኔ ቤትህን እንደ ገና እሠራዋለሁ ይልሃል

አለኝ እና ወደ መጣበት ተመለስ። ገነት ከጋበዘቻቸው ሌሎች ሦስት ሰዎች ጋር ምሣችንን ሆቴል በልተን ወደ ቤታችን ስንመለስ፥ የተነገረኝን መልእክት ነገርኳት። "እንደዚህ አለህ?" አለችኝ። "አዎ፥ እንደዚህ አለኝ። ዛሬ በጣም ደስ ብሎኛል" አልኳት። ምንም አልመለስችልኝም።

በግንቦት ወር 1987 ዓ.ም. ደግሞ ሶል፥ ደቡብ ኮሪያ፥ ነበርኩ - "GLOBAL CONSULTATION ON WORLD EVANGELIZATION (GCOWE)" የተባለ ስብሰባ ልካፈል። 200 ከሚሆኑ አገሮች የመጡ 4,000 የሚሆኑ ጉባዔተኞች ነበሩ። በጉባዔው ውስጥ 8 ኢትዮጵያውያን አለን - ከአገር ቤት 6፥ ከኬንያ ፡ ከአሜሪካ ደግሞ ፡። ጉባዔው የ24 ሰዓት የጸሎት እና የምልጃ ሽፋን ነበረው። ከዓለም ዙሪያ በጸሎት እና በምልጃ ጸጋቸው የሚታወቁ ወንድሞች እና እኅቶች፥ የተለየ ቦታ ተዘጋጅቶላቸው፥ በፈረቃ ይጸልያሉ። እነዚህ ሰዎች ስለ ትዳሬ እንዲጸልዩልኝ ልለምናቸው በጣም ፈለግሁ። አንድ ቀን ጉባዔተኛው ለምሣው ሲወጣ፥ እኔ ሹልክ ብዬ ወደሚጸልዩበት ከፍል ሄድኩ። በሩ ላይ ደርሼ ግን ሳልገባ ተመለስኩ። እነዚህ የጸሎት ሰዎች በሚጸልዩባቸው ትልልቅ እጅንዳዎች መካከል የግል እጅንዳዬን ማስገባት ኃጢአት መስሎ ተሰማኝ።

ፍላጎቴ ግን ጨመረ እንጂ አልቀነሰም። ስለዚህ አራሴን አበረታትቼ፥ በሦስተኛው ቀን በዚያው ሰዓት ሄድኩ። ቀስ ብዬ በሩን ነካ ሳደርገው ለካ አልተዘጋም ነበር ተከፈተልኝ። ገባሁ። ከሰድስት ወይም ከሰባት የማይበልጡ ወንዶች እና ሴቶች በጸጥታ ይጸልያሉ። የተንበረከኩ አሉ። በደረታቸው የተዘረጉ አሉ። እግሮቻቸውን አጣጥፈው ምንጣፉ ላይ የተቀመጡም አሉባቸው። እንድ ዐሥራ አምስት የሚሆኑ ባዶ ወንበሮች በዙሪያ ከብ ተዘጋጅተው ተቀምጠዋል። እኔም ድምፄን አጥፍቼ አንድ ጥግ ላይ ተንበረከክሁ እና መጸለይ ጀመርኩ። አንድ ዕሩብ ሰዓት ያህል እንደ ቆየን፥ ከመካከላቸው እንዲት እኅት ሁላችንም ተነሥተን እንድንቀመጥ እዘዘችን። የፕሮግራሙ መሪ መሆኗ ነው። ሁላችንም በዙሪያ ከብ ተዘጋጅተው በነበሩት ወንበሮች ላይ ተቀመጥን።

መሪዋ፥ "በጸሎታችን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለን ወይም ወደ ልባችን ያመጣው ነገር ካለ፥ አሁን እንስማ እና በጋራ እንጸልይበታለን" አለች። ቀስ በቀስ፥ አንድ በአንድ አያሉ፥ ከእርሷ በስተቀር ሁሉም ተናገሩ። በተለያየ አገላለጽም ቢሆን፥ ሁሉም ያሉት እንድ ነገር ነበር። "የጊዜው የጠላት የውጊያ ስልት፥ የቅዱሳንን ትዳር ማወክ እና ማፍረስ ነው። በዚህ ዙሪያ እጥብቀን መጸለይ ያለብን ይመስለናል።" እየተገረምኩ ሰማኋቸው።

እነርሱ ተናግረው ሲጨርሱ መሪዋ፥ "ጠዋት ስንጀምር፥ በዚህ ስፍራ የማይፈለግ ማናቸውም ሰው ወደዚህ እንዳይገባ ይህንን በር በቁልፍ ሳይሆን በጸሎት ዘግተነው ነበር። አሁን ግን አንድ እንግዳ በመካከላችን አለ። መግባት የቻለው በዚህ ስለሚፈለግ ነው ብለን እናምናለን። ማን እንደ ሆነ እና ለምን እንደ መጣ ብንጠይቀውስ?" አለቻቸው። ሁሉም ተስማሙ። "ወንድም፥ ማነህ? ከየት ነህ? ወደዚህስ ለምን መጣህ?" አለችኝ።

ስሜን እና አገሬን ነገርኳቸው። ከትናንትና በስቲያ፥ በዚሁ ሰዓት መጥቼ እንደ ነበረ፥ እነርሱ በሚጸልዩባቸው ትልልቅ እጅንዳዎች መካከል የእኔን የግል እጅንዳ ማስገባት ኃጢአት መስሎ ስለ ተሰማኝ፥ ከበር ላይ መመለሴንም ነገርኳቸው። ከራሴ ጋር ስታገል ትናንትናን እሳልፈ፥ ዛሬ ግን ስላቃተኝ ደፍሬ መግባቴን ገለጽኩላቸው። ከዚያም ችግሬን አጠር አድርጌ ነገርኳቸው፦

> "ባልተቤቴ እና እኔ ሁለታችንም ከርስቲያኖች ነን ... ከሚስቴ ጋር ያልተለያየን ቢሆንም፥ አብረንም ደግሞ አይደለንም ... እርሷ ኢትዮጵያ፥ እኔ ደግሞ አሜሪካ መኖር እንፈልግም ... እና ትዳራችን አደጋ ላይ ነው ... አባካቹሁ ጸልዩልን"

አልኳቸው። በተራቸው፥ እነርሱ ደግሞ ተገረሙ። "መንፈስ ቅዱስ ወደ እያንዳንዳችን ልብ ያመጣውን ነገር፥ አሁን በዚህ ወንድማችን የጸሎት ጥያቄ እረጋገጠልን" አሉ። ከዚያም ለእያንዳንዳችን አንድ እንድ አህጉር ታደለን እና በየአኅጉሩ ላሉ ቅዱሳን ትዳር ጸለይን። ለእኔ የደረሰኝ እፍሪቃ ነበር።

ትንቢት የተናገሩልኝን እነዚያን ዐሥራ ዘጠኝ ሰዎች "ሐሰተኞች ነቢያት" ናቸው ማለቴ አይደለም። በፍጹም። ሁሉንም እንኳን ባይሆን፥ ግማሽ ያህሉን በደንብ ዐውቃቸዋለሁ። ከመካከላቸው አንዳንዶቹ ለግለ ሰቦች፥ ሰቢተ ከርስቲ

ያን እና ለእገር ስለ ተናገሯቸው እና ስለ ተፈጸሙ ትንቢቶቻቸውም ዐውቃ ለሁ። ለእኔ የተናገሩት ለምን እንዳልተፈጸመ ግን አላውቅም።

በግሌ እግዚአብሔር የሚናገረኝ በሕልም ነው። እኔም ያየኋቸው እንድ ሁለት አስገራሚ ሕልሞች ነበሩ። ስለ ትዳሬ ነበር የመለሱኝ። እነርሱም አልተፈጸሙም። እናቴ "ሕልም የጋለሞታ ልጅ ነው" ትላለች። አባቱ አይታወቅም ለማለት ነው። እነዚያ ትንቢቶች እና ሕልሞች ያልተፈጸሙት "የጋለሞታ ልጅ" ስለ ነበሩ አይመስለኝም። "ምስጢር የሆነው ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን ... የእኛ እና የልጆቻችን ነው" (ዘዳ. 29፥29) ብል ነው የሚሻለኝ።

ተምሬአለሁም፥ አልተማርኩምም

የሆነው ነገር ብዙ አስተምሮኛል - ስለ እራሴ፥ ስለ ሰዎች፥ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ እምነት፥ ስለ ጸሎት፥ ስለ ግንኙነት፥ ወዘተርፈ። እንድን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት በአእምሮ በመረዳት እና በተሞከሮ በውስጡ በማለፍ መካከል ለካ ሰፊ ልዩነት ኖሯል? እንደ አገልጋይነቴ፥ መሠረታዊ ስለ ሆኑት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች የተረዳሁትን ያህል በተለየዩ መድረኮች ላይ አስተምሬ ዐውቃለሁ - አገልግሎት "ሀ" ብዬ ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ። ለምሳሌ ስለ ሰው ኃጢአተኛነት፥ ስለ እኛ ስለ ሰዎች የበጎ እና የክፉ ውሑድነት፥ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እና ስለ እግዚአብሔር ቅዱስነት፥ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ እና ስለ እግዚአብሔር ምሕረት፥ ወዘተርፈ።

የማስተምራቸውን እነዚህን እውነቶች በግሌ ልረዳቸው - በመጠኑ ልረዳቸው - የጀመርኩት ግን በገነት እና በእኔ መካከል የሆነው ሁሉ ከሆነ በኋላ ነበር ማለት እችላለሁ። በእራሴም ሆነ በገነት ላይ የተቆጣሁባቸው፥ እ! በጣም የተቆጣሁባቸው፥ ጊዜያትም ነበሩ። ምክንያቶችም፥ ምናልባት በቂ ምክንያቶችም እንኳን፥ ነበሩኝ ይሆናል። አሁን ግን፥ ቁጣ በውስጤ የለም - በገነትም ሆነ በእራሴ ላይ። በሕይወቴ ባለፉት እና እኔም በውስጣቸው ባለፍኩት በእነዚያ ተሞክሮዎቼ እማካይነት ይመስለኛል እግዚአብሔር ይህንን ያስተማረኝ።

ሆኖም ከተማርኳቸው ይልቅ ያልተማርኳቸው ትምህርቶች ይበዛሉ። ማንም ቢሆን ሁሉን ሊማር እንደማይችል ዐውቃለሁ። እኔ ግን ልማራቸው የሚገቡ

ብዙ ነገሮችንም መማር አቅቶኝ ብዙ ጊዜ እራሴን እማኝቼዋለሁ። እስከ ዛሬም ድረስ ያልቻልኳቸው፥ ፈጽሞ ያቃቱኝ ማለቴ ነው፥ ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ ከመንገድ ስገባ፥ በተለይም ከውጭ አገር ስመለስ፥ በጣም እቸገራለሁ። አሁን፥ ከልጆቻችን ሁለቱ የየራሳቸውን ቤት ከመሠረቱ እና ባለ ብዙ ኃላፊነት ከሆኑ በኋላም እንኳን፥ ከውጭ አገር ስመለስ በቤቴ ድግስ ደግሰው የሚቀበሉኝ ጊዜ አለ። እኔ ግን ብዙ ጊዜ ወና ቤት ውስጥ የገባ ሰው ያክል ነው የሚሰማኝ። እና ሆድ ባስ ይለኛል።

ሰዎች ጥንድ ጥንድ (ባል እና ሚስት) እየሆኑ በሚገኙባቸው እንዳንድ ጎብረቶች መገኘትም ይከብደኛል። እንግዶችንም ወደ ቤቴ መጋበዝ ካቃተኝ ቆየሁ። ይህንን እንኳን የቤት ሠራተኞችም ችግር አባብሶታል። ልጆቻችን ካልሆኑ በስተቀር፥ አሁን እሁን ወደ ቤቴ የሚመጣ ብዙ ሰው የለም። እራሴን ጠጋ ብዬ ስመለከተው፥ ወይ በትናንት ትዝታ፥ ወይም በነገ ተስፋ መካከል የሚኖር ሰው ሆኜ አገኘዋለሁ። በካሌንደሬ ውስጥ ትናንት እና ነገ እንጂ፥ ዛሬ ጎልቶ አልታይህ ይለኛል። መጥፎው ነገር ደግሞ፥ ይህንን ሁኔታዬን ለመቀየር ብዙ ተነሣሽነት የሌለኝ መሆኑ ነው - "ለየትኛው ዕድሜ?" እላለሁ።

በአስተዳደር (MANAGEMENT)፥ "የአለመብቃት እርከን" (LEVEL OF INCOMPETENCE) የሚባል ነገር ነበረ። የሰው ዕድገቱ፥ ጉልላቱ ላይ ሲደርስ ማለት ነው። እንድ ሰው ምንም ተደርጎለት፥ ካለው በላይ ብቃት ሊጨመር ለት ከማይችልበት ነጥብ ላይ ሲደርስ ማለት ነው። ለእርከኑ ይህንን ስም ያወጣለት ሰው ዶከተር ሎውረንስ ፒተር ይባላል። ስለዚህም እርከኑ በአስተዳደር ባለ ሞያዎች አካባቢ "የፒተር መርሕ" በመባል ይታወቃል። ሆኖም ፒተር ስም ያውጣለት እንጂ፥ በባለሞያዎቹ ዘንድ ነገሩ ከፒተርም በፊት ይታወቅ ነበር። "የአለመብቃት እርከን" የሚባል ነገር ዛሬም አለ እንደ ሆነ አላውቅም። ይህንን ያነሣሁት፥ እየጻፍኩበት ባለው ርእስ ጉዳይ ረገድ፥ እኔም ከአለመብቃት እርከኔ ላይ ሳልደርስ የቀረሁ አልመሰለኝም ለማለት ነው።

የማይመረጡ አማራጮች

"ያልሰማው ሲመጣ፥ የሰማው ሲሄድ" አሉ ከበደ ሚካኤል? እኔ እንደዚህ ሆኜ ባለሁበት ጊዜ፥ ሁለት እጎቶች ደግሞ ለሁለተኛ ዙር ትዳር ጠየቁኝ። ባለ ትዳር መሆኔን፥ ባለቤቴ በሕይወት መኖሯን እና በእገር ውስጥ ግን አለመኖሯን

ሁለቱም ያውቃሉ። መለያየታችንን ባያውቁም እንኳን፥ ጤናማ የሆነ ግንኙነት በመካከላችን እለ መኖሩን እንዲያው ቀልባቸው ነግሮአቸዋል። የመጀመሪያዋን አጎት ያወቅኋት በሚያዝያ ወር 1991 ዓ.ም. ነው።

ለኮንፈረንስ ከአዲለ አበባ ውጭ በሄድኩበት ነው የተገናኘነው። እርሷ ዘመድ ለመጠየቅ ነው ከአዲስ አበባ የመጣችው። ኮንፈረንሳችንን በሙሉ ተካፈለች። የመጀመሪያውን አገልግሎቴን ስጨርስ ነው፥ ከጉባዔው ተለይታ ወደ ፊት በመምጣት ያነጋገረችኝ። በቅርብ የማውቃቸውን ሰዎች ለም ጠራችልኝ እና በሥጋ ዘመዶቿ እንደ ሆኑ ነገረችኝ። የሞቀ ሰላምታ ለመለዋወጥ እና በየፕሮግራሙ መጨረሻ ላይ ቆም ብለን ስለ ተለያዩ ጉዳዮች ትንሽ ለማውራት ይህ መነሻ ሆነን።

ከአንድ ሁለት ሳምንታት በኋላ ደግሞ አዲስ አበባ ውስጥ ተገናኘን። የተገናኘነው በአንድ መንፈሳዊ ፕሮግራም ላይ ነው። ፕሮግራሙ አልቆ ወደየ ቤታችን ስንበታተን፥ እርሷን የመሸኘት ዕጣ በእኔ ላይ ወደቀ። እየሸኘኋት እያ ለሁ፥ አንድ ልጅ እንዳላት፥ ከልጇ አባት ጋር ግን መለያየታቸውን፥ እርሱ ሌላ ማግባቱን፥ እጫወተችኝ። ቀጥሎ ደግሞ በእርሷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማስተምርበት ሳምንታዊ ፕሮግራም ላይ ተገናኘን። ቤቷ በመንገዴ ላይ ለለ ነበረ፥ በዚያም ምሽት አደረለኳት። እያደረስኳት እያለሁ፥ "የእኔን ነግሬህ፥ የአንተን ሳትነግረኝ" አለችኝ። "ምን ልንገርሽ? ጠይቂኝ" አልኳት። "ቤተ ሰብ አለህ ወይ?" አለችኝ። ሚስቴ አሜሪካ መሆኗን፥ አሁን ያለሁት ከሁለት ልጆቼ ጋር መሆኑን ነገርኳት።

አሁንም በዚያው ሳምንታዊ ፕሮግራም ላይ አገኘኋት። እንዳለፈው ጊዜ አሁ ንም ሸኘኋት። አሁን አፈረጠችው -

"እወድሃለሁ ... ጌታም ተናግሮኛል ... በርህን ከፈት ... ከጌታ ጋር ተስማማ ... በኋላ ይጸጸትሃል ... ብቻህን ሆነህ እገልግሎትህ እንካሣ ነው ... የሚደግፍህ ሰው ያስፈልግሃል ... እገሌን ታውቀው የለም? ... ሙሉ ጊዜውን እንደሚሰጥ ጌታ መጀመሪያ የተናገረው በእኔ በኩል ነበር" አለችኝ።

በጣም ተረጋግቼ፥ "እጎት እገሊት ... እኔ ሚስት አለችኝ እኮ ... እንዲያው እንደ ባለ አእምሮ ለው ብቻ እንኳን ብታስቢው፥ በዕድሜ 20 ዓመታት ያህል አበልጥሻለሁ ..." አልኳት።

"እንድ ዓመትም እንኳን ቢሆን በደስታ መኖር አለብህ ... ሚለትህ ለዚህን ያህል ጊዜ ከተለየችህ እትፈልግህም ማለት ነው ..." አለችኝ። ያን ምሽት በዚሁ ተለያየን።

በሌላ ቀን ሰልከ ደወለችልኝ እና በቁጣ እነጋገረችኝ -

"እንተ የማትወስን ወንድ ነህ ... ለካ በጌታ ቤት መቆየት ሰውን አይለውጥም ... ስለ ዕድሜ ያነሣኸውም ነገር ገርሞኛል ... ከእንግዲህ ላልደውልልህ ወስኛ ለሁ ... ከማይወስን ለው ጋር ጊዜዬን ማጥፋት አልፈልግም ወዘተ ..." አለችኝ።

ይህች እጎት ጥንቃቄ እንደሚያስፈልጋት አሰብኩ። እንድ ቀን ደወልኩላት እና ከእንድ ሆቴል ቀጠርኳት። ለማድረግ ያሰብኩትን ለሚቀርቡኝ እንድ ወንድም እና እንዲት እጎት እማከርኳቸው። መልካም ነው አሉኝ። በቀጠሯችን ሰዓት ተገናኘን እና ከሆቴሉ በረንዳ ላይ ተቀመጥን። ሁለታችንም ጭማቂ አዘዝን እና እየጠጣን፥ ነገሬን ተናገርኩ -

"መጀመሪያ በተገናኘን ጊዜ የቀረብኩሽ የእነ እገሌ ዘመድ መሆንሽን ስለ ነገር ሸኝ ነበር ... አዲስ አበባ በተገናኘን ጊዜ ደግሞ ስለ ትዳርሽ እና ስለ ልጅሽ የነገ ርሽኝ ነገር እንዳዝንልሽና የበለጠም እንድቀርብሽ አደረገኝ ... በሌለ ዓለማ የቀረ ብኩሽ እንዲመለልሽ እድርጌ ከሆነ፥ ባለማወቅ እንጂ ሆነ ብዬ ያደረግሁት ነገር አይደለም ... እዝናለሁ፥ ይቅርታም አለምንሻለሁ ... ባለቤቴ አብራኝ ባትኖ ርም፥ እኔ በቃል ኪዳን ያለሁ ሰው ነኝ ... ደግሞ፥ ባለቤቴ ብታፈርሰውም እን ኳን፥ እኔ ቃል ኪዳኔን አላፈርሰውም ... አንቺ እንደ ወደድሽኝ መግለጽሽ ኃጢ አት የለበትም ... እኔም ከዚህ የተነሣ ምንም ዐይነት ግምት አልወስድብሽም ... ለሌላ ሰውም ስምሽን አላነሣም ... ሆኖም የእንቺ ባል እኔ አይደለሁም ... እግዚአብሔር የእንቺ የሆነውን ሰው እንዲለጥሽ እጸልይልሻለሁ" አልኳት።

ተግባባን። "ሰለ ቃል ኪዳን፥ ሰው እንደዚህ እንዳንኑ ሲናገር ለምቼ አላው ቅም" አለችኝ። ጸልየን ጨረስን። እቤቷ አድርሻት እና "ደኅና እደሪ" ብያት ወደ ቤቴ ሄድኩ። በዚያ ምሽት ላደርገው ያሰብኩትን ላማከርኳቸው ወንድም እና እኅትም ደወልኩላቸውና የሆነውን ሁሉ ሪፖርት አደረግሁላቸው። ሦስታ ችንም "ተመለገን" አልን። በየሄድኩባቸው ሁለት ሦስት ቦታዎች ያገኘኋትን ያችን እኅት፥ ከዚያ በኋላ የትም ቦታ በአካል አግኝቻት አላውቅም። ለጥቂት ጊዜ ግን ተደዋውለን ነበር።

ሁለተኛዋ እኅት ባለ ትዳር ናት። ሆኖም፥ እንደ እኔው ትዳር፥ የእርሷም ትዳር ችግር ነበረበት። አርሷ እና ባለቤቷ ብዙ ሰዎች የሚያውቋቸው የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው። እኔም ሁለቱንም በደንብ ዐውቃቸዋለሁ። አርሷም "አንተን እንዳገባ አማዚአብሔር ተናገረኝ" ነው የምትለው። ጉዳዩን እንዳ ውቀው ያደረጉኝ በነሐሴ ወር 1991 ዓ.ም. ውስጥ ነው። ጠላት ትዳሯን፥ ምስክርነቷን እና ሕይወቷን ሊያጠፋ፥ መሣቂያ እና መሣለቂያ ሊያደርጋት ጨክኖ መውጣቱ ገባኝ። ለእኔም በአንድ ዓመት ውስጥ ሁለት እኅቶችን እንደ አዘጋጀልኝ አለተዋልኩ። ለእራሴም ሆነ ለአርሷ ጸለይኩ። ይህ የአማዚአብሔር ፈቃድ ሊሆን በፍጹም እንደማይችል፥ ጊዜ ወለጀ ላሰረዳት ሞከርኩ። ቀላል አልነበረም። አለመሆኑም አላስገረመኝም - ፈተና አይደል?

በመጨረሻም፥ "ጌታ እራሱ፥ በሕልም እና በራእይ ሳይሆን፥ በአካል ወደ እኔ መጥቶ፥ እገሊትን እንድታገባት ፍጹም ፈቃዱ ነው ቢለኝ እንኳን 'ኖ' አለዋ ለሁ ... ገነት፥ እይደለም በሕይወት አያለች፥ ብትሞትም እንኳን እኔ ሌላ ሚስት ላላገባ ወሰኛለሁ" አልኳት። አሁንም ሊገባት አልቻለም። "እንዴት ሰው ጌታን 'ኖ!' ይለዋል?" ትለኛለች - እየደጋገመች።

እኔም እየደጋገምኩ፥ "... ያገባ መልካም አደረገ፤ ያላገባም የተሻለ አደረገ" እንደሚለው (1ቆሮ. 7፥38) ሰላሉት እንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖች አስረ ዳታለሁ። "ጌታን ያለመታዘዝ ጉዳይ እይደለም፤ የምርጫ ጉዳይ ነው" አላታ ለሁ። የገነትን "የሰእለት ሚስትነት" ግን አልነገርኳትም። አሰፈላጊ አልመሰለ ኝም። ቆይቶም ቢሆን፥ የምላት ነገር የገባት ይመስለኛል። አሳቤን ተቀበለች። ጠላት ካጠመደላት ወጥመድም አመለጠች። ጌታን አጅግ አድርጌ አመሰግነዋለሁ።

የገነት ሌጋሲዎች

በሰፔሊንግ ይለያያሉ አንጂ፥ "ሌጋሲይ" (LEGACY) የኢንግሊዝኛ እና የፈረንሳ ይኛ ቃል ነው። ሌጋሲይ ሰዎች በኑዛዜ ለሌላ ሰው የሚያስተላልፉት ወይም የሚያወርሱት ገንዘብ ወይም ንብረት ወይም ሌላ ማናቸውም ዐይነት አሴት ነው። ሥርወ ቃሉ የላቲን ነው። "ዴሊጌት" ወይም "ዴሌጋሲዮን" ወይም "ዴሊጌሽን" የሚባሉት ቃላት ሁሉ ከዚያው ሥርወ ቃል የተገኙ ናቸው። አንድን መንግሥት ከአገሩ ውጭ አንዲወክል ሕጋዊ ሥልጣን የተሰጠው ለው

ወይም መልእክተኛ ማለት ናቸው። አንዳንድ "የኢንግሊዝኛ-አማርኛ መዝገበ ቃላት" ሌጋሲይን ቅርለ ወይም ውርስ ይሉታል። ልክ ናቸው። ሆኖም እሱ ትርጉም እኔን አላረካኝም።

ቅርስ እና ውርለ ዐጥንት ናቸው፤ መረቅ አብሯቸው የለም። በትርጉም ሥራ ውስጥ ከባዱ ዐጥኑን ከእንዱ ቋንቋ ወደ ሌላው ቋንቋ ማስተላለፍ አይደ ለም። ከባዱ መረቁን (ፍሌቨሩን) ማስተላለፉ ነው የሚመስለኝ። እኔም ብሆን መረቁን ከየትም ላመጣው አልችልም። ስለዚህ ነው የኢንግሊዝኛውን ቃል እንዳለ ወሰጀ ልጠቀምበት የመረጥኩት። እንደዚህ በማድረጌ ማንንም እንደ ማልበድል አርግጠኛ ነኝ - የአማርኛ አንባቢዎቼ እንዳይጎዱብኝ ሌጋሲይ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ፥ ቢያንስ ዐጥኑን አለከ ለጠኋቸው ድረለ። ለለ ሌጋሲይ ይህንን ያህል ካልኩ፥ አሁን ወደ ነገሬ ልመለስ።

ገነት አሁን ከሕይወቴ ወጥታለች። ወይስ አልወጣችም? በስሜታዊው ለሌት የሄድኩ እንደ ሆነ፥ እንኳን ልትወጣ መጀመሪያ ነገር አልተንቀሳቀለችም ማለት እችላለሁ። አሱ ግን አሁን ምንም አይጠቅምም። ምናልባትም ይጎዳል፤ እርሷን ባይሆን እኔን። በተጨባጩ ነገር ላይ ቆሞ መነጋገር ነው የሚሻለው። ተጨባጩም፥ ከሕይወቷ ካስወጣችኝ እና ከሕይወቴም ከወጣች አሁን፥ ይህንን ክፍል በምጽፍበት ጊዜ፥ 16 ዓመት ከመንፈቅ ያለፈ መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ፥ የተወችልኝ ብዙ ሌጋሲዎች አሏት። እና ስለ እነዚህ ሌጋሲዎቿ ትንሽ መናገር እፈልጋለሁ።

ገነት፥ ጌታ እኔን ለማስገር የተጠቀመባት "ብርብራው" ወይም "መንጠቆው" ነበረች። ከገነት ጋር ባልገናኝ ኖሮ፥ ጓደኛዬ እንድትሆን ባልጠይቃት እና አርሷም "እሺ" ባትለኝ ኖሮ፥ የሚሆነው ምን እንደ ነበረ ለመገመት ብዙ ጊዜ ሞከሬ ዐውቃለሁ። ባለ ጸጋው አማዚአብሔር እኔን ከከርሰቶስ ጋር ለማገናኘት ምናልባት ሌላ መንገድ አያጣም ነበር ይሆናል። እኔ ግን ስለዚያ "ሌላ መንገድ" በእርግጠኛነት መናገር አልችልም። ትልቁን እግዚአብሔር በሙከራ (TRIAL AND ERROR)፥ እንደሚሠራ አድርጌ ማሰብም አልችልም። ለለዚህም ገነት ለእኔ የተዘጋጀች ብቸኛዋ ብርብራ፥ ወይም መንጠቆ፥ ወይም - በምዕራፍ አምስት ውስጥ በተጠቀምኩበት የሲ. ኤስ. ሉዊስ ቋንቋ - ብቸኛዋ "ቼክ ሜት" ነበረች ብዬ እምናለሁ።

ወደ እለታ ወንዶ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ የወሰደቸኝ ገነት ናት። ምንም እንኳን ቀደም ሲል በዎላይታ ሶዶ፥ በይርጋዓለም እና በባሌ ጎባ ከተሞች ወዳሉት የፕሮቴስታንት እብያተ ክርስቲያናት ሄጂ የማውቅ ቢሆንም፥ በእነዚያ መሄዶቼም እግዚአብሔር በጠንካራው ልቤ ላይ የማለስለስ እና የማንኳኳት ሥራ እንደ ሠራበት ባውቅም፥ በወሳኙ ጊዜ በወሳኙ ቦታ እንድገኝ ለማድረግ ግን እግዚአብሔር የተጠቀመው በገነት ነበር።

በመንፈሳዊ ሕይወቴ ሥር እንድሰድድ፥ ጥልቅ የሆኑትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች በተሞከሮ ጭምር እንዳውቃቸው (ቃሉ በሕይወቴ ሥጋ እንዲሆን ማለት ነው)፥ የእራሴን እና የሌሎችንም ድካም እንድገነዘብ፥ ከእግዚአብሔርም ጋር እንድጣበቅ ለማድረግ፥ ገነት በእግዚአብሔር እጅ የተያዘች መሣሪያ ሳት ሆን እልቀረችም። ትዳራችንን በተመለከተ ለእንዳንድ የሚቀርቡን ወዳጆቻ ችን፥ "ልቤ እምቢ አለኝ"፥ "እግዚአብሔር ልቤን እንዲለውጥልኝ ጸልዩልኝ" ስትል ብዙ ጊዜ ነው የሰማኋት። ልቧ ምን ነካው ይባላል? መቼስ ጀመረው ይባላል? ለእነዚያ ሁሉ ዓመታት ከገዛ ልቧ ጋር ያደረገችው ትግል፥ እኔን ከጌታዬ ጋር ለማጣበቅ የምትከፍለው ዋጋ ይሆን? መልስ ከሌላቸው ጥያቄዎቼ አንዱ ሆኖ ይቆጠርልኝ።

ሌሎቹ የገነት ሌጋሲዎች ልጆቻችን ራሔል ወንድም አገኘሁ፥ ጌዲዎን እሉላ እና የሴፍ ይድነቃቸው ናቸው። ራሔል ትንሽዋ እኅቷ ስትሆን፥ ጌዲዎን ብቸኛው ልጇ ነው። የሴፍ ደግሞ የታናሽ ወንድሟ የይድነቃቸው ልጅ ነው። ራሔል እና የሴፍ ከእኛ ጋር መኖር ሲጀምሩ የስድስት እና የአራት ዓመት ልጆች ነበሩ። እኔን "መሬት ለማስያዝ"፥ እኔን "መሬት እንዳልለቅ" ለማድረግ፥ እግዚአብሔር በእነዚህ ልጆች በእጅጉ ተጠቅሞባቸዋል። አሁን እንደ ገባኝ፥ ሁሉን የሚያውቀው እግዚአብሔር እነርሱንም "ልጆች ሁኑት" ብሎ ለእኔ ሰጥቷቸዋል። እጅግ እድርጌ እመሰግነዋለሁ።

እንደሚመስለኝ፥ እግዚአብሔር እርሷን ለእኔ የቱን ያህል ለበረከት እንደ እደረጋት፥ ገነት አታውቅም። የዚያኑ ያህል ደግሞ፥ በእነዚህ ሌጋሲዎቿም እግዚአብሔር የቱን ያህል እንደ ባረከኝ፥ አታውቅም። አስከነ አካቴው፥ በእኔ ዘንድ የተወችው ሌጋሲይ እንዳላትም እንኳን የምታውቅ አይመስለኝም። ብዙ ጊዜ ነው "ሕይወትህን አበላሽሁብህ" ስትለኝ የሰማኋት። ከምን እቅጣጫ

እያየችው እንደ ሆነ አላውቅም። እኔ ደግሞ - ሁል ጊዜም እንኳን ባይሆን ብዙ ጊዜ - "ሕይወቴን እንዳበለጸገችው እንዴት ብዬ ልንገራት ይሆን?" ነው የምለው። አሁን ግን ይኸው፥ ይህችን መጽሐፍ ከሚያነቡ ሁሉ ጋር አብራ፥ እርሷም ለመጀመሪያ ጊዜ ሰማችው።

ማስታወሻ

1. ተስፋዬ ጋቢሶ፤ "በዚያን ጊዜ" አሳታሚ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን፤ 2002 ዓ/ም ገጽ 16፥19፥ 22፥ 26።

ምዕራፍ ስምንት

ጣልቃ እየገባ

በዚህች መጽሐፍ ዓውድ መሠረት፥ አቅጣጫ ለማለለወጥ ወይም ደግሞ ቀድሞውኑ ወደ ተተለመለት አቅጣጫ ውስጥ መልሶ ለማስገባት፥ የሚደረግ ነገር ነው - ጣልቃ መግባት። የመጽሐፍ ቅዱሱ አግዚአብሔር፥ ጣልቃ በመግባት አጅግ የታወቀ አምላክ ነው - በግለ ሰብ፥ በቤተ ክርስቲያን፥ በሕዝብ እና በአገር ታሪክ። አነዚህ አራቱም ከዐቅማቸው በላይ የሆነባቸውን ነገር ሊያደርግላቸው ነው ጣልቃ የሚገባው። ጣልቃ ሲገባም አንዳንድ ጊዜ የተፈጥሮን ሕግ አለክ መጣስ ይደርሳል። ያን ጊዜ "እግዚአብሔር ተአምር አደረገ" ይባላል። "ትንግርት" የምንለው እንደሱ ያለውን ነገር ነው። አግዚአብሔር ጣልቃ የሚገባው አልፎ አልፎ ነው። አግዚአብሔር ጣልቃ የሚገባው "ሁል ጊዜ" አይደለም። ሁል ጊዜ ጣልቃ ከተገባ፥ የተገባው "ጣልቃ" አይሆንም።

"ለምን ጣልቃ?" የሚል ጥያቄም ይነሣል። አግዚአብሔር የሚመራን ሁል ጊዜ አይደለም አንዴ? አይመለለኝም። ሁል ጊዜ የሚመራን ከሆነማ ጣልቃ መግባት ለምን ያስፈልገዋል? ጣልቃ የሚገባውም አንዳንድ ጊዜ በራሱ ተነሣሽነት፥ አንዳንድ ጊዜም የለዎችን ጸሎት ለመመለስ ነው። ለምሳሌ አባታችንን አብርሃምን በመጀመሪያ ከከለዳውያን ዑር ሲጠራው፥ በዚያ ሰው ሕይወት - ከአርሱ በኋላም የሥጋ ዝርያዎቹ በሆኑት እና ባልሆኑት ሁሉ ሕይወት - ጣልቃ መግባቱ ነበረ። ያንን ጣልቃ ገብነት ያደረገው ግን ተለምኖ አልነበረም፤ በራሱ ተነሣሽነት ነበረ። ኤርምያስን "ወደ አኔ ጨኽ፤ አኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና የሚይመረመር ነገር አገልጥልሃለሁ" ሲለው (ኤር. 33፥3)፥ "ጣልቃ አገባለሁ" ማለቱ ነበረ። ጣልቃ የሚገባውም ለኤርምያስ ብቻ ሳይሆን፥ ለይሁዳም ጭምር ነበረ። ጣልቃ የሚገባው ግን በራሱ ተነሣሽነት ሳይሆን፥ በኤርምያስ ጩኽት ነበረ።

ከሩቅ ስናያቸው ቀላል እና ተራ የሚመስሉን አንዳንድ ነገሮች፥ ቀረብ ብለን ስናያቸው ቀላልም ተራም እንዳይደሉ አናስተውላለን። ውስብስብ ናቸው፤ ወላ

ኝም ነበሩ። ለምሳሌ ሰው የአራሱን ሕይወት ይመራል። የወደደውን እና የፈለገውን ነገር - በተወሰነ ደረጃም ቢሆን - ማድረግ ይችላል ማለት ነው። አንደዚሁም ሰው የቤተ ሰቡን፥ የአገርን እና የቤተ ክርስቲያንንም ሕይወት ይመራል። የወደደውን እና የፈለገውን ነገር - በተወሰነ ደረጃም ቢሆን - ማድረግ ይችላል ማለት ነው። "አለክ ምን ደረጃ ድረስ?" የሚለውን የሚወሰኑ፥ ብዙ ተፈጥሮአዊ እና ሰብአዊ፥ ውሰጣዊ እና ዉጫዊ ሁኔታዎች ሁል ጊዜ፥ በሁላችን ዙሪያ አሉ። አነዚህ ተፈጥሮአዊ እና ሰብአዊ፥ ውስጣዊ እና ዉጫዊ ሁኔታዎችም - ተወደደም ተጠላም - በሁለት መንፈሳዊ ኃይሎች ተጽዕኖ ሥር ናቸው - በአግዚአብሔር እና በሰይጣን። ጣልቃ መግባት ያሰፈለገው ለዚህ ይሆን?

ከጥቂት ሳምንታት በፊት ከሔዋን (የነነት አኅት፥ የስናይት ልጅ) ጋር ስንጫወት፥ የሆነ ነገር አንሥታ "አንዲያው ብቻህን ..." አለችኝ።

አኔም "አይ፥ ብቻዬን እንኳን አይደለሁም፤ አምስት አራሴን ነኝ" አልኳት። ከብዙ ዓመታት በፊት ከአቶ (በኋላ ዶከተር) ተሰፋ ጽዮን ደለለው የሰማሁት አባባል ነው። አርሱ ያለኝ ግን "አራት እራሴን" ነበር። አምሰተኛውን አኔ ነኝ የጨመርኩት።

"አራቱ ደግሞ አነማን ናቸው?" ለትል ጠየቀችኝ።

"አብ፥ ወልድ እና መንፈለ ቅዱስ" አልኳት።

"ከአንተ ጋር አራት ሆናችሁ ማለት ነው፤ አምስተኛውስ?" ሰትል አሁንም መልሳ ጠየቀችኝ። "አምሰተኛውማ ሰይጣን ነው" አልኳት። ንግግሬ አንዳስገረማት ያኔውንም አይቻለሁ። አሁን፥ ይህንን ከፍል ከመጻፌ ሦስት ቀናት ቀደም ብሎ፥ ደወለችልኝ እና -

"ጋሽ በቅዱ፥ አሁን የሆኑ ወዳጆቼ ቤት ሆኜ ነው የምደውልልህ ... በቀደም ዕለት 'ብቻዬን አይደለሁም፥ አምስት አራሴን ነኝ' ያልከኝን ብነግራቸው፥ በምንም ዐይነት ሰይጣን አሱጋ ሊቀርብ አይችልም አሉኝ ... አከራሪ አርቶዶ ከሶች ናቸው ... ምን ልበላቸው?" አለችኝ። አኔም -

"ይህንን ሰይጣን ከአንዳንድ ሰዎች ዙሪያ 'አርባ ከንድ ይርቃል' የሚባለውን ተረት 'አርሱት' በያቸው ... ኢዮብን ሊከስሰው ከመላእክት ጋር አብሮ በአግዚአ

ብሔር ፊት የቆመ ሰይጣን ... በእካል ወደ ጌታ ኢየሱስ የመጣው እና ደጋግሞ የፈተነው ሰይጣን ... ወደ በቀለ እንዳይቀርብ ምን ይከለክለዋል?" አልኳት::

"የሞባይሌን ድምፅ LOUD ላይ አድርጌዋለሁ ... እየሰሙህ ናቸው ... ተናገር" አለችኝ::

እኔም - "ጳውሎስ ለአገልግሎት ወደ ተሰሎንቄ እንዳይሄድ ሰይጣን ደጋግሞ እንደ አዘገየው (1ተሰ. 2፥18)፥ ከርስቲያኖችም ከሰይጣን ጋር ሁል ጊዜ በፍል ሚያ ላይ እንደ ሆንን (ኤፌ. 6፥10-18)፥ ፍልሚያውን በምናፋፍምበት ጊዜ 'የሰላም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል' እንደ ተባለ (ሮሜ 16፥20)፥ ፍልሚያውን ረገብ በምናደርግ ጊዜ ደግሞ፥ አራሳችን ላይ ቤቱን ከመሥራት እንደማይመለስ" ልነግራቸው ጀምሬ ነበር:: የሞባይል ኔትዎርክ መነጋገር ሳያስችለን ቀረ እንጂ:: ምናልባት መናፍስቱ ተጽዕኖ እድርገውበት ይሆናል::

በትንሹም፥ በትልቁም

ኤርምያስ ሲደልይ "እግዚአብሔር ሆይ፤ የለው ሕይወት በራሱ እጅ እንዳል ሆነች፥ እካሄዱንም በራሱ አቃንቶ ሊመራ እንደማይችል ዐውቃለሁ" ብሏል (ኤር 10፥23):: ሌላ ምን ማለት ይችል ኖሯል? ገና በልጅነቱ እግዚአብሔር "በማሕፀን ሳልሠራህ ዐወቅሁህ፤ ከመወለድህ በፊት ለየሁህ፤ ለሕዝቦችም ነቢይ እንድትሆን ሾምሁህ" አለው (ኤር. 1፥5):: የሕይወቱ ዕጣ ፈንታ (DESTINY) በእርሱ በራሱ እጅ እልነበረም ማለት ነው::

"... እንዴት እንደምናገር አላውቅም፤ ገና ሕፃን ልጅ ነኝና" በማለት ለመከራከር ሞክሮ ነበር:: ከእግዚአብሔር ጋር ተከራክሮ ሊረታው የሚችል ግን ማንም የለም:: "'ገና ሕፃን ልጅ ነኝ' አትበል ... እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ..." አለው (1፥7-8):: ከመወለዱ በፊት እግዚአብሔር ያወቀውን እና ለራሱ የለየ ውን ሰው፥ "... አድንህ ዘንድ ከእንተ ጋር ነኝና ..." ማለት ለምን ያስፈልጋል? ሌላ ጣልቃ ገቢ ስላለ አይደለም?

ባለፉት የዚህች መጽሐፍ ለባት ምዕራፎች ውስጥ፥ እግዚአብሔር በሕይወቴ ጣልቃ የገባባቸውን የተለያዩ ኢጋጣሚዎች እነሣለቻለሁ:: "ጣልቃ መግባት" ከሚለው አሳብ ጋር በቀጥታ ሳላያይዛቸው እንዲያው ዝም ብዬ ያነሣሣኋቸው ኢጋጣሚዎችም አሉ:: በዚህች ንዑስ ርእስ ሥር ደግሞ በጣም ተራ የሚመስል፥

ነገር ግን በሕይወቴ ሦስት በጣም ወሳኝ ፈርጆች የነበሩትን፥ የእግዚአብሔርን እንድ ጣልቃ ገብነት እሦላለሁ:: እሱም እንዴት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሠራተኛ እንደ ሆንኩ ነው::

የመጀመሪያው በጣም ወሳኝ ፈርጅ፥ ባንክ ባልገባ ኖሮ በ1964 ዓ.ም. የመጨረሻ እሩብ ባሌ ነባ አልገኝም ነበር፤ ባሌ ነባ ባልገኝ ኖሮ ገነትን አላገኛትም ነበር፤ ገነትን ባላገኛት ኖሮ ...:: ሁለተኛው በጣም ወሳኝ ፈርጅ፥ ባንክ ባልገባ ኖሮ በ1966 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ አለታ ወንዶ አልሆንም ነበር፤ አለታ ወንዶ ባልሆን ኖሮ ከሚስተር ፋርገር ጋር አልገናኝም ነበር፤ ከሚስተር ፋርገር ጋር ባልገናኝ ኖሮ ...:: ሦስተኛው በጣም ወሳኝ ፈርጅ፥ ባንክ ባልገባ ኖሮ ከ1967 ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ የይርጋ ዓለም ከተማ ነዋሪ አልሆንም ነበር፤ የይርጋ ዓለም ከተማ ነዋሪ ባልሆን ኖሮ ከእነ ወንጌላዊ ተሾመ ጋር አልገናኝም ነበር፤ ከእነ ወንጌላዊ ተሾመ ጋር ባልገናኝ ኖሮ ...::

እና ባለ ሦስት ፈርጁ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት በሕይወቴ እንዴት ተከናወነ? በመስከረም ወር 1957 ዓ.ም. የመጨረሻ ሳምንት፥ የአገር ውስጥ ገቢ ዋና መሥሪያ ቤት ወደ ሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ቢሮው እዛወረኝ:: ወደ ይርጋ ዓለም ከመሄዴ በፊት (የጠ/ግዛቱ ዋና ከተማ ያኔ ይርጋዓለም ስለ ነበረ)፥ ወደ ዎላይታ ሶዶ ሄጀ እናቴን እና ልጆቼን እየጎትኩ:: ከዚያ ስመለስ፥ ሻሸመኔ ላይ ወደ ይርጋዓለም በሚወስደኝ አቶቡስ ተሳፈርኩ:: አቶቡሱ በቂ ተሳፋሪዎችን እስከሚያገኝ ድረስ ቆሞ አያለ፥ የኢትዮጵያ ሬድዮ የእኩለ ቀን ፕሮግራሙን እያስተላለፈ ነበረ::

ዐይኖቼ በሻሸመኔ መንገድ ላይ የሚካሄደውን ግር ግር እያዩ፥ ጆሮቼም በዙሪያዬ የሚንቻቻውን ወሬ እያዳመጡ፥ አእምሮዬም ከእንዱ አሳብ ወደ ሌላው አሳብ በፍጥነት እየዘለለ ባለበት፥ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሥራ ፈላጊዎች ያወጣው ማስታወቂያ በኢትዮጵያ ሬድዮ እየተነገረ ነበረ:: ድንገት ነበር ማስታወቂያውን የሰማሁት:: በዚያ ትርምስ ውስጥ እንዴት ልሰማው እና እንዴትስ ትኩረት ልሰጠው እንደ ቻልኩ ይገርመኛል:: ይርጋዓለም እንደ ደረስኩ፥ ማመልከቻዬን ጽፌ፥ የዘኛ ከፍልን ያጠናቀቅሁበትን የትምህርት ማስረጃ ፎቶ ኮፒ አያይዤ፥ በፖስታ አድራሻቸው ላክሁላቸው:: የገንዘብ ሚኒስቴርን ፈተና ለመፈተን እንደ አደረግሁት፥ አሁን ዲፕሎማ ፎርጅ ማድረግ አላሰፈለገኝም::

አመልካቾች አንድ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ለፈተና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቬርሲቲ አራት ኪሎ ካምፓስ መገኘት አለባቸው። ከዚያ ቅዳሜ ቀደም ብሎ ባለው ዓርብ ዕለት በአቶቡስ ተሳፍሬ አዲስ አበባ መጣሁ። አንደ ገባሁም ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፔርሰኔል ከፍል መንገዴን አቀናሁ። የቀኑ የሥራ ሰዓት ሊጠናቀቅ አሩብ ሰዓት ያህል ሲቀረው ነበር የደረስኩት። ሠራተኞቹ በዓርብ ምድር፥ ከሥራ ሊወጡ ጥቂት ደቂቆች ሲቀሯቸው፥ የመጣውን ይህንን ባለ ጉዳይ ማስተናገድ በፍጹም ደስ አላሰኛቸውም። ይህ ባለ ጉዳይ፥ አግዚአብሔር "ጣልቃ" አየገባለት ያለ ሰው መሆኑን በጊዜው ማን ዐውቆት?

የነገ ተፈታኞችን በተመለከተ፥ የሚሠራው ሥራ ሁሉ ተሠርቶ አንደ አለቀ ነገሩኝ። ከብዙ ሳምንታት በፊት በፖስታ አድራሻቸው ማመልከቻ ለማስገባቴ የፖስታ ቤት ደረሰኜን በአስረጂነት አሳየሁ። እኔ የምኖረው በሌላ የመንግሥት ሥራ ላይ በሌላ ጠቅላይ ግዛት በመሆኑ፥ በአካል ልመጣ አለመቻሌን አስረዳሁ። ማመልከቻዬ ተፈልጎ ተገኘ። አሪጅናሉን የትምህርት ማስረጃህን አልላ ከልንም አሉኝ። ፎቶ ኮፒውን ከማመልከቻዬ ጋር መላኬን፥ አሪጅናሉን ግን አሁን ይገፈው መምጣቴን ተናገርኩ። ወዲያውም ከማጎደረ ላጥ አደረግሁ አና ሰጠኋቸው።

በቀላሉ በጅ አላሉኝም። ተከራከርኳቸው። በመጨረሻም የከፍል ኃላፊውን፥ በኋላም ወዳጄ አና በጊታም ታላቅ ወንድሜ ሆኖ ያገኘሁትን፥ አቶ ሠመረ ዘርዑን አነጋገሩት። "ተቀበሉት" አላቸው። የመጨረሻው አመልካች አድርገው መዘገቡኝ። ለትንሽ ተረፍኩ። የጠቅላይ ግዛቱ አቶቡስ አዘግይቶኝ ቢሆን ኖሮ፥ የሥራ ሰዓት ካለፈ በኋላ ደርሼ ቢሆን ኖሮ፥ ... ኖሮ ... ኖሮ። ቢያንስ በነገው ፈተና ላይ መቀመጥ አችላለሁ። ቅዳሜ ከለዓት በኋላ ፈተናውን ወሰጄ፥ በማግሥቱ ዕሑድ ወደ ይርጋዓለሜ ተመለስኩ።

ከጥቂት ወራት በኋላ ወዳጄ አቶ ዘዘ ሎራቶ ደወለልኝ አና ፈተናውን ማለፌን አበሠረኝ። እኔም ወዲያው ከሥራዬ በፍቃዴ ለመሰናበት ማመልከቻ አስገ ባሁ። የአገር ውስጥ ገቢው ሹም በጥያቄዬ ተስማሙ። በጅሮንዱ ግን ጠመሙ።

"አንተ ልጅ፥ አልለቅህም ነው የምልህ፤ ዐርፈህ ትሠራ አንደ ሆነ ዐርፈህ ሥራ" ይሉኛል። ዝም ብዬ ከፈታቸው አወጣለሁ። በማግሥቱ ወይም በሣልስቱ

አመጣ አና አንደ ገና አፈታቸው አቆማለሁ። አርሳቸውም ያንኑ ነገር ደግመው ይሉኛል። አንድ አምስት ጊዜ አንደዚህ ተመላለሰን መሰለኝ። መጨረሻ ላይ -

"የት ነው ሥራ ያገኘኸው?" ሲሉ ጠየቁኝ።

"ኧረ አኔ ሥራ አላገኘሁም ... መሥሪያ ቤቱን መልቀቅ የፈለግሁትም ሥራ ለመቀየር ብዬ አይደለም" አልኳቸው።

"ታዲያ ለምንድነው?"

"ትምህርት ቤት ለመግባት ነው" ውሸቴን ነበር።

"አውነትህን ነው?"

"አዎን፥ አውነቴን ነው"

"አይ፥ አንደዚህስ ከሆነ፥ በቃ አፈቅድልሃለሁ" አሉ አና ማመልከቻዬ ላይ ምልክት አደረጉበት። ከሰምንት ዓመታት በኋላ ከገነት ጋር ስንጋባ፥ በጅሮንድ አሉላ ወልደ ሰማያት አማቼ ሆኑ። ከሁለት ተኩል ዓመታት በፊት ጀምሮ፥ ባለቤታቸው ወይዘሮ ጤናዬ የጌዴዎን ሁለተኛ አናት፥ አርሳቸውም የጌዴዎን አባት ሆነው ነበሩ።

"አግዚአብሔር አስወጣኝ አንጂ፥ አርለዎ አኮ ገንዘብ ሚኒስቴር አስቀርተውኝ ነበር" አልኳቸው አንድ ጊዜ - ለንጫወት።

"ልጅ በቀለ፥ ቂም ይዘህብኛል ማለት ነው?" ሲሉ ጠየቁኝ።

ቀልዴን አንደ ሆነ፥ ቂም የሚባል ነገር ግን በፍጹም አንዳልያዝኩባቸው አረጋገ ጥኩላቸው። አንዴት ቂም አይዝባቸዋለሁ? በጊዜው ዕውቀቱ ባይኖረኝም፥ ጉዳዬ ተይዞ የነበረው በዋናው ባለ ጉዳይ፥ ማለትም በአግዚአብሔር እጅ አልነበር?

በታሕሣስ ወር 1967 ዓ.ም. ውስጥ ይመስለኛል፥ አለቃዬ አቶ መሐሪ ይሥሐቅ ከሐዋሳ ስልክ ደውሎ ወደ ይርጋዓለም ሊያዛውረኝ አንደሚፈልግ አና በቅድሚያ ግን ፈቃደኛነቴን ማወቅ አንዳለበት ነገረኝ።

"ለምን? አለታ ወንዶ ወይም ይርጋዓለም ምን ተፈጠረ?" አልኩት። አለታ ወንዶ ምንም አልተፈጠረም። ቢፈጠር ኖሮ፥ በደረጃው ከዚያ ይልቅ ከፍ ወዳለ ቅርንጫፍ ላዛውርህ አንደማይለኝ ገለጸልኝ። ፈቃደኛነቴን ነገርኩት።

በመርሕ ደረጃ፥ እንድ ሠራተኛ በአንድ ቅርንጫፍ ቢያንስ ሁለት ዓመታት ማገልገል አለበት። አሱ መርሕ ግን ብዙ ጊዜ በሥራ ላይ አይውልም። ለምሳሌ እኔ በባሌ ጎባ አራት ዓመታት ልደፍን ምንም ያህል አልቀረኝም ነበር - በመርሕ ደረጃ የተቀመጠውን የአገልግሎት ዘመን እጥፍ ማለት ነው። ይህም ደግሞ እጅግ ዘገየ፤ የዘገየው ግን ገነት የራሷን ጣጣ ጨርሳ ጎባ እስክትመጣ ድረስ ነበር።

ከአለታ ወንዶ የተዛወርኩት ግን ሁለት ዓመት ሳይሞላኝ ነው። የሚረከበኝ ሰው ደግሞ በባንክ ቆይታው የእኔም የይርጋዓሰሙም ሰውዬ ታላቅ (SENIOR) ነው። ወደ አለታ ወንዶ የሚመጣውም ከባሕር ዳር ቅርንጫፍ ተዛውሮ ነው። የባሕር ዳሩ ወደ አለታ ወንዶ፥ የአለታ ወንዶው ወደ ይርጋዓለም ከሚዛወሩ፥ ለምን የባሕር ዳሩ በቀጥታ ወደ ይርጋዓለም አይዛወርም? እንደዚያ ቢደረግ ኖሮ፥ ለባንኩ ሎጂስቲካዊ ጣጣው ይቀልለት አልነበረም? የማጓጓዣ ወጭውስ ይቀንስለት አልነበረም? አለቆቼ ግን ይሽ የሚጠፋቸው አይደሉም። ያለ ጥርጥር ባንኩ ከሁለቱ ሰዎች ጋር የሆነ ጉዳይ ነበረው። ባንኩ ብቻም ሳይሆን፥ ምናልባት እግዚአብሔርም ከሁለቱ ሰዎች ጋር የሆነ የሆነ ጉዳይ ነበረው ይሆናል።

የዚህች መጽሐፍ ጉዳይ ስላልሆነ፥ ወደዚያ ውስጥ አልገባም። ከእኔ ጋር ግን፥ ባንኩ ሳይሆን እግዚአብሔር፥ ብርቱ ጉዳይ ነበረው። ወደ አለታ ወንዶ ያመጣኝ ያንን ብርቱ ጉዳይ ለማከናወን ነበር። ያንን ጉዳዩን አሁን አከናውኖ ጨር ሷል። ብርቱ ብቻ ሳይሆን፥ ጉዳዩ ቀጣይነትም ያለው ነው። ቀጣዩ የጉዳዩ ክፍልም የሚከናወነው በአለታ ወንዶ ሳይሆን በይርጋዓለም ነው። ስለዚህም ባንኩ እኔን ወደ ይርጋዓለም ማዛወር ነበረበት - በመርሕ ደረጃ ያስቀመጠውን የአገልግሎት ዘመን ገና ያላጠነቀቅሁ ቢሆንም። ምክንያቱስ? ቢባል፥ ምክንያቱማ እግዚአብሔር ለሕይወቴ ወዳለው፥ ወደ ቀጣዩ እጅጉዳው ሊያሸጋግረኝ ነው። በአጭሩ ጣልቃ መግቢት ፈልጓል። ጣልቃ መግቢያውም ጊዜ አሁን ነው - እንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርም ከጊዜ ጋር ይሽቀዳደማል ልበል?

የሙሉ ወንጌል አማኝ

ይርጋዓለም እንደ መጣን፥ ገነት እና እኔ ዕሑድ ዕሑድ ቀጥ ብለን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ መመላለስ ጀመርን። በዚያም የመካነ ኢየሱስ

ሆስቴል ዳይሬክተር ክነበረው ክአቶ (በኋላ ዶክተር) ተክሥተ ተክሉ ጋር ተዋወቅን። ተዋውቀን ብዙም ሳንቆይ፥ ተክሥተ አንድ ከሰዓት በኋላ ደወለልኝ እና "ክርስቲያን በሥራ ገበታው ላይ" በሚል ርእስ የፓነል ውይይት እያዘጋጀ እንደ ሆነ ነገረኝ። ከተወያዮቹም አንዱ እንድሆን ጠየቀኝ።

ተክሥተ ይህንን ጥያቄ በሚያቀርብልኝ ጊዜ፥ እኔ የማውቀው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል፥ እግዚአብሔርም ቅዱስ፥ ሰውም ኃጢአተኛ፥ ኢየሱስም የኃጢአተኛው ሰው አዳኝ ስለ መሆናቸው እና እነዚህን ስለሚመሰስሉ እንዳንድ መሠረታዊ እውነቶች ብቻ ነበር። ስለ ቤተ ክርስቲያን፥ ስለ ክርስቲ ያናዊ ሥነ ምግባር እና ስለ መሳሰሉት ጉዳዮች ገና ምንም አላውቅም። ሆኖም በአላዋቂ ሰው ድፍረት፥ ለተክሥተ ጥያቄ እምንታዊ ምላሽ ሰጠሁ።

ውይይቱ እንድ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ በሆስቴሉ አዳራሽ ውስጥ ተካሄደ። ውይይቱን ጨርሰን ስንወጣ፥ እንደ ተለመደው በሩ ላይ ቆም ብለን ስላምታ መሰዋወጥ እና ስለ ውይይቱ የሆነ የሆነ ነገር መባባል ተጀመረ። በመጨረሻም አብዛኛው ሰው ወደሚሄድበት ሄዶ እንድ ሰባት የምንሆን ሰዎች ብቻ ቀረን። ትዝ የሚሉኝ ተክሥተ፥ ወንጌላዊ (በኋላ መጋቢ) ተሾመ ወርቁ እና መምህር ግዛው ናቸው። ግዛው "ለምን ወንድም በቀለን ወደ ጎብረታችን እንጋብ ዘውም?" አላቸው። አንዳቸው ደግሞ ስለ ጎብረቱ ትንሽ መግለጫ ሰጡኝ። እሺ አልኩ። በሚቀጥለው ሐሙስ ጎብረቱ ወንድም ተክስተ ቤት እንዲሆን ተባለ።

ቆይቼ እንደ ተረዳሁት፥ የጎብረቱ አባላት የመካነ ኢየሱስ እና የሙሉ ወንጌል አብያተ ክርስቲያናት ምዕመናን ናቸው። ገነትን እና እኔን ጨምሮ በጎብረቱ ውስጥ ዐሥራ አምስት ያህል የምንሆን ሰዎች አለን። በየሣምንቱ በየአባላቱ ቤት እየዞርን እንሰበሰባለን። እንዘምራለን፤ ክእግዚአብሔር ቃል የሆነ ሰው ይሰብክልን እና እንሰማለን። ተንበርክከን እንጸልያለን። ክዚያ መንፈሳዊው ፕሮግራም ያልቅና ባለቤቶቹ ሻይ እና ቆሎ ወይም እምባሻ ይጋብዙናል፤ እንበላለን፤ እንጫወታለን። ክዚያ በሚቀጥለው ሳምንት የምንገናኝበት ቤት ይነገረን እና እንለያያለን። ገነት እና እኔ ይህንን ጎብረት በጣም ወደነዋል። ሻይ እና ቆሎው እንኳን የዚያን ቀኑ የተለየ መጣፈጥ ነው የሚጣፍጠን። ሳምንቱ እስኪደርስ እና ዳግመኛ እስክምንገናኝ ድረስ እንናፍቀዋለን።

ማኅበረተኞቼ በፓኔል ውይይቱ ላይ ሲናገር የሰሙት እና አሁን በኅብረቱ ውሰጥ ያወቁት በቀለ ሁለት ሆኑባቸው። ይቺኛው በቀለ እና ባለቤቱ ገና ጥሬ ናቸው። ለለ ከርሰትና ምንም አያውቁም ማለት ይቻላል። ጥያቄዎቻቸውም ብዙ ናቸው። ስለዚህም ከፍተኛ ጥንቃቄ ያለፈልጋቸዋል።

"ዐሥራ አምስት ደቂቃ ሙሉ ተንበርከካችሁ ምንድነው የምትጸልዩት? የእኔ ጸሎት በሁለት ወይም ቢበዛ በሦስት ደቂቃ ውሰጥ ነው የሚያልቀው" ይላቸዋል - በቀለ።

"እንዴ? ለምንድነው ጸጥ ብላችሁ የማትጸልዩት? የእናንተን ጸሎት ልሰማ ወይስ የእራሴን ጸሎት ልጸልይ?" ትላቸዋለች - ገነት።

"ምንድነው እሱ ይቺ የሚሰማኝ መነፋረቅ? የምን ለቅሶ ነው?" ይላቸዋል ባልዮው።

ሚለትዮዋ ደግሞ "ብቻ እንደ እነዚያ 'ጴንጤዎች' እንደሚባሉት እንዳንሆን" ትላቸዋለች።

እነርሱም፥ በዚህ ሳምንት "እሺ ወንድማችን"፤ በሚቀጥለው ሣምንት ደግሞ "እሺ አኅታችን" ይሏቸዋል።

ይህንን ውጥረት ለማርገብ ሲል መሆን አለበት፥ ወንጌላዊ ተሾመ "የጸም እና የጸሎት ጊዜ ቢኖረንስ?" የሚል አሳብ በእንደኛው የኅብረታችን ጊዜ ላይ ያቀረበው። በአሳቡ ሁላችንም ተሰማማን፤ በቀኑ ላይ ለመስማማት ግን ጊዜ ወሰደ ብን። ጊዜ ለመውሰዱም ምክንያቶቹ እኛው ነን። ወንጌላዊው የፈለገው ቅዳሜ እንዲሆን ነው። በከተማው ውሰጥ እኛ ገና የማናውቃቸው ሌሎች "ጴንጤ ዎች" አሉ። አብዛኞቻቸውም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸው። ከእነዚህ ጋር እንድንቀላቀል - "ያበጠውም እንዲፈነዳ" - ፈልጓል። እስከ መቼ ሲያስታ ምመን ይኖራል? ተማሪዎቹ ደግሞ ከቅዳሜ በስተቀር አይመቻቸውም።

ገነት እና እኔ የምናውቀው እርቶዶክሶች ሳለን እንጸመው የነበረውን ጸም ነው። በዚያ እህል ሳይበላ ሙሉ ቀን አይዋልም - አከፍሎት ካልሆነ በስተቀር። ቅዳሜም አይጾምም - "ቅዳሜ ለውር" ካልሆነ በስተቀር።

ሆኖም የወንጌላዊው አሳብ አሸነፈ። ቅዳሜ ከሥራ ስወጣ ወደ ቤት መጣሁ እና ገነትን "ፒክ" አደረግሁ። ተያይዘን ወደ መካነ ኢየሱስ ሆስቴል ሄድን።

ከፍሉ ሞልቷል። ሁሉም ተንበርከክዋል። ገነት እና እኔ ከበሩ አጠገብ፥ የመ ጨረሻዎቹ መንበርከኪያዎች ላይ ተንበረከክን። በበኩሌ ለመንበርከክ እንጂ፥ ለመጸለይ ግን በአውነት አልቻልኩም ነበር። ምክንያቱም በአዳራሹ ውሰጥ በጣም ብዙ ድምፅ ነበረ። ድምፅ ብቻም እይደለም፤ ጩኸትም ነበረ። ድምፅ እና ጩኸትም ብቻ አይደሉም፤ መዝለል እና ግድግዳውን ወይም ወንበሩን በቡጢ መደለቅም ነበሩ።

ያለ ጥርጥር ዕብዶች መካከል ነው ያለሁት። ጎኔ የተንበረከከችውን ባልተቤቴን ትከሻዋ ላይ መታ መታ አደረግኋት። ቀና ሰትልልኝ "እንቺ ቆዩ፤ እኔ ወደ ቢሮ እሄዳለሁ፤ ዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ እመጣ እና ፒክ እደርግሻለሁ" አልኳት እና ምላሽም ሳልጠብቅ ተነሥቼ ወጣሁ።

ጋሽ አዲሱ ተከትሎኝ መጣ እና "ወንድም በቀለ፥ ምነው? የት መሄድህ ነው?" አለኝ።

"ወደ ቢሮ መሄዴ ነው፤ በኋላ እመለሳለሁ" አልኩት።

"የጸሎቱ ጊዜ እኮ አሁን ያልቃል ... እስከዚያው ቢሮ ውሰጥ ትሆናለህ ... ና ወደ ቢሮው ልውሰድህ" አለኝ። ብለው፥ ብሠራው፥ ሊለቀኝ ነው?

"ተረብሻለሁ" አላልኩትም። ማለትም አላስፈለገኝም። በጣም ግልጽ ነበር። ስለዚህም ነው እርሱም ሊለቀኝ ፈቃደኛ ያልሆነው። እጄን የመጠምዘዝ ወይም የመጎተት ያህል ነው፥ ከኋላው አስከትሎኝ ቢሮ ያስገባኝ እና በሩን ዘግ ቶብኝ የሄደው። በተንበረከኩት ሰዎች መካከል ዐልፈን ወደ ቢሮው ሰንገባ፥ ወንጌላዊ ተሾመ ለገነት እጁን ጭኖ ሲጸልይላት አይቼዋለሁ።

ትንሽ ቆይቶ ደግሞ እኔ ወደ አለሁባት ቢሮ መጣ። ለእኔም እጅ ጭኖ ስመጸለይ ፈልጓል ይመስለኛል። እኔ ግን አልተንበረከክሁም። ወንበር ስቤ ቁጭ ነው ያልኩት። ተቀምጬም እየጸለይኩ አልነበርኩም። ዐይኖቼን አፍ ጥጬ ዙርያዬን እያየሁ ነበርኩ። በፍጹም በጸሎት "ሙድ" ውሰጥ አልነበር ኩም። ይልቁንም "በውጊያ ሙድ" ውሰጥ ነው የነበርኩት። ለለዚህ እርሱም በቢሮዋ ሌላ ማዕዘን፥ ወንበር ይዞ ተቀመጠ። ምን ምርጫ አለው?

ሁለታችንም አንዳች ቃል አልተነፈስንም። እንዲያው ዝም ብለን ተፋጠጥን። ምናልባት ብዙ ጊዜ አልቆየንም ይሆናል። ለእኔ ግን በጣም ረዥም ጊዜ የቆየሁ

ያህል ሆኖ ነበር የተሰማኝ። አሁን አሁን ሰዓቴን አያለሁ። በጌታ ከቆየሁ፥ በአገልግሎትም ውስጥ ስለሚያጋጥሙ እንዳንድ ፈተናዎች በመጠኑ ካወቅሁ በኋላ እንደ ተረዳሁት፥ ያቺ ጊዜ ለጋሽ አዲሱ እና ለወንጌላዊ ተሾመ የብርቱ ምጥ፥ የብርቱ ምልጃ እና የብርቱ መንፈሳዊ ውጊያ ጊዜ ነበረች። "IT'S NOW OR NEVER" የሚባል፥ ኤልቪስ ፕሬስሊይ የሚዘፍነው እንድ ዘፈን ዐውቃለሁ። እነዚህ ሁለቱ፥ በጊዜው ባያውቁትም እንኳን፥ እንደዚያ የተባሉ ይመስለኛል - "አሁን! አሁን ካልሆነ ግን፥ ፈጽሞ!"

አዚያኛው ክፍል ጸሎቱ ቀጥሏል። እንዳንዴ ድምፃቸው ጸጥ ይላል። እኔም በውስጤ "አሁንስ መጨረሳቸው ነው" እላለሁ። ብዙም ሳይቆይ ግን እንደ ገና በኃይል ይነሣል። ቆፏቴ ይሆናል። ያውካካል። መልሶ ደግሞ ጸጥ ይላል። እኔም እንደ ገና "አሁንስ በእርግጥ መጨረሳቸው ነው" እላለሁ። ወንዙ ግን ሜዳውን ይጨርስ እና ደግሞ ክሴላ ገደል አፋፍ ላይ ይደርሳል መሰለኝ፥ እንደ ገና ሌላ ቆፏቴ ይፈጠራል። አንደ ገና ሌላ ማውካካት ይሆናል። ብዙ ጊዜ እንደዚህ ቀጠለ። እኔም በውስጤ እንዳንዴ አየተገረምኩ፥ እንዳንዴም አየተቆጣሁ፥ እንዳንዴም እየጠየቅሁ - ምን ማለት ነው? እያልኩ - ቆየሁ።

እንዳያልቅ የለም፥ አለቀ እና እኔም ከታገትኩባት ቢሮ ተለቅቄ ወጣሁ። በጸሎት ላይ የነበሩት ሰዎች መደበኛውን የወጣቶች ስብሰባ ለመካፈል ወደ ትልቁ አዳራሽ ገቡ። ገነትም አብራቸው ገቦች። እኔ ግን በዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ ገነትን ፒክ ለማድረግ ተመልሼ እንደምመጣ ለጋሽ አዲሱ ነው መሰለኝ ነግሬው ወደ ቢሮዬ ሄድኩ። ባልኩት ሰዓት ስመጣ፥ ሕዝቡ ሁሉ ሄዶ የሐሙሱ ጎብረታቸን አባላት ብቻ ቀርተው አገኘኋቸው። ሰላምታ ተለዋውጠን ቁጭ እንዳልን፥ ሲክነክነኝ የቆየውን ጥያቄ አፈረጥኩት - ቅድም ያየሁት እና የሰማሁት ነገር በፍጹም አልገባኝም። ምንድነው? ምን ማለት ነው? ጥያቄዬ ያነጣጠረው ወደ ወንጌላዊ ተሾመ ነው።

ሲጠብቀው የነበረ ጥያቄ ይመስለኛል። ክብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በመነሣት፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሊያስረዳን ጀመረ። ጥቅሶቹን ሁሉ እያወጣ እነበበልን። ከዚያ ወደ ወንጌላቱ መጣ እና ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ስለ መንፈስ ቅዱስ ደቀ መዛሙርቱን ያስተማራቸውን ትምህርቶች አሳየን። በመጨረሻም የብሉይ ኪዳኑ ተስፋ በጴንጤቆስጤ ቀን መፈጸሙን፥ በተፈጸመም ጊዜ ሐዋርያቱን፥

እናቱን ማርያምን እና ወንድሞቹን ጨምሮ፥ 120 የሚያህሉ ደቀ መዛሙርት "በሌሎች ልሳኖች" መናገራቸውን፥ በተናገሩም ጊዜ "ስክረዋል" መባላቸውን፥ ከመጽሐፉ እያነበበ አብራራልን። ያም ተስፋ "ለእናንተ እና ለልጆቻችሁ እንዲሁም ጌታ እምላካችን ወደ ራሱ ለሚጠራቸው፥ በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነው" መባሉን፥ "በሩቅ ላሉትም ሁሉ" የተባለው እኛንም እንደሚያካትት አበሠረን። መጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ እንደዚህ ያለ ነገር መኖሩን ስሰማ፥ ያ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ቀደም ሲል ያመንኩ ስለ ሆነ፥ የስማሁትን ለመቀበል ምንም አልተቸገርኩም። ቅድም ሲዘልሉ እና ሲፎኹ ያየኋቸው ወጣቶች፥ የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት "ስክረዋል" የተባሉትን ዐይነት ስካር የሰከሩ ነበሩ ማለት ነው። እኔም እንደዚያ ዐይነቱን ስካር "ስከሯል" ብባል፥ እንደ ትልቅ ክብር አንጂ በፍጹም እንደ ውርደት አልቆጥረውም። የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት፥ በሐዋርያቱ እና በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ሕይወት የሆነው ነገር በሚሆንበት በዚህ ቦታ፥ በመገኘቴ እጅግ ደስ አለኝ። "ኦርጅናሌውን ክርስትና አገኘሁት!" አልኩ በውስጤ። በዚያ ለነበሩት ደግሞ፥ እንደዚህ ከሆነማ "እኛም ይህ በረከት ያስፈልገናል" አልኳቸው - በገነት እና በአራሴ ስም።

ይህ ከሆነ ከወራት በኋላ፥ አንድ ጥያቄ በውስጤ ተፈጠረ - ዱሮ የተጠመቅሁት ጥምቀት ይበቃኛል? ወይስ እንደ ገና መጠመቅ አለብኝ? ወንድም ተክስተን ልጠይቀው ቀጠሮ ያዝኩ እና ሄድኩ። ስደርስ ከጋሽ አዲሱ ጋር ነበረ። ወንድም ተክሥተ የመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አባል እና ሠራተኛ ነው። መካነ ኢየሱሶቹ ሉተራኖች፥ ማለትም ሕፃናትን አጥማቂዎች ናቸው። ሙሉ ወንጌሎቹ ባፕቲስቶች፥ ማለትም እማኞችን አጥማቂዎች ናቸው።

እኔ ደግሞ ይህንን ሁሉ ጣጣ አላውቅም። "ስለ ውሃ ጥምቀት ምን ትመክረኛለህ? የዱሮው ይበቃኛል? ወይስ አሁን እንደ ገና መጠመቅ ያስፈልገኛል?" አልኩት። ተክሥተ ይበቃሃልም እይበቃህምም አላለኝም። "ማድረግ የሚገባህን እግዚአብሔር እንዲያሳይህ ለምን እንጸልይም?" አለኝ። በመልሱ በጣም ተደሰትኩ። በመጠየቄም እንኳን ተጸጸትኩ። ተንበረከክሁ እና ተከስተ እና አዲሱ እጃቸውን ጭነው ጸለዩልኝ።

ልቤ ፈጽሞ ዐረፈ። ይህ ከሆነ ከጥቂት ወራት በኋላ፥ ለመጠመቅ ወሰንኩ። ማንም ምንም ብሎኝ አይደለም። መሠረታዊ የክርስትና ትምህርትም ሆነ የጥምቀት ትምህርት አልተማርኩም። የዱሮው ለምን እንደማይበቃኝ፥ እንደ ገና መጠመቅም ለምን እንደሚያስፈልገኝ፥ ከሰውም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አልተማከርኩም። እንድ ቀን፥ እንዲያው ዝም ብሎ፥ "OUT OF THE BLUES" እንደሚባለው፥ መጠመቅ እንዳለብኝ ዐወቅሁ። ማታ ቤት ስገባ - "እኔ እና አንቺ መቼ ነው የምንጠመቀው?" አልኳት ገነትን።

"እንደሱ ወሰንክ እንዴ?" አለችኝ።

"አዎን" አልኳት።

"እንግዲያውስ እንተ ተጠመቅ፤ እኔ እንደዚያ ለማድረግ ገና አልወሰንኩም"

"እይ፥ ብቻዬንማ አልጠመቅም፤ እጠብቅሻለሁ" አልኳት። ቢቃ፥ ነገሩን እዚሁ ላይ ተውኩት። መልሼም አላነሣሁትም።

ይህንን ከተባባልን ከአንድ ወር ያህል በኋላ፥ ገነት ደግሞ በተራዋ "እኔም እሁን ለመጠመቅ ወስኛለሁ" አለችኝ። ለወንጌላዊ ተሾመ ነገርነው። በዚያው ሰሞን፥ አንድ ዕሑድ ጠዋት፥ ጊዳቦ ወንዝ ወረድን እና እጠመቀን። ከእኛ ጋር 18 ሌሎች ተጠማቂ ወጣቶች ነበሩ። በዚያን ዕለት በቤተ ክርስቲያን በነበረን የአምልኮ ጊዜ፥ "የጌታ እራት" ሥርዓት ፈጸምን። ከርስቲያን ከሆንኩ እና ትርጉ ሙም ከገባኝ በኋላ፥ ይህንን ከቡር ሥርዓት ስፈጽም የመጀመሪያ ቀኔ ነበር። ደስታዬ ወሰን አልነበረውም። ከንፍ እንዳወጣሁ እና በአየር ላይ እንደምበርር ሲሰማኝ ነበር የዋለው።

በይርጋዓለም የቆየነው በአጠቃላይ ለአንድ ዓመት ከአምስት ወራት፥ ከተጠመቅን በኋላ ደግሞ ለአምስት ወራት ብቻ ነው። ወደ ዲላ ተቀየርን። እነርሱ ስለ እጠመቁን፥ ይርጋዓለሞቹ አባላቸው አድርገው ይቆጥሩናል። ይነበ ጉናል። የጌታ እራት ሥርዓት በሚኖራቸው ጊዜ ይጠሩናል፤ እኛም እንሄዳ ለን። ሆኖም፥ አንድ አማኝ ለምን የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን እንዳ ለበት እኔ አይገባኝም ነበር። ሙሉ ወንጌሎቹ ዘንድ መሄድ እንደ ጀመርኩ፥ ከመካነ ኢየሱሱ መሪዎች መካከል ሁለት ሰዎች ወደ ቢሮዬ መጥተው፥ ሙሉ ወንጌሎቹ ከመንግሥት ፈቃድ ስለሌላቸው፥ የሚሻለኝ የመካነ ኢየሱስ አባል

ብሆን እንደ ሆነ አለጠንቅቀውኝ ነበር። የዲላው መካነ ኢየሱስ ወንድሞችም ቆራቢ አባላቸው መሆን እንድችል፥ የሃይማኖት ማጽኛ ትምህርት እንስጥህ ብለውኝ ነበር። አባል የመሆን አስፈላጊነት እልታየኝም ነበር እና ማስጥንቀቂ ያውንም ሆነ ጥያቄውን አልተቀበልኩም።

በአባልነት እና በውሃ ጥምቀት መካከል ያለው ግንኙነትም እንደዚሁ አይገ ባኝም ነበር። ዲላ መካነ ኢየሱስ እንሄዳለን። ከዲላ ቃለ ሕይወቶችም ጋር በጣም እንቀራረባለን። የጌታን እራትም አብረናቸው እንወስዳለን። ዐልፎ ዐልፎ ሐዋሳ ሕይወት ብርሃንም ድረስ እየሄድን እናመልካለን። ወደዚያ የምንመላለስበት ዋና ምክንያት፥ በዚያ ጌዲዎን እና ሌሎችም የቤተ ሰባችን አባሎች መኖራቸው ነው። በእንደዚህ ዐይነት፥ በውሃ ከተጠመቅንም በኋላ የየትኛውም ቤተ ክርስቲያን አባል ሳንሆን፥ ለአንድ ዓመት ያህል የቆየን ይመስ ለኛል። ግፊቶች ግን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ነበሩ። እና መጸለይ ነበረብኝ - እግዚአብሔር የት እንድንሆን እንደሚፈልግ እንዲያስታውቀኝ። መልሱም ደግሞ ወዲያው መጣልኝ - ይርጋዓለም ሙሉ ወንጌል!

የይርጋዓለሟ ሙሉ ወንጌል በጣም ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ከአባላቱም አብዛኞቹ በጣም ወጣቶች እና ተማሪዎች ነበሩ። ገነትን እና እኔን ባጠመቀችን ጊዜ፥ የምትለበልብባት ቤት "የደሀ ማድ ቤት" ነበር የምታከለው። አሷኑ በዛችባችሁ ብለው፥ እስወጥተውን ቦትነውናል። ለምን እንደ ሆነ እንጃ፥ ስደቱም በእርሷ ላይ ይበረታል። ሆኖም ለእኔ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደ ሆነ እንድ ጊዜ ለይቼ ዐውቄዋለሁ። ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት እና ከአገልጋዮቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት ይኖረኛል። እጥቢያዬ ግን የይርጋዓለም ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች - የይርጋዓለምን ከተማ ከለቀቅሁ እንድ ዓመት ያለፈኝ ቢሆንም።

የከርስቶስ ተከታዮች ሕይወት፥ የከርስቶስም አገልጋዮች አገልግሎት፥ ምን እንደሚመስል ትከከለኛውን ሞዴል ይርጋዓለም ነው ያየሁት። አገልግሎት የጀመርኩትም እዚያው ነው። ወንጌላዊ ተሾመ ነው ያስጀመረኝ - በውሃ ከመ ጠመቄ በጣም በፊት። እኔን በሚያስብከኝ ቦታዎች፥ እርሱ ሁል ጊዜ የፕሮግ ራሙ መሪ ይሆናል። እኔ በለብኩቴ ውስጥ የዘባረቅኋቸውን ነገሮች ሁሉ፥ እርሱ ከእኔ በኋላ መድረኩን ሲይይዝ ያስተካከላቸዋል - እኔን ሳይወቅሰኝ እና ሳይክሰኝ። እኔም በልቤ፥ "ወይኔ፥ ለካ እንደዚህ ማለት እልነበረብኝም"፤

ወይም ደግሞ "ወይኔ፥ ሰካ እንደዚህ ኖሯል ማለት የነበረብኝ" እላለሁ። በእነዚያ በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ሕይወቴ ወራት፥ በአስደናቂ ሁኔታዎች በሕይወቴ ጣልቃ ገብቶ፥ በዚያች ቤተ ክርስቲያን እገልጋዮች እንድያዝ ስለ አደረገኝ፥ ጌታን ሁል ጊዜ እጅግ አድርጌ እመሰግነዋለሁ።

ጴንጤቆስጤአዊ ክርስቲያን

ጴንጤቆስጤአዊ ክርስቲያን መሆን ግን፥ የሙሉ ወንጌል እማኝ የመሆንን ያህል ቀላል አልሆነልኝም። ረዥም ጊዜ ወስዶብኛል። በትክክል ለመናገር፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከሰማሁባት ዕለት እንሥቶ በመንፈስ ቅዱስ እስክ ተጠ መቅሁባት እስክ መጋቢት 02 ቀን 1973 ዓ.ም. ድረስ፥ እምስት ዓመት ከመንፈቅ ያህል ወስዶብኛል። ስመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በመጸለይ ጸጋቸው የሚታወቁ ብዙ ወገኖች ጸልየውልኛል። እኔም በበኩሌ በዚህ ሁሉ ረዥም ጊዜ ውስጥ በመንፈሉ እንዲያጠምቀኝ ጌታን በጸሎት ሳልጠይቀው የዋልኩበት ወይም ያደርኩበት እንድም ቀን አልነበረም ለማለት እደፍራለሁ። ሆኖም ነገሩ የሰማይን ያህል ነው የራቀብኝ። ያም ብቻ አይደለም፤ ጌታ ባይረዳኝ ኖሮ፥ የማላልፋቸው ብዙ ፈተናዎችም አጋጥመውኛል።

"ከዘር የተላለፈ እርግማን ሳይኖርብህ አይቀርም" ያሉኝ እገልጋዮች ነበሩ። "ባትድን ነው" ያሉኝም አሉ። "በልሳን ባትናገርም፥ እንተ በእርግጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተሃል" ያሉኝም ነበሩ። ለዚህ አባባላቸው የሚሰጡኝ ምክንያት "ጥሩ ታገለግላለህ እኮ!" የሚል ነው። "ዶክተር ቢሊይ ግራሃምን እታያቸ ውም? በልሳን አይናገሩም፤ ነገር ግን እርሳቸውን በመንፈስ ቅዱስ አልተሞሉም ስማለት ማን ይደፍራል?" ይሉኛል። እኔ ደግሞ ስሰ "ክላሲካል ፔንቴኮስታል እስተምህሮ" እንብቤአለሁ። በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ከመንፈስ ቅዱስ ከመወለድ የተለየ እና እርሱን የሚከተል ልምምድ እንደ ሆነ ነው የተረዳሁት። አዲስ ኪዳናዊ ምልክቱም በልሳን መናገር ነው። በልሳን ለመናገሩ ምንም ማስረጃ የለኝም እንጂ፥ ከመንፈስ ቅዱስ የተጻነሰው ጌታ ኢየሱስ እራሱም እገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተጠመቀ ነው የሚገባኝ (ዮሐ. ፩፥33)።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ ከምናገኝባቸው አምስት ምዕራፎች ውስጥ (ሐዋ. 2፤ 8፤ 9፤ 10፤ 19)፥ በሦስቱ የተጸለየላቸው ሰዎች

ወዲያው በልሳን ተናግረዋል (ሐዋ 2፤ 10፤ 19)። በቦታው አልተጠቀሰም እንጂ (ሐዋ. 9፥17-18)፥ ሐዋርያው ጳውሎስም በልሳን ተናግሯል (፩ቆሮ. 14፥18)። የሰማርያ ክርስቲያኖችም በልሳን ተናግረው መሆን አለበት። ያለዚያ ስለ ሲሞን፥ "ሐዋርያት እጃቸውን በሚጭኑበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ አይቶ ..." ተብሎ ለምን ተጻፈ? (ሐዋ. 8፥18) ሲሞን "በዐይኖቹ ያየው" መን ፈስ ቅዱስን የመቀበል ምልክትስ፥ በልሳን ከመናገር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? በተጨማሪም፥ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁት ሁሉ በልሳን እንደ ተናገሩ ነው መጽሐፉ የሚተርከው (ሐዋ. 2፥4፤ 8፥19፤ 10፥44፤ 19፥6-7)።

ስለዚህም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላመንኩ በመንፈስ ቅዱስ የማልጠመቅ በት፥ በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቅሁም በልሳን የማልናገርበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ሐዋርያው ጳውሎስ "... ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሎችን ለማስተማር፥ ዐሥር ሺህ ቃላት በልሳን ከምናገር ይልቅ፥ እምስት ቃላት በአእምሮዬ ብናገር ይሻላል" ማለቱንም ዐውቃለሁ (፩ቆሮ. 14፥19)። እኔ ግን ለጌታ፥ "ዐሥር ሺህ ቃላት በአእምሮዬ ከምናገር ይልቅ፥ እምስት ቃላት በልሳን ብናገር ይሻላል" ብዬዋለሁ። በእእምሮ መናገር እያስፈልገኝም ማለቴ አልነበ ረም። በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ግን ከዚያ ይልቅ የበለጠ ያስፈልገኛል ማለቴ ነበር። እርሱ ደግሞ ተረድቶኛል። እንድም ቀን misunderstand አድርጎኝ (ባልሆነ መንገድ ተረድቶኝ)፥ አያውቅም።

ከፈተናዎቹ ሁሉ የከበደብኝን ግን ልጥቀስው። አንድ ዕሑድ፥ ገነት እና እኔ ከሐዋላ ስንመለስ ወንጌላዊ ጻድቁ አብዶን እና ወንድም እዳነ ገብሬን እቤታችን እንዳገኘናቸው በምዕራፍ አንድ ውስጥ ጠቅሻለሁ። ያች ዕለተ ዕሑድ መቼ እንደ ነበረች እርግጠኛ መሆን አለመቻሌን፥ ሆኖም በምዕራፍ ሰምንት ውስጥ እንደምመለስበትም በዚያው ቦታ ተናግሬአለሁ። በእንድ በኩል ወንድም እዳነ ብቻውን ወደ ቤታችን የመጣበት ቀን በ1968 ዓ.ም. በጳጉሜን ወር ውስጥ ሳይሆን አይቀርም አላለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ ቀኑ እሱ መሆኑን አጠራ ጠራለሁ። ለምን እንደዚያ እንደምል አሁን፥ ለምን እንደምጠራጠር ደግሞ ትንሽ ዝቅ ብዬ እናገራለሁ።

መስከረም 03 ቀን 1969 ዓ.ም. ጀምሮ በናዝሬት ባይብል አካዳሚይ በሚካሄደው በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ኮንፈረንስ ላይ ተካፋይ እንድሆን የመግቢያ ካርድ ተልኮልኛል። ማን

እንደ ላከልኝ ወይም አንደ አስላከልኝ አልተነገረኝም። አኔ ግን በሥራ ምክን ያት ለመሄድ አልችልም ነበር። ለለዚህም ከባለቤቷ ጋር ተመካክረን፥ ካርዱን ለአንዲት እኅት አንደ ሰጠናት አሰታውሳለሁ። ያች እኅት እንድትሄድ የፈለግ ንበት ምክንያትም የሚከተለው ነው።

ወንድም አዳነ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ቤታችን በመጣበት ቀን በቤተ ሰብ ደረጃ አብረነው ጸልየናል። ምዕራፍ እንድ ውስጥ እንደ ገለጽኩት፥ መልእከትም አም ጥቶልናል። ከጸሎቱ በኋላ ቁጭ ብለን የሆነ የሆነ ነገር ስንነጋገር፥ በመንፈስ ቅዱስ ባለመሞላቱ በጣም ስለሚያዝን አንድ ወንድም ነገርነው። በዚህ ጊዜ፥ ወንድም አዳነ "ጌታ ይመሰገን፤ አገልግሎት ሰጠኝ ማለት ነው፤ ይህንን ወንድም አሁን ልናገኘው እንችላለን?" አለ። "አዎን" አልኩት እና ለዚያ ወንድም ወዲያው ደወልኩለት። አቤት መኖሩን ካረጋገጥኩ በኋላ፥ "ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሊጸለይልህ ነው፤ አሁን አመጣ አና ፒክ አደርግሃለሁ" አልኩት።

አቤቱ ስደርስ፥ አልጋው አጠገብ ተንበርክኮ አገኘሁት። "አሁንኮ እየጸለይኩ ነበር። መጽሐፍ ቅዱሴን ስገልጠው የወጣልኝን ጥቅስ ተመልከተው" አለኝ እና ኤርምያስ 23፥23ን አሳየኝ - "እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም" ይላል። አሰምሮበታል። "እውነት ነው ... የቅርብ አምላክ ነው ... ብቻ አሁን ቶሎ ተነሥ ... ሊጸለይልህ ነው" አልኩት። ፒጃማውን አና ጋቢውን አንደ ለበሰ ይመስለኛል ይዤው የበረርኩት። ወንድም አዳነ ሲጸልይለት ወዲያው በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ።

በዚህ ጊዜ፥ ወደ ወንድም አዳነ ጠጋ አልኩ እና "እኔም አኮ አልተሞላሁም፤ አንድትጸልይልኝ እፈልጋለሁ" አልኩት። የተሞላሁ ሲመስለው ነበረ መለለኝ፥ አለመሞላቴን ሲሰማ ትንሽ ተገረመ። ሆኖም ጸለየልኝ። አልተሞላሁም። በማግስቱ አንደ ገና ልንገናኝ ተቃጥረን፥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የሚፈልጉ ሌሎችንም ልንሰበስብለት ተነጋግረን ተለያየን።

ገነት መልእከቱን በስልክ፥ በእካል እና በሰው በሰው ሊታዳርስ ዋለች። ማታ ላይ ቤታችን በሰዎች ግጥም ብሎ ሞላ። ትዝ አንደሚለኝ ከሆነ፥ ክእኔ እና ከዚያ ትናንትና ከተሞላው ወንድም ባለቤት በስተቀር ሁሉም ተሞሉ። በዚያን ምሽት ወንድም አዳነ አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፈው በእኔ ላይ ነበረ ለማለት አችላለሁ። ጉሮሮዬ አሰኪዘጋ ድረስ ነው "ሃሌ ሉያ፥ ሃሌ ሉያ" ያልኩት።

ሁሊታችንም ባለመሞላታችን ግን በጣም አዘንን። በዚህ ጊዜ ነው ያች እኅት ናዝሬት ብትሄድ አኮ ተሞልታ ትመጣለች ብለን ያሰብነው። የአኛ አለማወቅ ነው እንጂ፥ አንደዚያ ለማሰብ ምንም ምክንያት አልነበረንም።

ያ ለብሰባ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለመጸለይ የተጠራ ለብሰባ አልነበረም። ከተሳታፊዎቹም ውስጥ አብዛኞቹ በመንፈለ ቅዱስ ያልተሞሉ እና በመንፈሰ ቅዱስ በመሞላትም የማያምኑ ነበሩ። አንዲያውም "ተሳታፊዎቹ አጅ ለአጅ ተያይዘው አንዲጸልዩ አድርጓል፤ አንደዚህም ያደረገው ጴንጤዎቹ በአጀቻቸው የያዟቸው ለዎች በመንፈስ ቅዱስ አንዲሞሉ ሁኔታውን ሊያመቻችላቸው ፈልጎ ነው" ተብሎ አቡነ ፈሰቶ ኬቬንጀሬ ተከስሦበታል። ጋሽ መስፍን ተስፋዬም (ማራናታ) የጴንጤዎቹን ትምህርት የሚደግፍ ስብከት ሰብኳል ተብሎ የአንድ ቤተ እምነት ተወካዮች ጉባዔውን ረግጠው ለመውጣት ፎከረው ነበር። የጉባ ዔው አዘጋጆች ጋሽ መስፍንንም ይቅርታ አንዲጠይቅ ለምነውት ነበር። "አላደ ርገውም" አላቸው። ስለዚያ ጉባዔ "ለዚህ ጊዜ" በተባለችው መጽሐፌ ውስጥ በስፈው አትቻለሁ።

ሆኖም፥ ያች እኅት ወደ ናዝሬት ሄደች። ስትመለስ አንደ ነገረችን፥ በናዝሬቱ ጉባዔ ላይ ቀደም ሲል መምህራን ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት በነበረች ጊዜ የም ታውቀውን አንድ "ጴንጤ" ወንድም ድንገት ታገኛለች። ከዲላ ናዝሬት ድረስ የተጓዘችበትን ምክንያት ያልረሳችው ያችም እኅት፥ ያንን ወንድም ባገኘችው ጊዜ "ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት አንዲጸልይላት" ትጠይቀዋለች። እርሱም አዚ ያው ከተገናኙበት ቦታ ላይ፥ በቀኖቹው እና በግራቹው ሕዝቡ ወደ ጉባዔው እየነረፈ አየገባ አያለ፥ አንበርከኳት እና አጆቹን ጭኖባት ይጸልይላታል። ያችም እኅት በልሳን ትናገራለች።

ወደ ዲላ በተመለለች እና የሆነውን ነገር በነገረችን ጊዜ ሁላችንም በጣም ደሰ አለን። ከሆኑ ሳምንታት በኋላ፥ ወንድም አዳነ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ዲላ መጣ። ተገናኙተን ስንጨዋወት፥ ባለፈው ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉትን ሁሉ ሊያገ ኛቸው እንደሚፈልግ ነገረን። ገነት ለብሰባውን ጠራች። ፕሮግራሙንም በዝማሬ እና በጸሎት መራች እና ለወንድም አዳነ ሰጠችው። እርሱም "በመ ንፈስ ቅዱስ ከተሞላችሁ በኋላ እንዴት ናችሁ? በሕይወታችሁለ ምን ዐይነት ለውጥ እያችሁ?" በማለት በጥያቄ ጀመረ። ሁሉም ደሰ ደሰ የሚል ምስከርነት

ሰጡ። ያች እኅት ብቻ "እኔ ይጨንቀኛል" አለች። ከዚያ የእግዚአብሔርን ቃል አካፈለን እና ለጸሎት ተንበረከከን።

ሁሉም በልሳኖቻቸው አንዲጸልዩ አበረታታቸው። ከእኔ ብቻ በስተቀር፥ ሁሉም አስነኩት። ያችን እኅት ጠጋ ብሎ አዳመጣት እና "ይኸ የእግዚአብሔር መንፈስ አይደለም፤ በዚህ ልሳን እንዳትጸልይ" አላት። ሁላችንም ደነገጥን። መንፈሱ አንዲለቅቃት በጌታ በኢየሱስ ስም ደጋግሞ አዘዘው። አላስጮኻትም። ሌላም ምንም አላደረጋትም። እኔንም መኝታ ቤት አስገብቶኝ በግሌ እነጋገረኝ -

"ዳግም የተወለድከው መቼ ነው?" አለኝ።

"ቀኑን አላውቀውም ... ምናልባትም ቀን የለውም ... የእኔው እንዲያው በሂደት ነበር የሆነው" አልኩት።

"ለው የተወለደበትን ቀን እንዴት አያውቀውም?" አለኝ፥ ኮስተር ብሎ።

"እንግዲህ እኔ እንጃ" አልኩት። አለታ ወንዶ አያለሁ፥ ጌታን የተቀበልኩበትን ሁኔታ ላስረዳው ሞከርኩ። "በግሌ ቢሆንም፥ ከመጻሕፍት ጋር ቢሆንም፥ ለው ለመዳን ማድረግ ያለበትን ሁሉ ግን አድርጌአለሁ ... ኃጢአተኛነቴን ተረድቼ ንሰሐ ገብቻለሁ ... የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትም በትክክል ገብቶኝ በአምነት ተቀብዬዋለሁ ... ሕይወቴም ደግሞ ፈጽሞ ተለውጧል ... በውሃም ተጠምቄአለሁ" አልኩት።

ቃሌን ለመቀበል እጅግ አቅማማ። በመጨረሻም "የማይከብድህ ከሆነ፥ በእነ ዚህ ወገኖች ፊት ጌታን አንደ ገና ብትቀበል" አለኝ።

"ለምን ይከብደኛል? ... በፍጹም አይከብደኝም ... ጌታን ለሁለተኛ ጊዜ አይደለም፥ ለመቶኛ እና ለሺህኛ ጊዜም ቢሆን አቀበለዋለሁ" አልኩት። ወደ ጉባዔው ተመለሰን እና በተሰበሰቡት ሁሉ ፊት ጌታን አንድቀበል አደረገኝ። እኔም ምንም አልከፋኝም።

ያችን እኅት በተመለከተ ደግሞ፥ "ይህ መንፈስ ከአንግዲህ በውስጥዋ ሊኖር አይችልም፤ እናንተ በጸሎት አግዟት፤ ወይ ጮኽ ይወጣል፥ ወይም ጸጥ ብሎ ትታት ይሄዳል አለን። አንድ ዓርብ ቀን፥ ይህ ከሆነ ከሁለት ወይም ከሦስት ቀናት በኋላ፥ ማታ ከሥራ ወጥቼ ቤት ስመጣ ገነት አቤት የለችም። የት አንደ

ሄደች ጠየቅሁ። ወደዚያች፥ ወንድም አዳነ "በዚህ ልሳን እንዳትጸልይ" ወዳላት እኅት ቤት አንደ ሄደች ነገሩኝ። ሆኖም ብጠብቅ ብጠብቅ አልመጣ አለች። ጊዜው ደግሞ እየመሸ ሄደ። ቢቸግረኝ መኪና አስነሣሁ እና ወደዚያ ቤት ሄድኩ። ያየሁት ነገር አስገረመኝም፤ አስደነገጠኝም። ያች እኅት መሬት ላይ ተዘርራለች፤ ትለፈልፋለች። ገነት ቆማ መንፈሱን "በጌታ በኢየሱስ ስም እዝዝ ሃለሁ፤ ውጣ!" እያለች ትገሥጻለች። የዚያች እኅት ባለቤትም አብሯት አለ።

ለካ ሁለቱ እኅቶች በዚያን ቀን በጾም እና በጸሎት ሊውሉ እና ፲፥00 ሰዓት ላይ ተገናኝተው አብረው ሊጸልዩ ተስማምተው ኖሯል። በስምምነታቸው መሠረት ተገናኝተው አብረው ሊጸልዩ ነው ያችን እኅት ያስጮኻት። እኔም በላያቸው ተጨመርኩ እና አብረን መጸለይ ቀጠልን። መንፈሱ ግን አልወጣ አለን። ጩኸቷ ደግሞ እየጨመረ መጣ። ቤታቸው ያለው መንደር ውስጥ ስለ ሆነ፥ ሌላ ችግር መጥራት አንዳይሆን ፈራን። ወደ አእምሮዋ እንዲመልሳት መንፈ ሱን አዘዝነው እና ወዲያው ጤናማ ሆነች። ከዚያ በኋላ ተቀምጠን ምን ማድረግ እንዳለብን ተመካከርን። በበነጋው ቅዳሜ ነው። እነርሱ ጠዋት ወደ እኛ ቤት ይምጡ። እኛ በላያችን ሌሎችን ቅዱሳን ጨምረን አንጠብቃቸዋ ለን። እና ኃይላችንን አጠናክረን መንፈሱን አንገጥመዋለን። በዚህ ተስማማን እና ገነት እና እኔ ወደ ቤታቸን ሄድን።

ቅዳሜ ዕለት እኔ ሥራ አልሠራሁም። እንዴትስ ተብሎ ሥራ ይሠራል? ጠዋት ቢሮ ገባሁ እና ከገንዘብ ያዡ ጋር ካዝና ከፍተን፥ ለዕለቱ ሥራ የሚበቃውን ያህል ካሽ አውጥተን ተረካከብን። ከዚያ ወደ ውጪያው ወረዳ ተመለስኩ። በጸሎት ብርቱ ናቸው ብለን የምናስባቸውን አንድ አምስት የሚሆኑ ወንድሞች እና እኅቶች ጠራን። ባል እና ሚስቱም መጡ። እና ከዚያ ርኩስ መንፈስ ጋር አንደዚሁ ስንጨዋወቼዋህ ቀኑን ሙሉ ዋልን። እሁን "ወጣሁ" ይሉናል። ትንሽ ይቆይና ደግሞ "ተመልሼ ገባሁ" ይሉናል። ግራ ግብት አደረገን። በመካከላችን መናፍስትን በማስወጣት ረገድ ልምድ ያለው አንድም ለው አልነበረም። ዐሥር ሰዓት ገደማ ላይ ሁላችንም ተዳከምን እና በየበኢታችን ተበታተንን። ገነትም ወደ መኝታ ቤት ገብታ ጋደም ያለች ይመስለኛል።

ለእኔ የዚያን ቀኑ ውሎዬ የተበጠበጠ ነበረ። በአንድ በኩል ከሌሎቹ ጋር አብሬ እጸልያለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ ከአንድ አሳብ ጋር ብቻዬን እተናነቃለሁ። ወንድም አዳነ ስለዚህች እኅት የተናገራቸው ነገሮች ትከከል ሆኑ። አንግዲያው

ሰለ አኔም የተናገራቸው ነገሮች ትከክል መሆን አለባቸው:: መዳኔን በጣሙን ተጠራጥሯል:: ጌታን ሁለተኛ አንድቀበል ያደረገኝ በዚህ ምክንያት ነው:: ማመኔን፥ ሕይወቴ መለወጡን፥ በውሃ መጠመቄን እና ማገልገልም መጀመሬን አየጠቀሰኩ በተከራከርኩት ጊዜም፥ ፈራ ተባ እያለ፥ የሰማርያው ሊምንም በውሃ መጠመቁን እና ከፊልጶስ ጋር መተባበር መጀመሩን ነግሮኛል:: አየተ ጠራጠረ ያለው መዳኔን ብቻ ሳይሆን፥ ርኩሰ መንፈስ በውሰጤ አለ መኖሩንም ጭምር ነበር ማለት ነው:: ያን ዕለት ማታ "ይገርማል፥ ጋሽ አዳነ አኮ አንዲህ እና እንዲህ አለኝ" ስላት፥ ገነት ደግሞ "አይ፥ ዝም ብለህ ባትሚገተው፥ ይልቁ ንም ብትሰማው ነው የሚሻለው" ብላኛለች::

የመጣሁትም ከወደ ሮዚከሩሽያኑ ዓለም ነው:: አህእ፥ ማን ያውቃል? መጽሐፎቻቸው አንኳን አሁንም መደርደሪያዬ ላይ አሉ:: የአነ ሎብሳንግ ራምፓ መጻሕፍት፥ አነ "IN SEARCH OF THE MIRACULOUS" እና ሌሎቹም ሁሉ አሰከዚያ ቀን ድረሰ ከአኔው ጋር ናቸው:: በመንፈስ ቅዱስ አን ዳልጠመቅ ዕንቅፋት አየሆኑኝ ያሉት አንዲያውም አነርሱ ሊሆኑ ይችላሉ:: ሄድኩ እና ሁሉንም ከመጻሕፍት መደርደሪያዬ ላይ ለቅሜ አወጣኋቸው::

አራሴም ከ1957 ዓ.ም. ጀምሮ፥ ለ12 ዓመታት ያህል የጻፍኳቸውን 54 ያህል የሚሆኑ ግጥሞችን የያዘ መድብልም አለኝ:: ይርጋሳለም በነበርን ጊዜ ገነት ጥሩ አድርጋ ተይባልኛለች:: ለሣንሱሩ ከፍል ልሰጠው አና ላሳተመው ቀን አየጠበቅሁለት ነበር:: አሱንም አብሬ አወጣሁት:: ምን ያደርግልኛል? እኔስ ከአንግዲህ ወዲህ ምን አደርግበታለሁ? ግቢአችን ውሰጥ፥ በስተ ጓሮ በኩል፥ አንድ ቦታ ቆለልኳቸው:: ከዚያም ጋዝ አምጥቼ አርከፈከፍኩባቸው አና አሳት ለቀቅሁባቸው:: ጭሱ አየተትጎለጎለ፥ አኔም አሳቱን አየቆሰቆስኩ አና አየተቆጣ ጠርኩ አያለ፥ የቃለ ሕይወቱ ወንጌላዊ ወርቁ ጎሌ አቤታችን መጣ:: ገና ሰላምታ አንኳን በደንብ ሳይሰጠኝ፥ "እንዴ፥ አንዴ፥ ዛሬ ይኸ ግቢ ኤፌሶንን አይደል አንዴ የሚመስለው?" (ሐዋ. 19፥19) አለ:: እርሱም፥ አንደ ወንድም አዳነ፥ በሰይጣን አገልጋይነት ይጠረጥረኝ ነበር ማለት ነው? ለሁሉም፥ "አዎን" አልኩት:: ሌላ ምን አለዋለሁ?

የዚያን ሌሊቱን አዳሬን፥ አዳር አይበለው:: መቆምም ሆነ መቀመጥ፥ መተኛትም ሆነ ማንበብ፥ እንዲያው ማናቸውንም ነገር ማድረግ አቃተኝ:: አንቅልፍማ አይታሰብም:: እንዴት ተደርጎ፧ ማለቴ መጀመሪያ ማን ጎኑን

መሬት አሰነከቶለት? ሰለዚያ ሌሊት ሁኔታዬ በምናገር ጊዜ፥ "ሲያል ወርጂ ነበር" ነው የምለው:: ደግሞም ትከክል ነው:: "ሲያል" የሚባለው ቦታ አና/ወይም ሁኔታ፥ ያንን ሌሊት አኔ ከሆንኩት ሁኔታ ሊብስ የሚችል በፍጹም አይ መስለኝም:: ገነት ከአኔው ጋር አብራ ሰትንቆራጥጥ ቆይታ ከሴሊቱ ወደ 10:00 ሰዓት ገደማ ሊሆን አንቅልፍ ጣላት:: ትግሉን ትናንትና የጀመረች ናት:: እኔም ወደ 11:00 ገደማ ላይ፥ የሞት ሞቴን ተንበረከከሁ አና አጭር ነገር ለጌታ ተናገርኩ:: ካለፈ በኋላ ሳስበው፥ ጌታ ሊረዳኝ ስለ ፈለገ ብቻ ነው መንበርከከ የቻልኩት::

> ጌታ ሆይ፥ ከአንግዲህ ወዲህ የምኖረው በዚህ ዐይነት ከሆነ፥ ለአምስት ደቂቃም አንኳን ቢሆን መኖር አልፈልግም:: አሁን ቸርነት አንድታደርግ ልኝ አለምንሃለሁ፤ ወይ አሁን ፈጽመህ ፈውሰኝ፤ ወይም አሁን ፈጽመህ ግደለኝ

አልኩት:: አኔ በምተኛበት በኩል፥ አልጋዬ ጎን ሰንበረከከ፥ መብራቱን ማጥፋቴን አስታውሳለሁ:: አሁን ግን በልቤ ውሰጥ ይሁን ወይም ግድግዳው ላይ አላውቅም የተጻፈ ነገር ይታየኛል:: ጽሑፉ ኤፌሶን 6፥13-17 ላይ ያለው ነው:: በኢንግሊዝኛ ቋንቋ ነው የተጻፈው:: አንብቤ ከጨረስኩት በኋላ፥ የትራ ስጌ መብራቴን አበራሁ አና ከኮመዲኖዬ ላይ መጽሐፍ ቅዱሴን አነሣሁ:: አንደ ተንበረከከሁም፥ ያንኑ ከፍል ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱሴ ላይ ማንበብ ጀመርኩ:: "የመዳንንም ራስ ቁር" ከሚለው ሰፍራ ሰደርስ የሆነ ነገር አልፌ አንዳላነብ ከለከለኝ:: ገድግዶ አቆመኝ:: እና እየደጋገምኩ፥ እየደጋገምኩ "የመዳንን ራስ ቁር"፥ "የመዳንን ራስ ቁር" ማለት ብቻ ሆነ::

ሰንት ጊዜ አንደዚያ ካልኩ በኋላ አንደ ሆነ አላውቅም፥ "የመዳን ራስ ቁር" ምንድነው? ብዬ አራሴን ጠየቅሁት:: አሁን ደግሞ ሙሉ ትጥቁን የታጠቀውን የሮማ ወታደር ምስል በፊቴ አየሁ:: የራስ ቁሩ፥ ወታደሩ ጭንቅላቱን አንዳይ መታ የሚከላከልለት መሣሪያ ነው:: ወዲያው ነገሩ ሁሉ ወለል አሰልኝ:: የአኔ ጭንቅላት አሁን የመዳንን ራስ ቁር አልደፋም:: ባዶ ነው:: ወንድም አዳነ ያለኝን አና ያቸንም አነት ርኩስ መንፈስ ሲያሰፈኳት በመሰማቴ፥ አኔም የአራሴን መዳን ተጠራጥሬአለሁ:: በዚህም የተነሣ ሰይጣን አሁን ጭንቅላቴን አየደበደበው ነው:: ወዲያው ገነትን ከአንቅልፏ ቀሰቀስኳት:: ስትነሣልኝ -

"አሁን ችግሬን ደርሼበታለሁ" አልኳት::

"ምንድነው?" አለችኝ::

"የወንድም አዳነን ንግግር ሰምቼ ... እጎት እገሊትንም ኢጋንንት ሲያሰጮኻት አይቼ ... እኔም የእራሴን ደጎንነት ተጠራጥሬአለሁ ... በዚህም ምክንያት የእራስ ቁሬ ጭንቅላቴ ላይ የለም ... ይህንን የሚያውቅ ጠላትም ጭንቅላቴን በግለጭ አግኝቶ እየደበደበው ነው" አልኳት::

ችግር አላት:: ምነው አይቸግራት? "አሁን ታዲያ ...?"

አላስጨረስኳትም:: "አሁን እኔ በአንቺ ፊት ንስሐ እገባለሁ ... ጌታን በድዬዋ ለሁ ... እንደ አዳነኝ በግልጽ እያወቅሁት ... ሕይወቴን እንደ ለወጠ በግልጽ እያወቅሁት .. እንድ አገልጋይ ደጎንነቴን ተጠራጠረ ብዬ ... አንዲትም እጎት ኢጋንንት አሰጮኻት ብዬ ... እኔም ደጎንነቴን በመጠራጠሬ ... ያደረገልኝን ያንን ሁሉ ባለማመኔ ... ጌታን በድዬዋለሁ ... አሁን እኔ እንበረከካለሁ ... አንቺ ደግሞ እጅችሽን ጭነሽ ትጸልይልኛለሽ" አልኳት እና እፈቷ ተንበረከከሁ:: እግዚአብሔር ይባርካት እና ገነት እጅጉን ጭና በአማርኛም፥ በዚያ ስሰማው ሁል ጊዜ ደስ በሚለኝ ልሳኗም፥ ጸሰየችልኝ:: ጌታም በዚያችው ቅጽበት ፈጽሞ ፈወሰኝ:: እየነጋ ስለ ነበረ፥ ትንሽ ጎኔን አሳርፌ፥ ከዚያም ተጣጥቤ እና ለባ ብሼ፥ መጽሐፍ ቅዱሴን ይዤ፥ ወደ "ዲላ ጢኖ" ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ:: በዚያ እገልግሎት አለኝ - ዕሑድ አይደለ?

ያች ዕሑድ በጳጉሜን ወር 1968 ዓ.ም. ውስጥ መሆኗን እርግጠኛ መሆን ያልቻልኩበትን እና ትንሽ ዝቅ ብዬ አነሣዋለሁ ያልኩትን ምክንያት አሁን ላንሣው:: ወደ ዲላ ተዛውረን የመጣነው በሐምሌ ወር ኢጋማሽ 1968 ዓ.ም. መሆኑን ምዕራፍ አንድ ውስጥ ጠቅሻለሁ:: የጽሑፍ ማሰረጃ በእጄ ስላለ፥ ስለ እሱ እርግጠኛ ነኝ:: ከሐምሌ ኢጋማሽ ጀምሮ እስከ ጥቅምት ወር 1969 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ከሦስት ወራት የማይበልጡ ጊዜያት ውስጥ ዲላን ይህንን ያህል እንዴት ሰመድናት? የሚለው እንዱ ጥያቄዬ ነው:: ለምሳሌ በመንፈስ ቅዱስ ስላልተሞላ የሚያዝነውን ወንድም፥ በጸሎት የሚበረቱ የሚመስሉንን በቁጥር ጥቂት ወገኖች፥ ወንጌላዊ ወርቁ ጎሌን፥ የዲላ ጢኖ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን ከምን ጊዜው እንደዚህ ዐውቅናቸው?

ወንድም አዳነ ሰመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከጸለየላቸው እና ከተሞሉት ሰዎች መካከል አንዱ ወንድም (አሁን መጋቢ) ሙላቱ ወዳጄ ነው:: ይህንን ከፍል ሰጽፍ፥ መጋቢ ሙላቱ መንፈስ ቅዱስ የተሞላበትን ቀን ያስታውሰው እንደ ሆነ ጠይቄው ነበር:: "እሱን አላስታውሰውም፤ የማስታውሰው ጌታን የተቀበልኩበ ትን ቀን ነው፤ እሱም ሚያዝያ 23 ቀን 1969 ዓ.ም. ነበረ" አለኝ:: ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት የተጸለየለት ጌታን በተቀበለበት በዚያው ሰሞን ነበር:: ያስቀበ ለውም የዚያች ወደ ናዝሬቱ ኮንፈረንስ የላከናት እጎት ባለቤት ነው - እርግጠኛ መሆን ያልቻልኩበት ሁለተኛው ምክንያት:: መጋቢ ጻድቁንም ጠይቄው ነበር:: አርሱ እንዲያውም ወደ ቤታችን መምጣቱንም፥ በተሊይም ደግሞ ከወንድም አዳነ ጋር መምጣቱን፥ እያስታውሰውም::

ጥቂት ቃላት

ወደ ምዕራፍ አንድ፥ ወደ ዐሥሩ አስጨናቂ ቀናት፥ ልመለስ:: ያንን ምዕራፍ የዘጋሁት "ያ ሁሉ ኢንቬስትሜንትሳ?" በሚል ጥያቄ ነበር:: ከምዕራፍ ሁለት እንሥቶ እስከዚህ ድረስ የተረከሁትን ሁሉ ነው፥ "ያ ሁሉ ኢንቬስትሜንትሳ?" ያልኩት:: እንደዚህ ባከኖ የሚቀር ከሆነ፥ ለምን ሆነ? ማለቴ ነው:: አሱን ነው ማወቅ ያልቻልኩት:: ይኸው እንግዲህ እሱን በማውጣት እና በማውረድ በእግዚአብሔር ፊት ዐሥር ቀናት ሙሉ ቆየሁ:: ነገር ግን ምንም ያወቅሁት ነገር የለም:: አሁን ሳሰበው፥ እሱ እንዲያውም የእኔ ጉዳይ አይደለም:: የእኔ ጉዳይ ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ መሆን ብቻ ነው:: የእኔ ጉዳይ ለእግዚአብ ሔር ቃል መታዘዝ ብቻ ነው:: ቤቴን ማስተዳደር አላወቅሁበትም፤ ስላላወቅሁ በትም ቤቴ ፈርሷል:: ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቤት ላስተዳድር አልችልም፤ አራት ነጥብ::

ዛሬ - ማለትም ሰኞ፥ መስከረም 29 ቀን 1993 ዓ.ም - ከቤተ ክርስቲያኔ መሪዎች ፊት ስቀርብ፥ የምነግራቸው ይህንን እና ይህንን ብቻ ነው:: እኔ መጋቢ መሆን አልችልም:: "ለምን?" ካሉ፥ ቃሉ አይፈቅድልኝም፤ በቃ! እዚህ ውሳኔ ላይ የደረስኩት ከቀኑ 5፡30 ገደማ ላይ ነው:: ምሳ በልቼ ትንሽ ጋደም ልል ፈለግሁ:: ደክሞኛል ይመስለኛል:: ከዚያ እተጣጠብ እና ወደ ቸርች እሄዳለሁ:: እመቤትን "ምሳ አዘጋጂልኝ" አልኳት:: ወደ 6፡15 ላይ ይመስለኛል፥ የአጥሩ በራችን ተንኳኳ:: ወጥቼ ስከፍት አቶ መሰፍን ለማ፥ አቶ

ካሣዬ ኃይሌ እና ባለቤቱ ወይዘሮ ሥምረት እደጅ ቆመዋል። ተቃቀፍን፤ ተሳሳ ምን፤ ተጨባበጥን። "ምን እግር ጣላችሁ? አገር ደህና እይደለም እንዴ? በሉ ግቡ" አልኳቸው።

እነርሱ ሲገቡ እና የእመቤት ምሳ ሲቀርብ አንድ ሆነ። "እንግዲህ የመጣችሁት በምሳ ሰዓት ነው ... ቤት ያፈራውን ትበላላችሁ ... በሉ እጃችሁን ታጠቡ" አልኳቸው። እስቀድመው ካሣዬ እና ባለቤቱ ወደ መታጠቢያ ቤት ሄዱ። እነርሱ ሲመለሱ ደግሞ መስፍን እና እኔ ሄድን። እየታጠብን እያለን፥ ድምፁን ወረድ አድርጎ -

"ምን እስብከ?" አለኝ።

"ስለ ምኑ?" አልኩት።

"ስለ ዛሬው ስብሰባ" አለኝ። መስፍን ከቤተ ክርስቲያናችን ሽማግሌዎች መካከል አንዱ ነው። በገነት እና በእኔ መካከል ያሰውንም ነገር ከሞላ ጎደል ያውቃል።

"እኔ መጋቢ ስመሆን እልችልም፤ ቃሉ አይፈቅድልኝም፤ ልላችሁ ወስኛስሁ" አልኩት።

> "ለዚህ ነው ማስት ነው ጌታ ያስጨነቀኝ ... ስልከሀን ብለው ብሰው እምቢ አለኝ ... ነፍሴ ልትወጣ ደረሰች ... ሥራ መሥራት አቃተኝ ... እቤትህ እንዳልመጣ ቤትህን አላውቀውም ... ቢቸግረኝ ካሣዬ ጋ ደወልኩ እና የወንድም በቀለ ሰልክ ምን ሆኗል? አልኩት ... ላገኝህ በጣም እንደምፈልግ እና ላገኝህ ግን እንዳቃተኝ ነገርኩት ... ካሣዬም ሰልኩ ምን እንደ ሆነ አላውቅም ... ግን የግድ ማግኘት ካለብህ ለምን እቤቱ አልወሰድህም? አለኝ ... ተቃጠርን እና ተያይዘን መጣን ... በፍጹም እንደርሱ እንዳትል ..."

አለኝ። እጃችንን ታጥበን ጨርሰናል። ከገበታው ዘንድም ሌሎች ሰዎች ይጠብቁናል። ወደ ምሳችን ሄድን።

በልተን ስንጨርስ፥ እንግዶቹ መሄድ ነበረባቸው። የሥራ ሰዓት ነው። ትንሽ ጋደም ለማለት ያሰብኩት አሳብም እብሯቸው ሄደ። ለእኔም የሥራ ሰዓት ሆነ። እንደ ገና በጌታ ፊት ተንበረከክሁ -

> መሰፍንን ለምን እንደዚያ እንዳለኝ ጠይቄው ነበር ... ሁኔታው ሰላላመቸው መለለኝ፥ ምንም መልስ አልሰጠኝም ... አንተ ነህ መስፍንን የላከኸው? ... እና አሁን እኔ ምን እንዳደርግ ነው የምትፈልገው? ... አንተም እንደ መሰፍን ይህንን ነገሬን በባሮችህ ፊት እንዳላነሣው ነው የምትፈልገው? ... ውሳኔዬን መለወጥ አለብኝ ማለት ነው? ..."

ብቻ ልለው የምፈልገውን ሁሉ አልኩት። በቀጠሮዬ ሰዓት መሪዎቹ ቢሮ ሰደርስ፥ ከሰዓት በፊት በውስጤ አስፈው የነበረው ሁሉ ተፈትቶ ነበር።

አብረን ከጸለይን በኋላ፥ መሪዎቹ አንድ ጥያቄ ብቻ ነበር የጠየቁኝ። "የወደፊት እገልግሎትህን በተመለከተ፥ በውስጥህ ያለው ምንድነው?" እኔም ምዕራፍ አንድ ውስጥ የጠቀስኳቸውን፥ ጌታ ለመጋቢነት እንደ ጠራኝ የተረዳሁባቸውን፥ ሁለት ሦስት የሚሆኑ ነጥቦች ነገርኳቸው። እነርሱም "በእኛም ውስጥ ያለው ይኸው ነው" አሉኝ። በአጠቃላይ አብረን የቆየንበት ጊዜ ከሐያ ደቂቃ የሚበልጥ አልመሰለኝም፤ ተበራርከን ተለያየን - የዐሥሩን አስጨናቂ ቀናት፥ በጥቂት ቃላት። የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት።

የጨነገፈው የዕርቅ ሂደት

በዚህኛው እና በሚቀጥሉት አራት ርእሶች ሥር፥ ከሚያዝያ 1989 እስከ የካቲት 2000 ድረስ፥ ስለ ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ እና በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌሎች መካከል የነበረው አለመግባባት እንዴት እንደ ተፈታ በጣም በመጠኑ አተርካስሁ። ዝርዝሩ ብዙ ስለ ሆነ፥ ዝርዝሩ ውስጥ አልገባም። እሱን ለታሪክ ጸሐፊዎች እተወዋለሁ። እኔ በእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነቶች ላይ ብቻ፥ ከእነርሱም መካከል እንኳን እኔን በሚመለከቱት ላይ ብቻ ነው ማተኮር የምፈልገው። የዚህች መጽሐፍ ዓላማም ይህንን ማድረግ ነው። ጣልቃ ገብነቶቹ የተከናወኑበትን ጊዜ፥ ቦታ እና ሁኔታ ለአንባቢ ሳላሳይ፥ ስለ ጣልቃ ገብነቶቹ መናገር የነገሩን ከቡርነት የሚቀንስ መስሎ በሚሰማኝ ጊዜ ብቻ ወደ ታሪኩ ጎራ እላለሁ።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የሙሉ ወንጌል አማኞች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባዋ ናት። ንቅናቄዋ የጀመረው በ1958 ዓ.ም.መጀመሪያ ላይ ቢሆ ንም፥ የመጀመሪያዎቹን ሽማግሌዎቿን በመምረጥ በቤተ ክርስቲያን መልክ የተደራጀችው ግን በ1959 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ነው። ስያሜዋ "ሙሉ ወንጌል"

የሆነው ደግሞ ከሦስት ዓመታት በኋላ በ1962 ዓ.ም.ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት የሙሉ ወንጌል አማኞች አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የተሰባሰቡት እና በቤተ እምነት መልክ በሥርዓት የተደራጁት ከሰባት ዓመታት በኋላ በ1966 ዓ.ም. ላይ ነው።

በአጥቢያዋ እና በቤተ እምነቱ መካከል ጠንከር ያሉት አለመግባባቶች መታየት የጀመሩት የደርግ መንግሥት ከወደቀ በኋላ፥ ምናልባትም ከ1985 ዓ.ም. ወዲህ ሳይሆን አይቀርም። አንዳንድ ሰነዶችን ሳገላብጥ ለመረዳት እንደ ቻልኩት ከሆነ፥ መነሻው ላይ የአለመግባባቶቹ ምክንያት አጥቢያዋ እና የቤተ እምነቱ ጽሕፈት ቤት ሁለቱም በአንድ ከተማ ውስጥ መሆናቸው፥ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላትም በአብዛኛው ከአዲስ አበባ እና አንደ ደብረ ዘይት ካሉት በቅርብ ያሉ ከተሞች እንዲሆኑ መደረጉ ነበር። አንደዚያ እንዲሆን የተደረገው አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ በቶሎ መገናኘት እንዲችሉ ታስቦ ነበር። ሆኖም ለመልካም የታሰበው ነገር የችግሮች መንስዔም ሆኗል።

ለምሳሌ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መጋቢት 13 ቀን 1986 ዓ.ም. በቁጥር አሙ-ወ/01/252 ለኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ በጻፈችው ደብዳቤ እንደዚህ ብላለች፦

> የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት እንዲመሠረት አስተዋጽዖ ከማድረግ ጀምሮ ለአለፉት 20 ዓመታት ለጎብረቱ ዕድገት በማንኛውም ረገድ ድጋፍ ስታደርግ መቆየቷ ይታወቃል። ሆኖም ከአለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ በጎብረቱ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴና በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መካከል በሚፈጠረው አለመግባባት ... ቅሬታን ከመፍጠሩም ባሻገር የቤተ ክርስቲያኒቱን ውስጣዊ አሠራርና ህልውና የሚፈታተን ችግር ሲገጥመ ቆይቷል።
>
> ለምሳሌም ያህል፥ የጎብረቱ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የአጥቢያዬቱን የትምህርት ኮሚቴ በማፍረስ ወደ ኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ኮሚቴ እንዲለወጥ ሲያደርግ ቅዋሜ በማስማት ብቻ ቤተ ክርስቲያኒቷ በትዕግሥት አልፋዋለች ... ከዚህም በቀር በቅርቡ ማለትም በ1985 ዓ.ም. መጨረሻ ገደማ የጎብረቱ የሥራ አስኪያጅ

> ኮሚቴ የአዲስ አበባን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሳያሳውቅና ሳያስፈቅድ አባሎቾዋንና አገልጋዮቾዋን በቀጥታ በደብዳቤ በመጥራት የቤተ ክርስቲያኒቷ የሥራ ድርሻ በሆነው የጎብረቱ መተዳደሪያ ደንብ ላይ አላብ እንዲሰጡ በማድረግ ጉባዔ አካሂዷል። ይህ አሠራር በዝምታ የሚታለፍ ባለመሆኑ የአዲስ አበባ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰኔ 20 ቀን 1985 ዓ.ም. የአዲስ አበባና የአካባቢውን የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላት በመጥራት ሁኔታውን ገልጻ ተቃውሞ ያቀረበች ሲሆን ...

ከትምህርት ኮሚቴው አባላት መካከል አንዱ እኔ ነበርኩ። የተባለው ነገር እውነት ነው። ነገር ግን ሆን ተብሎ፥ የአጥቢያዋን የትምህርት ኮሚቴ ለማፍረስ የተደረገ አይመስለኝም። በአጥቢያዋም ሆነ በቤተ እምነቱ አመራር ላይ ያሉት ሰዎች እነዚያው ስለ ነበሩ፥ በደፏቸው ሁለት ባርኔጣዎች መካከል ያለውን እንድነት እና ልዩነት በውል ባለ ማጤን፥ ያደረጉት ነው የሚመስለኝ። ከእኔ ጋር በትምህርት ኮሚቴ አባልነት ከተመለመሉት ሰዎች መካከል፥ ይህንን እንድነት እና ሁለትነት በውል ያጤኑ፥ "በመጀመሪያ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኔን አስፈቅዱ" ያሉ ይኖሩ እንደ ሆነ አላውቅም። እኔ በበኩሌ ግን፥ እውነቱን ሰመናገር፥ የሁለቱ ልዩነት በጊዜው በፍጹም አልታየኝም ነበር።

እነዚህን እና እነዚህን የመሰሉ አለመግባባቶች ውስጥ ለውስጥ ሲብላሉ ቆይተዋል። ይፋ የወጡት ወይም ደግሞ ውጥረቱ የተበጠሰው ግን፥ የአጥቢያዋ ወንጌላዊ የነበረው ወንጌላዊ (በኋላ መጋቢ) አሸናፊ ዘማት በግሉ እንድ አዲሰ የሙሉ ወንጌል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ውስጥ ከከፈተበት ከሚያዝያ 1989 ዓ.ም. መጀመሪያ ጀምሮ ነው። አሸናፊ ቤተ ክርስቲያን የከፈተው በእንድ በኩል ያለ አጥቢያው ፈቃድ እና በሲላ በኩል ደግሞ በቤተ እምነቱ ዕውቅና ሰጭነት ነበር።

እኔ ሙሉ ጊዜዬን ለአገልግሎት ስሰጥ፥ ችግሩ መንተራፋት ከጀመረ ሁለት ወራት ገደማ ሆኖታል። አንዳንድ ወዳጆቼም "ኖረህ ኖረህ እንደዚህ ባለው ከፋ ቀን ሙሉ ጊዜህን ትሰጣለህ?" ብለውኛል - የሕይወቴ ዕጣ ፈንታ በእኔ እጅ ውስጥ ብቻ ያለ ይመስል። ጥቅምት 26 ቀን 1993 ዓ.ም. "መጋቢ" ተብዬ ስሾም ደግሞ፥ ችግሩ መንተራፋት እና ማንተራፋት ከጀመረ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ዐልፎታል። ከሰኔ ወር 1990 ዓ.ም. ጀምሮም ወደ ፍርድ ቤት ደርሷል - ከሣሽ ቤተ እምነቱ ነበረ። ከውስጥና ከውጭ፥ ከግለሰቦች እንሥቶ

አስከ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጉበረት የደረሰ የማሰታ ረቅ ሙከራም ተደርጎ ሳይሳካ ቀርቷል።

የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌልም፥ ቀደም ሲል በአዲስ አበባ እና በአካባቢው ባሉ አንዳንድ የመካነ ኢየሱስ አጥቢያዎች የተሄደውን መንገድ በመከተል፥ ከጳጉሜን ወር 1990 ዓ.ም. ጀምሮ ከአዲሰ አበባ ከልላዊ መስተዳድር ፈቃድ አግኝታ አራሷን ሕጋዊ አድርጋለች። በሁለቱ ግንባሮች መካከል የሚካሄደው መንተራፋት እና ማንተራፋት እየተካሄደ እያለ፥ በ1992 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ አራት ወንድሞች ያቀረቡት፥ ሁለቱን ወገኖች የማቀራረብ ጥያቄ በሁለቱም ተቀባይነት አግኝቶ፥ ሊንቀሣቀስ ጀምሯል። አራቱ አቀራራቢዎች ከሐዋሳ መጋቢ ተሾመ ወርቁ፥ ከሐረር ወንድም (በኋላ መጋቢ) መኮንን ወ/ሰማያት፥ ከአሰላ መጋቢ ታዬ ታከለ እና ከዎላይታ ሶዶ ወንጌላዊ (በኋላ መጋቢ) ወልዴ ቴጋ ነበሩ።

ይህ የማቀራረብ ሂደት አንደ ተጀመረ ነው እኔ የሥራ አመራር ቦርዱን የተቀላቀልኩት። እኔ ከመቀላቀሌ በፊት አንድ ወይም ሁለት ስብሰባዎች ተደርገው ቢሆን ነው። የማቀራረቡን ስብሰባ በተካፈልኩበት በመጀመሪያው ዕለት ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር፥ በሁለቱ ተቀራራቢ አካላት መካከል መተማመን አለመኖሩን ነው። የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል ከክልሉ መስተዳድር በስሚ ፈቃድ ማውጣቷ እና የሚደግፏትንም አጥቢያዎች በዙሪያዋ ማሰባሰብ መጀመሯ፥ እራሷን ቤተ አምነት የሚድረግ ሙከራ አንደ ሆነ ተደርጎ በቤተ አምነቱ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ በኩል ተወስዷል። በእኔ ዘንድ ያለው መረዳት ደግሞ፥ ያ ድርጊታችን አራሳችንን ለማዳን ስንል፥ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት፥ የፈጸምነው እንደ ሆነ ነው።

ስለ ሆነም በስብሰባዎቻችን ላይ፥ በዚያኛው አካል በኩል ይህንን ሥጋት ያስተዋልኩ በመሰለኝ ጊዜ ሁሉ፥ እጄን አነሣለሁ። ሲፈቀድልኝም፥ አኛ ከቤተ አምነቱ የመውጣትም ሆነ ወይም ሌላ ቤተ አምነት የመመሥረት ፍላጎት በፍጹም እንደ ሌለን፥ አሁን ላለው ቤተ አምነት መመሥረት በሰው ኃይል እና በፋይናንስ ጭምር ከፍተኛውን አስተዋጽዖ ማድረጋችንን፥ አንደዚያ አድርገን ያቋቋምነው ቤተ አምነትም ሠላሳ ዓመታት በማይሞላ አጭር ዕድሜው ውስጥ አንደዚህ ካለ ችግር ውሰጥ ሲወድቅ አያየን፥ ደግሞ ሌላ ቤተ አምነት ለመመሥረት የምንነሣ አለመሆናችንን፥ አብረውኝ ባሉት ሁሉ ስም በፍጹም

አርግጠኛነት አናገራለሁ። ይህንን በሁለት እና በሦስት ስብሰባዎቻችን ላይ ደጋግሜ የተናገርኩ ይመስለኛል። ይህ የእኔ ብቻም አቋም አይደለም። በጊዜው የመላው አዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አመራር፥ አገልጋዮች እና ምዕመናንም አቋም ይመስለኛል።

አንድ ቀን፥ አቢሮው ውስጥ ሆነን ይመስለኛል፥ ከፓስተር መርዕድ ጋር ስለዚሁ ጉዳይ አንነጋገራለን። በማቀራረቡ ስብሰባዎቻችን ላይ ስለሚነሡ የተለያዩ አሳቦች እና ስለሚሰጡ የተለያዩ አስተያየቶች ሰናነሣ፥ እኔም አየደጋገምኩ የማነሣው አሳብ አብሮ ተነሣ። እኔው ነኝ ያነሣሁት ይመስለኛል። "አንተ ግን የዚህን ያህል አርግጠኛ ሆነህ አትናገር አንጂ" አለኝ። አኔም "እንዴ? ለምን አርግጠኛ አልሆንም? አነርሱስ ቢሆኑ ይህንን ያህል አየተጠራጠሩን እንዴት ተደርጎ መቀራረብ ይቻላል ብለው ያስባሉ?" አልኩት። "ነገ ስለሚሆነው ሁላችንሰ ብንሆን ምን አናውቃለን ብለህ ነው?" አለኝ። አንደ ዋዛ ነው ነገሩን ጣል ያደረገው። ከዚህ ያለፈ ሌላ ምንም ዐይነት ማብራሪያም አላከለበትም። አርሱ ይህንን ያለው በፍጹም በንጹህ ልብ ሊሆን ይችላል። ምናልባት የአኔ አእምሮ ይሆናል ይህንን ንግግሩን አርሱ ባላሰበው መንገድ የተረጎመው።

ብቻ ተረጎመው። አዚያው አጠገቡ ተቀምጬ በውስጤ ጥያቄ ተፈጠረብኝ - "ምን ማለቱ ነው?" አልኩ። "እኔ ወደዚህ አመራር ከመምጣቴ በፊት የተመከረ፥ እኔ የማላውቀው ሌላ አሳብ አለ ማለት ነው አንዴ?" አልኩ። ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አንደ ወጡ ለመቀረት፥ ሌላ ቤተ አምነት ለመመሥረት፥ የታሰበ ወይም የተመከረ ነገር ይኖር ይሆን አንዴ? ያን ዕለት ብዙ አሰብኩ። አና መጸለይ ነበረብኝ -

> "ጌታ ሆይ፥ አነዚህ ወንድሞቼ እንደዚህ ያለ አሳብ ቢያነሡ፥ እኔ ከአነርሱ አለያለሁ። በዚህ ጉዳይ ቢያስፈልግ ቤተ ክርስቲያኗንም አለቅቃለሁ። ቤተ አምነቱን እና አገራቱንም ጭምር አለቅቃለሁ። ከአነዚህ ወንድሞቼ የምለይ ከሆነ፥ በዚህ ጉዳይ አለያለሁ"

አልኩ። ለምን የዚህን ያህል አሩቅ መሄድ እንዳሰፈለገኝ በእውነት አላውቅም። በጊዜው የነበረኝን አቋም ለማሳየት ነው ይህንን የምጠቅሰው።

ጥርጥሬ ትከክል እንደ ነበረ የሚያረጋግጥልኝ ምንም ዐይነት ምልክት አላየ ሁም። እንዲያውም ምንም በሌለበት እንደዚያ በማሰቤ አራሴን አሰከ መኮነን

ደርሻለሁ፡፡ የመቀራረቡ ስብሰባ በጣም መንፈሳዊ በሆነ መልኩ ቀጥሏል፡፡ አራቱ አቀራራቢ ወንድሞች ትሑታን ናቸው፡፡ ስብሰባውን ከመምራት ያለፈ በሁሰቱም በኩል ባሉት ተቀራራቢዎች ላይ የሚያደርጉት አንዳችም ዐይነት ተጽዕኖ አልነበረም፡፡ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል ሥራ አስኪያጅ ከሚቴ በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል ላይ በአዲስ አበባ እና በነቀምት የከፈተቻቸውን የፍርድ ቤት ፋይሎች፥ ያስ ምንም ቅድመ ሁኔታ ዘጋች፡፡ የማቀራረቡ ሂደት ጳጉሜን 02 ቀን 1994 ዓ.ም. በተደረገ "አገር አቀፍ የንስሐ፥ የይቅርታና የምስጋና ፕሮግራም" ተደመደመ፡፡ በጣም ደስ አሰኝ፤ እግዚአብሔርንም አመሰገንኩ፡፡

ሆኖም፥ የዕርቁ አፈጸጸም የሚቀሩት ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ነበሩ፡፡ እነዚህም የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል ሕጋዊ ሰውነት አንዲኖራት ያስቻለውን ፈቃድ፥ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንን ስያሜ እና ቀጣዩን አስተዳደራዊ ግንኙነት የሚመለከቱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በእነርሱ በኩል፥ እኛ ከአዲስ አበባ መስተዳድር ያወጣነውን ፈቃድ አንድንመልስ፥ በእኛ በኩል ደግሞ አነርሱ "ቤተ ክርስቲያን" ሳይሆን "ጽሕፈት ቤት" እንዲባሉ ፍላጎት ነበረ፡፡ ሆኖም አኛም ፈቃዳችንን ስመመለስ፥ አነርሱም ስያሜአቸውን ሰመለ ወጥ ፈቃደኞች አልነበርንም፡፡ የወደ ፊቱን አስተዳደራዊ ግንኙነታችንንም በተመለከተ ገና ከስምምነት ላይ አልደረስንም፡፡ አነርሱ ብዙ አጥቢያዎች ያሏት አንድ አገር አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ሲሆኑ፥ እኛ ደግሞ ብዙ ጸሎት ቤቶች ያሏት አንድ ከተማ አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ነበርን፡፡

ፈቃዳችንን ለመመለስ ያልፈለግነው አገራችን አሁን ፌዴራሳዊ አደረጃጀት መከተል ስለ ጀመረች፥ በቅርቡ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ከየክልላቸው ፈቃድ እንዲያወጡ ሳይጠየቁ አይቀርም በሚል ነው፡፡ አንደምንሰማው ከሆነ፥ ፌዴራላዊ አደረጃጀት ባላቸው አገሮች አጥቢያዎች ፈቃድ የሚያወጡት ከየክልላቸው መንግሥታት ነው፡፡ የፌዴራሉ መንግሥት ፈቃድ የሚያስፈልገው ቤተ እምነቱ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የአሁኑ አንቅስቃሴአችን በአገር አቀፍ ደረጃ ሊመጣ ሳለው አሠራር ፋና ወጊ ከመሆኑ በስተቀር፥ የሚያስከትለው አንዳች ጉዳት የለውም የሚል አቋም ነበረን፡፡ በተጨማሪም አሁን በአብያተ አምነቶች እና በአጥቢያዎቻቸው መካከል አልፎ አልፎ የሚታየውን "የአስቃ እና የምንዝር" ግንኙነት ያስወግዳል ብለን አሰበናል፡፡

ቤተ አምነቱ "ጽሕፈት ቤት" እንዲባል የፈለግነውም የራሱ የሆኑ ምዕመናን ስለ ሌሉት፥ የውሃ ጥምቀት እና የጌታ አራት ሥርዓቶችን ስለማይፈጽም፥ አገልግሎቱ በአገሪቱ ያሉትን አጥቢያዎች የማስተባበር ብቻ ስለ ሆነ ነው፡፡ በጊዜው አኛ፥ ቤተ አምነቶች "የቤተ ክርስቲያን ኢጋዥ" (PARA CHURCH) እንጂ፥ "ቤተ ክርስቲያን" አይደሉም የሚል አቋም ነበረን፡፡ አገር አቀፉ የንስሐ፥ የይቅርታና የምስጋና ፕሮግራም፥ በዚያም ላይ የምንፈራረመው የጋራ ሰነድ፥ ገና ባልተስማማንባቸው በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር እና ለመግባባት ልባችንን ያስሰልስልናል የሚል እምነት በሁላችንም በኩል ነበረ፡፡ እነዚህን ነገሮች መቼ እንደምንመስስባቸው የጊዜ ገደብ ያላስቀመጥን ቢሆንም፥ በእኔ ዘንድ የነበረው መረዳት ግን በእንድ እና ቢበዛም በሁስት ወራት ዕድሜ ውስጥ ሳይሆን እንደማይቀር ነበር፡፡

በእኔ ውስጥ በነበረው መረዳት ዕድሜ ውስጥ ይመስስኛል አቀራራቢዎቹም ዕርቁን ወደ መቋጨቱ ሂደት እንድንመለስ ሊጎተጉቱን የጀመሩት፡፡ በእኛ፥ በአዲስ አበቦቹ መካከል ግን፥ ጳጉሜን 02 ቀን የፈጸምነው ድርጊት "ይቅርታ" ነው ወይስ "ዕርቅ?" የሚል ከርከር ወዲያውኑ ተነሣ፡፡ ከርከሩ እልባት ሳያገኝ ደግሞ፥ አዳዲስ መሪዎችን፥ ዲያቆናትን እና የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን የማስመረጥ እንቅስቃሴ ጀመርን፡፡ ስለዚህም የዕርቁን ሂደት ወደ መቋጨቱ በቶሎ ልንመለስ እንደማንችል ስለቀራራቢዎቻችን ነገርናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌሎቹም በኩል "የተደረሰበት ስምምነት ፍትሐዊ አይደለም ... ወደ አዲስ አበቦቹ የሚያደለ ነው ... ልንቀበለው አይገባም... " የሚል አንቅስቃሴ ነበረ፡፡ በዚህ መሐል ዓመቱ ተገባደደ፡፡ የዓመቱ መገባደጃም ቤተ አምነቱ አዲስ ምርጫ የሚያደርግበት ወቅት ሆነ፡፡ በዚያ ምርጫም በመቀራረቡ ሂደት ውስጥ ያልነበሩ አዳዲስ ሰዎች ወደ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባልነት መጡ፡፡ አዲስ ዋና ጸሐፊም ተመረጠ፡፡ በአዳዲሶቹ ተመራጮችም መካከል ከአንድ ዓመት በፊት የተደረገው ዕርቅ ከልብ መሆኑን የሚጠራጠሩ ሰዎች ነበሩ፡፡

ጥርጥሩ በአነርሱ ብቻም አልተወሰነም፡፡ ከእኛም በኩል የአነርሱን ጥርጣሬ የሚጋሩ ሰዎች ተገኙ፡፡ "ንስሐ ከገባን እና ይቅርታ ከተጠያየቅን ታርቀናል ማስት አይደለም ወይ? እንዴ ከታረቅን ደግሞ ስምንድነው ወደ ኋላ

የምንመለሰው?" የሚል አስተሳሰብ ከየት እና ለምን መጣ? ዳር አድርሰነው ለነበረው የዕርቅ ሂደት አልባት ሳናደርግለት፥ በእኛ አሠራር ብዙ ወራት ወደሚወስደው የመሪዎች፥ የዲያቆናት እና የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ምርጫ ውስጥ ተንደርድረን እንዴት ገባን? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ አልነበረም፡፡ አምስት አባላት ያሉት "አመቻች" የሚል ስያሜ የተሰጠው አካል በእኛ በኩል ነበረ፡፡ ከመጀመሪያው ጀምሮ የዕርቁን ሂደት የሚከታተለው እና የሚያሰፈጽመው ይህ አካል ሲሆን፥ አሁን ግን የዕርቁ ሂደት ለምን እንዳልቀጠለ ያም አካል እያውቅም፡፡ ፓስተር መርዕድ በጊዜው በአገር ውስጥ አልነበረም፡፡ ምክትል ሰብሳቢው ፓስተር ፈቃዱ ደግሞ ያለፈው ዕርቅ ሲደረግ አገር ውስጥ ስላልነበረ፥ ዝርዝር ሁኔታውን አያውቀውም፡፡

መዋዠቅ

በዚህ ዐይነት ነገሩ እንደ ገና ጥሬ ሆነ፡፡ ጥሬ መሆን ብቻም ሳይሆን፥ በሁለታችንም በኩል ያለ ልክ እየጦዘ ሄደ፡፡ ከእኛ ጋር ያሉት አጥቢያዎችም ቁጥር እየጨመረ መጣ፡፡ መጨረሻ ላይ ቁጥራቸው ከ40 በላይ እንደ ደረሰ ነው ትዝ የሚለኝ፡፡ አነርሱን በማስተባበር "የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል ..." በሚል ሳይሆን፥ "የሙሉ ወንጌል አማኞች አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት" በሚል ስያሜ ሌላ ቤተ እምነት ለማቋቋም ተንቀሳቀስን፡፡ እኔ በበኩሌ ለዚህ እንቅስቃሴአችን ከእንድም ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ያገኘሁለትም መስሎኝ ነበር፡፡

> በዚያ ጊዜም ኢዮርብዓም ከኢየሩሳሌም ሲወጣ፥ የሴሎው ነቢይ አኪያ በመንገድ ላይ ተገናኘው፤ አኪያም አዲስ መጎናጸፊያ ለብሶ ነበር፤ ሁለቱ ብቻቸውን ሳሉ፥ አኪያ የለበሰውን አዲስ መጎናጸፊያ ይዞ ዐሥራ ሁለት ቦታ ቀደደው፡፡ ከዚያም ኢዮርብዓምን እንዲህ አለው፤ 'ዐሥሩን ቁራጭ ለራስህ ውሰድ፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤ እነሆ፤ መንግሥቱን ከሰሎሞን እጅ አቀዳለሁ፤ ዐሥሩን ነገድ ለአንተ እሰጣለሁ ...
>
> ይህን የሚደርገው እኔን ትተው የሲዶናውያንን አምላክ አስታሮትን ... ስላመለኩ እንዲሁም አባቱ ዳዊት እንዳደረገው በመንገዴ ስላልሄዱ በፊቴ ትክክለኛውን ነገር ስላላደረጉ፥ ሥርዓቴንና ሕጌን ስላልጠበቁ ነው ... እንጉን ግን እኔ እወስድሃለሁ፤ ልብህ በወደደው ሁሉ ላይ ትነግሣለህ፤ የእስራኤልም ንጉሥ ትሆናለህ፡፡ ባሪያዬ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ እንተም ያዘዝሁህን ሁሉ ብትፈጽም ... የዳዊትን ሥርወ መንግሥት እንዳጸናሁ፥ ለአንተም እንዲሁ እስከ ዘላለም የሚኖር ሥርወ መንግሥት እጸናለሁ፤ እስራኤልንም ለእንተ አሰጣለሁ ... (1ነገ. 11፥29-39)

ኢዮርብዓም እግዚአብሔር እንደ ተናገረው እድርጎ ቢሆን ኖሮ፥ ይሁዳ እና እስራኤል የተባሉ ሁለት ኃያላን መንግሥታት በመካከለኛው ምሥራቅ ሊኖሩ ነበር ማለት ነው፡፡ ልክ እንደዚሁ፥ ሁለት የሙሉ ወንጌል አብያተ አምነቶች በኢትዮጵያ እንዲኖሩ እግዚአብሔር ፈልጎ ቢሆንስ? አርግጥ እንደዚህ ለማድረግ መፈለጉን (ለኢዮርብዓም እንደ ተናገረው) ለእኛ አልተናገረንም፡፡ ሆኖም በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ አብነት (PRECEDENCE) ሊሆነን የሚችል ነገር ይኸው አግኝተናል፡፡

ይህም ብቻ አይደለም፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አጥቢያ ዘለል ስለ ሆነ የቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት ምንም ዐይነት አስተምህሮ የለም፡፡ ጌታም ሆነ ሐዋርያቱ ስለዚህ ጉዳይ ምንም አላስተማሩም፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ በዓለም ዙሪያ ወደ ፊት ልታልፍባቸው ያለውን የተለያዩ የፖለቲካ፥ የኤኮኖሚ፥ የባሕል እና የማኅበራዊ ሁኔታዎች የሚያውቀው ጌታ፥ አደረጃጀቷን እንደ ጊዜው፥ እንደ ቦታው እና እንደ ሁኔታው "እጥፍ ዘርጋ" (FLEXIBLE) ማድረግ እንድትችል ሆነ ብሎ ከፍት የተወላት ይመስለኛል፡፡ ለቤተ እምነት አሠራር የምንከራከረው ከዚህ እንጻር ነው እንጂ፥ መቼም "መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው" ከሚል እንጻር ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ እንድ ቤተ እምነት በውስጥ ችግሮች አስገዳጅነት ብቻ ሳይሆን፥ አለቅጥ ላለማበጥ እና ለአስተዳደራዊ ቅልጥፍናም ሲባል፥ አራሷን በስምምነት ለሁለት ወይም ለሦስት ብትከፍል ምን አለበት?

ዳሩ "ሞኝ እና ወረቀት" እንደሚባለው፥ እንዴ የያዝነውን መልቀቅ ለሚቸግረን አበሾች ይህ እንዴት ይሆንልናል? እና በቤተ እምነቱ አቤት ባይነት ይህ እንቅስ ቃሴአችን ታገደ፡፡ ትንሽ ቆይቶ በአዲስ አበባ መስተዳድር የተሰጠን ፈቃድም እንዳይታደስ ተከለከለ፡፡ ወዲያውም የማኅበራት ፈቃድ የሚሰጠው በፌዴራል መንግሥት ደረጃ ብቻ እንዲሆን የሚያደርግ አዲስ መመሪያ እንደ ወጣም ሰማን፡፡ ይህንንም መንግሥት በራሱ ምክንያት ያደረገው እንጂ ከእኛ የተነሣ ያደረገው አልመሰለኝም፡፡

ከዚህ ከዚህ ሁሉ ጋር ተያይዞ፥ ጊዜአችን በነገር፥ በጭቅጭቅ፥ በወሬ፥ በሐሜት፥ ከተለያዩ የሕግ ባለሞያዎች ጋር በመነጋገር፥ ደብዳቤ በማርቀቅ፥ ተወጥሮ ተያዘ። ከ1996 ዓ.ም. መጀመሪያ ገደማ ጀምሮ ለአራት ተከታታይ ዓመታት የየዕለት ሥራችን ይኸው ሆነ። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ፥ በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጭ፥ በተለያዩ ደረጃዎች ያደረግናቸውን የውስጥ ስብሰባዎች ቁጥር ውስጥ ሳላስገባ (በየቀኑ፥ አንዳንዴም በቀን ሁለቴ እና ሦስቴም ነበሩና)፥ ከሁለት የፍትሕ ሚኒስትሮች ጋር አንድ አራት ጊዜ፥ ከፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ ጋር አንድ ሁለት ጊዜ፥ ከፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ጋር አንድ ጊዜ፥ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ጋር አንድ ጊዜ፥ ከአዲስ አበባ መስተዳድር የማኅበራት ምዝገባ ከፍል ኃላፊ ጋር ሁለት ጊዜ ያህል እንደ ተሰበሰብኩ እስታውሳለሁ።

አዲዮ (ADIEU) ጸሎት። አዲዮ ጥሞና። በዚህ ጊዜ ነው "'ሙሉ ወንጌል' የሚለውን ስያሜ ለኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌሎች ለቅቀንላቸው ለምን አኛ በሌላ ስም አንመዘገብም?" ብዬ ማሰብ የጀመርኩት። ሕዝቡ ለስሙ ያለውን ፍቅር ዐውቃለሁ። እኔ አራሴም የሙሉ ወንጌል አባል እንዴት አንደ ሆንኩ አልረሳ ሁም። ስም መቀየር ማለት በ"ሙሉ ወንጌል" ስም ያካበትነውን ንብረት ሁሉ መልቀቅ ማለት ሊሆን እንደሚችልም አላጣሁትም። ሆኖም ከነገር ይሻለኛል። የደም ግፊት ጀምሮኛል። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆኖ ከይርጋዓለም ጀምሮ የማውቀው፥ ዶከተር እንዳለ ካሣ ለሆነ ያህል ጊዜ ከተከታተለኝ በኋላ መድ ኀኒት አስጀምሮኛል። መሞት አስብኝ? ለማን ብዬ ነው የምሞተው? ለጌታ? በሆነማ እንዴት ባማረብኝ።

የከርስቶስ ኢየሱስን የፍቅር ወንጌል፥ ቢሆንልኝ ከኦርቶዶከሶች እና ከካቶሊኮ ችም ጋር ሳይቀር፥ አብሬ የምሰብከበትን ቀን ስናፍቅ እና ስጸልይም የኖርኩ ሰው፥ እንዴት ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌሎች ጋር አብሮ ማገልገል ያቅተኛል? አሳቤን በቦርድ ስብሰባ ላይ ተናገርኩ። ከመጋቢያኑ አንዳንዶቹ በጎብረታችን ላይ ከሰሱኝ። "ፓስተር በቀለ ስም እንቀይር አያለ ነው። በመካከላችን ካሉት እንደዚህ ያሉ ሰዎች አራሳችንን ሳናጸዳ፥ እንዴት ጎብረት ማድረግ እና አብረን መጸለይ እንችላለን?" አሉ። እኔም "አዎን ብያለሁ፤ ያልኩበትም ምክንያት አንደዚህ እና እንደዚህ ነው፤ ይቅርታም አልጠይቅም" ስል መልስ ሰጠሁ።

ዓርብ፥ ጥቅምት 01 ቀን 2000 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል ዓመታዊው የመሪዎች ጉባዔ ተጀመረ። የበዓል ቀን ስለ ነበረ፥ ከወትሮው የበለጠ ብዙ ተሳታፊዎች ነበሩ። በጠዋቱ የጥሞና ጊዜ ላይ፥ ወንጌላዊ (በኋላ መጋቢ) ደረጀ ጉበረ አምላክ የእግዚአብሔርን ቃል አካፈለን። እኔ ዘግይቼ ስለ መጣሁ፥ የተቀመጥኩት ከመጨረሻው አግዳሚ ላይ ነበር። ወንጌላዊ ደረጀ ስብከቱን ጨርሶ አየጸለየ አያለ፥ መልእክት አመጣ። በመልእክቱ ውስጥም "አሁን በር የምትቀይርበት ጊዜ እይደለም" የሚል ዓረፍተ ነገር በተደጋጋሚ ተናገረ።

ዓረፍተ ነገሩ በቀጥታ ተወርውሮ መጥቶ እኔ ልብ ውስጥ ተቀረቀረ። በሚቀጥ ሉት ቀናት፥ ከብዙ አባልጋሮች ጋር መልእክቱን ለማጣራት ሞከራለሁ። አብዛኞቻቸው እንደዚህ መባሉን አንኳን አልሰሙም። አንዳንዶቹ ሰምተውታል፤ ነገር ግን ምንም ትርጉም አልሰጣቸውም። መልእክቱ ለእኔ ብቻ ነው የነበረው ማለት ነው። አዚያው ወንጌላዊ ደረጀ እየጸለየ አያለ፥ "ጌታ ሆይ፥ ስም ለመቀየር ያስብኩበትን ምክንያት አንተ ታውቀዋለህ፤ ካልወደድክው ግን ይኸው አሁኑኑ አሳቤን አንሥቻለሁ፤ አንደዚህ ስላስብኩም ይቅርታ አለምናለሁ" አልኩት።

በእነዚያ ዓመታት ውስጥ የአኔን ያህል የአቋም መዋዠቅ የታየበት ሌላ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አገልጋይ ያለ አይመስለኝም። ከላይ ለመግለጽ አንደ ሞከርኩት በተደጋጋሚ ነው አቋሜን የለዋወጥኩት። አቋሜን የለዋወጥኩት አንደ ተሳሳትኩ ወይም ደግሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳይደለ ስለተረዳሁ ነው። አቋሜን መለወጥ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘሁት ነው አንጂ፥ በሌላ ተልካሻ ምክንያት አልነበረም። ይሁን አንጂ፥ "ኧረ እንዲያው ምን ያለሁት ነኝ? አቋም ለመያ ዝም ሆነ እቋም ለመቀየር ለምን አቸኩላለሁ? ስው ሁሉ የሚናገረውስ ለምንድነው አውነት የሚመስለኝ?" እያልኩ አራሴን በተደጋጋሚ ከስሼዋለሁ።

ከዚያም ዐልፌ፥ ከብዙ ዓመታት በፊት እነዚያ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ካድሬዎች "አስመሳይ እና አደገኛ ጴንጤ" ያሉኝንም አንኳን አስታውሼዋለሁ። የእግዚአብሔርን ቃል ሳስተምር ብቻ የምታውቀኝ ወርቅ ውሃ የተባለች አኅትም፥ አንድ ጊዜ "ፈከ ትመስለኛለህ" ብላኛለች - በጉባዔ አያስተማርኩ አያለሁ አቋርጣኝ። አርግጥ ያንን ያደረገችው ወደ ጌታ ከመምጣቷ በፊት ነበር። ወደ ጌታ ከመጣች በኋላ በጣም የምንዋደድ ወንድም እና እኅት ሆነናል። አንድ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል ከፍተኛ የአመራር አካል

የሆነ ሰው ደግሞ፥ "ስማኝ ... እንግዲህ ዛሬ ልንገርህ ... እኔ መንፈሰን የመለየት የጸጋ ሰጠታ አለኝ" ብሎኛል። "መልካም መንፈሰ እንደሌለህ በተሰጠኝ መንፈሰን የመለየት ሰጠታ አማካኝነት ዐውቄዋለሁ" ማለቱ ነበር።

ከገነት ጋር በተጋበንባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በሆነ ጉዳይ ስንነጋገር፥ አርሷም እንደዚሁ የሚመስል ነገር ብላኝ ነበር። በግንቦት ወር 1967 ዓ.ም. የጻፍኳት "እንደምትናገረው ኑር?" የተሰኘች ግጥም በጊዜው ለአርሷ የሰጠኋት ምላሽ ነበረች። ለሌሎቹስ ምን ምላሽ ልሰጣቸው? እውን እንደሚሉኝ ነኝ ይሆን? ማን ያውቃል? መጠርጠርሰ ምን ከፋት አለው? ከሆንኩኝ ነኝ። ካልሆንኩም ደግሞ እልሆንኩም።

"ቡፋ ነህ!" አልሽኝ?
"እንደምትናገረው የማትኖር?"
ካልሽስ፥ እንደማስበውም እልናገር።
"ፈሪ ነህ!" ብትይኝ ወይም "እጭበርባሪ!"
ልክ ነሽ፤ ሁለቱንም ነኝና፥ እስክ ተወሰነ ዲግሪ።
ኧረ እነዚህ ብቻም አይደሉ!
አንቺ ገና ያላየሻቸው -
አያሌ ሕጸዮች በውስጤ አሉ።
ለዚህ ነው ማንም "ምን" ቢለኝ፤
እኔን እንደኔ የማይሰድበኝ።
ሁሉ የተሰማውን ቢናገር -
የተናገረውንም ሁሉ ቢኖር -
ዓለማችንስ ምን በመሰለች ነበር?
"እንደምትለው አትኖርም!" አልሽ?
እውነት ተናገርሽ።
እኔስ የማስበውንም አልል፤
የምለውንም አላሰተውል፤
ነባቢት ነፍሴ በውስጤ፥
የምታነበንበውን ንብነባ፥
በምላሴማ ባስተጋባ፤
የት ልውል? የት ላድር? የት ልገባ?

እንቺስ መች እጣሽው፥ የልቡን የሚናገር፥
"ዕብድ" እንደሚባል በኖ አገር።'
ታዲያ መለፍሰፉን አንጂ -
የሚለውን ለማያውቅ ዲዳ -
ለመኖር በመዘጋጀት ዕድሜውን ላገባደደ፥
መኖር ምን እንደሆን ማን ላልተረዳ -
"እንደምትናገር ኑር!" ብትይው፤
እውን የሚቻል ነገር ነው የጠየቅሽው?
የማይቻል ደግሞ አትጠይቂ፤
ከጳውሎስ[2] እንዳንሻል ሰታውቂ።
እንዳይሳሳት እይደለም የሰው ዕጣ፤
በሰህተቱ እንዲያዝን እንጂ፤
አራሱን በጸጸት እንዲቀጣ፤
በኑዛዜ እንዲታጠብ፥ በንስሐ እንዲነጣ።

የግዱ ዕርቅ

የሙሉ ወንጌል ችግር በዚያም ሆነ በዚህ በኩል ያሉትን ብዙ የቤተ ክርስቲያ ኒቱን አገልጋዮች ዐንገት ያለደፋ ችግር ነበር። ያ ችግር በጣም የሚዋደዱ፥ ሰለ ጌታ ብዙ መከራ እብረው የተቀበሉ ቅዱሳንን የለያየ ችግር ነበር። ጎብረቶች እና አጥቢያዎች፥ ባል እና ሚስት፥ ወላጆች እና ልጆች፥ እብረው ማምለክ እና ማገልገል እለክ እለመቻል ድረስ የደረሱባቸው ቤቶች እና ቦታዎች አሉ። እነዚያ ዓመታት በራሳቸንም ሆነ በሌሎች እብያተ ክርስቲያናት ጉባዔዎች ፊት ብቻ ላይሆን፥ በትንንሽ ጎብረቶች እና በቤተ ሰቦችም ፊት እንኳን ለመቆም ድፍረት ያጣንባቸው ዓመታት ነበሩ። ፍቅርን እና ምሕረትን፥ ይቅርታን እና ዕርቅን፥ ሰለ መሳሰሉት ታላላቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች እንዴት ብለን እንናገራለን? እነዚያ ዓመታት በራሳችን ጎሊና ብቻ ሳይሆን፥ በብዙ በሚያውቁን እና በማያውቁን ሰዎች ምላሰ የተገረፍንባቸው ዓመታትም ጭምር ነበሩ።

እነዚያ ዓመታት የሙሉ ወንጌል አባላት የሆኑ እና ያልሆኑ፥ በአገር ውሰጥ እና ከአገር ውጭ ያሉ፥ ብዙ ቅዱሳን በጌታ ፊት የጮኹባቸው ዓመታትም ነበሩ። በችግሩ ዕድሜ ሁሉ በአልጋቸው ላይ ያልተኙ ሰዎች አሉ ሲባል ሰምቻለሁ።

ቢያንስ ለ፴ሥር ዓመታት ያህል ማለት ነው። እኔ በነበርኩበት ጎራ በኩል፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተካሄዱት የጾም እና የጸሎት ፕሮግራሞች ለቁጥር ያታክታሉ። የጾም እና የጸሎት ኮንፈረንሶችንም አድርገናል። ለችግሩ ምንም ፀይነት እስተዋጽዖ ያላደረጉ እና ስለ ችግሩም እንዳች የማያውቁ፥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምዕመናን ዕንባቸውን በእግዚአብሔር ፊት አፍስሰዋል።

"ሳል ይዞ ሥርቆት፥ ቂም ይዞ ጸሎት" አንዲሉ፥ በእነዚህም መካከል የችግሩ ባለቤቶች የሆንን፥ ችግሩም ለእኛ በሚመቸን እና እኛ በምንፈልገው መንገድ ብቻ እንዲፈታልን የጸለይን ሰዎችም እንጠፋም። ሁላችንም ግን እግዚአብሔርን "እባክህን ጣልቃ ግባ" ብለነዋል። ሆኖም፥ ጣልቃ የሚገባው መንግሥትን እስታራቂ አድርጎ በማስነሣት ይሆናል ብሎ ያሰበ ሰው፥ ከእኔ ጀምሮ እንድም የነበረ አይመስለኝም። መጸለይ ሌላ፤ የጸሎትን መልስ መቀበል ሌላ።

እንዳንድ ወገኖች የዕርቁ ሂደት ከተጠናቀቀም በኋላ እንኳን፥ በመንግሥት አስገዳጅነት የመጣ ዕርቅ እንጂ፥ እግዚአብሔር ያመጣው ዕርቅ ነው ብሰው ለመቀበል እንደ ተቸገሩ ዐውቃለሁ። መንግሥታትን በማስነሣት፥ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በሕዝቡ እና ለሕዝቡ ያደረጋቸውን ታላላቅ ነገሮች ባያውቋቸው ነው መቼም አልልም። ለምሳሌ ሕዝቡን ከተስፋው ምድር ለመንቀል የከለዳውያንን ንጉሥ ናቡከደነፆርን፥ ሕዝቡን ወደ ተስፋው ምድር ለመመለስ ደግሞ የፋርሱን ንጉሥ ቂሮስን ተጠቅሞባቸዋል። ሁስተኛው ቤተ መቅደስ በኢየሩሳሌም እንዲሠራ የሚደናውያንን ንጉሥ ዳርዮስን፥ የኢየሩሳሌም ቅጥርም እንዲጠገን የፋርሱን ንጉሥ አርጤክስስን ተጠቅሞ ባቸዋል። ሌሎችንም አያሌ ምሳሌዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከታሪክ መጥቀስ ይቻላል።

በአዲስ ኪዳንስ ቢሆን "እንግዲህ ከሁሉ አስቀድሞ ልመናና ጸሎት፥ ምልጃና ምስጋና ለሰዎች ሁሉ፥ <u>ለነገሥታትና ለባለ ሥልጣናት ሁሉ</u> እንዲደረግ አላስባለሁ፤ ይህም በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና ሁሉ፥ <u>በሰላምና በጸጥታ እንድንኖር</u> ነው። ይህ በእግዚአብሔር በአዳኛችን ፊት ደስ የሚያሰኝ ነው። እርሱ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ ይፈልጋል" (1ጢሞ. 2፥1-4 ሥርዝ የተጨመረ) የተባለው፥ እግዚአብሔር

በምድራዊ መንግሥታት በኩል ለቤተ ክርስቲያኑ የሚያደርግላት በጎ ነገር ስላለ አይደለምን?

መንግሥት እና ሃይማኖት እንዳቸው በሌላቸው ጉዳይ እንደማይገቡ በሕገ መንግሥት የተደነገገ ቢሆንም፥ ሕዝብ በሠላም እንዲኖር የማድረግ ግዴታ በመንግሥት ጫንቃ ላይ እንዳለ ማን አሌ ይላል? እኛስ ብንሆን እርስ በርሳችን በተጣላን ጊዜ፥ አቤቱታዎቻችንን እና ከሦቻችንን እየያዝን የሄድነው ወደነዚያው፥ በፌዴራል እና በክልሎች ደረጃ ወዳሉት የመንግሥት አካላት አይደል? የሕዝቡን ጩኸት የሚሰማው እና የሚመልሰው እግዚአብሔር፥ የኢትዮጵያን መንግሥት በማስነሣት በእኛም ጉዳይ በድንቅ ሁኔታ ጣልቃ ገብቷል።

"አሁን በር የምትቀይርበት ጊዜ አይደለም" በተባልኩ ልክ በሣምንቱ፥ ጥቅምት 08 ቀን 2000 ዓ.ም. ሌሊት ከእንቅልፌ ስነቃ፥ ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ደርሷል። የሆንኩትን አላውቀውም፤ ነገር ግን በፍጹም ጤና አልነበርኩም። በጣም ደነገጥኩ። እጅግም ፈራሁ። "አሁንስ ማበዴ ነው መስለኝ፥ ተነሥቼ ወደ እግዚአብሔር ልጩኽ እንጂ፥ ምኑን ተኛሁት?" አልኩ። ጉልበቶቼ ገና መሬት ሲነኩ ደግሞ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል፥ ከዚያ በፊት በፍጹም በማላውቀው ፀይነት፥ ወረደብኝ። ስንበረከክ ከሌሊቱ ምናልባት 9:00 ሰዓት ይሆን ይሆናል። ከተንበረከክሁበት ስነሣ ግን ከቀኑ 5:00 ሰዓት ሆኖ ነበረ። እግዚአብሔር በሚያውቀው፥ ይህንን የምናገረው የእርሱን ቸርነት መመስከር ስላለብኝ እንጂ፥ እኔ በጸሎት ብርቱ ነኝ ለማለት አይደለም።

በእማርኛ ወይም በኢንግሊዝኛ ቋንቋዎች አልጸለይኩም። ተጀምሮ እስኪጨረስ በልሳን ነው የጸለይኩት። የዚያን ቀኑ ልሳኔ ደግሞ ከዚያ በፊት የማውቀው ዐይነት ልላን አይደለም። ፈጽሞ የተለየ ነው። በዐይነቱም በጣም ብዙ ነው። የመንፈስ ቅዱስ መቃተት ደግሞ በጣም ብርቱ ነው። ከእንጀቴ ውስጥ ስቅስቅ አድርጎኝ ነው የሚወጣው። ነፍሴ ልትወጣ ወደ ላይ መጥታ ጉሮሮዬ ውስጥ ትወተፋሰች። የታረደ ከብት፥ ወይም ደግሞ ነፍሱ ልትወጣ በጣር ላይ ያለ በሽተኛ እንደሚያንቋርረው ያለ ድምፅ ነው ከውስጤ የሚወጣው። ላብ በላብ እሆናለሁ።

ይህ "የምልጃ መንፈስ" እንደ ሆነ ዐውቃለሁ። ከቀድሞም ጀምሮ፥ ዐልፎ ዐልፎ እንደዚህ ያደርገኛል። እንደዚህ በሚያደርገኝ ጊዜ ሁሉ፥ እጅግ ደስ ይለኛል። ለለሚያደከመኝ እና ፈጽሞ ለለምዝል ነው አንጂ ባያቋርጥ፥ ዝም ብሎ ቢቀጥል ነበር የምወደው። ሁሉ ነገር ቀርቶብኝ፥ ሥራዬ ይኸ ብቻ ቢሆን ነው የምመኘው። አሁንም ቢሆን፥ ከዚያ የሚበልጥ ሌላ ሥራ ያለ አይመስለኝም። ነገር ግን አይቀጥልም፤ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ያቆማል። ምንም ላደርገው አልችልም፤ ሊመጣም ሆነ ሊሄድ በራሱ ፈቃድ ነው። አንዳንድ ጊዜ ቶሎ ቶሎ ይመጣል። ለዓመታት ቆይቶ የመጣበት ጊዜም እለ። ሲቆይብኝ እንዴት እንደምናፍቀው፥ ሲመጣልኝ ደግሞ ነፍሴ እንዴት ሐሴት እንደምታደርግ ለመግለጽ አልችልም።

የዚያን ቀኑ ግን ከዚያ በፊት ከማውቀው ሁሉ ፈጽሞ የተለየ ነው። የምጡ ጣር፥ የነፍሴ ሐሴት እና የጊዜው እርዝመት ሁሉ ከዚያ በፊት ከማውቃቸው የተለዩ ነበሩ። እየቃተትኩ እያለሁም፥ በውስጤ "ደግሞ ምን ሊመጣ ይሆን?" የሚል ጥያቄ ይመላለሳል - በእኔ፥ ወይም በቤተ ክርስቲያን፥ ወይም በአገር ላይ። ይህ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ መቃተት እንዲያው ዝም ብሎ ሊሆን አይችልም። "... መንፈስ ቅዱስ በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል" ተብሎ ስለ ተጻፈ ማለት ነው (ሮሜ 8፥26)። በዚያን ዕለቱ ዕምቃምነቱ (INTENSITY) ልክ ባይሆንም፥ የምልጃው መንፈስ ከእንድ ወር ተኩል በላይ ለሚሆን ያህል ጊዜ ያለ ማቋረጥ እብሮኝ ቆይቷል።

ከተንበረከክሁበት ለነሣ፥ ወዲያው ለልኬ ጮኽ። የደወለው የቤተ ክርስቲያና ችን ዋና ጸሐፊ ወንድም መላኩ ወልደ ሰንበት ነው።

"የት ነው ያለኽው?" አለኝ።

"እቤት ነኝ"

"ልትመጣ ትችላለህ?"

"እዎን፥ እችላለሁ፤ ምነው? ደህና አይደለንም?"

"ዛሬ በ9:00 ለዓት ፓስተር መርዕድ ፍትሕ ሚኒስትሩ ቢሮ ተጠርቷል ... ብቻውን ነው የተጠራው ... እንድትመጣ እና እንድንመካከር ብዬ ነው የደወልኩልህ"

"እሺ፥ መጣሁ።" መተጣጠቡን እና መስባበሱን በጥድፊያ አደረግሁ እና በ6:00 ለዓት ወንድም መላኩ ቢሮ ደረስኩ። ከአርሱ ጋር ትንሽ ከተነጋገርን በኋላ፥ ወደ ፓስተር መርዕድ ቢሮ ሄድኩ። ቀድመውኝ ይሆን ወይም ቀድሜአቸው እላስታውስም፥ ሌሎች ሰዎችም የመጡ ይመለለኛል። "እይዘህ" ካልነው እና እብረነውም ከጸለይን በኋላ እኔ ወደ ቢሮዬ ሄድኩ። ወደ 8:00 ለዓት ላይ ወንድም መላኩ እንደ ገና ደወለልኝ። የእስተዳደር ቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ፓስተር አበራ በላይ፥ ወንድም መላኩ እራሱ እና እኔ እብረነው እንድንሄድ፥ ከተፈቀደልን ልንገባ፥ ካልተፈቀደልንም እንዲያው በቅርቡ እንድንሆን መባሉን ነገረኝ እና፥ "በል ቶሎ ና" እለኝ። ቢሮቻቸን "እፍ እና እፍንጫ" ስለ ሆኑ፥ ወዲያው ተነሥቼ ሄድኩ።

አራታችንም በጸሐፊእቸው ቢሮ ተቀምጠን እየተጠባበቅን እያለን፥ ከቡር ሚኒስትሩ እና ክብርት ሚኒስትር ደኤታዋ ስብሰባውን ወደምናደርግበት ከፍል ገቡ። ፓስተር መርዕድ ብቻውን ተከትሏቸው ገባ እና እብረነው ያለነው ሰዎች በስብሰባው ላይ መገኘት እንችል እንደ ሆነ ጠየቀ። ከዚያ ብቅ አለ እና መግባት እንደምንችል ነገረን። እስጥ አገባውን ቀንሼለት፥ ከቡር ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ እና በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል መካከል ስላለው እስልቺ ውዝግብ መሥሪያ ቤታቸው የደረሰበትን ውሳኔ በእጭሩ ነገሩን።

የኢትዮጵያ እና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌሎች እያንዳንዳቸው ሕገ ደምብ የሚያ ረቅቁ እምስት እምስት ሰዎች (ውሳኔው በጽሑፍ ሲደርሰን የኢትዮጵያዎቹ ድርሻ ወደ ለባት ከፍ ብሏል) ይመርጡ እና በዐሥራ እምስት ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት ስማቸውን ያስታውቃሉ። የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት ቢጋር (TERMS OF REFERENCE) እዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል። ሰብሳቢ ይመድብላቸዋል። ስብሰባው እንዴት እየተካሄደ እንዳለም በቅርብ የሚከታተል ለው ያደርጋል። ይህ እንዳለቀ ከኢትዮጵያ 166፥ ከአዲስ አበባ ደግሞ 134 ለዎች ያሉበትን ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራ እና ሕገ ደምቡን ያስጸድቃል። በጸደቀው ሕገ ደምብ መሠረትም አዲስ ምርጫ ይደረጋል። ከቡር ሚኒስትሩ ይህንን ካስረዱን በኋላ፥ ምላሻችንን ጠየቁ።

ፓስተር መርዕድ ምላሽ ሰጠ - "ጉባዔያችንን ጠርተን የተነገረንን ውሳኔ እናስረዳለን። ከዚያም ጉባዔው የሚለንን እናስታውቅዎታለን።" ፓስተር አበራ እና እኔ ተያየን። በእኔ ውስጥ የመጣው አሳብ "ይህንን ዕድል አፈፍ

ብናደርገው እይሻለንም ወይ?" የሚል ነው። ፓስተር አበራ ግን ያለበውን ወዲያው ተናገረ - "እኛ ቀድሞም ቢሆን ስንለው የነበረው ያጣላን ደንብ ስለ ሆነ፥ ደንብ አብረን እናርቅቅ እና ከዚያ በኋላ በዚያ ደንብ መሠረት እንዋሐድ ነው። ይህንን አሳባችንን ለዚህ መሥሪያ ቤትም በጽሑፍ ጭምር አሳውቀናል። አሁን ከቡርነትዎ የነገሩን ውሳኔ ይህንን ጥያቄአችንን የሚመልስ ነው። ለለዚህም አንቀበለዋለን። ውሳኔውን ለእኛ ጉባዔ ማስረዳት እና ማሳመን ያስቸግረናል ብዬ እላስብም። ከእኛ በኩል የሚፈለጉትን አምስት ሰዎች መርጠን በተሰጠን ጊዜ ውስጥ እናስታውቃለን" አለ።

በአንድ በኩል በእኔ ውስጥ የመጣውን አሳብ ጥሩ አድርጎ ለለ እስቀመጠው ደስ አለኝ። በሌላ በኩል ደግሞ በዚያ መድረክ ላይ በሰብሳቢአችን እና በምክትል ለብሳቢአችን መካከል የአሳብ ልዩነት በመታየቱ አዘንኩ። አሁን ከቡር ሚኒስትሩ ትንሽ መለስ አሉ። እኔ ደግሞ፥ "ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌሎች ይህንን ውሳኔ ተቀብለውታል ወይ?" ለል ጠየቅሁ። ከቡር ሚኒስትሩም ውሳኔው ለኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌሎች ገና እንዳልተነገራቸው፥ እንዲቀበሉት ማድረግ ግን የመሥሪያ ቤታቸው ኃላፊነት መሆኑን ነገሩን። የማንኛቸንን ጥያቄ ሲመልሱ እንደሆነ አሁን ትዝ አይለኝም፥ የጠቅላላ ጉባዔው ቁጥር 166 እና 134 የሆነበትንም ምክንያት አስረድተውናል - "ቁጥሩን ያገኘነው በእኛ ዘንድ ካሉት ከእናንተ ከአራሳችሁ ሰነዶች ላይ ነው" ነበር ያሉን።

የፍትሕ ሚኒስቴር ውሳኔ በጽሑፍ የደረሰን ኅዳር 10 ቀን ነው - ከእንድ ወር ከእንድ ቀን በኋላ። ለምን እንደዚህ እንደ ዘገየ እናውቅም። ምናልባት በኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል በኩል ያሉት ወገኖች ውሳኔውን እንደ እኛ በደስታ እልተቀበሉላቸውም ይሆናል። የፍትሕ ሚኒስቴርን በፍርድ ቤት እስከ መክሰስ ድረስ እንደ ደረሱ በኋላ ላይ ለመረዳት ችለናል። በጽሑፍ በደረሰን ውሳኔ መሠረት፥ የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቢት ከኅዳር 09 ጀምሮ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌልን ሥራ እስኪያጅ ኮሚቴ እና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌልን የሥራ አመራር ቦርድ ከሥራ እግዷቸዋል። የሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባዔ፥ ማለትም ከእነርሱ 166 ከእኛ ደግሞ 134 ለዎች፥ ለኅዳር 21 እና 22 ጠርቷል። ጠቅላላ ጉባዔው የሚወስነው ውሳኔ በሁለቱም ወገኖች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

ይህንን ውሳኔ፥ ፈረንጆቹ እንደሚሉት፥ "BITTER SWEET" (መራራ ጣፋጭ) ሆኖ ነው ያገኘነው። ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌሎች ጋር አብረን ተቀምጠን ደንብ ማርቀቅ መቻላችን፥ ስንጠይቀው የነበረ ነገር በመሆኑ፥ ጣፋጩ ነገር ነው። ይህንን ግን የቤተ ክርስቲያንን አሠራር በማያውቁ፥ መንግሥት በሚወክልልን ሰዎች አማካይነት አንድናደርገው መገደዳችን መራራው ነገር ነው። የፖለቲካ ለው በሚጠራው እና በሚመራው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ስለ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ለመነጋገር እና መሪዎችን ለመምረጥ መገደዳችን እጅግ መራራ ነገር ነው። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለዘለቄታው እጅግ ከፉ ነገሮችን ሊያስከትሱ ሰሚችሉ ከሥተቶች፥ አብነት (PRECEDENCE) እናኖራለን። እና በጣም ተጨነቅን። የሐሙስ ኅዳር 12 ቀን ማስታወሻዬ እንደዚህ ይላል -

> መቼም ይህንን የመንፈስ ቅዱስ መቃተት በጣም ወድጄዋሰሁ። ለእርሱ ባለመመቸቴ፥ ማለትም የሚፈልገውን ያህል ጊዜ ባለመስጠቴ ብቻ ነው የማዝነው። ዛሬ ጸለይኩ። ጸለይኩ ማለት ያለብኝ አይመስለኝም። መንፈስ ቅዱስ ግን ቃተተ። በጣም ቃተተ። በእእምሮ የጸለይኩት ነገር ቢኖር፥ 'ጌታ ሆይ! ጣልቃ ግባ!' የሚል ብቻ ነው - ለ2ፐ እና ለ22 ኅዳር የተቀጠረው የጠቅላላ ጉባዔ ለብሰባ እንዲሰረዝ ማለት ነው።
>
> ታዲያ ጠዋት 4፡10 ገደማ ላይ ወይዘሮ ተናኘ ለማ ደወለች። 'እሁን እቶ ሽፈራው ወልደ ሚካኤል ደወለልኝ ... በጣም እዝነናል ... ደንግጠናል ... እንዴት እንደዚህ ይሆናል? ... እቶ መላቱ በላቸው፥ ቄስ ዓለሙ እና እኔ ወደ ሚኒስትሩ መሄድ እንፈልጋለን ... ነገሩን ለእኛ እንዲተውልን መጠየቅ እንፈልጋለን ... ግን አዲስ አበባ ሙሉ ወንጌሎች በኋላ ያነጋግሩናል ወይ? ብሎ ጠየቀኝ። ምን ልበለው?' አለችኝ።
>
> በእኔ በኩል ችግር አንደ ሌለ፥ ነገር ግን ፓስተር መርዕድን እና አቶ መላኩን እንድታነጋግር ነገርኳት። ወንድማገኝን እንዳነጋገረችው ነግራኛሰች። እርሱም እሺ ብሏታል። በኋላ ደውላ እንደ ነገረችኝ፥ ፓስተር መርዕድም እሺ ብሏታል። እቶ መላኩን ገና አላገኘችውም። እንደገና የጸሎቱ ሸክም መጣብኝ። መኝታ ቤቴ ገብቼ ጮኽኩ። አሁን ትንሽ ፋታ አግኝቼ ነው ይህንን የምጽፈው። ጌታን አመሰግነዋሰሁ። እንዲያውም አንድ ነገር ለመንፈስ ቅዱስ ቃል ገባሁ። መቼም፥ የትም

ቦታ ቢሆን በእኔ ለመቃተት ከፈለገ አሺ እንደምለው፥ ማንም ባለበት ቢሆን ይቅርታ ጠይቄ ለመጮኽ፥ በልሳን ለመጸለይ፥ ቃል ገባሁ:: ጌታ ሆይ! ተመስገን:: ከብር ሁሉ ለአንተ ይሁን"

ሕገ ደንብ የማሰረቀቁን እና የማስጸደቁን ሂደት እንዲመራ ኃላፊነቱ ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ተሰጥቷል:: ኃላፊነቱ ለጎብረቱ የተሰጠውም በጎብረቱ በእራሱ ጥያቄ ነው:: ጎብረቱ የፍትሕ ሚኒስቴርን ውሳኔ ሲሰማ፥ ጉዳዩ ለእርሱ እንዲሰጠው መንግሥትን ጠየቀ:: መንግሥትም እንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎችን ካስቀመጠ በኋላ ፈቀደለት:: ከቅድመ ሁኔታዎቹ ውስጥ፥ የኢትዮጵያ እና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አብያተ ክርስቲያናት ጎብረቱ ጣልቃ ለመግባት መንግሥትን ፈቃድ መጠየቁ በጽሑፍ እንዲገለ ጽላቸው፤ እነርሱም ፈቃደኛነታቸውን በጽሑፍ እንዲያረጋግጡ እና ይህንኑም ለሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት በግልባጭ እንዲያስታውቁ የሚሉ ይገኛሉ::

ይኸኛው የዕርቅ ሂደት እንዳይጨናገፍ የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት የተለየ ጥንቃቄ እያደረገ እንዳለ ግልጽ ነበር:: ለምሳሌ የመተዳደሪያ ደንቡን በማርቀቁ ሂደት ውስጥ ከሁለቱ ሙሉ ወንጌሎች ብቻ ሳይሆን፥ ከጎብረቱም ጽሕፈት ቤት የሚወከሉት ሰዎች ስም ዝርዝር ጭምር እንዲሰጠው እና የዕርቁም ሂደት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ አዝዟል:: ከሥስቱ ተቋማት ለተወ ከልነው 15 ሰዎች ለእያንዳንዳችን በጽሑፍ ዕውቅና ሰጥቷል (አባሪ ሦስትን ይመልከቱ)::

"ኖርማላይዜሽን ኮሚቴ"

በእኛ በኩል ሕገ ደንቡን የሚያረቅቁትን አምስት ሰዎች የመረጥነው ማክሰኞ ጥቅምት 12 ቀን ባደረግነው ስብሰባ ላይ ነው:: ከቡር ሚኒስትሩ አቢሮአቸው ጠርተውን ውሳኔአቸውን በቃል ከነገሩን ከአንድ የሥራ ቀን በኋላ ብቻ ማለት ነው:: ምርጫው የተደረገውም የሥራ አመራር ቦርዱ፥ የቀድሞው አመቻች ኮሚቴ እና የአገር አቀፉ ጎብረት የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ባደረጉት የጋራ ስብሰባ ላይ ነው:: ከተመረጥነው አምስት ሰዎች መካከል፥ ወንድም አገኘሁ መርሻ የቀድሞው አመቻች ኮሚቴ እና የአሁኑ የሥራ አመራር ቦርድ አባል ነው:: ከበደ ሉሌ ደግሞ የሥራ አመራር ቦርዱ ጸሐፊ ነው:: ከተማ ባዩ እና ሸለመ ቴሬሳ የቀድሞው አመቻች ኮሚቴ አባላት የነበሩ ሲሆኑ፥ እኔ ደግሞ

ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል የተገነጠሉትን ከ140 በላይ አጥቢያዎች የሚያስተባብረው የአገር አቀፉ ጎብረት ምክትል ሰብሳቢ ነኝ:: ምርጫው ለጠቅላላው ጉባዔ ቀርቦ ጸድቋል:: እጅ ተጭኖም ተጸልዮልናል::

በዚህች መጽሐፍ ውስጥ በአባሪነት ከተካተቱት ሰነዶች መመልከት እንደ ሚቻለው፥ ለዚህ ጉዳይ ከሦስቱ የአምነት ተቋማት የተወከልነው 15 ሰዎች እንታወቅ የነበረው በተለያዩ ስያሜዎች ነው:: እኛ ግን አራሳችንን የምንጠራው አብዛኛውን ጊዜ "ኖርማላይዜሽን ኮሚቴ" በሚለው ስያሜአችን ነበር:: "ኖርማላይዜሽን" ማለት፥ በመካከላችን አለመግባባት ከመፈጠሩ በፊት፥ ቀደም ሲል ወደ ነበርንበት ሰላማዊ ሁኔታ፥ መመለስ ማለት ነው:: ተልዕኳችን የሚመነጨው ከዚህ ስያሜአችን ነው::

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት የመጀመሪያው ተግባሩ ያደረገው ያዘጋጀውን ቢጋር ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲያዩት እና አሳባቸውን እንዲሰጡበት መጠየቅ ነበር:: የሁለቱን አሳቦች ካካተተ በኋላ ሁለቱ ተቋማት የተሰማሙበትን የመጨረሻውን ቢጋር (አባሪ አራትን ይመልከቱ)፥ ለሁለታችንም ላከልን:: በዚያ ቢጋር መሠረት የኖርማላይዜሽን ኮሚቴው የመጀመሪያ ሥራ የአዲሱን መተዳደሪያ ደንብ ይዘት የሚወስኑትን መርሖች ማዘጋጀት ነው:: መርሖቹ ከተዘጋጁ እና ኖርማላይዜሽን ኮሚቴው ከተሰማማባቸው በኋላ፥ "የ15፡11፡10 ጉባዔ" ተጠርቶ ይነጋገርባቸው እና ያጸድቃቸዋል::

"የ15፡11፡10 ጉባዔ" ማለት፥ ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል 15 ሰዎች፥ ከአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል 11 ሰዎች እና ከኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት 10 ሰዎች የተወከሉበት ጉባዔ ማለት ነው:: በኢትዮጵያ እና በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌሎች በኩል፥ ይህ ቁጥር የኖርማላይዜሽን ኮሚቴ አባላቱን አይጨምርም:: "የ15፡11፡10 ጉባዔ" መርሖቹን ካጸደቀ በኋላ፥ የመተዳደሪያ ደንቡን የማዘጋጀቱ ሂደት ይቀጥላል:: እሱ ሂደት ሲያልቅ፥ "የ15፡11፡10 ጉባዔ" ለሁለተኛ ጊዜ ይጠራ እና በተዘጋጀው ደንብ ላይ በዝርዝር ተነጋግሮ ያጸድ ቃል:: ይህም እንደ ተጠናቀቀ፥ ከኢትዮጵያ 166፥ ከአዲስ አበባ ደግሞ 134 ሰዎች ያሉበት ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራ እና በተረቀቀው ደንብ ላይ እንደ ገና ተነጋግሮ ለመጨረሻ ጊዜ ያጸድቀዋል::

ደንቡ በሦስት የተለያዩ አርከኖች ከታየና ሰምምነት ከተደረሰበት በኋላ ነው የሚጸድቀው ማለት ነው። የቅዳሜ ጎዳር 21 ቀን ማስታወሻዬ እንደዚህ ትላለች፡-

> የመንፈስ ቅዱስ መቃተት ቀጥሏል። በውስጤ በጣም ደስተኛ ነኝ። በውጭ ያለውም ነውጥ እንደ ቀጠለ ነው። እየሰፋም በመሄድ ላይ ያለ ይመሰለኛል። ጉዳያችንን የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎበረት ከፍትሕ ሚኒስቴር እጅ ተረከቧል። የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌልም አዲስ መተዳደሪያ ደንብ በመረቀቁ ተስማምታለች። ስምኑን በጎበረቱ በኢትዮጵያ እና በእኛ መካከል ብዙ መጻጻፍ ነበረ። ከኢትዮጵያ 7ቱ ከእኛ 5 እና ከጎበረቱ 3፣ በድምሩ 15 ሰዎች ደንቡን አንድናረቅቅ ተመርጠናል።
>
> ነገ የመጀመሪያውን የጸሎት ሰብሰባ እናደርጋለን ተብሏል። ቤተ ክርስቲያኗን ለማዳን፣ ወደሚቀጥለውም ምዕራፍ በሰላም ለመሸጋገር ይህ ብቸኛው መንገድ ይመስለኛል። እግዚአብሔር እንዲያሳካው አጸልያለሁ። ሆኖም ፍርሃት አለኝ። ሥጋት አለኝ። ምናልባት ላይሳካ ይሆን? ዕንቅፋት ያጋጥመው ይሆን? ወደ አልተጠበቀ አቅጣጫ የሚወሰደን የሆነ የሆነ ችግር ከሆነ ከሆነ ቦታ ይነሣ ይሆን? እያልኩ አስባለሁ

በእኛ በኩል፣ ከሥራ አመራር ቦርዳችን ጋር በየጊዜው እየተገናኘን የደረስንበትን ሁኔታ በዝርዝር ሪፖርት እናደርጋለን። አሳባቸውን እንሰማለን፣ ምክራቸውን እና መመሪያቸውንም እንቀበላለን። ለምሳሌ የተዘጋጀውን የመርሖች ረቂቅ በቅድሚያ ሰጥተናቸው እና ተነጋግረውበት ነበር ወደ ጉባዔው የመጡት። በዚያ ጉባዔ ላይ በጣም አከራካሪ ከነበሩት ነጥቦች መካከል ለእኛ ዋነኛው፣ "የቤተ ክርስቲያኗ መሠረታዊ አካላት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው" የሚለው ነበር።

የእኛ አቋም "አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እና ጸሎት ቤቶች ናቸው" ይባል የሚል ነበረ። "የቤተ ክርስቲያኗ መሠረታዊ አካላት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው" የሚለው መርሕ በዕለቱ በሙሉ ድምፅ የጸደቀ ቢሆንም እንኳን፣ ደንቡ በሚረቀቅበት ጊዜ ግን ኖርማላይዜሽን ኮሚቴው "የቤተ ክርስቲያኗ መሠረታዊ አካላት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እና ጸሎት ቤቶች ናቸው

የሚለውን የአዲሰ አበባን አቋም በጥልቀት እንደሚነጋገርበት ቃሉን ከሰጠ በኋላ ነበር።

የመጀመሪያው "የ15፡11፡10 ጉባዔ" በሠላም ተጠናቅቋል። በአመራር፣ በእስተዳደር እና በአደረጃጀት ሥር ያስቀመጥናቸው በድምሩ 19 የሚሆኑ መርሖችም ጸድቀዋል። ደንብ ወደ ማርቀቁ ሂደት ተሸጋገርን ማለት ነው። እኛ የኢትዮጵያውን መተዳደሪያ ደንብ እንዳለ ወሰድን እና እንዳንዶቹን አናቅጽ ብቻ እኛ በምንፈልገው ዐይነት እንደ ገና በቀይ ቀለም ጻፍናቸው። እንደዚያ ያደረግነው በኋላ ላይ ሁለቱን የማጣጣሙን ሂደት ያቀልልናል ብለን ስላሰብን ነው። በዚህ ዐይነት ያዘጋጀነውን ደንብ ረቂቅ በቅድሚያ ለራሳችን የሥራ አመራር ቦርድ አቀረብን። ቦርዱ ረቂቁን በዝርዝር ከተመለከተ እና የሚለውን ካለበት በኋላ ለወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎበረት አሰረከብን። እነርሱም የሁለታችንንም ረቂቆች ማየት፣ ከተስማማንባቸው መርሖች እና ከእርሰ በራሳቸውም ጋር ያላቸውን መጣረሶች ለቅመው ማውጣት ጀመሩ። እኛም ይህንኑ እንድናደርግ የእንዳችንን ረቂቅ ለሌላችን ሰጡን።

የሚቀጥሉት ሁለት እና ሦስት ስብሰባዎቻችን ይህንን በጋራ በማድረግ የተጠመድንባቸው ነበሩ። የጸሎት ቤት አሠራራችንን እና ያሰገኘልንንም ጥቅሞች በተመለከተ፣ ከሥራ አመራር ቦርዳችን ጋር ሰፊ ውይይት አደረግን። በኖርማላይዜሽን ኮሚቴው ሰብሰባ ላይም እንዲሁ ሰፊ ገለጻ አደረግን። በተለይ ይህንን ጉዳይ የሚመለከተውን ገለጻ የማድረጉ ኃላፊነት የተሰጠው ለእኔ ነበር። አብረውኝ ከነበሩት አራት ወንድሞችም ሆነ ወይም ከሥራ አመራር ቦርድ አባላት መካከል አቋማችንን በደንብ አላስረዳህልንም ብሎ የከሰሰኝ አንድም ሰው የለም። "የጸሎት ቤት" ጉዳያችንን ያቀረብንበት፣ የቅዳሜ ጥር 10 ቀን ማስታወ ሻዬ እንዲህ ትነበባለች -

> ዓርብ ጥር 02 ቀን በተገናኘንን ጊዜ ሁሉታችን ወገኖች በሠራናቸው ደንቦች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ሽማግሌዎቻችን አውጥተው፣ ጎን ለጎን በጽሑፍ አስቀምጠው ሰጡን። ጥሩ ሥራ ሠርተዋል። የቀሩ ልዩነቶቻች ንንም ጨምረን ሰጥተናቸው፣ በልዩነቶቹ ላይ ለመነጋገር ለዛሬ ሙሉ ቀን ተቃጥረን፣ ተለያየን። በእኛ በኩል ዘወትር እንደምናደርገው በሚቀጥለው ሰኞ ማለትም ጥር 05 ቀን የሆነውን ነገር ለቦርድ አስታወቅን። ምክራቸውንም ሰማን። ዛሬ በቀጠሮአችን መሠረት ተገናኘን።

የተገናኘነው በ"ተገን የእንግዶች ማረፊያ" ነው። ከኢያሱ በስተቀር ሁላችንም ነበርን። በልዩነቶቻችን ላይ በሰፊው ተነጋገርን።

ዛሬ የፍትሕ ሚኒስቴሩ የማኅበራት ምዝገባ ጽ/ቤት ኃላፊ፥ ወንድም ጅማ ዲልቦ፥ አብረውን ውሰዋል። በንግግራችን ወቅት ብዙ እዎንታዊ አስተዋጽዖችን አድርገዋል። መኖራቸው በጣም ነው የጠቀመን። በአንዳንድ ልዩነቶቻችን ላይ ወዲያው ተስማምተን እና ውሳኔ አድርገን ወልፈናል። አንዳንዶቹ ላይ ግን በቂ አሳብ በሁለቱም በኩል ከተሰጠባቸው በኋላ ሽማግሎቹ የራሳቸውን አሳብ ይዘውልን ሊመጡ ወስደዋቸዋል። በድምሩ 34 የሚሆኑ ልዩነቶች ነበሩ። አብዛኞቹን ጨረስናቸው። ሰባት ወይም ስምንት የሚሆኑትን ሽማግሎቹ ወሰዷቸው። ልቤ ዐርፏል። ያረፈው እኛ ያልነው ሁሉ ይሆንልናል ብዬ ሳይሆን፥ ማስት ያለብንን ሁሉ ማስት ስለ ቻልን ነው። ጌታ ሆይ! ተመስገን። ክብር ለእንተ ይሁን፤ አሜን

ልዩነቶችን የማጥበቡ ሥራ ቀጥሎ፥ በመጨረሻ እንድ ልዩነት ላይ ብቻ ተቸከልን ማለት ይቻላል። ይኸውም በኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል በኩል "አጥቢያ" እና በእኛ በኩል ደግሞ "ጸሎት ቤት" በመባል የሚታወቀው "ታሪካዊው ልዩነት" ነው። "ታሪካዊው ልዩነት" ያልኩት ልዩነቱ፥ በ"ኢትዮጵያ" እና በ"አዲስ አበባ" ሙሉ ወንጌሎች መካከል ብቻ ሳይሆን፥ በእኛ በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌሎችም መካከል የነበረ ልዩነት በመሆኑ ነው።

ለምሳሌ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል የመሪዎች ስብስብ፥ ሰድስት ገደማ ጸሎት ቤቶችን፥ አጥቢያ ለማድረግ የወሰነበት ጊዜ ነበር። ውሳኔውንም በጥቅምት ወር 1986 ዓ.ም. አንድ ከሰዓት በኋላ፥ አገልጋዮችን በጉለሌው ጸሎት ቤት ሰብስቦ አስታወቀን። ሆኖም ከመሪዎቹ ስብስብ መካከል የነበሩት ሁለት የሙሉ ጊዜ መሪዎች በጉዳዩ እንዳላመኑበት ሁኔታቸው ያስታውቅ ነበር። አሳብ አይለጡም፤ ጥያቄ አይመልሱም፤ እንዲያው ዝም ብለው እና ግንባራቸውን ከስከሰው ተቀምጠዋል።

ስብሰባው አልቆ ከአዳራሹ ለንወጣም፥ አንዳንድ ወንጌላውያን "በአንድ ከተማ ውስጥ እንዴት ሰባት አጥቢያ ይኖራል? አንድ ሆነን የኖርነውን ሰዎች ለምን እንደዚህ ይከፋፍሉናል?" ሲሉ ተደምጠዋል። ኡ! ኡ! ብለው የፅኹ እና መሬት ላይ ወድቀው እስከ መንከባለል የደረሱም ነበሩ። በኋላ እንደሰማነ

ውም፥ ሁለቱ የሙሉ ጊዜ መሪዎች ወንጌላውያኑን እና ዲያቆናቱን ለብቻቸው ሰብሰበው፥ ጸሎት ቤቶችን አጥቢያ ለማድረግ አሁን ጊዜው አይደለም አሏቸው። እና የጋራ የነበረውን ውሳኔአቸውን እሁን በግላቸው አመከኑት።

ዕሑድ ጥር 25 ቀን ስኖርማላይዜሽን ኮሚቴው የሞቱ ወይም የሸረቱ ቀን ነበር ለማለት ይቻላል። ሁል ጊዜም ባይሆን፥ የኖርማላይዜሽን ኮሚቴው ሰብሰባዎች እጅግ ከባድ የነበሩባቸው ጊዜያት ነበሩ። "ዱላ ቀረሽ" ከርከሮች አድርገን፥ ተጣልተን እና ተኳርፈን፥ እጅ ለእጅ ላንጨባበጥ ወይም "ደህና እደሩ" ሳንባባል የተለያየንባቸው ምሽቶች ነበሩ። የዛሬው ግን የከርከር እና የጥል ሳይሆን፥ የሞት እና የሸረት ነበር። እንደዚህ የሆነውም፥ "በታሪካዊው ልዩነታችን" ላይ አንድ ነገር የሚባልበት ቀን ስለ ሆነ ነው።

ያን ዕለት የተጨዋጨዋሀን አይመስለኝም። ያን ዕለት በዝግታ እና በእርጋታ እንደ ተነጋገርን ነው ትዝ የሚለኝ። ሁለታችንም ወገኖች የምንለውን ሁሉ ካልን እና ከጨረስን በኋላ፥ በዚያ ወገን ያሉት ወንድሞች "የምንችለውን ሁሉ አድርገናል ... ከዚህ ለማለፍ ግን እንችልም ... እንግዲህ እዚህ ላይ ቢበቃን ይሻላል ... ያው እናጣችኋለን ... እናንተም ታጡናላችሁ ... እግዚአብሔር የወደደውን ያድርግ ከማለት በስተቀር፥ እንግዲህ ምን ይደረጋል?" አሉ።

በጣም አስጨናቂ ጊዜ ነበር። ለምን ያህል ጊዜ እንደ ሆነ አላውቅም፤ ሰብሳቢ ውንና ሽማግሎቹን ጨምሮ፥ ሁላችንም ዝም አልን። ከሆነ ያህል የዝምታ ጊዜ በኋላ፥ "አሰቲ እንድ ሌላ ዕድል ለእራሳችን እንስጥ ... ሌሎች አማራጮችን እናስብ እና በሌላ ቀን ደግሞ እንገናኝ" አልኩ።

"ምን ዋጋ አለው? እስከ አሁን የደከምነው ይበቃናል" አለ ከዚያ በኩል አንድ ሰው። ቀጥሎም አንድ ... ሁለት ... ሦስት ሌሎች ለዎች ተናገሩ - ከዚህም ከዚያም በኩል። አሰቡን በመቃወምም፥ በመደገፍም።

ለብሳቢው ጭልጥ ብለው ከሄዱበት ተመለሱ። ምን እያስቡ ነበር ይሆን? "እምላኬ ሆይ ... ጎብረቱን እዚህ ውስጥ ይዤው እንድገባ ለምን ፈቀድከ? ... ምንድን ነው እሱ የኢትዮጵያን አብያተ ክርስቲያናት የተጠናወታቸው ነገር? ... ቀደም ሲል እነ ... እንደዚያ፤ አሁን ደግሞ እነዚህ እንደዚህ ... ይህንን ጉድ ለፍትሕ ሚኒስትሩ ምን ብዬ ነው ሪፖርት የማደርገው? ... የሚኒስቴሩ

መሥሪያ ቤት ከእንግዲህ ወዲህ ምን እርምጃ ይወሰድ ይሆን? ... ይኸ ነገር PLAN B የለውም? ... ወዘተ ... ወዘተ ..."

ከሄዱበት ሲመለሱ ግን፥ "ደግ፥ እሺ ... እስቲ ሁላችንም አማራጮች አለበን አንምጣ ... መቼ እንገናኝ?" አሉ። ለረቡዕ ጥር 28 ቀን ተቃጥረን ተለያየን። ግቢውን ከመልቀቃችን በፊት ግን፥ እኛ እምስታችን በማግሥቱ እኔ ቢሮ ይሁን ወይም መጋቢ አበራ በላይ ቢሮ ትዝ አይለኝም፥ ልንገናኝ ተቃጥረን ተለያየን።

ለመታረቅም ምክንያት ለሚሹ

የሰኞው ስብሰባ ለእኛ ለአምሊታችን ወሳኙ ስብሰባ ነበረ። "በአጥቢያ" እና "በጸሎት ቤት" ጉዳይ ላይ አንዳችን የሌላችንን አቋም ስለማናውቅ፥ ከዚያን ቀን በፊት እንደዚህ በግልጽነት እልተነጋገርንም። አሁን ግን ሁላችንም በግልጽ መናገር ነበረብን። በግልጽ ብቻም አይደሰም፥ የመጨረሻ ንግግር መናገርም ነበረብን። እስከሚበቃን ድረለም መናገር ነበረብን። ይህችን መጽሐፍ ሳዘጋጅ፥ በዚያ ስብሰባ ላይ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የተባባልናቸውን እና ወደ አንድ ውሳኔ ለመድረስ የረዱንን አሳቦች በሥርዓት ለማለቀመጥ ሙከራ አድር ጌአለሁ። የሚከተለውን ነው የሚመስሉት -

1. ይኸ የተማከለ አሠራራችን፥ "ከእያንዳንዱ እንደ ገቢው፥ ለእያንዳንዱ ደግሞ እንደ ፍላጎቱ" የሆነ የበጀት አመዳደባችን፥ የአገልጋዮች አሹዋሹዋም፥ የማሕተሞች በዞኖች አጅ መሆን፥ የነገሮች ሁሉ አንድ ቦታ መታቆር እና በቶሎ ውሳኔ ማግኘት አለመቻል፥ ወዘተርፈ፥ ያልተመቻቸው ጸሎት ቤቶች ሞልተዋል። የጸሎት ቤቶቻችን ቁጥር ትንሽ በነበረ ጊዜ፥ ይህ አሠራራችን ጠቅሞን ሊሆን ይችላል። አሁን ግን ቁጥራችን አጅግ ስለ በዛ፥ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን እየሆነ እየመጣ ነው። ነገ የአንዳንዶቹ ጸሎት ቤቶች መሪዎች እና አገልጋዮች ገቢአቸውን ወደ ማዕከሉ ላለማስገባት ወይም ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል ለመሄድ ቢወስኑ፥ ምን እናደርጋቸዋለን?

2. ቤተ ክርስቲያናችን አሁን የመሰነካጠቅ አደጋ ኢጋጥሚታል። በወንድም ወርቁ ተከሌ የሚመራው ቡድን ከ1,500 በላይ የሚሆኑ አገልጋዮችን እና ምዕመናንን ፔቲሽን አስፈርሞ ፍትሕ ሚኒስቴር አስገብቷል። በወንድም ስምዖን ታቦር የሚመራ ሌላ ቡድን ደግሞ ተመሳሳይ ዓላማ ያለው፥ ነገር

ግን ሌላ ዐይነት እንቅስቃሴ መጀመሩን እናውቃለን። አገልጋዮችን እና ምዕመናንንም እየጠራ በየቦታው ስብሰባዎችን እያደረገ ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ምን እስከተሆን ድረለ ነው ዝም ብለን የምናየው?

(በኢትዮጵያ እና በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል መካከል በተፈጠረው ችግር ላይ ለመነጋገር እና የቤተ ክርስቲያናቸውን መሪዎች በሚያስፈልገው መንገድ ሁሉ ለመደገፍ የየአገልግሎት ዘርፎቹ እስተባባሪዎች እንቅስቃሴ ማድረግ የጀመሩት ከመስከረም ወር 1990 ዓ.ም. ጀምሮ ነው። እያንዳንዱን የአገልግሎት ዘርፍ የሚወክል አንድ አንድ ሰው በማድረግ፥ አራሳቸውን በኮሚቴ ደረጃ ያዋቀሩት ደግሞ ከሚያዝያ ወር 1990 ዓ.ም. ቤተ እምኑቱ የአጥቢያዋን ምዕመናን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተነገረ ማስታወቂያ ጠርቶ መሪዎቻቸውን ከሥልጣን ማውረዱን ባስታወቀ ጊዜ ነበር። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ችግሩን በግንባር ቀደምነት ሲመክት የነበረው ይህ "የአገልግሎት ዘርፎች አስተባባሪ ኮሚቴ" ነው።

አሁን ግን ከዚያ ኮሚቴ አባላት መካከል፥ ሁለቱ በወንድም ወርቁ ተከሌ እና በወንድም ስምዖን ታቦር ቡድኖች ውስጥ ገብተዋል። እነዚህም ሁለቱ የኮሚቴው ምክትል አስተባባሪ የነበረው ወንድም ስምዖን ታቦር እራሱ እና በጊዜው የወንጌላውያን ተወካይ - አሁን ግን መጋቢ - የሆነው ታደሰ ዐወቀ ናቸው። ከቤተ ክርስቲያኗ አመራር አካላት መካከልም መጋቢ ታደሰ ዐወቀን ጨምሮ፥ ሦስት መጋቢዎች - ፓስተር ግርማ በጋለ እና ፓስተር ተመስገን ብርሃኑ፥ ሁለት ሽማግሌዎች - ወንድም አክሊሉ በቀለ እና ወንድም ሰሎሞን ዓለም ሰገድ - ቡድኖቹን ተቀላቅለዋል)

3. ከአዲስ አበባ መለተዳድር የተሰጠን ፈቃድ አብቅቶለታል። ፍትሕ ሚኒስቴር ደግሞ ተመሳሳይ ስያሜ ላላቸው ሁለት ማኅበራት ሁለት ፈቃድ እንደማይሰጥ በጽሑፍ ጭምር አስታውቆናል። የሥራ አመራር ቦርዳችን ከታገደ ሁለት ወራት ዐልፈውታል። ከእንግዲህ ወዲህ ያሉን አማራጮች አንድም የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌልን መቀላቀል፥ አንድም ደግሞ በሌላ ስም ፈቃድ ማውጣት ብቻ ናቸው። በሌላ ስም ፈቃድ ብናወጣ፥ እንደኛ በሙሉ ወንጌል ስም ያለንን ንብረታችንን ሁሉ ለኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል እንድናስረክብ በሕግ እንገደዳለን። ሁለተኛም ቤተ ክርስቲያኑን የሚወ ደው አብዛኛው ምዕመን አይከተለንም።

4. ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌሎች ጋር ያጣላን "ደንብ" ነው፤ "ደንቡን አብረናችሁ ቢጋራ አናርቅቅ እና በዚያ ደንብ መሠረት እንዋሐድ" ብለናቸው፥ አነርሱ ግን "እምቢ" አሉን ብለን ለአገልጋዮቻችን እና ለምዕመናን፥ እናስታርቃችሁ ለሚሉን እና ለመንግሥት አካላትም ጭምር ሳይቀር ተናግረናል፡፡ ይኸው አሁን መንግሥት ደንብ አብረን እንድናረቅቅ ዕድሉን ሰጥቶናል፡፡ እንደዚያ ስንል የነበርነው ውሸታችንን ካልሆነ በስተቀር፥ አሁን የማንታረቅበት ምክንያት ምንድነው?

5. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንደ ሆነ ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ለጊዜው የሚጠቅመን ሆኖ ስላገኘነው የጸሎት ቤት አሠራርን ተከትለን ነበር፡፡ በዚያ አሠራር መቀጠል የማንችልበት አስገዳጅ ሁኔታ አሁን ተፈጥሯል፡፡ ያንን አሠራር እንድንከተል አግዚአብሔር የፈለገው ምናልባት እስከዚህ ጊዜ ድረስ ብቻ ይሆናል፥ ስለዚህ እና ለሰላምም ጭምር ስንል ወደ አዲስ ኪዳኑ ሞዴል ብንመለስ ምን ኃጢአት አለበት?

6. ይህች፥ እግዚአብሔር በምድራችን ላይ በዓላማ ያስነሣት ቤተ ክርስቲያን፥ በእኛ በመሪዎቿ አልኸኖነት ብትፈራርስ ትውልድና ታሪክ ምን ይሉናል?

7. ሰዎችን በወንጌል እንድንደርስበት አግዚአብሔር የሰጠንን፥ ይህንን ከዚህ በፊት በታሪካችን አይተነው የማናውቀውን ዐይነት መልካም ጊዜ፥ ፋይዳ በሌለው እንደዚህ ባለ የእርስ በርስ ጭቅጭቅ ማባከናችን በእግዚአብ ሔርስ ዘንድ አያስጠይቀንም ወይ?

በመጨረሻም፥ አምስታችንም የአጥቢያ አደረጃጀትን ልንቀበል እና ይህንንም በማግስቱ ለሥራ አመራር ቦርዱ ሪፖርት ልናደርግ ተስማማን፡፡ የሥራ አመራር ቦርዱም በተራው ብርቱ ክርክር አደረገበት፡፡ 12:30 ላይ የተጀመረ ስብሰባ እስከ ሌሊቱ 6:30 ድረስ አንደ ዘለቀ ነው ትዝ የሚለኝ፡፡ በመጨረሻም፥ "የአጥቢያን አደረጃጀት እንቀበላለን" የሚለውን አሳብ ቦርዱም በድምፅ ብልጫ አሳለፈው፡፡ በሚቀጥለው ሐሙስም ያንን ውሳኔውን ለጠቅላላ ጉባዔው አብረን ልናቀርብ እና የመጨረሻ ውሳኔ ልናሰጥበት ተስማምተን ተለያየን፡፡

በነገው የኖርማላይዜሽን ኮሚቴ ስብሰባ ላይ፥ እኛ "የአጥቢያ አደረጃጀትን እንቀበላለን" የሚለውን ቦርዱ በድምፅ ብልጫ ያሳለፈውን አማራጭ ይዘን እንድንቀርብ፥ ምናልባት ሐሙስ ዕለት የሚገናኘው ጠቅላላ ጉባዔ የቦርዱን

አማራጭ ያልተቀበለው እንደ ሆነ፥ ዓርብ ዕለት በሚኖረው የ"15:11:10 ጉባዔ" ላይ ቦርዱ አራሱ ደግሞ የጠቅላላ ጉባዔውን ውሳኔ ይዞ እንዲቀርብ ተቆረጠ፡፡

በረቡዑ የኖርማላይዜሽን ኮሚቴ ስብሰባ ላይ፥ ባለፈው ዕሑድ ውሳኔአችን መሠረት፥ አማራጭ አሳብ ይዞ የመጣ ከእኛ በስተቀር ሌላ ማንም አልነበረም፡፡ ሰብሳቢአችን ወንድም ወንድም አገኘሁ "የአጥቢያ አደረጃጀትን በመርሕ ደረጃ እንቀበላለን" በማለት የእኛን አማራጭ ለኖርማላይዜሽኑ ኮሚቴ ባስታወቀ ጊዜ፥ ከሁለቱ ተቋማት አብረውን የነበሩት ወንድሞች ተነፈሱ፡፡ እጅግ ደሰ አላቸው፤ አግዚአብሔርንም አመሰገኑ፡፡

እኛ እዚያ ስብሰባ ላይ ሆነን፥ በቦርዱ ውሳኔ ውሰጥ ያልተካተተ እና ተቃራኒ አጀንዳ ያለው፥ ሌላ ስብሰባ በቀጣና ሁለት ተደርጎ ነበር፡፡ በዚያ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ጥሪ የተደረገው ለዞኖች እና ለጸሎት ቤቶች ተጠሪዎች ነው፡፡ በስብሰባው ላይ የተንሸራሸረው ዋና አሳብም "እኛን እንዲወክሉ የመረጥናቸው የኖር ማላይዜሽን ኮሚቴ አባላት ከተሰጣቸው ሥልጣን (MANDATE) ውጭ ስለ ሄዱ በቶሎ ማስቆም አለብን፤ ይህንን ካላደረግን የቤተ ክርስቲያኗ ሕልውና አደጋ ላይ ይወድቃል" የሚል ነበረ፡፡

በ1986 ዓ.ም. አንዳንድ ጸሎት ቤቶችን አጥቢያ ለማድረግ የመሪዎቹ ስብሰብ ሲወስን አብረው ከወሰኑ በኋላ ዘወር ብለው ውሳኔውን ያመከኑት ሰዎች፥ አሁን ደግሞ የአጥቢያን አሠራር ለመቀበል ከቦርዱ ጋር አብረው የወሰኑትን ውሳኔ ለማምከን ግልጽ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመሩ ማለት ነው፡፡ የአጥቢያን አደረጃጀት አለመቀበላቸው በፍጹም አያስነቅፋቸውም፡፡ ላመኑበት የጸሎት ቤት አደረጃጀት በአደበባይ መሟገታቸውም ትከከል ነው፡፡ ያ መንፈሳዊም ሰብአዊም መብታቸው ነው፡፡ ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ ግን፥ በተለይም ደግሞ ውሳኔውን አብረው ከወሰኑ በኋላ፥ ዘወር ብለው ውሳኔውን ለማምከን በጎን ያደረጉት እንቅስቃሴ በፍጹም ትከከል አይደለም፡፡ እንደዚያ ዐይነቱ ድርጊት በክርስቲያናዊውም ሆነ በዓለማዊው ሥነ ምግባር ተቀባይነት የለውም፡፡

ሐሙስ ዕለት የቦርዱ ውሳኔ ለአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባዔ ቀረበ፡፡ ጠቅላላ ጉባዔውም የኖርማላይዜሽን ኮሚቴውን አሳብ እና የቦርዱን ውሳኔ በ01 የተቃውሞ፥ በ18 የተዓቅቦ እና በ111 የድጋፍ ድምፅ አጸናው፡፡ ዓርብ "የ15:11:10 ጉባዔ" የሚካሄድበት ዕለት ነበር፡፡

በኖርማላይዜሽኑ ኮሚቴ በተረቀቀው የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ለመነጋገር በተጠራው በዚያ ጉባዔ፥ ከእኛ በኩል የተገኙት ፲0 ሰዎች ብቻ ነበሩ። የቤተ ክርስቲያኗ ሰብሳቢ በዚያ ጉባዔ ላይ አልተገኘም።

ለዚያ ጉባዔ የእግዚአብሔርን ቃል ያካፈሉት ሰው መጋቢ ሙሴ ይባላሉ። ከኤርትራ እና ከቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እንደ ሆኑ ሲነገር ብቻ ነው የለማሁት። ያንንም በቅጡ ሰምቼ እንደ ሆነ እርግጠኛ አይደለሁም። እኚህን ሰው ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ፥ አይቻቸውም ሆነ ሰምቻቸው አላውቅም። የስብከታቸው ርእስ "አንድነት ኃይል ነው" የሚል ነበረ። በጣም ለአጭር ጊዜ ነው የሰበኩት። የሰበኩበትን ለሚሆን ያህል ጊዜም የጸለዩ መስሎኛል።

በጸሎታቸውም መካከል፥ ደስ የሚል እና የሚያስፈራ፥ መልእክት አምጥተዋል። ደስ የሚለው እግዚአብሔር ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ጋር ገና የሚሠራው ሥራ እንዳለው የተናገሩት ሲሆን፥ የሚያስፈራው ደግሞ ትዕቢተኞችን እንደሚያዋርድ የተናገሩት ነው። የተረቀቀው መተዳደሪያ ደንብ ጸድቆ ከአዳራሹ ስንወጣ፥ የእኔ ስሜት የተቀላቀለ፥ ማለትም - የደስታ እና የኀዘን - ነበረ። ያዘንኩት በስብሳቢው አለመኖር ነው። ሁለቱም ስሜቶች፥ እስከ ዛሬም ድረስ፥ አብረውኝ አሉ። የቀረው ታሪክ ነው - "THE REST IS HISTORY" - እንዲሉ (አባሪ 5፥ 6 እና 7ን ይመልከቱ)።

ከፍተቱስ ተዘጋ?

መጠየቅ እና መመለስ ('ጠ' እና ሁለተኛዋ 'መ' ይጠበቃሉ) ያለባቸው ጥያቄዎች ናቸው አሁን በእጃችን ላይ የቀሩት። ጥያቄዎቹን ለመጠየቅም ሆነ መልሳቸውን ለማወቅ ትከከለኛው ጊዜም አሁን ነው። ምከንያቱም የደፈረሰው ውሃ አሁን ጠርቷል። የሰዎች ስሜት ለከኗል። የኋሊት ማየት፥ ትርፍን እና ኪሣራንም ማስላት አሁን ይቻላል። ስለዚህ አኔ ጥያቄዎቹን ብቻ ልወርውር። ጉዳዩ የሚመለከተው አያንዳንዱ ሰው ጥያቄዎቹን በታማኝነት ለራሱ ይመልላቸው።

የደረለውን ችግር እንዳይደርስ ማድረግ አይቻልም ነበር ወይ? ማንኛችን፥ ምን ብናደርግ ኖሮ ነበር፥ የደረሰውን ችግር እንዳይደርስ ማድረግ ይቻል የነበረው? ችግሩ ከደረሰም በኋላ የፈጀውን ያህል ጊዜ ሳይፈጅ፥ የለፋውንም ያህል

ሳይለፋ እና ያደረሰውንም ያህል ጉዳት ሳያደርስ፥ ለመግታት እንችልም ነበር ወይ? ታዲያ ለምንድነው ልንገታው ያልቻልነው? ልንገታው ስላልፈለግን? መደማመጥ ስላልቻልን? ሁለታችንም ወገኖች "አልሸነፍም" ባዮች ወይም ዕልኸኞች ስለ ሆንን?

"በርታ! ጽና! እኔ ከአንተ ጋር ነኝ! ማንም አይቋቋምህም" በሚሉ ዐይነት የሐሰት ትንቢቶች፥ ራእዮች፥ ስብከቶች እና መዝሙሮች ምናልባት ተታልለን ይሆን? ከጥሉ እና ከከርከሩ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ የሆኑ ለዎች በሚለጡን አሳቦች፥ ምከሮች፥ መረጃዎች እና አሉባልታዎች ተሸንግለንስ ይሆን? የጸለይነው እግዚአብሔር ችግሩን በተለይ እኛ በምንፈልገው መንገድ እንዲፈታልን ነበር? ወይስ እርሱ በወደደው በማናቸውም መንገድ እንዲፈታው? እግዚአብሔር ችግሩን በፈታው ጊዜ፥ ችግሩ የተፈታበትን መንገድ መቀበል ያቃታቸው ለዎች ታዲያ ለምን አቃታቸው?

በዚያ ፈተና አለፍን ወይስ ወደቅን? ተጎዳንበት ወይስ ተማርንበት? ወደ እግዚአብሔር ቀረብንበት ወይስ ከእግዚአብሔር አራቅንበት? ወደ ፊት ሌላ ፈተና ሲያጋጥመን (መቼም ማጋጠሙ አይቀርምና)፥ አራሳችንን እና ቤተ ክርስቲያንን ከጉዳት ለማዳን የሚያስችለንን ተሞከሮ አገኘንበት? ባጭሩ ያንን ፈተና አተረፍንበት ወይስ ከሰርንበት? አዎን፥ ከፍተቱ አሁን ተዘግቷል፤ እግዚአብሔር ይመስገን። ሆኖም፥ ከጥቂት አጥቢያዎች እና አገልጋዮች ጋር አለያይቶን ነው የተዘጋው። ይህም፥ ጥል እና ከርከር፥ ሁልጊዜም የሚያሰከፍሉት ዋጋ ነው።

ማስታወሻ

1. "ዕብድ እና ዘመናይ የልቡን ይናገራል" የሚል ተረት በአገራችን አለ።
2. በሮሜ 7፥15 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እራሱ የጻፈውን በጊዜው እንደዚህ ነበር የተረዳሁት።



አያኑብ አንባዉ
(1957 ዓ.ም.)




የስአለት ሚስት
(1965 ዓ.ም.)



ዶሪስ ብራያን ሩርክ ልንዴ ጃነስ እና ዳያን
(አለታ ወንዶ 1966 ዓ.ም.)



የሙሉ ወንጌል አማኞች አሎ ቤት
(ዶር.ጋ ዓለም፡ 1968 ዓ.ም.)



ዕፁኔ መጋዚዎች ፡ ከግራ ወደ ቀኝ አቶ በቀለ ወ/ኪዳኑ አቶ ዓባይ ኃይሉ እና ወንጌላዊ ጌዲዎን ተስፋዬ (ጥቅምት 26 ቀን 1993 ዓ.ም.)



ወ/ሮ ገቡ ሀበተ ማርያም
(1977 ዓ.ም.)



ዮሴፍ ይድነቃቸው
(2004 ዓ.ም.)




ራሔል ወንድም አገኘሁ፣ ካሣ ኃ/ጊዮርጊስ፣
ባስልኤል እና አቢጋኤል ካሣ (2004 ዓ.ም.)



ጌዲዎን አሉላ፣ የትናየት መንግሥቱ፣
ገለዓድ እና ጌልገላ ጌዲዎን (2004 ዓ.ም.)



የልዩ ጠቅላላ ጉባዔው ሰብሳቢ እና ቡድናቸው
(አቶ መሉጌታ ዘውዴ፣ ቄስ ዓለሙ ሼጣ እና አቶ መላኩ በላቸው)



ከሥስቱ ተቋማት የተውጣጣው የልዩ ጠቅላላ ጉባዔው ቃለ ጉባዔ ያዥ ቡድን
(አቶ ዓይናለም ሃይማኖት፣ አቶ ሰለሞን ከበደ እና አቶ ከበደ ሉሌ)




ዕርቁን ያጸደቀው ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ በከፊል



ዕርቁን ያጸደቀው ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ በከፊል



ዕርቁን ያጸደቀው ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ በከፊል



ዕርቁን ያጸደቀው ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ በከፊል

ምዕራፍ ዘጠኝ

“ልብማ ልባሙ”

ዱሮ ከአባቴ ጋር መንገድ ስንሄድ፥ ከዘራውን በቀኝ እጁ እያሸከረከረ፥ ዝማ ባስ ድምፅ ሲያንጎራጉር አሰማዋለሁ። ከግጥሞቹ ሁለት ሦስት ያህሉ በውስጤ ቀርተዋል። አንዱ ይኸው -

ልቤማ ልባሙ ሄደ ገስገሰ፤
ዐይኔ በስንፍናው ቀረ እያለቀሰ።

ካደግሁ በኋላ፥ ብዙ ዘፋኞች ይህንን ሲሉት ሰምቻለሁ። ግጥሙ በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ያሉትን ሦስቱን የጊዜ ቋቶች ያካትታል። ልብ ሄዷል - ወደ ፊት፤ ገና ወዳልተደረሰበት። ዐይን ቀርቷል - ዛሬ ላይ፤ አሁን ካለበት ላይ - ተተክሎ። ደግሞ ያለቅሳል። የሚያለቅሰውም የትናንትናው ስንፍናው ነው - ነገን ማየት፥ ልቡን መከተል፥ አለመቻሉ። ትናንት - ዛሬ - ነገ። ሦስት የሰው ሁሉ የሕይወት ቋቶች። እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ። አንዳቸው ያለ ሌላቸው የሌሉ።

ስሞኑን የማይክ ቢክልን “GROWING IN THE PROPHETIC” እያነበብኩ ነበር። ማይክ በካንሳስ ከተማ የሚገኘው የኢንተርናሽናል ሃውስ አፍ ፕሬየር መሥራች እና ዳይሬክተር ነው። በእኔ እጅ ያለው በ2008 የታተመው ሁለተኛው የመጽሐፉ እትም ነው። በዚያን ጊዜ 500 የሚሆኑ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች፥ 1,000 የሚሆኑ ተለማማጅ ተማሪዎች (INTERNS) ነበሩት። እያንዳንዳቸው በሳምንት 50 ሰዓታት ያህል በአገልግሎቱ ላይ ያሳልፋሉ። የየራሳቸውን ወጭ በየራሳቸው ይሸፍናሉ። በኢንተርናሽናል ሃውስ አፍ ፕሬየር በሳምንት ሃያ አራት ሰዓት ይጸለያል። ስለ ሪቫይቫል ነው የሚጸለየው። ትንቢታዊ አገልግሎትም ይሰጣል። ተለማማጅ ተማሪዎቹ ስለ ትንቢት አገልግሎት በተሞክሮ ይማራሉ።

የቢክልን መጽሐፍ ሳነብብ የተስማኝ የቁጭት ስሜት ነው - “ምነው ይህንን ከ20 እና ከ25 ዓመታት በፊት ዐውቄው ቢሆን ኖሮ” የሚል። ለእኛ “ክላሲካል ጴንጤቆስጤአዊነት” ማለት በልሳን መናገር ብቻ ሆኖ ቀርቷል። አሁን ሳየው እንኳን እኛ፥ ለጴንጤቆስጤአዊው ልምምድ ከተጋለጥን ገና 50 ዓመት ብቻ የሆነን ቀርቶ፥ 112 ዓመታት ያለፏቸው እነርሱም ገና “ተማሪዎች” ናቸው። ትልቁ ልዩነታችንም እዚህ ላይ ነው - እነርሱ ይማራሉ። ስንት እና ስንት በልም ምዱ የበሰሉ ሰዎች እያሏቸውም። ስንት እና ስንት መጻሕፍትም በየዓመቱ እየተጻፉ። ስንት እና ስንት ስህተቶችም እየተሠሩ። እኛ ግን ዐውቀነው የጨረስነው እንመስላለን። ጉጉት የለንም።

መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ወዳለ ከፍታ ይሆን ይዟት እየወጣ ያለው? ምነው አልቆጭ? ስነገሩ እኔ የማይክ ቢክልን መጽሐፍ ሳነብብ ብቻ አይደለም እንደዚያ የተሰማኝ። የቢል ሐሞንን መጻሕፍትም ባነበብኳቸው ጊዜ እንደዚያው ተሰምቶኛል። አሁን በቅርቡ የኪም ክሌመንትን “CALL ME CRAZY but I’m hearing God” በማነብበትም ጊዜ እንደዚያው ተሰምቶኛል። የአፍሪቃዊውን ነቢይ፥ የቲ. ቢ. ጆሽዋን ፕሮግራሞች በቴሌቪዥን በተከታተልኩ ቁጥርም የሚሰማኝ ስሜት እንደዚያው ያለ ነው።

ከላይ የጠቀስኩት የእማርኛ እንጉርጉሮም የቁጭት ነው። በእስራኤል “የነቢያት ማኅበር” የሚባል ነበረ - ከሳሙኤል ዘመን ጀምሮ እስከ እነ ኤልሳዕ ዘመን ድረስ (2ነገ. 9፥1)። ሳሙኤል ሳይጀምረው እንዳልቀረ ነው የሚታመነው። ዳዊትንም ለአጭር ጊዜ ሥልጠና ወደዚያ ወስዶት ነበር (1ሳሙ. 19፥18-24)። ዳዊት ከሕይወቱ እና ከአገልግሎቱ “ነገ” ጋር የተዋወቀው (ሐዋ. 13፥36) በዚያ ላይሆን አይቀርም። እቤቱ በቃል እና በተሞከሮ የሚያስተምሩንን ሰዎች እባክህን ስጠን! አቤቱ ስለኛም መማር የሚወድ ማንነት እባክህን ስጠን!! እቤቱ ካለንበት ከዚህ ሸለቆም ውስጥ እባክህን አውጣን!!!

ስንት ዓመት ቢኖር?

‘ኖ’ ትጠብቃለች። ባለፉት ስምንት ምዕራፎች ስለ ትናንትናዬ፥ ግፋም ቢል ትንሽ ስለ ዛሬዬ፥ ነው ያወራሁት። በዚህ በመጨረሻው ምዕራፍ፥ ስለ ሦስተኛው የሕይወት ቋት ትንሽ መናገር ያስፈልገኛል። ጠቢቡ ስሎሞን፥ “ሰው ምንም ያህል ብዙ ዓመት ቢኖር ... ጨለማዎቹንም ቀናት ያስብ፤ እነርሱ

ይበዛሉና ..." ብሏል (መክ. ፲፪፥8)። ከሞት በኋላ ስላለው ጊዜ ማለቱ ነው። እውነቱን ለመናገር፥ ከሞት በኋላ ያለው ጊዜ አያላስበኝም። ምክንያቱም "ዘሀለወ ምሉሌሁ ወልድ ቡቱ ሕይወት፤ ወዘሰ ኢሀሎ ምሉለ ወልደ እግዚአብ ሔር አልቦቱ ሕይወት" (ጁኹ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም) ተብሎ ተጽፎአልና (፩ዮሐ. 5፥12)።

"ከአንግዲህ በኋላ በምድር ላይ ለንት ዓመት እኖራለሁ?" ብዬ አሰቤ ዐውቃለሁ። እንዲያውም ከዚያም አልፌ፥ "የምድር ላይ ዕድሜዬ ለንት ዓመት ቢሆን ይሻለኛል?" ብዬም አሰቤ ዐውቃለሁ። የዕድሜዬን ጣራ አሰክ መወሰንም ድረስ ሄጃለሁ። ያንን የወሰንኩት ግን መቼ እና እንዴት እንደ ሆነ በትክክል አላሰታውሰም። ሆኖም ይህችን ክፍል ለመጻፍ ማሰታወሻዬን ሳገላ ብጥ DECEM8ER 0፩፥ 1995 (ጎዳር 21/88) የጻፍኩትን አንድ ጸሎቴን አግኝ ቻለሁ። አንዳንድ ጊዜ በጽሑፍ እንደምጸልይ በምዕራፍ አንድ ውሰጥ ተናግሬ አለሁ። አንደ ወረደ ነው የጻፍኩት። እንደዚህ ይላል -

> "Friday፥ 3:00 A.M. ጌታ ሆይ፥ አምላኬ ሆይ፥ መድኅኒቴ ሆይ፥ አባቴ ሆይ፥ እረኛዬ ሆይ፥ አመሰግንሃለሁ። አልዋሸህም፤ It hurts. ግን ሐኪሜ እንተ ነህ። በእጆችህ ውስጥ ነኝ። አምንሃለሁ። Go ahead and deal with me. I still want to live the 21 years - until I become 75. I still want to preach the Gospel of Jesus Christ. If this - which I want - is not your will for me, then there is, for me, no purpose in life. You may as well call me home. ጌታ ኢየሱስ ሆይ - አወድሃለሁ። ፍቅሬን ከወረት አጥራው። አመሰግንሃለሁ። የሕይወቴ ገሎች እነሆ በፊትህ፤ እነሆ በእጅህ። ምስጋ ናቸውን ተቀበል። ከእንግዲህ ተመልለው ሙሉ ሸክላ መሆን ይችሉ እንደሆን አላውቅም። ሙሉ ሸክላ መሆን እሰፈላጊ ላይሆንም ይችላል። ጌታ ኢየሱስ ሆይ! በሥጋዬ ካለ ድካም ጠብቀኝ። ከሁለተኛ ጋብቻ ጠብ ቀኝ። ከሁለተኛ ቃል ኪዳን ጠብቀኝ። አራሴን አላምነውም። አንተን ግን አምንሃለሁ። ፊጽመህ ጠቅልለኝ። ስለ ከበረው፥ በሕይወቴም እንዲከብር ስለምፈልገው፥ ስለ ሰምህ ብለህ፤ አሜን።"

ይህ የትዳሬ መፍረስ ያጠላበት ጸሎት ነው። የተጸለየውም የገነትን ውሳኔ ከሰማሁ ከአንድ ወር ገደማ በኋላ ነው። የዕድሜዬን ጣራ በተመለከተ

የወሰንኩት ውሳኔ ከዚያ ቀደም ሲል ለመሆኑም ፍንጭ ይሰጣል - "I still want ..." ይላልና። በተለያዩ አጋጣሚዎች ስለዚህ ውሳኔዬ ስናገር የሰሙኝ ሰዎች ሁሉ ማለት ይቻላል፥ ተቃውመውኛል። ለምን እንደሚቃወሙኝ ግን አይገባኝም። ብዙ ነገሮችን ከእግዚአብሔር እንለምን የለም እንዴ? ልክ እንደዚያው፥ እኔ ደግሞ የዕድሜዬን ጣራ ወሰኜ፥ "ይህንን ያህል ዕድሜ ነው አንድትለጠኝ የምፈልገው" ብለው፥ ምንድነው ችግሩ?

አንደኛ በመጽሐፉ ውስጥ ለሰው ልጆች የተቀመጠላቸውን የዕድሜ ጣራ አልጣለኩም (መዝ. 90፥10)። ሁለተኛ "ከጠየቅሁት ብታሳንስ ወይም ብታስበ ልጥ አልቀበልህም" አላልኩም። አንደዚያ ልለውም ደግሞ አልችልም። ሦስተኛ "በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፥ የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር ለምኑ፤ ይለጣችኋልም" ብሏል (ዮሐ. 15፥7))። በጥቅሱ ውሰጥ ያለውን ቅድመ ሁኔታ ማሚላቴን እርግጠኛ ባልሆንም፥ የምፈልገውን ግን ለምኜዋለሁ። አራተኛ እግዚአብሔር እቦቴ ነው። የዕድሜ ነገር ደግሞ - ቢያጥርም ቢረዝምም - ዋና ነገር ነው። ሰለዚህ ዋና ነገር እንዴት ነው አባቴን የማልለምነው? አምስተኛ የእግዚአብሔር መንፈስ ለቅዱሳኑ የጸሎት ርእስ እንደሚለጣቸው ከቃሉ ብቻ ሳይሆን (ፊል. 2፥13)፥ ከልምድም ጭምር ዐው ቃለሁ። ይህ የጸሎት ርእስ ለእኔ በእግዚአብሔር የተሰጠኝ ቢሆንስ? ጠብቀን ማየት ብቻ ነው ያለብን።

ምን ቢሠራበት?

'ሠ' ትጠብቃለች። ትልቁ መጽሐፍ እንደሚለው፥ ላልዳኑ ለዎች እግዚአብሔር ዕድሜ የሚሰጣቸው ወደ ንሰሐ እንዲደርሱበት ነው።

> "... ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ የሚመራህ መሆኑን ሳትገነዘብ፥ የቸርነቱን፥ የቻይነቱን የትዕግሥቱን ባለጠግነት ትንቃለ ህን?" (ሮሜ 2፥4) "... አንዳንድ ሰዎች የዘገየ እንደሚመስላቸው ጌታ የተስፋ ቃሉን ለመፈጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ማንም እንዳይጠፋ ፈልጎ፥ ሁሉ ለንስሐ እንዲበቃ ሰለ እናንተ ይታገሣል" (2ጴጥ. 3፥9)።

ለዳኑ ለዎች ደግሞ እግዚአብሔር በምድር ላይ ዕድሜ የሚጨምርላቸው ለእገልግሎት፥ ማለትም ለክርስቶስ ክብር እና ለቅዱሳኑ ጥቅም ነው።

"... ዛሬም በሕይወትም ሆነ በሞት ከርስቶስ በሥጋዬ እንዲከብር ሙሉ ድፍረት ይኖረኛል። ለእኔ፥ መኖር ከርስቶስ ነው፤ ሞትም ማትረፍ ነው። በሥጋ ከቆየሁ፥ ፍሬያማ ተግባር ይኖረኛል፤ ነገር ግን የትኛውን እንደምመርጥ አላውቅም። በእነዚህ በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ፥ ከክር ስቶስም ጋር ልሆን እናፍቃለሁ፤ ይህ እጅግ የተሻለ ነውና። ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ለእናንተ ይበልጥ አስፈላጊ ነው። ይህን በማስተዋል፥ በእምነት እንድታድጉና ደስ እንዲላችሁ፥ በሁላችሁ ዘንድ እንደምቆይና እንደምኖር ተረድቻለሁ" (ፊል. 1፥20-25)።

ሐዋርያው ጳውሎስ የመጀመሪያው የሮም እስራቱ ለምን እንዳጠረለት (ሐዋ. 28፥30-31)፥ ለምንስ በሁለተኛው እስራቱ ጊዜ እንደ ሆነው የሞት ፍርድ እንዳልተፈረደበት (2ጢሞ. 4፥6) እሁን እንረዳለን። ከመሞቱ ይልቅ፥ በሥጋ መኖሩ፥ ለሚያገለግላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ይበልጥ አስፈላጊ ስለ ነበረ ነው። ስለዚህም እንደሚቆይና እንደሚኖር መረዳቱን ይነግራቸዋል። ይህንን ደብዳቤ ለፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ከጻፈላቸው በኋላ አራተኛውን የወንጌል አገልግሎት ጉዞውን አድርጓል። እንደኛ ጢሞቴዎስን እና ቲቶን ጽፏል። ከዚያም የመጨረሻ አስራቱን ታስሮ እያለ ሁለተኛ ጢሞቴዎስን ጽፏል።

የሚቀርቡንን ብዙ ሰዎች ጠርቼ እግዚአብሔር ያደረገልንን ቸርነት ለመመስከር ከብዙ ጊዜ በፊት ጀምሮ ፍላጎት እንደ ነበረኝ፥ ስለዚያ የምስክርነት ጊዜ ሳስብ እና ስጸልይ እንደ ቆየሁ፥ በመጨረሻ ግን ሳይሳካልኝ እንደ ቀረ፥ በምዕራፍ አምስት አውስቻለሁ። እርግፍ አድርጌ ተውኩት ማለት ነው። ምስክርነቴን በመጽሐፍ መልክ የማውጣት አሳብ ወደ እኔ ሊመጣ የጀመረው ግን ቆይቶ ነው። የኅርብ፥ ጥር 30 ቀን 1997 ዓ.ም. ማስታወሻዬ እንደዚህ ትላለች፤

"ጌታ ሆይ! ያንተን አሳብ አላውቅም። ያንተ አሳብ ከሰው አሳብ ለማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ የራቀም፥ ከፍ ያለም ነው። በእኔ ውስጥ ያለው አሳብ ግን፥ አንተ ዕድሜ ብትሰጠኝ፥ በሚቀጥሉት 10 እና 12 ዓመታት ውስጥ ሦስት መጻሕፍት ለመጻፍ እና 'ሪቫይቫል' የሚለውን መጽሐፌን revise ለማድረግ ነው። ይህ የአንተ አሳብ ከሆነ፥ በውስ ጤም ያደረግኸው አንተ ከሆንክ፥ የምጽፍበትን እና የማሳትምበትን environment ፍጠርልኝ"

በጸሎቴ ውስጥ፥ የምጽፋቸውን ሦስት መጻሕፍትም በስም ጠቅሻለሁ። በስም ከጠቀስኳቸው ከሦስቱ መካከል አንዱ "ትውስታ" ነው። ጸሎቱ ላይ በሦስተኛ ተራ ቁጥር ነበር የተጠቀሰው። እሁን ግን የመጀመሪያው ሆኗል። በማስታ ወሻዬ ላይ ተጽፎ ያገኘሁት፥ በዚህ ጉዳይ ላይ የጸለይኩት ሁለተኛው ጸሎት፥ ዓርብ ሚያዝያ 07 ቀን 1997 ዓ.ም. ነው የተጻለየው። ያን ዕለት እኅት (አሁን ወንጌላዊት) እበበች ዓለሙ የሆነች አኅት ያየችልህ ነው ብላ የሆነ ሕልም ነግራኝ ነበር። ማስታወሻዬ ላይ እንደዚህ ብዬ ጽፌ እግኝቻለሁ -

"... ለሕልሙ እንኳን ከብደት አልሰጠሁትም። ይልቅስ የጸሎት ጥያቄዬን በጥቅስ አለደግፌ ልጻፍ፡- 'አምላከ ሆይ፤ ሳረጅና ሰሸብትም አትተወኝ፤ ከንድህን ለመጭው ትውልድ፥ ኃይልህን ኋላ ለሚነሣ ሕዝብ ሁሉ እስከ ምገልጽ ድረስ' (መዝ. 71፥18)። ለትውልድ የሚነገር ነገር የሚነገርበት መንገድ ደግሞ ጽሑፍ ነው፡- 'ወደ ፊት የሚፈጠር ሕዝብ እግዚአብ ሔርን ያወድስ ዘንድ፥ ይህ ለመጭው ትውልድ እንዲህ ተብሎ ይጻፍ፤' (መዝ. 102፥18)። አቤቱ ጌታ ሆይ! ያደረግህልኝን ያንን ሁሉ ምሕረትና ቸርነት ከኋላዬ ለሚመጣ ትውልድ በመጽሐፍ መልክ እንድ ተውለት ፈቃድህ ይሆንልኝ ዘንድ አለምናለሁ። ይህንኑም ማድረግ የምችልበትን ጤና፥ ሰላም እና የተመቻቸ ሁኔታ እንድትሰጠኝ አለምን ሃለሁ፤ በጌታ በኢየሱስ ስም፤ አሜን"

ምስክርነቴን በመጽሐፍ ስለ ማውጣት ጉዳይ፥ ማስታወሻዬ ላይ ተጽፎ ያገኘሁት፥ ቀጥሎ የጸለይኩት ጸሎት ያለው ዓርብ ጥቅምት 24 ቀን 1999 ዓ.ም. ነው።

"ጌታ ሆይ! ልመናዎች አሉኝ። አለምንሃለሁ። አንተን ያልለመንኩ ማንን አለምናለሁ? ከብር ሁሉ ለሰምህ ይሁን! አወድሃለሁ። ዕድሜዬ እያለቀ ነው። ያሳስበኛል። የሚያሳስበኝ መሞት ስለምፈራ አይደለም። ወደ አንተ መምጣት የምወደው፥ ደስ የሚለኝ፥ አንጂ የሚያሳስበኝ እና የሚያ ስፈራኝ አይደለም። የሚያሳስበኝ ፈቃድህ፥ የዘላለም ዕቅድህ፥ በሕይወቴ ተፈጽሞ ተጠናቀቀ ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። ያደረግህልኝ ብዙ ነው። ያስተማረከኝም ብዙ ነው። ከኋላዬ ለሚመጡ ሳልነግራቸው ልለፍ ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። ለመጻፍ እፈልጋለሁ። ጌታ ሆይ! ጊዜ ለጠኝ። ኮምፒውተር አለተምረኝ። ሁኔታዎችን አመቻችልኝ። ስፖንሰር

እዘጋጅልኝ። እንተ ብትፈቅድ እነዚህ ከፊቴ ያሉ ዐሥር ዓመታት ያህል የምጽፍባቸው ዓመታት ይሁኑ። ከብሩ ደግሞ ለእንተ ብቻ ይሁን። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም - አሜን።"

ከላይ የጠቀስኳቸው እነዚህ ጸሎቶች ማስታወሻዬ ላይ ተጽፈው ያገኘኋቸው ናቸው። እነዚህን ጸሎቶቼን የጸፍኳቸው፥ እግዚአብሔር በሚያውቀው፥ ለዚህ ጊዜ እስቤአቸው አይደለም። ማስቴ እንድ ቀን በዚህ ጉዳይ ላይ በምጽፈው መጽሐፍ ውስጥ በማስረጃነት ኡጠቅሳቸዋለሁ ብዬ አይደለም። በፍጹም። እሁን ነገሩ እንደዚያ ሆኖ ሳገኘው፥ ተገርሜአለሁ።

መጽሐፍ ስለ መጻፍ ጉዳይ፥ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መልእክት የነገሩኝ እራት ወንድሞችም አሉ። ከእነዚህም የመጀመሪያው ወንድም ራእዩን ያየው፥ እኔ እዚህ ከመዘገብኩት ከመጀመሪያው ጸሎቴ ሦስት ወራት ቀደም ብሎ፥ ማስትም ጥቅምት 29 ቀን 1997 ዓ.ም. ነው። ያው ወንድም፥ በዚያው ዓመት የካቲት 06 ቀን፥ በዚያው ጉዳይ ላይ፥ ሁለተኛ ራእይ አይቷል። ከዚያ ወንድም ጋር እንተዋወቃለን። ሆኖም ራእዮቹን በሚያያቸው ጊዜ እኔ አብሬው አል ነበርኩም። የእርሱም፥ የእኔም ወዳጅ ከሆነው ከወንድም በዛብህ ወርቅነህ ጋር አብረው ሲጸልዩ ነው ሁለቱንም ራእዮች ያያቸው። የመጀመሪያውን ራእይ ጽፎ በወንድም በዛብህ እጅ ልኮልኛል። ሁለተኛውን ወንድም በዛብህ አራሱ ነው ጽፎ የሰጠኝ።

ያ ወንድም እና ወንድም በዛብህ በየማለዳው፥ ከአካላዊ እንቅስቃሴ በኋላ፥ እየተገናኙ መኪናቸው ውስጥ ይጸልያሉ። በተጠቀሰው ማለዳ ሲገናኙ፥ ያ ወንድም "ሰሞኑን ጋሽ በቁ በልቤ ላይ አለ። አልሄድልህ አለኝ። አስቲ እንጸልይለት" ይላል። ሌላውን ከላከልኝ ማስታወሻ ልጥቀስው፦

> "ስለ እንድ የምናውቃቸው የቤ/ክ መጋቢ እንድንጸልይ መንፈስ ቅዱስ ባሳሰበን መሠረት በጸሎት ላይ ነበርን። እየጸለይን እያለን ሰውዬውን መንፈስ ቅዱስ በራእይ አሳየኝ። የራሳቸው ጸጉር በሙሉ ነጭ ነው። በጣም ረዥም ነጭ ጺም ወደ ታች ወርዶ ይታያል። ልክ ጺማቸውን የሚመስል ነጭ ረዥም ጭራ በእጃቸው ይዘዋል። ኩርምት ብለው በጎዘንና በትካዜ ስሜት እና በተመስጦ ውስጥ ናቸው። ዐይናቸውም ዕንባ አቅርሯል ... የምታየው የዘመኑ ቤተ ክርስቲያን እና የሕዝቤ ሁኔታ ነው። እንደዚህ ያስጠላል። በዚህ መካከል የተመለከትከው ሰው

> የተከዘበትና ያዘነበትም ይህ ሁኔታ ነው። እርሱ ይህንን የቤቴን ሁኔታ፥ እኔ የማደርገውንም ለትውልድ እንዲነግር ያስቀመጥኩት ሰው ነው።"

ያየውን ነገር ላለመናገር ስል ነው ጠቃጠቆ አድርጌ ያሰፍኩት። እንደ ተባለ ውም የሚያስጠላ ነገር ነው። ሦስተኛው መልእክት የመጣው ኅዳር 12 ቀን 2001 ዓ.ም. ሦስት ሆነን ለጸሎት በተገናኘንበት አንድ ጎብረት ላይ ነው። መል እክቱን ያመጣው ሰው ሊያገለግለን ተጋብዞ የመጣ፥ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነው። ከዚያ ወንድም ጋር ከዚያን ቀን በፊት ጨርሶ አንተ ዋወቅም - በመልከም፥ በስምም። አራተኛው መልእክት የመጣበትን ቀን እልጻ ፍኩትም። ነገር ግን በሰኔ ወር 2001 ዓ.ም. ውስጥ እንደ ሆነ እርግጠኛ ነኝ።

ጊዜውን እርግጠኛ ለመሆን የቻልኩት፥ በልጅነቷ ስእጋንንት ተሰዋታ የነበረች እንዲት የቤት ሠራተኛ ነበረችን። ምንም እንኳን እሁን በጌታ ብትሆንም፥ ብርቱ የሆነ የርኩሳን መናፍስት ውጊያ ነበረባት። በዚያን ሰሞን ታዲያ፥ "እንደ ርቢ" በሚበለው የርኩሳን መናፍስት እሠራር፥ በቤታችን ጣራ ላይ የድንጋይ ናዳ ይወርድ ነበረ። ጊዜውን በትክክል ዐውቀዋለሁ። በዚህ ጉዳይ ለመጸሰይ ከእኅት ገነት ከበደ ጋር አብሮ ወደ ቤታችን የመጣ አንድ የመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነው መልእክቱን ያመጣው።

አምስተኛው እና የመጨረሻው መልእክት የመጣው ዓርብ ታሕሣሥ 16 ቀን 2002 ዓ.ም. ሲሆን፥ መልእክቱ የመጣው (ለምን እንደ ሆነ አላውቅም) አሁንም ወንድም በዛብህ ወርቅነህ እና እንድ ሌላ ወንድም አብረው ሲጸልዩ ነው። መልእክቱን የተቀበለው ወንድም የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስ ቲያን አገልጋይ ነው። ሆኖም የእኔ አጥቢያ አገልጋይ ስላይደለ፥ እኔ አላውቀ ውም። በሌላ ጊዜ ተገናኝተን እርሱ ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምሮ ያውቀኝ እንደ ነበረ ነግሮኛል።

ይኸኛውንም መልእክት ስልከ ደውሎ የነገረኝ ወንድም በዛብህ ነው። ሁለተኛውን፥ ሦስተኛውን እና አራተኛውን መልእክቶች መናገር እያስፈል ገኝም። "ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል" ስለሚበል አይደለም። ሌላ ነገር አብሮት ስላለ እና ያ ሌላ ነገርም አሁን እየጻፍኩት ካለሁት ጉዳይ ጋር ግንኙነት ስለ ሌለው ብቻ ነው። የመጨረሻው ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነው - ኤርምያስ 36፥4። እንደዚህ ይላል፦

"ኤርምያስም የኔርያን ልጅ ባሮክን ጠራው፤ ባሮክም እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ሁሉ ከኤርምያስ አፍ ተቀብሎ በብራናው ላይ ጻፈ።"

ይህ መልእክት የመጣበትን ሁኔታም ግልጽ ባደርገው ጥሩ ይመለስኛል። ያን ዕለት ረፋዱ ላይ ለወንድም በዛብህ ሰልክ ደውዬ የሆነ የሆነ ነገር እሜወ ትኩት። እርሱም "እንኳን ደወልከልኝ፤ አሁን ከእንድ ወንድም ጋር አብረን ልንጸልይ መጥተን አቤት ነው ያለሁት። እንጸልይበታለን" አለኝ። እና አየጸለዩ አያሉ፥ "ለወንድም በቀለ አንጸልይለት" የሚል የጸሎት ጥያቄ ያቀርባል። ከዚህ ያለፈ ሌላ ምንም ነገር እንዳልተናገረም ነግሮኛል። ወንድም በዛብህ ላለፉት 30 ዓመታት የማውቀው ወዳጄ ነው። "በለመ የጸሎት ጥያቄ" አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ዝም ብሎ የሚያወራ ሰው አይደለም ማለቴ ነው።

አብሮት የተንበረከከውም ሰው ከቤቱ ሲወጣ ዛሬ ለወንድም በቀለ እንጸልያለን ብሎ አልወጣም። ከበቀለ በለተቀርም፥ ስለ በቀለ የሚያውቀው ምንም ነገር የለውም። ለእኔ በሚጸለይበት ጊዜ፥ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ወደ ልቡ ይመጣሉ። ሁለተኛው ጥቅስም ከላይ የጠቀስኩት ነው። ከአግዚአብሔር ካልሆነ በለተቀር፥ ይኸ ከሌላ ከየት ሊሆን ይችላል? ለብዙ ዓመታት ስጸል ይበት በነበረው በዚህ ጉዳይ ላይ፥ ሌላ ማን ሊናገረኝ ይችላል?

ፍጥሞ

ዓርብ የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም። ከለሻ ጀምሮ በቀጣና ሁለት በጸም እና ጸሎት ኮንፈረንስ ላይ ነን። በብዙ አገራዊ እና ቤተ ክርስቲያናዊ ጉዳዮች ላይ ጸልየናል። ከመጋቢት 24-26 በአዲስ አበባ ስቴድየም ሊደረግ በታቀደው የጀማ ስብከተ ወንጌል መርሐ ግብርም ላይ ጸልየናል። ዛሬ ቀን ላይ በእግዚአ ብሔር ቃል የማገለግለው እኔ ነበርኩ። አገልግዬ ሰጨርስ ዕረፍት ሆነ። በዕረፍቱ ጊዜ እኅት አበበች ዓለሙን አገኘኋት እና ወደ ቢሮዬ ይዣት ሄድኩ። ሰሞኑን አልተገናኘንም ነበር እና በሚቀጥለው ሳምንት ወደ አውሮፓ እንደ ምበርር አታውቅም። በዎርልድ ቪዥን ከተቀጠርኩበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ከአቢ ጋር በጣም ቅርብ ነን። የምሆነውን ነገር ሁሉ አነግራታለሁ።

"ጌታ ቢፈቅድ እና ብንኖር የፊታችን ረቡዕ ወደ ግሪክ አበርራለሁ ... የጋበዘኝ የአውሮፓው ኅብረት ነው ... ስለዚህ ከግሪክ ወደ ቤልጅዬም፥ ስዊድን፥ ኖርዌይ፥ ጀርመን፥ ኢንግሊዝ እቀጥላለሁ። ከሁለት ወራት በኋላ ነው

የምመለሰው። ከዚያ ስመለስ ደግሞ ወደ አሜሪካ እሄዳለሁ ... ሰሞኑን ስላልተገናኘን ይህንን አልነገርኩሽም ... ለዚህ ነው የፈለግሁሽ" አልኳት። አንደ መገረም አለች እና "ለምኑን ያየሁት እና የጸለይኩበት ነው" ብላ አንድ ሕልም ነገረችኝ።

"ምግብ ይበላል ... ብዙ ሰዎች አሉ ... አንተም እኔም አለን ... አንተ የምትበላውን ምግብ ሳትጨርለው ትተወዋለህ ... እየደጋገምኩ 'ብላ እንጂ' አልሃለሁ ... አንተም 'በቃኝ' ትለኛለህ ... ከዚያም ትነሣ እና ትወጣለህ ... ከሕልሙ ስነቃ በሰላም ይሁን አንጂ አሁንስ ይብቃው" ብዬ ጸለይኩልህ አለችኝ።

"ምነው ታዲያ ሳትነግሪኝ?" አልኳት።

"ምን ላድርግ ትለኛለህ? ዘመኑ የሚያስፈራ ሆነ እኮ" አለችኝ።

"ታዲያ ሊያስፈራ ውሎ ቢያድር በአንቺ እና በእኔ መሐል ነው እንዴ? ... ብቻ ጸልይልኝ ... ሊሆን ያለ ነገር ያለ ይመለለኛል ... እኔም አጸልያለሁ" አልኳት። በዚሁ ተለያየን።

መጽሐፍ ለለ መጻፍ በውስጤ ከቆየው ጸሎት፥ በዚሁ ጉዳይ ላይ በሌሎች ወንድሞች በኩል ከመጡልኝ መልእክቶች፥ አሁን ደግሞ ከአቢ ሕልም የተነሣ፥ ወደ አውሮፓ የበረርኩት የከበደ ልብ ይዤ ነበር ማለት እችላለሁ - በፊቱ ወዳለው፥ ገና በውል ወዳላወቀው፥ የእግዚአብሔር ዕቅድ ሊሻገር ጫፍ ላይ ያለ ሰው።

የአቴንስ አገልግሎቴን ሳጠናቅቅ፥ የፍጥሞን ደሴት ሊያሳዩኝ ዕቅድ እንደ ያዙልኝ፥ የቤተ ክርስቲያኗ መሪዎች አንድ ቀን ነገሩኝ። ይህንን በለማሁ ዕለት አገር ቤት እና አሜሪካ ወደሚኖሩ ሦስት ወዳጆቼ ኢ-ሜይል አደረግሁ -

> "የአቴንስ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሎች ወደ ፍጥሞ እንወስድሃለን ብለው ኖል ... ጸሎት ያስፈልገኛል ... እንደ ዮሐንስም ባይሆን ... ራእይም ባይ ሆን ... ለዓለሙ ሁሉም ባይሆን ... ጌታ ለእኔ የምትሆን ትንሽ ነገር ሳይና ገረኝ ከዚያ እንዳልመለስ ... እባካችሁ ጸልዩልኝ"

ስል ተማጠንኳቸው። ጉዳዩ ከቦታው ጋር እንዳልሆነ አላጣሁትም። በቤት ልሔም፥ በናዝሬት፥ በቅፍርናሆም፥ በኢየሩሳሌም፥ ወዘተርፈ፥ ማንም እንደ

ሚኖር ዝም ብሰው የሚኖሩ ሰዎች ቁጥር እጅግ ብዙ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ። እኔ ግን የተለየ ነገር ነበር የተሰማኝ።

በመስከረም ወር 1984 ዓ.ም. ካምፓላ፥ ዩጋንዳ፥ ሄጄ በነበርኩ ጊዜ አንድ ታሪክ ሰማሁ። ታሪኩ እንደ ጎርጎሰውያኑ አቆጣጠር በ1880ዎቹ፥ በካቶሊክ እና በእንግሊካን ሚሲዮናውያን እማኻይነት ወንጌል ሰመጀመሪያ ጊዜ በቡጋንዳ መንግሥት ግዛት ውስጥ ሊሰበክ የተፈጸመ ነው። የመጀመሪያዎቹ አማኞች በ"ካባካ"ው (ንጉሡ) ቤተ መንግሥት ውስጥ የሚያገለግሉ፥ በመልካቸው እና በቁመናቸው የተመረጡ ወጣቶች ነበሩ። የሚቹ "ካባካ" ሴት ልጅ እና በጊዜው በዙፋኑ ላይ ያለው "ካባካ" አጎት የሆነችው ልዕልትም የሚሲዮናውያኑን ሃይማኖት ከተቀበሉት መካከል እንዷ ነበረች።

ረዥሙን ታሪክ ለማሳጠር፥ በድምሩ 51 የሚሆኑ ካቶሊካውያን እና እንግሊካን ምዕመናን እንዲገደሉ ተፈረደባቸው። አንዳንዶቹ በጦር ተገደሉ። አንዳንዶቹ በሕይወታቸው እያሉ፥ በቁመታቸው ልክ ያደገ የሰንበሌጥ ሣር በዙሪያቸው ታሰሮ በእሳት ተቃጠሉ። "የናሙጎንጎ ሰማዕታት" እየተባሉ ይጠራሉ። ናሙጎንጎ በሰማዕትነት የሞቱበት ቦታ ነው። ለእነዚህ ሰማዕታት የመታሰቢያ ሰፍራ በካምፓላ መሠራቱን፥ ታሪካቸውን የሚዘክሩ መጻሕፍትም መጻፋቸውን ነገሩኝ። መታሰቢያቸውን እንዲያሳዩኝ፥ ከመጻሕፍቱም እንድገዛ ወደ ቤተ መጻሕፍት እንዲወስዱኝ፥ የአገሩን ልጆች ውጥር አድርጌ ያዝኳቸው። የወሰደኝ ሰው አንድ መጽሐፍ ገዝቶ ሰጦታ ሰጠኝ። በመጽሐፉ የመጀመሪያ ገጽ ላይም እንደዚህ ብሎ ጽፎበታል -

"Brother Bekele,

You were gripped by the story of the martyrs. This is presented to you and to all who will read it in order that it may stir our faith anew.

God bless.

Warren Nyamugasin

Kampala, 20th Sept. 1991."

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ "ደቂቀ እስጢፋኖስ" ሰተባለው መጽሐፋቸው በጸፉት መቅድም፥ "እዚህ በሰደት በምኖርበት አገር እንዲት ኢትዮጵያዊት እማኝቼ ሰንወያይ በጨዋታችን ላይ የደብረ ብርሃን ልጅ መሆኗን ነገረችኝ። 'ከተማዋን የቆረቆሯት ዘርአ ያዕቆብ ናቸው ይባላል፤ መነኩሴ ነበሩ ወይ? ብላ ጠየቀችኝ። የሀገርሽን ታሪክ እንቺ ንገሪኝ እንጂ' ብዬ ግዴታዋን ካስታወስኳት በኋላ የማውቀውን ነገርኳት" ይላሉ። ከዚያም "የሚያውቁትን?" እንዲህ ሲሉ ነገሯት -

> "... በየካቲት 2 ቀን በዕለተ ዓርብ ወገራቸው። እነዚህን ከአይሁድ ጋራ እንድ የሚሆኑ ከሓዲዎች በወገራቸው በ38 ቀን እግዚአብሔር ሰለ እናቱ በ2 መንገድ ድንግል እመቤታችንና ሰለ ክቡር መስቀሉ መጋቢት 10 ቀን፥ በክርስቶስ መስቀል በዓል ዕለት፥ ሰኞ ሌሊት ድንቅ ተአምር ሠራ። በንጉሡ አደባባይ ላይና ከንጉሡ አደባባይ ሩቅ አስከ ሆነ ቀበሌ ድረስ ትልቅ ብርሃን ወጥቶ እንደ ኀርፍ ፈሰሰ ... በንጉሡ ሰፈር ታላቅ ደስታ ሆነ። ስለዚህ ያችን (አቦ የምትባለዋን) ቦታ ሁሉም ወደዳት፤ (ንጉሡ) ደብረ ብርሃን ብሎ ጠራት" ይላሉ።[1]

የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር፥ እንኳንስ በልጁ ደቀ መዛሙርት መወገር፥ በአረማውያንስ መወገር እንዲህ ደስ የሚሰኝ እምላከ ነውን?

> "ወዳጅህን ውደድ፤ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚያሰድዷችሁም ጸልዩ እላችኋለሁ። እንደ ዚህም በማድረጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ ... ወንድሞቻችሁን ብቻ እጅ የምትነሡ ከሆነ ከሌሎች በምን ትሻላላችሁ? አሕዛብስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን? ስለዚህ የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ" (ማቴ. 5፥43-48)

ያለን አይደለምን? ይልቁንስ በኢባ ብርሃን የሆነው፥ "ቀዳሜ ሰማዕት" አስጢፋኖስ በተወገረ ጊዜ እንደ ሆነው ዐይነት፥ ሰማያት ስለ ተከፈቱ፥ የእግዚአብሔርም ክብር ስለ ተገለጠ ነው ብንል ወደ እውነቱ እንጠጋምን? ይህን ያነሣሁት፥ በዩጋንዳ መታሰቢያ የተሠራላቸው "የከርሰቶስ ሰማዕታት" በእኛ አገር ደግሞ መሣለቂያ መደረጋቸው ገርሞኝ ነው።

ጸሎቴ፥ በደብረ ብርሃን ታላቅ ሪቫይቫል ተነሥቶ፥ "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላለ

ስም" ያለው የኢየሱስ (ዮሐ. 8፥12) ማዳን ለብዙዎች አውን አንዲሆን ነው። የሰዎችን ሕይወት በጨለማ ከመመላለስ ያላዳነ ብርሃን፥ በምን መስፈርት ነው "ድንቅ ተአምር" የሚባለው? "በጊዜው የሆነ ኮሜት (ሻራታም ኮከብ) በዚያ ዐልፏል፤ ብርሃኑ ከዚያ ኮሜት የመነጨ ነበረ" የሚል ታሪክም የሆነ ቦታ እንብቤአለሁ።

ወደ ፍጥሞ ጉዞዬ ልመለስ። ይዞኝ እንዲሄድ የተመደበልኝ ከቤተ ክርስቲያኗ ሽማግሎች አንዱ የሆነው ወንድም ወንድይፍራው ንጋቱ ነው። ሰኞ ማርች 22 (መጋቢት 13 ቀን) ከምሽቱ 12:30 ሰዓት ገደማ ላይ በፈሪይ (የሰዎች ማጓጓዣ አነስተኛ መርከብ) ተነሣን። በውስጤ ከኢትዮጵያ ይዤው በመጣሁት ጥያቄ ላይ እየጸለይኩ፥ በውጭዬ ደግሞ ከወንድም ወንድይፍራው ጋር እየተጫወ ትኩ፥ ከሌሊቱ 8:00 ሰዓት ላይ ፍጥሞ ገባን። ወዲያውም ከወደቡ አጠገብ ካለች አንዲት የእንግዶች ማረፊያ ውስጥ ሁለት አልጎች ያሏት አንዲት መኝታ ክፍል ያዝን እና ተኛን።

ከጠዋቱ 11:30 ላይ ከአንቅልፌ ነቃሁ። ወንድይፍራውን አንዳልቀሰቅሰው፥ ቀሰ ብዬ ከአልጋዬ ላይ ወረድኩ እና ተንበረከክሁ። ድምፄን አጥፍቼ፥ በልቤ ያለውን ሁሉ ለእምላኬ ነገርኩት። የምለውን ብዬ የጨረስኩ ሲመስለኝ፥ እዚያው በተንበረከክሁበት አንዳለሁ፥ የትራስጌ መብራቴን ወደማኑበበው መጽ ሐፍ እንደምታበራ አድርጌ አበራኋት እና ማንበብ ጀመርኩ። ላነብበው የጀመ ርኩት የመጽሐፍ ቅዱስ ከፍል የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ አንድ ነው። ድምፄን እንዳጠፋሁ፥ በውስጤ እንዲናገረኝ ወደ ጌታ አየተማጠንኩ፥ በጣም ረጋ ብዬ፥ ማንበብ ጀመርኩ። ቁጥር 11 ላይ ስደርስ የሆነ ኃይል አስቆመኝ። መቼስ "አስቆመኝ" ነው አንጂ ሌላ ምን ለማለት አችላለሁ? ያስቆመኝ፥ በእጄ ላይ በነበረው በቀ.ኃ.ሥ. ትርጉም " ... የምታየውን በመጽሐፍ ጽፈህ ወደ ... ላክ አለኝ" የሚለው ላይ ስደርስ ነው።

ያየሁት እንዳች ነገር ወይም የለማሁት እንዳች ድምፅ የለም። ሌላም ምንም የሆነ ነገር የለም። ልገልጸው የማልችለው፥ የሆነ ነገር ግን፥ በውስጤ ሆነ። እግ ዚአብሔር በቀጥታ ቢቃሉ እንደ ተናገረኝ ዐወቅሁ። "ጻፍ" ነው ያለኝ። ከዚያ መጽሐፉን ከደንኩ እና ጸለይኩ -

> "ሁኔታዎች ቢመቻቹልኝ እና ብጽፍ እወድ ነበር ... ነገር ግን እንዴት አድርጌ ነው የምጽፈው? ... በየትኛው ጊዜ ነው የምጽፈው? ... በቀጣና

> ሁለት የመሪዎች ስብስብ አባል ነኝ ... የመካከለኛው ቀጣና የሥራ እመ ራር ቦርድ ሰብሳቢ ነኝ ... ሁለቱም ጋ ነገሮች፥ አተኳሮች፥ አሉ ... በየትኛው የሰከነ አእምሮ ነው የምጽፈው? ... በዚያ ላይ የእግዚአብሔር ቃል እገልግሎት አለብኝ ... ጌታ ሆይ! ምንድነው ማድረግ ያለብኝ? ... ከአሜሪካ እስከምመለስ ድረስ በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ የሆነ ምሪት ከእንተ እፈልጋለሁ ..."

አልኩ። አለቀስኩ። ስናፈጥ፥ ምን ሰል፥ ወንድይፍራውን ሳልቀሰቅሰው አልቀረሁም።

ዕለተ ልደት፥ ዕለተ ሞት

ከግሪክ ወደ ቤልጅየም ነው የሄድኩት። በዚያ ሦስት አጥቢያ አብያተ ክርስቲ ያናት አሉ - በብራሴልስ፥ በሉቨን እና በአንቴወርፕ። ሦስቱም በአንድነት ሆነው መጀመሪያ በሉቨን፥ ቀጥሎ በብራሴልስ እና በመጨረሻም በአንቴወርፕ ተሰበሰብን። ለእኔ መኝታ የተያዘልኝ በሉቨን በሚገኝ የካቶሊክ ዩኒቬርሲቲ ሆስቴል ውስጥ ነው። ዓርብ መጋቢት 17 ቀን ምሽት በሉቨን የነበረንን ስብሰባ ስንጨርስ፥ ወንድም (አሁን መጋቢ) ጌታቸው ፈይሣ ለጉባዔው "አግዚአብሔር ለወንድም በቀለ ዕድሜ እንዲጨምርለት እንጸልይ" የሚል የጸሎት ጥያቄ አቀረበ። እርሱ ጉባዔውን እየመራ በተለይ ለእኔ እግዚአብሔር ዕድሜ እንዲ ጨምርልኝ ተጸለየ።

በሣልስቱ ዕሑድ ጠዋት ፀጉሬን ልስተካከል ከአንቴወርፕ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ሽማግሎች ወደ አረፍኩበት ሆስቴል መጥተዋል። ከሁለቱ እንደኛው፥ ዮሴፍ ተፈራ፥ ፕሮፌሽናል የፀጉር አስተካካይ ነው። እያስተካከለኝ እያለ፥ "ጋሽ በቄ፥ በትምህርትህ ውስጥ በ1948 ዓ.ም. የእስራኤል መንግሥት በተመሠረተ ጊዜ አንተ ተወልደህ እንደ ነበረ ነገርከን፤ ዕድሜህ ቀላል አይደለም ማለት ነው" አለኝ። እኔም "አዎን፤ ቀላልስ አይደለም፤ በጎርጎሳውያኑ አቆጣጠር በ1942 ዓ.ም. ነው የተወለድኩት" እያልኩ እየነገርኩት እያለሁ፥ ቀኑ በፈረንጆቹ አቆጣ ጠር መጋቢት 28 እንደ ሆነ ትዝ አለኝ። "ባይገርምህ ዛሬ እንዲያውም የልደት ቀኔ ነው" አልኩት። ነገሩ ልከ ከአፈ ከወጣ በኋላ፥ "ምን ያለሁት ሰው ነኝ? እስቲ አሁን ምን አስለፈለፈኝ?" አልኩ - በውስጤ። እርሱ ደግሞ ምንም እንዳልሰማ መስሎ ዝም አለ።

ፀጉሬን ተሰተካከዬ እንደ ጨረስኩ ገላዬን ለመሊቃለቅ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባሁ። እኔ ከሻወር እስከወጣ ድረስ ለካ ሁሰቱ ሽማግሎች ወሬውን ለሦስቱ አጥቢያዎች አዳርሰውት ኖሯል! የዚያን ዕሑዱ ፕሮግራም የሚካሄደው በእንቴ ወርፐ ቤተ ክርሰቲያን ነው። ሰለዚህም ከሉቨን ወደ እንቴወርፐ ተጉዘን፥ በዚያ ምሣ ለንበላ፥ ምናምን ለንል፥ የፕሮግራሙ ሰዓት ደረሰ። ፕሮግራሙን ከማሰጀመሩ ቀደም ብሎ፥ ወንድም ዮሴፍ "በትምህርትህ መካከል እንድ ወሥራ እምሰት ደቂቃ ትሰጠናለህ፤ የሻዩን ጊዜአችንን ያኔ ማድረግ እንፈል ጋለን። አብዛኞቹ ምዕመኖቻችን ከሌሎች ከተሞች ሰለሚመጡ፥ ትምህርቱ ካለቀ በኋላ ለመሄድ ይቸኩላሉ። ሰለዚህ ትምህርትህን እሚመችህ ቦታ ላይ ለሁለት ብትከፍለው ምን ይመሰልሃል?" አለኝ። "ችግር የለም" አልኩት።

የፕሮግራሙ መሪ እርሱው ሰለ ነበረ፥ ለጉባዔውም ይህንኑ ተናገረ። እኔም ትምህርቴን ወገቡ ላይ አቋረጥኩና ጊዜውን ለእርሱ መልሼ ሰጠሁት። ዮሴፍም ወጣና -

> "እኛ እንቴወርፐኖች በጣም ዕድለኞች ነን ... እግዚአብሔር በየጊዜው ውድ ውድ የሆኑ ዕድሎችን ይሰጠናል ... ባለፈው ጊዜ እንደምታስታ ውሱት ፓስተር አሳየኸኝ ከዚያ ከባድ ሕመም ጌታ ከፈወሰው በኋላ የመጀመሪያውን አገልግሎት የሰጠው በእንቴወርፐን ነበር ... እና ያኔ ደስታችንን እና ምስጋናችንን በተለየ ሁኔታ ገልጸን ነበር ... ዛሬ ደግሞ የፓስተር በቀለ የልደት ቀን ነው ... እና ደስታችንን እና ምስጋናችንን እንደዚሁ በተለየ ሁኔታ እንገልጻለን ... እኅቶች ወደዚህ ትመጣላችሁ"

አለ። "ዛሬ ደግሞ" ሲል ነው ነገሩ የገባኝ። ግን ምን ለማድረግ እችላለሁ? "ካፍ የወጣ ካፋፍ።" የእነ ዮሴፍን እርፍና ግን አደነቅሁ። ዕልል ተባለ። መዝሙር ተዘመረ። እግዚአብሔር ተመሰገነ። ኬክ ቆረሰኩ። ተጸለየልኝ። ብዙ ፎቶግራፎች አብረን ተነሣን። ፕሮግራሙ ካለቀ በኋላ ሁሉ ከብዙዎቹ ጋር እየተጫወትን እዚያው አብረን ዘገየን። ከዚያ ሰንወጣ ደግሞ ጉዞአችን ወደ ብራሴልስ ወደ ዘማሪ ሚራክ ቤት ሆነ። ሚራክ እራት ጋብዞኛል። እዚያ ለንደርስ እራት የተጋበዙት ሰዎች ብዙ እንደ ሆኑ እየሁ። ከእራት በኋላ፥ በዘማሪ ሚራክ ቤት ሌላ የልደት ፓርቲ ተደረገ። እንደ ገና ዕልል ተባለ። እንደ ገና ተዘመረ። እንደ ገና እግዚአብሔር ተመሰገነ። እንደ ገና ኬክ ቆረስኩ። እንደ ገና ተጸለየልኝ። እንደ ገና ፎቶግራፎች አብረን ተነሣን።

ይኸ ሁሉ ተከናውኖ፥ ወደ ሉቨን ተጉዘን፥ መኝታ ክፍሌ ስገባ ከሌሊቱ 7፡00 ለዓት አልፏል። የደከመኝ ቢሆንም እንኳን፥ ጌታን ለማመሰገን ተንበረከክሁ። ባለፈው ሳምንት፥ ልክ በዛሬው ቀን፥ የገነት ልደት ነበር። ከእቴና በኢ-ሜይል "እንኳን እደረሰሽ" ብያታለሁ። የእኔውም ከእንድ ሳምንት በኋላ እንደ ሆነ ያን ጊዜ አሰታውሼው ነበረ። ቀኑ ሲደርስ ነው የረሳሁት። ያን ዕለት ጠዋት፥ ዮሴፍ ፀጉሬን እያሰተካከለኝ እያለ "ጋሽ በቁ፥ ዕድሜህ ቀሳል አይደለም ማለት ነው" ባይለኝ ኖሮ፥ ላሰታውሰው አልችልም ነበር። የሆነውም ሁሉ አይሆንም ነበር።

ከዛሬ በፊት ሁለት ጊዜ ብቻ ነው የልደቴ ቀን ታስቦ የሚያውቀው። 50 ዓመት የሞላኝ ጊዜ፥ እኔው እራሴ በቤቴ የምሰጋና ፕሮግራም አዘጋጅቼ እና በቤተ ክርሰቲያን ውሰጥ ያሉ የቅርብ ወዳጆቼን ጠርቼ አብረን አምሽተናል። 60 ዓመት በሞላኝ ጊዜ ደግሞ፥ በሆነ አጋጣሚ ዕድሜዬን ያወቁ የቤተ ክርሰቲያን ለዎች በዶክተር ኢንጅኔር ዳንኤል ቅጣው ቤት የምሰጋና ፕሮግራም አዘጋ ጅተው ነበር። የዛሬው ሦስተኛው መሆኑ ነው።

ተንበርከኬ፥ ጌታን -

> "በእውነት ዛሬ surprise እድርገኸኛል። sense of humourህም አስገር ሞኛል። 68ኛውን የልደቴን ቀን በዚህ ዐይነት - ከሦስት አብያተ ክርስ ቲያናት ምዕመናን ጋር፥ ደግሞ በቀን ሁለት ጊዜ - ሰለ አከበርከልኝ አመሰ ግንሃለሁ። 'ሰፈልግ፥ እንደዚህም አደርጋለሁ' እያልከኝ ነው አይደል? Thank you፥ Lord"

አልኩት እና ተኛሁ።

በሕፃንነቴ እንጥሌን አራት ጊዜ እንደ ተቆረጥሁ ሰምቻለሁ። ቶንሲሌም ብዙ ጊዜ ተቧጥጧል። እና እኔ እንጥልም፥ ቶንሲልም የለኝም። ሰለዚህ በልጅነቴ ሰናገር በሰርኔ ነው እናገር የነበረው። እንደ መነፋነፍ ያደርገኝ ነበር ማለት ነው። በተለይ መጽሐፍ በማነብበት ጊዜ፥ አባ ወልደ ማርያም ናቸው "በትናጋህ! በትናጋህ! ፊደሱን እርገጠው! እርገጠው!" እያሱኝ በሰርኔ ከማንበብ የመለሱኝ።

ዕልፎ ዕልፎ ደግሞ ከባድ ትንታ ያጋጥመኛል። ከልጅነቴ ጀምሮ ነው ትንታው የእንጥል እጦት ውጤት እንደ ሆነ የተነገረኝ እና እኔም "እሜን" ብዬ የተቀ

በልኩት። ሳይንሳዊ ምክንያቱን ያስረዳኝ ሰው የለም። እኔም፥ እስከ ዛሬም ድረስ፥ የነገሩን እውነትነት ለማረጋገጥ ምንም ጥረት አላደረግሁም። እኖ በ68ኛው የልደት ቀኔ ሌሊት "ትን" አለኝ። ከዚያ በፊት ብሎኝ በማያውቀው ዐይነት ከፉኛ "ትን" አለኝ።

በጣም ስላመሸሁ፥ ደግሞም በጣም ደክሞኝ ስለ ነበረ፥ በከባድ እንቅልፍ ውስጥ ነበርኩ። ዳሩ ነቅቼ እያለሁ ሆኖ ቢሆን ኖርስ ምን ለማድረግ አችል ነበር? በእንቅልፍ ልቤ ውስጥ ሆኜ፥ መንፈራፈሬ ይታወቀኛል። እጆቼ እና እግሮቼ "ፍር፥ ፍር" ሲሉ እንደ ሰመመን ይታወቀኛል። ያለ ጥርጥር፥ በሆነ ያህል ርቀት የሕይወትን ጠርዝ ጥሻለሁ። ከሄድኩበት ለመመለሴ ምክንያቱ ከትናንትና በስቲያ "ዕድሜ ጨምርለት" ተብሎ የተጸለየው ጸሎት መሆን አለበት።

ተነሣሁ እና ተንበረከክሁ። ተንበርከኬም -

> "ጌታ ሆይ ... ለምን መለስከኝ? ... አንድ ደቂቃም አይወስድም ነበር እኮ! ... I had almost crossed it እኮ! ... ለምን መለስከኝ? ... የሚሠራ ሥራ አለ? ... እጽፋለሁ? ... እንግዲያው፥ ከዚያ ሥራ ጋር አንተው እራስህ አገናኘኝ"

አልኩት። የሆነውንም ነገር ለማንም ሳልተነፍስ ወደ ኢትዮጵያ ተመለስኩ።

የሚናገር እግዚአብሔር

ሐሙስ ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ እኅት (አሁን ወንጌላዊት) ገረመች ወርቁ ወደ ቢሮዬ መጣች። ማታ ያየችውን ሕልም ልትነግረኝ ነው የመጣችው። "በጣም ትልቅ ፈረስ ... መልኩ ሽሮአማ የሆነ ፈረስ ... በደንብ የተጫነ ፈረስ ... በኮርቻው ላይ የተጣለው ግላስ በጣም የሚያምር ፈረስ አያለሁ ... በፈረሱ ላይ እንተ ተቀምጠህበታል ... ሆኖም ፈረሱ የሚሄደው ቀስ እያለ፥ በሰው ፍጥነት ነው ... ነቃሁ" አለችኝ።

"ምን ተረዳሽ?" አልኳት።

"እዚያው ሕልሙ ውስጥ ሆኜ ... ጋሽ በቂ ምን ማለቱ ነው? ... እንደዚህ የተጫ ነውን ፈረስ እንዴት በሰው ፍጥነት ያስሄደዋል? አላለሁ። ሕልሙን ለወንድም

(በኋላ መጋቢ) ዘርጋው ስትነግረው፥ እርሱም 'እዬ! ምነው ሽምጥ ቢጋልበው ኖሮ?'" አለኝ አለችኝ።

እርሷ እየተናገረች፥ እኔ በውስጤ እየተገረምኩ ነበረ። ይህ የፈረስ ሕልም ሁለተኛዬ መሆኑ ነው። የመጀመሪያው ነሐሴ 01 ቀን 1991 ዓ.ም. እኔው እራሴ ያየሁት ነው። ምዕራፍ አንድ ውስጥ አንሥቼዋለሁ። ልዩነቱ ያ ፈጽሞ ሴጣ ሲሆን፥ ይኸኛው ግን በደንብ የተጫነ መሆኑ ነው። ያንን ሕልሜን ለገረመች ነገርኳት። "እግዚአብሔር ያልደበቀሽን እኔ ለምን እደብቅሻለሁ?" አልኳት። ከአስተዳደራዊው የአመራር አገልግሎት ለመውጣት እያሰብኩ እንዳለሁም አጫወትኳት እና "ጸልዩልኝ" አልኳት። እኔም ጸለይኩ - "ጌታ ሆይ፥ የመጀመሪያው ፈረስ ሕልም የተፈጸመው ከሰምንት ዓመታት በላይ በኋላ ነው። አባከህን ይኸኛው የዚያኛውን ያህል አይቆይብኝ።"

ይህ በሆነ በማግሥቱ፥ ማለትም ግንቦት 20 ቀን ጠዋት በ11፡00 ሰዓት ከቤት ወጥቼ "ጆግ" እያደረግሁ እያለሁ፥ የቆየ ጥያቄዬ በውስጤ ተመልሶ አገኘሁት -

> "ወደ አሜሪካ ከመሄዴ በፊት አሳቤን በጽሑፍ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስታውቃለሁ ... የጊዜዬን 3/4ኛ ለጽሑፍ ሥራ እንዳውለው እንዲፈቅዱልኝ እጠይቃቸዋለሁ ... የገረመች ሕልም ፈረሱን በሰው እርምጃ ሳይ ሆን፥ በፈረሰ ፍጥነት እንዳስሄደው የሚጠይቅ ነው ... እየተጎተትኩ አስቸገርኩት። ጌታ ሆይ፥ ተመስገን፤ ከብር ሁሉ ለሰምህ ይሁን፤ አሜን።"

ደብዳቤዬን ጽፌ ለቤተ ክርስቲያን ያስገባሁት ሐሙስ ግንቦት 26 ቀን ከሰዓት በኋላ ነው። አበበች ሕልሟን በነገረችኝ ልክ በሦስተኛው ወሩ። በማስታወሻዬ ላይ የጻፍኩት እንደሚከተለው ይነበባል -

> "ጌታ ሆይ፥ ወደዚህ ውሳኔ ስለ አደረስከኝ አመሰግንሃለሁ። ለእኔ ለደካማው እንደሚገባኝ አድርገህ ስለ ተናገርክ አመሰግንሃለሁ። ደቡዳ ቤዬ መሪዎቼን እንደምታስደነግጣቸው አገምታለሁ። አልፈርድባቸውም። ሁሉን ግን ለእንተ አሳልፌ አስጣለሁ። እነ ወንድም ... በዚሁ ጉዳይ ላይ ሊጸልዩ አሁን ይገናኛሉ። እኅት ... ም እንድትጸልይ አሁን እደውልላታለሁ። አንተ ከእኔም፥ ከቤተ ክርስቲያኔ መሪዎችም ጋራ ሁን። በሰማይ የሆነችው ፈቃድህ በሕይወቴ እና በአገልግሎቴ ትሁን። በኢየሱስ ስም፥ አሜን።"

እነ ወንድም ... በደብዳቤዬ ኮፒ ላይ እጆቻቸውን ጭነው ሲጸልዩ የመጣ መልእክትም አለ። ከሦስቱ ወንድሞች እንዱ ደውሎ እንደ ነገረኝ፥ እንደኛው "እግዚአብሔር ተነሣ፤ እግዚአብሔር ተንቀሳቀሰ፤ እንተም ተነሣ፤ ተንቀሳቀስ" ነው የሚለው። ሁለተኛው፥ በይዘቱ እንደ እንደኛው ሆኖ፥ ትንሽ ከዚያ አለፍ የሚል ነገር አለው። ወንጌላዊት ፍቅሬ በቀለ ደግሞ ግንቦት 28 ያየችውን አስገራሚ ሕልም በማግሥቱ እጫውታኛለች። በይዘቱ እንደ ወንጌላዊት ገረመች ሕልም ሆኖ፥ እሱም ከዚያ ትንሽ አለፍ የሚል ነገር አለው። ለውሳኔዬ ትከከለኛነት ማረጋገጫ አድርጌ ነው የወሰድኩት። ስው ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መሆኑን እርግጠኛ ሲሆን የሚሰማው ደስታ ነበር የተሰማኝ።

ሰባት ወጣ፤ ሰባት ገባ

ለቤተ ክርስቲያን በጻፍኩት ደብዳቤ በጣም ግልጽ ለመሆን ነው የሞከርኩት። ግልጽ ለመሆን ባደረግሁትም ሙከራ፥ የሚቀረኝ ዕድሜ ሰባት ዓመት እንደ ሆነ ጠቅሼ ነበር። ለራሴ ከወሰንኩት የዕድሜ ጣራ ላይ 68 ሲቀነስ የሚቀረው ማለት ነው። ጋሽ መሹ (ወንድም በዛብህ) ረቂቁን አንብቦ፥ "ሰባት ዓመት ያል ከውን እውጣው፤ እሱ በእንተ እና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ነገር ነው። ለሽማግሌቹ አያስፈልጋቸውም" አሉኝ። እኔ ደግሞ "አላወጣውም" አልኩት። ትንሽ ተሟገተኝ እና ከዚያ ተወኝ። ከእርሱ በኋላ ደግሞ ለገረመው ሰጠሁት። ለገረመው እንኳን የሰጠሁት እንዲያትምልኝ ነበር። ግን "ልታነበውም ትችላለህ" ብዬዋለሁ እና እነበበው። ገረመውም "ሰባት ዓመት ያልከውን ብታወጣው" አለኝ። ሁለት ሲሆኑብኝ ጊዜ "እሺ" አልኩ እና እወጣሁት።

ረቡዕ ሰኔ 09 ቀን ወደ አስተን፥ ቴከሳስ፥ በረርኩ። በሳምንቱ መጨረሻ ላይ በዚያ በሚኖራቸው ኮንፈረንስ ላይ ተናጋሪ ነኝ። በ19 ደግሞ፥ በዚያው በአስተን፥ ታናሽ እኅቴ አዘነጋሽ ታገባለች። በእርሷ የቃል ኪዳን ሥነ ሥርዓት ላይ ኩተገኘሁ በኋላ፥ በ22 ወደ ዳላስ፥ ቴከሳስ፥ በረርኩ። ከ23 እስከ 27 ባለው ጊዜ ደግሞ በዚያ የጾም እና የጸሎት ኮንፈረንስ አለ። ኮንፈረንሱ የሚያልቀው ዕሑድ፥ በእነርሱ አቆጣጠር ጁላይ 04 ነው። ጁላይ 04 በአሜሪካ "የነጻነት በዓል" (INDEPENDENCE DAY) ነው። ያን ዕለት ሁለት ፕሮግራሞች ናቸው የነበሯቸው።

የማስተምረውን ትምህርት በከሰዓት በኋላው ከፍለ ጊዜ ላይ ጨረስኩ። ከዚያ ጉባዔው ቆሞ፥ እኔ ተንበርክኬ እና ሽማግሌቹ እጅ ጭነው ተጸለየልኝ። ልክ ጸሎቱ እንዳለቀ በቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ፥ ቢፓስተር በድሉ በኩል እጅር መልእክት መጣ -

> ሌላ ሰባት ዓመት እለ ... ተጽዕኖህ፥ INFLUENCEህ፥ የሚጨምርበት አዲስ ምዕራፍ ይሆናል ... በጥያቄ የምትጠብቀው ላይሆን በፈቃዴ ዕውቀት የምትራመድበት ... አዲስ ምዕራፍ ነው ... እመራሃለሁ ... እጠብቅሃለሁ

ይላል። ከዚያ የጌታ እራት ጊዜ ነበረን። በመጨረሻም ሁላችንም እዚያው በአንድነት እራት በልተን ተለያየን። አንባቢው መጋቢ በድሉ ታንቁን ከምዕራፍ አንድ ንባቡ ያስታውሰዋል። እርግጥ ምዕራፍ አንድ ውስጥ ዘማሪ ነው የነበረው።

በጣም ከመደነቄ የተነሣ፥ ያንን ሌሊት ሳልተኛ ነው ያደርኩት ለማለት እችላለሁ። ያስደነቀኝ አንደኛ በመልእክቱ ውስጥ "ሰባት ዓመት" መጠቀሱ ነው። የጋሽ መሹን እና የወንድም ገረመውን ፈቃድ አፈጽም ብዬ "ከዕድሜዬ የሚቀረኝ ሰባት ዓመት ነው" የሚለውን ከደብዳቤዬ ውስጥ አውጥቼው ነበር። ይኸው ባለቤቱ መልሶ እስገባው። ሁለተኛው ያስደነቀኝ ነገር "ዕድሜዬ በ75 ዓመት ጸንቶልኛል ማለት ነው" የሚለው አሳብ ነው።

"ጌታ ሆይ፥ ስለ ተናገርከኝ በጣም ደስ ብሎኛል። የወሰንኩት ውሳኔ (ማመልከቻ ማስገባቴ) ያንተ ፈቃድ መሆኑን ማወቄ በጣም ደስ ብሎኛል። ስምህ ይባረክ።" በማግሥቱ ነገሩን ለፓስተር በድሉ፥ ለዶክተር ከፍሌ አድማሱ እና ለባለቤቱ ለእኅት መርጌ ኡሉማ እጫወትኳቸው። መርጌ ብቻ እንደ ተቃወመችኝ ነው ትዝ የሚለኝ። ወንዶቹ ዝም ዝም ያሉ ነው የሚመስለኝ። "ከእንግዲህ በምድር ላይ የሚቀርህ ዕድሜ ሰባት ዓመት ብቻ ነው" መባል ያስደነግጣል እንዴ? "ሰባት ቀን ብቻ ነው" ብሎኝ ቢሆንስ ኖሮ? አይችልም ነው? ወይስ ይችላል፥ ግን አይልም ነው?

ከአሜሪካ የተመለስኩት ሐምሌ 29 ቀን ነው። ስመለስ ብዙ ወሬ ሲወራ እንደ ለነበተ ሰማሁ። "አይመለስም" ያሉ ነበሩ። "ይመለሳል፤ ግን ቤተ ክርስቲያኗን ይለቅቃል" ያሉም አሉ። "ሌላ ቤተ ክርስቲያን ሊከፍት ነው፤ ሚኒስትሪ

ሊጀምር ነው፤ በኢትዮጵያ የአውሮፓ አብያተ ክርስቲያናት ተወካይ ሆኗል፤ ወዘተርፈ" በማለት በእርግጠኛነት የተናገሩም ሞልተዋል። ወሬውን ከየት ይሆን የሚያመጡት? ጉድ እኮ ነው!

ወንጌላዊ በለጠ ሀ/ጊዮርጊስ "እኔ የማውቀው በቀለ ከሆነ፥ ወይም ደግሞ ጨርቁን ጥሎ አብዶ ካልሆነ በስተቀር፥ እንደዚህ አያደርግም" አልኳቸው አለኝ - ለነገሩት ሰዎች። እንደሚታወቀው፥ በአኛ ቤተ ክርስቲያን ወቅቱ አንዳንድ ሰዎችን ሰፍራ ያሰለቀቀ ስለ ነበረ፥ እንደዚያ እንደዚያ ካሉት ሁኔታዎች በመነ ሣት ይመስለኛል አንዳንዶች ለወሬው ከብደት የሰጡት። ምናልባት ሊፈረድ ባቸው አይገባም ይሆናል።

ሐሙስ፥ ነሐሴ 12 ቀን የቤተ ክርስቲያኔ መሪዎች ስለ አስገባሁት ማመልከቻ አነጋገሩኝ። ከጊዜ አጡት የተነሣ በማመልከቻዬ ላይ አንዳች ሳይሉ ነበር ወደ አሜሪካ የሄድኩት። የተለያዩ ጥያቄዎችን ጠየቁኝ። ሁሉንም እንደ አግባብነቱ መለስኩ። ያንን ሁሉ ወሬ ንቀው፥ ወይም ደግሞ "እናይ ኋላ" በሚል በልባ ቸው ይዘው፥ የጠየቅሁትን ዕድል ሊሰጡኝ ፈቃደኞች ሆኑ። ቀጥዬም ለአጥቢ ያችን የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ባለን ሳምንታዊ የጸሎት ፕሮግራም ላይ ጊዜ አንዲሰጠኝ ጠይቄ፥ ሁኔታውን በዝርዝር አሰረዳኋቸው። ደሰ አላቸው። ጸለዩልኝ። እግዚአብሔርን እጅግ አድርጌ አመሰገንኩት።

ለማናቸውም ቃሌን በተቻለ ፍጥነት በተግባር ማሳየት መልካም እንደሚሆንም አሰብኩ። ለረዥም ጊዜ ያሰተማርኩት፥ ብዙ ዝግጅት የማይጠይቀኝ፥ ሕዝቡም የሚወደው እና በመጽሐፍ መልክ እንዲዘጋጅለት በተደጋጋሚ ሲጠይቀኝ የነበረ፥ ትምህርት አለኝ። ተጽፎ፥ የአርትአት ሥራ ተሠርቶበት፥ ከአገር ውሰጥ እና ከውጭ ሰድሰት ሰዎች አንብበውት እና አሰተያየት ሰጥተውበት፥ አሰተያየ ታቸው ተካትቶ፥ ለቤተ ክርሰቲያን መሪዎች ቀርቦ እና ተፈቅዶ፥ ከዚያም ወረፋ ተጠብቆ እና ታትሞ፥ የምረቃ ቀን ተቀጥሮለት፥ በሰምንት ወራት ተኩል ውስጥ ለገባያ ደረሰ - "ከሌሊቱ ሰንት ሰዓት ነው?"

ሲያበቃ፥ በጣልቃ

ከእንግዲህ ወዲህ፥ እግዚአብሔር በሕይወቴ ጣልቃ ከሚገባባቸው ሁኔታዎች ውስጥ፥ ቢያንስ ሰለ አንዱ በእርግጠኛነት ዐውቃለሁ። እርሱም ጌታ ወደ አራሱ በሚጠራኝ ጊዜ የሚሆነው ነው። ዕድሜዬ 75 ዓመት ሲሞላ፥ ወይም

ከዚያ በፊት፥ አለዚያም ከዚያ በኋላ፥ አንድ ቀን ይሆናል። አማኞች ብንሆን አላማኞች፥ ተዘጋጅተንበት ቢሆን አልተዘጋጀንበት፥ ሞት በሰው ሁሉ ሕይወት ውስጥ ትልቅ እና ጉልኅ የሆነው የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ነው። አርግጥ መጽሐፉ የአማኞችን ሞት፥ "ሞት" አይለውም። ስለ አስጢፋኖስ "እንቅ ላፋ" (ሐዋ. 7፥60)፥ ስለ ጳውሎስ "ተሰይቼ የምሄድበት ጊዜ" (2ጢሞ. 4፥6)፥ ስለ ጴጥሮስም "ይህን ምድራዊ ድንኳን ቶሎ ጥዬ እንደምሄድ" ነው የሚለው (2ጴጥ. 1፥14)። ሆኖም ሞት በሰው ሁሉ ሕይወት ትልቁ እና አይቀሬው የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ነው።

ይህንን ጣልቃ ገብነት ሲሆን ሲሆን ለማሰቀረት፥ ያንን ማድረግ እስከሚቻልም ድረስ ለማዘግየት የሚደረጉ ሙከራዎች ከጥንት ጀምሮ ነበሩ - በምርምሩም፥ በሌላ ሌላውም ሁሉ። ማሰቀረቱ እና ማዘግየቱ ያልተቻሉም እንደ ሆነ፥ አብረ ውት የሚመጡትን ሕማም እና ጻዕር ሲሆን ሲሆን ለማሰቀረት፥ ያንን ማድረግ እስከሚቻልም ድረስ ለመቀነስ በተጓዳኝ የሚደረጉ ሙከራዎችም ከጥንት ጀምሮ ነበሩ - በምርምሩም፥ በሌላ ሌላውም ሁሉ። የሞራል እና የሥነ ምግባር ወሰናችንን አስካልጣሱ ድረስም፥ በተለይ በምርምሩ መሰክ የሚደረጉትን ሙከራዎች የምንቃወምበት በቂ ምክንያት ላይኖረን ይችላል።

ይህ ሁሉ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ግን፥ በግልም ሆነ ግሎባዊ በሆነ ሁኔታ፥ ሊሆን ሰላለው ሰለዚህ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ማሰብም ሆነ መነጋገር መልካም ነው። ሊያንዳንዳችን አሁን እንዳለነው እንደዚሁ እንደማንቀጥለው ሁሉ፥ ዓለማችንም አሁን እንዳለችው እንደዚሁ አትቀጥልም። የቆየ ነገር፥ የቀረ ነገር አይደለም። እግዚአብሔር በዓለማችን ጉዳይ ጣልቃ ይገባል - ያለ ጥርጥር በቅርቡ፤ ምናልባትም በዚሁ ትውልድ ዕድሜ። በትልቁ መጽሐፍ ውሰጥ፥ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት፥ በጣም በዝርዝር እና በጣምም በግልጽ፥ የተሰጡን ምልክቶች ሁሉ አሁን እየተፈጸሙ ናቸው - በሚያሰገርም ፍጥነት - በዐይኖቻችንም ፊት።

"አላይም፥ አልሰማም" ለማለት እንችላለን። እንደዚያ በምንል ጊዜ ሁሉ ግን እንደ ለጎኗ ነው የምንሆነው። ሰጎን "የገደል ሰባሪ" የምታህል ወፍ ናት። ክንፍ ቢኖራትም ለመብረር አያገለግላትም። ረዣዥም እግሮች አሏት - ፈጣን እሯጭም ናት። ፍሰቨር ጠመንጃውን የደገነባትን አዳኝ ባየችው ጊዜ፥ ዐይኖቿ

የሚታየውን እንዳያዩ ታደርጋለች ይባላል - አሸዋውን ትጭር እና ጭንቅላቷን ከዚያ ውስጥ ትደብቀዋለች። "የማይታይ ነገር፥ የሌለ ነገር ነው" ትላለች - ለእራሷ። ትልቁ መጽሐፍ ስለዚህች ወፍ እንደዚህ ይላል፦

> "ሰጎን ከንፎቿን በደስታ ታራግባለች፤ ነገር ግን እንደ ሽመላ ላባዎች ሊሆኑ እይችሉም። ዕንቁላሏን መሬት ላይ ትጥላለች፤ እንዲሞቅም በአሸዋ ውስጥ ትተወዋለች። እግር እንደሚሰብረው፤ የዱር አውሬም እን ደሚረግጠው እታስብም። የእርሷ እንዳልሆኑ ሁሉ በልጆቿ ትጨከ ናለች። ድካሟም በከንቱ ቢቀር ደንታ የላትም። እግዚአብሔር ጥበብ ነሥቶአታልና፤ ማስተዋልንም አልሰጣትም። ለመሸምጠጥም ከንፎቿን ሰትዘረጋ፥ በፈረሰና በጋላቢው ትሥቃለች" (ኢዮ. 39፥13-18)።

ሰጎን እግዚአብሔር ጥበብን እና ማስተዋልን የነፈጋት ፍጥረቱ ናት። ሰው ግን ሰጎን አይደለም። ሰው እግዚአብሔር በመልኩ እና በአምሳሉ የሠራው፥ እጅግ ከቡር የሆነው ፍጡሩ ነው። እርሱ እራሱን እንደ ሰጎን ለማድረግ ቢሞክርም፥ እግዚአብሔር ግን በምንም ዐይነት እንደ ሰጎን አያየውም። ዕውቀት፥ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት የሰጠው፥ በምድርም ላይ እንደራሴው እድርጎ የሾመው፥ እንደ ሆነ ነው የሚያየው። ዕውቀት ቢጎድለው እና ኃላፊነቱን የሚወጣበት ዐቅም ቢያንሰው፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ረድኤት መጠየቅ ይችላል። እግዚአብሔርን ማን ብሎ እንደሚጠራው ባያውቅ እንኳን - ከ40 ዓመታት በፊት እኔ እንደ ጠራሁት - "እግዚአብሔር የምትባል ካለህ?" ብሎ ሊጠራው ይችላል። ለእኔ ጥሪ ምላሽ የሰጠ ጌታ፥ ለማንኛውም ሰው ጥሪ ምላሽ ይሰጣል። ለእኔ መን ገዱን የገለጠ ጌታ፥ ለማንም መንገዱን ይገልጣል።

"IT'S NEVER TOO LATE TO DO THE RIGHT THING" ይላሉ ኢንግሊዞቹ። "ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ምን ጊዜም ቢሆን ከልክ በላይ አልዘገየም" ማለታቸው ነው። "እሁንም ገና ጊዜ አለ" ማለታቸው ነው። ይሽ ደግሞ እውነት ነው። አሰትንፋሱ በአፍንጫው ውስጥ አስካለ ድረስ፥ ለማንም ሰው ተሰፋ አለ። ጌታ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በነበረ ጊዜ፥ እንደ እርሱው የተፈረደባቸው ሁለት ወንጀለኞች አብረውት ተሰቅለው እንደ ነበረ እናውቃለን። የእንደኛው - "ፈያታዊ ዘየማን" ይሉታል ዘመዶቼ - ነፍስ ግን፥ ከጌታ ነፍስ ጋር አብራ ወደ ገነት ገባች - መጨረሻዋ ደቂቃ ላይ። እንዴት እንደዚያ ሆነ?

ታሪኩ በሉቃስ ወንጌል 23፥39-43 ባለው ከፍል ውስጥ ተጽፎልናል። ሁለቱም በመሰቀል ላይ ተሰቅለው እያሉ፥ ጌታ በዚያ ወንጀለኛ ሕይወት ጣልቃ ገባ። መጀመሪያውን ሰውዬው ቢያበላሸውም እንኳን፥ መጨረሻውን ግን ጌታ አሳመረለት። በዚያች የመጨረሻ ደቂቃ፥ እንዱ ፍርደኛ በሌላው ፍርደኛ ሕይወት ውስጥ ጣልቃ መግባቱ - ለእኛ መልእክቱን ለማንበብ ዕድል ላገኘን ለዎች ታላቅ የምሥራች ነው። መልእክቱ ምንድነው? መልእክቱማ "እሁንም ገና ተሰፋ አለ!" የሚል ነው - ብቻ እኛ ያ ፍርደኛ እንደ እደረገው እናድርግ። እግዚአብሔርም ረድኤቱን ይለጠን።

* * *

ማስታወሻ

1. ጌታቸው ኃይሌ፤ "ደቂቀ አስጢፋኖስ"፤ ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ)፤ 1996 ዓ.ም. ገጽ 17፥ 53-54።

አባሪዎች

አባሪ አንድ

ለሐዋሳ ሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስቲያን 40ኛ ዓመት መታሰቢያ

በታተመ ልዩ መጽሔት ላይ የወጣ ጽሑፍ። ነሐሴ 1992 ዓ.ም.

ቀኑ የሥራ እንደ ነበረ ብቻ ነው ትዝ የሚለኝ። ያን ዕለት ጠዋት ከይርጋ ዓለም ወደ ሐዋሣ የመጣሁት ለሥራ ጉዳይ ነበርና። ብዙ ጊዜ እንደምናደርገው፥ ያን ዕለትም ከባልተቤቴ ጋር አብረን ነበር የመጣነው። እርሷ ዘመድ ልትጠይቅና በ"ፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን" በመካሄድ ላይ የነበረውን ኮንፈረንስ ልትካፈል። እኔ ደግሞ የመሥሪያ ቤቴን ሥራ ልከውን። በምሣ ሰዓት መጥቼ "ፒክ" ላደርጋት ተስማምተን፥ ቤተ ክርስቲያኑ በር ላይ "ድሮፕ" አድርጌያት፥ ወደ ሥራዬ ሄድኩ።

በሰምምነታችን መሠረት ሰባት ሰዓት ገደማ ላይ መጣሁ። ምኣችንን የትኛው ሆቴል ልንበላ እንደ ነበረ ያሰብነው አሁን አረሰቻለሁ። የባንኳን ቮልከሰዋገን መኪና ወደ "ዐረብ ሰፈር" በሚወስደው ዋና መንገድ ላይ ማሽከርከሬ ብቻ ነው የሚታወሰኝ። ትንሽ እንደ ተጓዝን፥ ገነት "በመንፈስ ቅዱስ ተሞላሁኮ!" አለችኝ። የመኪናዋን ፍሬኖች በእግሬ ወደ ታች አርግጥ፥ በእጅም ወደ ላይ ሸ-ጠ-ጥ አደረግ ኋቸው። መኪናዋ መሐል መንገድ ላይ "ቀጥ" አለች። በሩን ከፍቼ ወጣሁ። ሁለት እጆቼን ወደ ላይ እንሥቼ ሁለት ሦስት ጊዜ ዘለልኩ።

የ1968 ዓመተ ምሕረትዋ ሐዋሣ በእኔ ድርጊት ሊታወክ የሚችል ያህል የትራፊክ ብዛት ነበራት። በተለይም ደግሞ በዚያ መንገድ ላይ። በዚያች ጊዜ ግን ያ መንገድ ከጫፍ እስከ ጫፍ ድረስ ከባለ ፈረስ ጋሪ እና ከባለ ሞተር ተሸከርካሪ ሳይጸዳልኝ አልቀረም። ወደ ልቤ ስመለስ፥ ወደ መኪናዋና ወደ ገነትም ተመለስኩ።

"እስቲ እባክሽን ንገሪኝ ... እንዴት ሆነ?" አልኳት።

"ሰባኪው አቶ ረጋሣ ነበሩ ... አቶ ረጋሣን አወቅሃቸው? ... በስብከታቸው መሐል ስለ መንፈስ ቅዱስ ተናገሩ ... ከዚያም ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ሁሉ ባላችሁበት ቦታ ቁሙ አሉ ... ወደ ሁለት መቶ የምንገመት ሰዎች ተነሥተን ቆምን ... እጆቻቸውን ወደ እኛ ዘርግተው ጸለዩ ... በቃ"

"ከዚያስ?"

"ከዚያማ ብዙ ሰዎች በልሳን ተናገሩ"

"ማንም እጁን ሳይጭንባቸው?"

"አዎን ፤ ማንም እጁን ሳይጭንባቸው ... እቶ ረጋሣ እንዲያውም ከመድረኩም ላይ አልወረዱም ነበር"

"እንቺሳ? ... ማለቴ ... በልሳን ተናገርሽ?"

"እዎና!"

"እ? በቃ? በደንብ ተናገርሽ?"

"እንዴ? ... አዎን ... በደንብ ተናገርኩ ... እንዴት እንደ ሆነ ግን ... አንቺ? ..."

"እስቲ ልስማሽ?" ሳልላት የቀረሁ አይመስለኝም።

"ቤታችን ስንመለስ" ብላኝ ይሆናል።

ጌታ ካገኘን፥ ገነትና እኔ ያን ጊዜ ገና ሁለት ዓመት አልሞላንም። አልም ካለችው ዓለም ነበር የመጣነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከሰማን ደግሞ ጥቂት ወራት ቢሆኑን ነው። ከሰማንበት ከመጀመሪያው ቀን አንሥቶ በሕይወታችን በጣም ስንጠማው ነበርን። ከእኔ ይልቅ የገነት ጥማት እጅግ ይበረታ ነበር። "እኔ ይቆየኛና እባክህን እርስዋን ቶሎ አጠጣልኝ" ብዬ እስከምጸልይ ድረስ ነበር የጠናባት። ለዚህ ነው በመንፈስ ቅዱስ መሞላትዋን ስትነግረኝ ደስታው አራሴ ላይ የወጣው።

ከሐዋሣ የሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስቲያን ጋር ካሉኝ ብዙ ትዝታዎች መካከል አንዱን ነው የጠቀስኩላችሁ። ጌታ በኢትዮጵያ ዴንጤቆስጤአዊውን እሳት ማን ደድ ሲጀምር፥ ቤተ ክርስቲያናችሁ የመጀመሪያዋ ምድጃው ነበረች። ከዚህ ትዝ ታዬ ዐሥራ ሦስት ዓመታት ያህል ቀደም ብሎ ማለት ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ ለብዙ ዓመታት በዚህች ምድጃው የማገዳቸውን ማገዶች ብዛት የሚያውቀው እርሱ ባለቤቱ ብቻ ነው። የቤተ ክርስቲያንዋ መዝገብ ከሚያውቃቸው ይልቅ የማያውቃቸው በብዙ እጥፍ እንደሚበልጡ ግን አረጋግጥላችኋለሁ።

አንኳን ጌታ ለአርባኛው ዓመቱ ልደታችሁ በሰላም አደረሰን።

የእናንተው

በቀለ ወልደኪዳን

አባሪ ሁለት

Prophecy given by Cindy Jacobs

in Guatemala City, Guatemala, on October 30, 1998.

"The river is going to flow through Zimbabwe and I see a powerful torrent of water, a mighty rushing torrent, many fish. I see that there are strongholds in the church of division and the accuser of the brethren is active to discourage souls. An army of women with the Deborah anointing will march across the land. They will be like a net all over Zimbabwe with prayer. With a powerful anointing, the women first and men following. I see ancient thrones coming down, reconciliation between black and white, the spirit of racism which goes back further down to the tribes. I will use Zimbabwe like a jewel; she will help feed the world with beautiful produce. God will break the curse that came through civil war .... the curse will be broken. (I know nothing about Zimbabwe.) The land will produce beautiful beef. New factories will be built. Zimbabwe has the ministry of reconciliation that reunites the African people. The anointing of reconciliation will be all over Zimbabwe. Do not be afraid of the change. Although it looks like you are going backwards, I have a plan for you. Satan thinks he is advancing; but I will expose wickedness at high levels. Do not be afraid. Satan will try to bring war; this army will be used to stop war and bloodshed. A treaty will be written with other nations. Zimbabwe will be used like Switzerland to bring the healing of nations to break ancient things. Your nation came through trickery; but God will restore it. You will be given a piece of land, a beautiful place to pray. You will build a place to watch and pray. It will be like a compound with a place to sleep. The Annas will give their lives for intercession. Senior citizens will have places to stay and give their time to pray day and night."

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፍትሕ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Justice

ቁጥር: ደ/ገ/ጽ/ፍ/ሚ/ቁ/ሥ/ሥ/
Ref.No.
ቀን
Date: ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም.

ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት ህብረት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፣ ሰመተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅ ኮሚቴ አውቅና መስጠትን ይመለከታል

የኢትዮጵያ መ/አ/ህብረት በኢትዮጵያ ሙስሊም/ክርስቲያኖች እና በአስተዳ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክርስቲያን መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ሠላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ከማገር መሪዎችን ፈቃድ አግኝቶ በአንቀሳቃሽ ሳይ የሚገኝ መሆኑ ይታወቃል።

በዚሁ መሠረት በብረቱ ዘዘጋጀው ቢ.ጋር (TOR) መሠረት የህክርስቲያኒቱን መተዳደሪያ ደንብ የሚያዘጋጅ የኮሚቴ አባላት አውጥተም በአክርስቲያናት እና ከህብረቱ የተወከሉ መሆኑ ይታወሳል።

እኛም ከ3ቱም አካላት የተወከሉትን የክሚቴ አባላት ማለትም፡-

- ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክርስቲያን፡-
  1. ዶር ግርማ ተሰፋዩ
  2. ፓስ ንጉሴ ሽሽ
  3. ወሮ ዕለምን ብንቲ
  4. አቶ ዘለለው አርጋው
  5. አቶ አበበነህና ታደሰ
  6. አቶ ኢያሱ ቶሎሳ
  7. አቶ ሰለሞን ክፀጸ
- ከአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክርስቲያን፡-
  1. ፓስተር ብቀለ ወሸሻን
  2. አቶ ክበደ ሰሉ
  3. አቶ ወንድምአገኘው መርሻ
  4. አቶ ሽሰመ ተረሳ
  5. አቶ ስተማ ባዮ
- ከኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት፡-
  1. አቶ ሙሳኒ በላቸው
  2. አቶ መሰንቃ ዝውዴ
  3. ቀፀ ዓለሙ ሺጣን የተቀበልን መሆኑን እያሰታወን ኮሚቴው ኃላፊነቱን በታማኝነት እንዲወጣ አደራ ጭምር አናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ፕሮግ ዲ.ዶ
የኅብረተሰብ ሥነሀገ ዩጠቅ
ሥ/ ኃላፊ

ግልባጭ፣

- ለሚኒስትሩ ጽ/ቤት
- ለሕጋዊ አስተዳደር ጉዳዮች ሚ/ዴኤታ
- ዓ/ጠ/ፐብሊክ
- ለኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን
- ለአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን
  ለሰ/ጉ.አበባ
- ለክሚቴው አባላት በሙሉ
  ግለሰብ

የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን
መተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ የሚያዘጋጅ ኮሚቴ ቢ.ጋር (TOR)

በኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንና በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ከተፈጠረው አለመግባባት የተነሳ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሁሰቱ ተከፍሳ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን በሚል መለያዎች እንዳለ ይታወቃል። ለዚህ ችግር የሁለቱ ቤተ ክርስቲያናት ምዕመናን አቅጣጫ እንዲቀይሱ ጉ/ር 8 ቀን 2000 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፍትሕ ሚኒስቴር ባደረገው የሰዋሳላ ጉባኤ ጥሪ መሠረት ጉ/ር 21-22 ቀን 2000 ዓ.ም. ጉባኤ በሚኒስቴሩ ጽ/ቤት የጋራ ስብሰባ እንዲካሄድ ተወሰኗል።

ጉ/ር 12 ቀን 2000 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጉባሬት የሥራ አስኪያጅ ቦርድ ባካሄደው ስብሰባ ጉዳዩ ሁኔባሬቱ ጽ/ቤት ደረጃ እንዲታይ የፍትሕ ሚኒስቴር እንዲሰየቅ ቦርዱ ባሳለፈው መሠረት ዋና ጸሐፊው ኮሚኒስትሩ ጋር በመወያየት ከጉ/ር 21-22 ቀን 2000 ዓ.ም. የሚሰበሰበው ጉባኤ እንዲያከናውን የታቀዱትን ጉዳዮች የጉባሬቱ የሥራ አስኪያጅ ቦርድ ከሁሰቱም ወገኖች ጋር በመገናኘት ዘወጪ አከናውኖ ውጤቱን ለጉ/ር 18 ቀን 2000 ዓ.ም. ለፍትሕ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያቀርብ ከስምምነት ተደርሷል።

ዘዚህ መሠረት የጎባሬቱ የሥራ አስኪያጅ ቦርድ ሁለቱም ወገኖች ጉባሬቱ ጉዳዩን እንዲመለከተውና ፈቃደኝነታቸውን እንዲገልጹ በጽሑፍ ጠይቆአቸው፣ ሁለቱም ወገኖች በመስማማት መፍትሔ እንዲሰጥ በቃልና በጽሑፍ ማረጋገጫ ሰጥተዋል።

በመሆኑም የሚከተለው ቢ.ጋር (Terms of Reference) የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ለሚያዘጋጅ ኮሚቴ ተሰጥቷል።

1. ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የሚወከሉ ሰባት ሰዎች፣ ከአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የሚወከሉ አምስት ሰዎች፣ ከኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጉባሬት የሚወከሉ ሦስት ሰዎች የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ አዘጋጅ ኮሚቴ ሆነው ያገለግላሉ። (ቁጥር 8ን ይመልከቱ)

2. የክሚቴው ሊቀመንበርና ጸሐፊ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጉባሬት ቦርድ የሚሠየሙ ይሆናሉ።

3. ኮሚቴው የሚቀርጸው መተዳደሪያ ደንብ ይዘት የሚወስኑትን መረጋገጫዎች ያዘጋጃል። መረጋገጫዎቹንም በኢ.ሙ.ወ.አ. ቤተ ክርስቲያን 15 ሰዎች፣ ከአ.ሙ.ወ.አ. ቤተ ክርስቲያን 11 ሰዎች እና የጎባሬቱ ቦርድ በሚያንብቡት ጉባኤ ያጸድቃል።

4. ኮሚቴው አዘጋጀ መረጋገጫዎች መሠረት በማድረግ የቤተ ክርስቲያኒቱን መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል።

5. ኮሚቴው የደንበን ሪቂቅ ከኢ.ሙ.ወ.ኤ. ቤተ ክርስቲያን 15 ሰዎች፣ ከኢ.ሙ.ወ.ኤ. ቤተ ክርስቲያን 11 ሰዎች እና ለጎበረቱ ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ያቀርባል።

6. በተራ ቁጥር 5 መሠረት ሪቂቁን የተቀበለው አካል በደንቡ ላይ ተወያይቶ የታስማማበትን ሰነድ የኢ.ሙ.ወ.ኤ.ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ መርቶ እንዲጸድቅ ያቀርባል። ጠቅላላ ጉባኤውም ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንና ከአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የተውጣጣ ይሆናል።

7. በሚዘጋጀው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ምርጫ ያካሂዳል።

8. የሚከተሉት ሰዎች የኮሚቴ አባላት ሆነው ተሠይመዋል።

ከኢ.ሙ.ወ.ኤ. ቤተ ክርስቲያን

1. አቶ በለለው ዘርጋ
2. አቶ እስክንድር ታደሰ
3. ፓስተር ፍጹም መኮንን
4. ወ/ሮ ሰለሞን በንቲ
5. ዶ/ር ግርማ ተስፋዬ
6. ዶ/ር ዓለም ባዘዘው
7. ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ

ከኢ.ሙ.ወ.ኤ.ቤተ ክርስቲያን

1. ፓስተር በቀለ ወ/ኪዳን
2. አቶ ከበደ ሉሌ
3. አቶ ወንድማገኘሁ መርሻ
4. አቶ ሽለመ ተሬሳ
5. አቶ አተግ ባዞ

ከኢ.ሙ.ወ.ኤ.ጎበረት

1. ቁስ ዓለሙ ሹማ
2.
3.

9. የጊዜ ገደብ

ሀ. የኮሚቴ መመሠረትና የሥራ ድልድል እስከ *ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም*

ለ. የደንቡን መርቆዎች አዘጋጅቶ በቁጥር 3 ለተሠየመው አካል የማቅረቢያ ጊዜ እስከ *ሰኔ 5 ቀን 2000 ዓ.ም*

ሐ. መርቆዎችን በመተዳደሪያ ደንብ አነጋገቶ ረቂቅ ደንቡን በቁጥር 5 ለተመለከተው አካል ማቅረቢያ ጊዜ እስከ *ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም*

መ. የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ የሚጠራበት ጊዜ *ሰኔ 25-26 ቀን 2000 ዓ.ም*

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ
EVANGELICAL CHURCHES FELLOWSHIP OF ETHIOPIA
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
ADDIS ABABA - ETHIOPIA

ኢወአክሃኢ/ስ/459/2000
ታኅሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም.

ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፍትሕ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

እንኳን ለብርሃን ልደቱ በሰላም አደረሰዎ!

ጉዳዩ፡ የአርቆ ሂሳት ያገዘ ገደብ አንዲፈዘም ስለመጠየቅ

በቁጥር ኢወአክሃኢ/ስ/376/2000 ጎዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ለክቡር ሚኒስትር ባቀረብነው የኢትዮጵያና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ዜተ ክርስቲያን የማሻሻያ ሠነድ (TOR) ሂደቱ ሁሉ ተጠናቅቆ ታኅሣሥ 25-26 ቀን 2000 ዓ.ም. የጋራ ጉባኤ እንዲካሄድ ታስበና ታቅዶ ነበር።

እስከሁን ሂደቱ በመልካም ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን በንገልጽ በደስታ ነው። ይሁንና ሥራው ካተጀገው የበለጠ ጊዜ በመጠየቁ ከኢኮን በኋላ ሚኒስቴር መሥሪቤ የአንድ ወር ጊዜ እንዲፈቅድልኝና መልሡን እጠባ ከፍጽሚው እንድናደርግ ትብብርም እንዲደለኮን በትህትና እናሳስባለን።

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር

ዓለሙ ሹማ (ዶ/ር)

ግልባጭ፡
- ለኢ.ሙ.ወ.ኤ.ማኞች ቤተ ክርስቲያን
- ለኢ.ኦ. ሙ.ወ. አማኞች ቤተ ክርስቲያን
- [illegible]

የመተዳደሪያ ደንብ አተገባበርን አስመልክቶ የተዘጋጀ መመሪያ

የመግቢያ ሐሳብ

በኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንና በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክ ላለፉት አሥር ዓመታት በመካከላቸው በተነሳ አለመግባባት ምክንያት የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን በመሆን ሁለቱም ሕጋዊ ሰውነት ኖሯቸው ሲንቀሳቀሱ የቆዩ በመሆናቸው፡-

ዘመካከላቸው ያለ አለመግባባት ተወግዶ አንዲት የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ሆና እንድትቀጥል ሲሞክሩ የነበሩ የእርቅ ሂደቶችን ለማለካት ከተደረጉ ሙከራዎች አንዱ በሆነው በአሁኑ ጊዜ በአ/ወ/አ/ክ/ጎበረት አደራዳሪነት እየተሞከረ ባለው የእርቅ ድርድር ሁለቱም ወገኖች የጋራ መተዳደሪያ ደንብ ቀርፀው ያቀረቡት ተቀናጅቶ በሥራ ላይ ለማዋል ዝግጅት እየተደረገ በመሆኑ፡-

የተዘጋጀው መተዳደሪያ ደንብ ዝርዝር ጉዳዮችን በሙሉ ስለማይዝ ዝርዝር መመሪያዎችን፣ ውስጠ ደንቦችንና ሥልታዊ አቅድን ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ከአሥር ዓመት በላይ ሁለቱም የተደራጁበትን አደረጃጀት ወደ አንድነትና ውኅደት ለማምጣት በጠቅላላ ጉባዔ የሚጸድቅ መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቷል።

1. በዚ.ጋሩ /TOR/ መሠረት ጠቅላላ ጉባዔ ተወክሮ በእንድ ሕጋዊ ፈቃድና በእንድ መተዳደሪያ ደንብ የምትመራ አንዲት የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መሆኗ እንዲረጋገጥ።
2. የተዘጋጀ መተዳደሪያ ደንቡን ለማጽደቅና መሪዎችን ለመምረጥ የሚደረገው የጠቅላላ ጉባዔ አባላት ጥሪ ከዚህ ቀደም የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር ሲጠራ ባዘጋጀው አባላት ቁጥር መጠን እንዲሆን።
3. ጠቅላላ ጉባዔው ደንቡን መርምሮ ሲቀበል ላለፉት አሥር ዓመታት የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ተለያይተው ሲንቀሳቀሱ በነበረ ጊዜ የነበሯቸው አሠራሮች፣ ልምዶች፣ ሲሥራ የቆጠሯቸው የሰው ኃይል፣ ያፈሯቸው ንብረቶችና ከሌላ ወገን ጋር የገቧቸው ግዴታዎች መኖራቸው ይታወሳል። በተለይም በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክ የነበረውን ሁኔታ ማስተ፡-

   1. የቤት ኪራይ ሁኔታ
   2. የነቡት ልዩ ልዩ ግዴታዎች

      ለምሳሌ፣ የቤት ግንባ፣ የልማት ስምምነቶች እና ሌሎችም

   3. በሂደት ላይ ያለው የአንልጋዮችና የሠራተኞች ሁኔታ ተዘዉን ማጣሪያ ተደርጎበት መፍትሔ እንዲሰጥ።

      እነዚህ አሠራሮችን ወደ አዲሱ የጋራ ደንብ ለማምጣት ጊዜ የሚወስድ መሆኑን ጠቅላላ ጉባዔ በማመን ውስጥ አስጉበዶ ኃላፊነት በመውሰድ የNormalization ወቅት ወስኖ ጉዳዩ ተግባራዊ እንዲሆን እንዲያደርግ ጠቅላላ ጉባዔ ኃላፊነት ለአገር አቀፉ ሥ.አ.ደ. እንዲሰጥና ከአዲስ አበባ ልዩ ቀጠና ጋር ክትትል እንዲያደርግ።

4. አዲሱ መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ያሉት ጸሎት ቤቶች የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንነት መሥፈርት የሚያሟሉ በአጥቢያነት ተደራጅተው በንውስ ቀጠና/ ዘንውስ ክልል እና በቀጠና/ክልል የሚደራጁበትን መንገድ በNormalization ሂደት ውስጥ እንዲመቻች። በኖርማላይዜሽን ጊዜ ውስጥ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል ልዩ ቀጣና ሆኖ እንድተሰራ ይሆናል።
5. የኖርማላይዜሽን ጊዜ ሲያበቃ የአዲስ አበባ ልዩ ቀጣና መሆኑ ቀርቶ በኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይደራጃል።
6. ከአ/ወ/አ/ክ/ጎበረት፣ ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክና ከአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክ የቀረቡ ዝርዝር ሰነዶች በጠቅላላ ጉባዔ ሰሚመረጠው አመራር ከአ/ወ/አ/ክ/ጎበረት ይሰጣል።

ለኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ
ከአስማሚና መተዳደሪያ ደንብ አርቃቂ ኮሚቴ የቀረበ ሪፖርት
የካቲት 14-15 ቀን 2000 ዓ.ም
ደብረ ዘይት

ኢየሩሳሌም እንዲሆ ለሰኞ ‹‹በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፣ ነፍሴም በአምላኬ ሐሴት ታደርጋለች። የሰበዘ አክሊል እንደሚደፋ ወንድ ሙሽራ፣ በጌጣጌጥም እንዳሸበረቀች ሴት ሙሽራ አድርጐ የመዳንን ልብስ አልብሶኛልና፣ የጽድቅንም መጐናጸፍያ ደርቦልኛል። ምድር ቡቃያዎችን እንደምታበቅል፣ የአትክልት ቦታም ተክሎችን እንደምታሳድግ ጌታ እግዚአብሔርም ለሕዝቡ ጽድቅን ለሚያሥጐናጽፍ፣ አሠባብ ሁሉ ያመሰግኑታል።›› (ኢሳ. 61:10-11)

1. በጌታ የተወደዳችሁ የዚህ ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ መልእክተኞች፣ የክብር እንግዶችና እንልጋዮች። ይህንን ጉባዔ ልዩ የሚያደርገው ላለፉት አሥር ዓመታት ከተራጠረ አለመግባባት የተነሳ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ተብለው በመክፈል ሲከናወኑ የቆየው አሠራርና አመራር አብቅቶ አንዲት የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን <u>በአንድ መተዳደሪያ ደንብና በአንድ ሕጋዊ ሰውነት እንድትመራ ለማድረግ የሚያስችል ሥራ ተሠርቷ</u> ይህ የተከበረው ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ የቀረበለትን <u>የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅና የየጉባኤን አፈጻጸም መመሪያ መርምሮ እንዲያጸድቅ፣ የቤተ ክርስቲያኒቷን መሪዎች እንዲመርጥና ጠቅላ ክርስቲያኒቱ በመሳ አርዕት ወርዶ ሠላም የሚሠፍንበትን መሪዎች እንዲሰጥ መጠራቱ</u> ነው። ብዙዎቻችሁ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ለመሆኑ ይቻላል ወይ? የሚል ጥያቄ እናነሳ ይሆናል። ለሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻላልና ይህች ቤተ ክርስቲያን ረዥም ጉዳና ተጉዛ እዚህ ደርሳለች። ክብርና ምስጋና ለስፉ ክርስቲያኒቱ መሥራ ለእያንዳንዱ ይሁን!

2. በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ነፍሳትን ለጌታ በመማረክና ሰዎችን የጌታ ደቀመዛሙርት በማድረግ፣ እንዲሁም የጌጋ ስሞታዎችን በመለማመድ የምትታወቀውና ለብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ምሳሌ ሆና በቁጥሮች በማደግ ላይ ባለች በዚህች ቤተ ክርስቲያን በውስጣዊ የተነሳ መለያየት ያሳሰባቸው ግለሰቦች፣ ዑደኖች፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ የመንግሥት አካላት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሠላምን ለማምጣትና እንድነቷን ለመመለስ ብዙ ዋጋ መክፈላቸው ይታወቃል። ይህ ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ ይህች ቤተ ክርስቲያን ባለፈችበት ጉዳና ባለውለታ ሰሆኑት ሁሉ ምስጋናውን እንዲያስመነግብ በትህትና አሳስባለሁ።

3. ከቀፈጠረው አስመግባት የተነሳ መሪዎች ከመሪዎች ጋር፣ መሪዎች ከምዕመናን ጋር፣ ምዕመናን ከምዕመናን ጋር የቃየው መከፋፋት፣ ከሁሉም በላይ እግዚአብሔርን ስላሳዘንነው የሰማይ አምላክ ይቅር ይበለን። በብዙ ምሕረትም ይደግፈን።

4. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፍትህ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የወደፊት ፅሣ ፈንታ የሚወስን ጉባዔ እንዲካሄድ ሰነዳር 21-22 ቀን 2000 ዓ.ም. በሚኒስቴሩ መ/ቤት እንዲካሄድ ውስኖ ውሳኔውን ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት በማሳወቅ የጎበረቱ ዋና ጸሐፊ ቋስ ኅለሙ ጌጣ የተጠራውን ጉባኤ በስብሰቢነት አገዲመሩ ጠየቋቸው። ዋና ጸሐፊው ከሚኒስቴሩ ጥሪ እንደደረሳቸው የጎበረቱን ሥራ አስኪያጅ ዘርጋ አስቸኳይ ስብሰባ ጠርተው አሚከሩአቸው። ከርሱም ጉባዔ በመንግሥት ውሳኔ ከሚያገኝ ጎበረቱ ጣልቃ እንዲገባ የሁለቱ ወገኖች ፈቃደኝነት እንዲጠየቅና ሰሚኒስቴሩ ጥያቄ እንዲቀርብ ወሰኑ። በሰሱቱ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተገበይተው የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ጣልቃ ገብተ የአርት ሂደት እንዲያካሄድ ተወይዶተው በታሪም በጽሑፍም ሚረጋገጥ ሰጡ። (ነሓሚ 16 ቀን 2000 ዓ.ም.)

5. ዋና ጸሐፊውም ሚኒስትሩ ጋ ቀርበው ጉዳዩን በቤተ ክርስቲያን አመራር ሰማዖት የጎብረቱ ቦርድ መወሰኑንና ሁሉቱም ወገኖች መተማመን በያዘና በጽሑፍ እንደሰጠ አመሰከቱ። ሚኒስትሩም በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የማስማማያ ቢጋር (TOR) ተዘጋጅተ እንዲቀርብላቸው ወሰኑ። ቢጋሩም በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተዘጋጅተ ለአስተያየት ወደ ኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንና አዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ተልከ የሁለቱም ስምምነት ስተረጋገጠ በኋላ ነሓሚ 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ለሚኒስቴሩ መ/ቤት ቀረበ። ሚኒስትሩም የቀረበውን ቢጋር ከመረመሩ በኋላ ተቀብለው ሰነዳር 21-22 ቀን 2000 ዓ.ም. ተጠርቸቅ የነበረ ጉባዔ ተሠርቦ የአርቁን ሂደት የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት በሙሉ ኃላፊነት መቀበሱን ነሓሚ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ አረጋገጡ።

6. በቢጋሩ መሠረት ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን 7 ሰዎች፣ ከአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን 5 ሰዎች አጎብረቱ ሥራ አስኪያጅ ዘርጋ 3 ሰዎችና አንድ ታሰ ጉባዔ ተቀባይ ሆነው በጸምና በጸሎት፣ በእግዚአብሔር ቃል ምሪት ከሰኔር 22 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ የካቲት 12 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽረስ 13 መደበኛ ስብሰባዎችንና 2 መሰስተኛ ጉባዔ ሰማካሄድ በተዘጋጀ ቢጋር መሠረት ሥራውን ሲሠራ ቆይቷል።

7. አስማሚና ደንብ አርቃቂ ኮሚቴ በተዘጋጀው ቢጋር መሠረት ተገናኝቶ በመመካከር የሥራ ሂደት ሥልቶችን ቀየሰ። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ሰሚዘጋጅ መተዳደሪያ ደንብ መርሆዎችን በመቅረጽ ላይ ኮሚቴ ከስምንት ላይ ደረሰ። ከሁሉቱም ወገኖች የተወከሉ የኮሚቴ አባላት በየሰከላቸው አዘጋጅተው አንዲያቀርቡ ከስምንት ሳይ ተደርሶ አዘጋጅተው አቀረቡ። በጎበረቱ በኩል የተወከሱ የኮሚቴ አባላት ሁሉቱን አስማምተውና አዋህደው ያቀረቡትን ኮሚቴው ተቀብሎ በቢጋሩ መሠረት ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን 15 መሪዎች፣ ከአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን 11 መሪዎችና ኮሚቴው ቡጎንበት መለስተኛ ጉባዔ ቀርቦና ውይይት ተከሂዶበት እጀቱ።

8. በጀደቁ መርሆዎች መሠረት ኮሚቴው ወደ መተዳደሪያ ደንብ ቀረፃ ገባ። ከሁለቱም በኩል የተወከሉት በየበኩላቸው አዘጋጅተው ሪቂቁን ደንብ እንዲያቀርቡ ከስምምነት ላይ ተደረሰ። ሁሉቱም በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሪቂቅ ደንቦቸን አዘጋጅተው አቀረቡ። ከኅበረቱ የተወከሱ አባላት በቀረቡ ሁለት ሪቂቅ ደንቦች ያሉትን ልዩነቶች አጥንተው ለኮሚቴ ሲያቀርቡ ኮሚቴውም የተሩትን ካስመዘገበ በኋላ ልዩነቶችን የማቀራረብ

የማስማማት ሥራ ተሠራ። ከሁሉም በላይ ሙሉ የተረጋት የልደንት ሐሳቦች እንዲተዘጋጡ፣ እንዲ የሌላውን እንዲቀበልና መቻቻል እንዲኖር ተደርጉ ል15፣ ል11 እና 10 መለስተኛ ንዳዓ ቀረበ።

9. የተዘጋጀው መተዳደሪያ ደንብ በሥራ ላይ የሚውልበትን አሠራር የሚያግዝ መመሪያም በአሚቴ ተዘጋጀ። የተለዘለበ መለስተኛ ጉባዔ የተዘጋጀውን ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ ላይ መክሮበት ሁለቱም ዝግጅቶች ለዚህ ልዩ ጠቅላላ ንባዔ እንዲቀርብ በመለነው መሠረት ቀርቦለል።

10. በዚህ በመርሆዎች ዝግጅት፣ በደንብ ቀረጻና በለፈጻጸም መመሪያ ሂደት የፍትህ ሚኒስቴር ተወካይ ከእኛ ጋር በመማማት ከመንግሥት መመሪያ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅያያደረጉ ስለሆነ የዚህ ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ ምስጋና እንዲመዘንብ አጠይቃለሁ።

11. ይህ ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ የፍትህ ሚኒስቴር ለህዳር 21- 22 ቀን 2000 ዓ.ም. በጠራው ንባዔ በሰጠው ኩታ መሠረት የተጠራ ነው። ልዩ ንጣዔ አፈት ዋና ዋና ተግባራት እንዲያከናውን ይጠበቃል። እነዚህም፣

   ሀ. ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ የሚውለውን የኢትዮጵያ ሙስ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንን መተዳደሪያ ደንብ መርምሮ ያጸድቃል።

   ለ. ለመተዳደሪያ ደንብ አፈጻጸም እንዲረዳ የቀረበውን መመሪያ መርምርና አሻሽሮ ያጸድቃል።

   ሐ. በሚያጸድቀው መተዳደሪያ ደንብ የቀደነገገውን አሠራር ተከትሉ ቤተ ክርስቲያኒቱን በብሔራዊ ደረጃ የሚመሩ መሪዎችን ይመርጣል /ይሾማል/።

   መ. ችግሩ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተሠሩ የቤተ ክርስቲያኒቱን አንድነት የማያስጠብቁ አሠራሮች የሚስተካከሉበት፣ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያንና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መከከል ያሉ ልዩነቶች የሚቀሩበትና የተለያዩ ወገኖችን መንፈሳዊ ደዘት ባለው አርቅ ወደ አንድነት የሚመጡበትን መመሪያ ለሚመረጠው አካል ይሰጣል።

12. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፍትህ ሚኒስቴር በዚህች ቤተ ክርስቲያን ለመሰድ ያቀደውን እርምጃ ከመውሰድ ተቆጥቦ ንዳዋን ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በመስጠት ለቤተ ክርስቲያኒቱ አንድነትና እርቅ ስላሳየው ትብብርና በጉ ምላሽ የዚህ ልዩ ጠቅላላ ንብዔ ምስጋና እንዲመዘንብ አለምናለሁ።

13. ለአያሌ ዓመታት ቤተ ክርስቲያኒቱን ሲፈታተኗት የቆየው የመለያየት ችግር እንዲሁም የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቀርበኛ ውሳኔ በመወሰናቸውና ለአዳ ከአስማሚና ደንብ አርቃቂ ኮሚቴ ጉን በመዶማቸው አዚህ ደርሰናል። ስላሳዩት ቀና ትብብርና ለአንድነት ሲሉ ስለከፈሉት መሥዋዕትነት በዚህ ጠቅላላ ጉባዔ ፊት እንዲመሰግናቸው ይፈቀድልኛ። የልዩ ጠቅላላ ንብዔውም ምሥጋና ይመዘንበልኛ።

14. በአዲስ አበባ ስተማ፣ በየክለልና ከኢትዮጵያም ውጭ ያሉት የሙሉ ወንጌል አማኞች፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ምክሮናንና አቢሊናት በአሉትና በፈጣበ ስላደረጉልን ትብብርና ስለሳዩት በጉ አነሳሳሉት የዚህ ልዩ ጠቅላላ ንብዔ ምስጋና እንዲመዘንብላቸው አመለክታለሁ።

15. አስማሚና ደንብ አርቃቂ ኮሚቴ ይህንን ብርቱ ሥራ በሞንቃቅና በመሳጠበት ሠርተውል። ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የተወከሉ ሰባት ወንድሞች፣ ከአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የተወከሉ አምስት ወንድሞችና ከኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የርጅ የተወከሉት አራት ወንድሞች ጊዜያቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ችሎታቸውን ሠውተው ይህንን ብርቱ ንዳዔ አዚህ ለማድረስ በመቻላቸው በክሚቴው ስም ጥሞንጠቅም ባረያሁት ነን፣ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል። (ሉቃ. 17፡10) ስለ ለክሚቴው አገልግሎት ናልዩ ጠቅላላ ንባዔ ምስጋና እንዲመዘንላ አሳስባለሁ።

ይህንን ልዩ ጠቅላላ ንባዔ ጌታ ዘመንፈሱ ይምራ!!

ዓለሙ ሼጣ (ዲስ)
የአስማሚና ደንብ አርቃቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ

ጋሽ በቀለ ከወሬ ፍጆታ በላይ ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ ሰብዓዊና መንፈሳዊ ብልጥግናዎች አንዳሉት አውቃለሁ። ታሪኩን በብልጥግናዎቹ ጀቡኖ አቅርቦልኝ ቢሆን ኖሮ በነፍሱ መቋጠሬ ቀርቶ ወደ ላይ አያንጋጠጥኩ ከአርሱ መማሩ በአሰለቸኝ ነበር። ዝቅ ብሎ እንደ ምድጃ ዳር ትረካ ሲያዋየኝ ግን ከወመድና ከትቢያ የሚያነሳውን፥ ሰባራ ጠጋኙን፥ ፍርስራሽ (መቃብርም) ቆፋሪውን፥ የመደዴዎች ወዳጅ የሆነውን የጌታ አምላኬን የምሕረቱን ባለጠግነት አሳየኝ። ይኼ ነው ባዶነት፤ ከቶስ ድኻ ልሸሽግ ቢልስ ምኑን ይሸሽገዋል!!? (በመንፈስ ድኻ የሆኑ... ብዬ ልቀጥል ነበር፤ የሰባኪዎቹን ሥራ መሻማት ይሆንብኛል።)

ጋሽ በቀለ እንደ ባለ አእምሮም - እንደ እግዚአብሔርም ሰው፥ እንዲህ ሆኖ ወደ አንባቢ መቅረቡ ወደ ፊት ሕይወታቸውን በጽሑፍ መልክ ለሚያካፍሉን አንጋፋ አገልጋዮቻችንና የሕይወት ታሪክ ጸሐፊዎቻችን ፈር የቀደደ ይመስለኛል። ግልጽነት፥ ቁጥሮችነት፥ ሽንገላ-አልቦነት፥ ጎሊናዊ ሰሱነት፥ አርአያነት - ሰውነት፤ ... የተርከፈከፈበት አተራረክ ሰው ያበጃጃል - እስከ ማዶው ትውልድ ድረስ። እኔን መቼም አንጠኖል።

ረዥም ዕድሜ ሊጋሽ በቀለ
ወንድዬ አሊ

ይህን መጽሐፍ ለማየት ብዙ ቁየን። ጭብጥ ሐሳቡ አንድ ሰው ከአከራሪ አማኝነት ወደ ከሀዲነት፥ ከከሀዲነትም በ"ምኑን ዐውቄነት" (agnosticism) ዐልፎ ወደ አማኝነት የተመለሰበት ታሪክ ትውስታ ነው ፤ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ደግሞ የአያንዳንዱ አርከን መሸጋገሪያ ሆኗል። የአንድ ግለ ሰብ ታሪክ ብቻ ግን አይደለም፤ የቤተ ክርስቲያንና የአገር ታሪክንም ዐቅፏል። የዘመን መስታዎት ነው። ጋሽ በቁ፥ "የሕይወት ታሪክህን ለምን አትጽፍም?" ስለው፥ "የሕይወት ታሪክ እንዴት በልጅነት ይጻፋል?" ይለኝ ነበር፤ ታዲያ አሁን ማርጀቱን አመነ ማለት ነው? የሆነስ ሆኖ እግዚአብሔር "ጣልቃ እየገባ" የሚታይበትን ታሪክ መርጦ ማቅረቡን የሚነግረን፥ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት የሌለበት ምን ታሪክ አለውና ነው? ምን አባቴ ዐውቃለሁ፤ መጽሐፉን ጠይቁታ! ጸሓፊው ድካሙንና ውድቀቱን ሳይቀር አውስቷል፤ ቁም-ጭንም። በተለይ ካልተመለሱ ጥያቄዎች ጋር መኖሩን ማንበቤና "መልስ በኪሱ" አለመሆኑን ማወቄ አስደስቶኛል። ለካ ጋሽ በቁ እኛ ሰፈር ነው! እንኳንም መጽሐፉን ለማግኘት ብዙ ቁየን!

ጳውሎስ ፈቃዱ



ዋጋ $20.00